# ዜና ባስልዮስ ሊቀ ጳጳሳት ፡

## ኢ ት ዮ ጵ ያ ዊ ።

ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ በነገሡ ፡ በ፳፯ኛው ፡ ዓመት ፡
ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ በሆኑ ፡
በ፰ኛው ፡ ዓመት ።

ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ በትንሣኤ ፡ ዘጉባኤ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ


አዲስ ፡ አበባ ፡ ሰኔ ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶ ፡ ዓ. ም.

www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ ፡ አቡነ፡ ባስልዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘኢትዮጵያ።

www.ethiopianorthodox.org



## መቅድም ።

የቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ታሪክ ፡ በጥንቃቄ ፡ አዘጋጅተው ፡ ወደ ፡ ትው
ልድ ፡ ያስተላለፉ ፡ መንፈሳውያን ፡ ሊቃውንት ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ።

ከቤተ ፡ ክርስቲያን፡ታሪክም ፡ አንደኛው ክፍል ፤ የመንፈሳዊ ፡ ሥራ ፡ አብነቶችና ፡
ምሳሌዎች ፡ የሆኑ ፡ ደጋግ ፡ ቅዱሳን ፡ ለራሳቸው ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ጽድቅን ፡ ያገኙበ
ትና ፡ ለሰው ፡ ዘር ፡ በጎ ፡ አርአያ ፡ ያደረጉት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥን ፡ ትሩፋት ፡ ነው ።

ሊቃውንቱ ፤ ይህንኑ ፡ መነሻ ፡ በማድረግ ፡ ሲጽፉ ፤ እንደዚህ ፡ ብለዋል ።
«ወሀሎ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ ብእሲ ፡ ጻድቅ ፡ ዘስሙ ፡ እገሌ ። ወሀሎ ፡ ውስተ ፡ ጾማ
ት ፡ ብእሲ ፡ ጻድቅ ፡ ዘስሙ ፡ እገሌ ። ወሀሎ ፡ ውስተ ፡ ደብር ፡ ብእሲ ፡ ጻድቅ ፡
ዘስሙ ፡ እገሌ» ።

ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ታሪካዊ ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ እያደረጉ ፤ የዓለምን ፡
ጣዕም ፡ ንቀው ፡ የምንኵስናንም ፡ ቀምበር ፡ ተሸክመው ፤ ጸዋሚ ፡ ተሐራሚ ፡ በመ
ሆንና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የገድልና ፡ የትሩፋትን ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፡ እግዚአብሔርን ፡
የገለገሉትን ፡ የደጋጎቹን ፡ አበው ፡ ዜና ፡ ጽፈው ፡ አቆይተዋል ።
ታሪኩ ፡ የሚገኝባቸው ፡ መጻሕፍት ፡ መጽሐፈ ፡ መነኰሳት ፤ ዜና ፡ አበው ፤
ንክሳርና ፡ የየራሳቸው ፡ መጽሐፈ ፡ ገድል ፡ ናቸው።

የመንፈሳውያን ፡ ሀብታቸው ፡ ተባሕትዎ ፡ ብቻ ፤ ባለመሆኑ ፤ እንደነቢዩ ፡ ኤል
ስ ፤ እንደ ፡ ዮሐንስ ፡ መጥምቅ ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በከተማ ፡ እየተዘዋ
ሩ ፡ ወንጌልን ፡ የመስበክና ፡ ለሕዝብ ፡ በጎ ፡ አርአያ ፡ ሆኖ ፡ የመታየት ፡ እድል ፡
ተሰጥቷቸው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ የደገፉ ፡ ብዙ ፡ አዕማድ ፡ አሉ ። እነዚሁም ፡
መምህራን ፡ ናቸው ።

ከእነዚህም ፡ አንዳንዶቹ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቀባዒነት ፡ በሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡
ምራጭነት ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ ጳጳሳት ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ሆነው ፡ እስከ ፡ መሸም ፡
ርሰው ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጠፈር ፡ ላይ ፡ እንደንጋት ፡ ኮከብ ፡ አብርተዋል ።

ሊቃውንቱ ፤ ከእነዚሁ ፡ መካከል ፡ የታላላቆቹን ፡ አባቶች ፡ የእነቅዱስ ፡ ዮሐ
ስ ፡ አፈ ፡ ወርቅን ፤ የእነቅዱስ ፡ ቄርሎስን ፤ የእነቅዱስ ፡ ባስልዮስን ፤ የእነቅዱስ ፡
ትናቴዎስን ፤ የእነቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስን ፡ የእነቅዱስ ፡ ኤጲፋንዮስን ፡ የእነቅዱስ ፡
ዮስቆሮስንና ፡ እነሱን ፡ የመሳሰሉትን ፡ የብፁዓን፡ሊቃነ ፡ ጳጳሳትና ፡ የጳጳሳትን ፡ ታሪክ፡
ፈው ፡ ለቅድስት ፡ ቤተ፡ክርስቲያን ፡ አደራ ፡ ሰጥተዋታል ።

ይህንኑ ፡ ታሪክ ፡ የሚያስገኙ ፡ መጻሕፍት ፤ ሃይማኖተ ፡ አበው ፤ ዮሐንስ ፡ መደ
ር ፤ አቡሻክር ፤ ጊዮርጊስ ፡ ወልደ ፡ አሚድ ፤ ሐዊ ፤ ስንክሳርና ፡ የየራሳቸው ፡
መጽሐፈ ፡ ገድል ፡ (ታሪክ) ፡ ናቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

የእግዚአብሔር ፡ ጸጋው ፡ ያደረባቸውና ፡ መንፈሳዊው ፡ ብርሃን ፡ ልቡናቸውን ያበራላቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቅዱሳንም ፤ የነቢያትንና ፡ የሐዋርያትን ፤ የቅዱሳን ፡ ጻ ቃንና ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሊቃውንትን ፡ አብነትነት ፡ ተከትለው ፡ የላመ ፤ የጣመ እንቅመስ ፤ የሞቀ ፡ የደመቀ ፡ እንልበስ ፡ ሳይሉ ፤ ዕድሜያቸውን ፡ በተባሕትዎና በጽኑ ፡ ገድል ፡ አሳልፈዋል ።

የገድልና ፡ የትሩፋታቸው ፡ ዜናም ፡ ከምሉ ፡ በክፍሉ ፡ ተጽፎ ፡ ለቤተ ፡ ክር ቲያናችን ፡ አደራ ፡ በመሰጠቱ ፤ እስከሁን ፡ የክብር ፡ ሥፍራውን ፡ ሳይለቅ ፡ ከትው ልድ ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡ እየተላለፈ ፤ ሲነገር ፡ ይኖራል ።

ደግነታቸውም ፡ በጣም ፡ ከታወቀውና ፡ የታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ በቅድስና ፡ አ ራር ፡ ከሚጠራቸው ፡ ከኢትዮጵያውያን ፡ ቅዱሳን ፡ የያንዳንዶቹን ፡ ስም ፡ በዚህ እናስታውሳለን ።

| <u>ስማቸው ።</u> | ሀገራቸውና ፡ ገዳማቸው ፡ |
|---|---|
| ቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ | አክሱም ፡ ዐፅማቸውና ፡ ገ ማቸው ፡ በስሜን ፡ |
| አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ | ሸዋ ። ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ |
| አቡነ ፡ ዜና ማርቆስ ፡ | ሸዋ ። ደብረ ፡ ብሥራት ፡ |
| አባ ፡ ዮሐኒ ፡ | ተምቤን ፡ (ትግሬ) ። |
| አባ ፡ ጊዮርጊስ ፡ | ጋሥጫ ። |
| እጨጌ ፡ ፊልጶስ ፤ | (ዝማ) ፡ ዐፅማቸው ፡ ጌርጌስ ፡ ውስጥ ፡ ሐቃሊት ። አሁን ፡ ደብረ ሊባኖ |
| አቡነ ፡ ዮሴፍ ፡ | እንጃፋት ፤ (ላስታ) ። |
| አባ ፡ ሳሙኤል ፡ | ደብረ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ። |
| እጨጌ ፡ መርሐ ፡ ክርስቶስ ፡ | ዐፅማቸው ፡ በደብረ ፡ ሊባኖስ |
| አቡነ ፡ አሮን ፡ | ቆላ ፡ መቄት ። |
| አቡነ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ | ሚዳ ። |
| አቡነ ፡ መድኃኒነ ፡ እግዚእ ፡ | ደብረ ፡ በንኰል ። |
| አባ ፡ በትረ ፡ ማርያም ፡ | ሸዋ ፡ ገዳማቸው ፡ ዘጌ ። |
| አባ ፡ ዮሐንስ ፡ | ሸዋ ፡ ገዳማቸው ፡ ክብራን ፡ ገብርኤል ፡ ዘጌ |
| አቡነ ፡ መባአ ፡ ጽዮን ፡ ሀብተ ፡ ጽዮን ፡ | (ሸዋ) ፡ ዐፅማቸውና ፡ ገዳማቸው ፡ ያለበት ፡ ተጉለት ፡ ማጢ ፡ ቆላ ። |

ኤጲስ ፤ ቆጶሱ ፡ ዕጨጌ ፡ ፊልጶስ ፡ የሾሟቸው ፡ አሥራ ፡ አንዱ ፡

<u>ንቡራነ ፡ እድ ።</u>

| | |
|---|---|
| ፊልጶስ ፡ | ኤጲስ ፡ ቆጶስ ። |
| አኖሬዎስ ፡ | ወረብ ። |
| አድኅኔ ፡ | ዳሞት ፤ (ወላሞ) ። |
| ኢዮስያስ ፡ | ወንጂ ፡ (አሩሲ) ፡ |
| ማትያስ ፡ | ፈጠጋር ። |
| ዮሴፍ ፡ | እናርያ ፡ (ሊሙ) ። |
| ታዴዎስ ፡ | ጽላልሽ ፡ (ቡልጋ) ። |
| ገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ | ቦረና ፡ ደብይ ። |
| ቀውስጦስ ፡ | መሐግል ፡ (ጥጥ ፡ አምባ) ፡ |
| ሳሙኤል ፡ | ወገግ ፡ (አሰቦት) ። |
| መርቆሬዎስ ፡ | መርሐ ፡ ቤቴ ። |
| አኖሬዎስ ፤ | ወግዳና ፡ ሞረት ። |



እነዚህ ፡ በሦስተኛው ፡ ዕጨጌ ፡ በአቡነ ፡ ፊልጶስ ፡ ቡራኬ ፡ ተሹመው ፡ ስብ ከተ ፡ ወንጌልን ፡ ያስፋፉ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ቅዱሳን ፡ ናቸው ።

<u>የኢትዮጵያውያን ፡ ቅዱሳን ፡ ስም ፡ ይቀጥላል ።</u>

| | |
|---|---|
| ዕጨጌ ፡ ዮሐንስ ፡ ከማ ፡ | ገዳማቸው ፡ ትግሬ ፡ ጠ ፡ ግ ፡ |
| አባ ፡ ቶማስ ፡ | ትግሬ ፡ ገዳማቸው ፡ ሽሬ ፤ |
| አባ ፡ መዝሙረ ፡ ድንግል ፡ | ትርጓሜ ፡ ወንጌልን ፡ ወደ ግዕዝ የመለሱ ፡ እነብሴ ፡ ገዳማቸው ፡ ዲማ ። |
| አቡነ ፡ ሐራ ፡ ድንግል ፡ | እንደርታ ፡ (ትግሬ) ፡ ገዳ ፡ ደራ ። |
| አቡነ ፡ ዐቢየ ፡ እግዚእ ፡ | ትግሬ ፡ ገዳ ፡ ተምቤንና ፡ ዛና ። |
| አባ ፡ ሠርፀ ፡ ጴጥሮስ ፡ | ገዳማቸው ፡ ደብረ ፡ ወርቅ ። |
| አባ ፡ ተከሥተ ፡ ብርሃን ፡ | ሸዋ ፡ ገዳማቸው ፡ ዲማ ፡ |
| አቡነ ፡ ተክለ ፡ አልፋ ፡ | ሸዋ ፡ ገዳማቸው ፡ ዲማ ። |
| አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሐዋርያት ፡ | ሸዋ ፡ ደብረ ፡ ጽሙና ። |
| አቡነ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡ | ሸዋ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ። |
| አቡነ ፡ አላኒቆስ ፡ | ያዬ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ልጅ ፡ ሸዋ ፡ (መንዝ) ፡ ገዳማቸው ፡ ማይ ፡ በራዝዮ ፡ (ትግሬ) ። |
| አቡነ ፡ እስትንፋሰ ፡ ክርስቶስ ፡ | ዳውንት ። |
| አባ ፡ መልክአ ፡ ክርስቶስ ፡ | ግሼቅ ፡ (ወረሂመኑ) |
| አቡነ ፡ ኢየሱስ ፡ ሞዐ ፡ | ሐይቅ ፡ (የወሎ ፡ ደብረ ፡ ነጐድጓድ) ፤ |
| አባ ፡ ሳሙኤል ፡ | ዘዋልድባ ፡ (ትግሬ) ። |
| አባ ፡ ፊልጶስ ፡ | ዘደብረ ፡ ቢዘን ፡ (ሐማሴን) ። |

ስማቸው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተነገረውና ፡ ስማቸው ፡ ለጊዜው ፡ ሳይነገር ፡ የታ ለፈው ፡ ሌሎቹ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ቅዱሳን ፡ ሁሉ ፤ ለኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ታማኝ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ምስክርነት ፡ ያለው ፡ የሃይማኖታቸውንና ፡ የትሩፋታቸውን ፡ ዜና ፡ ስለተዉልን ፡ ልንመከባቸው ፡ ችለናል ።

ሐዋርያው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ስለቅዱሳን፡ሲናገር ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ። «ማቅና ዐጽፍን ፡ የፍየልንም ፡ ሌጦ ፡ ለብሰው ፡ የዞሩ ፡ አሉ ፤ ተቸገሩ ፡ ተጨነቁ ፡ ይህ ዓለም ፡ የማይገባቸው ፡ እኒህ፡ መከራ ፡ ተቀበሉ ። ዱር ፡ ለዱር ፡ ተራራ ፡ ለተራራ ዋሻ ፡ ለዋሻ ፡ ፈረፈር ፡ ለፈረፈር ፡ ዞሩ ፡ እሊህ ፡ ሁሉ ፡ በሃይማኖት ፡ ሰማዕት ሆኑ ። የነገራቸውን ፡ ተስፋ ፡ ግን ፡ አላገኙም ፡ የሚበልጠውን ፡ክብር ፡ ያለኛ ጨርሰው ፡ እንዳይወርሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለኛ ፡ በይኖዋልና፡» ዕብ ፡ ም ፡ ፲፩ ቊ ፴፯—፴ ።

ሐዋርያው ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ የዘረዘረውን ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የተባሕትዎ ፡ ገድል ብዙዎቹ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቅዱሳን ፡ በበለጠ ፡ ሠርተውታል ።

የእነሱ ፡ የምናኔ ፡ አርኣያ ፡ እስካሁኑ ፡ ትውልድ ፡ ድረስ ፡ ስለተላለፈ ፤ ዛሬም ይህን ፡ ዓለም ፡ እየናቁ ፡ የላመ ፡ የጣመ ፡ አንቀምስም ፤ የሞቀ ፡ የደመቀ ፡ አንለብስም ፡ እያሉ ፡ ማቅ ፡ ዐጽፍና ፡ የፍየል ፡ ሌጦ ፡ ለብሰው ፡ ዱር ፡ ለዱር ፡ ተራራ ለተራራ ፡ ዋሻ ፡ ለዋሻ ፡ ፈረፈር ፡ ለፈረፈር ፡ በመዞር ፡ እንደአባቶቻቸው፡ የምናኔና የተባሕትዎ ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ ብዙ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ይገኛሉ ።

«ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ስለመናንያን ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ ዳግመኛ ፡ እንዲህ ፡ ብሏል፡ እንደደመና ፡ የሚከቡን ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምስክሮች ፡ ያሉን ፡ እኛም ፡ ስለዚህ የከበደውን ፡ ሁሉ ፡ ሸክም ፡ የኃጢአትንም ፡ ትብትብ ከላያችን ፡ እንጣል ፡ በመታገሥም ፡ በሃይማኖት ፡ ወደተጠበቀልን ፡ ተስፋ ፡ እንገሥግሥ ፡ ዕብ ፡ ም ፲፪ ቊ ፩

ስለዚህ ፤ በአካለ ፡ ሥጋ ፡ ሁነው ፡ የገድል ፡ የተባሕትዎ ፡ ሥራ ፡ እየሠሩ በአካለ ፡ ነፍስም ፡ ሁነው ፡ እንደ ፡ መላእክት ፡ «ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ በማለት በምስጋና ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያገለግሉት ፡ ቅዱሳን የመንፈስ ፡ መሪዎቻችን ፡ በመሆናቸው ፤ እነሱን ፡ አብነት ፡ ማድረጋችን ፡ የከበደውን ፡ የኃጢአት ፡ ሸክም ከላያችን ፡ ለመጣልና ፡ በሃይማኖት ፡ ወደተጠበቀልን ፡ ተስፋ ፡ ለመገሥገሥ ይረዳናል ።

ሆኖም ፤ ዛሬ ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ሳሉ ፡ በጸሎት ፡ የረዱንን ፤ ወደፊትም በጸሎት ፡ የሚረዱንን ፡ ያንድ ፡ ብፁዕ ፡ አባት ፡ ታሪክ ፡ በጥቂቱ ፡ እናስታውሳለን ፤

ትዕግሥት ፡ ፈተናን ፡ እንዲያመጣ ፡ ፈተናንም ፡ ድል ፡ ማድረግ ፡ የተቻለው ትዕግሥት ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ተስፋን ፡ እንዲያስከትል ፤ ዘለዓለማዊው ፡ ተስፋም የሚያሳፍር ፡ እንዳልሆነ ፡ በማስተዋል ፤ ብፁዕነታቸው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ተአምራት ብዙ ፡ ፈተናን ፡ አልፎ ፡ የተገኙ ፡ ስለሆነ ፤ የዚህ ፡ ታሪክ ፡ ባለቤት ፡ አዲሱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተወላጅ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፤ ናቸው ።

የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ በታላቁ ፡ ገዳም በደብረ ፡ ሊባኖስና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ገዳማት ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ብዙ ፡ የገድል ፡ ሥራ ሠርተዋል ።



ቀኖና ፡ እየያዙ ፤ ሱባዔም ፡ እየገቡ ፡ ገና ፡ በሕጻንነታቸው ፡ ወራት ፡ ሰውነታቸውን ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ በስግደት ፡ ቀጥተውታል ።

የእግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ፈቃዱ ፡ ከተባሕትዎ ፡ ሥፍራ ፡ አምጥቶ ፡ ወደ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ መንበር ፡ ያደረሳቸው ፡ ቢሆንም ፤ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ዱር ለዱር ፤ ተራራ ፡ ለተራራ ፡ ዋሻ ፡ ለዋሻ ፡ ፈረፈር ፡ ለፈረፈር ፡ ዞሩ ፡ ብሎ ፡ ብሕትውናቸውን ፡ ከተናገረላቸው ፡ መናንያንና ፡ ባሕታውያን ፡ አንዳንዱ ፡ መሆናቸውን ፡ ራሱ ፡ ሥራቸው ፡ ይመሰክራል ።

ይህንኑም ፡ በአጭሩ ፡ ለማስረዳት ፡ ይህ ፡ የታሪካቸው ፡ መጽሐፍ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ። ገና ፡ በ፲፩ዓመታቸው ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገዳም ፡ ፲፰፻፺፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ገብተው ፡ ገድልና ፡ ትሩፋትን ፡ እየሠሩ ፤ መንፈሳዊ ፡ ትምህርትንም ፡ ከታላቁ ፡ ሊቀ ፡ ከመምህር ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስ ፡ እየተማሩ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ከኖሩ ፡ በኋላ ፡ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ መንፈሳዊ ፡ አርኣያ ፡ በመከተል ፡ ወደ ፡ ገዳሙ ፡ ቤተ ፡ ማኅበር ፡ ገብተው ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ በእርድና ፡ አገልግለዋል ።

ከዚህ ፡ በኋላም ፤ መዓርገ ፡ ምንኵስናን ፡ ተቀብለው ፡ በሥልጣነ ፡ ሐዋርያት ፡ የቤተ ፡ መቅደስን ፡ አገልግሎት ፡ ጀምረዋል ። በቤተ ፡ መቅደስ ፡ አገልግሎትና ፡ በትምህርት ፡ ተወስነው ፡ ሳሉ ፤ በ፲፱፻፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከሰው ፡ ተለይተው ፡ በዐባይ ፡ ዳር ፡ ወደሚገኘው ፡ በኀሐ ፡ ጽዮን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በታች ፡ ወደ ፡ አለው ፡ ወደ ፡ ዋሻ ፡ ሚካኤል ፡ ገዳም ፡ ገብተው ፡ በንዲት ፡ ዋሻ ፡ ውስጥ ፡ የገድል ፡ ሥራ ፡ ይዘው ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ተቀመጡ ።

ኋላ ፡ መንፈሳዊትም ፡ ስለመራቻቸው ፤ ከዋሻ ፡ ሚካኤል ፡ ገዳም ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ መናገሻ ፡ (ወደ ፡ አምባ) ፡ ማርያም ፡ ገዳም ፡ ገብተው ፡ ከባሕታውያን ፡ ጋራ ፡ የገድል ፡ ሥራቸውን ፡ በመቀጠል ፡ ተወሰኑ ።

በተባሕትዎ ፡ ራሳቸውን ፡ ብቻ ፡ ከማዳን ፡ ይልቅ ፡ በሐዋርያነታቸው ፡ (በስብከታቸው) ፡ ብዙ ፡ ምእመናንን ፡ ማዳናቸውና ፡ መጥቀማቸው ፤ ለብዙዎችም ፡ መንፈሳዊ ፡ አርኣያ ፡ ሆነው ፡ መታየታቸው ፡ እጅግ ፡ የበለጠ ፡ አገልግሎት ፡ በመሆኑ ፤ ኑሮዋቸው ፡ በገዳም ፡ ሥራቸው ፡ ጸሎትና ፡ ጾም ፡ የሆነ ፡ ኤልያስንና ፡ ዮሐንስ ፡ መጥምቅን ፡ አዕላፈ ፡ እስራኤል ፡ ወደተሰበሰቡበት ፡ ሥፍራ ፡ የጠራ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ምእመናን ፡ ወደ ፡ ተሰበሰቡበት ፡ ጠራቸውና ፡ መጀመሪያ ፡ የአምባ ፡ ማርያምን ፡ ገዳም ፡ አቀኑ ። ኋላም ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ መንበረ ፡ መንግሥት ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤልን ፡ ደብር ፤ ከዚያ ፡ ቀጥሎ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ያሉ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ገዳማት ፡ በመንፈሳዊ ፡ መሪነት ፡ አስተዳድረዋል ።

ሕሊናቸው ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ከሰው ፡ ተለይቶ ፡ የተባሕትዎ ፡ ገድል ፡ መያዝን ፡ ብቻ ፡ ቢመርጥም ፤ የእግዚአብሔር ፡ ረቂቅ ፡ ጥበቡ ፤ ከፍ ፡ ባለው ፡ በአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መንበር፡ (በዕጨጌነት ፡ ላይ)፡ ለመተካት ፡ ስላበቃቸው ፤ በ፲፱፻፴፯ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ የካቲት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ የዕጨጌነቱን ፡ መዓርግ ፡ ተቀብለው ፡ «ብፁዕ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ዘነበረ ፡ በመንበረ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት» ፤ ተብለው ፡ ተሾሙ ።

እግዚአብሔር ፡ ብርቱ ፡ ፈተና ፡ ከማምጣቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ብርቱ ፡ ነቢይ ፡ ብርቱ ፡ ሐዋርያ ፡ ማስነሣት ፡ ልማዱ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ መጠን ፡ በዕጨጌነታቸው ፡ ዘመን ፡ የፋሺሽት ፡ ወረራ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ባጠቃ ፡ ጊዜ ፤ በጦርነቱ ፡ ግምባር ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ስንኳ ፡ ሳይለዩ ፤ አብያተ ፡ ክርስቲያናትንና ፡ መጻሕፍትን ፡ የሚያቃጥል ፡ የምእመናንን ፡ ዘር ፡ የሚያጠፋ ፡ ጠላት ፡ መጥቷልና ፡ በሃይማኖት ፡ በጸሎት ፡ በምህላ ፡ በርታ ፡ እያሉ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ በሐዋርያነታቸው ፡ አጽናንተዋል ። በአምስቱ ፡ የመከራ ፡ ዘመናትም ፡ የታላቁን ፡ የእስራኤልን ፡ መሪ ፡ የሙሴን ፡ ምሳሌነት ፡ ተከትለዋል ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ስለሙሴ ፡ በጎ ፡ አርአያ ፡ መሆን ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ። «ሙሴ ፡ ካደገ ፡ በኋላ ፡ የፈርዖን የልጅ ፡ ልጅ ፡ ነህ ፡ ቢሉት ፡ በሃይማኖት ፡ አይደለሁም ፡ አለ ። በኃጢአት ፡ ጥቂት ፡ ዘመን ፡ ደስ ፡ ከሚለው ፡ ይልቅ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ወገን ፡ ጋራ ፡ መከራ ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ ወደደ ።

ከግብፅ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ይልቅ ፡ የክርስቶስ ፡ መከራ ፡ እንዲበልጥ ፡ ዐውቋልና» ፡ ዕብ ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ቁ ፡ ፳፬—፳፮ ።

ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ይህን ፡ የሙሴን ፡ አርአያነት ፡ በሙሉ ፡ ሠርተውብታል ። ይኸውም ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከጦርነቱ ፡ ሥፍራ ፡ ተመልሰው ፡ የኢትዮጵያን ፡ በግፍ ፡ መመረር ፡ ለዓለም ፡ ነገሥታት ፡ ለማመልከት ፡ ወደ ፡ ኤሮፕ ፡ በሔዱ ፡ ጊዜ ፤ አብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ ከሚያቃጥልና ፡ ምእመናንን ፡ በግፍ፡በዐመፅ ፡ ከሚገድል ፡ አረማዊ ፡ ጠላት ፡ ጋራ ፡ ተስማምቶ ፡ ከመኖር ፤ በቅድስት ፡ ሀገር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ጸሎት ፡ መያዝና ፡ ወገኖቼን ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ በመንፈሳዊ፡ ምክር ፡ እያጽናናሁ ፡ መቆየት ፡ ይበልጣል ፡ ብለው ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሔደዋል ።

ቅዱሳን ፡ ነቢያት ፡ እነ ፡ ኤርምያስ ፡ እነ ፡ ሕዝቅኤል ፡ እነ ፡ ዳንኤል ፡ እነ ፡ ዕዝራ ፡ እነጦቢት ፡ እነአቤሜሌክ ፡ ስለሀገራቸው ፡ ስለኢየሩሳሌም ፡ መጥፋት ፤ ስለወገኖቻቸው ፡ መማረክና ፡ መሰደድ ፤ ስለቤተ ፡ መቅደሳቸው ፡ መፍረስ ፤ ስለ ፡ ሕጋቸው ፡ መደምሰስ ፡ ያዝኑ ፡ ያለቅሱ ፡ ቀኖና ፡ ይይዙና ፡ ወገኖቻቸውን ፡ በመንፈሳዊ ፡ ምክር ፡ ያጽናኑ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ በቅድስት ፡ ሀገር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተቀምጠው ፡ ስለ ፡ ሀገራቸው ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጥፋት ፤ ስለ ፡ ወገኖቻቸው ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በግፍ ፡ መገደልና ፡ መሰደድ ፡ ስለ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትና ፡ ስለ ፡ መጻሕፍት ፡ መቃጠል ፡ እያዘኑ ፡ እያለቀሱ ፡ ቀኖና ፡ ይዘው ፡ ቆይተዋል ።

በኢየሩሳሌም ፡ አብረዋቸው ፡ የነበሩትን ፡ የኢትዮጵያን ፡ መሳፍንትና ፡ መኳንንት ፡ በመንፈሳዊ ፡ ተስፋ ፡ ከማጽናናታቸው ፡ በላይ ፡ አርበኞችንና ፡ ስደተኞችን ፡ የሚያበረታታ ፡ መንፈሳዊ ፡ ጦማር ፡ በየጊዜው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ልከዋል ።



ባሮክና ፡ አቤሜሌክ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ሳሉ ፡ በባቢሎን ፡ ለነበሩ ፡ እስራኤል ፡ «ሚጠት ፡ ደርሷል» ፡ ብለው ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ እንደላኩላቸውና ፡ እንደ ፡ አጽናኑዋቸው ፤ እርሳቸውም ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ እየላኩ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጀግኖች ፡ በሃይማኖታዊ ፡ ተስፋ ፡ አበረታተዋል ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጦርነቱን ፡ እንደገና ፡ ለመቀጠል ፡ ፲፱፻፳፰ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ጥር ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጠረፍ ፡ በኦሜድላ ፡ ላይ ፡ በተከሉ ፡ ጊዜ ፤ አምላከ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የአባቶችዎን ፡ ሀብተ ፡ መዊዕ ፡ ያሳድርብዎ ፡ ብለው ፡ ጸሎተ ፡ ቡራኬ ፡ አድርሰዋል ።

ከዚያ ፡ ጀምረው ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሳይለዩ ፤ በኀዘን ፡ በጸሎት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እያመለከቱ ፡ ቆይተው ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡ ወደ ፡ መናገሻ ፡ ከተማቸው ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ይህን ፡ ታላቅ ፡ ትድግና ፡ ላደረገ ፡ አምላክ ፡ ምስጋና ፡ አቅርበዋል ።

ከዚያ ፡ በኋላም ፡ በዕጨጌነት ፡ በጳጳስነት ፡ በሊቀ ፡ ጳጳስነት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሲጠብቁ ፤ በጸሎታቸው ፡ በሐዋርያነታቸው ፡ በአባትነታቸው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕይወት ፡ እጅግ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ ሠርተዋል ። የቤተ ፡ ክርስቲያንንም ፡ ችግር ፡ ለኦርቶዶክሳዊው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ለቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ እያሳሰቡ ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የምትስፋፋበትን ፡ ምእመናን ፡ ወንጌል ፡ የሚበዙበትን ፡ ታላላቅ ፡ ጉዳዮችን ፡ አስፈጽመዋል ።

ከዚሁም ፡ ዋና ፡ ዋናውን ፡ ጉዳይ ፡ አንባቢዎች ፡ በዚህ ፡ በታሪካቸው ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ ሊያገኙት ፡ ይችላሉ ። ብፁዕነታቸው ፡ የርኅራኄ ፡ ዕድል ፡ የተሰጠው ፡ ስለሆነ ፤ ገዳማትና ፡ አድባራትን ፤ የትምህርትና ፡ የሕክምና ፡ ቤቶችን ፡ እየጐበኙ ፡ ችግራቸውን ፡ በማቃለል ፡ ብዙ ፡ የትሩፋት ፡ ሥራ ፡ ሠርተዋል ።

ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴን ፡ ሰፊ ፡ ትጋት ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ የሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ መዓርግ ፡ ሰጥቶ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በታላቅ ፡ አስተያየት ፡ ለመምራት ፡ ስላበቃቸው ፤ በበታቻቸው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሥራ ፡ የሚመሩ ፡ ዐሥራ ፡ ሦስት ፡ ጳጳሳት ፡ በብፁዕነታቸው ፡ ቡራኬ ፡ ተሹመው ፡ የኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ሃይማኖት ፡ ስብከት ፡ በበለጠ ፡ እንዲስፋፋ አድርገዋል ።

ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ለሰው ፡ መራራት ፤ ሰውን ፡ አጥብቆ ፡ መውደድ ፤ ሰውን ፡ አክብሮ ፡ መመልከት ፤ ፍቅርን ፡ በተመላ ፡ ቃል ፡ ማጽናናት ፤ የሚያመለክታቸውን ፡ ጉዳዩን ፡ አክብሮ ፡ መያዝና ፡ መፈጸም ፡ የተለየ ፡ ስጦታቸው ፡ ነው ።

ስለዚህ ፤ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጠፈር ፡ እንደንጋት ፡ ኮከብ ፡ ሆነው ፡ በማብራታቸው ፤ በተባሕትዎ ፡ እንደ ፡ ተከተሏቸው ፡ እንደ ፡ መንፈሳውያን ፡ አባቶቻቸው ፡ እንደ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትና ፡ እንደ ፡ አቡነ ፡ ዜና ፡

www.ethiopianorthodox.org

ማርቆስ ፤ በስብከታቸውና ፡ በሐዋርያነታቸው ፡ እንደ ፡ ተከተሏቸው ፡ እንደ ፡ አባ
ቶቻቸው ፡ እንደነ ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ፡ወርቅና ፡ እንደነ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ፡
ዜና ፡ ገድላቸውና ፡ ዜና ፡ ትሩፋታቸው ፡ ለዘለዓለም ፡ ሲነገር ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ "ዜና ፡
ባስልዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ኢትዮጵያዊ" ፡ ተብሎ ፡ የተሰየመ ፡ ይህ ፡ የታሪካቸው ፡
መጽሐፍ ፡ በአፈ ፡ ሊቀ ፡ ሊቃውንት ፡ አክሊሉ ፡ ገብረ ፡ ኪሮስ ፡ ተጠባባቂነት ፡
ታተመ ።

---

## መ ግ ቢ ያ ።

«ዜና ፡ ባስልዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ኢትዮጵያዊ» ፡ ተብሎ ፡ የተሰየመ ፡ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በዝርዝር ፡ የተገለጠው ፡ የብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ቅድስናዊ ፡ ታሪክ ፡ ይገኝበታል ።

፩ኛ/ ኢትዮጵያ ፡ በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ መሪነት ፡ ከ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ፡ ም፡ ጀምራ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ የግፍ ፡ ወራሪዎችን ፡ በተከላከለች ፡ ጊዜ ፡ በመንፈሳዊ ፡ መሪነታቸው ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነጻነት ፡ ያደረጉት ፡ ሐዋርያዊ ፡ ተጋድሎ ።

፪ኛ/ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የግፍ ፡ ወራሪ ዎችን፡ ድል ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ መናገሻ ፡ ከተማቸው ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከገቡ ፡ ጀምሮ ፤ በዕጨጌነታቸው ፡ በጳጳስነታቸውና ፡ በሊቀ ፡ ጳጳስነታቸው ፡ ስለ ኢትዮጵያና ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ቤተ ክርስቲያን ፡ የፈጸሟቸው ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያሉ፡ መንፈሳውያን ፡ ሥራዎች ፤ እንዲሁም ፡ በየበዓላቱና ፡ በየአጽዋማቱ ፡ ለሕዝብ ያሰሟ ቸው ፡ የስብከተ ፡ ወንጌል ፡ ቃላትና ፡ ጥልቅነት ፡ ያላቸው ፡ የሃይማኖት፡ ምሥጢራት።

፫ኛ/ በኢትዮጵያ አውራጃዎች ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ገዳማትንና ፡ አድባራትን ፡ በጎበኙ ፡ ጊዜ ፡ ያደረጉት ፡የትሩፋት ፡ ሥራ ።

፬ኛ/ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መነኰሳት ፡ ታሪክና ፡ ብፁዕነታቸው ፡ ከ፲፱፻፴፰ ዓ፡ ም፡ ጀምሮ ፡ በደብር ፡ ቅዱስ ፡ (ደብረ ፡ ጽጌ ፡) ማርያም ፡ ገዳም ፡ ያቋቋሙት ፡ መታሰቢያ ።

፭ኛ/ በጳጳስነታቸውና ፡ በሊቀ ፡ ጳጳስነታቸው ፡ ጊዜ ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን ፡ አዲስ ፡ ዕድገት ፡ ከእስክንድርያ ፡ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባለሥልጣኖች፡ ጋር ፡ ያደረጉት ፡ መንፈሳዊ ፡ ግንኙነት ።

፮ኛ ከ፲፰፻፺፱ ዓ፡ ም፡ ጀምሮ ፤ እንደ ፡ መንፈሳዊ ፡ አባታቸው፡ እንደ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በታላቁ ፡ ገዳም ፡ በደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መንፈሳዊ፡ ትምህርትን ፡ እየተማሩ፡ ለቅዱስ ፡ ተልእኮም ፡ እየተፋጠኑ ፡ ከማደጋቸው ፡ በላይ ፡ በዚሁ ፡ በሕፃንነታቸው ፡ ጊዜ ፡ የሠሩት ፡ ገድልና ፡ ትሩፋት ፡ እንዲሁም ፡ በሌሎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ገዳማት ፡ የፈጸሙት ገዳማዊ ፡ አገልግሎት ።

፯ኛ/ የብፁዕነታቸው ፡ ጠቅላላ ፡ ታሪክ ባጭሩ ።

፰ኛ/ሊቃውንትና ፡ መምህራን፡ ስለ ፡ ብፁዕነታቸው፡ ደግነት፡ያበረከቷቸው ፡ ቅኔዎች።

፱ኛ/ የደብረ ፡ ሊባኖስን ፡ ገዳምና ፡ የደብር ፡ ቅዱስ ፡ ደብረ ጽጌ ፡ ማርያምን ፡ ገዳም ፡ በመንፈሳዊ ፡ ፍቅር ፡ አስተሣስሮ ፡ እንዲኖር ፡ ብፁዕነታቸው ፡ የወሰነው ፡ ገዳማዊ ፡ ሥርዓት ።

www.ethiopianorthodox.org

እንዚህ ፡ ከአንድ ፤ እስከ ፡ ስምንተኛ ፡ ቍጥር ፡ የተዘረዘሩ ፡ አርእስተ ፡ ነገራት ፤ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የብፁዕነታቸውን ፡ መንፈሳዊ ፡ መሪነትና ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ ከብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ ሊያስረዱን ፡ እነሆ ቀርበዋል ።

ስለ ፡ ዚህ ፡ ዐመፀኞቹ ፡ የፋሺሽት ፡ ሠራዊት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ምእመናን ፡ ሕይወት ፡ በጋዝና ፡ በመርዝ ፡ ጢስ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለመደምሰስ ፤ አብያተ ፡ ክርስቲያናትንም ፡ በእሳት ፡ ለመተኰስ ፤ ሃይማኖትንም ፡ ለማጥፋት ፡ በወረራ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በመጡ፡ ጊዜ ፡ ብፁዕነታቸው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ኃያላን ፡ ያበረታታበትን ፡ ሐዋርያዊ ፡ ኃይል ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ እያንዳንዱ ፡ እንመልከት ።

---

# አንደኛ ሐዋርያዊ መልእክት ።

ብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ዘመንግሥተ ፡ ኢትዮጵያ ፤ በኅዳር ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ኃያላን ፡ አርበኞች ፡ ያደረጉት ፡ ስብከት ።

ይድረስ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ተወላጆች ፡ ኃያላን ፡ አርበኞች ፡ የአብ ፡ በረከት ፤ የወልድ ፡ ፍቅር ፤ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሀብት ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ ይሁን ፡



ልጆቼ ፡ ሆይ ፤ የቀድሞ ፡ ጠላታችን ፡ ጣሊያን ፡ እንዲህ ፡ እንደዛሬው ፤ የዛሬ ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ በአጥቂነት ፡ አገራችንን ፡ ለመውሰድ ፡ ቢመጣባቸው ፡

www.ethiopianorthodox.org

የታደሉ ፡ አባቶቻችን ፡ ደማቸውን ፡ አፍስሰው ፡ አጥንታቸውን ፡ ከስክሰው ፡ ሕይወታቸውን ፡ በማሳለፍ ፡ አባርረውት ፡ እንደነበረ ፡ ሁላችሁም ፡ ታውቃላችሁ ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ እንደዚያን ፡ ጊዜው ፡ ሳንገፋው ፡ ገፍቶ ፡ ሳንሔድበት ፡ መጥቶ ፡ በብሉይም ፡ በሐዲስም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አምና ፡ ነጻነቷን ፡ እየጠበቀች ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቷ ፡ ሥልጣን ፡ ስትገዛ ፡ የምትኖረውን ፡ አገራችንን ፡ ወስዶ ፡ እኛን ፡ ባሮች ፡ ለማድረግ ፡ ወንድነታችንን ፡ ንቆ ፡ ወሰናችንን ፡ ጠቅጥቆ ፡ በተጋፊነት ፡ መምጣቱ ፡ ሕፃንና ፡ ሽማግሌ ፡ ሴትና ፡ ወንድ ፡ ቄስና ፡ መነኰሴ ፡ እስላምና ፡ ክርስቲያን ፡ ሳይለይ ፡ ሁላችንንም ፡ በመደዳው ፡ በእሳት ፡ እያቃጠለ ፡ በጥይት ፡ እየገነጠለ ፡ በመግደል ፡ የኛን ፡ ዘር ፡ ከገጸ ፡ ምድር ፡ አጥፍቶ የሱን ፡ ዘር ፡ በሀገራችን ፡ ላይ ፡ አልምቶ ፡ ለማስፈር ፡ ነውና ፡ ነፃታችሁን ፡ ለማዳን ፡ ስትከላከሉ ፡ ብትሞቱ ፡ ሰማዕታት ፡ አልሞቱም ፡ ወደፈጣሪያቸው ፡ ሔዱ ፡ እንጂ ፡ የተባለው ፡ ቃል ፡ ይፈጸምላችኋል ። የጀግንነታችሁም ፡ ዘውድ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ እንደከበረ ፡ ዕንቊ ፡ ይሆናልና ፡ እንደ ፡ ጻድቃንና ፡ እንደ ፡ ሰማዕታት ፡ ደማችሁን ፡ ስለሀገራችሁ ፡ ቤዛ ፡ አፍስሱላት ፡ ይኸውም ፡ የምታፈሱት ፡ ደም ።

፩ኛ| ስለሃይማኖታችሁ ፡
፪ኛ| ስለንጉሠ ፡ ነገሥታችሁ ፡
፫ኛ| ስለሀገራችሁ ፡ ነጻነት ፡
፬ኛ| ስለርስታችሁ ፡
፭ኛ| ከራሳችሁ ፡ ጀምሮ ፡ ስለወገኖቻችሁ ፡ ነውና ፡ ይኸ ፡ ጠላታችን ፡ የመዋቲ ፡ እጅ ፡ የሠራውን ፡ መማሪያ ፡ እንደ ፡ አምላክ ፡ ተማምኖ ፡ ቢመጣባችሁ ፡ እናንተም ፡ ትምክህተኞችን ፡ በሚያጠፋ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ተማምናችሁ ፡ በሀገራችሁ ፡ ፍቅር ፡ ተቃጥላችሁ ፡ ብትገጥሙት ፡ አፍሮ ፡ ይመለሳል ። ይህም ፡ የመጣው ፡ ጠላታችን ፡ የሰውን ፡ ሕይወት ፡ የቅጠል ፡ መቊረጥ ፡ ያህል ፡ የማይቈጥረው ፡ ስለሆነ ፤ ስንኳን ፡ ቤትና ፡ ንብረት ፡ ሊያሲዝ ፡ ከፍ ፡ ነጥቆ ፡ ከእጅ ፡ ፈልቅቆ ፡ የሚቀማ ፡ ለባሕርዩ ፡ ርኅራኄ ፡ የማይስማማው ፡ ጨካኝ ፡ ፍጥረት ፡ ነው ። ያዘጋጀልንም ፡ ሥቃይ ፡ ብርቱ ፡ መሆኑን ፡ ከኛ ፡ ወስዶ ፡ በሚገዛው ፡ ሀገር ፡ ታይቷል ። ስለ ፡ ነፃነት ፡ ብሎ ፡ መሞትም ፡ መግደልም ፡ አሁን ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ሐዋርያት ፡ የሰማዕትነትን ፡ አክሊል ፡ ለመቀበል ፡ ስለ ፡ ሀገራቸውና ፡ ስለ ፡ መንግሥት ፡ ሰማያት ፡ ለመሞት ፡ ይቀዳደሙ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እናንተም ፡ ስለ ፡ ሀገራችሁ ፡ በሞታችሁ ፡ ጠላታችሁን ፡ ድል ፡ ለማድረግ ፡ ተቀዳደሙ ።

በሽታ ፡ እየቀጠቀጠ ፡ ወበ ፡ ምች ፡ ወረርሽኝ ፡ አስጨንቆ ፡ አስጠብቦ ፡ የሚወስዳትን ፡ ሕይወት ፡ ስለ ፡ ሀገራችሁ ፡ አትንፈጓት ፡ የሰው ፡ ዕድሜው ፡ እንደ ፡ ጥላ ፡ ነውና ፡ የዕድሜያችሁ ፡ ገመድ ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ ተበጥሶ ፡ በብላሽ ፡ ከሚቀር ፡ ሠርግና ፡ ኰራት ፡ ሆኖ ፡ በሚታየው ፡ በጀግንነት ፡ ሞት ፡ መሞት ፡ የዋጋው ፡ ግምት ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለው ፡ ነው ።



ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፤ እንጌዴዎን ፡ እንባርቅ ፡ እንዮፍታሔ ፡ እንሶምሶን ፡ እንዳዊት ፡ እንሳሙኤል ፡ ሌሎችም ፡ ነቢያት ፡ ሁሉ ፡ በሃይማኖታቸው ፡ ጸንተው ፡ ተዋግተው ፡ ድል ፡ ቢያደርጉ ፤ የዚህንም ፡ ዓለም ፡ የወዲያኛውንም ፡ ዓለም ፡ ክብር ፡ እንደወረሱ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ነግሮናልና ፡ የነዚህን ፡ አርበኞች ፡ ፍለጋ ፡ ተከትላችሁ ፡ ሥጋችሁን ፡ የሚገድሉትን ፡ አትፍሩ ፡ እንደተባለ ፡ ሳትፈሩ ፡ ሳትሸበሩ ፡ ተዋግቶ ፡ ድል ፡ ለመንሣት ፡ ያብቃችሁ ። ገና ፡ በእጁ ፡ ሳንወድቅ ፡ በምኞት ፡ ብቻ ፡ ስማችንን ፡ እንዲህ ፡ ያጠፋው ፡ ይህ ፡ ጠላታችን ፡ በእጁማ ፡ ብንወድቅ ፡ ምን ፡ ያደርገን ፡ ይሆን ? ሰው ፡ ሁነን ፡ እንዳልተፈጠርን ፡ ሊያደርገን ፡ አይደለምን ? ይህን ፡ ግፍ ፡ አስባችሁ ፡ የሀገራችሁ ፡ ጸጸት ፡ በልቡናችሁ ፡ ይደር ።

እግዚአብሔር ፡ በንጉሣችን ፡ አድሮ ፡ ጠላታችንን ፡ ከእግራችን ፡ በታች ፡ ይጣልልን ። እኔም ፡ አባታችሁ ፡ በሞትም ፡ በሕይወትም ፡ ከናንተ ፡ የተለየ ፡ ክብር ፡ ስለሌለኝ ፤ ስለሀገሬና ፡ ስለንጉሠ ፡ ነገሥቴ ፡ እንድሞት ፡ ተዘጋጅቻለሁና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተወላጆች ፡ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ ምንም ፡ የሃይማኖት ፡ ልዩነት ፡ ቢኖርብን ፤ ክርስቲያኖቹን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናችንን ፡ እስላሞቹንም ፡ መስጊዳችሁን ፡ ከፈጣሪያችን ፡ የምንገናኝበትን ፡ ቤተ ፡ ጸሎታችንን ፡ አፍርሶ ፡ ማርናወተት ፡ የሚያፈስ ፡ ጡቷን ፡ እያጠባች ፡ ከምትመግበን ፡ እናታችን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ለይቶ ፡ በጭራሽ ፡ ሊያጠፋን ፡ የመጣውን ፡ ጠላታችንን ፡ ጣሊያንን ፡ ለመውጋትና ፡ በግፍ ፡ ከያዘብን ፡ ርስታችን ፡ ለማባረር ፡ የማይረዳውን ፡ ሰው ፡ ወደሱም ፡ ለመክዳት ፡ የሚመሳጠረውን ፡ ሁሉ ፡ እስላምም ፡ ክርስቲያንም ፡ ቢሆን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በረከትና ፡ ከኢትዮጵያ ፡ እድል ፡ ይለየው ፡ ስል ፡ ረግሜአለሁ ። ክርስቲያን ፡ ወንድሞቼንም ፡ ካባቶቼ ፡ ከሐዋርያት ፡ ባገኘሁት ፡ ሥልጣን ፡ ገዝቻለሁ ፡ ኅዳር ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ሺ፱፻፳፰ ፡ ዓ ፡ ም ።

ሁለተኛ ፡ ሐዋርያዊ ፡ መልእክት ፡ ከዘመቻው ፡ በኋላ ።

መልእክት ፡ ዘተፈነወት ፡ እምዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ዘነበረ ፡

በመንበረ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።

ትብጻሕ ፡ ኀበ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ ካህናት ፤ ቀሳውስት ፡ ወዲያቆናት ፡ ወኀበ ፡ መኳንንተ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ባላባት ፡ ወሕዝብ ።

የጌታችን ፡ የአምላካችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋና ፡ በረከት ፡ ይደርባችሁ ። አጥቂውና ፡ ግፈኛው ፡ ጠላታችን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ አፍርሶ ፡ ድንበር ፡ ጥሶ ፡ በወረራት ፡ ጊዜ ፤ በዘመቻው ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ጋራ ፡ እንደነበርኩና ፡ አሁንም ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያና ፡ ስለ ፡ ሕዝባቸው ፡ ነጻነት ፡ በዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ ለመከራከርና ፡ ፍርድ ፡ ለመጠየቅ ፡ ወደ ፡ ኤሮፕ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሲመጡ ፡ አብሬ ፡ መምጣቴን ፡ ሰምታችሁ ፡ ይሆናል ። ይኸው ፡ እኔም ፡ በቅደ
ስት ፡ ሀገር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ገዳማችን ፡ እንዳይደፈር ፡ የሃይማኖታችን ፡ መሠ
ረት ፡ እንዳይናወጥ ፡ በኀዘንና ፡ በጸሎት ፡ ተጠምጄ ፡ በአሳብ ፡ ከናንተ ፡ ሳልለይ
እኖራለሁ ።

## የኢትዮጵያ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትና ፡ መኳንንት ፡ ባላባትና ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ።

ጠላታችን ፡ በጨካኝነት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናችንን ፡ ማቃጠሉን ፤ ካህናቶቻችንን
መፍጀቱን ፡ ሕዝባችንን ፡ ወንዱንም ፡ ሴቱንም ፡ ሕፃናትም ፡ ሳይቀሩ ፡ በአረ
መኔ ፡ አደራረግ ፡ ማቃጠሉን ፡ የኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡ ካህናትም ፡ ለግርማዊ
ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ እያመለከታችሁ ፡ ግርማዊነታቸውም ፡ ለዓለም ፡ መንግሥ
ታትና ፡ ሕዝብ ፡ ሲያስታውቁ ፡ አያለሁ ፡ እሰማለሁ ። ምንም ፡ ጠላታችን ፡ በኃ
ይል ፡ ቢመካ ፡ በሃይማኖታችሁ ፡ ጸንታችሁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ተማምናችሁ
በመተባበር ፡ ካህን ፡ በጸሎቱ ፡ ጀግና ፡ በጕልበቱ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ መከ
ላከላችሁና ፡ እንደ ፡ ኃይሉ ፡ መጠን ፡ ሊያጠቃችሁ ፡ ባለመቻሉ ፡ ለዳዊት
አምላክ ፡ ምስጋና ፡ እናቅርብለት ።

## የአገሬ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ።

በአፍሪቃ ፡ ክፍል ፡ ነጻነቷን ፡ ጠብቃ ፡ በክርስቲያንነት ፡ ከብዙ ፡ አገሮች ፡ ይልቅ
ጥንታዊ ፡ ተቀዳሚነት ፡ ያላትን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመግዛት ፤ ሕዝቧን ፡ ለመደ
ምሰስና ፡ የሱን ፡ ሕዝብ ፡ ለመትከል ፡ ቈርጦ ፡ የተነሣው ፡ የፋሺስት ፡ መንግ
ሥት ፡ የዲያብሎስ ፡ አሳቡን ፡ እየሸሸገ ፡ ለጥቅምህ ፡ መጣንልህ ፡ እያለ ፡ ቢሰ
ብክ ፡ እውነት ፡ አይምሰልህ ። ዘርህን ፡ ለማጥፋት ፡ ርስትህን ፡ ለመቀማት
ቤትህን ፡ ንብረትህን ፡ ለማፍረስ ፡ ክብትህን ፡ ለመዝረፍ ፡ ሚስትህን ፡ ልጅህን
ለማርከስ ፡ ቈርጦ ፡ የመጣ ፡ መሆኑን ፡ ባለፈው ፡ ሥራው ፡ ተረድተኸዋል ።
ዛሬ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡ ስላስጨነቁት ፡ አገርህን ፡ እንድትከድ ፡ ንጉሠ
ነገሥትህን ፡ እንድትረሳ ፡ የለመደውን ፡ ሐሰተኛ ፡ ስብከት ፡ እየሰበከልህ ፡ እንደዚሁ
«የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሃይማኖት ፡ የሌለው ፡ አሕዛብ ፡ ነው ። ዘሩም ፡ ወራዳ ፡ ስለሆነ
ሊጠፋ ፡ ይገባዋል ። በጋብቻም ፡ በትምህርትም ፡ በመንፈሳዊና ፡ በዓለማዊ ፡ ማዕ
ርግም ፡ ቢሆን ፡ ከኢጣልያ ፡ ሕዝብ ፡ የሚተካከልበት ፡ የለምና ፡ ዘሩን ፡ እናጠ
ፋዋለን ፡ እያለ ፡ ዘራችንን ፡ ሃይማኖታችንን ፡ እያዋረደ ፡ ሕዝባችንን ፡ በዓለም
ፊት ፡ ነውረኛ ፡ ለማድረግ ፡ መስበኩን ፡ አትዘንጋ ።

ይህን ፡ የተንኰሉን ፡ ስብከት ፡ ካወቃችሁ ፡ በኋላ ፡ ለጠላት ፡ መንግሥት
ግዛት ፡ ለማስፋት ፡ እርስ ፡ በርሳችን ፡ የምንለያይበትን ፤ አንድነትና ፡ ፍቅር ፡ እን
ዳታገኙ ፡ ለመነጣጠል ፡ የሚጣጣርበትን ፡ አታላይ ፡ አሳቡን ፡ (መንፈሱን ፡) የሚ
ሰማው ፡ ማነው ? የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ለርሱ ፡ እንደሚመስለው ፡ የነጻቱን



ዋጋ ፡ የማያውቅ ፡ መስሎታል ። ለነጻነቱና ፡ ላገሩ ፡ የማይታገል ፡ ለባዕድ ፡ መን
ግሥት ፡ ለመገዛት ፡ የሚፈቅድ ፡ ሕዝብ ፡ እንኳንስ ፡ በወዳጁ ፊት ፡ በጠላቱም
ፊት ፡ ቢሆን ፡ የተዋረደ ፡ ነው ።

ጠላታችን ፡ ፋሺሽት ፡ ትሩፖሊን ፡ ሲያቀና ፡ በፈቃዳቸው ፡ በፋኖነት ፡ ይዘ
ምቱለት ፡ የነበሩትን ፡ ኢትዮጵያውያኖች ፡ የተለየ ፡ ስም ፡ አውጥቶላቸው ፡ የተ
ሸጠ ፡ ሥጋ ፡ እያለ ፡ ይጠራቸው ፡ ነበረ ። ይህንንም ፡ ሁላችሁ ፡ በፈተናችሁ
ጊዜ ፡ ልታስቡት ፡ ይገባችኋል ።

ከዚህ ፡ ከሚያስጨንቅ ፡ ፈተና ፡ የምንድንበት ፤ ተጠቂው ፡ ፍርድ ፡ የሚ
ያገኝበት ፡ ግፈኛው ፡ ፍርዱን ፡ የሚቀበልበት ፡ ተስፋ ፡ ጎሕ ፡ ቀዶ ፡ ጮራው
ይታያል ። በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ተመክታችሁ ፡ በሃይማኖታችሁ ፡ ጸንታችሁ
ተስፋ ፡ ሳትቈርጡ ፡ አንድነትንና ፡ ፍቅርን ፡ ጠብቃችሁ ፡ እንድትቆዩ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ኃይሉን ፡ እንዲሰጣችሁ ፡ ረድኤቱንና ፡ ቡራኬውን ፡ በመካከላችሁ
እንዲያሳድር ፡ እንለምናለን ።

ንጉሠ ፡ ነገሥታችንን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጠብቅልን ።
ኢትዮጵያ ፡ ነጻነቷን ፡ ጠብቃ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

ሰኔ ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፩ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ቅድስት ፡ ተጻፈ ።

ፊርማ ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ።

## ሦስተኛ ፡ ሐዋርያዊ ፡ መልእክት ።

መልእክት ፡ ዘተፈነወት ፡ እምዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ።

## ዘነበረ ፡ በመንበረ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።

ትብጻሕ ፡ ኀበ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ ካህናት
ቀሳውስት ፡ ወዲያቆናት ፡ ወኀበ ፡ መኳንንተ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ባላባት ፡ ወሕዝብ ፡
አርበኞች ።

የጌታችን ፡ የአምላካችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋና ፡ በረከት ፡ ይደ
ርባችሁ ። ጌታ ፡ በማቴዎስ ፡ ወንጌል ፡ ወበ ፡ ዘወድቀ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ሠናይት
በ ፡ ዘምዕት ፡ ወበ ፡ ዘ፷ ፡ ወበ ፡ ዘ፴ ፡ ብሎ ፡ ሰማዕታትን ፡ በበኀ ፡ ልጅ ፤
መነኰሳትን ፡ በበን ፡ ሎሌ ፤ ሕጋውያንን ፡ በበኀ ፡ ባሪያ ፡ መስሎ ፡ ተናግሮአል ።
በኀ ፡ ልጅ ፡ አባቱ ፡ ሳለ ፡ ካባቱ ፡ ጋራ ፡ ይወጣል ፡ ይወርዳል ። አባቱ ፡ ከሞተ
በኋላም ፡ በአባቱ ፡ ርስት ፡ ዘምቶ ፡ ይሞታል ። የሰማዕታት ፡ መደበኞች
ሐዋርያት ፡ ናቸው ። በኀ ፡ ልጅ ፡ አባቱ ፡ ሳለ ፡ ከአባቱ ፡ ጋራ ፡ እንዲወጣ ፡ እንዲወርድ
ሐዋርያትም ፡ ጌታ ፡ ሳለ ፡ ከጌታ ፡ ጋራ ፡ ፫ ፡ ዓመት ፡ ከ፫ ፡ ወር ፡ ሲወጡ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሲወርዱ ፡ ኑረዋል። አባቱ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ በአባቱ ፡ ርስት ፡ ዘምቶ ፡ እንዲሞት ፡ ጌታ ፡ ከሞተና ፡ ከተነሣ ፡ በኋላ ፡ ወንጌልን ፡ ሲያስተምሩ ፡ በሰማዕትነት ፡ ሞተዋል ።

እናንተም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንትና ፡ ካህናት ፡ መነኰሳት ፡ መኳንንት ፡ ባላባትና ፡ ሕዝብ ፡ አርበኞችም ፡ ቀድሞም ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ከቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጋራ ፡ ሁናችሁ ፡ አቅማችሁ ፡ በሚችለው ፡ ከጠላት ፡ ተከላክላችሁ ፡ የጀግንነት ፡ ሥራችሁን ፡ ከፈጸማችሁ ፡ በኋላ ፩ ጠላት ፡ በዓለም ፡ ሕግ ፡ ተነቅፎ ፡ በተከለከለው ፡ መሣሪያ ፡ በቦምብ ፡ በጋዝ ፡ መርዝ ፡ በጭከና ፡ ስለመጣብንና ፡ በግፍ ፡ ኃይል ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ አፍርሶ ፡ ወደ ፡ አገራችን ስለገባ ፩ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ለዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ በኢትዮጵያና ፡ በሕዝቧ ፡ ላይ ፡ የወደቀውን ፡ ግፍና ፡ መከራ ፡ አመለክታለሁ ፡ ብለው ፡ ለመቃወም ፡ ቢመጡ ፩ እናንተም ፡ እንደወንድሞቻችሁ ፡ ሰማዕታት ፡ እንደአባቶቻችን ፡ ሐዋርያት ፡ ሁናችሁ ፡ እስካሁን ፡ ለነጻነታችሁ ፡ የምታፈሱት ፡ ደም ፡ ፩ኛ ፡ ስለሃይማኖታችሁ ፡ ፪ኛ ፡ ስለተወደደች ፡ አገራችን ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነጻነት ፡ ፫ኛ የንጉሠ ፡ ነገሥታችንን ፡ ክብር ፡ እናስነካም ፡ ስትሉ ፡ እስካሁን ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ በአርበኝነታችሁ ፡ እንደጐርፍ ፡ የምታፈሱት ፡ ደም ፡ በፈጣሪያችሁ ፡ ፊት ፡ ለነፍሳችሁ ዋጋ ፡ ክብር ፡ ሆኖ ፡ በደማችሁ ፡ ቀለም ፡ ከዓምደ ፡ ወርቅ ፡ የተጻፈ ፡ ነው ። ለሥጋችሁ ፡ ክብር ፡ ሆኖ ፡ በዓለም ፡ ታሪክ ፡ የተጻፈ ፡ ነው ።

በሥጋችሁ ፡ የሚገድሏችሁን ፡ አትፍሯቸው ፡ ነፍሳችሁን ፡ መግደል ፡ አይቻላቸውምና ፡ መፍራትስ ፡ ከገደለ ፡ በኋላ ፡ ነፍስንና ፡ ሥጋን ፡ አዋሕዶ ፡ አስነሥቶ ፡ በገሃነም ፡ ፍዳ ፡ ያመጣ ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ እሱን ፡ ፍሩት ፡ የራሳችሁ ፡ ጸጕር ፡ ሳይቀር ፡ የተቈጠረ ፡ ነውና ፡ አትጠፉም ፡ ይላል ። ማቴ ፡ ፲ ፡ ፳፰ ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ «ወደሰልፍ ፡ የሚቀዳደሙ ፡ ሁሉ ፡ እንዲፋጠኑ ፡ አታውቁምን ፡ አስቀድሞ ፡ ለደረሰው ፡ አርበኛ ፡ የሚደረግለት ፡ ምስጋና ፡ አለ ። እንዲሁም ፡ ታገኙ ፡ ዘንድ ፡ ሩጡ ፡ ተቀዳደሙ ፡ የሚጋደል ፡ አርበኛ ፡ ሁሉ ፡ መከራውን ፡ ይታገሣል» ፡ ማለቱን ፡ አስቡ ። ሁለተኛም ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ እንደሚያገለግል ፡ እንደበጎ ፡ አርበኛ ፡ መከራ ፡ ተቀበሉ ፡ ወደሰልፍ ፡ ሲሔድ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ኑሮ ፡ የሚያስብ ፡ የለምና ፡ የሾመውን ፡ ደስ ፡ ያሰኝ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ። አርበኛ ፡ እንደሚገባው ፡ ካልተዋጋ ፡ መመስገን ፡ አይሆንለትም ፡ በሥራ ፡ የሚደክም ፡ ገበሬ ፡ አስቀድሞ ፡ ፍሬውን ፡ ያገኛል ፡ ይላል ።

ጠላታችን ፡ ፋሺስት ፡ የሰላም ፡ ስብከት ፡ አስመስሎ ፡ የሚሰብክላችሁ ፡ የሰው ፡ ጥፋትና ፡ የአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መደምሰስ ፡ አሳዝኖት ፡ አይደለም ። ስለ አገሩ ፡ ቈርጦ ፡ የተነሣው ፡ አርበኛ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ለዘር ፡ ተርፎ ፡ ያመልጠኛል ፡ በማለትና ፡ የዓለም ፡ ጦርነትም ፡ እየገፋ ፡ በመሔዱ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ችግር ፡ ያገኘኛል ፡ ብሎ ፡ ይህ ፡ ሳይደርስ ፡ እያታለለ ፡ ወንድሙን ፡ ከወንድሙ ፡ ጋር ፡ እያዋጋ ፡ ለማፋጀት ፡ ነውና ፡ እናንተም ፡ ድካማችሁ ፡ እስከመጨረሻ ፡ ካልደረሰ ፡ እስካሁን ፡



የሠራችሁት ፡ ድካም ፡ በከንቱ ፡ ቀሪ ፡ እንዳይሆን ፡ በራእየ ፡ ዮሐንስ ፡ ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፲፩ ፡ የተጻፈውን ፡ ማዘ ከሪያ ፡ ጽፌላችኋለሁ ፡ ወናሁ ፡ እመጽእ ፡ ፍጡነ ፡ ወአጽንዕ ፡ ዘብከ ፡ ከመ ፡ አልቦ ፡ ዘይነሥእ ፡ አክሊለከ ፡ (ፈጥኜ ፡ እመጣለሁና ፡ ባለህበት ፡ ግብር ጸንተህ ፡ ኑር ፡ ክብርህንም ፡ የሚወስድብህ ፡ እንዳይኖር) ። ያንዱን ፡ አንዱ ፡ ይወስደዋልን ፡ ቢሉ ፡ ሥራውን ፡ ከሠራ ፡ ይወስደዋል ፡ ፵ ፡ ሐራ ፡ ሰማይን ፡ እንደሰይፍ ፡ የሚቈርጥ ፡ ውርጭ ፡ ወዳለበት ፡ ቦታ ፡ አገቧቸውና ፡ አንዱ ፡ ቢጸናበት ፡ ፩ ቀን ፡ ሲቀረው ፡ ክጃለሁ ፡ አውጡኝ ፡ አለና ፡ አወጡት ፡ ወዲያውም ፡ ሞተ ፡ ፴፱ ፡ መላእክት ፡ ፴፱ ፡ አክሊላተ ፡ ብርሃን ፡ ይዘው ፡ ወረዱ ፡ ፴፱ኙን ፡ ተቀብለውት ፡ አንዱ ፡ ተሰቅሎ ፡ ሲቀር ፡ አየ ። ከሚያሠቃዩአቸው ፡ አረማውያን ፡ አንዱ ፡ እኔ ፡ በክርስቶስ ፡ አምኛለሁና ፡ አግቡኝ ፡ ቢል ፡ ዕለቱን ፡ ገብቶ ፡ ዕለቱን ፡ ተቀብሎታልና ፡ የመከራችሁን ፡ ጊዜ ፡ መርዘም ፡ አትመልከቱ ። የደከማችሁበት ፡ ክብር ፡ ወደሌላ ፡ እንዳያልፍ ፡ ልቡናችሁን ፡ ያጽናው ። እኛንም ፡ ወገኖቻችሁን ፡ ለክርስቶስ ፡ የሚሰነው ፡ የለምና ፡ ሕይወታችሁንም ፡ ሞታችሁንም ፡ አብሮ ፡ ለመሳተፍ ፡ እንዲያበቃን ፡ ተስፋችን ፡ አያቋርጥም ። ይህንኑም ፡ ስንል ፡ በኢትዮጵያ ፡ የወደቀባትን ፡ ፈተና ፡ በ፷፰ኛ ፡ መዝሙር ፡ የተጻፈውን ፡ እግዚኦ ፡ ቦኡ ፡ አሕዛብ ፡ ውስተ ፡ ርስትከን ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ የተጻፈውን ፡ እያሰብን ፡ ዘወትር ፡ ከሕሊናችንም ፡ ከቃላችንም ፡ ሳናጠፋ ፡ ነው ። መጋደልንም ፡ ተጋደልኩ ፡ ቅድድሜንም ፡ ፈጸምኩ ፡ ሃይማኖቴንም ፡ ጠበቅሁ ፡ እንግዴህ ፡ ወዲህስ ፡ በዚያች ፡ ቀን ፡ እውነት ፡ የሚፈርድ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚሰጠኝን ፡ የጽድቅ ፡ አክሊልና ፡ የኢትዮጵያን ፡ ነጻነት ፡ ለማየት ፡ ያበቃኛል ፡ የማለት ፡ አሳብን ፡ ያሳድርባችሁ ፡ መቸውንም ፡ ከልቡናችሁ ፡ አያጥፋባችሁ ፡ ሰላመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አይለያችሁ ፡ በዓይነ ፡ ሥጋ ፡ ለመገናኘት ፡ ያብቃን ።

ሰኔ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፩ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ተጻፈ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ቅድስት ።

## ዐራተኛ ፡ ሐዋርያዊ ፡ መልእክት ።

በኢትዮጵያ ፡ አውራጃ ፡ ስለነጻነታቸውና ፡ ስለመንግሥታቸው ፡ ለሚከላከሉ ፡ መኳንንትና ፡ አርበኞች ፡ የተጻፈ ፡ ይድረስ ፡ ለክቡር ፡ ወንድማችን ፡ ............ በአንድነት ፡ ላላችሁ ፡ ለጦር ፡ አርበኞች ፡ ሁሉ ።

እጅጉን ፡ እንደምን ፡ ሰንብታችኋል ፡ እኛ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ከተለየናችሁ ፡ እስካሁን ፡ ደኅና ፡ ነን ። በዓለም ፡ የተደነቃችሁ ፡ ስመ ፡ ጥሩዎቹ ፡ ጀግኖች ፡ ወንድሞቻችን ፡ ሆይ ፡ በሥጋ ፡ ብንራራቅ ፡ በመንፈስ አንድ ፡ ስለሆንን ፡ በመጠየቅ ፡ መልካሙን ፡ የጀግንነት ፡ ሥራችሁን ፡ እየሰማን ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ስላለን ፡ በተሰደድንበት ፡ አገር ፡ ሁነን ፡ ስለአገራችን ፡ እኛም ፡ የሰማነውንና ፡ የደረስንበትን ፡ ጊዜ ፡ እንድታውቁት ፡ በማለት ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተጻፉትን ፡ ቃሎች ፡ እናስታውቃችኋለን ።

www.ethiopianorthodox.org

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በኢትዮጵያ
ሕዝብ ፡ ላይ ፡ በተሠራው ፡ ግፍና ፡ በፈሰሰው ፡ ደም ፡ ስለሀገራቸው ፡ ነጻነት ፡ ለ
ከራከር ፡ የተሰደዱበት ፡ ጉዳይ ፡ መፈጸሚያው ፡ ጊዜ ፡ የደረሰ ፡ ይመስለናል ።

በደማችሁ ፡ የዘራችሁትን ፡ ፍሬ ፡ ለማግኘት ፡ እንደፈማዳችሁ ፡ በርቱ ፡ ይ
ንንም ፡ የምንልበት ፡ ምክንያት ፡ ኢጣሊያ ፡ እንግሊዝንና ፡ ፈረንሳይን ፡ ትቶ ፡ ከ
ርመን ፡ ጋራ ፡ ለመረዳዳት ፡ የጸና ፡ ወዳጅነት ፡ አበጅቶ ፡ ጀርመን ፡ ሲነካ ፡ እኔም
አብሬ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ በኦፊሴል ፡ በግልጽ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ለዓለም ፡ ሁሉ ፡ አ
ታውቋል ።

ይኸው ፡ አሁን ፡ የጀርመን ፡ መንግሥት ፡ ፀብ ፡ አንሥቶ ፡ ከእንግሊዝና
ከፈረንሳይ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ የበረታ ፡ ጦርነት ፡ ጀምሮ ፡ ይዋጋሉ ። የጦሩ
አኳሁን ፡ የእንግሊዝና ፡ የፈረንሳይ ፡ የጦር ፡ ኃይል ፡ ገፍቶ ፡ ወደጀርመን ፡ አገ
ገብተው ፡ ነው ፡ የሚዋጉት ።

ስለዚህ ፤ እግዚአብሔር ፡ የኢትዮጵያን ፡ ደም ፡ ተበቅሎ ፡ ሥራውን ፡ የ
ሠራ ፡ መስሎ ፡ ይታያልና ፡ አርበኞች ፡ ወንድሞቻችን ፡ ሆይ ፡ የተለመደ ፡ የጀ
ንነት ፡ ሥራችሁን ፡ ሳታቋርጡ ፡ ለሕዝቡም ፡ በሰፊው ፡ እያስረዳችሁ ፡ መጠንከር
ነው ። ደግሞ ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ለሚደከሙበት ፡ ጉዳይ ፡ እርዳታ ፡ የነገር ፡ መ
ረሻ ፡ የሚሆን ፡ ለዓለም ፡ ነገሥታት ፡ ማኅበር ፡ ፊት ፡ የሚቀርብ ፡ እስከሁን
የሠራችሁትንና ፡ ወደፊትም ፡ የምትሠሩትን ፡ አሳብ ፡ በሰፊው ፡ በጉባኤው ፡ ፊት
የሚቀርብ ፡ የተቃና ፡ ቃል ፡ ጽፋችሁ ፡ ማኅተም ፡ ያለው ፡ በማኅተሙ ፡ ማኅተም
የሌለው ፡ በፊርማው ፡ እያደረጋችሁ ፡ ብትልኩልን ፡ መልካም ፡ ነው ።

ስትልኩልንም ፡ ይህን ፡ ወረቀት ፡ በሚያደርስላችሁ ፡ በኩል ፡ ብትል
ልን ፡ በቀጥታ ፡ ይደርሰናል ። እኛም ፡ የተሰደድነው ፡ ወንድሞቻችሁ ፡ ሁሉ
ያለነው ፡ ከእንግሊዝና ፡ ከፈረንሳይ ፡ ጋር ፡ ነን ። በቅርብ ፡ ጊዜም ፡ እንድንገና
ሙሉ ፡ ተስፋ ፡ አለን ፡ ወደፊትም ፡ የሚሆነውን ፡ ነገር ፡ እያከታተልን ፡ እን
ፍላችኋለንና ፡ እናንተም ፡ በየጊዜው ፡ እንድትጽፉልን ፡ ይሁን ።

ከኛ ፡ ጋር ፡ ያሉ ፡ መኳንንቶች ፡ ስማቸው ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተጻፈው ፡ የናፍቆት
ሰላምታቸውን ፡ ያቀርቡላችኋል ፡ ኅዳር ፡ . . . ፲፱፻፴፪ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ።

ልዑል ፡ ራስ ፡ ካሣ ፡
ክቡር ፡ ፊታውራሪ ፡ ብሩ ፡ ኋላ ፡ ራስ ፡
ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ይገዙ ፡
ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ዓምዴ ፡
ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ መኩንን ፡ እንዳልካቸው ፡ አሁን ፡ ራስ ፡ ቢትወደድ
ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ አበበ ፡
ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ አደፍርሰው ፡ አሁን ፡ ራስ ፡
ክቡር ፡ ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ ኃይሌ ፡ ወልደ ፡ ሩፌ ፡



በዚህ ፡ ቃል ፡ የተጻፈላቸው ፡ አርበኞች ፡ ስም ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈው ፡ ነው ።

ለደጃዝማች ፡ አውራሪስ ፡
ለግራዝማች ፡ ዘውዴ ፡ አስፋው ፡ አሁን ፡ ደጃዝማች ፡
ለቀኛዝማች ፡ በዛብህ ፡
ለፊታውራሪ ፡ በዳኔ ፡ አሻግር ፡
ለልጅ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፤ ሥዩም ፡
ለልጅ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ ሥዩም ፡
ለልጅ ፡ አየለ ፡ ኃይሌ ፡ ኋላ ፡ ወህኒ ፡ አዛዥ ፡
ለአቶ ፡ ከበረ ፤
ለቀኛዝማች ፡ ኃይሌ ፡ እንደብላቱ ፡
ለታደሰ ፡ ሸዋ ፡ እርካብህ ፡
ለበሻ ፡ ወልዴ ፡
ለደጃዝማች ፡ ዮሴፍ ፡ ብሩ ፡
ለደጃዝማች ፡ እሸቴ ፡
ለሻለቃ ፡ መስፍን ፡ ስለሺ ፡ አሁን ፡ ራስ ፡
ለልጅ ፡ ደምሴ ፡ ብሩ ፡
ለባላምራባራስ ፡ ታደሰ ፡
ለፊታውራሪ ፡ ወሊቃ ፡
ለፊታውራሪ ፡ ዘውዱ ፡ አባ ፡ ኰራን ፡ ኋላ ደጃዝማች ፡
ለደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ በዛብህ ፡
ለደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬ ፡
ለነጻነት ፡ ጦር ፡ አዝማች ፡ አበበ ፡ ጐበና ፡ ኋላ ፡ ራስ ፡
ለባላምባራስ ፡ ገረሱ ፡ ዱኪ ፡ ኋላ ፡ ደጃዝማች ፡
ለልጅ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ ማሞ ።
ለፊታውራሪ ፡ ተድላ ፡ ክፈተው ፡
ለባሻ ፡ ወልደ ፡ ኪሮስ ፡ አሁን ፡ ብላታ ፡
ለቀኛዝማች ፡ እንደሻው ቀኘጨ ፡
ለቀኛዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በላይነህ ፡
ለልጅ ፡ ግዛቸው ፡ ኃይሌ ፡
ለደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ አበዬ ፡
ለደጃዝማች ፡ ዘትግሬ ፡
ለብላታ ፡ ታከለ ፡ አሁን ፡ ደጃዝማች ፡
ለአዛዥ ፡ ቦጋለ ፡
ለግራዝማች ፡ በላይ ፡ በዛብህ ፡
ለፊታውራሪ ፡ አይሩ ፡ ወለጋ ፡ ጒድሩ ፡
ለዋግ ፡ መኳንንትና ፡ ባላባት ሠራዊትም ፡

www.ethiopianorthodox.org

ለላስታ ፡ መኳንንትና ፡ ባላባት ፡ ሠራዊትም ፡
ለየጁ ፡ መኳንንትና ፡ ባላባት ፡ ሠራዊትም ፡
ለራያ ፡ ለአዘቦ ፡ መኳንንትና ፡ ባላባት ፡ ሠራዊትም ፡
ለበጌምድር ፡ መኳንንትና ፤ ባላባቶችና ፡ ሠራዊትም ፡
ለደጃዝማች ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ አሁን ፡ ራስ ፡
የተላከላቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ አውራጃዎች ፡ በጌምድር ፤ ጐጃም ፤ ዋግ ፤ ላስታ ፡
ሸዋ ፡ ወሎ ናቸው ።

## ዐምስተኛው ፡ ሐዋርያዊ ፡ መልእክት ።

መልእክት ፡ ዘፈነዋ ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡
ዘመንግሥተ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዘልሀቀ ፡ በውስቴታ ፡ ለደብረ ፡ ሊባኖስ ፡
ዘነበረ ፡ በመንበረ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።

ኢትዮጵያ ፡ በተባለች ፡ ሀገር ፡ በየአውራጃዋ ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማኅበ[ር] ለሆኑ ፡ ምእመናን ፡ አርበኞች ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ክፍል ፡ ላሉ ፡ ከህናትና [...] መነኰሳትም ፡ ሁሉ ፡ ትድረስ ። ከአባታችን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ከጌታችን ፡ ከ[...] የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰላምና ፡ ጸጋ ለናንተ ፡ ይሁን ። የምሕረት ፡ አባት ፡ የደስታ [...] ሁሉ ፡ ባለቤት ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አባት ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገ[ን] [...]

እግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ ባሰኘን ፡ ደስታ ፡ ያዘኑትን ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ለማሰኘ[ት] [...] ይቻለን ፡ ዘንድ ፡ በመከራው ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ያሰኘን ፡ የክርስቶስ ፡ መከራው ፡ በእ[...] እንደበዛ ፡ መጠን ፡ እንደዚሁ ፡ በክርስቶስ ፡ ደስታችን ፡ ይበዛል ። መከራውን [...] ቀበል ፡ እናንተ ፡ ከመከራ ፡ ትድኑ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ደስ ፡ ቢለንም ፡ እናንተን ፡ ደ[ስ] ይላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። እኛ የተቀበልነውን ፡ መከራ ፡ ታግሣችሁ ፡ ትድኑ ፡ ዘንድ [...] ነው ። ስለናንተም ተስፋችን ፡ ጽኑ ፡ ነው ። በመከራ ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ እንደ[...] ናችሁ ፡ በደስታችንም ፡ አንድ ፡ ትሆናላችሁ ።

ወንድሞቻችን ፡ በኢትዮጵያ ፡ መከራ ፡ እንደተቀበልን ፡ ልታውቁ ፡ እወዳለሁ [...] ከኃይላችን ፡ መጠን ፡ የወጣ ፡ እጅግ ፡ መከራ ፡ አጽንተውብናልና ። የሕይወታችን[ም] ተስፋ ፡ ቈርጠን ፡ ለሞት ፡ እስክንጨክን ፡ ድረስ ፡ ብሎ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ለቆሮ[ን]ቶስ ፡ ሰዎች ፡ እንደጻፈላቸው ፡ ሁሉ ፡ ከልእ ፡ ቆሮንቶስ ም ፡ ፩ ቍ ፡ ፱ ፡ ክፍል ፤ [...] ጠቅሼ ፡ ሰላምታዬን ፡ እጽፍላችኋለሁ ።

፩ኛ/ መሠረታዊው ፡ ምክሬ ፡ ግን ፡ ስለሀገሩ ፡ የገደለም ፡ የሞተም ፡ ሰማዕት ፡ ይሆና[ል] ለማለት ፡ ነው ።

፪ኛ ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ነጻነት ፡ መከራውን ፡ ታግሠው ፡ ስለሚዋጉ ፡ አርበኞ[ች] ክብራቸው ፡ በመጻሕፍት ፡ የተጻፈ ፡ ነው ። ጳውሎስ ፡ ሮሜ ፡ ም ፡ ፰ ፡ ቍ ፡ ፫ ፡ በ[...] ከራችንም ፡ እንመከለን ፡ እንጂ ፡ መከራ ፡ ትዕግሥትን ፤ ትዕግሥት ፡ ተስፋን ፡ እ[...] ዲያመጣልን ፡ እናውቃለን ።



በፈተናም ፡ ተስፋ ፡ ይገኛል ፡ ተስፋውም ፡ አያሳፍርም ፡ በሰጠን ፡ በመንፈስ ፡ [ቅ]ዱስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍቅሩ ፡ በልባችን ፡ መልቷልና ፡ ይላል ።

አቡቀለምሲስም ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፲ ፡ «ስውነትህን ፡ ለመከራ ፡ ስጥ ፡ እንጂ ፡ ከመ[ከ]ራ ፡ አትለይ ፡ ለማለት ፡ መከራ ፡ ትቀበል ፡ ዘንድ ፡ ስላለህ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ አት[ፍ]ራ ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ የታመንህ ፡ ሁን ፡ የሕይወትም ፡ አክሊል ፡ እሰጥሃለሁ ፡ [ጆ]ሮ ፡ ያለው ፡ ይህን ፡ ይስማ» ፡ ይላል ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ የተናገረው ፡ መከራ ፡ ለሚቀበል ፡ ለክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ [...]መሆኑን ፡ ያመለክታል ። ያውም ፡ ስለሀገራቸው ፡ ነጻነት ፡ ደማቸውን ፡ ለሚያፈሱ ፡ [...]ኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡ እንደሆነ ፡ የዛሬውን ፡ ያሳያል ።

፫ኛ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ነውር ፡ እንዲሆንባት ፡ ርስቱን ፡ ለጠላት ፡ ሊያወርስ ፡ አባት ፡ ልጁን [...]ጅ ፡ አባቱን ፡ (ይወጋል) ፡ ወንድም ፡ ወንድሙን ፡ ይወጋል ። እንዲህ ፡ ያለ ፡ [ነ]ውር ፡ በነጮች ፡ የለም ። ጠላት ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ስለሀገሩ ፡ ነጻነት ፡ ርስቱን ፡ ለመ[...]መለስ ፡ ከዘመዶቹ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ ጠላቱን ፡ ይወጋል ፡ እንጂ ፡ ርስታቸውን ፡ ለጠ[ላ]ት ፡ ለማውረስ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ነጻነት ፡ ለማፍረስ ፡ ለነጻነታቸው ፡ የሚከላከሉትን ፡ [ዘ]መዶቻቸውን ፡ የሚወጉ ፡ ቢኖሩ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰዎች ፡ በነውር ፡ ከመኖር ፡ [...]መሞት ፡ ይሻላቸው ፡ ነበር ።

ስለኢትዮጵያ ፡ ነጻነት ፡ ደማቸውን ፡ አፍስሰው ፡ የሞቱ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ክብራ[ቸ]ውን ፡ አግኝተው ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ገብተው ፡ ይኖራሉ ። መንግሥተ ፡ ሰማ[ያት] ፡ በብዙ ፡ መከራ ፡ እንድትገባ ፡ መጽሐፍ ፡ ተናግሮዋል ፡ ግብረ ፡ ሐዋርያት ፡ [...] ፲፬ ፡ ቍ ፡ ፳፪ ።

በሃይማኖት ፡ ጸንተን ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ በብዙ ፡ መከራ ፡ እን[ድን]ገባ ፡ ዘንድ ፡ ይገባናል ፡ ይላል ።

፬ኛ ፡ ስለወገኑ ፡ ጠላትን ፡ የሚገድል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወዳጅ ፡ ሙሴን ፡ ይመ[ስ]ላል ። አሪት ፡ ዘፀአት ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፲፪ ። ሙሴ ፡ በግብጽ ፡ ሳለ ፡ ወንድሞቹን ፡ [...]ሊጠይቅ ፡ ወጣና ፡ መከራቸውን ፡ አየ ። ግብጻዊም ፡ ዕብራዊውን ፡ በግፍ ፡ ሲመታ ፡ [...] ግብጻዊውን ፡ ገድሎ ፡ ዕብራዊውን ፡ አድኖ ፡ አገር ፡ ለቆ ፡ ምድያም ፡ ወደሚ[ባ]ል ፡ አገር ፡ ተሰዶ ፡ ኖረ ፡ ይላል ። ጠላትን ፡ ገድሎ ፡ ወገኑን ፡ ማዳኑ ፡ ከጽድቅ ፡ ተቈጠረለት ፡ እንጂ ፡ ዕዳ ፡ አልሆነበትም ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ሙሴ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወዳጅ ፡ ተባለ ። ዛሬም ፡ ስለሀ[...]ገሩና ፡ ስለሃይማኖቱ ፡ ደሙን ፡ የሚያፈስ ፡ ሙሴን ፡ ይመስላል ።

፭ኛ ፡ ስለስንፍናና ፡ ስለ ፡ ዝንጋዔ ፡ እስራኤል ፡ በበረሃ ፡ ሳሉ ፡ ሙሴ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ [...]ስንብቶ ፡ በፃቀን ፡ ቢመለስ ፤ ጣዖት ፡ አቁመው ፡ መሥዋዕተ ፡ ጣዖቱን ፡ በልተው ፡ ሲዘፍኑ ፡ ሲአጨበጭቡ ፡ አገኛቸውና ፡ ድርጎውን ፡ እየተቀበላችሁ ፡ በእግዚአብሔር ፡

www.ethiopianorthodox.org

ትማለቃላችሁ ?፣ ብሎ ፡ ሌዋውያንን ፡ ወንድሞቹን ፡ አስከትቶ ፡ ፫ሺህ ፡ እስራኤ
ልን ፡ አስፈጀ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ መናፍቃን ፡ ሲጠፉ ፡ አይቶ ፡ እጅግ ፡ ደስ
አለው ። ሙሴም ፡ በመናፍቃን ፡ ጥፋት ፡ ደስ ፡ ብሎታል ፡ ኦሪት ፡ ዘፀአት ፡ ም ፡ ፴፪
ቍጥር ፡ ፳፯ ።

ሙሴም ፡ በከተማው ፡ ደጅ ፡ ቆመ ፡ አለም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወገን ፡ የሆነ
ወደኔ ፡ ይቅረብ ። የሌዊ ፡ ልጆችም ፡ ሁሉ ፡ ወደሱ ፡ ተሰበሰቡ ፡ አላቸውም
እግዚአብሔር ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሚለው ፡ ይህ ፡ ነው ። የእናንተ ፡ ሰው
ሁሉ ፡ ሰይፉን ፡ በወገቡ ፡ ላይ ፡ ይታጠቅ ፡ በሠፈሩም ፡ መኻከል ፡ እለፉ ፡ ከደጅ
እስከ ፡ ደጅም ፡ ተመላለሱ ፡ የእናንተ ፡ ሰውም ፡ ሁሉ ፡ ወንድሙን ፡ ይግደል ፡ ወዳ
ንም ፡ ዘመዱንም ። የሌዊም ፡ ልጆች ፡ ሙሴ ፡ እንዳለ ፡ አደረጉ ። በዚያን ፡ ቀን
ከሕዝቡ ፡ ፫ሺህ ፡ የሚያህሉ ፡ ሰዎች ፡ ሞቱ ። ሙሴም ፡ አላቸው ፡ እጃችሁን
በዚህ ፡ ቀን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምሉ ፡ ከላንተም ፡ እያንዳንዱ ፡ በልጁ ፡ በወን
ሙም ፡ ዛሬ ፡ በረከት ፡ እንዲወርድላችሁ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ አሰ
ችሁት ፡ ለማለት ፡ ነው ። ዛሬም ፡ በድንቍርና ፡ በስንፍና ፡ ርስታችንን ፡ ነጻነታችንን ፡ ሃ
ማኖታችንንም ፡ ለማጥፋት ፡ የጠላት ፡ ረዳትና ፡ ወገን ፡ ሆነው ፡ ሊያጠፏችሁ ፡ የሚመጡ
ቢኖሩ ፡ ብታጠፉዋቸው ፡ ሙሴ ፡ እንዳጠፋቸው ፡ መናፍቃን ፡ እግዚአብሔር ፡ እ
ደፈረደባቸው ፡ መሆናቸው ፡ ነውና ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ዕዳ ፡ የለባችሁም ፤ ክብር
እንጂ ።

እኔም ፤ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እንዳለው ፡ ሁሉ ፡ ቈላስይስ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፭
እኔስ ፡ በሥጋዬ ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ ባልኖር ፡ በልቡናዬ ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝ ፡ ግ
ራችሁንና ፡ ሥራችሁን ፡ በክርስቶስም ፡ የሚሆን ፡ የሃይማኖታችሁን ፡ ጽናት ፡ ስ
የሁ ፡ እነሆ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ። ም ፡ ፬ ቍ ፡ ፲፰ ፡ እኔ ፡ በጄ ፡ ጽፌ ፡ እንደ
ናችሁ ፡ እላችኋለሁ ፡ ስደቴን ፡ አስቡ ፡ ጸጋ ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ ይሁን ።

ታሕሣሥ ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፪ ፡ ዓ ፡ ም ።

በኢየሩሳሌም ፡ ቅድስት ።

ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ።

---

## ስድስተኛ ሐዋርያዊ መልእክት ።

በኢትዮጵያ ፡ አውራጃ ፡ ላለ ፡ ለያንዳንዱ ፡

### አርበኛ ፡ አለቃ ፡ የተጻፈ ።

መልእክት ፡ ዘፈነዋ ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ዘመንግሥተ ፡ ኢትዮጵያ ።
ዘልህቀ ፡ በውስቴታ ፡ ለደብረ ፡ ሊባኖስ ።
ዘነበረ ፡ በመንበረ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡



ለክቡር ፡ ................................................ ትድረስ ፡ ሰላም ፡ ለናንተ ፡ ይሁን ።

ፍቅርና ፡ ይቅርታም ፡ በመካከላችሁ ፡ ትብዛ ። ልጄ ፡ ሆይ ፡ ስለሁላችን ፡ ሕይወት ፡
እጽፍልህ ፡ ዘንድ ፡ እጅግ ፡ ቸኰልኩ ። ብዙ ፡ እጽፍልህ ፡ ዘንድ ፡ ተግቼ ፡ ነበርና ።
ለቅዱሳን ፡ ስለተሰጠች ፡ ሃይማኖት ፡ ትጋደል ፡ ዘንድ ፡ እማልድሃለሁ ። ነሐሴ ፡ ፳፯ ፡
ቀን ፡ የተጻፈ ፡ በኢትዮጵያ መንግሥት የጦር ፡ ሚኒስቴር ፡ ማኅተም ፡ የታተመ ፡
ደብዳቤ ፡ ደርሶኝ ፡ ሳነብ ፡ ደኅንነታችሁን ፡ በመስማቴ ፡ እጅግ ፡ አድርጎ ፡ ደስ ፡ አለኝ ።
ከደስታዬም ፡ ብዛት ፡ ዕንባዬ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ፈሰሰ ።

ከሁሉም የሚበልጠው ፡ ደስታዬ ፡ አንድነታችሁን ፡ በመስማቴ ፡ ነው ። ዕንባ
ዬም ፡ የመከራችሁ ፡ ጽናት እየታሰበኝ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ልጅ ፡ ካባቱ ፡ ይበል
ጣል ፡ የሚባለውን ፡ ነገርና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነጻነቷን ፡ አጥታና ፡ ተደምስሳ ፡ እንዳትቀር ፡
ለዓለም ፡ ታሪክ ፡ ለኋላ ፡ ዘርና ፡ ትውልድ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መልካሟ ፡ ወላድ ፡
እናንተን ፡ አርበኞቿን ፡ በማስገኘቷ ፡ እጅግ ፡ አድርጌ ፡ ፈጣሪዬን ፡ አመሰግነዋለሁ ።

እናንተም ፡ እስካሁን ፡ ከጠላት ፡ አደጋ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ተጠብቃ
ችሁ ፡ መቆየታችሁና ፡ ኃይል ፡ ማግኘታችሁ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ታበጽሕ ፡ እደዊሃ ፡ ኀበ ፡
እግዚአብሔር ፡ ያለውን ፡ ያሳያል ። አሁንም ፡ ሁሉን ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ የዳዊትን
ሀብተ ፡ መዊዕ ፡ ያሳድርባችሁ ፣ ጢሞቴዎስ ፡ ካልእ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፭ ። ቅዱስ ፡ ጳው
ሎስ ፡ እንደተናገረው ፡ ሁሉ አንተ ፡ ግን ፡ ንቃ ፡ በሁሉም ፡ ጥበበኛ ፡ ሁን ፡ መከ
ራውን ፡ ተቀበል ፡ በመከራው ፡ ጸንተህ ፡ ንጉሥህ ፡ ያዘዘውን ፡ ሥራ ፡ አገልግሎ
ትህንም ፡ ፈጽም ፡ ቍ ፡ ፯ ። በጎ ፡ መጋደልን ፡ ተጋደልሁ ፡ ቅድድሜንም ፡ ፈጸምሁ ፡
ሃይማኖቴንም ፡ ጠበቅሁ ፡ እንግዲህስ ፡ በዚያች ፡ ቀን ፡ እውነት ፡ የሚፈርድ ፡
አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚሰጣኝ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነጻነትና ፡ የጽድቅ ፡ አክሊል ፡
ይቆየኛል ፡ መስጠቱም ፡ ለኔብቻ ፡ አይደለም ። እኔን ፡ ለመሰሉ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አርበ
ኞች ፡ ሁሉ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሚል ፡ ሕሊና ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ድረስ ፡ ያሳድ
ርብህ ፡ በዓይነ ፡ ሥጋ ፡ ለመገናኘት ፡ ያብቃን ። ሰላመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አይለይህ ።
ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እንደጻፈው ፡ ሁሉ ፡ ካልዕ ፡ ተሰሎንቄ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፲፯ ፡ ይኸን ፡
ሰላምታ ፡ እኔ ፡ በእጄ ፡ ጻፍሁ ፡ በምጽፈው ፡ ደብዳቤ ፡ ሁሉ ፡ ምልክቴ ፡ ይህ ፡ ነው ፡
እንዲህ ፡ እጽፋለሁ ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋ ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡ ይሁን ።
ታሕሣሥ ፡ ፲፱፻፴፪ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ተጻፈ ።

በቅድስት ፡ ሀገር ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በትልቁ ፡ ንጉሥ ፡ ከተማ ።

## ሰባተኛ ፡ ሐዋርያዊ ፡ መልእክት ።

መልእክት ፡ ዘፈነዋ ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ።
### ዘመንግሥተ ፡ ኢትዮጵያ ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በግፍ ፡ ከመጣብን ፡ ጠላታችን ፡ ጋራ ፡ ስለሃይማኖቱና ፡
ስለሀገሩ ፡ ነጻነት ፡ በሚገባው ፡ ሲጋደልና ፡ ሲሰየፍ ፡ አንዳንዱ ፡ እየተለየ ፡ መላ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ኢትዮጵያን ፡ ካጠፉ ፡ ዘራችንን ፡ ከደመሰሰ ፡ በግፍ ፡ ደማችንን ፡ ካፈሰሰ ፡ ጠላታ
ችን ፡ ጋራ ፡ እየተባበረ ፡ ለጠላት ፡ መሣሪያ ፡ ሆኖ ፡ የሚረዳውን ፡ ይልቁንም
ሊቃውንትና ፡ ካህናት ፡ ሕዝቡን ፡ ስለሃይማኖታቸውና ፡ ስለሀገራቸው ፡ ጠንክረው
እንዲጋደሉ ፡ መምከርና ፡ ማጥናናት ፡ አብነትም ፡ መሆን ፡ ይገባቸው ፡ የነበረውን
ሕዝቡ ፡ ተባብሮ ፡ በአርበኝነት ፡ ስለሀገሩና ፡ ስለሃይማኖቱ ፡ ሲዋጋ ፡ የሕዝቡን
ልብ ፡ ለማስነፍ ፡ ለጠላት ፡ መሣሪያ ፡ ሁነው ፡ ጥፋቱን ፡ ልማት ፡ እያስመሰሉና ፡ በገን
ዘብ ፡ እየተገዙ ፡ የሀገራቸውን ፡ ነጻነትና ፡ ሃይማኖት ፡ የሚጠፋበት ፡ ስብከት ፡ የሚሰ
ብኩትን ፡ ይህን ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ትተው ፡ በግፍ ፡ የፈሰሰውን ፡ የወንድሞቻቸውን
ደም ፡ አስበው ፡ ስለሀገራቸው ፡ ነጻነት ፡ የሚጋደሉትን ፡ ወንድሞቻቸውን ፡ መ
ለው ፡ እያጥናኑ ፡ ስለሀገራቸው ፡ እንዲረዱ ፡ እንመክራቸዋለን ።

ስለሀገርና ፡ ስለሃይማኖት ፡ መጋደል ፡ ስለወገን ፡ መቅናት ፡ የሚገባ ፡ መሆ
ንም ፡ በቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ከተጻፈው ፡ ከብዙው ፡ በጥቂቱ ፡ ከሙሉ ፡ በክፍሉ
ከዚህ ፡ አስከትለን ፡ ጽፈነዋል ።

፩ኛ ፡ በኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ ም ፡ ፳፭ ፡ ቊ ፡ ፳፱ ፡ ም ፡ ፳፯ ፡ ቊ ፡ ፴፮ ፡ እንደተጻፈው ፡ ዔሳው
ብኵርናውን ፡ ላንዲት ፡ መብል ፡ ስለሸጠ ፡ ለወንድሙ ፡ ባሪያ ፡ ሆኖ ፡ የመገዛትን
መርገም ፡ እንደተቀበለ ፡ እንዲሁም ፡ በፍቅረ ፡ ንዋይ ፡ ተታለው ፡ ለወንድሙ ፡ ገዳይ
ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አቃጣይ ፡ ነጻነቱን ፡ የሸጠ ፡ ከዔሳው ፡ የበለጠ ፡ መርገምና
ኵነኔ ፡ የሚያገኘው ፡ መሆኑን ።

፪ኛ ፡ በቀዳማዊ ፡ መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ም ፡ ፳፩ ፡ ቊ ፡ ፩–፳ ፡ እንደተጻፈ ፤ ናቡቴ
የአባቶቹን ፡ ርስት ፡ አልሸጥም ፡ አልለውጥም ፡ ስለማለቱ ፡ በግፍ ፡ እንደሞተ ፡ እን
ሁም ፡ ስለ ፡ ሃይማኖቱና ፡ ስለ ፡ ሀገሩ ፡ የመጣውን ፡ ሞትና ፡ መከራ ፡ ስደትና
ጭንቀት ፡ መቀበል ፡ የሚገባ ፡ መሆኑን ።

፫ኛ ፡ በኦሪት ፡ ዘፀአት ፡ ምዕ ፡ ፪ ፡ ቊ ፡ ፲፩–፲፫ ፡ እንደተጻፈ ፡ ሙሴ ፡ ለወገኖቹ
ቀንቶ ፡ ግብጻዊውን ፡ እንደገደለ ፡ እንዲሁም ፡ በወገኖቹ ፡ ላይ ፡ የተደረገውን ፡ የ
ቃይ ፡ አገዳደልና ፡ የግፍ ፡ አቀባበል ፡ አስቦ ፡ መጋደል ፡ የሚገባ ፡ መሆኑን ።

፬ኛ ፡ በመጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፡ ም ፡ ፲፮ ፡ ቊ ፡ ፲፱ ፡ እንደተጻፈው ፡ ከገፊዎች ፡ ጋራ
ምርኮን ፡ ከመካፈል ፡ ከተገፊዎች ፡ ጋራ ፡ መከራ ፡ መቀበል ፡ የሚበልጥ ፡ መሆኑን

፭ኛ ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፵፬ ፡ እንደተጻፈ ፡ ወይኩን ፡ ንጉሥ ፡ ዘት
ይሞ ፡ እምአኃዊከ ፡ ወኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ትሢም ፡ ላዕሌከ ፡ ብእሴ ፡ ነኪረ ፡ ተብሎ
የታዘዘው ፡ በሃይማኖት ፡ ለማይመስለው ፡ በምግባር ፡ ለማይተባበረው ፡ ባዕድ ፡ መገዛት
የማይገባ ፡ መሆኑን ።

፮ኛ ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ አንቀጽ ፡ እንደተጻፈ ፡ እመቦ ፡ ካህን ፡ አው ፡ ዲያቆን
አው ፡ መነኰስ ፡ ዘየሐውር ፡ ኀበ ፡ ሰብአ ፡ አፍአ ፡ ወይከውን ፡ መስተዋድየ ፡ ተብሎ
የታዘዘው ፡ የሀገርንና ፡ የወገንን ፡ ምሥጢር ፡ በሰላይነት ፡ አውጥቶ ፡ ለባዕድ ፡ መንገ
የማይገባ ፡ መሆኑን ፡ እናስታውቃችኋለን ።



ይህን ፡ ምክራችንን ፡ አልቀበልም ፡ ብሎ ፡ የማይመለሰውን ፡ ከነጻነት ፡ ባርነት
ይሻለኛል ፡ ብሎ ለጠላት ፡ ወገን ፡ ሆኖ ፡ ወንድሙን ፡ የሚወጋውን ፡ ሰላይም ፡ ሆኖ ፡
ለጠላት ፡ የሚረዳውን ፡ ሰባኪም ፡ ሆኖ ፡ የሕዝቡን ፡ ልብ ፡ የሚያሰንፈውን ፡ በቤተ ፡
ክህነትም ፡ ወገን ፡ ያለውን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በአባታችን ፡ በቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ መን
በር ፡ የተቀመጡት ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ዮሐንስ ፡ ከመ
ላው ፡ ከግብጽ ፡ ጳጳሳት ፡ ጋራ ፡ ሁነው ፡ አውግዘዋል ። እኔም ፡ ይህን ፡ ምክራችንን ፡
አልቀበልም ፡ ብሎ ፡ የማይመለሰውን ፡ ከነጻነት ፡ ባርነት ፡ ይሻለኛል ፡ ብሎ ፡ ለጠላት
ወገን ፡ ሆኖ ፡ ወንድሙን ፡ የሚወጋውን ፡ ሰላይም ፡ ሆኖ ፡ ለጠላት ፡ የሚረዳውን ፡ ሰባ
ኪም ፡ ሆኖ ፡ የሕዝቡን ፡ ልብ ፡ የሚያሰንፈውን ፡ መምህራንም ፡ መነኰሳትም ፡ ቀሳ
ውስትም ፡ ዲያቆናትም ፡ ቢሆኑ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተለዩ ፡ ከሥልጣናቸውም ፡
የተሻሩ ፡ ናቸውና ፡ የሊቀ ፡ ጳጳሳቱን ፡ ውግዘት ፡ መሠረት ፡ አድርጌ ፡ በሥልጣነ ፡ አብ
ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የተለዩ ፡ እንዲሆኑ ፡ ገዝቻለሁ ።

ከሕዝቡም ፡ ወገን ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ የሚሠራ ፡ ቢሞትም ፡
በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዳይቀበር ፡ እንዳይፈታም ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ አውግዘን ፡
እንደነበረው ፡ አውግዣለሁ ።

የካቲት ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፱ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ።

ተጻፈ ፡ በቅድስት ፡ ሀገር ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በትልቁ ፡ ከተማ ።

ፊርማ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ።

www.ethiopianorthodox.org

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ፲፱፻፷፩ ፡ ዓመተ ምሕረት ፡ ጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ርስትና ፡ ጕልት ፡ የሚ ገኘው ፡ የአሥራት ፡ ገንዘብ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እየተከፈለ ፡ ለመንፈሳዊ ትምህርትና ፡ ለመንፈሳዊ ፡ ሥራ ፡ ማስፋፊያ ፡ እንዲሆን ፡ በፈቀዱ ፡ ጊዜ ብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ (አሁን ፡ ብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት አቡነ ፡ ባስልዮስ ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ፡ ም፡ ጥቅምት ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ በግርማዊነታቸው ፡ ፊት ፡ የተናገሩት

## ቃለ ፡ በረከት ።

## ግርማዊ ፡ ሆይ ።

መጀመሪያ ፤ ከፀዋትወ ፡ መከራ ፡ ሁሉ ፤ በጽኑዕ ፡ ክንዱ ፡ ጠብቆ ከዚህ ፡ ያደረሰዎ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰግናለሁ ።

ሰው ሲሞት ፤ ሥራውና ፡ ስሙ ፡ እንዳይሞት ፡ ያውቃሉና ፡ ይህ ፡ ዛሬ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሰጡት ፡ የርስቷ ፡ ሁሉ ፡ አሥራት ፡ ከጕልላቷ ፡ በላይ ካለ ፡ ከመስቀሉ ፡ ጋራ ፡ ተቀርጾ ፡ የታሪክዎ ፡ ምልክት ፡ ሊሆን ፡ ለዘለዓለም ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ ነው ።

ይህንንም ፡ ነቀዝ ፡ የማይበላው ፤ ሌባ ፡ የማይሰርቀው ፤ በሰማይ ፡ ያደለ ቡትን ፡ ዐሥራት ፡ ተቀባይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነውና ፡ ስምዎን ፡ በማይደመሰስ በመጽሐፈ ፡ ሕይወት ፡ ይጻፈው ።

አባትዎ ፤ ይኩኖ ፡ አምላክ ፤ ለአባቴ ፡ ለተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ከሰጧቸው ሲሶ ፡ መንግሥት ፡ በልቡና ፡ ሚዛን ፡ ሲመዘን ፡ በዝቶና ፡ ተርፎ ፡ ይታያል ።

አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የትሩፋት ፡ አበጋዝ ፡ ናቸውና ፡ በትሩፋ ታቸው ፡ በጸሎታቸው ፡ ይረዱኛል ፡ ብለው ፡ ነው ፡

እኔ ፡ ግን ፤ ደካማ ፡ ምንም ፡ ልረዳዎ ፡ የማልችል ፡ መሆኔን ፡ ሲያውቁ ፤ የአባትዎን ፡ የተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ለማክበርና ፡ ለመጠበቅ ሲሉ ፤ ምንም ፡ ከልብዎ ፡ የሚገኝ ፡ አሳብዎ ቢሆን ፡ አመልካችነቴንና ፡ አስታ ዋሽነቴን ፡ ቸል ፡ ሳይሉ ፡ በመፈጸምዎ ፡ እግዚአብሔር ፡ አሳብዎን ፡ ሁሉ ፡ ይፈጽምልዎ ።

ይህ ፡ ስጦታዎም ፡ ምንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ውለታ ፡ ጋራ ፡ የማይነጻጸ ርና ፡ የማይመዛዘን ፡ ቢሆን ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ «ሀቡ ፡ ዘእግዚአብ ሔር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ «ያለውንና ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ» ፡ ወለዘሂ ፡ ዐሥራት ፡ ዐሥሩ ፡ ያለውን ፡ ተመልክተው ፤ ያንጊዜም ፡ በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ስንዘምት ፡ «አምላከ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ያንተ ፡ ያልሆነ ፡ የለኝም» ፡ ብለው ፡ የተናገሩትን ፡ ቃል ፡ ከልቡናዎ ፡ ሳያጠፉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ውለታ ፡ መላሽ ፡ በመሆንዎ ፡ አመሰ ግንዎታለሁ ።



ይህም ፡ ልማድ ፡ ነው ። በኦሪት ፡ የሌዊ ፡ ልጆች ፡ ልዩ ፡ የሆነች ፡ የመቅ ደስን ፡ ሥራ ፡ ስለሚሠሩ ፤ እስራኤል ፡ የሚያወጡትን ፡ ዐሥራት ፡ እነሆ ፡ ሰጠኋቸው ፡ ብሏል ። ዘኍ ፡ ፲፰ ፡ ፳፩ ።

አባትዎ ፡ አብርሃምም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አገልጋይ ፡ ለካህኑ ፡ ለመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ዐሥራቱን ፡ ሰጥቶ ፡ እንደተመረቀ ፡ ጳውሎስ ፡ ተናግሯል ፡ ዕብ ም፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፩–፰ ።

የአባቶች ፡ አለቃ ፡ አብርሃም ፡ ከሚሻል ፡ ገንዘቡ ፡ ሁሉ ፡ ከ፲ ፡ ፩ድ ፡ የሰጠውን ፡ ክብሩን ፡ ታያላችሁን ? የሌዊ ፡ ልጆች ፡ ከ፲ ፡ ፩ድ ፡ ይቀበሉ ፡ ዘንድ ፡ የታዘዘ ፡ ሥርዓት ፡ ነበራቸው ። እሱም ፡ ተስፋ ፡ የሰጠው ፡ አብርሃምን ፡ መረ ቀው ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚሞት ፡ ሰው ፡ ከ፲ ፡ ፩ድ ፡ ይቀበላል ። በወዲያ ፡ ዓለም ፡ ግን ፡ ሕያው ፡ እንደሆነ ፡ መጽሐፍ ፡ የመሰከረለት ፡ እሱ ፡ ይቀበላል ፡ ብሏል ። ዕብ ፡ ፯ ፡ ፬ ፡ ፰ ።

እስመ ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ እሙነ ፡ ተፈጸመ ፡ ፍሥሓሃ ፡ ለቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጉባኤ ፡ እንተ ፡ ሐዋርያት ፡ ብሎ ፡ ሊቁ ፡ አርካዎስ ፡ የተናገረው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተድላ ፡ ደስታዋ ፡ ዛሬ ፡ ተፈጸመ ።

## ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ምድራዊ ፡ መንግሥትን ፡ እንደሰጠዎ ፤ የማያልፍ ፡ ሰማያዊ ፡ መንግሥትን ፡ ያውርስዎ ። እግዚአብሔር ፡ ላባትዎ ፡ ለዳዊት ፡ ከባሕርይህ ፡ የተወለደ ፡ ልጅህን ፡ በዙፋንህ ፡ እንዳኖርልህ ፡ ብሎ ፡ የማለውን ፡ መሐላ ፡ አስቦ ፡ መንግሥትዎን ፡ ከዘርዎ ፡ አያውጣው ። ልጅህን ፡ ለዘለዓለሙ ፡ መንግሥት ፡ አዘጋጅልሃለሁ ። መንበረ ፡ መንግሥትህንም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ዘመን ፡ አጸናልሃለሁ ፤ በሱ ፡ የሚነሣ ፡ ጠላትም ፡ አይጠቀምም ። የዓመፅ ፡ ልጅም ፡ ዳግመኛ ፡ መከራ ፡ አያመጣበትም ። ጠላቱን ፡ ከፊቱ ፡ አጠፋለሁ ። ጠላቶቹን ፡ አጕሳቍላለሁ ። ይቅርታዬንና ፡ ቸርነ ቴን ፡ ለሱ ፡ አደርግለታለሁ ። ልጁን ፡ ለዘለዓለም ፡ እንዲገዛ ፡ አደርጋለሁ ፡ ተብሎ ። ለአባትዎ ፡ ለዳዊት ፡ የተነገረው ፡ እስከ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ድረስ ፡ ሲያያዝ ፡ እንደ መጣ ፤ ይህ ፡ መንግሥት ፡ ከዘርዎ ፡ ሳይወጣ ፡ ለዘለዓለም ፡ ከልጆችዎ ፡ ጋራ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ተዋሕዶ ፡ ይኑር ።

እኛ ፡ የኢትዮጵያ ፤ ኢትዮጵያ ፡ የኛ ፡ ሁና ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

ንጉሠ ፡ ነገሥታችንን ፡ ሰላማዊ ፡ ዘመን ፡ ሰጥቶ ፤ ይጠብቅልን ።

ጥቅምት ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ፡ ም፡

www.ethiopianorthodox.org

## የኢትዮጵያና ፡ የእስክንድርያ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሰላማዊ ፡ ግንኙነት

ታድሶ ፡ እንዲኖር ፡ በኅዳር ፡ ፱ ቀን ፡ ፲፱፻፴፰፡ ዓ፡ም፡ ብፁዕ ፡ ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ፡ ለጉባኤው ፡ ሥራ ፡ መክፈቻ ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ።

### የአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መልእክተኞች ፡ ሊቃውንትና ፡ መምህራን ።

ዛሬ ፡ የተሰበሰብንበት ፡ ጉዳይ ፤ ያገራችን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ፡ መዓርግ ፤ በዓለም ፡ እንዳሉት ፡ እንደ ፡ ክርስቲያን ፡ አገሮች ፡ የሚ ገባትን ፡ ክብር ፡ አግኝታ ፡ የምትኖርበትን ፡ ቍርጠኛ ፡ አሳብ ፡ ለመወሰንና ለመመሥረት ፡ ነው ።

ከቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ አብርሀ ፡ ወአጽብሐ ፡ ዘመን ድረስ ፡ በሥርዓተ ፡ ኦሪት ፡ ስትኖር ፡ የነበረችው ፡ የኛ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የክ ርስትናን ፡ ሥርዓት ፡ ለመቀበል ፡ የበቃችው ፡ ነገሥታትዋ ፡ ፈቅደው ፡ በላኩት በፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ መልእክተኛነት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ከግብጽ ወይም ፡ ከሌላ ፡ ሥፍራ ፡ ወደ ፡ አክሱም ፡ መጥቶ ፡ የሰበከ ፡ እንዳልነበረ ፡ ታሪኩ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ነውና ፡ ዝርዝር ፡ ሐተታ ፡ የማያስፈልገው ፡ አይደ ለም ። ስለዚህም ፤ ኢትዮጵያ ፡ ክርስቲያንነትን ፡ በፈቃድዋና ፡ በትጋቷ ፤ ብቻ ከማግኘቷ ፡ በቀር ፡ እኔ ፡ መሥራች ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ የሚመካበት ፡ የለም ።

ፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ላገራችን ፡ መጀመሪያ ፡ ጳጳስ ፡ ተብሎ ፡ በነገሥታቱ ጥያቄ ፡ ተሾሞ ፡ ከመጣ ፡ ወዲህ ፤ ጳጳስ ፡ ሲሞት ፡ ከእስክንድርያ ፡ ሊቀ ጳጳስ ፡ አሹሞ ፡ ማስመጣት ፡ ልማድ ፡ ሆነ ። ይህ ፡ አኳኋን ፡ አዲስ ፡ ተክል በሚያሰኝበት ፡ በመጀመሪያው ፡ ሰዓት ፡ ምናልባት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ኖሮ ይሆናል ። ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በትምህርትም ፡ በስብከትም ፡ ራሷን ፡ ከቻለች በኋላ ፡ ግን ፤ አስተዳዳሪዋን ፡ ከራስዋ ፡ ለማግኘት ፡ ፈላጊ ፡ ሆነች ። በታሪክ እንደምናውቀው ፡ የመጀመሪያው ፡ ክርክር ፡ በ፲፩ኛው ፡ መቶ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን በነገሠው ፡ በአጼ ፡ ይምርሐ ፡ ዘመን ፡ ተደረገ ።

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ራስዋን ፡ ለመቻል ፡ መንቃትዋ ፡ ከታወቀ በኋላ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሰዎች ፡ ከዐዋቆቻቸው ፡ ውስጥ ፡ አለቃ ፡ የሚሆናቸውን አባት ፡ አይሹሙ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ በቅዱሳን ፡ አበው ፡ በሠለስቱ ፡ ምዕት ፡ ስም አመካኝተውና ፡ በኒቅያ ፡ ጉባኤ ፡ እንደተደረገ፡ አስመስለው ፡ የተገዥነትን ፡ ሥር ዓት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ብቻ ፡ ጻፉበት ። ባለፈው ፡ ዘመን ፡ የግብጽ ፡ መልእክተኞች እንዳስታወቁን ፡ በዐረብኛው ፡ የተጻፈውማ ፡ ዐዋቆቻቸውን ፡ አይሹሙ። እነሱም ራሳቸው ፡ አይሾሙ ፡ የሚል ፡ ስለሆነ ፤ በግዕዙ መጽሐፋችን ፡ የተጻፈውን እንኳ ፡ አሁን ፡ አፍልሰውታል ።



በኢትዮጵያውያን ፡ ላይ ፡ የተጻፈብን ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ ከአባቶቻችን ፡ ከሠለ ስቱ ፡ ምዕት ፡ ሳይሆን ፤ ከባለ ፡ ጥቅሞች ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ የተፈጠረና ፡ የተጨ መረ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀው ፡ በኒቅያ ፡ ጉባኤ ፡ የነበሩትና ፡ መጽሐፉን ፡ የያዙት ሌሎቹ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ለምሳሌ ፡ ቍስጥንጥንያ ፤ አንጾኪያ ፤ ሮምያ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በጭራሽ ፡ እንደማያውቁትና ፡ በመጽሐፋቸው ፡ አለመኖሩ ፡ ስለታ ወቀ ፡ ነው ።

እንዲያውም ፡ ቢሆን ፤ ነገሩ ፡ ቢመረመር ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈው ፡ ቃል ፡ የሚያስረዳ ነው ። የኒቅያ ፡ ጉባኤ ፡ የተደረገው ፡ በ፫፻፳፭ ፡ ዓ፡ ም፡ ነው ።

ኢትዮጵያ ፡ ሥርዓተ ፡ ክርስትናን ፡ የተቀበለችው ፡ ግን ፡ ከኒቅያ ፡ ጉባኤ ፡ በኋላ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ቆይታ ፤ (ሌሎች ፡ በለታሪኮች ፡ እንደሚሉትም ፡ ቢሆን ፡ ፲፭ ፡ ዓመት ፡ ቆይታ ፡) ስለሆነ ፡ ከማመንዋና ፡ ሥርዓተ ፡ ክርስትናን ፡ ከመቀበሏ ፡ በፊት ፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ ታወጀባት ፡ ሊባል ፡ የማይቻል ፡ ነው ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ይህ ፡ የጵጵስና ፡ ሹመት ፡ በየጊዜው ፡ ክርክር ፡ ሲደረግበትና ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ፍጻሜ ፡ ሲያገኝ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ሲሰናከል ፡ የኖረ ፡ ነው ።

በ፲፫ኛው ፡ መቶ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሐዋርያ ፡ የነበሩት ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ሊቃውንት ፡ ጉባኤ ፡ (ሲኖዶስ)፡ ተመርጠው ፡ ጳጳስ ፡ ሆነዋል ። ከሳቸው ፡ በኋላም ፤ በመንበራቸው ፡ የተተኩት ፡ ሦስተኛው ፡ ዕጨጌ ፡ አቡነ ፡ ፊልጶስ ፡ ጳጳስ ፤ ሆነው ፡ ነበር ። በአጼ ፡ እስክንድርም ፡ ዘመን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ የሚከለክሉት ፡ በምን ፡ መር ገም ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ታላቅ ፡ ክርክር ፡ ተነሥቶ ፡ ነበር ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በየጊ ዜውና ፡ በየዘመኑ ፡ የተደረገውን ፡ ማሰብ ፡ የተገባ ፡ ነገር ፡ ነው ።

በልማድ ፤ ካንድ ፡ አገር ፡ ጳጳስ ፡ ማስመጣት ፡ በኛ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በሌ ሎችም ፡ አገሮች ፡ ላይ ፡ ነበረ ። ነገር ፡ ግን ፡ ልማዱ ፡ በልማድ ፡ ታደሰ። እነሆ ፡ ሁሉም ፡ ነጻነቱን ፡ አግኝቷል ። ለምሳሌ ፡ የአንጾኪያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የቆጵሮ ስንና ፡ የጆርጂያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ታዝዝ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ሁለቱም ፡ ራሳቸውን ፡ ችለዋል ። እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ የቍስጥንጥንያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የአ ቴናንና ፡ የመስኮብን ፤ የሴርብያንና ፡ የሩማኒያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ታዝዝ ፡ ነበር ።

አሁን ፡ ግን ፡ ሁሉም ፡ ራሳቸውን ፡ ችለው ፡ በክርስቶስ ፡ እምነት ፡ ጐል ምሰዋል ።

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ የጠየቀችው፡ ተወላጅዋ ፡ መዓርጉ ፡ ሢመት ፡ እንዲያገኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ካንድነት ፡ ለመለየት ፡ ስላልሆነ ፤ የነገሩ ፡ አኳኋን ፡ በሌ ሎች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ከተደረገው ፡ ጋራ ፡ ሲነጻጸር ፡ በጣም ፡ የለ ሰለሰ ፡ ነው ።

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የዛሬ ፡ ፲፯ ፡ ዓመት ፡ ስለ ፡ መብትዋ ፡ የጠ ነከረ ፡ ጥያቄ ፡ አቅርባ ፡ ነበር ። ከብዙ ፡ ንግግር ፡ በኋላም ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ትጋት ፡ አምስት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ጳጳሳት ፡ እንዲሾሙ ፡ ሆኖ ፡ ተቈረጠ ። እነር

www.ethiopianorthodox.org

ሱም ፡ በፓትርያርኩ ፡ በአቡነ ፤ ዮሐንስ ፡ ተባርከው ፡ በግንቦት ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፩
ዓ፡ ም፡ ከይሮ ፡ ላይ ፡ የተሾሙት ፡ አራቱ ፡ ጳጳሳትና ፡ በጥር ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፪ ፡ ዓ፡ ም
አዲስ ፡ አበባ ፡ የተሾሙት ፡ አምስተኛው ፡ ጳጳስ ፡ ናቸው ። እነዚህንም ፡ አምስቱን
ጳጳሳት ፡ መርጦ ፡ ያቀረባቸው ፡ በ፲፱፻፲፱ ፡ ዓ፡ ም፡ በመስከረም ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ የተሰ
ሠረተውና ፡ አሁንም ፡ ያለው ፡ የኢ.ትዮጵያ ፡ መንፈሳዊ ፡ ጉባኤ ፡ ነው ። በጠላት
ወረራ ፡ ዘመን ፡ በኢ.ትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አስቸጋሪ ፡ የሆኑ ፡ ነገሮች ፡ ደረ
ሱባት ። ፩ኛ ፡ ጳጳሳቱ ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስና ፡ አቡነ ፡ ሚካኤል ፡ ተገደሉ ። አብያተ
ክርስቲያናቱ ፡ ተቃጠሉ ፡ መምህራኑ ፡ ተደበደቡ ። እንደነ ፡ ደብረ ፡ ሊ.ባኖስ ፡ ያሉት
ታላላቆቹ ፡ ገዳማት ፡ ተመዘበሩ ፡ መነኰሳቱም ፡ ተገደሉ ።

፪ኛ ፡ ጳጳሱ ፡ አቡነ ፡ ቄርሎስ ፡ ስለጕዳያቸው ፡ ባደረጉት ፡ ጥያቄ ፡ መሠረት
ወደ ፡ ሮማ ፡ ሔደው ፡ ነበርና ፡ ከዚያ ፡ ሲመለሱ ፡ በሀገራቸው ፡ ቀሩ ።

፫ኛ ፡ ለምክሩም ፡ ሆነ ፡ ለመረዳዳቱ ፡ ወደ ፡ አባቶቻችን ፡ ወደ ፡ ግብጻውያን
የሚያደርሰው ፡ መገናኛ ፡ ሁሉ ፡ በጠላት ፡ የጦር ፡ ኃይል ፡ እጅ ፡ የተጠበቀ ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የኢ.ትዮጵያ ፡ መንፈሳዊ ፡ ጉባኤ ፡ ሊ.ቃውንቱንና ፡ መምህራ
ኑን ፡ ምእመናኑን ፡ ጭምርም ፡ ሰብስቦ ፡ ጉባኤ ፡ (ሲኖዶስ) ፡ አቁሞ ፡ የጐንደርና
የጐጃም ፡ ጳጳስ ፡ የነበሩትን ፡ አቡነ ፡ አብርሃምን ፡ ለሊ.ቀ ፡ ጵጵስና ፡ መረጣቸውና
የኢ.ትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ የምትተዳደር ፡ ሆነች ።

ይኸውም ፡ ነገር ፡ ግብጻውያን ፡ ደስ ፡ ያልተሰኙበትና ፡ ችግራችንን ፡ ሳይመለ
ከቱ ፡ ግዝት ፡ እስከ ፡ ማድረግ ፡ የደረሱበት ፡ ነው ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የኢ.ትዮጵያን ፡ ነጻነት ፡ ይዘው ፡ ከተመለሱ
በኋላ ፤ የመጀመሪያዎቹ ፡ ዐሥር ፡ ወሮች ፡ ፈርሶ ፡ የነበረውን ፡ መንግሥት ፡ እን
ደገና ፡ በማቋቋም ፡ ያለፉ ፡ ናቸው ። በ፲፱፻፴፬ ፡ ዓ፡ ም፡ በመጋቢት ፡ መጨረሻ
ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ ጕዳይ ፡ በግብጽና ፡ በኢ.ትዮጵያ ፡ መከከል ፡ ንግግር
ተጀመረ ። ወዲያው ፡ የግብጽ ፡ ፓትርያርክ ፡ መልክተኞች ፡ ከጳጳሱ ፡ ከአቡነ
ቄርሎስና ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ሹማምንት ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መጥ
ተው ፡ በሰኔ ወር ፡ ንግግር ፡ ተደረገ ።

የኢ.ትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያቀረበችው ፡ አሳብ ፡ ለግብጽ ፡ መልክተ
ኞች ፡ በ፲፬ ፡ ሰኔ ፡ ተሰጥቷቸው ፡ ሲሔዱ ፤ ገና ፡ ከመድረሳቸው ፡ በፊት ፡ ፓት
ርያርኩ ፡ አቡነ ፡ ዮሐንስ ፡ በድንገት ፡ ማረፋቸው ፡ በ፲፰ ፡ ሰኔ ፡ ተሰማ ። በመ
ንበራቸውም ፡ የሚተኩት ፡ አዲሱ ፡ ፓትርያርክ ፡ እስኪመረጡና ፡ እስኪሾሙ ፡
ድረስ ፡ ፲፱ ፡ ወሮች ፡ ያህል ፡ ስለፈጀ ፡ ነገሩ ፡ ፍጻሜ ፡ ሳያገኝ ፡ ዘገየ ።

አቡነ ፡ መቃርዮስ ፡ በ፲፱፻፴፮ ፡ ዓ፡ ም፡ በየካቲት ፡ መጀመሪያ ፡ ከተሾሙ ፡
በኋላ ፤ ንግግሩን ፡ ለመቀጠል ፡ የግብጽ ፡ መልክተኞች ፡ በግንቦት ፡ ወር ፡ ወደ ፡
አዲስ ፡ አበባ ፡ መጡ ። እነዚህ ፡ መልክተኞች ፡ ስለፊተኛው ፡ ጥያቄ ፡ መል



ሱን ፡ ይዘው ፡ ይሆናል ፡ ተብሎ ፡ ሲጠበቁ ፡ አንዳች ፡ መልስ ፡ አለመያዛቸ
ውንና ፡ ለንግግር ፡ የመጡ ፡ መሆናቸውን ፡ አስረዱ። ከብዙ ፡ ንግግር ፡ በኋላም፡
የኢ.ትዮጵያ ፡ ሊ.ቃውንት ፡ መክረው ፡ ያቀረቡት ፡ አሳብ ፡ በ፳፩ ፡ ሰኔ ፡ ተሰጥቷ
ቸው ፡ ተመለሱ ።

የኢ.ትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያቀረበችው ፡ ጥያቄ ፡ ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ከዚህ ፡
በታች ፡ በተመለከቱት ፡ በስድስት ፡ ክፍሎች ፡ የተገለጸ ፡ ነው ።

፩ኛ ፡ ከኢ.ትዮጵያ ፡ ተወላጆች ፡ ውስጥ ፡ በቤተ ፡ ክህነት ፡ ክፍል ፡ አድገው ፡
በሃይማኖት ፡ ጸንተው ፡ ከሚኖሩት ፡ ከመንፈሳውያን ፡ አባቶች ፡ ለሊ.ቀ ፡ ጳጳስነት ፡
የሚገባው ፡ ሰው ፡ ተመርጦ ፡ በእስክንድርያው ፡ አባታችን ፡ ተባርኮና ፡ ተቀብቶ ፡
እንዲሾምላት ።

፪ኛ ፡ የእስክንድርያው ፡ ሲኖዶስ ፡ በሚመርጥበት ፡ መሠረት ፡ የኢ.ትዮጵያም ፡
ሲኖዶስ ፡ ለጵጵስናና ፡ ለኤጲስ ፡ ቆጶስነት ፡ የሚገቡትን ፡ መንፈሳውያን ፡ አባቶች ፡
እንዲመርጥና ፡ በእስክንድርያ ፡ አባታችን ፡ ተቀብቶ ፡ የመጣው ፡ ሊ.ቀ ፡ ጳጳስ ፡
ባርኮ ፡ እንዲሾማቸው ።

፫ኛ ፡ በማርቆስ ፡ መንበር ፡ ላይ ፡ የሚቀመጠው ፡ አባታችን ፡ በሚመረጥ
በት ፡ ጊዜ ፤ የቅዱስ ፡ ሲኖዶስ ፡ በር ፡ ለኢ.ትዮጵያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ክፍት ፡
እንዲሆንና ፡ መልክተኞቿ ፡ በምርጫው ፡ ውስጥ ፡ እንዲገኙ ።

፬ኛ ፡ የኢ.ትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘወትር ፡ በእስክንድርያው ፡ ቅዱስ ፡
ሲኖዶስ ፡ ውስጥ ፡ መንበር ፡ እንዲኖራትና ፡ ሲኖዶሱ ፡ በተሰበሰበ ፡ ቍጥር ፡ መል
እክተኞቿ ፡ በሚገባቸው ፡ ደረጃ ፡ ተቀምጠው ፡ እንዲገኙ ።

፭ኛ ፡ ኢ.ትዮጵያ ፡ በውድ ፡ ሳይሆን ፡ በግድ ፡ በጦር ፡ ኃይል ፡ ከእስክን
ድርያ ፡ ጋራ ፡ እንዳትገናኝ ፡ ተከልክላ ፡ በተቋረጠችበት ፡ ጊዜ ፡ በሃይማኖቷ ፡
ጸንታ ፡ ወደ ፡ ሰላም ፡ ዘመን ፡ እስክትደርስ ፡ መርጣ ፡ የሾመቻቸው ፡ ጳጳሳት ፡
ከግዝቱ ፡ እንዲፈቱላት ።

፮ኛ ፡ በኢ.ትዮጵያና ፡ በእስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መካከል ፡ ያለው ፡
መንፈሳዊ ፡ ግንኙነት ፡ አሁን ፡ ካለው ፡ የበለጠ ፡ እንዲሆን ፤ የእናትነትና ፡ የል
ጅነትም ፡ መሠረት ፡ የጠነከረ ፡ ሆኖ ፡ እንዲኖር ፤ የገዳም ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በአ
ዲስ ፡ አበባ ፡ እንዲከፈት ፤ ስለ ፡ ዚሁም ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አቋቋምና ፡ አካሔድ ፡
ቅዱስ ፡ አባታችን ፡ አቡነ ፡ መቃርዮስ ፡ ቡራኬያቸውን ፡ እንዲሰጡን ፤ በዚህ ፡
ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተመርቀው ፡ ለጵጵስና ፡ ወይም ፡ ለቁምስና ፡ የታጩት ፡ መምህሮች ፡
ወደምስር ፡ ገዳማት ፡ ውስጥ ፡ እየሔዱ ፡ ከወንድሞቻቸው ፡ ጋራ ፡ በመንፈስ ፡ ተባብ
ረው ፡ እንዲመለሱ ፤ እንደዚሁም ፡ ከምስር ፡ የሚመጡት ፡ ወንድሞቻችን ፡ ወደኢ.ትዮ
ጵያ ፡ ገዳም ፡ ውስጥ ፡ ሲመጡ ፤ በመንፈሳቸው ፡ ሁሉ ፡ የተባበሩ ፡ ወንድሞች ፡
አግኝተው ፡ እንዲመለሱ ፡ የሚል ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

የጥያቄውም ፡ መልስ ፡ ከአምስት ፡ ወር ፡ የሚበልጥ ፡ ስለዘገየ ፣ የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ፡ ጉባኤ ፡ በኅዳር ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በደብዳቤ ፡ ያስ[...] ውስ ፡ ዘንድ ፡ ግድ ፡ ሆነበት ። ከብዙ ፡ ጉትጎታም ፡ በኋላ ፣ ስለ ፡ መልሱ ፡ በየ[...] ቲት ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የጻፉልን ፡ ደብዳቤ ፡ ለጊዜ ፡ ማርዘሚያ ያህል ፡ እንጂ ፡ ለሌላ ፡ የማይጠቅም ፡ መሆኑ ፡ ስለ ፡ ታወቀ ፣ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ክርስቲያን ፡ ጥያቄ ፡ ቀጥተኛው ፡ መልሱ ፡ በቶሎ ፡ እንዲሰጣት ፡ እንደገና ፡ ሌላ የልመና ፡ ደብዳቤ ፡ በመጋቢት ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተጻፈላቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፣ ከግብጻውያን ፡ ጉባኤ ፡ በሰኔ ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፮ ፡ ዓ ፡ ም[...] ተጽፎ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተላከላት ፡ መልስ ፡ ከማሳዘኑ ፡ በቀ[...] የስምምነቱን ፡ መንፈስ ፡ ለማጽናት ፡ የማይደግፍ ፡ ሆነ ።

የኢትዮጵያ ፡ ተወላጅ ፡ ባገሩ ፡ ላይ ፡ የሊ.ቀ ፡ ጳጳስነት ፡ መዓርግ ፡ እንዲ[...] ገኝ ፡ ተብሎ ፡ በ፩ኛና ፡ በ፪ኛ ተራ ፡ ቍጥር ፡ የተጻፈውንና ፡ የተጠየቀውን[...] ዋናውን ፡ ጉዳይ ፡ በፍጹም ፡ እንደማይቀበሉት ፡ እያረጋገጡ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሊሾም[...] የሚገባው ፡ ሊ.ቀ ፡ ጳጳስ ፡ ግብጻዊ ፡ ነው ፡ አሉ ።

በሌላው ፡ በታናናሹ ፡ ክፍል ፡ ግን ፣ በጉባኤ ፡ እንዲገኝ ፡ በተባለውና ፡ ስለ[...] ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ አቋቋም ፡ ለተመለከተው ፣ ፈቃድ ፡ እንዳላቸው ፡ አስታወቁ[...]

ከግብጽ ፡ የመጣው ፡ ይህ ፡ መልስ ፡ በሐምሌ ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ወደኢትዮጵያ ፡ መ[...] ፈሳዊ ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ ቀርቦ ፡ ከተነበበ ፡ በኋላ ፣ ግብጻውያን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ግ[...] ጻዊ ፡ ሊ.ቀ ፡ ጳጳስ ፡ እንጂ ፣ ኢትዮጵያዊ ፡ ሊሾም ፡ እንደማይችል ፣ ከወሰኑ[...] ይህ ፡ አስተያየት ፡ ዘራችንን ፡ የሚያሳንስ ፣ የነጻነት ፡ ክብራችንንም ፡ የሚቀንስ[...] ነውና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ራሷን ፡ ችላ ፡ መኖር ፡ ይገባታል ፡ ሲል ፡ የኢትዮጵያ ፡ መ[...] ፈሳዊ ፡ ጉባኤ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ አስታወቀ ።

የንጉሠ ፡ ነገሥቱም ፡ መንግሥት ፡ የነገሩን ፡ አኳኋን ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ[...] ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ እንደቈየው ፡ ሥርዓታችን ፡ ቤተ ፡ ክህነትና ፡ ቤተ ፡ መን[...] ሥት ፡ የተባበሩ ፡ ስለሆኑ ፣ ይልቁንም ፡ የቤተ ፡ ክህነታችን ፡ ጠባቂዋና ፡ ደጋፊዋ[...] ቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ስለሆነ ፣ መልእክተኞቹን ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ለመላክና[...] የመጨረሻ ፡ ቃላቸውን ፡ ለመቀበል ፡ አስቦበታል ።

በመልእክተኞቹም ፡ እጅ ፡ የሚሔደው ፡ ቍርጠኛው ፡ ቃል ፡ በኢትዮጵያ[...] የመላው ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መልእክተኞች ፡ የሆናችሁት ፡ እናንተ ፡ ሊ.ቃው[...] ቱና ፡ መምህራኑ ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋራ ፡ ተባብራችሁ ፡ በምትወስኑት ፡ መ[...] ረት ፡ እንዲሆን ፡ ስላስፈለገ ፡ እነሆ ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ተጠርታችኋል ።

ከያውራጃው ፡ በሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ ድምፅ ፡ በሚገባ ፡ ተመርጣችሁ ፡ የመ[...] ችሁ ፡ ሊ.ቃውንትና ፡ በተለይም ፡ ለጉባኤው ፡ ተካፋይነት ፡ የተጠራችሁ ፡ ክቡራን[...] የገዳማት ፡ መምህራን ፡ ሆይ !



ሁሉን ፡ መርምሮ ፡ የሚያውቅ ፡ ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ በእውነተኛው ፡ መንገድ ፡ እንዲመራን ፡ እውነተኛውንም ፡ ምክር ፡ እንዲገልጽልን ፡ እየለመንን ፡ ሥራችንን ፡ እንጀምር ።

የአብ ፡ በረከት ፣ የወልድ ፡ ቸርነት ፣ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አንድነት ፡ በሁላችን ፡ ላይ ፡ አድሮ ፡ ይኑር ።

ኅዳር ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዲስ ፡ አበባ ።

ብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያለውን ፡ ንግግር ፡ ባደረጉ ፡ ጊዜ ፡ ከየጠቅላይ ፡ ግዛቱና ፡ ከያውራጃው ፣ እንዲሁም ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ አድባራት ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ተመርጠው ፡ የተሰበሰቡት ፡ ሊ.ቃውንትና ፡ መምህራን ፡ ቍጥር ፡ ከሦስት ፡ መቶ ፡ የማያንስ ፡ ነበር ።

የጽጽስናው ፡ ሹመት ፡ ጉዳይ ፡ ግን ፣ በግብጽ ፡ ሲኖዶስ ፡ በኩል ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ክርክር ፡ እየገጠመው ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ የሚቈይ ፡ ሆነ ።

የኢትዮጵያ ፡ ሊ.ቃውንትና ፡ መምህራንም ፡ ባምስቱ ፡ የመከራ ፡ ዘመናት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተወላጆች ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስና ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ሚካኤል ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተጋድለው ፡ በጠላት ፡ እጅ ፡ ሲሞቱ ፡ ከግብጽ ፡ የመጡት ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ቄርሎስ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በመከራዋ ፡ ሰዓት ፡ ተለይተዋት ፣ አጋልጠዋት ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ መሔዳቸውን ፡ እያሰቡ ፣ ከዚያ ፡ ወዲህም ፣ ክርክሩን ፡ ስምምነት ፡ እንዲወስነው ፡ ቢታሰብ ፣ የግብጽ ፡ ሲኖዶስ ፡ አሳብ ፡ የስምምነቱን ፡ መንገድ ፡ እየዘጋ ፡ ስላስቸገረ ፣ ዳግመኛ ፡ ግብጻውያንን ፡ አንፈልጋቸውም ፡ በማለት ፡ አሳባቸውን ፡ ቈርጠው ፡ ነበር ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ግን ፣ የኢትዮጵያን ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ በትዕግሥት ፡ መሣሪያነት ፡ ማከናወን ፡ የተለመደ ፡ ተግባራቸው ፡ በመሆኑ ፡ በኀዘንና ፡ በብስጭት ፡ የተሰበረውን ፡ የሊ.ቃውንቱንና ፡ የመምህራኑን ፡ መንፈስ ፡ በትዕግሥታዊ ፡ ቃላቸው ፡ አጽናንተው ፡ ጉዳዩን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ የግብጽን ፡ ሲኖዶስ ፡ በጐበኘበት ፡ በ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እንዲፈጸም ፡ በትዕግሥት ፡ ጠበቁ ።

በ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ ፡ ም ።

ስለ ፡ ኀዘን ፡ ሥርዓት ።

ብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የወሰኑት ፡ መንፈሳዊ ፡ ሥርዓት ።

በአብ ፡ ስም ፡ አምነን ፣ አብን ፡ ወላዲ ፣ በወልድ ፡ ስም ፡ አምነን ፡ ወልድን ፡ ተወላዲ ፣ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ አምነን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ሠራፂ ፡ ብለን ፡ ምንም ፡ በአካል ፡ ሦስት ፡ ብንል ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ ብለን ፡ አምነን ፡ በቀቢጸ ፡ ተስፋ ፡ ኀዘን ፡ ስለሚያዝኑ ፡ ሰዎች ፡ መንፈሳዊ ፡ ተግሣጽ ፡ እንጽፋለን ።

ሰው ፡ በኃጢአቱ ፡ ተፈርዶበት ፣ በግዞት ፡ ከሚኖርበት ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ ተለይቶ ፡ በዕረፍት ፡ ለመኖር ፡ በጣዕም ፡ በመዓዛ ፡ ተከናውና ፡ ወደ ፡ ተፈ

www.ethiopianorthodox.org

ጠረችለት ፡ ቦታ ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ በሔደ ፡ ጊዜ ፤ ተስፋ ፡ ትንሣኤ ፡ እንደሌላቸው
በመቃብር ፡ በስብሰን ፡ እንቀራለን ፡ እንደሚሉ ፡ እንደ ፡ አሕዛብ ፡ ማተባቸውን
ፈትው ፤ ራሳቸውን ፡ ላጭተው ፤ ፊታቸውን ፡ ነጭተው ፤ ደማቸውንና ፡ ዕን
ቸውን ፡ ቀላቅለው ፡ እያወረዱ ፤ ልብሳቸውን ፡ እየቀደዱ ፤ እየተነሡና ፡ እየወደቁ
ደረታቸውን ፡ እየደቁ ፡ በቀቢጸ ፡ ተስፋ ፡ የሚያለቅሱ ፡ ሰዎች ፡ ይህን ፡ ክፉ ፡ ል
ዳቸውን ፡ እንዲተዉ ፤ የሚከተለውን ፡ ቃል ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት አወጣጥተን
ጽፈንላቸዋል ።

፩ኛ] እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ እንደ ፡ መላእክት ፡ ሕያው ፡ ሆኖ ፡ ሕጉን
እየጠበቀ ፡ ስሙን ፡ ሊቀድስ ፤ ክብሩን ፡ ሊወርስ ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ ሊኖር
ፈጠረውና ፡ እስከ ፡ ፯ ፡ ዓመት ፡ ሕጉን ፡ ጠብቆ ፡ በዕረፍት ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ ኖረ

ከ፯ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ግን ፤ ሕጉን ፡ ጥሶ ፡ ትእዛዙን ፡ አፍርሶ ፡ አምላክ
ቱን ፡ ሲሻ ፡ ቢገኝ ፤ ስለ ፡ ተዋረደ ፡ በየጊዜው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ፈተና ፡ እየደረሰበት ፤ በ
ዘን ፡ በልቅሶ ፡ የሚኖር ፡ ሆኗል ። በሞተ ፡ ሥጋ ፡ ላይ ፡ ሞተ ፡ ነፍስ ፤ በርደተ ፡ መ
ብር ፡ ላይ ፡ ርደተ ፡ ገሃነም ፡ ተፈርዶበታል ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ከአዳም ፡ እስከ ፡ ክ
ስቶስ ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ጻድቃ ፡ ሳይኖራቸው ፡ በጨካኙ ፡ ጠላት ፡ በዲያብሎስ
እጅ ፡ ተይዘው ፡ ሞት ፡ ጥላውን ፡ በጣለበት ፡ ጨለማ ፡ ውስጥ ፡ ተግዘው ፡ ሲጨነቁ
ከመኖር ፡ በቀር ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ እንገባለን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ እንወርሳለን ፡ የሚል
ተስፋ ፡ ስላልነበራቸው ፡ ሞትን ፡ እየፈሩ ፡ በጽኑ ፡ ኃዘን ፡ ያዝኑና ፡ ያለቅሱ ፡ ነበረ ።

ዛሬ ፡ ግን ፤ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባውና ፤ ፈጣሪያችን ፡ መድኃኒታችን ፡ ኢየ
ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በመልዕልተ ፡ መስቀል ፡ ተሰቅሎ ፤ ዲያብሎስን ፡ ድል ፡ ነሥቶ
ክብርት ፡ ነፍሱን ፡ ከክቡር ፡ ሥጋው ፡ በገዛ ፡ ሥልጣኑ ፡ ለይቶ ፡ ወደ ፡ መቃብር
ወርዶ ፡ ሙስና ፡ መቃብርን ፡ አጥፍቶ ፤ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ወርዶ ፡ ነፍሳትን ፡ ከቍራኝ
ነት ፡ ለይቶ ፡ ለኛም ፡ ዲያብሎስን ፡ ድል ፡ የምንነሣበትን ፡ ሥልጣን ፡ ከሰጠን ፡ ወዲህ
ሞትን ፡ መፍራታችን ፡ ለዲያብሎስ ፡ መገዛታችን ፡ ቀርቶ ፡ «አይቴኑ ፡ ቀኖትከ ፡ ሞት
ወአይቴኑ ፡ ሙዓትከ» ፡ ሲአል ፡ እያልን ፡ በሞት ፡ የምንዘብት ፡ ሆነናል ።

በሞትም ፡ ጊዜ ፡ በፈቃዳቸው ፡ ለዲያብሎስ ፡ ከሚገዙ ፡ ሰዎች ፡ በቀር
በክርስቶስ ፡ ክርስቲያን ፡ የተባለ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፤ በይባቤ ፡ መላእክት ፡ በመ
ሙረ ፡ ዳዊት ፡ በመዓዛ ፡ ገነት ፡ ነፍሱ ፡ ከሥጋው ፡ ከተለየች ፡ በኋላ ፤ ከቅዱ
ሳን ፡ ነቢያት ፡ ከቅዱሳን ፡ ሐዋርያት ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ መላእክት ፡ ሥላሴን
እያየ ፡ ለመኖር ፡ ጣዕም ፤ መዓዛ ፤ ሥን ፤ ዕረፍት ፡ የተዘጋጀበትን ፡ ጥንተ ፡ ር
ቱን ፡ ወርሶ ፡ በዕረፍት ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ የሚኖር ፡ ሆኗል ፡ እንጂ ፤ በቍ
ራኝነት ፡ መያዝ ፤ በገሃነም ፡ መጋዝ ፡ የለበትም ።

እንዲህ ፡ ከሆነ ፤ መከራ ፡ እንጂ ፡ ሕይወት ፤ ድካም ፡ እንጂ ፡ ዕረፍት
ከሌለባት ፡ ከዚች ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ ተለይተን ፡ ሕይወት ፡ እንጂ ፡ ሕማም
ዕረፍት ፡ እንጂ ፡ ድካም ፡ ወደሌለባት ፡ ወደ ፡ ጥንተ ፡ ርስታችን ፡ ስንሔድ ፤ ይህ ፡ ሁሉ
ተስፋ ፡ እንደሌላቸው ፡ እንደ ፡ አረማውያን ፤ ወይም ፡ ተስፋ ፡ ትንሣኤ ፡ እንደ



ላቸው ፡ እንደ ፡ ሰዱቃውያን ፡ የቀቢጸ ፡ ተስፋ ፡ ኀዘን ፡ ስናዝን ፤ ከልክ
ሌ ፡ ልቅሶ ፡ ስናለቅስ ፡ ብንገኝ ፤ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ተስፋችንን ፡ ከንቱ ፡ ማድ
ረጋችን ፡ ነው ።

በክርስቶስ ፡ መድኃኒትነት ፡ ከላመንም ፤ አለመዳናችን ፡ የተረጋገጠ ፡ ነውና ፤
እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ወገናችን ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፤ የሚገባ ፡ ልቅሶ ፡ እናልቅስ ፤ የሚገባ
ዘን ፡ እንዘን ፡ እንጂ ፤ እንደዚህ ፡ ቀደሙ ፡ የማይገባ ፡ ኀዘን ፡ ስናዝን ፤ የማ
ገባ ፡ ልቅሶ ፡ ስናለቅስ ፡ እንዳንገኝ ፡ መላልሰን ፡ አደራ ፡ እንላችኋለን ።

የሚገባውንና ፡ የማይገባውን ፡ ልቅሶና ፡ ኀዘን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ ስልት ፡
ልታቸውን ፡ ጽፈናል ።

## የሚገባ ፡ ልቅሶ ።

፩ኛ ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ ጌታችን ፡ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ለእኛ ፡ በዕለተ ፡ ዓርብ ፡ የተቀበለውን ፡ መከራ ፡ እያሰቡ ፡ ማልቀስ ፡ ነው ።
ሐንስ ፡ ወልደ ፡ ነጐድጓድ ፡ የዕለተ ፡ ዐርቡን ፡ መከራ ፡ እያሰበ ፡ ፸ዘመን ፡
ያለቅስ ፡ እንደኖረ ። እንዲህም ፡ አድርገን ፡ ብናለቅስ ፡ ራሳችንን ፡ እንጠቅም
ታለን ፡ እንጂ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ የምንጠቅመው ፡ አይደለንም ። እሱስ ፡ ስንኳን
ሬ ፡ በዕለተ ፡ ዐርብም ፡ አይሁድ ፡ መስቀሉን ፡ አሸክመው ፡ ሲወስዱት ፡ ሴቶች ፡
የተከተሉ ፡ ቢያለቅሱለት ፡ «አዋልደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ኢትብክያኒ ፡ ኪያየሰ ፡ አላ ፡
ክያ ፡ ላዕለ ፡ ርእስክን» ፡ ብሏቸዋል ። ሉቃ ። ፳፫ ፡ ፳፰ ። ትርጓሜውም ፡ ለኔ ፡ አታ
ቅሱልኝ ፡ ለራሳችሁ ፡ አልቅሱ ፡ እንጂ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፪ኛ ፡ ሰማዕታት ፡ በክርስቶስ ፡ ስላመኑ ፡ ከዐላውያን ፡ ነገሥታት ፤ ከዐላውያን
መኳንንት ፡ በግፍ ፡ የተቀበሉትን ፡ መከራ ፡ እያሰቡ ፡ ማልቀስ ፡ ይገባል ። «ወለእስጢ
ፋኖስስ ፡ ነሥእዎ ፡ ዕደው ፡ ጻድቃን ፡ ወቀበርዎ ፡ ወለሀውዎ ፡ ዐቢየ ፡ ላሁ» ፡ እንደ
ተባለ ፤ እስጢፋኖስን ፡ አይሁድ ፡ በግፍ ፡ በድንጋይ ፡ ወግረው ፡ በገደሉት ፡ ጊዜ ፡
ደጋግ ፡ ሰዎች ፡ አልቅሰው ፡ ቀብረውታል ።

፫ኛ ፡ የራስን ፡ ኃጢአት ፡ አስቦ ፡ ማልቀስ ፡ ይገባል ፡ እንደ ፡ አዳም ፡ እንደ ፡
ዳዊት ፤ እንደ ፡ ጴጥሮስ ። አዳም ፡ ዕፀ ፡ በለስን ፡ በልቶ ፡ ፈጣሪውን ፡ በበደለ ፡ ጊዜ ፡
ገሙቴ ፡ ተሻርኩ ፤ ከመዓርጌ ፡ ተዋረድኩ ፡ ሰይል ፡ የማይገባ ፡ ሥራ ፡ ሠርቼ ፡ ፈጣ
ሪዬን ፡ አሳዘንኩት ፡ ብሎ ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ አልቅሶ ፡ አምስት ፡ ሺ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡
ዘመን ፡ ሲፈጸም ፡ ክልጅ ፡ ልጅህ ፡ ተወልጄ ፡ አድንሃለሁ ፡ የሚል ፡ ተስፋ ፡ አግኝ
ቷል ፡ (መቅድመ ፡ ወንጌል) ፡ ቀሌምንጦስ ። ።

ዳዊትም ፡ ሚስቱን ፡ ቤርሳቤህን ፡ ቀምቶ ፡ ኦርዮን ፡ በስገደለ ፡ ጊዜ ፡ ነቢዩ ፡
ናታን ፡ ሞተ ፡ ሥጋ ፡ ሞተ ፡ ነፍስ ፡ ተፈርዶብሃል ፡ ቢለው ፡ ማቅ ፡ ምንጣፍ ፡ ለብሶ ፡
ቢያ ፡ ነስንሶ ፤ ፵ ፡ ቀን ፡ አልቅሶ ፡ ሥርየት ፡ አግኝቷል ። ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ።

www.ethiopianorthodox.org

ጴጥሮስም ፡ በዕለተ ፡ ዐርብ ፡ ጌታውን ፡ ከካደ ፡ በኋላ ፤ ዶሮ ፡ ሲጮህ ፡ በሰማ ፡
ኅሙስ ፡ ማታ ፡ የነገረው ፡ ትንቢት ፡ ትዝ ፡ ብሎት ፡ መሪር ፡ ልቅሶ ፡ አልቅ
ሥርየት ፡ አግኝቷል ፡ ማቴ ፡ ፳፮ ፡ ፸፭ ፡ ሉቃ ፡ ፳፪ ፡ ፷፪ ።

፫ኛ ፡ በወገን ፡ ላይ ፡ የሚደርሰውን ፡ መከራ ፤ ወይም ፡ የደረሰውን ፡ ፈተ
አስቦ ፡ ማዘን ፡ ይገባል ። እንዲያውም ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ሳሉ ፡ ለሚጨነ
ወገኖችስ ፡ ተለውጦ ፡ ራስን ፡ ሊሠዉላቸው ፡ ይገባል ።

ስለዚህም ፡ ጕዳይ ፡ ራሳቸውን ፡ ለወገኖቻቸው ፡ ለውጥ ፡ ያደረገ
ሙሴን ፤ ዳዊትን ፤ ቅዱስ ፡ ጳውሎስን ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ሳናነሣቸው ፡ አናልፍ
ሙሴ ፡ ወገኖቹ ፡ እስራኤል ፡ ኃጢአት ፡ ሠርተው ፤ ጣዖት ፡ አምልከው ፡ እግ
ብሔር ፡ ሊያጠፋቸው ፡ ወዶ ፡ ተወኝ ፡ ላጥፋቸው ፤ አንተን ፡ ከዚህ ፡ በሚበ
ሰዎች ፡ እሾምሃለው ፡ ቢለው ፤«እነሱን ፡ ከምታጠፋቸው ፡ እኔን ፡ አጥፋኝ» ፡ ብሏ
ዘፀ ፡ ፴፪ ፡ ፴፪ ።

ዳዊትም ፡ ወገኖቹ ፡ እስራኤል ፡ ሲጨነቁና ፡ ሞት ፡ ሲከባቸው ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፤ እ
እስራኤል ፡ ምን ፡ አደረጉ ? የበደልኩ ፡ እኔ ነኝና ፡ ፍርድህ ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ይሁ
ብሎ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለምኗል ። ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፳፬ ፡ ፲፯ ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ ወገኖቹ ፡ እስራኤል ፡ በእንቢተኛነታቸው ፡ ወንጌልን ፡
ቀበልም ፡ ብለው ፡ ከተስፋ ፡ እንደወጡ ፤ ከፍዳ ፡ እንዳላመለጡ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ «እ
ስለ ፡ ወገኖቼ ፡ ስለ ፡ እስራኤል ፡ ብዬ ፡ ከክርስቶስ ፡ አንድነት ፡ ልለይ ፡ እወዳለሁ
ብሏል ፡ ሮሜ ፡ ፱ ፡ ፫ ፡ የሚገባ ፡ ልቅሶ ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ ሁሉ ፡ ነው ።

ይኸውም ሲሆን ፡ ፊት ፡ መንጨት ፤ ራስ ፡ መላጨት ፤ ማተብን ፡ መፍታ
ደረትን ፡ መድቃት ፡ (መምታት)፡ ልብስን ፡ ማውለቅ ፤ መነሣትና ፡ መውደቅ ፡
ክል ፡ ነው ።

## የማይገባ ፡ ልቅሶ ።

የማይገባ ፡ ልቅሶ ፡ ሰው ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ የለም ፡ ወደ
ማለት ፡ የሚያደርስ ፡ የማይረባና ፡ የማይጠቅም ፡ ልቅሶ፡ ማልቀስ፡ እንዳይገባ ፡ በመ
ሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ተጽፎ ፡ እናገኘዋለን ።

፩ኛ እግዚአብሔር ፡ በኦሪት ፡ ሙሴን ፡ ለሞተ ፡ ሰው ፡ ጠጕራችሁን ፡ አትላጩ
ሥጋችሁን ፡ አትንጩ ፡ ብሎ ፡ አዟታል ። ዘሌዋ ፡ ፲፱ ፡ ፳፰ ።

፪ኛ ዳዊት ፡ ልጅህ ፡ ታመመ ፡ ቢሉት ፡ ከእኽል ፤ ከውኃ ፡ ተከልክሎ ፡ በመሬት
እየተኛ ፡ አዘነ ፡ አለቀሰ ። ቤተ ፡ ሰቦቹም ፡ ከወደቅህበት ፡ ተነሥና ፡ እኽል ፡ ውኃ
ቅመስ ፡ ቢሉት ፡ አልሰማቸውም ። በ፯ኛው ፡ ቀን ፡ ሕፃኑ ፡ ስለሞተ ፡ ቤተ ፡ ሰቦቹ
ታመመ ፡ ብንለው ፡ እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ ያዘነ ፡ ሞተ ፡ ብንለውማ ፡ ታንቆ ፡ ይሞት
የለምን ፡ ብለው ፡ ሲጠቃቀሱ ፡ አይቶ ፡ ያ ፡ ሕፃን ፡ ሞተን ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው



እምን ፡ ሞተ ፡ አሉት ፤ ከወደቀበት ፡ ተነሥቶ ፡ ልብሱን ፡ አንጽቶ ፡ ወደቤተ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ገብቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ አቅርቦ ፡ ዋለ ። ቤተ ፡ ሰቦቹም ፡ ቀር
በው ፡ ሕፃኑ ፡ ታመመ ፡ ብንልህ ፡ እኽል ፡ ውኃ ፡ ትተህ ፡ በመሬት ፡ ተኝተህ ፡ አዘ
ንህ ፤ ሞተ ፡ ብንልህ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ አደረግህ ። ነገሩ ፡ እንደምንድነው ፡ አሉት ፡
እርሱም ፡ ቢታመምስ ፡ ይድንልኛል ፡ ብዬ ፡ አዘንሁ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ባዝን ፡ ምን ፡
እጠቀማለሁ ፡ ላስነሣው ፡ እችላለሁን?፤ እኔ ፡ ወደርሱ ፡ እሔዳለሁ ፡ እንጂ ፡ እሱ ፡
ወደኔ ፡ ይመጣልን ፡ ብሏቸዋል ፡ ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፪ ፡ ፲፯–፳፬ ።

እንዲህ ፡ ማለቱ ፡ ትንሣኤ ፡ እንዳለ ፡ ሲያስረዳ ፡ ነው ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለው ፡ የሚያዝኑት ፡ ኃዘን ፡ ወደ ፡
ዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ የሚያደርስ ፡ ንስሐ ፡ ነው ፡ ለሞተ ፡ ሰው ፡ ብለው ፡ የሚያለ
ቅሱት ፡ ልቅሶ ፡ ግን ፤ ሞተ ፡ ሥጋን ፤ ሞተ ፡ ነፍስን ፡ ያመጣል ፡ ብሏል ፡ ፪ ፡ ቆሮ ፡
፯ ፡ ፲ ።

ለተሰሎንቄ ፡ ሰዎች ፡ በጻፈውም ፡ ወንድሞቻችን ፡ ስለሞቱት ፡ ሰዎች ፡ ትንሣኤ ፡
ሙታን ፡ የለም ፡ እንደሚሉ ፡ እንደ ፡ አሕዛብ ፡ በቀቢጸ ፡ ተስፋ ፡ ልታዝኑላቸው ፡
እንዳይገባ ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ እንወዳለን ። ክርስቶስ ፡ ሞቶ ፡ እንደ ፡ ተነሣ ፡ ከመን ፡
በክርስቶስ ፡ ያመኑትን ፡ እግዚአብሔር ፡ አስነሥቶ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ እንዲያመጣቸው
እናምናለን ፡ ብሏል ፡ ፩ ፡ ተሰ ፡ ፬ ፡ ፲፫ ።

ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅም ፡ ባራተኛው፡ ተግሣጹ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ለዕብራውያን
በጻፈላቸው ፡ ክታብ ፡ መልአክ ፡ ሞትን ፡ በሞቱ ፡ ድል ፡ ይነሣ ፡ ዘንድ ፡ ባለ ፡ ዘመ
ኑም ፡ ሁሉ ፡ ሞትን ፡ በመፍራት ፡ በመንቀጥቀጥ ፡ ለዲያብሎስ ፡ ይገዙ ፡ የነበሩ
ትን ፡ ሰዎች ፡ ክርስቶስ ፡ ሞትን ፡ ከመፍራት ፡ ለዲያብሎስ ፡ ከመገዛት ፡ ሊያድና
ቸው ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ያለውን ፡ ሲተረጕም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነበር፡ ወንድሞች፡ ሆይ ፡
ሞትን ፡ የምንፈራበትን ፡ ሀብት ፡ ገንዘብ ፡ ያደረገን ፡ አይደለንምና ፡ በሞት ፡ እየተጠ
ቃቀስን ፡ የተሰጠንን ፡ ሀብት ፡ እንዳንዘነጋ ፡ መሆን ፡ ይገባናል ።

ነገር ፡ ግን ፤ ምርር ፡ ብዬ ፡ አለቅሳለሁ ፡ ክርስቶስ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባውና
ቍራኛነትን ፡ አጥፍቶ ፡ ተስፋ ፡ ትንሣኤን ፡ ሰጥቶ ፡ አክብሮን ፡ ነበረ ።

እኛ ፡ ግን ፡ የቀቢጸ ፡ ተስፋ ፡ ኃዘን ፡ እያዘን ፡ ሰውነታችንን፡ እናስነቅፋለን ፡ እና
ዋርዳለን ። የቀቢጸ ፡ ተስፋ ፡ ኃዘን ፡ ማዘን ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ እንዳለ ፡ ለሚያውቅ
ሰው ፡ ሥራው ፡ አይደለምና ። አሕዛብ ፡ የወንድማቸውን ፡ አስከሬን ፡ ጸጥ ፡ ብሎ ፡
ማየት ፡ የማይቻላቸው ፡ እሊህ ፡ በሞት ፡ ሊዘብቱበት ፡ እንደምን ፡ ይቻላቸዋል ፡
እያሉ ፡ የሚዘብቱብን ፡ ስለሆነ ፡ አዝናለሁ ።

ክብር ፡ ይግባውና ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ማልቀስ ፡ ፈንታ ፡ ለሞቱት ፡
ሰዎች ፡ ዳዊት ፡ እንድናስደግምላቸው፤መታሰቢያ፡ እንድናደርግላቸው፡ አዘናልና፡ ክህና
ቱን ፡ ጠርተን ፡ መብራቱን ፡ አብርተን ፤ ብሩህ ፡ ልብስ ፡ ለብሰን ፡ እስመ ፡ አድ

www.ethiopianorthodox.org

ኀንካ ፡ ለነፍስየ ፡ እሞት ፡ ወለአዕይንትየኒ ፡ እምአንብዕ ፡ ግብኢ ፡ ነፍስየ ፡ ውስ
ዕረፍትኪ ፡ እያልን ፡ ወደቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ የምንወስዳቸው ፡ ከጨለማ ፡ ወደ
ብርሃን ፤ ከኀሣር ፡ ወደ ፡ ክብር ፤ ከድካም ፡ ወደ ፡ ዕረፍት ፡ እንደሚሔዱ ፡ ስናስረ
አይደለምን ፡ ?

እንዲህ ፡ ከሆነ ፤ ሴቶች ፡ ቃላቸውን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እያደረጉ ፡ ለምን ፡ ይ
ከለከላሉ ? እየተንከለከሉ ፡ ከማልቀስስ ፡ የከፋ ፡ ምን ፡ ተዋርዶ ፡ አለ ? እንደዚ
የሚያደርጉትን ፡ ሰዎች ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዳይገቡ ፤ ከምእመናን ፡ እን
ገናኙ ፡ መላ ፡ ዘመናቸውን ፡ ሊከለክሏቸው ፡ ይገባል ።

በልጅነት ፡ ከከበሩ ፤ በክርስቶስ ፡ ስም ፡ ከተጠሩ ፡ በኋላ ፡ ሞትን ፡ ሲፈሩ
ደንግጠው ፡ ሲሸበሩ ፡ ይታያሉና ። ለሞቱ ፡ ሰዎች ፡ ከማልቀስ ፡ ይልቅ ፤ ለነዚህ
ሰዎች ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ሳሉ ፡ ሊያለቅሱላቸው ፡ ይገባል ።

የሀገር ፡ ልማድ ፡ እንደመሆኑ ፤ እናለቅሳለን ፡ እንጂ ፤ ትንሣኤ ፡ ሙታን
ክደን ፡ አይደለም ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፤ ሳታፍር ፡ እየተንከለከለች ፡ ለምታ
ቅስ ፡ ለዚያች ፡ ቀብጣሪ ፡ እኔ ፡ እመልስላታለሁ ። ባልሽ ፡ ወደ ፡ ሩቅ ፡ አገር
በሔደ ፡ ጊዜ ፤ እንዲህ ፡ ታደርጊያለሽን ፡ አዎን ፡ አለቅሳለሁ ፡ ትይኝ ፡ እንደሆነ
ባልሽንስ ፡ ተመልሶ ፡ ይመጣል ፡ እያልሽ ፡ ታለቅሻለሽ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ው
ሰው ፡ አይመለስም ፡ ብለሽ ፡ አታለቅሽም ፡ ብዬ ፡ እመልስላታለሁ ። ብሎ
አንተስ ፡ ካህኑ ፡ ኢይፈርሆ ፡ ለእኩይ ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ ምስሌየ ፡ እያልክ
ስትጸልይ ፡ አታፍርምን? ፡ እንዲህ ፡ ካልክ ፡ በኋላ ፤ ለሰው ፡ ይምሰል ፡ አዛኝ ፡ ምን
ይወደው ፡ ኑሩዋል ፡ ይበሉኝ ፡ ብለህ ፡ ስታለቅስ ፡ ትገኛለህ ።

የዳዊትን ፡ መዝሙርስ ፡ እንደ ፡ ዋዛ ፡ ካየኸው ፤ ዳዊት ፡ ሊደግሙ ፡ የመ
ትን ፡ ሰዎች ፡ ለምን ፡ አስወጥተህ ፡ አልሰደድኻቸውም ። ይህስ ፡ የአረማውያን
ሥራ ፡ ነው ፡ ትሉኝ ፡ እንደሆነ ፡ ከነሱ ፡ ክህደት ፡ ያንተ ፡ ድንቁርና ፡ ይከፋል
ብዬ ፡ እመልስልሃለሁ ።

እኔስ ፡ ሞትን ፡ መራራ ፡ የምለው ፡ አይደለም ። ስለ ፡ ኃጢአታችሁ ፡ መራራ
ይሆንባችኋል ፡ እንጂ ፤ እሱስ ፡ እንደ ፡ እንቅልፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ዋይ
ሸሽ ፡ ተበላሽ ፡ እያለ ፤ የሚያለቅሰውን ፡ ሰው ፡ መምለኬ ፡ ጣዖትን ፡ እንድ
ክል ፡ እሱንም ፡ መላ ፡ ዘመኑን ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዳይገባ ፡ እከለክል
ለሁ ። አውግገዌም ፡ እለየዋለሁ ፡ ብሏል ።

፫ቱ፻ትም ፡ አልቃሽ ፡ ገዝቶ ፤ ብዙ ፡ ሰው ፡ አስከትቶ ፡ ማልቀስ ፡ ማስለቀስ
አይገባም ፡ ብለዋል ። ፊት ፡ ነጭቶ ፤ ራስ ፡ ተላጭቶ ፤ ከልብስ ፡ ተራቁቶ ፡ ማልቀስ
እንዳይገባም ፡ ሲያስረዱ ፡ ካህን ፡ ከዘመዶቹ ፡ ወገን ፡ አንዱ ፡ ቢሞት ፡ እንደ ፡ አሕዛብ ፡ ል
ሱን ፡ ቀዶ ፤ ራሱን ፡ ተላጭቶ ፡ የቀቢጸ ፡ ተስፋ ፡ ኃዘን ፡ አይዘን ፤ መከራውን
እንደ ፡ ኢዮብ ፡ ታግሦ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመስግን ፡ እንጂ ፤ ብለው ፡ አውግዘዋል

እሺ ፡ የምትሉስ ፡ ከሆነ ፤ በማይገባ ፡ እያለቀሳችሁ ፡ ሰውነታችሁን ፡ በመጉዳ
ችሁ ፤ ዐይናችሁን ፡ በማጥፋታችሁ ፡ ላይ ፡ ፍዳን ፡ ከምታስከትሉ ፡ እንደ ፡ አዳም



ተንደ ፡ ዳዊት ፡ እንደ ፡ ጴጥሮስ ፤ ኃጢአታችሁን ፡ እያሰባችሁ ፤ ሥርየት ፡ እየለመና
ሁ ፡ ብታለቅሱ ፤ ወይም ፡ እንደ ፡ ሳሙኤል ፡ ይህ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ በማይረባ ፡
ማይጠቅም ፡ ልቅሶ ፡ የምታለቅሱለት ፡ ወገናችሁ ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ሳለ ፤ ኃጢ
ት ፡ ሲሠራ ፡ አይታችሁ ፡ ከክፋት ፡ ወደ ፡ በጎነት ፤ ከኃጢአት ፡ ወደ ፡ ሥርየት ፡
ይመልሰው ፡ ብላችሁ ፡ ብታለቅሱ ፡ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ይላህዉ ፡ ይእዜ ፡ እስመ ፡ እሙ
ቱ ፡ ይትፌሥሑ ፡ ከተባሉት ፡ ትቈጠራላችሁ ፡ ማቴ ፭ ፡ ፬ ።

፩ኛ] ወንድም ፡ ወገን ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ነፍስህ ፡ ከሥጋህ ፡ እንደተለየች ፡
ኃጢአት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አንድነት ፡ ለተይተህ ፡ ይሆን? ብሎ ።

፪ኛ/ ሬሳ ፡ ከቤት ፡ ሲወጣ ፤ ከቤትህ ፡ እንደወጣህ ፡ በኃጢአትህ ፡ ከመንግሥተ ፡
ማያት ፡ ወጥተህ ፡ ይሆን? ብሎ ።

፫ኛ ወደ ፡ መቃብር ፡ ሲወርድ ፤ በነፍስህም ፡ ወደ ፡ ገሃነም ፡ ወርደህ ፡ ይሆን ?
በሎ ፡ ይህን ፡ እያስታወሱ ፡ በነዚሁ ፡ በተወሰኑት ፡ ሰዓቶች ፡ በልክ ፡ በመጠን ፡
ዋ ፡ ብሎ ፡ እንባን ፡ ብቻ ፡ ከማፍሰስ ፡ በቀር ፡ ልብሳቸውን ፡ ቀደው ፤ ማተባ
ቸውን ፡ አውልቀው ፤ ፊታቸውን ፡ ነጭተው ፡ ራሳቸውን ፡ ላጭተው ፤ ደረታቸውን ፡
እየደቁ ፡ እየተነሡ ፡ እየወደቁ ፡ አእምሮዋቸውን ፡ እያጡ ፡ የሚያለቅሱ ፡ ሰዎች ፡
ራሳቸውን ፡ ከመጉዳታቸው ፡ በላይ ፡ የክርስቶስን ፡ መድኃኒትነት ፡ የሚጠራጠሩ ፡
ክርስቲያንን ፡ የሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ የሚያስነውሩ ፡ መጻሕፍትን ፡ የሚያሰ
ሉ ፡ ከአይሁድና ፡ ከአረማውያን ፡ በግብር ፡ የተቀላቀሉ ፡ ናቸውና ፡ ሬሳችንን ፡ በዐ
ደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንቀብራለን ፤ ፍታት ፡ እናስፈታለን ፤ ተዝካር ፡ እናወጣለን ፤
ም ፡ እናስጠራለን ፤ ቢሉ ፡ ካህናቱ ፡ አትቀበሏቸው ። ምእመናንም ፡ ለማስተዛዘን ፡
ቀቀብሏቸው ፡ ስል ፡ መጀመሪያ ፡ ሐዋርያት ፡ ሁለተኛ ፡ ፫ቱ፻ት ፡ ፫ኛ ፡ ዮሐንስ ፡
ወርቅ ፡ ያወገዙትን ፡ ውግዘት ፡ እያስታወስኩ ። ደካማና ፡ ምስኪን ፡ የምሆን ፡
እኔም ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ከጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በተሰጠኝ ፡ ሥልጣን ፡
አውግዣለሁ ።

---

፲፱፻፷፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሚያዝያ ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የት
ንሣኤን ፡ በዓል ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ለምእመናን ፡ ያሰሙት ፡ ቃለ ፡ በረከት ።

ዛሬ ፡ የምናከብረው ፡ በዓል ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ፍጹም ፡ ክብር ፡ ያገኘበትና ፡
ከግብርናተ ፡ ዲያብሎስ ፡ ነጻ ፡ የወጣበት ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ትንሣኤ ፡
ስለሆነ ፤ ይህንን ፡ ቀን ፡ ስናከብር ፡ የሚሰማን ፡ ደስታ ፡ ወሰን ፡ የለውም ።

በዚህ ፡ ቀን ፡ ለአዳምና ፡ ለዘሩ ፡ የተመሠረተው ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ክብር ፡
ፍጡር ፡ ለፍጡር ፡ ያደርገው ፡ ዘንድ ፡ የማይቻል ፡ አምላካዊ ፡ ልግሥና ፡ በመ
ሆኑ ፤ ዓለም ፡ ይህንን ፡ ብድር ፡ ለመመለስ ፡ የሚችለው ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክር
ርስቶስ ፡ «እኑ ፡ ውእቱ ፡ ፍኖት ፡ ጽድቅ ፡ ወሕይወት» ፡ ብሎ ፡ በመለከተው ፡ መን
ገድ ፡ ሔዶ ፡ በሃይማኖት ፡ ፍጹምነትና ፡ በምግባር ፡ ሙሉነት ፡ ነው ።

የስንዴ ፡ ቅንጣት ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ወድቃ ፡ ከሞተች ፡ በኋላ ፡ ተነሥታ ፡ ብዙ ፡
ለማፍራት ፡ እንደሚቻላት ፤ ሰውም ፤ የሃይማኖት ፡ ፍሬ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን

www.ethiopianorthodox.org

ሙቶ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ከወደቀ፡በኋላ ፡ ተነሥቶ ፡ የሚያፈራው ፡ ፍሬ ፡ ትንሣኤ ፡
ሜና፡ጎልፈት ፡ የሌለበት ፡ ስለሆነ ፤ ዛሬ ፡ በዚህ፡ በ፡ኀላፊው ፡ ዓለም፡የማያልፍ ፡ ሶ
ሥርትን ፡ ለመጠቀም ፡ እንድንችል ፤ የጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ፍኖ
መስቀል ፡ መከተልና፡ የሱን ፡ ሕማሙን ፤ ሞቱን ፤ ትንሣኤውን ፤ ዕርገቱን ፡
መኛ ፡ መምጣቱን ፡ እያሰቡ ፤ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ «ድልዋኒክሙ ፡ ንበሩ» ፡ ብሎ
እንደነገረን ፤ ተዘጋጅቶ ፡ ዕለተ ፡ ፍጻሜውን ፡ መጠባበቅ ፡ ለትንሣኤ ፡ ዘለክብ
የሚያበቃ ፡ መሆኑን ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ ማሰብ ፡ አለበት ፡፡

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ልዑል ፡ በሕርዩን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ሰው
የሆነበትንና ፡ እስከ ፡ መሰቀል ፡ የደረሰበትን ፡ ስንመረምር ፡ ዓለምን ፡ ከፈጠረበ
ጥበቡ፡ ሰው፡ሆኖ ፡ ያዳነበት ፡ ጥበቡ ፡ ይበልጣልና፡ "አዕመቂሁ ፡ ለብዕለ ፡ ጥበቢሁ
ወአእምሮቱ ፡ ለእግዚአብሔር"፡ ብለን ፡ አንክሮዋችንን ፡ ከመወሰን ፡ በቀር ፤ ት
ቱን ፡ ዘርዝሮ ፡ ለመናገር ፡ አንችልም ፡፡ ዓለምን ፡ ለይኩን ፡ ብሎ ፡ እንደፈጠ
ሰውንም ፡ ዳን ፡ ብሎ ፡ በቃሉ ፡ ብቻ ፡ ለማዳን ፡ ሲቻለው ፤ ምክንያቱ ፡ ድኅነ
እሱ ፡ ራሱ ፡ መከራ ፡ በመቀበልና ፡ ሙቶ ፡ በመነሣት ፡ ያደረገው ፡ የሰው ፡ ፍ
ስለ ፡ አገበረው ፡ ነው ፡፡

የዕለት ፡ ዕንስ ፡ በመሆን ፡ የጀመረውን ፡ የቸርነት ፡ ሥራ በመስቀል ፡ ላይ ፡ «
ጸመ ፡ ኵሉ» ፡ ብሎ ፡ እስኪጨርሰውና ፡ የአዳምን ፡ የክብሩን ፡ ፍጻሜ ፡ በትንሣኤ
እስኪያጠቃልለው ፡ ድረስ ፡ የተቀበላቸው ፡ ፀዋትወ ፡ መከራዎች ፡ እያንዳንዳቸ
የሰውን ፡ ፍሬ ፡ ክብርና ፡ መንፈሳዊ ፡ ሀብት ፡ የሚገልጹ ፡ ናቸው ፡፡

የአምላክን ፡ ቃል ፡ አንዲቱን ፡ በማፍረስ ፡ ምክንያት ፡ ከንዲት ፡ የበለስ ፡ ቅ
ቅንጣቢ ፡ በፈሰሰው ፡ ደም ፡ በተፈጥሮ ፡ ንጹሕ ፡ የነበረው፡ የሰው ፡ ሕይወት ፡
ተዳደፈ ፤ አዳም ፡ አትብላ ፡ ከተባለው ፡ በለስ ፡ በበላ ፡ ቀን ፡ የሞት ፡ ሞ
እንዲሞት ፡ የተፈረደው ፡ አምላካዊ ፡ ፍርድ ፡ እንዳይፈርስና ፡ ምንም ፡ በደለ
ቢሆን ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ እንደተፈረደበት ፡ እንዳይቀር፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶ
ይህንን ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ መከራ ፡ ተቀብሎ ፡ በሚያፈሰው ፡ ደሙ ፡ የአዳምን ፡ ፍ
ለማስወገድና ፡ አዳምን ፡ ወደ ፡ ቀደመ ፡ ክብሩ ፡ ለመመለስ ፡ ሰው ፡ እስከ ፡ መሆ
ደረሰ ፡፡

ሰውም ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ አልቀረም ፡፡ ሕገ ፡ ወንጌልን ፡ አዘጋጅቶ፡ በሕጉ ፡ ው
ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ሠርቶና ፡ አሠርቶ ፤ ፈጽሞና ፡ አስፈጽሞ ፡ የመጣሁበት ፡ ፍጻሜ
ሰው ፡ በመሆን ፡ ብቻ ፡ ይወሰን ፡ ሳይል ፡ መራራውን ፡ የሞት ፡ ጽዋዕን ፡ ለመቀበ
ፈቀደ ፡፡ የሞትንም ፡ ጽዋዕ ፡ ለመቅመስ ፡ ያለ ፡ መከራ ፡ በጥቂት ፡ ወይም ፡ በን
ዐይነት ፡ መከራ ፡ ልሙት ፡ አላለም ፡፡

በፍርድ ፡ አደባባይ ፡ መቆምና ፡ መወቀስ፡ መገረፍና ፡ መገፈፍ ፡ መጸፋት
መመታት ፡ መስቀልን ፡ ተሸክሞ ፡ መሔድና ፡ መገፋት ፡ የርኵሳንን ፡ ምራቅ ፡ መ
በልና ፡ ውቅያኖስን ፡ የፈጠረ ፡ ሲሆን ፡ መራራ ፡ ሐሞትን ፡ ለጥማቱ ፡ መቀበል ፤ ይ
ሁሉ ፡ የትግዕሥትና ፡ የችሎታ ፡ በላይ ፡ ነው ፡፡



ከዚህም ፡ የበለጠ ፡ ዕፅፍ ፡ ድርብ ፡ የሆነውን ፡ የግፍ ፡ ግፍ ፡ ሁሉ ፡ ከተቀበለ ፡
በኋላ ፡ መጋቢት ፡ ፳፯ ቀን ፡ ዐርብ ፡ በ፮ሰዓት ፡ አጋዜ ፡ ዓለም ፡ የሆነ ፡ እጁን ፡
በመስቀል ፡ ላይ ፡ ዘርግቶ ፡ በፈቃዱ ፡ ቅድስት ፡ ነፍሱን ፡ ከቅዱስ ፡ ሥጋው ፡
ለየ ፡፡ በአካለ ፡ ነፍስም ፡ ወደ ሲኦል ፡ ወርዶ ፡ በአዳምና ፡ በሔዋን ፡ በልጆቹ ፡
ሁሉ ፡ ስም ፡ ተጽፎ ፡ የነበረውን ፡ ስመ ፡ ግብርናት ፡ አጥፍቶ ፡ በሲኦል ፡ ተግዘው ፡
የነበሩትን ፡ ነፍሳት ፡ አውጥቶ ፡ ከገቡ ፡ መውጣት ፤ ከገቡ ፡ ማጣት ፡ የሌለበትን ፡
የደስታ ፡ ገነትን ፡ አወረሳቸው ፡ ቈላ ፡ ም ፩ ፡ ቍ ፡ ፯ ፡፡ በመስቀል ፡ ባፈሰሰው ፡
ደሙ ፡ በሰማይና ፡ በምድር ፡ ያሉትን ፡ አስታረቀ ፡ በዕለተ ፡ ዐርብ ፡ በሠራው ፡
ሥራ ፡ የዕዳችንን ፡ ደብዳቤ ፡ ከባላገራችን ፡ እጅ ፡ አጠፋልን ፡፡ ከመካከላችን ፡ አራ
ቀው ፡ በመስቀሉም ፡ ቸነከረው ፡ ልብሱን ፡ በመገፈፉ ፡ ራቍቱን ፡ በመሰቀሉ ፡ የተሾ
ሙትንና ፡ የተሻሩትን ፡ አስፈራቸው ፡፡

በዚህም ፡ ቀን ፡ ፀሐይ ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ የተሰቀለው ፡ ፈጣሪው ፡ መሆኑን ፡
ዐውቆ ፡ ጨለማ ፡ ሆነ ፡፡ ጨረቃም ፡ ደም ፡ ለበሰች ፡ ከዋክብትም ፡ ረገፉ ፡ ምድ
ርም ፡ ተናወጠች ፡ መቃብራት ፡ ተከፈቱ ፡ ሙታን ፡ ተነሡ ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ ያል
ተደረገ ፡ ተአምራትና ፡ ያልታየ ፡ ምልክት ፡ የለም ፡፡

ዐርብ ፡ በሰርክ ፡ በአካለ ፡ ነፍስ ፡ ወደሲኦል ፡ ወርዶ ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ሲኦል ፡
ዐሎ ፡ ወእለ ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡ ተከሠቱ ፡ ወርእዩ ፡ ብርሃነ ፡ ዐቢየ ፡ ብሎ ፡
ነፍሳትን ፡ ካወጣ ፡ በኋላ ፡ መጋቢት ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ እሑድ ፡ ከሌሊቱ ፡ በ፯ሰዓት ፡
መቃብር ፡ ክፈቱልኝ ፡ መግነዝ ፡ ፍቱልኝ ፡ ሳይል ፡ በገዛ ፡ ሥልጣኑ ፡ ቅዱስ ፡
ከእንቅልፍ ፡ እንደሚነሣ ፡ ፈጥኖ ፡ ተናሣ ፡ ብሎ ፡ እንደተናገረ ፤ ሙስና ፡
መቃብርን ፡ አጥፍቶ ፡ ተነሣ ፡፡

ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የትንሣኤው ፡ ብርሃን ፡ ለዓለም ፡ ሁሉ ፡ ተገለጸ ፡፡ ብርሃነ ፡
ትንሣኤውም ፡ ተገልጾ ፡ በዐይነ ፡ ልቡና ፡ ስለታያቸው ፤ አሁን ፡ በቅርቡ ፡ ጊዜ ፡
በ፲፱፻፸፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከመስከረም ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ መጋቢት ፡ ፱ቀን ፡
ድረስ ፡ በከንባታ ፡ አውራጃ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
በብቻ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሀብቱ ፡ የሳባቸው ፤ በረድኤቱ ፡ ያቀረባቸው ፡
በወርቀ ፡ ደሙ ፡ የዋጃቸው ፡ ፩፻፵፩ ሺ፰፻፲፲ ፡ ምእመናን ፡ አመኑ ፡ ተጠመቁ ፡፡

ኤርምያስ ፡ በም ፡ ፴፩ ፡ በቍ ፡ ፩ ፡፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ለእስራኤል ፡ ወገ
ኖች ፡ የምሠራች ፡ ሥርዓት ፡ ይህች ፡ ናት ፡ ሕጌን ፡ በልባቸው ፡ አሳድረዋለሁ ፡
በሕሊናቸውም ፡ እጽፈዋለሁ ፡፡ አባታቸው ፡ እሆናቸዋለሁ ፡፡ እነሱም ፡ ልጆች ፡
ይሆኑኛል ፡፡

ከእንግዴህ ፡ ወዴህ ፡ ወንድም ፡ ወንድሞቹን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ዕወቁት ፡
ብሎ ፡ አያስተምራቸውም ፡ ሁሉም ፡ ታናሹም ፡ ታላቁም ፡ ያውቁኛልና ፡፡ ይቅር ፡
እላቸው ፡ ዘንድ ፡ ኃጢአታቸውንም ፡ አስተሠርይላቸው ፡ ዘንድ ፡ ኃጢአታቸው
ንም ፡ አላስብባቸውም ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ይደርስ ፡ ይፈ

www.ethiopianorthodox.org

ጾም ፡ ዘንድ ፡ ይህንን ፡ የሚያህሉ ፡ ምእመናን ፡ በክርስቶስ ፡ አምነው ፡ ልጅነት ፡
አግኝተው ፡ ደስ ፡ ስላላቸው ፤ የኢትዮጵያ ፤ ኦርቶዶክስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን
እጆዋን ፡ ዘርግታ ፡ ደስታዋን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ታደርጋለች ።

ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ቀን ፡ የሰው ፡ ፍጹም ፡ ክብሩ ፡ የተመሠረተበት ፡ የዲ
ሎስ ፡ ሥልጣን ፡ የወደቀበትና ፡ የተሻረበት ፡ ቀን ፡ ስለሆነ ፤ ዓለም ፡ ሁሉ ፡
ሣኤ ፡ ዘለክብርን ፡ ወደ ፡ ሚያድለው ፡ ወደ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ሕሊናውን ፡ ሰቅሎ ፡ ምስጋና ፡ ማቅረብ ፡ ይገባዋል ።

ይህ ፡ ቀን ፡ አዳም ፡ ከፈጣሪው ፡ የታዘዘውን ፡ ትእዛዝ ፡ በመተላለፍ ፡
ርዶበት ፡ ከነበረው ፡ ከሞት ፡ ፍርድ ፡ ወደዘለዓለማዊ ፡ ሕይወት ፡ የተመለሰበት
ቀን ፡ ነው ።

ይህ ፡ ቀን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከፅንስ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ መ
ቀል ፡ ድረስ ፡ ለሠራው ፡ ቸርነት ፡ ፍጻሜ ፡ ነው ።

ይህ ፡ ቀን ፡ ለዓለም ፡ ሁሉ ፡ ሰላም ፡ የወረደበትና ፡ ፍጡር ፡ ከፈጣሪው
ፍጹም ፡ ይቅርታ ፡ ያገኘበት ፡ ቀን ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተናገርነው ፡ መሠረት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ
ደሙን ፡ አፍስሶ ፡ ሰውነቱን ፡ ክሶ ፡ ያስታረቀውና ፡ ሰላምን ፡ የመሠረተለት ፡ ዓለም
እርስ ፡ በርሱ ፡ ታርቆና ፡ ከተቀባባው ፡ ደም ፡ ንጹሕ ፡ ሆኖ ፡ ለመኖር ፡ ይችል
ዘንድ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የምታቀርበው ፡ ጸሎት ፡ የማያቋርጥ ፡ ነው ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ ዓለም ፡ ቤዛ ፡ ከፈሰሰው ፡ ደም ፡ በቀር
ዓለምን ፡ የሚቀድሰው ፡ ሌላ ፡ ደም ፡ የለምና ፡ በክርስቶስ ፡ ደም ፡ የተቀደሰው
ዓለም ፡ ዳግመኛ ፡ በሰው ፡ ደም ፡ እንዳይረክስ ፡ ከሰላምና ፡ ከፍቅር ፡ በቀር ፡ ሌላ
የሚጠቅም ፡ ነገር ፡ እንደሌለ ፡ ማወቅ ፡ ያስፈልጋል ።

እንዲሁም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በስሜ ፡ ሁለት ፡ ሦስት ፡ ሰዎች
ካሉበት ፡ እኔም ፡ ከዚያ ፡ እኖራለሁ ፡ ብሏልና ፡ ወደፊት ፡ በሚደረገው ፡ በዓለም
የሰላም ፡ ጉባኤ ፡ መክከል ፡ እሱ ፡ እራሱ ፡ ተገኝቶ ፡ ፍጹም ፡ ሰላምን ፡ እንዲ
ሠረትና ፡ ለአደላዳዮች ፡ ፍጹም ፡ ፍርዱን ፡ እንዲገልጽ ፡ ጉባኤው ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ
ማደሪያ ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ አለበት ።

ከሙታን ፡ የተነሣው ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋውና ፡ ይቅርታው
በዓለም ፡ ላይ ፡ ይውረድ ።

እምይእዜሰ ፡ ይኩን ፡ ሰላም ፡ አሜን ።

ሚያዝያ ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፰ ፡ ዓ ፡ ም ።



## በብፁዕነታቸው ፡ መሪነት ፡ ኅዳር ፡ ፲፫ና ፡ ፲፬ ፡ ቀን ፡ ስለኢትዮጵያዊ ፡ ሊመተ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ የተከፈተው ፡ ታላቅ ፡ ጉባኤ ፡ ታሪክ ፡ ባጭሩ ።

(ሀ) ፲፱፻፷፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ኅዳር ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ሐሙስ ፡ ከጧቱ ፡ በ፫ ፤ ሰዓት ፡
ተኩል ፡ በተቀደሰው ፡ መንፈሳዊ ፡ ጉባኤ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መም
ህራን ፡ የሆኑ ፡ ፳፱ ፡ ሊቃውንትና ፡ ፳፬ ፡ መምህራን ፡ ፬ኛ ፡ ጊዜ ፡ ስብሰባ ፡ አደረጉ ።

በመጀመሪያ ፡ ጸሎተ ፡ ማኅበር ፡ አድርሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ በሰቂለ ፡ ሕሊና ፡
ከለመኑ ፡ በኋላ ፤ ሁሉም ፡ በየማዕርጋቸው ፡ ተቀመጡ ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ክቡር ፡
አፈ ፡ መስፍን ፡ አንዳርጋቸው ፡ መሳይ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፤
አስተያየት ፡ ካስረዱ ፡ በኋላ ፤ የጉባኤው ፡ አባሎች ፡ ነገሩን ፡ አጥንተው ፡ መል
ሱን ፡ እንዲሰጡ ፡ በማለት ፡ ለኅዳር ፡ ፲፬ ፡ ፲፱፻፷፰ ፡ ተቀጥሮ ፡ ጉባኤው ፡ ተመለሰ ።

(ለ) ኅዳር ፡ ፲፬ ፡ ቀን ፡ ሰኞ ፡ ከጧቱ ፡ በ፫ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ፭ኛው ፡ ስብ
ሰባ ፡ ተደረገ ። ሊቃውንቱም ፡ የተለመደውን ፡ ጸሎተ ፡ ማኅበር ፡ አድርሰው ፡ በየማ
ዕርግ ፡ ሥፍራቸው ፡ ተቀመጡ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተጻፉት ፡ የቤተ ፡
መንግሥት ፡ መልክተኞች ፤ በጉባኤው ፡ ውስጥ ፡ ነበሩ ።

ክቡር ፡ አፈ ፡ መስፍን ፡ አንዳርጋቸው ፡ መሳይ ።
ክቡር ፡ ፊታውራሪ ፡ ታፈሰ ፤ ሀብተ ፡ ሚካኤል ።
አቶ ፡ ዮፍታሔ ፡ ንጉሤ ።
ብላታ ፡ መርስዔ ፡ ኅዘን ፡ ወልደ ፡ ቂርቆስ ።

በቤተ ፡ መንግሥት ፡ በኩል ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ያለውን ፡ አስተያየት ፡ ክቡር ፡
አፈ መስፍን ፡ አንዳርጋቸው ፡ በጉባኤው ፡ ፊት ፡ ቆመው ፡ አስታወቁ ።

### የቤተ ፡ መንግሥት ፡ አሳብ ።

ባለፈው ፡ ጉባኤ ፡ በቤተ ፤ መንግሥት ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ አስተያየት ፡ እኛ
የቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ መልክተኞች ፡ ባጭሩ ፡ ገልጠንላችሁ ፡ ስለነበረ ፡ የናንተን ፡
አስተያየት ፡ ተገንዝበነዋል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ መንግሥት ፡ በበኩሉ ፡ ማድረግ ፡ የሚ
ገባውን ፡ ጉዳይ ፡ ተነጋግሮ ፡ ገና ፡ አልጨረሰም ፡ የምንል ፡ ነንና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡
የተቀበልውን ፡ አሳብ ፡ ዛሬ ፡ በሰፊው ፡ እንገልጽላችኋለን ።

ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የቤተ ፡ ክህነትን ፡ ሰዎች ፡ እንደምትሰበስብ ፡ ቤተ ፡ መንግ
ሥትም ፡ በምእመናን ፡ ሁሉ ፡ የተከበበ ፡ ነው ። በመጀመሪያው ፡ ጉባኤ ፡ በብፁዕ ፡
አባታችን ፡ ዕጨጌ ፡ ንግግር ፡ ውስጥ ፡ እንደሰማችሁት ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ቤተ ፡
መንግሥት ፡ የተባበሩ ፡ በመሆናቸው ፡ ነገሩ ፡ መልካም ፡ ፍጻሜ ፡ የሚያገኘው ፡
ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ተገናኝተውና ፡ ተስማምተው ፡ በቈረጡት ፡ ነው ።

ስለዚህ ፤ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ከእስክንድርያው ፡ ፓትሪያርክ ፡ ጋራ ፡ የተላላክ
ነው ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ ብቻ ፡ ናት ። የተገኘውም ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡

www.ethiopianorthodox.org

አለመሆኑን ፡ ቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ስለተረዳው ፤ የቤተ ፡ ክህነትን ፡ አ
ድጋፊ ፡ ሆኖ ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ ያደረገችውን ፡ ትሕትና ፡ ያህል ፡ እሱም ፡
ጉ ፡ ከእስክንድርያ ፡ ጉባኤ ፡ ጋራ ፡ የሚገባውን ፡ ንግግር ፡ ማድረግ ፡ እንደ
ባው ፡ ተረድቶታል ። ይልቁንም ፡ ይኸንን ፡ የሚያህል ፡ ታላቅ ፡ ጉዳይ ፡ ሲቈረ
ወደ እስክንድርያው ፡ ፓትረያርክ ፤ ወይም ፡ ወደጉባኤው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እንኳ ፡
ክተኛ ፡ ሳንልክና ፡ የቃል ፡ ንግግር ፡ ሳናደርግ ፡ በወረቀት ፡ መልክት ፡ ብቻ ፡ ይ
ያህል ፡ ዘመን ፡ በፈቃዳችን ፡ የያዝነውን ፡ ነገር ፡ ልንተወው ፡ አይገባንም ።

ቤተ ፡ ክህነታችን ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ስትለምን ፤ ቆይታ ፡ ከወገንዋ ፡ ሊ
ጳጳሳትን ፡ ለመምረጥና ፡ ለማሾም ፡ አትችልም ፡ የሚል ፡ ምላሽ ፡ ከመጣላት ፡ ወ
ከኮፕት ፡ ጉባኤ ፡ ጋራ ። ግንኙነቷን ፡ ለመተው ፡ ማሰቧ ፡ የሚታሰብበት ፡ ነ
መሆኑን ፡ መንግሥት ፡ ስለሚገነዘበው ። የንጉሠ ፡ ነገሥቱም ፡ መንግሥት ፡ በተረ
እንደዚሁ ፡ መላክተኛውን ፡ ልከ ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ በጠየቀችው ፡ መሠረት ፡ ከእ
ንድርያው ፡ ፓትረያርክ ፡ ጋራ ፡ ከተነጋገረ ፡ በኋላ ፤ በኅብረት ፡ የቀረበላቸውን ፡
ቄና ፡ ልመና ፡ እንደገና ፡ ገፍተውት ፡ የሚገኙ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ጉዳዩ ፡ መ
ሚያ ፡ ያገኛል ።

ክቡር ፡ አፈ ፡ መስፍን ፡ አንዳርጋቸው ፡ መሳይ ፡ ከዚህ ፡ ከተጻፈው ፡ በቀ
ልዩ ፡ ልዩ ፡ ማስረጃ ፡ እያመጡ ፡ በሰፊው ፡ ተናግረው ፡ ካስረዱ ፡ በኋላ ፤ ክቡ
ፊታውራሪ ፡ ታፈሰ ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤል ፤ ይህን ፡ አሳብ ፡ በመደገፍ ፡ ለጉባኤው ፡
ስረዱ ፡ የሚከተለውን ፡ አስታወቁ ።

በምስር ፡ ሳለሁ ፡ እንደተመለከትሁት ፡ መጠን ፡ ከግብጻውያንም ፡ ምሁራን
መንፈሳውያን ፡ የሆኑት ፡ አባቶች ፡ የሚገባንን ፡ መብት ፡ በመንሣት ፡ ሁለቱን ፡ ቤ
ክርስቲያኖች ፡ አለያይቶ ፡ ማስቀረት ፡ ደስ ፡ የሚያሰኛቸው ፡ አይመስለኝም ። ቤ
ክርስቲያናችን ፡ ያቀረበቻቸው ፡ ጥያቄዎች ፡ በሕገኛው ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ የቆመ
ናቸውና ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ወዳሰብነው ፡ አሳብ ፡ ለመድረስ ፡ ዕንቅፋት ፡
ብንም ። ይሁን ፡ እንጂ ፤ የመንግሥታችን ፡ ትሕትና ፡ በለዋጋ ፡ እንዲሆን ፡ መ
ተኞቹ ፡ አሁን ፡ በመጀመሪያ ፡ ሔደው ፡ አስፈላጊውን ፡ ጥያቄ ፡ ቢያቀርቡ
ምላሹ ፡ ሲታወቅ ፡ አሳባችንን ፡ ብንቀጥል ፡ የተሻለ ፡ ይሆናል ።

## የሊቃውንቱ ፡ ንግግር ።

ሊቃውንቱ ፡ ስለማስረጃ ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቃል ፡ እየጠቀ
በየተራ ፡ አሳባቸውን ፡ ከገለጹ ፡ በኋላ ፤ የዘኅብረት ፡ ውሳኔያቸውን ፡ አስታወቁ
ይኸውም ፡ ውሳኔ ፡ ወደፊት ፡ ተጽፎ ፡ የሚገኘው ፡ ነው ።

ብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የጉባኤው ፡ ሰብሳቢ ፡ ሆነው ፡ በተቀ
ጡበት ፡ በዚህ ፡ ውሳኔ ፡ መጨረሻ ፡ ስማቸውን ፡ የፈረሙ ፡ ፸፱ ፡ ሊቃውንትና
ሽ፬ ፡ መምህራን ፡ ከነእርሱም ፡ ፲፯ቱ ፡ የቆሞስነት ፡ ማዕርግ ፡ ያላቸው ፡ መምህራንና



ቃውንት ፡ በ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኅዳር ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ እሑድ ፡ ዳግመኛ ፡ በኅዳር ፡ ፲፫ ፡
፡ ሐሙስ ፤ ሦስተኛም ፡ በኅዳር ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ሰኞ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ቅድስት ፡
ላሴ ፡ ገዳም ፡ ተሰብስበው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸሎት ፡ አድርገው ፡ ከተነጋ
፡ በኋላ ፡ የሚከተለውን ፡ ውሳኔ ፡ አወጡ ።

፩ኛ ፤ ጉባኤው ፡ የተሰበሰበበት ፡ የነገሩ ፡ ዋነኛው ፡ አርእስት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡
ርስቲያን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ መሆን ፡ የሚገባው ፡ ኢትዮጵያዊ ፤ ወይም ፡ ግብጻዊ ፡
እንደሆነ ፡ ለመለየትና ፡ መንፈሳዊ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ነው ። በዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ምክ
ት ፡ በየጊዜው ፡ የተጻፉትን ፡ ጉባኤው ፡ ስለ ፡ መረመረ ።

(ሀ) የኢትዮጵያ ፡ መንፈሳዊ ፡ ጉባኤ ፡ በሰኔ ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡
ጥያቄዎች ፡ ጋራ ፡ የጻፈውንና ፡ ለእስክንድርያ ፡ ፓትረያርክ ፡ የላከውን ፡
ከእነ ደብዳቤ ።

(ለ) የእስክንድርያ ፡ ፓትረያርክ ፡ ፩ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ቆይተው ፡ የኢት
ጵያ ፡ መንፈሳዊ ፡ ጉባኤ ፡ ካቀረባቸው ፡ ጥያቄዎች ፡ ዐይነተኞቹን ፡ ሁለቱን ፡
ዎች ፡ አለመቀበላቸውን ፡ እያስረዱ ፡ ትእዛዝ ፡ ብለው ፡ በ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡
፱ ፡ ቀን ፡ የጻፉትንና ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንፈሳዊ ፡ ጉባኤ ፡ የላኩትን ፡ ቃል ።

(ሐ) የኢትዮጵያ ፡ መንፈሳዊ ፡ ጉባኤ ፡ በ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሐምሌ ፡ ፯ ፡
፡ ለኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ያቀረበውን ፡ የውሳኔ ፡ ማስታ
ቂያ ።

ጉባኤው ፡ ከመረመራቸው ፡ ነገሮች ፡ አንዳንዶቹን ፡ ከዚህ ፡ ማንሣት ፡
፡ ነው ።

(ሀ) የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የጠየቀችው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳትዋ ፡
ተወላጆችዋ ፡ መካከል ፡ በሊቃውንቶቹዋ ፡ እየተመረጠ ፡ የእስክንድርያ ፡ ፓትረ
ርክ ፡ ባርከው ፡ እንዲሾሙላት ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳትዋም ፡ በበታቹ ፡ ጳጳሳትንና ፡
ስ ፡ ቆጶሳትን ፡ ለመሾም ፡ መብት ፡ ያለው ፡ እንዲሆን ፡ ነው ።

(ለ) የኮፕት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ግን ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሚሾመው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳ
፡ ለዘለዓለም ፡ የግብጽ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ እንዲሆን ፡ እንጂ ፤ ኢትዮጵያዊ ፡ አይሆ
፡ ስትል ፡ መልስ ፡ ሰጠች ። ለዚሁም ፡ ማስረጃ ፡ ሺ፯፻ ፡ ዘመን ፡ የቆየ ፡ ልማድ ፡
ሆኑን ፡ ከማስታወሷ ፡ በላይ ፡ ከቅዱሳን ፡ አበው ፡ ከሠለስቱ ፡ ምእት ፡ በጉባኤ ፡
ያ ፡ ተጽፎ ፡ የተወሰነ ፡ ነው ፡ ስትል ፡ አሳብዋን ፡ አስታወቀች ።

## የጉባኤው ፡ ምርመራ ።

የተቀደሰው ፡ ዐቢይ ፡ መንፈሳዊ ፡ ጉባኤ ፡ ከግብጻውያን ፡ በኩል ፡ የቀረቡትን ፡
ክ ፡ ከመረመረ ፡ በኋላ ፤ የሚከተሉትን ፡ ነገሮች ፡ እነሆ ፡ ያስታውቃል ።

www.ethiopianorthodox.org

## ስለ ፡ ዘመን ፡ ብዛት ፡

የዘመን ፡ ብዛት ፡ ልማድን ፤ ወይም ፡ ሥርዓትን ፡ ከማሻሻል ፡ የሚያ
አይደለም ። ብዙ ፡ ዘመን ፡ የኖረው ፡ የአሪት ፡ ሥርዓት ፡ እንዳይሻሻል ፡ የዘ
ብዛት ፡ አላገደውም ። እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አምልኮት ፡ የሚኖሩ
ማውያን ፡ አሁን ፡ በወንጌል ፡ ሲያምኑ ፡ የዘመኑ ፡ ብዛት ፡ ሥርዓት ፡ ሆኖ
ግዳቸውም ። ይህን ፡ የመሰለ ፡ ብዙ ፡ ምሳሌ ፡ ይገኛልና ፡ ነገሩን ፡ ባጭሩ ፡ መ
አስፈላጊ ፡ ነው ።

የኢ.ትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፤ በፈቃድዋ ፡ ትሠራበት ፡ የነበረውን ፡ ል
አሁን ፡ ደግሞ ፡ በፈቃድዋ ፡ ታሻሽለው ፡ ዘንድ ፡ የሚገባት ፡ ሆነ ። ምክንያ
የቀድሞው ፡ ልማድ ፡ በኢ.ትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ላይ ፡ ብርቱ ፡ ጉ
የሚያደርስባት ፡ መሆኑ ፡ በሚከተሉት ፡ ቃላት ፡ ስለተገለጸ ፡ ነው ።

በኢ.ትዮጵያ ፡ ላይ ፡ የሚሾመው ፡ ግብጻዊ ፡ ሊ.ቀ ፡ ጳጳሳት

፩ኛ/ የሕዝቡን ፡ ቋንቋ ፡ የማያውቁና ፡ በሕዝቡ ፡ ቋንቋ ፡ የማይሰብኩ ፡ ናቸ

፪ኛ/ በቤተ ፡ ክርስቲያኒቱ ፡ ወይም ፡ በአገሩ ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ በደረሰ ፡
ወደ ፡ አገራቸው ፡ የሚሔዱ ፡ ናቸው ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ለጠቅላላው ፡ አስተ
ዕንቅፋት ፡ የሚሆን ፡ ምክንያትን ፡ የሚያስከትል ፡ መሆኑ ፡ አይጠረጠርም ።

ይህንን ፡ ሁሉ ፡ በማመዛዘን ፡ የቈየው ፡ ልማድ ፡ በሚገባ ፡ እንዲለ
አስፈለገ ።

## ስለ ፡ ኒቅያ ፡ ጥቅስ ።

የኮፕትን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፤ የግል ፡ ጥቅም ፡ ለመመሥረትና ፡ የኢ.ትዮ
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘለዓለም ፡ በበታችዋ ፡ ሆና ፡ እንድትኖር ፡ ለማድረግ ፡
ያት ፡ ሆኖ ፡ በየጊዜው ፡ የሚጠቀሰውን ፡ ቃል ፡ ጉባኤው ፡ መረመረ ። ቃ
የኢ.ትዮጵያ ፡ ሰዎች ፡ ከዐዋቆቻቸው ፡ ወገን ፡ አለቃ ፡ (ሊ.ቀ ፡ ጳጳሳት ) አይሹ
የሚለው ፡ ነው ።

ይህ ፡ ጥቅስ ፡ በኢ.ትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ዐዋቆች ፡ መኖራቸውን ፡ እየመሰ
ሹመቱን ፡ ብቻ ፡ ይከለክላል ። ይኸውም ፡ ቃል ፡ ለጥቅም ፡ ሲታሰብ ፡ የተፈ
መሆኑን ፤ የሚከተሉት ፡ ምክንያቶች ፡ ያስረዳሉ ።

(ሀ) ይህ ፡ ቃል ፡ በሌሎቹ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ዘንድ ፡ ስለማይገኝ
(ለ) የክርስትና ፡ ሥርዓት ፡ የዘርና ፡ የወገንን ፡ ልዩነት ፡ ስለማያደርግ ፤
(ሐ) ኢ.ትዮጵያ ፡ ሥርዓተ ፡ ክርስትናን ፡ የተቀበለችው ፡ ከኒቅያ ፡
በኋላ ፡ በመሆኑ ፤ ከመቀበልዋ ፡ በፊት ፡ የኒቅያ ፡ ጉባኤ ፡ ይህን ፡ ዓይነት ፡ ውሳ
ደማያወጣባት ፡ ለባለአእምሮው ፡ ሁሉ ፡ የተገለጠ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። በዚህና ፡
በመሰለ ፡ ምክንያት ፡ ሁሉ ፡ ከግብጻውያን ፡ የተጠቀሰው ፡ ጥቅስ ፡ ቀዋሚነት ፡
ሆኖ ፡ አልተገመተም ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ጉባኤው ፡ የተመለከተው ፡ ነገር ፡



ብጻውያን ፡ የጠቀሱት ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ቢባል ፡ ኖሮ ፡ እንኳ ፡ የአ
ተዳደር ፡ ጉዳይ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሃይማኖት ፡ ነገር ፡ አይደለም ። የአስተዳደርም ፡
ጉዳይ ፡ ለዘመኑ ፡ የሚስማማው ፡ በየጊዜው ፡ እየታየ ፡ ይሻሻል ፡ ዘንድ ፡ የሚገባ ፡ ስለ
ሆነ ፤ እንዲሻሻል ፡ ወይም ፡ እንዲለወጥ ፡ ከማድረግ ፡ የሚከለክል ፡ አንዳች ፡ ምክን
ያት ፡ አለመኖሩ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

የተቀደሰው ፡ ዐቢይ ፡ የኢ.ትዮጵያ ፡ መንፈሳዊ ፡ ጉባኤ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ስለ
መረመረና ፡ የኢ.ትዮጵያ ፡ መንፈሳዊ ፡ ጉባኤ ፡ በ፳ ፡ ሐምሌ ፡ ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡
ያወጣውን ፡ የውሳኔ ፡ ማስታወቂያ ፡ አረጋግጦ ፡ ስለተቀበለው ፤ የኢ.ትዮጵያ ፡ ቤተ ፡
ክርስቲያን ፡ ሊ.ቀ ፡ ጳጳሳትዋን ፡ ከተወላጆችዋ ፡ ውስጥ ፡ ማግኘት ፡ ይገባታል ፡ ሲል ፡
በአንድ ፡ ቃል ፡ ተስማምቶበታል ።

፫ኛ) ፡ የኢ.ትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ መንግሥትና ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ ተባብረውና ፡ ተሳ
ስበው ፡ የሚኖሩ ፡ ከመሆናቸው ፡ የተነሣ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ወደኮፕት ፡ ጉባኤ ፡
መልክተኞቹን ፡ ለመላክና ፡ እነዚያው ፡ የፊተኞቹ ፡ ጥያቄዎች ፡ እንዲፈጸሙ ፡
በበኩሉ ፡ እንደገና ፡ ለመጠየቅ ፡ ማሰቡ ፡ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ መልክተኞች ፡
እንደበት ፡ ለጉባኤው ፡ ተነገረ ።

የቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ አሳብ ፡ የኮፕት ፡ ጉባኤ ፡ ምናልባት ፡ አሳቡን ፡ አድሶ ፡
የኢ.ትዮጵያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጥያቄዎች ፡ የሚቀበል ፡ ቢሆን ፡ ግንኙነቱ ፡
እንዳያቋርጥ ፡ ለማድረግ ፤ ሳይሆን ፡ ቢቀር ፡ ግን ፡ ትሕትናውን ፡ እስከሚገባው ፡
ደረጃ ፡ አድርሶ ፡ ለመተው ፡ መሆኑን ፡ ጉባኤው ፡ በትክክል ፡ ተረድቶታል ።

ጉባኤው ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ተነጋግሮበታል ። ከአባሎቹ ፡ ከአራት ፡
አንዱ ፡ እጅ ፡ የሚሆኑት ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ አሳብ ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡
መታገሥና ፡ ቢሆን ፡ ይሆናል ፤ ባይሆንም ፡ ሥራችንን ፡ እንፈጽማለን ፡ የሚል ፡
ድምፅ ፡ ሲሰጡ ፤ ሦስት ፡ እጅ ፡ የሚሆኑት ፡ ግን ፡ ሥራችንን ፡ እንፈጽማለን ፡
እንጂ ፡ ዳግመኛ ፡ ጥያቄ ፡ አያስፈልግም ፡ ብለው ፡ ድምፃቸውን ፡ አሰሙ ። ይሁን ፡
እንጂ ፡ በጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡ ጉባኤው ፡ የመንግሥቱን ፡ አሳብ ፡ ተቃዋሚ ፡ አለ ፡
መሆኑን ፡ ገለጠ ።

የጉባኤው ፡ አባሎች ፡ በተከታዩ ፡ ሰሞን ፡ ሱባዔ ፡ ለማድረግና ፡ የሚገባ
ውን ፡ ሥርዓት ፡ ለማድረስ ፡ ማሰባቸውን ፡ ከገለጹ ፡ በኋላ ፤ ይህ ፡ ውሳኔ ፡ ፍጻሜ ፡
እንዲያገኝ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ያሳስቡላቸው ፡ ዘንድ ፡ ለቤተ ፡
መንግሥት ፡ መልክተኞች ፡ ሲያስታውቋቸው ፤ እነሱም ፡ መልካም ፡ ፈቃዳቸው ፡
መሆኑን ፡ ገለጡላቸው ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ምዕራግ ፡ ጸሎት ፡ ተደርጎ ፡ በ፱ሰዓት ፡
ጉባኤው ፡ ተመለሰ ። በዚህ ፡ ውሳኔ ፡ የፈረሙ ፡ የጉባኤ ፡ አባሎች ፡ የሚከተ
ሉት ፡ ናቸው ።

ብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የጉባኤው ፡ ሰብሳቢ ፡
ንቡረ ፡ እድ ፡ ተስፋዬ ፡ የአክሱም ፡ ጽዮን ፡ ገዳም ፡ ንቡረ ፡ እድ ፡

www.ethiopianorthodox.org

መምህር ፡ ገሪማ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ገዳም ፡ ራይስ ፡ የነበሩ ፡ አሁንም የግሼን ፡ ማርያም ፡ መምህርና ፡ ቆሞስ ።

መምህር ፡ ይርዳው ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ገዳም ፡ ራይስ ፡ የነበሩ ፡ አሁንም የአብዬ ፡ ገዳም ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መምህርና ፡ ቆሞስ ።

መምህር ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ የደብረ ፡ ዳሞ ፡ አሁን ፡ አረጋዊ ፡ ገዳም መምህርና ፡ ቆሞስ ። መምህር ፡ መልእክቱ ፡ የመካነ ፡ ሥላሴ ፡ ዘአዲስ ፡ አበባ ገዳም ፡ መምህርና ፡ ቆሞስ ። መምህር ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ እንዳላማው ፡ የዲማ ጊዮርጊስ ፡ ገዳም ፡ መምህር ። መምህር ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የፍርኩታ ፡ ኪዳነ ምሕረት ፡ ገዳም ፡ መምህር ።

መምህር ፡ ተክለ ፡ ገሪማ ፡ በደብረ ፡ በንኰል ፡ አቡነ ፡ መድኃኒነ ፡ እግዚእ ገዳም ፡ መምህርና ፡ ቆሞስ ። መምህር ፡ ዘፈረ ፡ ብርሃን ፡ የዝቋላ ፡ አቡነ ፡ ገብረ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ገዳም ፡ መምህርና ፡ ቆሞስ። ቄስ ፡ ገበዝ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ የአ ክሱም ፡ ገዳም ፡ ቄሰ ፡ ገበዝ ።

መምህር ፡ ተወልደ ፡ ብርሃን ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ የደብረ ፡ ቢዘን ፡ አቡነ ፡ ፊልጶስ ፡ ገዳም ፡ መልክተኛና ፡ ቆሞስ፤ መልአከ ፡ ሰላም ፡ ገሪማ ፡ ዋግ ፡ የወይብላ ማርያም ፡ መቅደስ ፡ አለቃ ።

## የመንፈሳዊ ፡ ጉባኤ ፡ የዘወትር ፡ አማካሪዎች ።

ሊቀ ፡ ሊቃውንት ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ የታዕካ ፡ ነገሥት ፡ በአታ ፡ ገዳም መምህርና ፡ ቆሞስ፤ የጉባኤውም ፡ ምክትል ፡ ሰብሳቢ ።

መልአከ ፡ ብርሃናት ፡ ገብረ ፡ አጋዕዝት ፡ ገብረ ፡ ሚካኤል ፡ የደብረ ፡ ብር ሃን ፡ ሥላሴ ፡ አለቃና ፡ የካህናት ፡ ባልደረባ ።

መልአከ ፡ ፀሐይ ፡ ዘለቀ ፡ የመንበረ ፡ ፀሐይ ፡ ማርያም ፡ ደብር ፡ አለቃ መምህር ፡ ክንፈ ፡ ሚካኤል ፡ የደብረ ፡ ሰላም ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ደብር አለቃ አለቃ ፡ መኰሪያ ፡ አብዬ ፡ ሆይ ፡ የቀራንዮ ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም፡ ደብር ፡ አለቃ ፡ የቅ ኔና ፡ የሐዲስ ፡ መምህር ፤ መምህር ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ብርሃን ፡ መስቀል የጽርሐ ፡ ጽዮን ፡ ጉባኤ ፡ ዘሐዋርያት ፡ ደብር ፡ አለቃና ፡ ቆሞስ ።

ሊቀ ፡ ጠበብት ፡ ውቤ ፡ ገብሬ ፡ የደብረ ፡ ጽጌ ፡ ዑራኤል ፡ ደብር ፡ ክህ ንና ፡ ሊቀ ፡ ጠበብት ፡ ሊቀ ፡ ጠበብት ፡ ተድላ ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡ የደብረ ኃይል ፡ ራጉኤል ፡ ክህንና ፡ ሊቀ ፡ ጠበብት ፡ የቅኔና ፡ የሐዲስ ፡ መምህር ።

ሊቀ ፡ መዘምራን ፡ ተረፈ ፡ ወርቄ ፡ የማኅደረ ፡ ስብሐት ፡ ልደታ ፡ ደብር፡ አለቃ ከያውራጃው ፡ የተሰበሰቡ ፡ የአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መልክተኞች ፡ (ሊቃውንት)፡

## የአዲስ ፡ አበባ ፡ አውራጃ ፡ መልክተኞች ።

አፈ ፡ ንቡረ ፡ እድ ፡ ተክለ ፡ ማርያም ፡ ወልደ ፡ ዜና ፡ የደብረ ፡ ጽዮን ፡



አዲስ ፡ ዓለም ፡ ማርያም ፡ ክህንና ፡ አፈ ፡ ንቡረ ፡ እድ ፡ (ዘአዲስ ፡ ዓለም ።)

አለቃ ፡ ወልደ ፡ መስቀል ፡ የደብረ ፡ ጽጌ ፡ ዑራኤል ፡ ደብር ፡ ክህንና ፡ የዜማ ፡ መምህር ። አዲስ ፡ አበባ ። ግራ ፡ ጌታ ፡ አበበ ፡ ወረደ ፡ የመንበረ ፡ ፀሐይ ፡ ማርያም ፡ ደብር ፡ ክህንና ፡ ግራ ፡ ጌታ ፡ እንጦጦ ። ርእሰ ፡ ደብር ፡ በልሁ፡ የቀራንዮ ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ደብር ፡ ክህንና ፡ ርእሰ ፡ ደብር ፡ (አቃቂ ፡) ሊቀ ፡ መዘምራን ፡ አክሊሉ ፡ ገብረ ፡ ኪሮስ ፡ የታዕካ ፡ ነገሥት ፡ በአታ ፡ ገዳም ፡ ክህንና ፡ የሐዲስ ፡ መምህር ፡ (አዲስ ፡ አበባ ።)

ሊቀ ፡ ጠበብት ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የጽርሐ ፡ አርያም ፡ ሩፋኤል ፡ ደብር ፡ ክህንና የሐዲስ ፡ መምህር ፡ (አዲስ ፡ አበባ ። )

አለቃ ፡ መርስዔ ፡ ኃዘን ፡ ወርቄ ፡ የቆርቋ ፡ ሥላሴ ፡ መቅደስ ፡ አለቃና ፡ የዜማ፡ መምህር ፡ (ሜጫ ፡ ) አለቃ ፡ ነጋሽ ፡ ኃይሉ ፡ የገነተ ፡ ጽጌ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ክህንና ፡ የመጻሕፍት ፡ ሊቃውንት ፡ መምህር ፡ (አዲስ ፡ አበባ ።)

## የሸዋ ፡ አውራጃ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መልክተኞች ።

ጸባቴ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገዳም ፡ ጸባቴ ፡ (ሰላሌ ፡ ) መጋቢ ፡ ባንት ፡ ይዋሉ ፡ ብርቅነህ ፡ የደብረ ፡ ብሥራት ። ዜና ፡ ማርቆስ ፡ ገዳም ፡ መጋቢና ፡ ቆሞስ ፡ (ሞረት ።)

አለቃ ፡ ጐላ ፡ መታፈሪያ ፡ የቀኑንዲ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቤ ፡ ክ ፡ አለቃ ፡ (አንኮበር ፡ መምህር ፡ ተከሥተ ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡ የሳማ ፡ ሰንበት ፡ ገዳም ፡ መምህርና ፡ ቆሞስ ) የሐዲስ ፡ መምህር ፡ (ምንጃር ። )

ግራ ፡ ጌታ ፡ ገብረ ፡ ጻድቅ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ የደብረ ፡ ብርሃን ፡ ሥላሴ ፡ ክህን ፡ (ተጉለት ፡) ርእሰ ፡ ደብር ፡ ገብረ ጻድቅ ፡ ወልደ ፡ ማርያም፡ የደብረ ፡ ብርሃን ፡ ሥላሴ ፡ ክህንና ፡ የሐዲስ ፡ መምህር፡ (ተጉለት ።)

መምህር ፡ ወልደ ፡ አማኑኤል ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስ ፡ የምሁር ፡ ኢየሱስ ፡ ገዳም ፡ የቅዳሴ ፡ መምህር ፡ (ሀገረ ፡ ጉራጌ ።)

## የትግሬ ፡ አውራጃ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መልክተኞች ።

ቄስ ፡ ገበዝ . ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ወልደ፡ ሥላሴ ፡ የአክሱም ፡ ጽዮን ፡ ገዳም፡ ክህንና ፡ ቆሞስ ፡ (አክሱም ።)

መምህር ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ገብረ፡ መድኅን ፡ የማይ ፡ አንበሳ ፡ ደብረ፡ ገነት ፡ ኪዳነ ፡ ምሕረት ፡ ገዳም ፡ መምህርና ፡ ቆሞስ ፡ (መቀሌ ።)

መምህር ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ የጕንዳጕንዲ ፡ ማርያም ፡ ገዳም ፡ መምህርና ፡ ቆሞስ ፡ (አጋሜ ።)

መልአከ ፡ ፀሐይ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ ባይሞት ፡ የማይጨው ፡ ማርያም ፡ ገዳም ፡ መምህርና ፡ ቆሞስ ፡ (አዘቦና ፡ ራያ) ።

www.ethiopianorthodox.org

መልአከ ፡ ገነት ፡ ፈትየዮ ፡ ለማ ፡ የደብረ ፡ ገነት ፡ አጽቢ ፡ ሥላሴ ፡ ደብር ፡ አለቃ ፡ (አጋሜ) ።

መምህር ፡ ዐሥራት ፡ ከከብ ፡ የመካነ ፡ ሕይወት ፡ ቋሀ ፤ ኪዳነ ፡ ምሕረት ፡ ገዳም ፡ መምህርና ፡ ቆሞስ ፡ (ተምቤን) ።

አለቃ ፡ ማርቆስ ፡ ተወልደ ፡ መድኅን ፡ የደብረ ፡ ገነት ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ደብር ፡ ካህንና ፡ የሐዲስ ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት መምህር ፡ (መቀሌ) ።

## የጐጃም አውራጃ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መልክተኞች ።

መልአከ ፡ ሰላም ፡ የውነቱ ፡ የጽርሐ ፡ አርያም ፡ ሚካኤል ፡ ደብር ፡ አለቃ ፡ ደምበጫ ።

መልአከ ፡ ብርሃን ፡ አድማሱ ፡ ጀምበሬ ፡ የደብረ ፡ ብርሃን ፡ ጊዮርጊስ ፡ ደብር ፡ አለቃና ፡ የቅኔ ፡ መምህር ፡ (ብቸና) ።

አለቃ ፡ በላይ ፡ ሻሹ ፡ የጽርሐ ፡ ጽዮን ፤ ማርያም ፡ ደብር ፡ አለቃና ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ መምህር ፡ (ደብረ ፡ ማርቆስ) ።

አለቃ ፡ ወርቅነህ ፡ ምሕረቱ ፤ የደብረ ፡ ኃይል ፡ ሚካኤል ፡ ደብር ፡ አለቃ ፡ የሐዲስና ፤ የአቋቋም ፡ መምህር ።

ቄሰ ፡ ገበዝ ፡ ልመንህ ፡ ለውጤ ፡ የሥርወ ፡ ሃይማኖት ፡ ኢየሱስ ፡ ገዳም ፡ ካህንና ፡ የቅኔ ፡ መምህር ፡ (ብቸና) ።

መምህር ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ ጉዳዩ ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ኪዳነ ፡ ምሕረት ፡ ገዳም ፡ መምህርና ፡ ቆሞስ ፡ (ብቸና) ።

መምህር ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ውቤ ፡ የዋሸራ ፡ ደብረ ፡ ምዕራፍ ፡ ማርያም ፡ ገዳም ፡ መምህርና ፤ ዜማ ፡ አስተማሪ ፡ (ደምበጫ) ።

## የወሎ ፡ አውራጃ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መልክተኞች ።

መልአከ ፡ ገነት ፡ ማኅፀንተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ የገነተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ደብር ፡ አለቃና ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ መምህር ፡ (ደሴ) ።

አለቃ ፡ ታመነ ፡ አግደው ፡ የቂስ ፡ ማርያም ፡ መቅደስ ፡ ካህን ፡ የቅኔና ፡ የብሉይ ፡ መምህር ፡ (አማራ ፡ ሳይንት) ።

አለቃ ፡ አበበ ፡ ኃይሉ ፡ የደሴ ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ አለቃ ፡ (ደሴ) ።

አለቃ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ንጉሤ ፡ የጼቶ ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ደብር ፡ አለቃና ፡ የዜማ ፡ መምህር ፡ (ደሴ)

አለቃ ፡ ጸጋ ፡ እንግዳ ፡ የተንታ ፡ ሚካኤል ፡ ደብር ፡ ካህን ፡ (ትንታ ።

አለቃ ፡ መክብብ ፡ እንግዳ ፡ ወርቅ ፡ የግሸን ፡ ማርያም ፡ ገዳም ፡ ካህንና ፡ የሐዲስ ፡ መምህር ፡ (አምባሰል) ።



አለቃ ፡ ዓለሙ ፡ ደርሰ ፡ የቆቅና ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መቅደስ ፡ ካህን ፡ የሐዲስና ፡ የሊቀ ፡ መምህር ።

## የሐረር ፡ አውራጃ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መልክተኞት ።

አለቃ ፡ ደስታ ፡ ነገዎ ፡ የደብረ ፡ ኃይል ፡ ሚካኤል ፡ ካህን ፡ (ሐረር) ።

አለቃ ፡ ሐዋዝ ፡ ታየ ፡ የመካነ ፡ ሥላሴ ፡ ደብር ፡ ካህን ፡ የብሉይና ፡ የሐዲስ ፡ መምህር ፡ (ሐረር) ።

ግራ ፡ ጌታ ፡ ኃይለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ በለጠ ፡ የደብረ ፡ ኃይል ፡ ሚካኤል ፤ ደብር ፡ ካህንና ፡ የዜማ ፡ መምህር ።

መሪ ፡ ጌታ ፡ አበበ ፡ ተክለ ፡ ሐዋርያት ፡ የደብረ ፡ ገነት ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ደብር ፡ ካህንና ፡ የዜማ ፡ መምህር ።

አለቃ ፡ ታመነ ፡ ዳርጌ ፡ የመካነ ፡ ሥላሴ ፡ ደብር ፡ ካህንና ፡ የቅኔ ፡ የዝማሬና ፡ መዋሥዕት ፡ መምህር ።

## የከፋ ፡ አውራጃ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መልክተኞች ።

መምህር ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ አድገሀ ፡ የደብረ ፡ መዊዕ ፡ መድኃኔ ። ዓለም ፡ ደብር ፡ አለቃ ፡ የብሉይና ፡ የሐዲስ ፡ መምህር ፡ (ጂማ) ።

አለቃ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ወልዱ ፡ የሰደቻ ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ መቅደስ ፡ መሪ ጌታና ፡ የዜማ ፡ መምህር ፡ ሊሙ ።

አለቃ ፡ ሙሴ ፡ ጐበዜ ፡ የዛንጅሮ ፡ ደብረ ፡ መድኃኒት ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ መቅደስ ፡ መሪጌታና ፡ የዜማ ፡ መምህር ፡ ዛንጅሮ ።

## የሲዳሞና ፡ የቦረና ፡ አውራጃ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መልክተኞች ።

መምህር ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፤ መርድ ፡ የደብረ ፡ መንክራት ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ገዳም ፡ መምህርና ፤ ቆሞስ ፡ (ወላሞ ፤ ሶዶ) ።

መምህር ፡ ምትኬ ፡ ይመር ፡ የይርጋ ፡ ዓለም ፡ ማርያም ፡ ደብር ፡ አለቃና ፡ ቆሞስ ፡ (ሲዳሞ ፡ ይርጋ ፡ ዓለም) ።

አለቃ ፡ እጅጉ ፤ ተበጀ ፡ የሀገረ ፡ ሰላም ፡ ኪዳነ ፡ ምሕረት ፡ ደብር ፡ ካህን ፡ (ጀምጀም) ።

## የአሩሲ ፡ አውራጃ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መልክተኞች ፡

መሪጌታ ፡ ጽጌ ፡ ወልደ ፡ ተክሌ ፡ የጢቾ ፡ ጊዮርጊስ ፡ መቅደስ ፡ መሪጌታና ፡ የቅኔ ፡ መምህር ፡ (ጢቾ) ።

አለቃ ፡ ተክለ ፡ ዮሐንስ ፡ መንግሥቱ ፡ የሰዴቃ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መቅደስ ፡ መሪጌታ ፡ የዜማና ፡ የአቋቋም ፡ መምህር ።

www.ethiopianorthodox.org

## የወለጋ ፤ አውራጃ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መልክተኞች ።

መምህር ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ ሐዲሱ ፡ የግዳሜ ፡ ማርያም ፡ ከህን ፡ (ቄለም
መምሬ ፡ ውሂብ ፡ ገብሩ ፡ የለቀምት ፡ ማርያም ፡ መቅደስ ፡ ከህን ፡ (ለቀምት

መምሬ ፡ ተስፋዬ ፡ የማኑ ፡ የከምቶ ፡ ሥላሴ ፡ መቅደስ ፡ ቄሰ ፡ ገበ ፡ (ለቀምት

## የልዩ ፡ ልዩ ፡ አውራጃ ፡ ሊቃውንቶችና ፡ መምህራን ።

አለቃ ፡ ኃይሉ ፡ ቢወጣ ፡ የሐዲስና ፡ የአቋቋም ፡ መምህር ። (ጐንደር)
መምህር ፡ ራስ ፡ ወርቅ ፡ የአፈር ፡ ባይኔ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ገዳም ፡ አለቃና
የመንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ሹም ፡ ሸዋ ፡ ላም ፡ ዋሻ ።

መልአከ ፡ ገነት ፡ ሀብተ ፡ ወልድ ፡ የገነተ ፡ ጽጌ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ደብር ፡ አለቃና
የሐዲስ ፡ መምህር ፡ ሸዋ ፤ ተጉለት ።

መልአከ ፡ ምሕረት ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ ኪዳኔ ፡ የደብረ ፡ መድኃኒት ፡ መድኃኔ
ዓለም ፡ አለቃ ፡ (ትግሬ ፡ አድዋ ።)

መምህር ፡ አረጋዊ ፡ ገብረ ፡ መድኅን ፡ የእንደ ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ ከሣቴ ፡ ብርሃን
ገዳም ፡ መምህር ፡ ትግሬ ። አለቃ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ የደብረ ፡ አሚን ፡ ተክለ ፡ ሃይ
ማኖት ፡ ደብር ፡ አለቃና ፡ የዜማ ፡ መምህር ፡ ሸዋ ፤ እንሳሮ ፡ አለቃ ፡ ወልደ ፡ ኪዳን
ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ የደብረ ፡ መዊዕ ፡ ግንባርዎ ፡ ማርያም ፡ ደብር ፡ አለቃና ፡ የብሉይ
መምህር ፡ (ሸዋ ፡ ተጉለት ።)

አለቃ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ የደብረ ፡ ሰላም ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ከህንና ፡ የመጻ
ሕፍተ ፡ ሊቃውንት ፡ መምህር ፡ ጐጃም ፡ ዲማ ።)
አለቃ ፡ አበበ ፡ ኃይሉ ፡ የጽርሐ ፡ አርያም ፡ ሩፋኤል ፡ ደብር ፡ ከህን ፡ የቅኔና
የአቋቋም ፡ መምህር ፡ ስሜን ። አለቃ ፡ በለጤ ፡ የደብረ ፡ ትፍሥሕት ፡ ማርያም
ደብር ፡ አለቃ ፡ (ሸዋ ፡ አንኮበር ፤ )

አለቃ ፡ በሻህ ፡ የአንጐለላ ፡ ኪዳነ ፡ ምሕረት ፡ ደብር ፡ አለቃ ፡ ወግዳ ።
አለቃ ፡ አስቤ ፡ የአንኮበር ፡ ጊዮርጊስ ፡ ደብር ፡ አለቃ ፡ ሸዋ ፡ አንኮበር ።
መምህር ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ የነአኵቶ ፡ ለአብ ፡ ገዳም ፡ መምህር ። (ላስታ )
መምህር ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የደብረ ፡ ቤቴል ፡ ሥላሴ ፡ ደብር ፡ አለቃ ፡ (ወሎ)
መምህር ፡ ፈንታ ፡ የእየላ ፡ ሚካኤል ፡ ደብር ፡ አለቃ ፡ (ላስታ)
መምህር ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ የአቡነ ፡ ገሪማ ፡ ገዳም ፡ መምህር ፡ (ትግሬ)
መምህር ፡ ምሕረቱ ፡ የሐዲስና ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ መምህር ፡ (ጐንደር)
አለቃ ፡ መንክር ፡ የቅኔ ፡ መምህር ፡ የአሰላ ፡ ጊዮርጊስ ፡ መቅደስ ፡ መሪጌታ ፡ (አሩሲ ፡)
አለቃ ፡ ወልደ ፡ ኢየሱስ ፡ በለው ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ የጴጥሮስ ፡ ወጳውሎስ ፡ ደብር
አለቃ ፡ የነበሩና ፡ አሁን ፡ በመካነ ፡ ሥላሴ ፡ ገዳም ፡ መንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡
የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ መምህር ፡ (ላስታ) ።



መሪጌታ ፡ መርዓዊ ፡ የጥቾ ፡ ገብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መቅደስ ፡ ከህንና ፡ የቅኔ ፡
መምህር (፡ አሩሲ ፡)
አባ ፡ ተመስገን ፡ የሞጣ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ከህን ፡ (ጐጃም ፡ ሞጣ ፡)
አባ ፡ ገብረ ፡ ወልድ ፡ የደብረ ፡ አሚን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ከህንና ፡ የኦርቶዶክሳ
ዊት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ (አዲስ ፡ አበባ ፡)
መምህር ፡ ገብረ ፡ ሚካኤል ፡ የመናገሻ ፡ ማርያም ፡ ገዳም ፡ መምህር ፡ (አዲስ ፡ አበባ ፡
ገነት ፡)
መምህር ፡ ገብረ ፡ ሚካኤል ፡ የወቄጣ ፡ ማርያም ፡ ገዳም ፡ አለቃ ፡ (በጌምድር ፡
ዋድላ ።)
መምህር ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ መምህር ፡ (ጐንደር ፡)

## ፪ኛ ፡ የበጌምድር ፡ ሊቃውንት ።

አለቃ ፡ ፀሐዩ ።
መልአከ ፡ ፀሐይ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
አለቃ ፡ ካሣ ፡
መምህር ፡ ጌታሁን ፡
መምህር ፡ ኪዳነ ፡ ማርያም ፡
አለቃ ፡ መርሻ ።
አለቃ ፡ ዓለሙ ፡

## የምድረ ፡ ሐማሴን ፡ ሊቃውንት ፡

አባ ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡
መምህር ፡ በኵረ ፡ ጽዮን ፡
አባ ፡ ስብሓት ፡ ለአብ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡
አባ ፡ ዓምደ ፡ ሃይማኖት ፡ ግርማ ፡ ጽዮን ፡
አባ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡
መልአከ ፡ ስብሓት ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስ ።

## የኢሉባቦር ፡ ሊቃውንት ።

አባ ፡ በላይ ፡ ደረሴ ።
መምህር ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ኃይለ ፡ ሰው ።

## የብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ ማሳሰቢያ ።

ለግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ዘኢትዮጵያ።

## ግርማዊ ፡ ሆይ ።

፩ኛ ፡ የመንፈሳዊ ፡ ዐቢይ ፡ ጉባኤ ፡ በኅዳር ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ከማታው ፡ በ፬ሰዓት ፡
ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፲፪ ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ በቅድስት ፡ ሥላሴ ፡
ገዳም ፡ ተሰብስበ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በእስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መካከል ፡
ስላለው ፡ የሹመት ፡ ሥልጣን ፡ ጉዳይ ፡ ንግግር ፡ ጀመረ ።

www.ethiopianorthodox.org

፪ኛ ፡ በዚሁ ፡ ወር ፡ በ፲፫ኛው ፡ ሐሙስ ፡ ቀን ፡ ተሰብስበ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ
የመንፈሳዊ፡ ጉባኤ፡ ሊቃውንት ከእስክንድርያው፡ ፓትርያርክ፡ ጋራ፡ የተላላኩትንና፡ የ
ቀባበሉትን፡ መልክት፤ እንዲሁም፡ ከእስክንድርያው፤ ፓትርያርክ፡ ጋራ፡ በየጊዜው፡ ያ
ረጉትን ፡ ሲያጠና፡ ቆየ ። ፫ኛ ፡ በዚሁ ፡ ወር፡ በ፲፯ኛው፡ ቀን ፡ ሰኞ ፡ ከጧቱ ፡ ከ፫
ሰዓት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፱ሰዓት ፡ ድረስ ፡ በተደረገው ፡ ስብሰባ ፡ ከግርማዊነትዎ
መልክተኞች ፡ ቃል ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ አሳብና ፡ ምኞት ፡ ከሰማ ፡ በኋላ
ከየአውራጃውና ፡ ከታላላቅ ፡ ገዳማት ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ተመርጠው ፡ የመጡት
መምህራንና ፡ ሊቃውንት ፡ እያንዳንዳቸው ፡ አሳባቸውን ፡ እየገለጡ ፡ ቃላቸውን
ሰጡ ።

## ቃላቸው ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

፩ኛ ፡ በኢ.ትዮጵያ ፡ ሊ.ቀ ፡ ጳጳሳትም ፡ ጳጳስም ፡ የሚሾመው ፡ ከኢ.ትዮጵያ
መምህራንና ፡ መነኮሳት ፡ ውስጥ ፡ ብቻ፡ እንዲሆን ፡ ብሎ ፡ መንፈሳዊ ፡ ጉባኤ
፲፱፻፴፯ ፡ ዓ ፡ ም፡ በሰኔ ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ያቀረበው ፡ ዋና ፡ ጥያቄ ፡ የሚገባ ፡ መሆኑን
ተስማምቶበታል ።

፪ኛ ፡ የእስክንድርያው ፡ ፓትርያርክ ፡ ይህን ፡ ጥያቄ፡ ያልተቀበሉት ፡ በማ
በቃ ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ መላው ፡ ጉባኤ ፡ ተረድቶታል ።

፫ኛ ፡ መላው ፡ ጉባኤ ፡ ለኢ.ትዮጵያ ፡ የሚገቡት ፡ ሊ.ቀ ፡ ጳጳሳት ፤ ከኢ.ትዮጵ
ተወላጆች ፡ ውስጥ ፡ እንዲመረጡ ፡ ማስፈለጉን ፡ ተስማምቶበታል ። ይኸውም
አሳብ ፡ በመንግሥታችን ፡ ወገን ፡ የተደገፈ ፡ ስለሆነ ፤ መንግሥታችን፡ መልእክተኞቹ
ልከ ፡ የኢ.ትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡ የጠየቀችውን፡ ሁሉ ፡ ከእስክንድርያው ፡ ፓ
ያርክ ፡ ተጠባባቂ ፡ ወይም ፡ ከጉባኤው ፡ ጋራ ፡ በሰላም ፡ ለመጨረስ ፡ ስለሆነ ፡ ይህ
በቶሎ ፡ ወደፍጻሜ ፡ እንዲያደርሱላት፡ የኢ.ትዮጵያ ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ግርማዊነት
በጸሎት ፡ እየደገፈች ፡ ትለምናለች ።

ነገር ፡ ግን ፤ ግርማዊነትዎ ፡ መላክተኞቹን ፡ ልከ ፡ ከሁን ፡ በፊት ፡ በዚሁ ፡ ነገ
ቤተ ፡ ክህነት ፡ የደከመችውን ፡ ያህል ፡ በነገሩ ፡ ደክመውበት፡ ከእስክንድርያው
ፓትርያርክ ፡ ተጠባባቂ ፡ ወይም ፡ ከጉባኤው ፤ ፍሬ ፡ ያለው ፡ ምላሽ ፡ ያልተገ
እንደሆን ፡ አሁን ፡ ዐቢይ ፡ ጉባኤያችን ፡ በቈረጠው ፡ ነገር ፡ ግርማዊነትዎ ፡ የተስማ
እንዲሆን ፡ ባለመጠራጠር ፡ እናምናለን ።

ኅዳር ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዲስ ፡ አበባ ።

ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ።

ዘመንበረ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።



ብፁዕ ፡ ሊ.ቀጳጳሳት ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ በዕጨጌነት ፡ መዓርግ ፡ ሳሉ ፡
ሚያዝያ ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለበዓለ ፡ ትንሣኤ ፡ ለምዕመናን ፡

## የተናገሩት ፡ ቃለ ፡ በረከት ።

መልእክት ፡ ዘፈነዋ ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ዘመንበረ ፡ ተክለ ፡ ሃይማ
ኖት ፡ ዘልህቀ ፡ በውስቴታ ፡ ለደብረ ፡ ሊ.ባኖስ ፡ ገብሩ ፡ ወሐዋርያሁ ፡ ለኢ.የሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ ኀበ ፡ ኵሎሙ ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ።

ዛሬ ፡ ሚያዝያ ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ የምናከብረው ፡ በዓል ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ፍጹም ፡
ክብር ፡ ያገኘበትና ፡ ከግብርናተ ፡ ዲያብሎስ ፡ ነፃ ፡ የወጣበት ፡ የጌታችን ፡ የኢ.የ
ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ትንሣኤ ፡ ስለሆነ ፡ ይህንን ፡ ቀን ፡ ስናከብር ፡ የሚሰማን ፡ ደስታ፡
ወሰን ፡ አለው ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ።

በዚህ ፡ ቀን ፡ ለአዳምና ፡ ለዘሩ ፡ የተመሠረተው ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ክብር ፡ ፍጡር፡
ለፍጡር ፡ ያደርገው ፡ ዘንድ ፡ የማይቻል ፡ አምላካዊ ፡ ልግሥና ፡ በመሆኑ ፤ ዓለም ፡
ይህንን ፡ ብድር ፡ ለመመለስ ፡ የሚችለው ፡ ጌታችን ፡ ኢ.የሱስ ፡ ክርስቶስ « አነ ፡
ውእቱ ፡ ፍኖት ፡ ጽድቅ ፡ ወሕይወት » ብሎ ፡ በመለከተው ፡ መንገድ ፡ ሒዶ ፡ በሃ
ይማኖት ፡ ፍጹም ፡ በመሆንና ፡ በምግባር ፡ ምሉ ፡ በመሆን ፡ ነው ። የስንዴ ፡ ቅንጣት ፡
በመሬት ፡ ላይ ፡ ወድቃ ፡ ከሞተች ፡ በኋላ ፡ ተነሥታ ፡ ብዙ ፡ ፍሬ ፡ ለማፍራት ፡ እን
ደሚቻላት ፤ ሰውም ፡ የሃይማኖት ፡ ፍሬ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ ሙቶ ፡ በመሬት ፡
ላይ ፡ ከወደቀ ፡ በኋላ፡ ተነሥቶ ፡ የሚያፈራው፡ ትንሣኤ ፡ ፍጻሜና ፡ ኅልፈት ፡ የሌለበት ፡
ስለሆነ ፡ ዛሬ ፡ በዚህ ፡ በኀላፊው ፡ ዓለም ፡ የማያልፍ ፡ ሥራ ፡ ሠርተን ፡ ለመጠቀም ፡
እንችል ፡ የጌታችንን ፡ የኢ.የሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ፍኖተ ፡ መስቀል ፡ መከተልና ፤
ሕማሙን ፡ ሞቱን ፡ ትንሣኤውን ፡ ዕርገቱን ፤ ዳግመኛ ፡ መምጣቱን ፡ እያሰቡ ፡
ቅዱስ፡ ጴጥሮስ ፡ «ድልዋኒከሙ፡ ንበሩ» ፡ ብሎ ፡ እንደነገረን ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ዕለተ ፡ ፍጻ
ሜውን ፡ መጠባበቅ ፡ ለትንሣኤ ፡ ዘለክብር ፡ የሚያበቃ ፡ መሆኑን ፡ ሕዝበ ፡ ክርስ
ቲያን ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ ማሰብ ፡ አለበት ።

ጌታችን ፡ ኢ.የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ልዑል ፡ ባሕርዩን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ሰው ፡
የሆነበትንና ፡ እስከ ፡ መሰቀል ፡ የደረሰበትን ፡ ስንመረምር ፤ ዓለምን ፡ ከፈጠረበት፡
ጥበቡ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ያዳነበት ፡ ጥበቡ ፡ ይበልጣልና ፡ „አዕመቂሁ ፡ ለብዕለ ፡ ጥበ
ቢሁ ፡ ወአእምሮቱ ፡ ለእግዚአብሔር" ፡ ብለን ፡ አንክሮዋችንን ፡ ከመወሰን ፡ በቀር፡
ቸርነቱን ፡ ዘርዝሮ ፡ ለመናገር ፡ አንችልም ። ዓለምን ፡ ለይኩን ፡ ብሎ ፡ እንደፈጠረ፡
ሰውንም ፡ ዳን ፡ ብሎ ፡ በቃሉ ፡ ብቻ ፡ ለማዳን ፡ ሲቻለው ፤ ምክንያተ ፡ ድኂኑን ፡
እሱ ፡ ራሱ ፡ መከራ ፡ በመቀበልና ፡ ሙቶ ፡ በመነሣት ፡ ያደረገው ፤ የሰው ፡ ፍቅር፡
ስለአገበረው ፡ ነው ። የዕለት ፡ ፅንስ ፡ በመሆን ፡ የጀመረውን ፡ የቸርነት ፡ ሥራ ፡
በመስቀል ፡ ላይ ፡ ተፈጸመ ፡ ኵሉ ፡ ብሎ ፡ እስኪጨርሰውና ፡ የአዳምን ፡ የክብ
ሩን ፡ ፍጻሜ ፡ በትንሣኤ ፡ እስኪያጠቃልለው ፡ ድረስ ፡ የተቀበላቸው ፡ ፀዋትወ ፡
መከራዎች ፡ እያንዳንዳቸው ፡ የሰውን ፡ ፍሬ ፡ ክብርና ፡ መንፈሳዊ ፡ ሀብት ፡ የሚ

www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

ገልጹ ፡ ናቸው ። የአምላክን ፡ ቃል ፡ አንዲቱን ፣ በማፍረስ ፡ ምክንያት ፡ ከአንዲ
የበለስ ፡ ቀጠል ፡ ቅንጣቢ ፣ በፈሰሰው ፡ ደም ፤ በተፈጥሮ ፡ ንጹሕ ፡ የነበረው ፡ የሰው
ሕይወት ፡ ስለተጓደፈ ፤ አዳም ፡ አትብላ ፡ ከተባለው ፡ በለስ ፡ በበላ ፡ ቀን ፡ የሞት
ሞት ፡ እንዲሞት ፡ የተፈረደው ፡ አምላካዊ ፡ ፍርድ ፡ እንዳይፈርስና ፡ ምንም ፡ በደለኛ
ቢሆን ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ እንደተፈረደበት ፡ እንዳይቀር ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክ
ስቶስ ፡ ይህንን ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ተቀብሎ ፡ በሚያፈስሰው ፡ ደሙ ፡ የአ
ምን ፡ ፍዳ ፡ ለማስወገድና ፡ አዳምን ፡ ወደቀደመ ፡ ክብሩ ፡ ለመመለስ ፡ ሰው
እስከመሆን ፡ ደረሰ ።

ሰውም ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ አልቀረም ። ሕገ ፡ ወንጌልን ፡ አዘጋጅቶ ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ
ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ሠርቶና ፡ አሠርቶ ፡ ፈጽሞና ፡ አስፈጽሞ ፡ የመጣሁበት ፡ ፍ
ሜው ፡ ሰው ፡ በመሆን ፡ ብቻ ፡ ይወሰን ፡ ሳይል ፤ መራራውን ፡ የሞት ፡ ጽዋዕን
ለመቀበል ፡ ፈቀደ ። የሞትንም ፡ ጽዋዕ ፡ ለመቅመስ ፡ ያለመከራ ፡ በጥቂት ፡ ወይ
ባንድ ፡ ዓይነት ፡ መከራ ፡ ልሙት ፡ አላለም ። በፍርድ ፡ አደባባይ ፡ መ
ምና ፡ መወቀስ ፡ መገፈፍና ፡ መገረፍና ፡ መመታት ፡ መስቀልን ፡ ተሸክሞ ፡ መ
ድና ፡ መገፋት ፡ የርኩሳንን ፡ ምራቅ ፡ መቀበልና ፡ ውቅያኖሶችን ፡ የፈጠረ
ሲሆን ፤ መራራ ፡ ሐሞትን ፡ ለጥማቱ ፡ መቀበል ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ የትዕግሥትና
የችሎታ ፡ በላይ ፡ ነው ።

ከዚህም ፡ የበለጠ ፡ ዕፅፍ ፡ ድርብ ፡ የሆነውን ፡ የግፍ ፡ ግፍ ፡ ሁሉ ፡ ከ
ቀበለ ፡ በኋላ ፤ በዕለተ ፡ ዐርብ ፡ አጋዜ ፡ ዓለም ፡ የሆነ ፡ እጁን ፡ በመስቀል ፡ ላ
ዘርግቶ ፡ በፈቃዱ ፡ ቅድስት ፡ ነፍሱን ፡ ከቅዱስ ፡ ሥጋው ፡ ለየ ። በአካለ ፡ ነፍስ
ወደሲኦል ፡ ወርዶ ፡ በአዳምና ፡ በሔዋን ፡ በልጆቻቸውም ፡ ሁሉ ፡ ተጽፎ ፡ የነበረው
ስመ ፡ ግብርናት ፡ አጥፍቶ ፡ በሲኦል ፡ ተግዘው ፡ የነበሩትን ፡ ነፍሳት ፡ አውጥቶ
ሁለተኛ ፡ ከገቡ ፡ መውጣት ፤ ካገኙ ፡ ማጣት ፡ የሌለባትን ፡ የደስታ ፡ ገነትን
አወረሳቸው ። (ቈላስይስ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፳) ፡ በመስቀል ፡ ባፈሰሰው ፡ ደሙ ፡ በሰማይና
በምድር ፡ ያሉትን ፡ አስታረቀ ።

በዕለተ ፡ ዐርብ ፡ በሠራው ፡ ሥራ ፡ የዕዳችንን ፡ ደብዳቤ ፡ ከባላጋራችን ፡ እጅ
አጠፋልን ። ከመካከላችን ፡ አራቀው ፡ በመስቀሉም ፡ ቸነከረው ፡ ልብሱን ፡ በ
ገፈፉ ፡ ራቍቱን ፡ በመሰቀሉ ፡ የተዯሙትንና ፡ የተሸሩትን ፡ አሳፈራቸው ፤ በዚህ
ቀን ፡ ፀሐይ ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ የተሰቀለው ፡ ፈጣሪው ፡ መሆኑን ፡ ዐውቆ
ጨለማ ፡ ሆነ ፤ ጨረቃም ፡ ደም ፡ ለበሰች ፡ ከዋክብትም ፡ ረገፉ ፡ ምድር ፡ ተ
ወጠች ፤ መቃብራት ፡ ተከፈቱ ፡ ሙታን ፡ ተነሡ ። በዚህ ፡ ቀን ፡ ያልተደረገ ፡ ተ
ምራትና ፡ ያልታየ ፡ ምልክት ፡ የለም ። ሀርብ ፡ በሠርክ ፡ በአካለ ፡ ነፍስ ወደ
አል ፡ ወርዶ ፡ «እለ ፡ ውስተ ፡ ሲኦል ፡ ፃኡ ፡ ወእለ ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡ ተከሠ
ወርእዩ ፡ ዐቢየ ፡ ብርሃነ» ፡ ብሎ ፡ ነፍሳትን ፡ ካወጣ ፡ በኋላ ፡ እሑድ ፡ በመንፈቀ
ሌሊት ፡ መቃብር ፡ ክፈቱልኝ ፡ መግነዝ ፡ ፍቱልኝ ፡ ሳይል ፡ በገዛ ፡ ሥልጣኑ ፡ ተነሣ
ቅዱስ ፡ ዳዊት ፡ «ከእንቅልፍ ፡ እንደሚነሣ ፡ ፈጥኖ ፡ ተነሣ» ፡ ብሎ ፡ እንደተ



ረው ፡ ሙስና ፡ መቃብርን ፡ አጥፍቶ ፡ ተነሣ ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የትንሣኤው ፡ ብር
ሃን ፡ ለዓለም ፡ ሁሉ ፡ ተገለጸ ። ብርሃነ ፡ ትንሣኤውም ፡ ተገልጦ ፡ በዐይነ ፡ ልቡናቸው ፡
ስለታያቸው ፡ አሁን ፡ በቅርቡ ፡ ጊዜ ፡ በ፲፱፻፴ ፤ ዓ ፡ ም ፡ ከመስከረም ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡
ጀምሮ ፡ እስከ ፤ መጋቢት ፡ ፬ ቀን ፡ ድረስ ፡ (በከምባታ ፡ አውራጃ) ፡ በኢትዮጵያ ፡ ኦርቶ
ዶክስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስብከት ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሀብቱ ፡ የሳባቸው ፡
በረድኤቱ ፡ ያቀረባቸው ፡ በወርቀ ፡ ደሙ ፡ የዋጃቸው ፡ ፩፻፶፩ሺ፭፻፲ ፡ ምእመናን ፡
አሙኑ ፡ ተጠመቁ ።

በነቢዩ ፡ ኤርምያስ ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ለእሥራኤል ፡ ወገኖች ፡ የም
ሠራት ፡ ሥርዓት ፡ ይህች ፡ ናት ። ሕጌን ፡ በልባቸው ፡ አሳድረዋለሁ ፤ በሕሊና
ቸውም ፡ እጽፈዋለሁ ፡ አባታቸው ፡ እሆናቸዋለሁ ፡ እነሱም ፡ ልጆቼ ፡ ይሆኑኛል ።
ከእንግዴህ ፡ ወዲህ ፡ ወንድም ፡ ወንድሞቹን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ዕወቁት ፡ ብሎ ፡
አያስተምራቸውም ። ሁሉም ፡ ታናሹም ፡ ታላቁም ፡ ያውቁኛልና ፡ ይቅር ፡ እላቸው ፡
ዘንድ ፡ ኃጢአታቸውንም ፡ አስተሠርይላቸው ፡ ዘንድ ። ኃጢአታቸውንም ፡ አላስብ
ባቸውም ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ይደርስ ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፤
ይህን ፡ የሚያህሉ ፡ ምእመናን ፡ በክርስቶስ ፡ አምነው ፡ ልጅነትን ፡ አግኝተው ፡ ደስ
ስላላቸው ፤ የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እጆቿን ፡ ዘርግታ ፡
ደስታዋን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ታቀርባለች ።

ስለዚህ ፤ ይህ ፡ ቀን ፡ የሰው ፡ ፍጹም ፡ ክብሩ ፡ የተመሠረተበት ፤ የዲያብሎስ ፡
ሥልጣን ፡ የወደቀበትና ፡ የተሻረበት ፡ ቀን ፡ ስለሆነ ፤ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ትንሣኤ ፡ ዘለክ
ብረን ፡ ወደሚያድለው ፡ ወደጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እደ ፡ ሕሊናውን ፡
ሰቅሎ ፡ ምስጋናን ፡ ማቅረብ ፡ ይገባዋል ። ይህ ፡ ቀን ፡ አዳም ፡ ከፈጣሪው ፡ የታዘ
ዘውን ፡ ትእዛዝ ፡ በመተላለፍ ፡ ተፈርዶበት ፡ ከነበረው ፡ ከሞት ፡ ፍርድ ፡ ወደዘለዓ
ለማዊ ፡ ሕይወት ፡ የተመለሰበት ፡ ቀን ፡ ነው ። ይህ ፡ ቀን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ ከፅንስ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ መስቀል ፡ ድረስ ፡ ለሠራው ፡ ቸርነት ፡ ፍጻሜ ፡
ነው ። ይህ ፡ ቀን ፡ ለዓለም ፡ ሁሉ ፡ ሰላም ፡ የወረደበትና ፡ ፍጡር ፡ ከፈጣሪው ፡
ፍጹም ፡ ይቅርታ ፡ ያገኝበት ፡ ቀን ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተናገርነው ፡ መሠረት ፡
ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ደሙን ፡ አፍስሶ ፡ ሰውነቱን ፡ ክሶ ፡ ያስታረቀውና ፡
ሰላም ፡ የመሠረተለት ፡ ዓለም ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ታርቆና ፡ ከተቀባበው ፡ ደም ፡ ንጹሕ ፡
ሆኖ ፡ ለመኖር ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የምታቀርበው ፡ ጸሎት ፡ የማያ
ቋርጥ ፡ ነው ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለዓለም ፡ ቤዛ ፡ ካፈሰሰው ፡ ደም ፡
በቀር ፡ ዓለምን ፡ የሚቀድሰው ፡ ሌላ ፡ ደም ፡ የለምና ፡ በክርስቶስ ፡ ደም ፡ የተቀደ
ሰው ፡ ዓለም ፡ ዳግመኛ ፡ በሰው ፡ ደም ፡ እንዳይረክስ ፡ ከሰላምና ፡ ከፍቅር ፡ በቀር ፡
ሌላ ፡ የሚጠቅም ፡ ነገር ፡ እንደሌለ ፡ ማወቅ ፡ ያስፈልጋል ። እንዲሁም ፡ ጌታችን ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በስሜ ፡ ሁለት ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ ባሉበት ፡ እኔም ፡ በዚያ ፡
እኖራለሁ ፡ ብሏልና ፡ ወደፊት ፡ በሚደረገው ፡ በዓለም ፡ የሰላም ፡ ጉባኤ ፡ መካ
ከል ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ ተገኝቶ ፡ ፍጹም ፡ ሰላም ፡ እንዲመሠረትና ፡ ለአደላዳዮች ፡

www.ethiopianorthodox.org

ፍጹም ፡ ፍርዱን ፡ እንዲገልጽ ፡ ጉባኤው ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ማደሪያ ፡ ሆኖ ፡ መ
ኘት ፡ አለበት ። ከሙታን ፡ የተነሣው ፤ የጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋውና
ይቅርታው ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ይውረድ ። እምይእዜሰ ፡ ይኩን ፡ ሰላም ፡ አሜን ።

ሚያዝያ ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡

ብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ስለትንሣኤ ፡ በዓል ፡ ለሕዝብ ፡ ያሰሙት
ቃለ ፡ በረከት ።

ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቡሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ፡ ዘወለ
ደነ ፡ በብዝኃ ፡ ምሕረቱ ፡ ለተስፋ ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ንሐዩ ፡ በትንሣኤቱ ፡ ለኢየሱስ
ክርስቶስ ፡ እምነ ፡ ምዉታን ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፤ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ በመነሣቱ ፡ ሕይወት
በምናገኝበት ፡ ተስፋ ፤ በቸርነቱ ፡ ብዛት ፡ የወለደን ፡ የጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክር
ስቶስ ፡ አባት ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ።

መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሙታን ፡ በመነሣቱ ፡ የማይጠፋውን
የማይለወጠውንና ፡ የማያልፈውን ፡ ለእኛና ፡ ለእናንተ ፡ በሰማይ ፡ የተጠበቀውን
የመንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ክብር ፡ ለመውረስ ፡ ሕይወትን ፡ በምናገኝበት ፡ ተስፋ
በቸርነቱ ፡ ብዛት ፡ የወለደን ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አባት ፡ እግዚአብሔር
ይመስገን ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰውን ፡ ወደ ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ክብር
ለማድረስ ፡ በሞቱ ፡ የፈጸመለትን ፡ ቸርነቱን ፡ በትንሣኤው ፡ ስለገለጸለት ፤ እስከ
ዕለተ ፡ ምጽአቱ ፡ የሚነሣው ፡ መላው ፡ የሰው ፡ ዘርእ ፡ በጌታችን ፡ ሞትና ፡ ትን
ሣኤ ፡ የወረሰውን ፡ ተስፋና ፡ ወደፊት ፡ በሃይማኖቱ ፡ ደጋፊነትና ፡ በምግባሩ
ቀናነት ፡ እንዲያገኘው ፡ የሚጠብቀውን ፡ ተስፋውን ፡ ስናስታውስ ፤ ሥራችን
ሁሉ በማይነዋወጽ ፡ በሃይማኖት ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ የጸና ፡ ይሆናል ።

ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ የትንሣኤውን ፡ ምሥጢር ፡ ከሙሉ ፡ በክፍሉ ፡ እንናገራለን ። ከሁ
ለት ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ከሁለት ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ የሆነ ፡ ክር
ስቶስ ፡ በሲኦል ፡ የተጋዙትን ፡ ነፍሳት ፡ ለማውጣት ፡ በአካለ ፡ ነፍስ ፡ ወደሲኦል
ወረደ ። ወዲህም ፡ በአካለ ፡ ሥጋ ፡ በከርሠ ፡ መቃብር ፡ አደረ ። ይህም ፡ ሲሆን
በዘባነ ፡ ኪሩብ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ከአብ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋር ፡ ይሠለሳል
ይቀደሳል ፡ ብንል ፡ ተዋሕዶውን ፡ በአንክሮ ፡ በተዘክሮ ፡ አስተያየት ፡ ከመመለ
ከታችን ፡ በላይ ፡ ዐይነ ፡ ልቡናችን ፡ መለኮታዊ ፡ ስፋቱንና ፡ ርቀቱን ኪማስተ
ዋል ፡ ሳያፈገፍግ ፡ ነው ።

ሙስና ፡ መቃብርንም ፡ አጥፍቶና ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ሆኖ ፡ በመነሣቱ ፡ የተዋ
ሕዶውንና የአምላክነቱን ፡ እውነተኛነት ፡ ንጹሕ ፡ በሆነ ሠሌዳ ፡ አእምሮ ላይ ፡ ቀርጾ
የምሥጢሩን ፡ ጉልህነት ፡ እንድናየው ፡ አድርጎዋል ።



እንግዴህ ፡ ሥግው ፡ ቃል ፡ (ክርስቶስ) ፡ በፈቃዱ ፡ ተሰቀለ ፤ በፈቃዱ ፡ ሞተ ፤ በፈቃዱ ፡ ተቀበረ ፤ በራሱ ፡ ሥልጣን ፡ ተነሣ ፡ እያልን ፡ ሥራውን ፡ ሁሉ ፡ በተዋሕዶ ፡ ፈጸመ ፡ የምንልበትን ፡ የሃይማኖታችንን ፡ መሠረት ፡ ለሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ ስንገልጽ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኃያል ፡ ዘአልቦ ፡ ድካም ፤ ጻድቅ ፡ ዘአልቦ ፡ ኃጢአት ፡ ሲሆን ፡ በኛ ፡ ኃጢአት ፡ በመልዕልተ ፡ መስቀል ፡ ተሰቅሎ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፤ በዚህች ፡ በዛሬ ፡ ቀን ፡ ከሞት ፡ ወደ ፡ ሕይወት ፡ ተመልሶ ፡ ተነሣ ። በትንሣኤው ፡ የሚያምኑት ፡ ሁሉ ፡ እንዲታደሱና ፡ እንዲከብሩ ፡ ተነሣ ። በትንሣኤውም ፡ የተገኘ ፡ የድኅነትን ፡ ፍሬ ፡ ለወገኖቹ ፡ በመስጠቱ ፡ ተመሰገነ ።

ከተነሣም ፡ በኋላ ፤ «የሰማይና ፡ የምድር ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጠኝ» ፡ በማለቱ ፡ ያመኑበትም ፡ ያላመኑበትም ፡ ቢሆኑ ፡ በዐጸደ ፡ ሰማይና ፡ በዐጸደ ፡ ምድር ፡ ያሉ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሥልጣን ፡ በታች ፡ እንደሆኑ ፡ ታወቀ ፡ ተረዳ ።

መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በከርሠ ፡ መቃብር ፡ ሠስት ፡ መዓልት ፡ ሠስት ፡ ሌሊት ፡ አድሮ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፤ በመጀመሪያ ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ሲያለቅሱ ፡ ለነበሩ ፡ ከገሊላ ፡ ለተከተሉት ፡ ሴቶች ፡ ተገለጸላቸው ።

ከትንሣኤውም ፡ በኋላ ፡ መድኃኒታችን ፡ ትንሣኤውን ፡ ለሚመሰክሩለት ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለብዙ ፡ ሕዝብ ፡ አልታየም ።

ሲገለጥላቸውም ፤ በሚያስደንቅና ፡ ደስ ፡ በሚያሰኝ ፡ አኳኋን ፡ ለልቡና ፡ አንክሮ ፤ ለነፍስ ፡ ጠል ፡ በሚሆን ፡ መገለጥ ፡ ሊገለጥላቸውና ፡ ሊያውቁት ፡ ሲወዱ ፡ አእምሮአቸው ፡ ከማወቅ ፡ ይገታ ፡ ነበረ ። ሉቃ ፡ ፳፬ ። ፲፮ ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ለማመን ፡ የሚያበቃ ፡ ምልክት ፡ የተወጋ ፡ ጎኑን ፤ የተቸነከረ ፡ እጁን ፡ እግሩን ፡ ዳስሰው ፡ እንዲያውቁት ፡ አደረጋቸው ። ከትንሣኤ ፡ በኋላ ፡ ምድራዊ ፡ መብልና ፡ መጠጥ ፡ የማያሻው ፡ ሲሆን ፤ በርግጥ ፡ እንደተነሣ ፡ ለማሳመን ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ ይበላ ፡ ይጠጣ ፡ ነበር ።

ለሚታያቸው ፡ ሁሉ ፡ በየበኩላቸው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አስተያየት ፡ ይታያቸው ፡ ነበር ። ለሴቶቹ ፡ ከታያቸው ፡ በኋላ ፤ ለጴጥሮስ ፡ ታየ ። ቀጥሎ ፡ ወደ ፡ ኢማሁስ ፡ በመሔዱ ፡ ለቀለዮጳና ፡ ለሌሎቹም ታየ ።

እሑድ ፡ ማታም ፤ ትንሣኤውን ፡ ላላዩ ፡ ለቀሩት ፡ ሐዋርያት ፡ በጥብርያዶስ ፡ ባሕር ፡ ታየ ። ዳግመኛም ፡ ከመስቀሉ ፡ እግር ፡ ለተነሡ ፡ ካምስት ፡ መቶ ፡ ለሚበዙ ፡ ሰዎች ፡ ተገለጠላቸው ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ለያዕቆብ ፤ በመጨረሻም ፡ በደብረ ፡ ዘይት ፡ ተሰብስበው ፡ ሳሉ ፡ ለሐዋርያት ፡ ሁሉ ፡ ተገለጠላቸው ።

ሐዋርያትም ፡ ይህንና ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ በዐይናቸው ፡ አይተው ፤ በእጃቸው ፡ ዳስሰው ፡ ስላመኑና ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስለተማወቁ ፡ ከግላ ፡ ዓለም ፡ ስለ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ተላቀቁ ፣ በስብከታቸው ፡ ሁሉ ፡ እናንተ ፡ ሰቅላችሁ ፡ የገደላችሁት ፡ ኢየሱስ ፡ የሞትን ፡ ማሠሪያ ፡ ፈቶ ፡ ተነሣ ።

ሞት ፡ ሁለተኛ ፡ ሊይዘው ፡ አይችልም ፡ ይሉ ፡ ነበረ ።

ይህ ፡ የመድኀኒታችን ፡ ትንሣኤ ፡ መለኮታዊ ፡ ሕይወት ፡ እንደሆነ ፡ ልንረዳ ፣ አላዋቆችና ፡ ድሆች ፡ በተባሉ ፣ ወገን ፡ ዘመድ ፡ በሌላቸው ፡ በሐዋርያት ፡ ስብከት ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ተዘረጋ ። ትንሣኤውን ፡ እሑድ ፡ ቀን ፡ ማድረጉም ፡ ዓለምን ፡ የፈጠረ ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ ነበረና ፡ በእሑድ ፡ የፈጠረውን ፡ ፍጥረት ፡ መልሶ ፡ እንዳደሰው ፡ ያስረዳናል ።

መጀመሪያም ፡ መዋዕለ ፡ ጾሙ ፡ ሲገባ ፡ በተናገርነው ፡ ቃለ ፡ ምዕዳን ፡ ካል ጾሙ ፡ ፋሲካ ፣ ካላዘኑ ፡ ደስታ ፡ የለምና ፡ ዛሬ ፡ በጊዜው ፡ ካልጾምን ፡ ካልጸለይን ፡ ብርሃነ ፡ ትንሣኤውን ፡ ባየን ፡ ጊዜ ፡ ደስታችን ፡ ወዴት ፡ አለ ? ብለን ፡ እንደ ፡ ነገ ርናችሁ ፡ ይኸውና ፣ መዋዕለ ፡ ጾሙን ፡ በሰላም ፡ አስፈጽሞ ፡ ወደዚች ፡ ወደተመረጠ ችው ፡ ዕለተ ፡ ትንሣኤ ፡ አድርሶናል ።

እነሆ ፡ መታዘዝ ፡ ከመሥዋዕት ፡ ይበልጣል ። (፩ ፡ ሳሙ ፡ ፲፭ ፡ ፳፪ ።) እንደተ ባለ ፡ እናንተም ፡ ስለጾምና ፡ ስለ ፡ ሃይማኖታችሁ ፡ አጠባበቅ ፡ ያስገነዘብናችሁን ፡ ጠብቃችሁ ፡ ተገኝታችሁ ፡ እንደሆነ ፡ በጥቂት ፡ ትሩፋት ፡ ብዙ ፡ ዋጋ ፡ መስጠት ልማዱ ፡ የሆነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለወዳጆቹ ፡ አዘጋጅቶ ፡ ላቆያት ፡ ለመንግሥተ ፡ ሰማ ያት ፡ ባለቤቶች ፡ ያደርጋችኋል ።

አሁንም ፡ በዚህ ፡ በመዋዕለ ፡ ኀምሳ ፡ መንፈሳዊ ፡ በዓል ፡ የሚሰማችሁ ፡ ደስታ ፣ በእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ቸርነት ፣ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፍቅር ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አጋዥነት ፡ ሕይወትን ፡ የተመላ ፡ ይሁንላችሁ ።

አ ሜ ን ።

ብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ፡ም፡ የካቲት ፡ ፳፡ ቀን ፡ በዕ ጨጌነታቸው፡ስለዐቢይ ፡ ጾም ፡ የተናገሩት ፡ ቃለ ፡ ምዕዳን ።

በወልድ ፡ ውሉድ ፡ በክርስቶስ ፡ ክርስቲያን ፡ ተብላችሁ ፡ የምትጠሩ ፡ ምእመ ናን ፡ ሆይ ፣ የዐቢይ ፡ ጾም ፡ መነትው ፡ በሆነው፡በዛሬው ፡ ቀን ፡ ከክርስቲያናዊ ፡ ተግባር ፡ አንዱ ፡ የሆነውን ፡ የጾምን ፡ ጠቃሚነት ፡ የማሰማችሁ ፡ ስለሆነ ፣ ዕዝነ ፡ ልቡ ናችሁን ፡ አንቅታችሁ ፡ እንድታዳምጡኝ ፡ አስቀድሜ ፡ እለምናችኋለሁ ።

አስተበቍዐክሙ ፡ አኃዊነ ፡ ተዐቀብዎሙ ፡ ለእለ ፡ ይገብሩ ፡ ሐከከ ፡ ወያመጽኡ ፡ ካህደ ፡ ላዕለ ፡ ትምህርት ፡ ዘተመሀርክሙ ፡ ትግበሩ ፡ ወተገሐሠዎሙ ፡ እስመ ፡ ለከርሦሙ ፡ ይትቀነዩ ፡ ወአኮ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወበሂጣነ ፡ ነገር ፡ ወበተየውሆ ፡ ያስሕትዎሙ ፡ ለብዙኃን ፣ የዋሃን ። (ወንድሞቻችን ፡ ጸብ ፡ ክር ክር ፡ የሚያደርጉትን ፣ በተማራችሁት ፡ ትምህርት ፡ ላይ ፡ ጥርጥር ፡ የሚያመጡትን፡ ሰዎች ፡ ተጠባበቁዋቸው ፡ ብዬ ፡ እማልዳችኋለሁ ፡ ተለይዋቸው ። ለጌታችን ፡ ለኢየ



ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያይደለ ፡ ለሆዳቸው ፡ ይገዛሉና ፣ በነገር ፡ ማታለልና ፡ የዋህም ፡ በመምሰል ፡ ብዙዎችን ፡ ሰዎች ፡ ያስታሉ ። አሁን ፡ በዚህ ፡ አርእስት ፡ መነሣታችን ፡ ጾም ፡ የበጎ ፡ ምግባር ፡ መሠረት ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፣ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋን ፡ ያለልክ ፡ ከመውደድ ፡ የተነሣ ፡ የማይጠቅም ፡ እያስመሰሉ ፡ የምእመናንን ፡ ሕሊና ፡ የሚያበክኑ ፡ በልዩ ፡ ልዩም ፡ ማሳሳቻ ፡ ወደክፉ ፡ ግብራቸው ፡ የሚስቧቸው ፡ ስለማ ይታጡ ፡ ለማስጠንቀቅ ፡ መሆኑን ፡ አንሠውርም ። በአርእስቱም ፡ የተመለከተው ፡ ከልባችን ፡ አንቅተነው ፡ ያይደለ ፡ ሐዋርያው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ወደፊልጵስዩስና ፡ ወደሮሜ ፡ ሰዎች ፡ በጻፈው ፡ መልእክቱ ፡ የሚገኝ ፡ ነው ።

ሮሜም ፡ ፲፯ ፡ ቍ ፡ ፲፯–፲፰ ፡ ፊልጵ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፲፱ ፡ ይህንንም ፡ ለማስረ ዳት ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ብዙ ፡ ምስክር ፡ ቢኖር ፡ ሰሚዎችን ፡ እንዳያታክት ፡ ስንል ፡ አን ዳንዶቹን ፡ ብቻ ፡ ልንገልጽላችሁ ፡ እንወዳለን ። የምንገልጸውም ፡ ጾም ፡ የበጎ ፡ ምግ ባር ፡ መሠረት ፡ መሆኑን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ እንዲሁም ፡ መብልና ፡ መጠጥም ፡ የኃጢ አት ፡ መሠረቶች ፡ መሆናቸውን ፡ ጭምር ፡ ለማስረዳት ፡ ነው ።

፩ኛ/ ኢሳይያስ ፡ መጠጥና ፡ ዘፈን ፡ ሰዎችን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ እንደሚያርቃ ቸውና ፡ ወደጕዳት ፡ እንደሚያደርሳቸው፡ሲያጠይቅ ፡ «አሌ ፡ ሎሙ ፡ ለእለ ፡ ይገይሡ፡ ቤተ ፡ መያሲ ፡ ወይውዕሉ ፡ ቤተ ፡ ስታይ ፡ ወያነድዶሙ ፡ ወይን ፡ ወይሰትይዎ ፡ ለወ ይን ፡ እንዘ ፡ የኀልዩ ፡ በመሰንቆ ፡ ወበከበሮ ፡ ወበእንዚራ ፡ ይሰትይዎ ፡ ለወይን ፡ ወኢ ይኔጽሩ ፡ ግብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢይሬእዩ ፡ ተግባረ ፡ እደዊሁ ፡ ኢሳ ፡ ም ፡ ፭፡ቍ፡ ፲፩–፲፪ ። በማለዳ ፡ ወደመሸታ ፡ ቤት ፡ ለሚገሠግሡና ፡ መጠጡ ፡ እስኪያቃጥላቸው ፡ ድረስ ፡ ሲጠጡ ፡ ለሚውሉ ፡ ሰዎች ፡ ወዮላቸው ። ሲጠጡም ፡ በመሰንቆ ፡ በከበሮና ፡ በበገናም ፡ እየዘፈኑ ፡ ይጠጡታል ። የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ ግን ፡ አይመለከቱም ። የእጁንም ፡ ሥራ ፡ አያዩም ፡ ሲል ፡ በወዮታና ፡ በአሳዛኝ ፡ ንግግር ፡ ገልጾታል ።

፪ኛ ሐዋርያው ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ እንደነዚሁ ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ ሲወቅስና ፡ ሲያስጠነቅቅ ፡ "እስመ ፡ የአክለክሙ ፡ ዘኀለፈ ፡ መዋዕል ፡ ዘገበርክሙ ፡ በቱ ፡ ፈቃ ዶሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ዝሙተ ፤ ወፍትወተ ፡ ወስክረተ ፡ ወስጥየተ ፡ ወስታየ ፡ ዘእን በለ ፡ ግዕዝ ፡ ወአፍቅሮ ፡ አማልክት ፡ ዑቁ ፡ እንከ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ምግባር ፡ ኢት ሩፁ ፡ ወነኪራነ ፡ ኩኑ ፡ እምኔሃ ፡ ለይእቲ ፡ ፍኖት ፡ ወእምነ ፡ ውእቱ ፡ ምግባር ፡ ዘአልበ ፡ አቅም» ። የአሕዛብን ፡ ፈቃዳቸውን ፡ ዝሙትንና ፡ ክፉ ፡ ፈቃድን ፡ ስካርንና ፡ ወድቆ ፡ ማደርን ፡ ያለልክ ፡ መጠጣትንና ፡ ጣዖት ፡ ማምለክን ፡ የሠራችሁበት ፡ ያለፈው ፡ ዘመን ፡ ይበቃችኋልና ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ወደዚህ ፡ ሥራ ፡ እንዳትሔዱ፡ ዕወቁ ። ከእንደዚህ ፡ ያለችውም ፡ መንገድና ፡ መጠን ፡ ከሌለው ፡ ከዚህ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ልዩ ፣ ሁኑ ፡ ሲል ፡ አስረድቷል ። ፩ ፡ ጴ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፫–፬ ።

፫ኛ/ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሉቃስ ፡ ወንጌል ፡ "ዑቁ ፡ ርእሰክሙ ፡ ኢታክብዱ ፡ ልበክሙ ፡ በስታይ ፡ ወበፈጊዕ ፡ ወበሐልዮ ፡ መንበርት ፡ ወትበጽሐ ክሙ ፡ ይእቲ ፡ ዕለት ፡ ግብተ ፡ ከመ ፡ መሥገርት፤እንተ ፡ ትወርድ ፡ ዲበ ፡ ኵሎሙ

www.ethiopianorthodox.org

እለ ፡ ይነብሩ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ ትግሁ ፡ እንከ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ ከመ ፡ ትክሀሉ ፡ አም
ስጠ ፡ በጸሎትክሙ ፡ እምነ ፡ ኵሉ ፡ ዝንቱ ፡ ዘይመጽእ ፡ ወትቁሙ ፡ ቅድሜሁ ፡
ለወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው" ፡ ልባችሁን ፤ በተድላ ፡ ደስታና ፡ በስካር ፡ ሥጋዊ ፡
ትዳራችሁንም ፡ ብቻ ፡ በማሰብ ፡ እንዳታደነድኑትና ፡ በምድር ፡ በሚኖሩት ፡ ሁሉ
ላይ ፡ እንደወጥመድ ፡ የምትወርድ ፡ ያቺ ፡ ቀን ፡ በድንገት ፡ እንዳትደርስባችሁ ፡
ራሳችሁን ፡ ጠብቁ ። በጸሎታችሁም ፡ ከሚመጣው ፡ መከራ ፡ ሁሉ ፡ ማምለጥና ፡
በወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ክርስቶስ ፡ ፊት ፡ መቆም ፡ ትችሉ ፡ ዘንድ ፡ ትጉ ፡ ሲል ፡
አምላካዊ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ሰጥቷል ። ሉቃ ፡ ም ፡ ፳፩ ፡ ቍ ፡ ፴፬-፴፮ ። መብልና ፡
መጠጥ ፡ የኃጢአት ፡ መሠረት ፡ እንደሆነ ፡ በጭሩ ፡ ካስረዳንም ፡ ዘንድ ፡ የጾምን ፡
ጠቃሚነት ፡ እናስከትላለን ።

፩ኛ| ሄኖክ ፡ ከምግብ ፡ በመከልከሉ ፡ ሳይሞት ፡ በሕይወቱ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ተለ
ይቶ ፡ በፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ ለምንነሣው ፡ ትንሣኤ ፡ ምልክት ፡ ሆኖ ፡ ቆይቷል ።

፪ኛ| ሙሴ ፡ ፵ ፡ ቀን ፡ ጾሞ ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተመሠረተበትን ፡
እሥራኤል ፡ ሕዝበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተብለው ፡ የተጠሩበትን ፡ ሕግ ፡ ተቀብሏል ።

፫ኛ ኤልያስ ፡ ፵ ፡ ቀን ፡ ከምግብ ፡ ተከልክሎ ፡ ሥጋ ፡ የለበሰ ፡ ፍጡር ፡ ሊሠ
ወረውና ፡ ሊያመልጠው ፡ ከማይቻለው ፡ ከሞት ፡ ተሠውሮ ፡ በእሳት ፡ ሠረገላ ፡ ዐርጓል ፡

፬ኛ| ዕዝራ ፡ ፵ ፡ ቀን ፡ ከምግብ ፡ ተከልክሎ ፡ የጠፉትን ፡ መጻሕፍተ ፡ ብሉያት ፡
በመንፈሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደገና ፡ አጽፎ ፡ ለመጪው ፡ ትውልድ ፡ አቆይቷል ።

፭ኛ| ሕዝቅኤል ፡ ፵ ፡ ቀን ፡ ከምግብ ፡ ተከልክሎ ፡ ለእሥራኤል ፡ ሚጠት ፡ ምል
ክት ፡ የሚሆኑ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሙታንን ፡ አስነሥቶ ፡ የትንሣኤ ፡ ሙታንን ፡ ምል
ክት ፡ አሳይቷል ።

፮ኛ| ዳንኤል ፡ በጾም ፡ ከአፈ ፡ አናብስትና ፡ ከዕቶነ ፡ እሳት ፡ ድኗል ።

፯ኛ| አስቴርና ፡ ዮዲት ፡ በጾም ፤ ኃያላን ፡ የተባሉ ፡ እሥራኤልን ፡ ሲያስፈሩዋ
ቸውና ፡ ሲያሸብሩዋቸው ፡ የነበሩ ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ ለማጥፋት ፡ ችለዋል ።

፰ኛ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እከብር ፡ የማይል ፡ ክቡር ፤ እጸድቅ ፡
የማይል ፡ ጻድቅ ፡ ሲሆን ፡ በዮርዳኖስ ፡ ከተጠመቀ ፡ በኋላ ፡ ወዲያው ፡ ሳይቆይ ፡ ገዳመ ፡
ቆሮንቶስ ፡ ገብቶ ፡ ለክርስቶሳውያን ፡ ሁሉ ፡ አብነትና ፡ አርአያ ፡ ሊሆን ፡ ፵ ፡ መዓልት ፡
፵ ፡ ሌሊት ፡ ጾሟል ።

በዚህም ፡ በዘረዘርነው ፡ ማስረጃ ፡ ጾም ፡ የበጎ ፡ ምግባር ፡ መሠረት ፡ መሆኑን ፡
መካድና ፡ ማሳበል ፡ ለማንም ፡ ማን ፡ የሚቻለውና ፡ የሚሆንለት ፡ አይደለም ። ጌታ
ችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ያለጾምና ፡ ያለጸሎት ፡ በጎ ፡ ምግባርን ፡ ለመሥራት ፡
እንደማይቻል ፡ ሲያስረዳ ፤ ጋኔን ፡ የተቈራኘው ፡ በሽተኛ ፡ ሲቅበዘበዝ ፡ አይቶ ፡ በላዩ ፡
አድሮ ፡ ያለውን ፡ ጋኔን ፡ እንዲወጣና ፡ ዳግመኛም ፡ ወደሱ ፡ እንዳይመለስ ፡ ገሥጾ ፡ በሽ



ተኛውና ፡ በሽተኛውንም ፡ በፈወሰው ፡ ጊዜ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ምነው ፡ ለኛ ፡ ማው
ጣቱ ፡ ሳይቻለን ፡ ቀረ ፡ ሲሉ ፡ ቢጠይቁት ፡ "ዝንቱ ፡ ዘመድ ፡ ኢይክል ፡ አውፅ
ኦቶ ፡ ዘእንበለ ፡ በጾም ፡ ወበጸሎት» ፡ (ይህ ፡ አብሮ ፡ አደግ ፡ ጋኔን ፡ በጸሎትና ፤
በጾም ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ማውጣት ፡ አይቻልም) ፡ ሲል ፡ በመለኮታዊ ፡ ቃሉ ፡ መል
ሶላቸዋል ፡ ማር ፡ ም ፡ ፱ ፡ ቍ ፡ ፳፱-፴ ።

ይህንንም ፡ ሁሉ ፡ ልንዘረዝርላችሁ ፡ ያስገደደን ፡ ከላይ ፡ እንደተመለከተው ፡
መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለኛ ፡ አርአያ ፡ ሊሆን ፡ የጾመው ፡ (ዐቢይ ፡
ጾም) ፡ ታላቁ ፡ ጾመ ፡ ፵ ፡ የሚጀመረው ፡ የካቲት ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ስለሆነ ፡ ከዚሁ ፡
ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ትንሣኤ ፡ ባሉት ፡ ሳምንቶች ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሁሉ ፡ ጾምና ፡
ጸሎታችሁን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሥዋዕት ፡ አድርጋችሁ ፡ እንድታቀርቡ ፡ የሚቻ
ለውን ፡ ያህል ፡ ምክርና ማስጠንቀቂያ ፡ ልናሰማችሁ ፡ የሚገባን ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

በሐዋርያትና ፡ በሊቃውንት ፡ ቀኖናም ፡ ስለዐቢይ ፡ ጾም ፡ ሲናገር ፤ «ወዘኢይጼ
ውም ፡ ጾመ ፡ ፵ ፡ ወረቡዕ ፡ ወዐርብ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፤ ካህን ፡ ይትመተር ፡ ዘእንበለ ፡
ዘሀሎ ፡ ዘቦቱ ፡ ደዌ ፡ ክሡት ፤ ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ ሕዝባዌ ፡ ይትፈለጥ ፡ ወኢይደሉ ፡
በጾመ ፡ ፵ ፡ ገቢረ ፡ ከብካብ ፡ ወኢብእሲት ፡ ሰበ ፡ ትወልድ ፡ ወኢይጼውዑ ፡ ሰብአ ፡
ኀበ ፡ መካነ ፡ ስቴ ፡ ለሰትዮ ። ወውእቱ ፡ ግብር ፡ ውፁእ ፡ እምሕግ ፡ ስብሳብ ፡ ከመ ፡
ኢይትላጸቅ ፡ ፩ዱ ፡ ውስተ ፤ ምንጻፉ ፡ በመዋዕለ ፡ ፵ ፡ ፍጹመ ። ወእመሰ ፡ ገበርነ ፡
ፈቃዳቲነ ፡ በጾመ ፡ ፵ ፡ ቅድስት ፡ በፍግዓ ፡ አይቴኬ ፡ ሀሎ ፡ ፍሥሐነ ፡ ሰበ ፡ ርኢነ ፡
ትንሣኤ ፡ ወአኮ ፡ ጾም ፡ እምኅብስት ፡ ወማይ ፡ አላ ፡ ጾምሰ ፡ ዘውኩፍ ፡ ቅድመ ፡
እግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ንጽሐ ፡ ልብ ፡ "ዐቢይ ፡ ጾምንና ፡ ዐርብ ፡ ረቡዕንም ፡
ያገለጠ ፡ ደዌ ፡ ካለበት ፡ ሰው ፡ በቀር ፡ ጠንቅቆ ፡ የማይጾም ፤ ካህን ፡ ቢሆን ፡
ይሻር ። ሕዝባዊም ፡ ቢሆን ፡ ከምእመናን ፡ ይለይ ። በዐቢይ ፡ ጾምም ፡ ሠርግ ፡ ማድ
ረግና ፡ ሴትም ፡ በወለደች ፡ ጊዜ ፡ ሰዎችን ፡ ወደመጠጥ ፡ ቦታ ፡ ጠርቶ ፡ ማጠጣት ፡
አይገባም ። በጾመ ፡ ፵ ፡ ውስጥም ፡ አንዱም ፡ አንዱ ፡ በምንጣፍ ፡ እንዳይገናኝ ፡ ከሩ
ካቤ ፡ የተለየ ፡ ይሁን ። በተቀደሰችውስ ፡ ጾመ ፡ ፵ ፡ የተድላና ፡ የደስታ ፡ ፈቃዳችንን ፡
የምናደርግ ፡ ከሆንን ፡ ብርሃነ ፡ ትንሣኤውን ፡ ባየን ፡ ጊዜ ፡ ደስታችን ፡ ወዴት ፡ አለ? ፡
ካልጾሙ ፡ ፋሲካ ፡ ካላዘኑ ፡ ደስታ ፡ የለምና ። ጾምም ፡ ማለት ፡ ከእህል ፡ ከውኃ ፡
መከልከል ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚቀበለው ፡ ጾም ፡ ከቂምና ፡ ከበ
ቀል ፡ ከክፋትና ፡ ከተንኰል ፡ ከኃጢአትም ፡ ሕሊናን ፡ ማንጻት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
ሲል ፡ ሥርዓት ፡ ሠርቶልናል ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ከሆነ ፡ ዘንድ ፡ መጻሕፍት ፡ ካዘዙን ፡ ቃል ፤ አበው ፡ ከሠሩ
ልን ፡ ሥርዓት ፡ ወጥተን ፡ እንቢተኞች ፡ መሆን ፡ መች ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ተግባር ፡
ይሆንልናል ? ኢትዮጵያ ፡ ከብዙ ፡ ሺ ፡ ዘመናት ፡ ጀምራ ፡ ነጻነቷ ፡ ሳይገፈፍ ፡
ሰንደቅ ፡ ዓላማዋ ፡ ሳይታጠፍ ፡ ወሰኗ ፡ ሳይታለፍ ፡ የምትኖረው ፡ በሃይማኖታዊ ፡ መሠ
ረትነቷ ፡ ላይ ፡ ሥረ ፡ ወጥ ፡ ሆነው ፡ የተገኙትን ፡ ጾምና ፡ ጸሎትን ፡ ጋሻና ፡ መከታ ፡

www.ethiopianorthodox.org

አድርጋ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ በሆነ ፡ መሣሪያ ፡ ብቻ ፡ የምትመከ
አይደለችም ።

በዚሁም ፡ በረጅም ፡ ዘመኗ ፡ ውስጥ ፡ የገጠማትን ፡ ትግልና ፡ ፈተና ፡ በዚሁ
መሣሪያዋ ፡ እየተከላከለች ፡ በመሣሪያቸው ፡ ኃይልና ፡ በጥበባቸው ፡ የሚመኩትን
ሁሉ ፡ ድል ፡ አድርጋ ፡ ነጻነቷን ፡ ጠብቃ ፡ ትኖራለች ። የታወቀው ፡ መሣሪያዋ
ይህ ፡ ከሆነ ፡ ይህንኑ ፡ መሣሪያዋን ፡ በየጊዜው ፡ በመወልወልና ፡ በመሰንገል
ፋንታ ፡ እንዲዝግና ፡ እንዲበላሽ ፡ ለማድረግ ፡ ችላ ፡ ልትል ፡ አይገባትምና ፡ ክ
ስቶሳውያን ፡ የሆናችሁ ፡ ልጆችዋ ፡ ሁሉ ፡ በመጻሕፍት ፡ የታዘዘውን ፡ ቃል ፡ እ
ድትፈጽሙና ፡ በሥጋችሁና ፡ በነፍሳችሁ ፡ ከሚታዘዝባችሁ ፡ መቅሠፍት ፡ ለመዳን
እንድትችሉ ፡ ስናስጠነቅቅ ፡ በሌላው ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ጉዳዩ ፡ የሚመለከታ
ቸውን ፡ ባለሥልጣኖች ።

፩ኛ! ሥጋ ፡ የሚሸጥባቸው ፡ ሉካንዳዎችና ፡ የዳንስ ፡ አዳራሾች ፡ እነዚህንም
የመሳሰሉት ፡ ሁሉ ፡ እንዲዘጉና ፡ በክበሮ ፡ ወይም ፡ በእምቢልታ ፡ ወይም ፡ በመ
ሰንቆ ፡ የሚያዘምሩ ፡ ተጫዋቾች ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡ ትንሣኤ ፡ ድረስ ፡ እንዲታገሡ ።

፪ኛ| ስካርና ፡ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ የሚመጣው ፡ ስሕተታዊ ፡ ተግባር ፡ ሁሉ
እንዲታረም ።

፫ኛ| ግብዝርና ፡ ሰፌ ፡ ጨዋታ ፡ ያለበት ፡ ስብሰባ ፡ ሁሉ ፡ ጊዜውን ፡ እን
ዲጠብቅ ፡ ለማድረግ ፡ በየሚቻላቸው ፡ ሁሉ ፡ እንዲደክሙበት ፡ በጌታችን ፡ በኢየ
ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ሆነን ፡ አደራ ፡ እንላቸዋለን ።

ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋን ፡ ለመደገፍ ፡ ምክንያት ፡ ባይታጣ
ለት ፡ እንኳ ፡ ለኀዘን ፡ ጊዜ ፡ አለው ፡ ለሳቅም ፡ ጊዜ ፡ አለው ፤ ለማልቀስ ፡ ጊዜ
አለው ፤ ለዘፈንም ፡ ጊዜ ፡ አለው ። (መክ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፬ ፡) ሲል ፡ ሰሎሞን ፡ እንደ
ተናገረው ፡ ሁሉ ፡ ዛሬ ፡ ጌታችን ፡ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለኛ ፡ ሲል
እንደተራበና ፡ እንደተጠማ ፡ የምናስታውስበት ፡ ሕማሙንና ፡ ሞቱን ፡ የምናስብ
በት ፡ ጊዜ ፡ ስለሆነ ፡ የደስታውን ፡ ጊዜ ፡ ለዘመኑ ፡ ፋሲካ ፡ ትተንለት ፡ በምንይ
ዘው ፡ ጾመ ፡ ፵ ፡ ምእመናን ፡ ሁሉ ፡ ለኃጢአታችን ፡ ሥርየት ፡ ማግኘት ፡ የም
ንችልበትን ፡ ጾምና ፡ ጸሎትን ፡ በማዘውተር ፡ ይቅር ፡ ባይና ፡ ቸር ፡ የሆነ ፡ ፈጣ
ሪያችንን ፡ እንድንማልደው ፡ ደግሜ ፡ አደራ ፡ እላችኋለሁ ።

---

በ፲፱፻፷፱ ፡ ዓ ፡ ም ።

ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ስለጌታ ፡ ልደት ፡ በዓል ፤

ለሕዝብ ፡ ያሰሙት ፡ ቃለ ፡ በረከት ።

(ስብሓት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በሰማያት ፡ ወሰላም ፡ በምድር ፡ ሥምረቱ ፡
ለሰብእ ። ይህ ፡ የዛሬው ፡ ቀን ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በቀን ፡ አቈጣጠር ፡ ልዩነት ፡



ሌሎቹ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ ያከበሩት ፡ ቢሆንም ፡ እኛና ፡ እኛንም ፡ የመሰሉት ፡ በኃ
ጢአት ፡ የጠፋውን ፡ የአዳምና ፡ የልጆቹን ፡ ሰውነት ፡ ለመፈለግ ፤ ሰማይና ፡ ምድ
ርን ፡ በማህል ፡ እጁ ፡ የጨበጠ ፡ አምላክ ፡ ልዑል ፡ ባሕርዩን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡
ትሑት ፡ ሥጋችንን ፤ ተዋሕዶ ፡ በኀቱም ፡ ድንግልና ፡ የተወለደበትን ፡ ሺ ፡ ፱፻
፷፱ነኛውን ፡ የመድኃኒታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ በዓለ ፡ ልደት ፡ የምናከ
ብርበት ፡ ታላቅ ፡ በዓላችን ፡ ነው ።

በዚህ ፡ ቀን ፡ «ዮም ፡ አሐደ ፡ መርዔተ ፡ ኮኑ ፡ መላእክት ፡ ወሰብእ ፡ ከመ ፡
ይሰብሕዎ ፡ ለክርስቶስ ፡ በቃለ ፡ አሚን» ፡ እንደተባለው ፡ ሰውና ፡ መላእክት ፡
ዓለምን ፡ ለማዳን ፡ ሰው ፡ የሆነውን ፡ አምላክ ፡ በማመስገን ፡ አንድ ፡ ሆነዋል ።

ለዚሁም ፡ በመላእክት ፡ ዘንድ ፡ ምስጋና ፡ ተደረገ ። በደቂቀ ፡ አዳምም ፡
ዘንድ ፡ የሰው ፡ ፍቅር ፡ አገብሮት ፡ አምላክ ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ በምድርም ፡ ሰላም ፡
(ፍቅር ፡ አንድነት) ፡ ሆነ ፤ እያልን ፡ የድኅነታችንን ፡ የምሥራች ፡ ለዓለም ፡ እን
ሰብካለን ፡ (እናሰማለን) ።

በዛሬው ፡ ቀን ፡ የሰማያዊቱ ፡ ጽርሐ ፡ አርያም ፡ ዙፋን ፡ ባለቤት ፡ የሆነው ፡
አምላክ ፡ ለኛ ፡ ሲል ፡ መኖሪያ ፡ እንደሌለው ፡ በከብት ፡ በረት ፡ ተጣለ ።

በዛሬው ፡ ቀን ፡ የዕሩቃን ፡ ልብስ ፡ የሆነው ፡ የነገሥታት ፡ ንጉሥ ፡ ለኛ ፡
ሲል ፡ በጨርቅ ፡ ተጠቀለለ ።

በዛሬው ፡ ቀን ፡ ሥጋ ፡ ለብሼ ፡ አድንሃለሁ ፡ ሲል ፡ ለአዳም ፡ የሰጠውን ፡
ተስፋ ፡ ለመፈጸም ፡ ከዕለቱ ፡ አንድ ፡ ቀን ፤ ከሰዓቱም ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ሳያስተ
ላልፍና ፡ ሳያጕድል ፡ ሰማይና ፡ ምድር ፡ የማይወስኑት ፡ አምላክ ፡ በጭር ፡ ቁመት ፡
በዐባብ ፡ ደረት ፡ ተወስኖ ፡ ታየ ።

ስለዚህም ፤ ሐዋርያው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ወደ ፡ ሮሜ ፡ ሰዎች ፡ በጻፈው ፡
መልእክቱ ፡ ‹ክርስቶስኒ ፡ መጽአ ፡ በዕድሜሁ ፡ ይሙት ፡ በእንተ ፡ ኃጢአትነ ፡
እንዘ ፡ ኃጥአን ፡ ንሕነ› ፡ ክርስቶስም ፡ እኛ ፡ ኃጢአተኞች ፡ ስንሆን ፡ ስለ ፡ ኃጢአ
ታችን ፡ ይሞት ፡ ዘንድ ፡ በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ መጣ ፡ ሲል ፡ አስረድቷል ። ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፮ ።

ዳግመኛም ፤ ለገላትያ ፡ ሰዎች ፡ በጻፈው ፡ መልእክቱ ፡ ፡፡ወአመ ፡ በጽሐ ፡
ዕድሜሁ ፡ ፈነወ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልዶ ፤ ወተወልደ ፡ እምብእሲት፡፡ ፡ ወገብረ ፡
በሕገ ፡ ኦሪት ፡ ከመ ፡ ይሣየጠሙ ፡ ለእለ ፡ ውስተ ፡ ኦሪት፡ (ጊዜውም ፡ በደረሰ ፡
ጊዜ ፤ እግዚአብሔር ፡ ልጁን ፡ ላከ ። ከሴትም ፡ (ከድንግል ፡ ማርያም) ፡ ተወልዶ ፡
በኦሪት ፡ የታዘዘውን ፡ ሠራ ። በኦሪት ፡ የነበሩትን ፡ ገንዘብ ፡ ያደርጋቸው ፡ ዘንድ ፡
ሲል ፡ ገልጾታል ። ገላ ፡ ፬ ፡ ፬—፭ ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ የተደረገለትስ ፡ ሰው ፤ ለወገኑ ፡ እንዲሁ ፡ ማድረግ ፡ የለበ
ትም ፡ ኖሯልን ? በቃሉ ፡ ብቻ ፡ ማዳን ፡ የሚቻለውስ ፡ አምላክ ፡ ሰው ፡ እስከ ፡
መሆንና ፡ ትሑት ፡ ሥጋን ፡ እስከ ፡ መልበስ ፡ የደረሰው ፡ ለሰው ፡ የትሕትናና ፡

www.ethiopianorthodox.org

የፍቅር ፡ አብነት ፡ ለመሆን ፤ አልነበረምን? ፡ እነሆ ፡ ሥጋ ፡ መልበሱን ፡ የምናምን
ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ ተደረገልን ፡ እያልን ፡ የመድኃኒታችንን
በዓለ ፡ ልደት ፡ እናከብራለን ።

እንዲህ ፡ ሲሆን ፤ በዓለም ፡ ላይ ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ እንዲሆን ፡ በንጥር
ይህ ፡ በዓሉን ፡ ያከበርነው ፡ ቀንና ፡ ታሪክ ፡ እየታዘበን ፡ ከማለፉ ፡ ሌላ ፡ ያፍ
ብቻ ክርስቲያን ፡ መባላችን ፡ ይቀራልን ? ።

ዓለም ፡ ሁሉ ፡ የመብት ፡ መበላለጥና ፡ መጓደል ፡ በፊቱ ፡ ተደቅነው ፡ በ
ስቸግሩት ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሰላም ፡ እግሩን ፡ እንዲዘረጋ ፡ የማይመኝ ፡ አል
ረም ።

እነዚህን ፡ ለማደላደልና ፡ ለማስተካከል ፡ ግን ፤ ለፈቃድ ፡ ደጋፊ ፡ የሆነው
ሰፊ ፡ ምኞት ፡ የተወሰነ ፡ ባለመሆኑ ፡ የምኞቱን ፡ ስፋት ፡ ያህል ፡ ጊዜና ፡ ንግግር
ሊወስድ ፡ አስፈለገ ።

የዓለም ፡ መድኃኒት ፡ የሰጠውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፤ በሰዓቱ ፡ እንዲፈጸም
የዓለምም ፡ መንግሥታት ፡ ስለ ፡ ተወከሉበት ፡ ዓለም ፡ ሆነው ፡ የሰጡትን ፡ ቃል
ኪዳን ፡ ለማክበርና ፡ ለመፈጸም ፡ ወይም ፡ ለማስከበርና ፡ ለማስፈጸም ፡ ሊታደሉ
እንጸልይላቸዋለን ።

ዳሩ ፡ ግን ፤ ያ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ጐርፍ ፡ የፈሰሰው ፡ የሰው ፡ ደም ። መ
ዋዕትነቱ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ሆኖ ፡ መሠረታዊ ፡ ሰላም ፡ እንዲመሠረት ፡ ሳይሆን
ቢቀር ፤ የዓለምን ፡ ዐዋቂዎችና ፡ ታላላቆች ፡ የሚያስወቅሳቸው ፡ ስለሆነ ፤ አስተ
ታቸው ፡ የዓለምን ፡ ሰላም ፡ ለማምጣት ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ እንዲሆን ፡ ቤተ ፡ ክ
ስቲያናችን ፡ ሰላምን ፡ ለማምጣት ፡ በዚሁ ፡ ቀን ፡ የተወለደ ፡ ፈጣሪዋን ፡ ትለምናለች ።

ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ የነበረው ፡ ዘመን ፤ ዓመተ ፡ ፍዳ ፤ ዓመተ ፤ ኵነ
የተባለውን ፡ ያህል ፡ ከልደቱም ፡ ጀምሮ ፡ ያለው ፡ ዘመን ፡ ዓመተ ፡ ሥጋዌ ፡ ዓመ
ምሕረት ፡ ተብሎ ፡ የታሪኮችና ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ጽሑፎች ፡ መነሻና ፡ መድረሻ ፡ (አ
እስትና ፡ ኅዳግ) ፡ ሆኖ ፡ በስመ ፡ ጥሩነቱ ፡ ሲነገር ፡ ይኖራል ።

እንደዚህም ፡ ሁሉ ፡ ያለፈው ፡ የጦርነት ፡ ዘመን ፡ ዓመተ ፡ ፍዳ፡ዓመተ ፡ ኵነ
ተብሎ ፤ ዓመተ ፡ ሰላም ፡ ለዓለም ፡ እንዲጀመርለት ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ጸሎታችን
የሚቋረጥ ፡ አይደለም ።

መቸም ፡ የታላላቆች ፡ ታላቅነት ፡ የሚገመተው ፡ ታሪክ ፡ ሲያስታውሰው
የሚኖረውን ፡ ቀዋሚ ፡ ነገር ፤ ለትውልድ ፤ ጥለው ፡ በማለፋቸው ፡ ካልሆነ
በቀር ፡ በኃይል ፡ የተገኘው ፡ ትልቅነት ፡ ለጊዜው ፡ እንጂ ፡ ዘላቂነትና ፡ መሠ
ታዊነት ፡ እንደሌለው ፤ ያለፈው ፡ ዘመን ፡ ሁኔታውን ፡ እያሳየን ፡ እንዳለፈ
የጊዜው ፡ ባለታሪኮች ፡ (በመዝገበ ዕለት) በዕለት ፡ ሁኔታ ፡ ማስታወሻቸው ፡ የ
በቃ ፡ ገጽና ፡ ምዕራፍ ፡ ሰጥተውት ፡ ቦታውን ፡ ይዞ ፡ ይገኛልና ፡ ይህ ፡ ገጽ ፡ በ



ያምር ፡ ቀለም ፡ ተሥሎ ፡ እንዳይታይ ፡ ዐዋቂዎች ፡ ወይም ፡ ታላላቆች ፡ እስካሁን ፡
እንደ ፡ ደከሙበት ፡ ሁሉ ፡ ወደፊትም ፡ በግዴታ ፡ መጠበብና ፡ መቸገርም ፡ ይኖርባ
ቸዋል ።

ክርስቶሳውያን ፡ ሆይ ፤ ክርስቲያንነታችን ፡ ለሰው ፡ ፊት ፡ እንዳትሆንና ፡ የአፍ ፡
ክርስቲያን ፡ በመሆን ፡ ከእውነተኛው ፡ ክርስቲያንነት ፡ ውጭ ፡ እንዳንሆን ፤ በሁላችን ፡
ውሴና ፡ ልቡና ፡ ቅን ፡ አስተያየትን ፡ ይቀርጽበት ፡ ዘንድ ፡ በምድርም ፡ ፍጹም ፡
ሰላም ፡ ይሆንልን ፡ ዘንድ ፡ ሁሉን ፡ ማድረግ ፡ የሚቻለውን ፡ አምላክ ፡ እንለምነው ።
በረከተ ፡ ልደቱ ፡ በሁላችን ፡ ይደር ፡ አሜን ።

---

ሰኔ ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ ፡ ም ፤ በታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ለመምህራ
ንና ፡ ፈተና ፡ ለዘለቁት ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከቀዳ
ማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሽልማት ፡ በተሰጠበት ፡ ቀን ፤ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡
የግርማዊነታቸውን ፡ ውለታና ፡ በጎ ፤ አድራጎት ፤ የሚያስታውስ ፡ ቃል ፡ ተናግ
ረው ፡ ነበርና ።

## የብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ቃለ ፡ በረከት ።

ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ በዚህ ፡ ጉባኤ ፡ እንድንገኝ ፡ ለፈቀደልን ፡ ለእግዚአብ
ሔር ፡ የሕሊና ፡ ምስጋና ፡ እያቀረብኩ ፡ ንግግሬን ፡ እጀምራለሁ ።

## ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ይህንን ፤ ጉባኤ ፡ ስመለከት ፡ በሕሊናዬ ፡ የሚታሰበኝ ፤ በግርማዊነትዎ ፡ ታላቅ ፡
አድራሻ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በታላቅ ፡ ረድኤት ፡ የጠበቃት ፡ የእግዚአብሔር ፡ቸርነት ፡
ነው ፡ በቀድሞ ፤ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትምህርት ፤ እንደዛሬ ፡ በየ
ሥፍራው ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ተቀምሞና ፡ ተስፋፍቶ ፡ ሳይገኝ ፡ በዋና ፡ በዋና ፡
ከተማዎች ፡ በታላላቆች ፡ አድባራትና ፡ በየከፍተኞች ፡ ገዳማት ፤ እንዲሁም ፡ ተራር
ቀው ፡ በሚገኙ ፡ አንዳንድ ፡ አውራጃዎች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ተከፋፍሎ ፡ ይነገር ፡ ስለ
ነበረ ፤ ተማሪዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ከመምህራን ፡ ጋራ ፤ ተገናኝተው ፡ የቀጠላ ፡ ሥራቸውን ፡ እስኪ
ጀምሩ ፡ ድረስ ፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይወስድባቸው ፡ ነበርና ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የሚደ
ርስባቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ፈተና ፡ እንዳሁኑ ፡ የትምህርታቸውን ፡ ጊዜ ፡ ለመቆጠብ ፡
የተመቸ ፡ አልነበረም ። ከዚህም ፡ ይልቅ ፡ ከዘመዶቻቸው ፤ ተለይተው ፡ (አንድ ፡
ወገን ፡ ሆነው) ፤ ትምህርታቸውን ፡ በሚቀጥሉበት ፡ ጊዜ ፤ በኑሮዋቸውና ፡ በጤና
ቸው ፡ ላይ ፡ የሚወድቅባቸው ፡ ታላቅ ፡ አደጋ ፡ ሲታሰብ ፤ እጅግ ፡ የሚያሰቅቅ ፡
በመሆኑ ፡ በየጊዜው ፡ ስለትምህርት ፡ የፈጸሙት ፡ ተጋድሎ ፡ ከከዊነ ፡ ሰማዕትና ፡ ከመ
ጥምት ፡ ርእስ ፡ የሚቈጠር ፤ ነው ። ይኸውም ፡ ምክንያት ፡ ሆኖን ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡
ትጋትና ፡ ብርታት ፡ ጥረው ፡ ግረው ፡ የትምህርታቸውን ፡ ቅርስ ፡ ከትውልድ ፡ ወደ
ትውልድ ፡ ያስተላለፉልንን ፡ አባቶቻችንን ፡ በዛሬዪቱ ፡ ቀን ፡ እናስታውሳቸዋለን ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ያባቶቻችንን ፡ ጸሎት ፡ ያልረሳ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለቤተ ፡ ክር
ስቲያናችን ፡ በብዙ ፡ ወገን ፡ የሚጥሩላትን ፡ ግርማዊነትዎን ፡ ስለሰጠን ፤ እነሆ ፡ ዛሬ ፡

www.ethiopianorthodox.org

በግርማዊነትዎ ፡ መልካም ፡ እርዳታና ፡ ሰፊ ፡ ልግሥና ፡ ተማሪዎች ፡ ከመምህራን ፡ ጋ
እየተገናኙ ፡ በፊታቸው ፡ የቀረበላቸውን ፡ የቀለም ፡ ምርት ፡ ያላንዳች ፡ ችግር ፡ የ
ያፍሱ ፡ ሆነዋል ።

በአራት ፡ ክፍል ፡ የተመደበው ፡ የትምህርት ፡ አቀራረብ ፡ ባንዳንድ ፡ ክፍል
ላይ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ እንዲገኝ ፡ በመደረጉ ፡ ከንባብ ፡ ወደ ፡ ፀዋትወ ፡ ዜማ ፤ ከዜማ
ወደቅኔ ፤ ከቅኔ ፡ ወደ ፡ ትርጓሜ ፡ መጻሕፍት ፡ ሲያልፉ ፡ እንደቀድሞው ፡ ሥፍራ
በመለወጥ ፤ ምክንያት ፡ መድከምና ፡ በከንቱ ፡ ጊዜን ፡ ማሳለፍ ፡ የለባቸውም ። ይህ
አኳኋን ፡ ከሌላው ፡ ይልቅ ፡ ጤናቸውንና ፡ ንጽሕናቸውን ፡ ለመጠበቅ ፡ ይረዳቸዋል
ብለን ፡ ተስፋ ፡ አድርገናል ።

ይኸውም ፡ ቀድሞ ፡ የነበረውን ፡ ችግር ፡ ደምስሶ ፡ መምህራንና ፡ ደቀ ፡ መ
ሙርት ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ምቾት ፡ እንዲያገኙ ፡ ያደረገ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በ፲፱፻፴፭ ፡
ም ፡ በቍርጥ ፤ ሕሊና ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሰጡት ፡ መልካም ፡ ችሮታ ፡ ነው
አሁንም ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፤ በ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተሰጠን ፡ የግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ችሮ
የዚህ ፡ ተባባሪ ፡ ሆኖ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናችንን ፡ ለመደገፍ ፡ ችሏል ። ስለዚህ ፡ ሐ
ርያው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ የስጦታን ፡ ነገር ፡ በገበሬ ፡ ዘር ፡ መስሎ ፡ በቆሮንቶስ
ላሉ ፡ ምእመናን ፡ ሲናገር ፤ አብዝቶ ፡ የዘራ ፡ መከሩን ፡ አብዝቶ ፡ ይሰበስባል
(ዘሰ ፡ በበረከት ፡ ይዘርዕ ፡ በበረከት ፡ የዐርር) ፡ በማለት ፡ አብዝቶ ፡ መስጠት ፡ መ
ቀሙን ፡ እንዳስረዳቸው ፡ ሁልጊዜ ፡ አስተፋጥን ፡ ከመ ፡ ትረሲ ፡ ርእሰከ ፡ ኅሩየ
ከመ ፡ ገባራዊ ፡ ዘርቱዐ ፡ ይመትር ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ። (፪ ፡ ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፲፭፡) እ
የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፤ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሀብት ፡ የሚያተጋ ፡ እንደ
ቈስጠንጢኖስ ፡ ለኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዕድል ፡ የሆነ ፡ ግርማዊነት
ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሰጣት ፡ መተዳደሪያ ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ብዛቱ ፡ መጠን ፡ ፍ
ውን ፡ አብዝቶ ፡ ለመስጠት ፡ ስለቻለ ፤ በአዲስ ፡ አበባና ፡ በየአውራጃው ፡ ትም
ርት ፡ ቤቶች ፡ ብዙ ፡ መምህራንና ፡ ተማሪዎችን ፡ አስገኘ ። ይልቁንም ፡ ዛሬ ፡ በ፲፱፻፵፯
ዓ ፡ ም ፡ ስለትምህርት ፡ የተወሰነው ፡ ገቢ ፡ (ከቤተ ፡ ክህነት ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ የሚ
ኘው ፡ ታክስ) ፡ ለመንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ማስፋፊያ ፡ እንዲሆን ፡ ስለፈቀ
ልን ፡ ወደፊት ፡ ቍጥራቸው ፡ እጥፍ ፡ እየሆነ ፡ እንዲጨመር ፡ ባለሙሉ ፡ ተስፋዎች ፡ ነ

## ግርማዊ ፡ ሆ ይ ።

ግርማዊነትዎ ፡ ደህ ፡ መንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ድጋፍ ፡ መ
ኑን ፡ ተመልክተው ፤ በሰፊው ፡ እንዲዘራ ፡ ስለአደረጉ ፤ በምግባር ፡ በሃይማኖት
ጠብቅልን ፤ ዘመኑንም ፡ አብዛለት ፤ መንግሥቱንም ፡ አጽናለት ፤ ሠራዊቱንም ፡ ጠ
ቅለት ፤ በዙሪያው ፡ ባሉ ፡ ጠብ ፡ በሚያደርጉ ፡ በጠላቶቹ ፡ ዘንድ ፡ ኀይልን ፡ ጽናትን
ድል ፡ መንሣትን ፡ ስጠው ፡ በልቡናው ፡ አድረህ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በጎ ፡ ነገርን
እንዲናገር ፡ አድርግ ።



እኛ ፡ በፍጹም ፡ ዕረፍት ፡ እንኖር ፡ ዘንድ ፡ ሰላምን ፡ ስጠው ፡ በፍጹም ፡ ቸር
ነትህ ፡ ትእዛዝን ፡ ለመጠበቅ ፡ የበቃን ፡ ሆነን ፡ እንገኝ ፡ ዘንድ ፡ እያለች ፡ የኢትዮ
ጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እጆቿን ፡ ዘርግታ ፡ ጸሎቷንና ፡ ልመ
ናዋን ፡ ያለማቋረጥ ፡ ታቀርባለች ፡ አሜን ።

---

## ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ።

## ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፤ ስለጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
## በዓለ ፡ ልደት ፡ ለሕዝብ ፡ ያሰሙት ፡ ቃለ ፤ በረከት ።

በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምናችሁ ፤ በልጅነት ፡ ከብራችሁ ፡ የምት
ኖሩ ፡ ሕዝበ ፤ እግዚአብሔር) ፡ ክርስቲያን ፡ ሆይ ፡ ከጌታችን ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
የሚሰጥ ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ በዝቶ ፡ ይደረግላችሁ ።

ዛሬ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ የምናከብረው ፡ በዓል ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ በአብ ፡
ዕሪና ፡ የነበረው ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልድ ፡ በተለየ ፡ አካሉ ፡ በሥጋ ፡ የተወለደበት፡
ልደት ፡ ስለሆነ ፤ ይህንን ፡ በዓል ፡ በያመቱ ፡ ስናከብር ፡ የሚሰማን ፡ ደስታ ፡
ወሰን ፡ የለውም ።

አሁን ፡ ስለ ፡ በዓሉ ፡ ክብር ፡ ከብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ እንነግራች
ኋለን ። በዝንቱ ፡ ተዐውቀ ፡ ፍቅሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ላዕሌነ ፡ እስመ ፡ ለወልዱ ፡
ዋሕድ ፡ ፈነዎ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ። ከመ ፡ ንሕየው ፡ በእንቲአሁ ፤ ወዝንቱ ፡ ውእቱ፡
ፍቅሩ ፡ ለእግዚአብሔር ። አኮ ፡ ንሕነ ፡ ዘአፍቀርናሁ ። አላ ፡ ውእቱ ፡ አፍቀረነ ።
ወፈነዎ ፡ ለወልዱ ፡ ይኅድግ ፡ ለነ ፡ ኃጣውኢነ ፡ ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፬ ፡ ፱—፲፩ ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከተው ፡ ንባብ ፡ እኛን ፡ በፍቅር ፡ እንደፈለገን ፤ እኛም፡
እርሱን ፡ በፍቅር ፡ መፈለግ ፡ እንደሚገባን ፡ ያስገነዝበናልና ፡ ንግግራችንን ፡ በዚሁ
እንቀጥላለን ።

ይህ ፡ የመድኀኒታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ልደት ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡
ብዙ ፡ አበውና ፡ መሳፍንት ፡ ብዙ ፡ ነገሥታትና ፡ ነቢያት ፡ ደጋግ ፡ ሰዎችም ፡
ሁሉ ፡ ሊያዩት ፡ ሲመኙ ፡ ያላዩት ፤ ሲሆኑ ፡ ወደጊዜው ፡ ደርሰው ፡ ላዩት ፡ ዕድለኞች ፡
የበለጠ ፡ ደስታና ፡ ክብር ፡ ሰጥቷቸዋል ።

እኛም ፡ በያመቱ ፡ ከበዓለ ፡ ዕንሱ ፡ እስከ ፡ በዓለ ፡ ልደቱ ፡ ያሉትን ፡ ዕለታት ፡
ቈጥረን ፡ ወደዚህ ፡ ዕለተ ፡ ልደቱ ፡ በደረስን ፡ ጊዜ ፤ «ዮም ፡ ተወልደ ፡ ከማኅቴ ፡ ብር
ሃን ፡ ዮም ፡ ተወልደ ፡ ቢዛ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም» ፡ እያልን ፡ ስናመሰግነው ፡ የበለጠ ፡ ደስ
ታና ፡ ክብር ፡ ይሰማናል ።

ወደጊዜው ፡ ደርሰው ፡ ካዩትም ፡ ዕድለኞች ፡ ጋር ፡ ያስተካክለናል ። ይሁን ፡
እንጂ ፡ አረፍተ ፡ ዘመን ፡ ምንም ፡ ኋለኞቹን ፡ ከፊተኞች ፡ ቢያራርቀን ፤ ጥንቱን ፡
ወርጇ ፡ ተወልጀ ፡ አድናችኋለሁ ፡ ሲል ፡ በሰጠን ፡ ቃሉ ፡ ከልደቱ ፡ በፊትና ፡

www.ethiopianorthodox.org

በልደቱ ፡ ጊዜ ፡ የነበሩትን ፡ ከልደቱ ፡ በኋላ ፡ ያለን ፡ እኛንም ፡ አንድ ፡ ወገን
አድርጎ ፡ (ሕዝበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውሉደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለመባል ፡ አብቅቶን
የማዳን ፡ ሥራውን ፡ ስለፈጸመልን ፤ እነሆ ፡ አሁን ፡ በሁላችን ፡ ይመሰገናል ፡ ስና
መሰግነውም ፡ በሕሊናችን ፡ የሚታሰበን ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለው ፡ ነው ።

፭ኛ ፡ ሰው ፡ ከሕጉ ፡ ከትእዛዙ ፡ ወጥቶ ፡ የበደለው ፡ ሲሆን ፡ የበደለውን
ሰው ፡ ሊታረቀው ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ መምጣቱ ።

፮ኛ ፡ በላይኛው ፡ ካባቱ ፡ ዕሪና ፡ ባለመለየቱ ፡ ኪሩቤል ፡ ሱራፌልና ፡ ነገደ
መላእክት ፡ ሁሉ ፡ ሲያመሰግኑት ፤ ከዚህም ፡ በፍጹም ፡ ተዋሕዶ ፡ በተዋሐደው
ሥጋ ፡ ተገልጦ ፡ በኖሎትና ፡ በመላእክት ፡ መመስገኑ ።

፯ኛ ፡ የማይታይ ፡ ረቂቅ ፡ የማይዳሰስና ፡ የማይጨበጥ ፡ እሳት ፡ ሲሆን ፤ የኛን
ሥጋ ፡ ነሥቶ ፡ በሕጻናት ፡ መጠን ፡ ተወልዶ ፤ በጠባብ ፡ በረት ፡ ተጥሎ ፤ በጨ
ርቅ ፡ ተጠቅልሎ ፡ በመካከላችን ፡ መገኘቱ ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባጫሩ ፡ የዘረዘርናቸው ፡ የታዳጊነቱ ፡ ሥራዎች ፡ በየሕሊና
ችን ፡ ትዝ ፡ ሳይሉን ፡ አይቀሩም ።

ስለዚህ ፤ በዛሬዪቱ ፡ ቀን ፡ የምንናገረው ፡ የምሥራች ፡ ቃል ፡ ከዚህ ፡ ቀጥ
ለን ፡ የምናሳስባችሁ ፡ ነው ።

፰ኛ ፡ ፈጥሮ ፡ መግዛቱ ፡ ይቅር ፡ እንዲል ፡ የሚያደርገው ፡ አምላክ ፡ በዛሬ
ዪቱ ፡ ቀን ፡ በይቅርታው ፡ ጐበኘን ።

፱ኛ ፡ ዙፋኑን ፡ በሰማይ ፡ የዘረጋ ፤ ምድርንም ፡ መመላለሻው ፡ ያደረገ ፡ አም
ላካችን ፡ ስለኛ ፡ ባጭር ፡ ቁመት ፡ በፀባብ ፡ ደረት ፡ ተወስኖ ፡ በዛሬዪቱ ፡ ቀን
የዕርቅ ፡ ምልክት ፡ አሳየን ።

፲ኛ ፡ ሥልጣኑና ፡ አገዛዙ ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፤ ከምድርም ፡ በታች ፡ ያለ
ትን ፡ ሥፍራዎች ፡ በጠቅላላውም ፡ አየረ ፡ አየራትን ፤ ዕመቀ ፡ ዕመቃትን ፡ የመላ
አምላካችን ፤ ከኃጢአትና ፡ ከሰይጣን ፡ በታች ፡ ወድቀን ፡ የነበርን ፡ እኛን ፡ ለማ
ንሣት ፡ ውሱን ፡ ባሕርያችንን ፡ ምክንያት ፡ አድርጎ ፡ በዛሬዪቱ ፡ ቀን ፡ ተገለጠልን
፲፩ኛ ፡ ብርሃኑ ፡ የማይጨልም ፡ ኃይሉ ፡ የማይደክም ፡ አምላካችን ፡ በጨለማ

ውስጥ ፡ ተውጠን ፡ የነበርን ፡ እኛን ፡ በልደቱ ፡ ወደብርሃን ፡ ረድኤቱ ፡ መለሰን
ደክመን ፡ ሳለንም ፤ እንድንበረታ ፡ አድርጎ ፡ በርኅራኄው ፡ አሰበን ። የዚህ
ሁሉ ፡ መጠቅለያውና ፡ መደምደሚያው ፡ ወርዶ ፡ ተወልዶ ፡ በምሕረቱ ፡ ሊጐበኘን
ባሰበ ፡ ጊዜ ፤ የመላእክትን ፡ ባሕርይ ፡ ልዋሐድ ፡ ሳይል ፡ የኛን ፡ ባሕርይ ፡ ተዋሕዶ
ይህንኑ ፡ የተዋሐደውን ፡ ባሕርያችንን ፡ የድኅነት ፡ መገኛ ፡ ማድረጉ ፡ ነው ።
ሐዋርያው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ ስለዚሁ ፡ ሲናገር ፤ በሞቱ ፡ የሞትን ፡ አለቃ
(ዲያብሎስን) ፡ እንደሻረውና ፡ በሕይወታቸው ፡ ዘመን ፡ ለሰይጣን ፡ ተገዝተው ፡ የ
በሩትን ፡ ከመገዛት ፡ እንዳሳረፋቸው ፡ ካስረዳ ፡ በኋላ ፤ የነሣው ፡ አካል ፡ ከአብ

ሃም ፡ ዘር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከመላእክት ፡ የነሣው ፡ አይደለም ፡ (ኢነሥአ ፡ ለዘነሥአ ፡
አመላእክት ፡ ዘእንበለ ፡ ዳእሙ ፡ እምዘርአ ፡ አብርሃም ፡ ብሂል ፡ ዕብ ፡ ፪ ፡ ፲፮ ።

እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ ለባሕርያችን ፡ ልዕልና ፡ ለሰጠ ፡ አምላክ ፡ የምንከፍለው
ወሮታ ፡ ከቶ ፡ ምን ፡ ይሆን ? ፡ ምንም ፡ የቸርነቱን ፡ ዋጋ ፡ ለመክፈል ፡ ባንችል ፡ በሚ
ቻለን ፡ እንድናገለግለው ፡ እነሆ ፡ ከልደቱ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ምሳሌ ፡ እናገኛለን ።

በተወለደ ፡ ጊዜ ፡ ሰብአ ፡ ሰገል ፡ ከሩቅ ፡ አገር ፡ መጥተው ፡ ወርቅ ፤ ዕጣን ፤ ከርቤ ፡
እንደገበሩለት ፤ እኛም ፡ እንደ ፡ ወርቅ ፡ መልካም ፡ ጽርየት ፡ ያለው ፡ ሃይማኖትን ፡
እንደ ፡ ዕጣን ፡ መዓዛ ፡ ያለው ፡ ምግባርን ፤ እንደ ፡ ከርቤ ፡ የተለያየውን ፡ አንድ ፤
የሚያደርግ ፡ ፍቅርንና ፡ ሰላምን ፡ የልደቱ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ አድርገን ፡ ማቅረብ ፡ ይገ
ባናል ።

አኑዋኑዋራችንም ፡ ሁሉ ፡ በክርስቶስ ፡ የተቀደሰ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ደጉን ፡
ምሳሌ ፡ ትተን ፡ ክፉውን ፡ ምሳሌ ፡ አንከተል ። ይኸውም ፡ ፍጻሜያችን ፡ መራራ ፡
እንዳይሆን ፡ ነው ።

ለምሳሌ ፡ የገሊላው ፡ ንጉሥ ፡ ሄሮድስ ፡ ጌታ ፡ በተወለደ ፡ ጊዜ ፤ ንጉሥ ፡
ከሆነ ፡ መንግሥቴን ፡ ይወስድብኛል ፡ በማለት ፡ ለሰብአ ፡ ሰገል ፡ የሕፃኑን ፡ ነገር ፡
ጠይቁና ፡ ተመልሳችሁ ፡ ንገሩኝ ፡ እኔም ፡ መጥቼ ፡ እሰግድለት ፡ ዘንድ ፡ ብሎ ፡ የአ
ፉን ፡ ሌላ ፡ የልቡን ፡ ሌላ ፡ አድርጎ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ጉህሉት ፡ እንደተናገረ ፤ ማና
ቸውም ፡ ፍጡር ፡ እንኳን ፡ በፈጣሪው ፡ በተፈጥሮ ፡ ጓደኛው ፡ ላይ ፡ ያፉን ፡ ሌላ ፡ የል
ቡን ፡ ሌላ ፡ አድርጎ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ጉህሉት ፡ ቢናገር ፡ ሄሮድሳዊ ፡ ያሰኘዋልና ፡
ከእንዲህ ፡ ያለው ፡ ስሕተት ፡ መጠበቅ ፡ ተፈጥሮን ፡ የሚያስከብር ፡ ታላቅ ፡ ጥን
ቃቄ ፡ ነው ።

በለዚህ ፡ በዓለ ፡ ልደቱን ፡ በማክበር ፡ ለተባበረ ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ደገኛው ፡ ምሳሌ ፡
እንጂ ፡ ክፉው ፡ ማሳሌ ፡ እንዳይደርስበት ፡ እንመኛለን ።

ይህንንም ፡ እስከ ፡ መመኘት ፡ ያደረሰን ፡ የተፈጥሮዋችን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ተባ
ብሮ ፡ በመኖሩ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ የሰውን ፡ ታሪክ ፡ ከሥሩ ፡ ጀም
ረን ፡ ስንመለከተው ፡ መጀመሪያም ፡ በሕይወቱ ፡ ኋላም ፡ በሞቱ ፡ የገጠመው ፡
ዕድሉ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ።

ይልቁንም ፡ ዛሬ ፡ በልደቱ ፡ ቀን ፡ መልአኩ ፡ እነሆ ፡ እኔ ፡ ለሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡
ታላቅ ፡ ደስታ ፡ የሚሆን ፡ የምሥራች ፡ እነግራችኋለሁና ፡ አትፍሩ ።

እነሆ ፡ ዛሬ ፡ በዳዊት ፡ አገር ፡ ቡሩክ ፡ ጌታ ፡ የሚሆን ፡ መድኅን ፡ ክርስ
ቶስ ፡ ተወልዶላችኋልና ። (ኢትፍርሁ ፡ እስመ ፡ ናሁ ፡ እዜንወክሙ ፡ ዐቢየ ፡ ዜና ፡
ፍሥሓ ፡ ዘይከውን ፡ ለክሙ ፡ ወለኵሉ ፡ ሕዝብ ። እስመ ፡ ተወልደ ፡ ለክሙ ፡
ዮም ፡ መድኅን ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእ ፡ ቡሩክ ፡ በሀገረ ፡ ዳዊት) ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡
የምሥራች ፡ ቃል ፡ የሰው ፡ ዕድል ፡ ባንድ ፡ አምላካዊ ፡ ፈቃድ ፡ ብቻ ፡ የሚመራ ፡
መሆኑን ፡ ያስረዳል ።

www.ethiopianorthodox.org

አምላክ ፡ በሥጋ ፡ ተወልዶለት ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ የምሥራች ፡ ቃል ፡ ለመ
ማት ፡ የታደለ ፡ ሕዝብ ፡ የአምላኩን ፡ ወሮታ ፡ ሊዘነጋ ፡ ከቶ ፡ አይገባውም ።
ወሮታውንም ፡ መዘንጋት ፡ ከፍቅረ ፡ ቢጽና ፡ ከፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ መራቅ
ነው ። ወሮታውን ፡ አለመዘንጋት ፡ ግን ፤ እግዚአብሔርን ፡ ወዶ ፡ ወንድምን ፡ መው
ደድ ፡ ነው ። (ፍቅረ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይዞ ፡ ፍቅረ ፡ ቢጽን ፡ አለመለየት ፡ ነው) ።

ሐዋርያው ፡ ዮሐንስ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መውደድ ፡ ባልንጀራን ፡ ከመውደድ
ጋራ ፡ እንዲሆን ፡ ሲመክርና ፡ ሲያስተምር ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ። የሚያየውን ፡ ባል
ንጀራውን ፡ የማይወድ ፤ የማያየው ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዴት ፡ ሊወደው ፡ ይችላል
(ወዘሰ ፤ ኢያፈቅር ፡ ቢጾ ፡ ዘይሬኢ ፡ እፎ ፡ ይክል ፡ አፍቅሮቶ ፡ ለእግዚአብሔር
ዘኢይሬኢ) ።

ከዚህም ፡ አያይዞ ፡ ከሱ ፡ የተቀበልነው ፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ አለን ፤ እግዚአብሔር
ንም ፡ ባልንጀራችንንም ፡ እንወድ ፡ ዘንድ ። እግዚአብሔርን ፡ የሚወድ ፡ ባልንጀራ
ውን ፡ ይወዳል ፡ ብሏል ። ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፬ ፡ ፳ ፡ -፳፩ ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የጠቀስነው ፡ የሐዋርያው ፡ ቃል ፡ ፍቅረ ፡ ቢጽና ፡ ፍቅረ
እግዚአብሔር እንዲጠቅም ፡ አስረድቶናልና ፡ ፍቅሩን ፡ አስቀድሞ ፡ በልጁ ፡ ልደት
የገለጠልን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ወደን ፡ ወንድሞቻችንንም ፡ እሱን ፡ አብነት ፡ አድርገን
ልንወዳቸው ፡ ይገባናል ።

ፍቅረ ፡ ቢጽና ፡ ፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ከተገኘ ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ዘንድ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ አገልግሎት ፡ የለም ።

ምክንያቱም ፡ ምግባራት ፡ ሁሉ ፡ በዚሁ ፡ ስለሚመሩ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ከላይ
አርእስት ፡ አድርገን ፡ በግዕዝ ፤ ያነበብነውን ፡ ቃል ፡ እናስታውስና ፡ እግዚአብሔር
እኛን ፡ ወዶ ፡ ኃጢአታችንን ፡ እንዲያስተሠርይልንና ፡ በሞቱ 'እንዲያድነን ፡ ተቀ
ዳሚ ፡ ወይም ፡ ተከታይ ፡ የሌለው ፡ አንድ ፡ ልጁን ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ እንደላ
ከው ፡ እናስብ ።

ይህንንም ፡ እናስብ ፡ ዘንድ ፡ ወደዚች ፡ ወደበረከት ፡ ዕለት ፡ ልደቱ ፡ በጸጋው
መርቶ ፡ ስላደረሰን ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ።

---

፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጳጕሚን ፡ ፫ ፡ ቀን ።

ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ስለ ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስና ፡ ስለ ፡ አዲሱ ዘመነ ፡ ሉቃስ
ለሕዝብ ፡ ያሰሙት ፡ ቃለ ፡ ስብከት ።

በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩አምላክ ። (አሜን ።
በአብ ስም ፡ አምነን ፡ አብን ፡ ወላዲ ፡ ብለን ፤ በወልድ ፡ ስም ፡ አምነን
ወልድን ተወላዲ ፡ ብለን ፤ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ አምነን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን



ሠራጺ ፡ ብለን ፡ አካላትን ፡ ለማስረዳት ፡ ምንም ፡ ሦስት ፡ ብንል ፤ አንድ ፡ አምላክ ፡
ብለን ፡ አምነን ፡ የመጥምቁ ፡ ዮሐንስን ፡ ታሪክ ፡ እንናገራለን ።

«ቃለ ፡ ዐዋዲ ፡ ዘይሰብክ ፡ በገዳም ፡ ወይብል ፡ ጺሑአ ፡ ፍኖተ ፡ እግዚአብሔር ፡
(የእግዚአብሔርን ፡ መንገድ ፡ ጥረጉ) ፡ ብሎ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ዐዋጅ ፡ የሚነግር ፡
ተብሎ ፡ በኢሳይያስ ፡ እንደተነገረ ፤ መጥምቁ ፡ ዮሐንስ ፡ ለጌታችን ለኢየሱስ ፡ ክርስ
ቶስ ፡ መንገድ ፡ ጠራጊነቱ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

፩ኛ| ፡ ዘካርያስና ፡ ኤልሳቤጥ ፡ መካነው ፡ ሲኖሩ ፤ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ከእግዚ
አብሔር ፡ ተልኮ ፡ መጥቶ ፡ "ወንድ ፡ ልጅ ፡ ትወልዳላችሁ" ፡ ብሎ ፡ ለዘካርያስ ፡
ነገረው ።

ይኸውም ፡ አልቀረ ፤ በመልአኩ ፡ በቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ብሥራት ፡ ተወለደ ።
፪ኛ| ፡ ዮሐንስ ፡ የንስሓ ፡ ጥምቀት ፡ ሲያጠምቅ ፡ "እኔ ፡ በውኃ ፡ አጠምቃችኋለሁ ፡
ከኔ ፡ የሚበረታው ፡ አምላክ ፡ ግን ፤ በኋላ ፡ መጥቶ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያጠምቃች
ኋል" ፡ ብሎ ፡ ለክርስቶስ ፡ ጥምቀት ፡ መንገድ ፡ ጠራጊ ፡ ሆኖ ፡ አጠመቀ ።

ዮሐንስ ፡ አስቀድሞ ፡ በብሥራተ ፡ ገብርኤል ፡ እንደተወለደ ፤ ጌታም ፡ በብሥ
ራተ ፡ ገብርኤል ፡ ስለተወለደ ፤ ዮሐንስ ፡ አስቀድሞ ፡ የንስሓ ፡ ጥምቀት ፡ እንደ ፡
አጠመቀ ፤

ጌታም ፡ ከዮሐንስ ፡ በኋላ ፡ መጥቶ ፡ የወንጌልን ፡ ጥምቀት ፡ ስለ ፡ አጠመቀ ፡
የክርስቶስን ፡ መንገድ ፡ ጠራጊነቱ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ያልነው ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

"እኔ ፡ በውኃ ፡ አጠምቃችኋለሁ ፤ ከኔ ፡ የሚበረታው ፡ አምላክ ፡ ግን ፡ በኋላ ፡
መጥቶ ፡ በሙቀተ ፡ መንፈስቅዱስ ፡ ያጠምቃችኋል" ፡ ማለቱም ፡ የዮሐንስ ፡
ጥምቀት ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መወለድን ፡ አለማስገኘቱን ፡ ያስረዳል ።

የጌታ ፡ ጥምቀት ፡ ግን ፤ በሱ ፡ ስም ፡ ለሚጠመቁ ፡ ክርስቶሳውያን ፡ ሁሉ ፡
ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ መወለድን ፡ አስገኝቷል ።
የዮሐንስ ፡ አስተዳደጉ ፡ በፈጣሪው ፡ ፈቃድ ፡ ከዓለማውያን ፡ ተለይቶ ፡ ነው ። ለንጽሕና
ውና ፡ ለድንግልናው ፡ ምልክቱም ፡ ልብሱ ፡ የግመል ፡ ጠጕር ፡ ነበር ፤ መታጠቂ
ያውና ፡ ምግቡ ፡ ከዓለማውያን ፡ የተለየ ፡ ሆኖ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ይኖር ነበር ።
ማቴ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፬ ።

«ውእቱሰ ፡ የአምር ፡ ሕሊና ፡ ሰብእ ፡ እምቅድመ ፡ ኩነታ ፡ (እግዚአብሔር ፡
የሰውን ፡ ሕሊና ፡ ከመደረጓ ፡ አስቀድሞ ፡ እንድትደረግ ፡ ያውቃታል ፡) ተብሎ ፡ በሊቁ ፡
በአፈ ፡ ወርቅ ፡ እንደተነገረ ፤ ጌታ ፡ ዮሐንስ ፡ ተወልዶ ፡ የእሥራኤልን ፡ ልጆች ፡ ከኃ
ጢአት ፡ ወደ ፡ ንስሓ ፡ እንዲመልስ ፡ ዐውቆ ፡ መልአኩ ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤልን ፡ ላከ ።
ቅዱስ ፡ ገብርኤልም ፡ በተላከበት ፡ ምሥጢር ፡ "ከንተ ፡ የሚወለደው ፡ በናቱ ፡
ማኅፀን ፡ ሳለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያድርበታል" ፡ ብሎ ፡ ለዘካርያስ ፡ ነገረው ፡ ሉቃ ፡ ፩ ፡
፲፭ ። ይኸውም ፡ አልቀረ ፡ እመቤታችን ፡ ጌታን ፡ ፀንሳ ፡ ሳለች ፡ ኤልሳቤጥን ፡ ልትጠ

www.ethiopianorthodox.org

ይቅ ፡ ሔዳ ፡ ለኤልሳቤጥ ፡ ሰላምታ ፡ ብትሰጣት ፤ ኤልሳቤጥ ፡ ሰላምታውን ፡ ስትሰማ ፡ በማኅፀኗ ፡ ያለው ፡ ፅንስ ፡ ስለሰገደ ፤ "አንቺ ፡ ከሴቶች ፡ ሁሉ፡ተለይተሽ ፡ የተባረክሽ ፡ ነሽ ፡ የሆድሽም ፡ ፍሬ ፡ የተባረከ ፡ ነው ።

የጌታዬ ፡ እናት ፡ ወደኔ ፡ ትመጪ ፡ ዘንድ ፡ ለኔ ፡ እንዴት ፡ ይገባኛል„?፡ብላ ፡ በማኅፀኗ ፡ በተፀነሰው ፡ በዮሐንስ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አድሮበታልና ፡ የመልአኩን ፡ ቃል አጕልታ ፡ ተናገረች ። ሉቃ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፴፱—፵፫ ።

ዮሐንስ ፡ (ነስሑ ፡ እስመ ፡ ቀርበት መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ቀርባለችና ፡ ንስሓ ፡ ግቡ ፡ ማለቱ ፡ (ማቴ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፪ ፡) ሰው ፡ ከኃጢአት ፡ ወደንስሓ ፡ ካልተመለሰ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ አለመገኘቷን ፡ ቈርጦ ፡ መናገሩ ፡ ነው ።

ሁለተኛም "ነዋ ፡ በግዑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘያአትት ፡ ኃጢአተ ፡ ዓለም„ ፡ በደሙ ፡ የዓለምን ፡ ኃጢአት ፡ የሚያስተሠርይ ፡ የእግዚአብሔር ፡ በግ ፡ ይህ ፡ ነው። ማለቱ ፡ ሰው ፡ ከኃጢአት ፡ ወደንስሓ ፡ ተመልሶ ፡ የክርስቶስን ፡ ሥጋና ፡ ደም ፡ ካልተቀበለ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ አለመገኘቷን ፡ ቈርጦ ፡ መናገሩ ፡ ነው ።

ሰው ፡ ግን ፤ በወንጌል ፡ አምኖ ፡ ከተጠመቀ ፡ በኋላ ፤ ቀን ፡ ጥሎት ፤ ሰይጣን፡ አገብሮት ፡ ኃጢአት ፡ እንኳ ፡ ቢሠራ ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ተስፋዋን ፡ አስቦ ፤ ከኃጢአት ፡ ወደንስሓ ፡ ተመልሶ ፤ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ከተቀበለ ፡ ክርስቶስ ስለኛ ፡ ሞቶ ፤ ሁለተኛ ፡ ሞት ፡ በሌለበት ፤ ትንሣኤ ፡ ተነሥቶ ፤ በተነሣ ፡ በ፵ ፡ ቀን ፡ ሰማየ ፡ ሰማያት ፡ ዐርጎ ፡ በአባቱ ፡ ዙፋን ፡ ተካክሎ ፡ እንደተቀመጠ ፤ ሰው ፡ ሙቶ ፡ ቆይቶ ፡ ክርስቶስ ፡ ለጻድቃን ፡ ዋጋ ፡ ለኃጥአን ፡ ፍዳ ፡ ለመስጠት ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ አባቱ ፡ ክርስቶስን ፡ መስሎ ፡ ሁለተኛ ፡ ሞት ፡ በሌለበት ፡ ትንሣኤ ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ይገባል ።

ክርስቶስ ፡ አስቀድሞ ፡ በአባቱ ፡ ዙፋን ፡ እንደተቀመጠ ፤ እኛም ፡ እሱን ፡ ተከትለን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ መግባታችንን ፡ ለማስረዳት ፡ የመጥምቁ ፡ ዮሐንስን ፡ ቃል ፡ ጠቅሶ ፡ ወስዶ ፡ ሊቁ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ተዘጋጅቶልን ፡ ያለውን ፡ (ወእምዝ ፡ አምጽአ ፡ ዘንተ ፡ ዘውእቱ ፡ በአተ ፡ ክርስቶስ ፡ በእንቲአነ) ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ተስፋዋን ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፤ ክርስቶስ ፡ በአባቱ፡ዙፋን፡ መቀመጡን ፡ ተናገረ ።

የክርስቶስን ፡ መንገድ ፡ ይጠርግ ፡ ዘንድ ፡ ዮሐንስ ፡ አስቀድሞ ፡ እንደመጣ ፤ ክርስቶስ ፡ ሙቶ ፡ ተነሥቶ ፡ በአባቱ ፡ ዙፋን ፡ በመቀመጡ ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ መንገድ ፡ ለኛ ፤ ጠረገልን ።

እኛም ፤ አባታችን ፡ ክርስቶስ ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ለመድረስ ፡ ሥራ ፡ ሠርተን ፡ ጌታችን ፡ ክርስቶስን ፡ ልንከተል ፡ ይገባናል ። በሚቀድምና ፡ በሚከተል ፡ መካከል ፡ ብዙ ፡ መራራቅ ፡ የለምና ፤ የሚቀድምና ፡ የሚከተል ፡ በንዲት ፡ ጎዳና ፡



ተካክለው ፡ ይደርሳሉ ፡ ብሎ ፡ ዮሐንስ ፡ ለክርስቶስ ፡ መንገድ ፡ ጠራጊ ፡ እንደሆነ፤ ክርስቶስም ፡ በአንጻሩ ፡ ለኛ ፡ በሰውነቱ ፡ በሠራው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ የመንግሥተ፡ ሰማይን ፡ መንገድ ፡ መጥረጉን ፤ እኛም ፡ ሥራ ፡ ሠርተን ፡ አባታችን ፡ ክርስቶስ፡ በጠረገልን ፡ መንገድ ፡ ተከትለን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ መግባታችንን ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ አራቶ ፡ ተርጕሞታል ፡ ድርሳን ፡ ፲ ።

የመጥምቁ ፡ ዮሐንስን ፡ ታሪክ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ዮሐንስ ፡ ጠቅሶ ፡ ወስዶ ፡ አራቶ ፡ መተርጐሙን ፡ ከተናገርን ፡ ወደ ፡ ዕረፍቱ ፡ እንመለስ ።

መጥመቁ ፡ ዮሐንስ ፡ በገሊላ ፡ ሲሰብክና ፡ ሲያጠምቅ ፡ ንጉሡ ፡ ሄሮድስ፡ነበረ። እሱ ፡ የወንድሙን ፡ የፊልጶስን ፡ ሚስት ፡ ቢያገባ ፡ ዮሐንስ ፡ የወንጌል ፡ ሥርዓት፡ መንገድ ፡ ጠራጊ ፡ ሆኖ ፡ መነሣቱን ፡ ተመልክቶ ፡ እንደቀድሞው ፡ ሥርዓት፡የወንድምህን ፡ ሚስት ፡ መውረስ ፡ አይገባህም ፡ ብሎ ፡ ስለገሠጸው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ሄሮድስ ፡ በወህኒ ፡ ቤት ፡ አሠረው ።

ሄሮድስም ፡ የተወለደበትን ፡ ቀን ፡ በዓል ፡ ለማክበር ፡ መኳንንቱንና ፡ ሠራዊቱን ፡ አስጠርቶ ፤ ባዳራሽ ፡ ግብር ፡ አግብቶ ፡ ሲበላ ፡ ሲጠጣ ፡ ሄሮድስ ፡ ያገባት ፡ የሄሮድያዳ ፡ ልጅ ፡ ወደአዳራሽ ፡ ገብታ ፡ በሄሮድስ ፡ ፊት ፡ ብትዘፍን ፡ የምትፈልጊውን ፡ ነገር ፡ ለምኝኝ ፤ አላስቀርብሽም ፡ ብሎ ፡ ማለላት ።

እሷም ፡ ሔዳ ፡ የሄሮድስን ፡ ነገር ፡ ለእናቷ ፡ ብትነግራት ፤ እናቷም ፡ ሄሮድስ ፡ እንዳያገባት ፡ ዮሐንስ ፡ መከልከሉን ፡ ታውቃለችና ፤ የዮሐንስን ፡ ራስ ፡ አስቈርጠህ ፡ በጻሕል ፡ ስጠኝ ፡ በዪው ፡ ብላ ፡ መከረቻት ። ልጅቷም ፡ እናቷ ፡ እንደመከረቻት ፡ ሔዳ ፡ ለሄሮድስ ፡ ብትነግረው ፡ ሄሮድስ ፡ ስለ ፡ መሐላው ፡ አዘነ ።

ነገር ፡ ግን ፤ ያደረበት ፡ ሰይጣን ፡ የዮሐንስን ፡ ራስ ፡ ቈርጦ ፡ እንዲሰጣት ፡ ስላስጨከነው ፡ ቆርጣችሁ ፡ ስጧት ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።

ሕዝቡ ፡ ዮሐንስን ፡ ያከብሩት ፡ ነበርና ፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ ከንጉሡ ፡ አፍ ፡ በመውጣቱ ፡ የልደቱ ፡ በዓል ፡ ደስታ ፡ ተለውጦ ፡ ለሕዝቡ ፡ ኃዘን ፡ ሆነባቸው ።

የታዘዙትም ፡ ባለወጎች ወደወህኒ ፡ ቤት ፡ ሔደው ፡ የዮሐንስን ፡ ራስ ፡ ቈርጠው ፡ ለሄሮድያዳ ፡ ልጅ ፡ በጻሕል ፡ ሰጧት ።

ልጅቱም ፤ ወስዳ ፡ ለናቷ ፡ ሰጠቻት ። (ወርእሱሰ ፡ ለዮሐንስ ፡ ድኅረ ፡ ተመትረት ፡ ዐርገት ፡ ውስተ ፡ አየር ፡) የዮሐንስ ፡ ራስ ፡ ግን ፤ ከተቈረጠች ፡ በኋላ ፤ ወደ አየር ፡ ወጥታ ፡ (ኢይደልወከ ፡ ከመ ፡ ትንሣእ ፡ ብእሲተ ፡ እኁከ ፡) የወንድምህን ፡ ሚስት ፡ ታገባ ፡ ዘንድ ፡ አይገባህም ፡ እያለች ፡ ሄሮድስ ፡ ሠውሮ ፡ ስለሠራው ፡ ሥራ፡ ዙራ ፡ በግልጥ ፡ ሰበከች ።

ይኸውም ፡ ልማድ ፡ ነው ፤ ቃኤል ፡ የወንድሙን ፡ የአቤልን ፡ ደም ፡ ሠውሮ ፡ ቢያፈስስ ፡ የአቤል ፡ ደም ፡ (ቃኤል ፡ እኁየ ፡ ቀተለኒ ፡) ብላ ፡ በግልጥ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኸች ።

www.ethiopianorthodox.org

የጻድቃን ፡ የቅዱሳን ፡ የሰማዕትነታቸው ፡ ምስክርነት ፡ እንደ ፡ ሐብል ፡ የተያያዘ ፡ ነው ። የኃጥአንም ፡ የጭከኔ ፡ ሥራቸው ፡ የተያያዘ ፡ ነው ። የዮሐንስንም ፡ ሥጋውን ፡ ተማሪዎቹ ፡ ወስደው ፡ ቀብረውት ፡ ነበርና ፤ የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አትናቴዎስ ፡ ሐዋርያዊ ፡ በተሾመ ፡ ጊዜ ፡ የዮሐንስን ፡ ሥጋውን ፡ ከተቀበረበት ፡ አፍልሶ ፡ ወስዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሠርቶበታል ።

ዮሐንስም ፡ ሰማዕትነት ፡ የተቀበለበት ፡ መስከረም ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ ነው ። ሊቃውንት ፡ ግን ፤ ዮሐንስ ፡ የሰማዕታት ፡ ሐዲስ መጀመሪያ ፡ ሆኖ ፡ ስለተገኘ ፤ በዓሉ ፡ ሁልጊዜ ፡ የዓውደ ፡ ዓመት ፡ መጀመሪያ ፡ ይሁን ፡ ብለው ፡ በመስከረም ፡ ፩ ቀን ፡ እንዲከበር ፡ ወስነዋል።

ስለዚህም ፡ አራቱን ፡ ዘመኖች ፡ ሲያዛውራቸው ፡ ይኖራል ። ስለ ፡ እስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ድሜጥሮስም ፤ ጥቂት ፤ ታሪክ ፡ እንናገራለን ።

እግዚአብሔር ፡ የሚሠራውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ለበዓለ ፡ ዕድሉ ፡ ያሳስበዋልና ፡ ቅዱስ ፡ ድሜጥሮስ ፡ በእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በተሾመ ፡ ጊዜ ፤ ከወንድሞቹ ፡ ሁሉ ፡ ተመርጦ ፤ ከፍጥረት ፡ ዓለም ፡ ጀምሮ ፡ ያለውን ፡ ዘመን ፡ በቀመር ፡ አግብቶ ፡ ቈጥሮ ፡ በአራት ፡ ዘመናት ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኙት ፡ ትልልቆች ፡ አጽዋማትና ፡ በዓላት ፡ ወሰን ፤ ልክና ፡ መጠን ፡ በመስጠት ፤ ያደረውን ፡ ሌሊት ፡ ለማወቅ ፡ በአበቅቴ ፡ ላይ ፡ ዕለትንና ፡ ሕፀፅን ፡ ጨምሮ ፤ በዓመት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ አጽዋማትንና ፡ በዓላትን ፡ ለማወቅ ፡ በመጥቅዕ ፡ ላይ ፡ የዕለት ፡ ተውሳክን ፡ ጨምሮ ፡ ነነዌ ፡ የምትገባበትን ፡ ቀን ፡ አስረድቶዋል ፡ (ነነዌን ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡) በነነዌ ፡ ላይ ፡ የአጽዋማትንና ፡ የበዓላትን ፡ ተውሳክ ፡ ጨምሮ ፡ አጽዋማትና ፡ በዓላት ፡ የሚውሉበትን ፡ ወራትንና ፡ ቀኑን ፡ ከቀመረ ፡ (ከቈጠረ) ፡ በኋላ ፤ ይህንን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ገልጾለት ፡ የወሰነውን ፡ ነገር ፡ በዓለም ፡ ላሉት ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳትና ፡ ሊቃውንት ፡ ጽፎ ፡ ቢልክላቸው ፤ እነሱም ፡ ለወንድማችን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የምትተዳደርበትን ፡ ትልቅ ፡ ነገር ፡ እግዚአብሔር ፡ ገልጾለታል ። ብለው ። ጽሑፉን ፡ ተቀብለው ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግነዋል ።

ይህም ፡ ድሜጥሮስ ፡ የወሰነው ፡ የቍጥር ፡ መጽሐፍ ፡ በያመቱ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ በዓመት ፡ መጀመሪያ ፡ (በቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ ዕለት ፡) ሲነገር ፡ ይኖራል ።

መነገሩም ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የተዋሕዶ ፡ ሃይማኖቱንና ፡ የሃይማኖቱን ፡ መከበሪያ ፡ ጾምን ፡ በጣም ፡ ስለወደደ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ የዮሐንስ ፤ የድሜጥሮስ ፤ የሉቃስ ፤ (የሦስቱ ፡ ቅዱሳን ፡) አምላክ ፡ ንጉሡን ፡ ከነሠራዊቱ ፡ ጠብቆ ፡ ከዘመነ ፡ ሉቃስ ፡ ወደ ፡ ዘመነ ፡ ዮሐንስ ፡ ያሻግርልን ።

(አሜን ።)



ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳ ፡ ቀን ፤ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የልደትን ፡

<u>በዓል ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ የተናገሩት ፡ ቃለ ፡ ምዕዳን ።</u>

ወአመ ፡ በጽሐ ፡ ዕድሜሁ ፡ ፈነወ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልዶ ፡ ወተወልደ ፡ እምብእሲት ፡ ወገብረ ፡ በሕገ ፡ ኦሪት ፡ ከመ ፡ ይሣየጦሙ ፡ ለእለ ፡ ውስተ ፡ ኦሪት ፡ ወከመ ፡ ንርከብ ፡ ትርሲተ ፡ ወልድ) ፡ ጊዜው ፡ ሲደርስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጁን ፡ ልኮ ፡ ከእመቤታችን ፡ ተወለደ ፡ በኦሪት ፡ ያሉትን ፡ ይገዛቸው ፡ ዘንድ ፡ የኦሪትን ፡ ሥርዓት ፡ ሠራ ፡ ገላ ፡ ም ፬ ፡ ቍ ፡ ፯ ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ የሐዋርያው ፡ ቃል ፤ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነፃነትንና ፡ አንድነትን ፤ ሰጥቶ ፡ ከማናቸውም ፡ ይልቅ ፡ ተፈጥሮተ ፡ ሰብእ ፡ የከበረ ፡ ሲሆን ፤ ሕግን ፡ መፈጸም ፡ ስለተሳነው ፡ ከሰው ፡ ወገን ፡ ተወልዶ ፡ ሰውን ፡ ማዳኑን ፡ ያበሥረናል ።

ይህንንም ፡ በምናስብበት ፡ ጊዜ ፤ በድሎ ፡ ንስሐ ፡ ባለመግባት ፡ የመጣውን ፡ ውርደትና ፡ በድሎ ፡ ንስሐ ፡ በመግባት ፡ የተገኘውን ፡ ክብር ፡ መመልከት ፡ ይገባናል ። በድሎ ፡ ንስሐ ፡ ባለመግባት ፡ የተዋረደ ፡ ዲያብሎስ ፡ ነው ።

በድሎ ፡ ንስሐ ፡ በመግባቱ ፤ በክብረ ፡ ልደቱ ፡ የከበረ ፡ አባታችን ፡ አዳም ፡ ነው ። የዛሬው ፡ በዓለ ፡ ልደቱ ፤ መላእክት ፡ ከተፈጠሩበት ፡ ዕለተ ፡ እሑድ ፡ ጋር ፡ በመተባበሩ ፡ ከመላእክት ፡ ተፈጥሮ ፤ ጥቂት ፡ እንናገራለን ።

እግዚአብሔር ፤ በጥንተ ፡ ፍጥረት ፡ መላእክትን ፡ ነባብያን ፤ ለባውያን ፡ ሕያዋን ፡ ሳጥናኤልንም ፡ አኃዜ ፡ መንጦላዕት ፡ ቅሩብ ፡ መንበር ፡ አድርጎ ፡ ፈጥሮአቸው ፡ ነበረ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አመስግን ፡ ቢሉት ፡ አመስግኑኝ ፤ ቀድስ ፡ ቢሉት ፡ ቀድሱኝ ፡ ስላለ ፤ ሳጥናኤል ፡ መባሉ ፡ ቀርቶ ፡ ዲያብሎስ ፡ ተብሏል ። ወገኖቹም ፡ መላእክት ፡ መባላቸው ፡ ቀርቶ ፡ ስሑታን ፡ አጋንንት ፤ ርኩሳን ፡ መናፍስት ፡ ተብለዋል ።

ዲያብሎስ ፡ ከወገኖቹ ፡ ጋር ፡ በንስሐ ፤ ተመልሶ ፡ ቢሆን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባሕርዩ ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ነውና ፡ ይቅርታ ፡ ሳያገኝ ፡ አይቀርም ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፤ እሱ ፡ ከክህደቱ ፡ ባለመመለሱ ፤ እግዚአብሔር ፡ ይቅር ፡ ባለማለቱ ፡ ጸና ። ስለዚህ ፤ ንስሐ ፡ ከዲያብሎስ ፡ እንደሰማይ ፡ ስለራቀ ፡ በፍዳ ፡ ተጨንቆ ፡ ይኖራል ።

ስሕተትም ፤ በዲያብሎስ ፡ ብቻ ፡ ተወስኖ ፡ የሚቀር ፡ ስላልሆነ ፤ ወደሰው ፡ ባሕርይ ፤ ተላልፏል ። በጥንተ ፡ ፍጥረት ፡ መምህራን ፡ አልተነሡም ። መጻሕፍት ፡ አልተጻፉም ፡ ነበርና ፤ እግዚአብሔር ፡ ፍሬ ፡ በለስ ፡ ወደሕገ ፡ ልቡና ፡ እንድታደርስ በማወቁ ፤ ሕግ ፡ ለመጠበቅ ፡ ምልክት ፡ ለገዥነትና ፡ ለተገዥነትም ፡ መታወቂያ ፡

www.ethiopianorthodox.org

እንድትሆን ፡ ለአዳምና ፡ ለሔዋን ፡ ሕግ ፡ አድርጎ ፡ እንዲጠብቋት ፡ እንጂ ፡ እንዳይበሏት ፡ አዘዛቸው ። ቢበሏት ፡ ግን ፤ የሞት ፡ ሞት ፡ እንዲፈረድባቸው ፡ አስታወቃቸው ።

እነሱም ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፤ ዲያብሎስ ፡ ፍሬ ፡ በለስን ፡ ብትበሉ ፡ አምላክ ፡ ትሆናላችሁ ፡ ብሎ ፡ አታሎ ፡ ፍሬ ፡ በለስን ፡ ስለበሉ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ተረገሙና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጸጋ ፡ አጥተው ፡ የሞት ፡ ሞት ፡ ተፈርዶባቸው ፡ ከገነት ፡ ወጡ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፤ የፈጣሪያቸውን ፡ ምሕረት ፡ ለማግኘት ፡ ንስሐ ፡ ገብተው ፡ ስለ አለቀሱ ፡ ከልጅ ፡ ልጃቸው ፡ ተወልዶ ፡ እንዲያድናቸው ፡ ቀጠሮ ፡ ሰጣቸው ።

ቀጠሮውም ፡ እስኪደርስ ፡ ነቢያትን ፡ እያስነሣ ፡ መውረዱን ፤ መወለዱን ፡ በትንቢት ፡ እያናገረ ፡ የሰጣቸውን ፡ ተስፋ ፡ በጽኑ ፡ እምነት ፡ ላይ ፡ መሠረተ ።

ከነቢያትም ፤ ቃሉ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የሚታሰበው ፡ ኢሳይያስ ፡ (ድንግል ፡ ትፀንስ ፡ ወትወልድ ፡ ወልደ) ፡ ድንግል ፡ በድንግልና ፡ ፀንሳ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ትወልዳለች ፡ ብሎ ፡ በተናገረው ፡ መሠረት ፡ ቀጠሮው ፡ ሲደርስ ፡ በድንግልና ፡ ፀንሳ ፡ በድንግልና ፡ መውለዷን ፡ ያበሥራት ፡ ዘንድ ፡ መልአኩ ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤልን ፡ ወደ ፡ ድንግል ፤ ማርያም ፡ ላከ ።

እመቤታችንም ፡ ቃሉን ፡ አምና ፡ እንደቃልህ ፡ ይደረግልኝ ፡ በማለቷ ፤ አካላዊ ፡ ቃል ፡ በማኅፀኗ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ሆኖ ተፀነሰ ።

ያለዘር ፡ በመፀነሱም ፤ ሰይጣን ፡ ያመጣውን ፡ የማኅፀን ፡ ቍራኝነት ፡ አጥፍቶ ፡ በዘጠኝ ፡ ወር ፡ ከምስት ፡ ቀን ፡ ዛሬ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ እነሆ ፡ ተወለደልን ።

ጌታ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ መወለዱ ፤ ለሕዝብም ፡ ለአሕዛብም ፡ ብርሃን ፡ ልደቱን ፡ አሳይቶ ፡ ለማሳመንና ፡ ለሁሉም ፡ መንፈሳዊ ፡ ነፃነትን ፡ ለመስጠት ፡ ነው ።

እስራኤል ፡ ከምድረ ፡ ግብፅ ፡ ወጥተው ፡ ወደከነአን ፡ ሲጓዙ ፤ ባላቅ ፡ ወልደ ፡ ሶፎር ፡ ባመጣጣቸው ፡ ስለፈራ ፤ በለዓምን ፡ አስጠርቶ ፡ እስራኤልን ፡ እንዲረግምለት ፤ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ሰጠው ።

በለዓምም ፡ እንደልማዱ ፡ ሊረግም ፡ ከፍ ፡ ካለ ፤ ቦታ ፡ ሆኖ ፤ የእስራኤልን ፡ ሠፈር ፡ ሲመለከት ፡ እግዚአብሔር ፡ መርገሙን ፡ ወደበረከት ፡ ስለመለሰበት ፤ (ኮከብ ፡ ይሠርቅ ፡ እምያዕቆብ ፡ ወየአትት ፡ ኀጢአተ ፡ እምእስራኤል) ፡ በኮከብ ፡ የተመሰለ ፡ ጌታ ፡ ከያዕቆብ ፡ ወገን ፡ ይወለዳል ። የእስራኤልንም ፡ ኀጢአት ፡ ያስተሠርያል ፡ ብሎ ፡ የጌታን ፡ ልደት ፡ ተናግሮ ፡ ነበር ። ዘኍ ፡ ም፡፳፫ ፡ ቍ ፡ ፳ ም ፡ ፳፬ ፡ ቍ ፳–፲፰ ።

ዝረደሽት ፡ የተባለውም ፡ ፈላስፋ ፡ ፍልስፍና ፡ ሲመለከት ፡ ድንግል ፡ በሠሌዳ ፡ ኮከብ ፡ ተሥላ ፤ ሕፃኑን ፡ አቅፋ ፡ አየ ። ይህን ፡ በብረት ፡ ቀርጾ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ኮከብ ፡ ሲወጣ ፡ ሰማያዊ ፡ ንጉሥ ፡ ይወለዳልና ፡ ይህን ፡ በቤተ ፡ መዛግብት ፡ ያለውን ፡ ወርቅ ፤ ዕጣን ፡ ከርቤ ፡ ወስዳችሁ ፡ ገብሩለት ፡ ብሎ ፡ ለልጆቹ ፡ ሰብአ ፡ ሰገል ፡ ማሳሰቢያ ፡ ጽፎ ፡ አኑሮላቸው ፡ ነበር ።



የምሥራቅ ፡ ነገሥታት ፡ ይህን ፡ በመመልከት ፡ የጌታ ፡ መልክ ፡ የተሣለበት ፡ ኮከብ ፤ በወጣ ፡ ጊዜ ፤ በኮከቡ ፡ መሪነት ፡ ተጕዘው ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ገቡ ።

ጌታ ፡ ወደ ፡ ተወለደበት ፡ በዓትም ፡ በደረሱ ፤ ጊዜ ኮከቡ ፡ በበዓቱ ፡ ላይ ፤ ቆመ ፡ (በጣት ፡ ጠቅሶ ፡ እንደማሳየት) ፡ ወደበዓቱም ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፤ እመቤታችን ፡ በድንግልና ፡ ጌታን ፡ ወልዳ ፡ አገኙ ። አምላክነቱን ፡ ሲመሰክሩ ፡ ወርቅ ፤ ዕጣን ፤ ከርቤ ፡ ገብረውለታል ።

አሁንም ፡ እላይ ፡ በልደቱ ፡ የተሰጠውን ፡ መንፈሳዊ ፡ ነጻነት ፡ ደስ ፡ እንዳሰኘን ፡ እንዲሁም ፡ በልዩ ፡ ቸርነቱ ፡ የታሪክ ፡ ዕድል ፡ የተሰጣቸው ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴን ፡ በማስነሣቱ ፡ በባዕድ ፡ ሥልጣን ፡ ተረግጣ ፡ የነበረች ፡ ኤርትራን ፡ በዚህ ፤ ወራት ፡ ነጻ ፡ አውጥቶ ፡ ከናቷ ፡ እንድትቀላቀል ፡ ማድረጉ ፡ የበለጠ ፡ ደስታ ፡ ሆነልን ።

በዕለተ ፡ ልደቱ ፡ መላእክትና ፡ኖሎት ፡ አንድ ፡ ሆነው ፡ እንዳመሰገኑና ፡ ኢትዮጵያም ፤ ኤርትራም ፡ ስብሓት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በሰማያት ፡ ወሰላም ፡ በምድር ፡ ሥምረቱ ፡ ለሰብእ ፡ እያሉ ፡ ምስጋናቸውን ፡ አንድ ፡ ሆነው ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ላደረገ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ምስጋና ፡ ይድረሰው ።

ከዘርአ ፡ አብርሃም ፡ መወለዱን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ተናግረናል ።

ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ እኛን ፡ ስለማዳን ፤ በአርእስቱ ፡ እንደተገለጠ ፡ ቀጠሮውን ፡ ሳያሳልፍ ፡ ሰው ፡ መሆኑን ፡ እያሰብን ፡ ለጌትነቱ ፡ የምናቀርበው ፡ አንክሮ ፡ ይህ ፡ ነው ።

አቤቱ ፡ መድኀኒታችን ፡ ሆይ ፡ ለፀሐይ ፤ ለጨረቃ ፤ ለከዋክብት ፡ ብርሃንን ፡ ያለበስክ ስትሆን ፡ ለእኛ ፡ ብለህ ፡ በክብት ፡ በረት ፡ በጨርቅ ፡ ተጠቀለልክ ።

አቤቱ ፡ መድኀኒታችን ፡ ሆይ ፤ የሰማይና ፡ የምድር ፡ ስፋት ፡ በእጅህ ፡ የተጨበጠ ፡ ሲሆን ፡ ዘጠኝ ፡ ወር ፡ ከምስት ፡ ቀን ፡ በጸባብ ፡ ማሕጸን ፡ አድረህ ፡ ተወለድኽ ።

## ቃለ ፡ በረከት ።

ይቅርታ ፡ ለሁላችን ፡ ይደረግልን ።

የሰማያዊ ፡ አባታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በረከት ፡ ለሁላችን ፡ ይሁን ።

ንጉሣችን ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴን ፡ በዕድሜ ፡ አሰንብቶ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ያሰቡላትን ፡ ሁሉ ፡ ለመፈጸም ፤ ያብቃልን ።

ዕድሜና ፡ ሕይወት ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነን ።

ለልዑላን ፡ ልጆቻቸውና ፡ ለንጉሣውያን ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ሕይወትና ፡ ጤና ።

የተቀደሰ ፡ ቡራኬና ፡ ሰላምን ፡ ለልዑላን ፡ መሳፍንት ። ለክቡራን ፡ መኳንንት ፡

www.ethiopianorthodox.org

ለክቡራት ፡ ወይዛዝር ፡ ለቡሩካን ፡ ካህናትና ፡ ለመላው ፡ ማኅበረ ፡ ክርስቲያን ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ ይስጥልን ።

በረከተ ፡ ልደቱ ፡ በሁሉችን ፡ ይደር ፡ አሜን ።

---

ጳጉሜን ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፬ ዓ ፡ ም ፡ ፡ በርእሰ ፡ ዐውደ ፡ ዓመት ፡ ዋዜማ ፡ ብፁዕ ፡ ሊቀ ፡

## ጳጳሳት ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ለሕዝብ ፡ ያሰሙት ፡ ቃለ ፡ ስብከት ።

ለማኅበረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ እለ ፡ ተቀደሱ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወተሰምዩዩ ፡ ቅዱሳነ ፡ ወለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይጼውዑ ፡ ስሞ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በኵሉ ፡ በሐውርቲሆሙ ፡ ወለነሂ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ጸጋ ፡ ወሰላም ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቡነ ፡ ወእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘልፈ ፡ አአኵቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በእንቲአክሙ ፡ ወበእንተ ፡ ጸጋሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘተውህበ ፡ ለክሙ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፩-፫ ።

ሰላም ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ የምትገኘው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ነው ። ሰላም ፡ የባሕርዩ ፡ ስለሆነች ፡ የሚያርቃትም ፡ የሚያቀርባትም ፡ እግዚአብሔር ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍጥረቱን ፡ በሰላም ፡ ለማስተዳደር ፡ ስለፈለገ ፡ ከተንቀሳቃሽ ፡ ሥነ ፡ ፍጥረቶች ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ባለአእምሮ ፡ ሰው ፡ ድረስ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ እያደረገ ፡ ከፈጠረ ፡ ጀምሮ ፡ ተንቀሳቃሾቹ ፡ ሕግን ፡ ሳይተላለፉ ፡ በየወገናቸው ፡ ተስማምተው ፡ ይኖራሉ ።

ሰው ፡ ግን ፡ የሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ገዥ ፡ አድርጎ ፡ ቢፈጥረው ፡ ፍጡርነቱን ፡ በመዘንጋት ፡ ፈጣሪነትን ፡ ተመኝቶ ፡ ሕግን ፡ ስለተላለፈ ፡ እንዲጠብቃት ፡ የተሰጠችው ፡ ሰላምን ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ አሰናከላትና ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የ፭ ፡ ሺህ ፡ ፭፻ ፡ ዘመን ፡ ግዞትና ፡ ቅጣት ፡ ተፈርዶበት ፡ በጥፋቱ ፡ ሲያዝንና ፡ ሲጸጸት ፡ ኖረ ።

የልጅ ፡ መሪውና ፡ መምህሩ ፡ አባቱ ፡ የሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ነው ። አባቱ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሲሠራ ፡ ቢያየው ፡ ያንኑ ፡ ያጠናል ። መልካም ፡ ሥራ ፡ ሲሠራ ፡ ቢያየው ፡ ግን ፡ መልካሙን ፡ ሥራ ፡ ያጠናል ።

ቃየል ፡ አባቱ ፡ አዳም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ሰላም ፡ መሳሳቱን ፡ ስለተመለከተ ፡ እኔም ፡ አንዱን ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ልያዝ ፡ እንደማለት ፡ ከሰላም ፡ በተለየ ፡ መንፈስ ፡ ተመርቶ ፡ ወንድሙን ፡ አቤልን ፡ ገደለ ።

ሰው ፡ አያየኝም ፡ ብሎ ፡ ሠውሮ ፡ መሥራትን ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ስለመሠረታት ፡ የአቤል ፡ ደም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አመልክታ ፡ ሠውሮ ፡ የሠራውን ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ገለጠችና ፡ አስፈረደችበት ።



እግዚአብሔርም ፡ በአቤል ፡ ደም ፡ ምክንያት ፡ ዓለም ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ ፍርድ ፡ (ኩን ፡ ርዑደ ፡ ወድንጉፀ ፡) ፈርተህ ፡ ተንቀጥቅጠህ ፡ ኑር ፡ ብሎ ፡ ፈረደበት ።

እንዲሁም ፡ እግዚአብሔር ፡ በየጊዜው ፡ በሚነሡት ፡ ነገሥታት ፡ እያደረ ፡ ይህን ፡ ፍርድ ፡ በነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ ላይ ፡ ሲፈርደው ፡ ይኖራል ።

እግዚአብሔር ፡ አያይብኝም ፡ ሰው ፡ አያውቅብኝም ፡ ብሎ ፡ ሠውሮ ፡ የሠሩት ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፍርድ ፡ መገለጡ ፡ እንደማይቀር ፡ ይህ ፡ ያስረዳል ።

ክፉውን ፡ ትቶ ፡ ደገኛውን ፡ ለመከተል ፡ የትዕግሥት ፡ ሰዎችን ፡ አብነት ፡ ማድረግ ፡ ያስፈልጋል ። የሥራዎችም ፡ መሪ ፡ ትዕግሥት ፡ እንደሆነ ፡ የአብርሃምና ፡ የኢዮብ ፡ ታሪክ ፡ በአንቀጸ ፡ መጻሕፍት ፡ ሁሉ ፡ ተጽፎ ፡ ያስታውሰናል ።

ብርሃነ ፡ ዓለም ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ በሥጋም ፡ ሆነ ፡ በነፍስ ፡ ሰላም ፡ የሥራ ፡ ሁሉ ፡ መሠረት ፡ መሆኑን ፡ ሲያስረዳ ፡ በ፲፬ ፡ መልእክቶቹ ፡ ሰላምን ፡ አርእስት ፡ አድርጎ ፡ ሃይማኖትን ፡ እያስከተለ ፡ የሃይማኖት ፡ መገለጫ ፡ የሆኑ ፡ ጸሎትን ፡ ፍቅርን ፡ ትሕትናን ፡ ምጽዋትን ፡ እየቀጠለ ፡ ጽፎ ፡ ሰላምን ፡ የተመሉ ፡ መልእክቶቹን ፡ በዐሥራ ፡ አራት ፡ ክፍሎ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለወለዳቸው ፡ ምእመናን ፡ ሁሉ ፡ ስለላከ ፡ ሰላምን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ አንግሦዋታል ።

የሰላምም ፡ ዋና ፡ መሠረት ፡ በገዥዎች ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ ነው ። ሐዋርያው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ « ገዥ ፡ ለሆነ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተገዙ ። ገዥ ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ አይሾምምና ፡ ብሏል ።

እንግዴህ ፡ ገዥ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ከተሾመ ፡ በእሱ ፡ አድሮ ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ የሚፈርድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነውና ፡ ቢያሥርም ፡ ቢፈታም ፡ ሥልጣን ፡ ሁሉ ፡ በእጁ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ እያሳፍርም ።

በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ለተሾመ ፡ ገዥ ፡ አልገዛም ፡ ብሎ ፡ የሚያምጥ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ አልቀበልም ፡ ማለቱ ፡ ነውና ፡ ፍዳው ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ እንዲሆን ፡ አይጠረጠርም ።

ገዥዎችም ፡ ጽኑዕ ፡ ፍርድን ፡ የሚፈርዱ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ አፍርሶ ፡ ክፉ ፡ ሕሊናው ፡ እንደመራው ፡ በራሴ ፡ ፈቃድ ፡ እኖራለሁ ፡ በሚል ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ተቀብሎ ፡ የገዥዎችን ፡ ፈቃድ ፡ ፈጽሞ ፡ በሚኖር ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የሚያስፈራ ፡ ግርማቸውን ፡ ሊያመጡበት ፡ አይፈልጉም ።

ሐዋርያውም ፡ መንፈሳዊ ፡ ምክሩን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ነግሮናል ፡ አንተ ፡ ሰው ፡ ገዥዎችን ፡ እንዳትፈራቸው ፡ ልትሆን ፡ ብትወድ ፡ ራስህን ፡ ዝቅ ፡ አድርገኽ ፡ ተገዛላቸው ። እነሱም ፡ በትሕትና ፡ ሥራህ ፡ ያመሰግኑኻል ።

www.ethiopianorthodox.org

እነሱ ፡ እውነትን ፡ የሚከተሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልክተኞች ፡ እንደመሆ
ናቸው ፡ መጠን ፤ ጥፋተኛውን፡የሚቀጡበትን ፡ ሰይፍ ፡(ሥልጣን) ፡እንዲያው ፡ በከንቱ፡
አልሰጣቸውም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ አፍርሶ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ የሚሠራውን፡
እንዲቀጡበት ፡ ነውና ፡ የሰላም ፡ ተቃዋሚ ፡ ሳይሆኑ ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ለንጉሥ፡
መገዛት ፡ የተገባ ፡ ሕግ ፡ ነው ።

የምትሠሩትን ፡ ሁሉ ፡ በስምምነት ፡ ሥሩ ። ግብር ፡ ለሚገባው ፡ ግብሩ፡
ክብር ፡ የሚገባውን ፡ አክብሩ ፡ ብሎ ፡ ያለሰላምና ፡ ያለፍቅር ፡ የሚጠቅም ፡ ሥራ፡
አለመኖሩን ፡ በሰፊው ፡ ዘርዝሮ ፡ ጽፎልናል ። ሮሜ ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ቍ ፡ ፩—፰ ።

ሹመትም ፡ ያለፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የማይገኝ ፡ መሆኑን ፡ ከዚህ ፡ የሚ
ከተለው ፡ ታሪክ ፡ ያስረዳል ።

እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ ጠርቶ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ መስፍን ፡ አድርጎ ፡ በሾ
መው ፡ ጊዜ ፡ ወንድሙን ፡ አሮንንም ፡ ለሕገ ፡ ኦሪትና ፡ ለደብተራ ፡ ኦሪት፡
ካህን ፡ አድርጎ ፡ ሾሞት ፡ ነበር ።

በኋላ ፡ ግን ፤ ዳታንና ፡ አቤሮን ፡ በራሳቸው ፡ ፈቃድ ፡ የሙሴን ፡ መስፍ
ንነት ፡ እንሾማለን ፤ ደቂቀ ፡ ቆሬ ፡ የአሮንን ፡ ሊቀ ፡ ካህናትነት ፡ እንወስዳለን፡
ብለው ፡ ቢነሡ ፡ ፍትሐ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ጥፋ
ትን ፡ አምጥቶባቸዋል ። ዘኍልቍ ፡ ፲፮ ፡ ፩—፴፯ ።

ስለዚህ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲችልለት ፡ ባወቀ ፡ ገንዘብ ፡ መርጦ፡
የሾመውን ፡ መቃወም ፡ እግዚአብሔርን ፡ መቃወም ፡ እንደሆነ ፡ እንመልከት ።

ዛሬም ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ፈቃድ ፡ ሳይመለከት ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ክብር፡
ለማግኘት ፡ የሚጣጣር ፡ ሰው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ አንድነት ፡ እንደሌለው፡
በዚህ ፡ ዕንወቅ ።

ሰላም ፡ ለሥራ ፡ ሁሉ ፡ መሠረት ፡ እንደሆነች ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡
በመዋዕለ ፡ ስብከቱ ፡ ለተማሪዎቹ ፡ (ሰላምየ ፡ አኀድግ ፡ ለክሙ ፤ ወሰላመ ፡ ዚአየ፡
እሁበክሙ ፤) ሰላምን ፡ አሳድርባችኋለሁ ። (ዮሐ ፡ ፲፬ ፡ ፳፯ ፡) ብሎ ፡ ሰላማውያን፡
ሆነው ፡ የሚኖሩበትን ፡ ተስፋ ፡ ነግሯቸዋል ።

ሰላም ፡ የዓለም ፡ መተዳደሪያ ፡ መሆኗን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለሐ
ዋርያት ፡ በቃሉ ፡ ከነገራቸው ፡ ሰላም ፡ የሕይወታችን ፡ መሠረት ፡ እንደሆነች ፡ እንመን፡

በወዲያኛውም ፡ ዓለም ፡ ነፍስን ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋር ፡ አስታርቃ ፡ ወደ ፡ መን
ግሥተ ፡ ሰማያት ፡ መሪ ፡ ሆና ፡ የምታገባ ፡ ሰላም ፡ ናትና ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡
ሰላምን ፡ እንዲሰጠንና ፡ ስለኛ ፡ በወዳጆቹ ፡ ላይ ፡ የተናገረውን ፡ የይቅርታውን ፡ ተስፋ ፡
እንዲፈጽምልን ፡ በሃይማኖት ፡ የተመሠረተ ፡ ቅን ፡ ሕሊናን ፡ ያሳድርብን ።

ነቢዩ ፡ ዳዊት የተናገረው ፡ ትንቢት ፤ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ሀገሩ ፡ ስለ ፡ ኢየሩሳ
ሌም ፡ ብቻ ፡ ወይም ስለ ፡ ወገኖቹ ፡ እስራኤል ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።



ስለ ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ሲናገር ፡ በ፹፭ኛው ፡ መዝሙር ፡ አቤቱ ፡ ምድር
ህን ፡ ይቅር ፡ አልኻት ብሎአል ።

የሰው ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ ይህንን ፡ ትንቢት ፡ ተስፋ ፡ በማድረግ ፡ ይቅርታን ፡
ከእግዚአሔር ፤ ቢለምን ፤ ሰላምን ፡ ማግኘቱ ፡ አይጠረጠርም ። ያለረድኤት ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ የሚሠራ ፡ ሥራ ፡ ግን ፡ ለሰው ፡ አጥፊው ፡ እንጅ ፡ ጠቃሚው ፡
እንዳይደለ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ይህንንም ፡ ለመገንዘብ ፡ ( ጥቅመ ፡ ሰናዖር ) ፡ የሰናዖር ፡ ግንብ ፡ እንዴት ፡
እንደፈረሰ ፡ እናስታውስ ፡ ዘፍ ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ፩—፲፱ ።

ሰው ፡ ይቅርታን ከፈጣሪው ፡ ለምኖ ፡ በላዩ ፡ የተቃጣው ፡ እደ ፡ መዓቱ ፡ እን
ዲመለስለት ፡ ንስሓ ፡ ገብቶ ፡ ቢጸምና ፡ ቢጸልይ ፡ የተቃጣበት ፡ ቍጣ ፡ ይመለስለታል።

ይኸውም ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፤ ንጉሡ ፡ ሕዝቅያስ ፡ የማይገባ ፡ ትምክህት ፡ በማ
ድረጉ ፡ ተግሣጽ ፡ አግኝቶት ፡ በእደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተይዞ ፡ (ታሞ) ፡ ከተኛበት ፡
አልጋ ፡ መንቀሳቀስ ፡ ስለአቃተው ፡ ከነአልጋው ፡ ወደቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዙሩኝ ፡
ካለ ፡ በኋላ ፤ «አይኖቼን ፡ ቀና ፡ አድርጌ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰማይን ፡ ለማየት ፡
ተሳነኝ ፤ አቤቱ ፡ ይህች ፡ ተግሣጽህ ፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እንግዲህ ፡ ትብቃኝ» ፡ እያለ ፡
ምህላ ፡ ቢያደርግ ፡ የተቃጣበት ፡ እደ ፡ መዓቱ ፡ ተመልሶለታል ።

እግዚአብሔርም ፡ መሐሪነቱን ፡ ለመግለጽ ፡ (ወናሁ ፡ ወሰኩከ ፡ ፲ወ፭ተ ፡
ዓመተ) ፡ እነሆ ፡ ስለምህላህ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ጨምሬልኻለሁ ፡ በለው ፡
ብሎ ፡ በኢሳይያስ ፡ ቃል ፡ ምሕረቱን ፡ እንዲሰማ ፡ ፈቅዶለታል ፡ ኢሳ ፡ ም ፡ ፴፰ ፡ ቍ ፡
፩—፮ ።

እኛም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ እንደሚያውቀው ፡ ወደ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ያቀረብነው ፡ ጸሎት ፡ ሁሉ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ሆኖብን ፡ አያውቅም ።

ቸር ፡ እግዚአብሔር ፡ በወዳጆቹ ፡ ያናገረው ፡ ተስፋ ፡ ሁሉ ፡ ለሀገራችን ፡
ለኢትዮጵያ ፡ እንዲፈጸምላት ፡ የተቀደሰ ፡ ፈቃዱ ፡ ስለሆነ ፤ በወዳጁ ፡ በዳዊት ፡
አድሮ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ያናገረውን ፡ ተስፋ ፡ ለወገኖቻችንና ፡ ለወንድሞቻችን ፡ ኤርት
ራውያን ፡ እነሆ ፡ ዛሬ ፡ ፈጸመላቸው ።

የእግዚአብሔር ፡ ቸርነቱ ፡ ለሚፈሩት ፡ ሰዎች ፡ ቅርብ ፡ ነው ። በሀገራችን ፡ ቸር
ነቱ ፡ እንዳደረበት ፡ ሲያስረዳ ፡ «ዛሬ ፡ ቅንነትና ፡ ይቅርታ ፡ ተገናኙ ፡ እውነትና ፡
ሰላም ፡ ተስማሙ ፡ በምድራችን ፡ ላይ ፡ የእውነት ፡ ፍርድ ፡ ተገለጠ ፤ የእግዚአብ
ሔር ፡ እውነተኛ ፡ ፍርድ ፡ ከሰማይ ፡ ጐበኘን ። በዘመኑ ፡ የጀመረው ፡ በጎ ፡ ነገር ፡
ሁሉ ፡ የሚፈጸምለት ፡ ደገኛ ፡ ንጉሥን ፡ ማግኘት ፡ ከዕድል ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ ዕድል ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ኤርትራን ፡ በመን
ፈሳዊ ፡ ጥበባቸው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ምሕረትና ፡ ቸርነትን ፡ በሥጋዊ ፡ ጥበባቸው ፡

www.ethiopianorthodox.org

ከዓለም ፡ ነገሥታት ፡ መልካም ፡ አስተያየትና ፡ ቅን ፡ ፍርድን ፡ እንድታገኝ ፡ ደክመው
ጕዳዩን ፡ ወደፍጻሜ ፡ ስላደረሱላት ፡ ይኽ ፡ ከፍተኛ ፡ ዕድል ፡ ለሁላችን ፡ ነው ።

አንድነታችንና ፡ ሥራችንም ፡ በአንድ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ አስተዋይነት
እየተከናወነ ፡ ስለተገኘ ፤ አሁን ፡ ዋና ፡ አሳባችንና ፡ አስፈላጊያችን ፡ ሆኖ
የምንደክምበት ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ረጅም ፡ ዘመናትን ፤ ሰፊ ፡ ወራትን
ሰጥቶ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ በጽኑ ፡ ክንዱ ፡ ጠብቆ ፡ ከዘመነ ፡ ወደዘመን ፡ በሰ
ላም ፡ እንዲያሸጋግርልንና ፡ የተጀመረውም ፡ አንድነታችን ፡ መሠረቱ ፡ የጸና ፡ ሆኖ
እድገትንና ፡ ሰላምን ፡ በሥራ ፡ እያስፋፋ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነዋሪ ፡ እንዲሆንልን ፡ ነው ።

ለኢትዮጵያና ፡ ለኤርትራ ፡ ብርሃን ፡ ረድኤቱን ፡ ለገለጠ ፡ እግዚአብሔር ፡ ክብር
ምስጋና ፡ ይግባው ።

ዘመነ ፡ ማቴዎስን ፡ ባርክ ፡ ቀድሶ ፡ ይስጠን ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፤ ንጉሠ ፡ ነገሥት ።

« ለግርማዊት ፡ እቴጌ ። »

በረከትና ፡ ጸጋን ፡ ለልዑላን ፡ ልጆቻቸው ፡ ሰላምና ፡ ሕይወትን ፡ ለልዑላን ፡ መሳ
ፍንትና ፡ ለክቡራን ፡ መኳንንት ፤ ፍቅርና ፡ አንድነትን ፡ ለመላው ፡ ዓለም ፡ ሕዝብ ፡
ይስጥልን ፡ አሜን ።

---

በ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ .................... ቀን ፡ ብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡነ
ባስልዮስ ፡ አዲሶቹን ፡ ጳጳሳት ፡ ወደ ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ባቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ የተናገሩት

## ቃ ለ ፡ በ ረ ከ ት ።

እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ ትፍሥሕት ፡ ወአቡሃ ፡ ለምሕረት ፤ የሀበነ ፡ ኀሢሢ
ዘዘዚአሁ ፡ ለኵልነ ፡ በእንተ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። ከመ ፡ ኵልነ ፡ ኅቡረ ፡ በአ
ሐዱ ፡ አፍ ፡ ንሰብሖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእነ ፡ ሮሜ
ም ፡ ፲፭ ፡ ቍ ፡ ፭-፮ ።

የተሰጠንን ፡ ጸጋ ፡ በማሰብ ፡ በአንድ ፡ ቃል ፡ በአንድ ፡ ልብ ፡ እናመሰግነው ፡
ዘንድ ፡ በሰማያዊ ፡ በረከት ፡ ለባረከን ፡ ላበቃን ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡
ይግባው ።

## ግርማዊ ፡ ሆይ ።

በሺህ ፡ ፱፻፺፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከግብጽ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጥቶ ፡ የነበረው ፡
አባ ፡ ያዕቆብ ፤ የተባለው ፡ ጳጳስ ፤ ሦስተኛውን ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ዕጨጌ ፡
አቡነ ፡ ፊልጶስን ፡ ለጵጵስና ፡ ማዕርግ ፡ ባበቃ ፡ ጊዜ ፤ ይህ ፡ ዛሬ ፡ በግርማዊነ
ትዎ ፡ ትጋትና ፡ ብርታት ፡ የተፈጸመው ፡ አድራጎት ፡ በትንቢት ፡ ተገልጾለት ፡ (አፍቀ
ርየ ፡ ፊልጶስ ፡ አማን ፡ እብለከ ፡ ለእመ ፡ ኮኑ ፡ ፲ቱ ፡ ወ፪ቱ ፡ ጳጳሳት ፡ እምኢክ
ሀሉ ፡ በጺሖታ ፡ መጠነ ፡ መንፈቃ ፡ ለሀገር ፡ እስመ ፡ ዛቲ ፡ ሀገረ ፡ ኢትዮጵያ ፡
ዐባይ ፡ ይእቲ ፡ እምኵሎን ፡ አህጉር) ።



(ወዳጄ ፡ ፊልጶስ ፡ ሆይ ፤ እውነት ፡ እልሃለሁ ፡ ለትልቂቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዐሥራ ፡
ሁለት ፡ ጳጳስት ፡ እንኳ ፡ ቢሾሙላት ፡ በስብከት ፡ ባላደረሷትም ፡ ነበር) ፡ በማለት
ያለበት ፡ ትንቢት ፡ ተናግሮ ፡ እንደነበር ፡ ተጽፎ ፡ እናገኛለን ።

ይህ ፡ ቃለ ፡ ትንቢት ፡ የተፈጸመው ፤ የታሪክ ፡ ሁሉ ፡ ዕድል ፡ በተሰጠው ፡
በግርማዊነትዎ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በመሆኑ ፤ ይህ ፡ ዛሬ ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ የተከና
ወነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጳጳሳት ፡ ሥርዓተ ፡ ሢመት ፡ ኢትዮጵያ ፡ በግርማዊነትዎ ፡
ሰፊ ፡ ሀብት ፡ ከፍ ፡ ላለ ፡ ታሪካዊ ፡ ዕድል ፡ መብቃቷን ፡ የሚገልጽ ፡ ማስረጃ ፡ ነው ።

ይኸውም ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በየጊዜው ፡ ከሠራቸው ፡
ውለታዎች ፡ ሁሉ ፡ አንደኛ ፡ መሆኑ ፡ በመላው ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘንድ ፡
የተገለጠ ፡ ነው ።

ይህን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ጕዳይ ፡ ለማከናወን ፡ የተቀቡ ፡
ግርማዊ ፡ በመሆንዎ ፡ (መንፈሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕሌየ ፡ በእንቲአሁ ፡ ዘቀብ
ዐኒ ፡ አስተፍሥሖሙ ፡ ለነዳያን ፡ ፈነወኒ ፡ ወእፈውሶሙ ፡ ለቍሱላነ ፡ ልብ ፡ ወእስ
ብክ ፡ ግእዛነ ፡ ለጼዉዋን) ።

የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ በላዬ ፡ ነው ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀብቶኛልና ፡
ለትሑታን ፡ የምሥራች ፡ እነግር ፡ ዘንድ ፤ ልባቸው ፡ የተሰበረውንም ፡ እጠግን ፡
ዘንድ ፡ ላከኝ ፤ ለተጋዙትም ፡ ነጻነትን ፡ እሰብክ ፡ ዘንድ ፤ ለታሠሩትም ፡ መፈታ
ትን ፡ ተብሎ ፡ በነቢዩ ፡ ኢሳይያስ ፡ የተነገረው ፡ ቃል ፡ በግርማዊነትዎ ፤ መፈጸሙ ፡
ሕዝብዎን ፡ በመላው ፡ ደስ ፡ አሰኝቷል ።

ይህ ፡ ሥራ ፡ ሲከናወንም ፡ ሺ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ሃይማኖታዊ ፡ አን
ድነትን ፡ አጽንተው ፡ የኖሩ ፡ ኢትዮጵያና ፡ እስክንድርያ ፡ አንዳች ፡ መለያየት ፡
ሳያገኛቸው ፤ ግርማዊነትዎ ፡ ባዘጋጀው ፡ ሰላማዊ ፡ መንገድ ፤ ፍቅራቸው ፡ እየቀ
ጠለ ፡ እንዲሔድ ፡ መደረጉ ፤ ለኢትዮጵያ ፡ የታሪኳ ፡ መሠረት ፡ ሆኖ ፡ የስምም
ነት ፡ ሕንጻዋን ፡ አጽንቶላት ፡ የሚኖር ፡ ነው ።

እነዚህም ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ተመርጠው ፡ የተሾሙትን ፡ አዲሶቹን ፤
ጳጳሳት ፡ ወደ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ሳቀርባቸው ፤ ከሰማያዊ ፡ አደራ ፡ ጋር ፡ ርቱዐ ፡
ሃይማኖት ፡ ኦርቶዶክሳዊ ፡ የተባሉ ፡ የግርማዊነትዎን ፡ አደራ ፡ በታማኝነት ፡ እንደ
ሚጠብቁ ፡ እየተማመንኩ ፡ ነው ።

ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ለኢትዮጵያ ፡ በየጊዜው ፡ የተጀመረ ፡ የታሪኳ ፡
ሁሉ ፡ መፈጸሚያ ፡ የሆነ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥትዎን ፡ ዘመነ ፡ ማህል ፡ ዘመነ ፡ ሰላም ፡
አድርጎ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ኃይልን ፡ ጽንዕን ፡ በረከትን ፡ ይስጥልን ።

ግርማዊት ፡ እቴጌንና ፡ ልዑላን ፡ ልጆችዎን ፡ በረድኤቱ ፡ ጠብቆ ፡ ያኑርልን ፤
በመላው ፡ ሕዝብ ፡ ላይም ፡ በረከቱን ፡ ያሳድር ፡ አሜን ።

www.ethiopianorthodox.org

በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ታሕሣሥ ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ሊ.ቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘኢ.ትዮጵያ ፤ በልደት ፡ በዓል ፡ ምክንያት ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ፡ በረከት ።

የጌታችን ፡ የኢ.የሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ የልደት ፡ በዓል ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ መንፈሳዊ ፡ ንግግሬን ፡ እጀምራለሁ ።

ወሰበ ፡ ተስእኖ ፡ ለሕገ ፡ አሪት ፡ ላዕለ ፡ ሞት ፡ በእንተ ፡ ድካመ ፡ ሥጋ ፡ ፈነወ ፡ እግዚ.አብሔር ፡ ወልዶ ፡ በአምሳለ ፡ ነፍስተ ፡ ኃጢ.አት ፡ ወኰነና ፡ ለይ እቲ ፡ ኃጢ.አት ፡ በነፍስቱ ፤ ከመ ፡ ያጽድቀነ ፤ ኪ.ያነ ፤ ወከመ ፡ ይረሲ ፡ ለነ ፡ ከመ ፡ ዘፈጸመ ፡ ገቢ.ሮቶ ፡ ለሕገ ፡ አሪት ፡ ለእለ ፡ በሕገ ፡ መንፈስ ፡ የሐውሩ ፤ ወአኮ ፡ ለዕለ ፡ በሕገ ፡ ነፍስቶሙ ፡ ይገብሩ ፤ እስመ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ለግዕዘ ፡ ነፍስ ቶሙ ፡ ይገብሩ ፡ ዘዝንቱ ፡ ዓለም ፡ የሔልዩ ። ወእለሰ ፡ ዘመንፈስ ፡ ይሔልዩ ፡ ዘመንፈ.ስ ፡ ሮሜ ፡ ም ፡ ፰ ፡ ቍ ፡ ፫-፮ ።

ልዑል ፡ እግዚ.አብሔር ፡ የሰው ፡ ዘር ፡ በኃጢ.አትና ፡ በሞት ፡ ወጥመድ ፡ እንዳይያዝ ፡ ከጥንተ ፡ ፍጥረት ፡ ጀምሮ ፡ ቸርነቱን ፡ ያልገታ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፤ ማናቸውም ፡ ሰብአዊ ፡ ፍጥረት ፡ በሕገ ፡ ነፍስ ፡ ተጠብቆ ፡ የሕይወቱና ፡ የክብሩ ፡ ባለቤት ፡ እንዲሆን ፡ መፍቀዱን ፡ አላቋረጠም ።

ሰው ፡ ግን ፤ ቀድሞ ፡ ሕገ ፡ ልቡና ፡ ኋላም ፡ ሕገ ፡ መጽሐፍ ፡ ምንም ፡ ቢሠራለት ፤ ሕጉን ፡ መፈጸም ፡ ስለተሳነው ፡ ኃጢ.አትና ፡ ሞት ፡ እርሱ ፡ ሊ.ሠለጥ ንባቸው ፡ በሚገባው ፡ ፈንታ ፡ ሠልጥነውበት ፡ በሚያሳዝን ፡ ውርደትና ፡ ጕስቍ ልና ፡ ላይ ፡ ይገኝ ፡ ነበር ።

በዚ.ህ ፡ ምክንያት ፡ ቸርና ፡ ሰውን ፡ ወዳጅ ፡ የሆነ ፡ እግዚ.አብሔር ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ከንቱነት ፡ ማዘንበሉን ፡ በባሕርያዊ ፡ ርኅራኄው ፡ ተመልክቶ ፡ መዳ ንንም ፡ የመሸሻ ፡ ፈቃድ ፡ እንዳለው ፡ አስተውሎ ፡ የሚወደውን ፡ ልጁን ፡ ወደዚ.ህ ዓለም ፡ ላከው ።

ሆኖም ፤ ወደዚ.ህ ፡ ዓለም ፡ የመጣው ፡ ይኸው ፡ የእግዚ.አብሔር ፡ አብ ፡ የባ ሕርይ ፡ ልጁ ፡ ኢ.የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከፅንሱና ፡ ከልደቱ ፡ ጀምሮ ፡ የትሕትናን ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፤ ኋላም ፡ በሞቱ ፡ ኃጢ.አትንና ፡ ሞትን ፡ በመደምሰስ ፡ ታላ ቁን ፡ ታዳጊነት ፡ ፈጽሞ ፡ ስለአዳነን ፤ ክርስቶስ ፡ ተብሎ ፡ ክርስቲ.ያን ፡ ሕያው ፡ ተብሎ ፡ ሕያዋን ፡ የምንባልበትን ፡ የተቀደሰ ፡ አጠራር ፡ ሰጥቶ ፡ ወደ ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ሕይወት ፡ (ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት) ፡ ስለመራን ፡ ከሥጋዊ ፡ ሕይወት ፡ ለመንፈ ሳዊ ፤ ከኃጢ.አት ፡ ለጽድቅ ፡ በጠቅላላውም ፡ ከሥጋዊነት ፡ ለመንፈ.ሳዊነት ፡ አድልተን ፡ በበጎ ፡ ሥራ ፡ ልንከተለው ፡ ተገባን ።

ይህንኑም ፡ የመድኃኒ.ታችን ፡ የኢ.የሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ታላቅ ፡ መሪነት ፡ በመከ ተል ፡ ታዳጊነቱን ፡ እንድናስብ ፡ ሐዋርያው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እላይ ፡ አርእስት ፡ አድርገን ፡ የጠቀስነውን ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነግሮናል ።



ስለ ፡ ሥጋ ፡ ደካማነት ፡ የአሪት ፡ ሕግ ፡ ከሞት ፡ ማዳን ፡ በተሳነው ፡ ጊዜ ፡ እግ ዚ.አብሔር ፡ ልጁን ፤ ኃጢ.አት ፡ በሚስማማው ፡ ሰውነት ፡ አምሳል ፡ ወደዚ.ህ ፡ ዓለም ፡ ላከ።

ልጁም ፡ እኛን ፡ ያከብረን ፡ ዘንድ ፡ ሕገ ፡ አሪትንም ፡ እንደፈጸመ ፡ ሰው ፡ ያደር ገን ፡ ዘንድ ፡ በሰውነቱ ፡ ያችን ፡ ኃጢ.አት ፡ ቀጣት ።

ይኸውም ፡ በፈ.ቃደ ፡ ነፍስ ፡ ጸንተው ፡ ለሚኖሩ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ በፈ.ቃደ ፡ ሥጋ፡ ጸንተው ፡ ለሚኖሩ ፡ አይደለም ። በፈ.ቃደ ፡ ሥጋቸው ፡ ብቻ ፡ ጸንተው ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ሁሉ ፡ የዚ.ህን ፡ ዓለም ፡ ነገር ፡ ያስባሉና ።

ይህ ፤ የሐዋርያው ፡ ቃል ፡ ከመድኃኒ.ታችን ፡ ከኢ.የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ በኃጢ.አት ፡ ምክንያት ፤ ከእግዚ.አብሔር ፡ መራቃቸውና ፡ መንፈሳዊ ፡ ሕይወትን ፡ ማጣታቸው ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጕዳት ፡ አምጥቶባቸው ፡ እንደ ነበረ ፤ መድኃኒ.ታችን ፡ እርሱ ፡ በሥጋ ፡ ተወልዶ ፡ ኃጢ.አትንና ፡ ሞትን ፡ በመልዕልተ መስቀል ፡ ከቀጣላቸውና ፡ ከደመሰሰላቸው ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወትን ፡ እንዳ ስገኘላቸው ፤ ከነገረን ፤ ዛሬ ፡ የሚገባን ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ነው ። ?

ሕጉን ፡ ትእዛዙን ፡ በመጠበቅና ፡ ልጆቹ ፡ ወዳጆቹ ፡ በመሆን ፡ ለአስገኘልን ፡ የዘለ ዓለም ፡ ሕይወት ፡ እንድንበቃ ፡ ሆነን ፡ መገኘት ፡ ነዋ ።

ከእንግዲ.ህ ፡ ወዲ.ህ ፡ እንደገና ፡ ሕጉን ፡ ትእዛዙን ፡ ወደመተላለፍ ፡ ተመልሰን ፡ በደሙ ፡ ያዘጋጀልንን ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ ማጣትን ፡ በፈ.ቃዳችን ፡ ብናመጣ ፤ ተዘ ጋጅቶ ፡ የሚቆየን ፤ ዘለዓለም ፡ ፍዳ ፡ ነውና ፡ የበለጠው ፡ ድካማችን ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይ ወትን ፡ ለማግኘት ፡ ሊ.ሆን ፡ ይገባል ።

ወደ ፡ ዘለዓለም ፡ ሕይወትም ፡ ለመድረስ ፡ የምንችለው ፡ የአፍ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን፡ የልብም ፡ ክርስቲ.ያኖች ፡ ሆነን ፡ መድኃኒ.ታችን ፡ ኢ.የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በቅዱስ ፡ ወን ጌሉ ፡ «የሕይወት ፡ ኅብስት ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ማንም ፡ ከዚ.ህ ፡ ኅብስት ፡ የበላ ፡ ዘለዓለም ፡ ይኖራል ።

ይህም ፡ ኅብስት ፡ እኔ ፡ ስለ ፡ ዓለም ፡ ሕይወት ፡ የምሰጠው ፡ ሥጋዬ ፡ ነው ። ሥጋዬ ፡ የእውነት ፡ መብል ፤ ደሜም ፡ የእውነት ፡ መጠጥ ፡ ነውና» ፡ ብሎ ፡ የተናገረ ውን ፡ ቃል ፡ በመከተል ፤ ጠፍተን ፡ እንዳንቀር ፡ የሚፈ.ልገንን ፡ እሱን ፡ መድኃ ኒ.ታችንን ፡ በሥጋው ፡ በደሙ ፡ እናገኘው ፡ ዘንድ ፡ ይቻልን ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። ዮሐ ም ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፴፭ ፡ ፶፩-፶፭ ።

መልአከ ፡ እግዚ.አብሔር ፡ በዕለተ ፡ ልደቱ ፡ ኖሎት ፡ የእግዚ.አብሔር ፡ ክብር ፡ በዙሪያቸው ፡ እንደአበራ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፤ መፍራታቸውን ፡ ተመልክቶ ፡ (ኢ.ትፍርሁ ፡ እስመ ፡ ናሁ ፡ እዜንወክሙ ፡ ዓቢ.የ ፡ ዜና ፤ ፍሥሓ ፡ ዘይከውን ፡ ለኵሉ ፡ ሕዝብ። እስመ ናሁ ፡ ተወልደ ፡ ለክሙ ፡ መድኅን ፡ ዘውእቱ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚ.እ ፡ ቡሩክ ፡ በሀገረ ፡ ዳዊት ፡) እነሆ ፡ እኔ ፡ ለሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ የሚሆን ፡ የምሥራች ፡ እነግራ ችኋለሁና ፡ አትፍሩ ።

www.ethiopianorthodox.org

ዛሬ ፡ በዳዊት ፡ አገር ፡ መድኅን ፡ እርሱም ፡ ክርስቶስ ፡ ቡሩክ ፡ የሆነ ፡ ጌታ ፡ ተወልዶላችኋልና ፡ ብሎ ፡ አጽናንቶዋቸዋል ፡ ሉቃስ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፲-፲፪ ።

ይህ ፡ መልአኩ ፡ የተናገረው ፡ የምሥራች ፡ ቃል ፡ ስለ ፡ ሁላችን ፡ መሆኑ ፡ እየ ተሰማን ፡ እነሆ ፡ ለደስታችን ፡ መጠን ፡ የለውም ።

ምክንያቱም ፡ ልደቱን ፡ የመላእክትም ፡ የደቂቀ ፡ አዳምም ፡ (የሁላችንም) ፡ መገናኛ ፡ አድርጎ ፡ በታላቅ ፡ ቸርነቱ ፡ ስለጐበኘንና ፡ በማመስገን ፡ ወገኖቹ ፡ በመባል ፡ አንድ ፡ ሁነን ፡ የምንኖርበትን ፡ ክብር ፡ ስለ ፡ መሠረተልን ፡ ነው ።

ነቢዩ ፡ ዳዊትም ፡ (ምስሌከ ፡ ቀዳማዊ ፡ በዕለተ ፡ ኃይል ፡ ) ብሎ ፡ አስቀድሞ ፡ በትንቢት ፡ እንደገለጠው ፡ በዕንሡና ፡ በልደቱ ፡ ጊዜ ፡ ታላላቅ ፡ የሆኑ ፡ ሁለት ፡ የኃይል ሥራዎችን ፡ ፈጸመልን ፡ የኃይል ፤ ሥራም ፡ ያለዘር ፡ ተፀንሶ ፡ ያለዘር ፡ መወለድ ነው።

እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ ስለኛ ፡ መለኮታዊ ፡ ጥበቡን ፡ ለገለጠ ፡ አምላክ ፡ በምን ፡ አገልግሎታችን ፡ ደስ ፡ ልናሰኘው ፡ ይገባን ፡ ይሆን ?

ከዚህ ፡ በቀር ፡ ወገኖቹ ፡ በመባል ፡ በክብር ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ እንድንቆም ፡ የማድረጉን ፡ ታላቅ ፡ ትድግና ፡ ወደማሰብ ፡ የተመለስን ፡ እንደሆነ ፤ ከላይ ፡ እንደገለጽነው ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ለተደረገልን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ ወደረኛ ፡ ይሆናል ፡ ተብሎ ፡ ባይገመት ፤ በመጠኑ ፡ ውለታ ፡ መላሾች ፡ ሆነን ፡ የምንገኘው ፡ የታዘዝነውን ፡ በመፈጸም ፡ ላይ ፡ ሆነን ፡ ስንገኝ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

የሰው ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋ ፡ የተፈጥሮ ፡ ዕውቀት ፡ ካልገታው ፡ በቀር ፡ ከውኃ ፡ ይልቅ ፡ እጁን ፡ ወደእሳት ፡ ለማግባት ፡ ስለሚያዘነብል ፤ ሰው ፡ ራሱንም ፡ ሆነ ፡ ወገኖቹን ፡ ለማጥፋት ፡ ወደሚያስችለው ፡ ሥራ ፡ ከመቸኰል ፤ ፍኖተ ፡ ሕይወት ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ በሥራ ፡ መምሰልና ፡ ለእውነተኛ ፡ ሥራ ፡ መፋጠን ፡ አለበት ።

ይህ ፡ ሲሆንም ፡ በበጎ ፡ ሥራው ፡ ዋጋ ፤ በክፉ ፡ ሥራው ፡ ፍዳ ፤ የመቀበል ፡ ዕድል ፡ በተለይ ፡ ለየአንዳንዱ ፡ እንደየሥራው ፡ የሚደርሰው ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ (አንተ ፡ አቡነ ፡ ወአንተ ፡ እምነ ፡ ) እያልን ፡ በፍጹም ፡ ልባችን ፡ ጌታችንና ፡ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ እንከተለው ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ።

« ለግርማዊት ፡ እቴጌ ።

« ለልዑላን ፡ ልጆቻቸው ።

በረከተ ፡ ልደቱ ፡ በሁላችን ፡ ይደር ፡ (አሜን ፡)

---

ብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ስለ ፡ ዐቢይ ፡ ጾም ፡ የካቲት ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡



## ለሕዝብ ፡ ያሰሙት ፡ ቃለ ፡ ምዕዳን ።

አስተበቍዐክሙ ፡ አኀዊነ በሣህሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ትረስዩ ፡ ነፍሳቲክሙ ፡ መሥዋዕተ ፡ ቅዱሰ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወሕያወ ፡ ወሥሙረ ፡ ወኅሩየ ፡ ይኩን ፡ ቍርባንክሙ ፡ ወቅኔክሙ ፡ ነባቢ ፡ ኢታፍቅርዎ ፡ ለዝዓለም ፡ ወሐድሱ ፡ ልበክሙ ፡ ወአመክሩ ፡ ዘይፈቅድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘሠናይ ፡ ወዘጽድቅ ፡ ወዘፍጹም ። ሮሜ ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ቍ ፡ ፩-፫ ።

ሐዋርያው ፡ ሰውነታችንን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማገልገያ ፡ አድርገን ፡ በመንፈሳዊ ፡ ሥራ ፡ መንፈሳዊ ፡ ክብርን ፡ እንድናገኝና ፡ እንድንጠቀም ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡ ይግልደናል ።

ወንድሞቻችን ፡ ሆይ ፤ ሕያው ፡ ለሚሆን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሰውነታችሁን ፡ የከበረ ፡ መሥዋዕት ፡ አድርጉ ፡ ብዬ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ይቅርታ ፡ እማልዳችኋለሁ ።

ቍርባናችሁ ፡ የተወደደ ፡ የተመረጠ ፡ ይሁን ። መገዛታችሁም ፡ በዕውቀት ፡ ይሁን ። ይህን ፡ ዓለም ፡ አትውደዱት ፡ ዕውቀታችሁን ፡ አድሱ ፤ እግዚአብሔር ፡ የሚወደውን ፡ መርምሩ ፤ የበጎውን ፤ የእውነቱን ፡ የፍጹሙን ፡ ያዙ ።

የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ በተዋሐደው ፡ ቃሉ ፡ እንዲህ እያለ ፤ በጾም ፡ በጸሎት ፡ በሰጊድ ፡ በአስተብርኮትና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ፈተና ፡ (ጸዋትወ ፡ መከራ) ፡ ሰውነታችንን ፡ ቅዱስ ፡ መሥዋዕት ፡ አድርገን ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ እንድናቀርበው ፡ መማለዱ ፤ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ተድላ ፡ ርቀን ፡ ለመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ክብር ፡ የተገባን ፡ ሆነን ፡ እንድንገኝ ፡ ነው ።

ሥጋችንን ፡ ለማስመቸት ፡ የምናደርገው ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ተድላ ፡ ደስታስ ፡ ይቅርና ፡ ነፍሳችንን ፡ ለማስመቸት ፡ የምንቀበለው ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ፈተና ፡ በወዲያኛው ፡ ዓለም ፡ የምናገኘውን ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ክብር ፡ ሊመጣጠነውና ፡ ሊተካከለው ፡ አይችልም ። ሮሜ ፡ ም ፡ ፰ ፡ ቍ ፡ ፲፰ ፡ ፳፪ ።

ስለዚህ ፡ ሰውነታችን ፡ ክቡር ፡ መሥዋዕት ፡ ሆኖ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለመቅረብ ፡ የሚችለው ፤ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ተድላ ፡ ለይተን ፡ ዋጋ ፡ በሚያሰጡን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ፈተናዎች ፡ ላይ ፡ ስንጥለው ፡ ነውና ፡ የተቀበልነው ፡ ማናቸውም ፡ (መከራ) ፡ ከመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ክብር ፡ ጋር ፡ የማይመጣጠንና ፡ የማይወዳደር ፡ መሆኑን ፡ በመገንዘብ ፤ ከጾም ፤ ከጸሎት ፤ ከሰጊድ ፤ ከቀዊም ፡ የተነሣ ፡ የሚመጣውን ፡ ድካም ፡ እየታገሥን ፡ እንዲራራልንና ፡ የመንፈሳዊ ፡ ሥራችንን ፡ ጒድለት ፡ በቸርነቱ ፡ እንዲመላልን በተስፋ ፡ ጸንተን ፡ እናመልክት ።

በደግነቱና ፡ በትሩፋቱ ፡ የታወቀው ፡ ሊቁ ፡ የቍስጥንጥንያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዮሐንስ ፡ አፈወርቅም ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በአባትነቱ ፡ ሲማልደን እንዲህ ፡ ብሏል ።

www.ethiopianorthodox.org

(አስተበቍዐክሙ ፡ አፍቁራን ፡ ከመ ፡ ትረስይዎ ፡ ለሥጋ ፡ ጽኑዐ ፡ ወአ... ድኩመ) ፡ ሥጋችሁን ፡ በተድላ ፡ እንዲደክም ፡ ሳታደርጉ ፡ በመከራ ፡ እንዲጸና... ታደርጉት ፡ ዘንድ ፡ እማልዳችኋለሁ ።

(ወአኮ ፡ ዘእቤ ፡ ዘንተ ፡ በእንተ ፡ ዕደው ፡ ባሕቲቶሙ ፡ አላ ፡ ለአንስትኒ)፡ ይህንን ፡ የተናገርኩ ፡ ለሴቶችም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለወንዶች ፡ ብቻ ፡ አይደለም፡ ዮሐ ፡ አፈወርቅ ፣ ተግሣጽ ፡ ፳፱ ፡ ገጽ ፡ ፫፻ ፡ ፺፯ ።

ሊቁ ፡ የተነሣው ፡ ለመንፈሳዊ ፡ ሥራ ፡ አጋዥ ፡ ሆኖ ፡ ነውና ፡ ሥጋችሁን፡ በመከራ ፡ እንዲጸና ፡ አድርጉት ፡ ያለን ፡ እንዲጾም ፡ እንዲጸልይ ፣ እንዲሰግድ... ከነዚህም ፡ ከፍ ፡ ያሉትን ፡ ጸዋትወ ፡ መከራ ፡ እንዲቀበል ፡ በትዕግሥት ፡ አበርቱ... ሲል ፡ ነው ።

የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ቅዱስ ፡ ያሬድም ፡ ዛቲ ፡ ጾም ፡ ኃዘን ለአብዳን ፡ ወፍ... ሥሓ ፡ ለጠቢባን ፡ በማለት ፡ የጾምን ፡ ሥርዓት ፡ አክብሮ ፡ ተናግሯል ። የሁሉ... መሪ ፡ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ሥጋችንን ፡ በተድላ ፡ በደስታ... ሳናደክም ፡ የነፍሳችንን ፡ ሥራ ፡ እንድንሠራበት ፡ ሲያዝዘን ፡ (ዘይረክባ ፡ ለነፍሱ... ይገድፋ ፣ ወዘሰ ፡ ገደፋ ፡ ለነፍሱ ፡ በእንቲአየ ፡ ይረክባ) ፡ ነፍሱን ፡ የሚያገኛት... ሁሉ ፡ ያጠፋታል ፡ ነፍሱንም ፡ ስለኔ ፡ ያጠፋት ፡ ያገኛታል ፡ ብሎዋል ። ማቴ... ም ፡ ፲ ፡ ቍ ፡ ፴፱ ።

ብፁዓን ፡ ሐዋርያት ፣ ጻድቃን ፣ ሰማዕታት ፡ ይህንኑ ፡ የመሪያቸው ፡ ኢየሱስ... ክርስቶስን ፡ ቃል ፡ በመከተል ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጸዋትወ ፡ መከራን ፡ በመቀበል ፡ ከሥ... ጋዊ ፡ ምቾት ፡ ተለይተው ፡ የነፍስ ፡ ዋጋ ፡ የሚገኝበትን ፡ ሥራ ፡ እየሠሩ ፡ የዘለ... ዓለም ፡ ሕይወት ፣ ጣዕም ፣ ተድላ ፣ መዓዛ ፡ ብርሃን ፡ ላለበት ፡ መንግሥተ... ሰማያት ፡ የበቁ ፡ ሆነዋል ።

ሐዋርያት ፣ ሰማዕታት ፣ የዐላውያንን ፡ እሳትና ፡ ስለት ፣ ጻድቃን ፡ (በሕታውያን)... ዕፀበ ፡ ገዳምን ፣ ግርማ ፡ ሌሊትን ፡ ድምፀ ፡ አራዊትን ፡ ታግሠው ፡ ከፍ ፡ ከፍ... ያለ ፡ መከራ ፡ ለተቀበሉላት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ እኛ ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ በሰ... ጊድ ፡ በቀዊም ፡ ሰውነታችንን ፡ ወስነን ፡ ገተን ፡ ብንይዝላት ይበዛብናል ? ፡ ወይስ... ጾም ፡ ጸሎትና ፡ መንፈሳዊ ፡ አገልግሎት ፡ ሁሉ ፡ ለክርስቲያን ፡ የተገባ ፡ መሆኑን... የሚዘነጋ ፡ አለን ?

አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ በወጣትነታችን ፡ ዘመን ፡ መጾም ፣ መጸለይ ፡ መስገድ... መቍረብ ፡ አይቻለንም ፡ እያሉ ፡ ይሳሳቱ ፡ ይሆናል ። እንዲህ ፡ ማለት ፡ ለክርስቲያን... የሚገባ ፡ አይደለም ።

ንጉሡ ፡ ሰሎሞን ፣ በሕፃንነትና ፡ በወጣትነት ፡ ወራት ፡ እግዚአብሔርን... ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ መንፈሳዊ ፡ ሥራን ፡ መሥራት ፡ እንዲገባ ፡ ሲናገር ፡ (ተዘከሮ... ለፈጣሪከ ፡ በመዋዕለ ፡ ውርዙትከ ፡ ዘእንበለ ፡ ይምጻእ ፡ መዋዕል ፡ እኩይ ፣ ወይ... ብጽሓ ፡ ዓመታት ፡ በዕለተ ፡ ትብል ፡ ኢኮነኒ ፡ ቦቶን ፡ ፈቃድየ) ፡ በሕፃንነትህ...



ወራት ፡ ፈጣሪህን ፡ አስብ ፡ የጭንቀት ፡ ቀን ፡ ሳይመጣ ፡ ደስ ፡ አያሰኙኝም ፡ የምትላቸው ፡ ዓመታት ፡ ሳይደርሱ ፡ ብሏል ። መጽ ፡ መክ ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ቍ ፡ ፩ ።

በሕፃንነት ፡ ወራት ፡ ጀምሮ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማሰብና ፡ መንፈሳዊ ፡ ሥራን፡ መከታተል ፡ እንዲገባ ፡ እንዲህ ፡ የተባለ ፡ ሲሆን ፣ ዐርባ ፡ ዓመት ፡ አምሳ ፡ ዓመት፡ ካልሞላኝ ፡ ዓቢይ ፡ ጾምን ፡ አልጾምም ፡ አፌን ፡ በጸሎት ፡ ጕልበቴን ፡ በስግደት ፡ ሕሊናዬን ፡ በትዕግሥ ፡ ሌሊት ፡ አላደክምም ፡ እያሉ ፡ የቡዋልት ፡ የሥላቅ ፡ ነገር ፡ መናገር ፡ ከክርስቲያን ፡ ሥርዓት ፡ መውጣት ፡ ነው ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወደቆርንቶስ ፡ በረሃ ፡ ገብቶ ፡ ዐርባ ፡ ቀን ፡ ዐርባ ፡ ሌሊት ፡ ሙሉ ፡ ከቆመ ፡ ሳያርፍ ፡ ከዘረጋ ፡ ሳያጥፍ ፡ መጾሙ ፣ ቅዱስ ፡ አርአያውን ፡ ለኛ ፡ ለመስጠት ፡ ስለኾነ ፣ በሕፃንነቴ ፡ ወራት ፡ ጌታ ፡ እንደጾመ ፡ አልጾምም ፡ ማለት ፡ ሕፃንነቴን ፡ ወይም ፡ ወጣትነቴን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አላስገዛም፡ ማለት ፡ መሆኑን ፡ ማንም ፡ አይስተውም ።

ሊቁ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈወርቅም ፡ ጾም ፡ ጸሎት ፣ ሰጊድ ፡ ቁመት፡በበለጠ፡ሊሠራ የሚቻለው ፡ ኃይለ ፡ ሥጋ ፡ በሚበረታበት ፡ በወጣትነት ፡ ዘመን ፡ መሆኑን፡ ሲያስረዳ ፣ በሕፃንነት ፡ ወራት ፡ የተጀመረውን ፡ የትሩፋት ፡ ሥራ ፡ በእርጅና ፡ ጊዜ ፡ መተው ፡ አይገባም ፡ ብሎ ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ (ለእመ፡ኮነ ፡ ምግባረ ፡ ሥጋ ፡ ይደሉ፡ ከመ ፡ ይደጉሩ ፡ በእንተ ፡ ድካመ ፡ ርስዓን ፡ እስመ ፡ ኢይትከሀሎ ፡ ይጻሙ ፡ በከመ፡ ቀዳሚ ፡ ዘአመ ፡ ውርዛዌሁ ፣ እስመ ፡ ሥጋዊ ፡ ውእቱ ፡ ፃማ ፡ ገድሉ) ፡ በኃይለ ፡ ነፍስ ፡ የሚሠራ ፡ አንክሮ ፡ ተደሞ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ርስዓን ፡ ስላመጣው ፡ ድካም፡ ጾምን ፡ ጸሎትን ፣ ሰጊድን ፡ ቁመትን ፡ በሕፃንነቱ፡እንደሚሠራው ፡ አድርጎ ፡ መሥራት ፡ አይችልም ።

በሕፃንነት ፡ ወራት ፡ ደክሞ ፡ የሚሠራው ፡ የትሩፋት ፡ ሥራ ፡ በኃይለ ፡ ሥጋ፡ የሚሠራ ፡ ነውና ፡ ብሏል ። ተግሣጽ ፡ ፺ ፡ ገጽ ፡ ፮፴ ።

ስለዚህ ፡ ኃይለ ፡ ሥጋ ፡ ጾምን ፡ ጸሎትን ፡ ሰጊድን ፡ ቁመትንና ፡ እነዚህን፡የመሳሰሉትን ፡ ቅዱሳት ፡ ምግባራት ፡ በበለጠ ፡ ሊሠራቸው፡ የሚችልበትን፡ የሕፃንነትንና፡ የወጣትነትን ፡ ዘመን ፡ በከንቱ ፡ አሳልፌ ፡ ኃይለ ፡ ሥጋ ፡ በሚደክምበት ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምግባራት ፡ አከናውናቸዋለሁ ፡ ማለት ፡ በአዲሱ ፡ ሰውነቴ ፡ ዓለምን ፣ በአሮጌው ፡ ሰውነቴ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አገለግላለሁ ፡ ማለት ፡ መሆኑ ፡ እርግጠኛ ፡ ነው ።

እስከዚያውስ ፡ ድረስ ፡ ቀጠሮው ፡ ያልታወቀ ፡ ሞት ፡ የመጣ ፡ እንደሆነ ፡ በኃጢአት ፡ ፍዳ ፡ ተይዞ ፡ መቅረት ፡ አያጸጽትምን? ፡ ለእውነተኛ ፡ ክርስቲያን ፡ የተገባ፡ አንዋንዋርስ ፡ ኃይለ ፡ ሥጋ ፡ በሚበረታበት ፡ በወጣትነት ፡ ዘመን ፡ ጾምን ፡ ጸሎትን፡ ሰጊድን ፡ ቁመትን ፣ ኃይለ ፡ ነፍስ ፡ በሚበረታበት ፡ በእርጅና ዘመን ፡ አንክሮን ፡ ተደሞን ፣ ተዘክሮተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አዘውትሮ ፡ መገኘት ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ሽማግሌም ፡ ቢሆን ፡ በወጣትነቱ ፡ ወራት ፡ የሠራውን ፡ ኃጢአት ፡ እያሰበ፡ወደ እግዚአብሔር ፡ የሚቀርብበትን ፡ መንፈሳዊ ፡ ሥራን ፡ ማዘውተር ፡ እንጂ ፡ በባልት በዕለት ፡ በሐሜት ፡ በዘፈን ፡ በጨዋታ ፡ መከከል ፡ ተቀምጦ ፡ የሕፃናትን ፡ ሥራ ሲሠሩ ፡ መገኘት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድም ፡ በሰውም ፡ ዘንድ ፡ ሊያስከብረው አይችልም ።

ሊቁ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈወርቅ ፡ ስለዚሁ ፡ ሲናገር ፤ የዳዊትን ፡ ቃል ፡ ጠቅሶ ፡ እን ዲህ፡ብሏል ፡ (ወሬዛ ፡ ለእመ ፡ በጽሐ ፡ ኀበ ፡ ርስዓን ፡ ያእምር ፡ ዘይደሉ ፡ ለሥርዓተ ልሂቅ ፤ ወይበል ፡ ኃጢአትየ ፤ ዘበንዕስየ ፡ ወእበድየ ፡ ኢትዝክር ፡ ሊተ) ፡ ጐል ማሳ ፡ የነበረ ፡ ሰው ፡ ወደእርጅና ፡ ወራት ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ሽማግሌ ፡ ሊሠራው የሚገባውን ፡ ሥራ ፡ ማወቅ ፡ ይገባዋል ፤ በሕፃንነቴ ፡ ወራት ፡ የሠራሁትን ፡ ኃጢ አት ፡ ሰንፌም ፡ የሠራሁትን ፡ ኃጢአት ፡ አታስብብኝ ፡ ማለት ፡ ይገባዋል ።

(ወእመሰ ፡ አዝለፈ ፡ ላዕለ ፡ ገቢረ ፡ ኃሣር ፡ በመዋዕለ ፡ ርስዓን ፡ ኢይደልዎ ይሰመይ ፡ አረጋዌ፡ እስመ፡ኢይቤ ፡ኃጢአትየ ፡ ዘበንእስየ ፡ ወእበድየ፡ኢትዝክር፡ሊተ)።

በእርጅናው ፡ ወራት ፤ በሕፃንነቱ ፡ ጊዜ ፡ ይሠራው ፡ የነበረውን ፡ ሥራ ፡ መለ ልሶ ፡ ከሠራው ፤ ኃጢአትየ ፡ ዘበንዕስየ ፡ ወእበድየ ፡ ኢትዝክር ፡ ሊተ ፡ ብሎ ፡ አል ጸለየምና ፡ ሽማግሌ ፡ መባል ፡ አይገባውም ፡ ተግሣጽ ፡ ፺ ፡ ገጽ ፡ ፻፴፬ ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፤ ልዑል ፤ እግዚአብሔር ፡ ወጣትነትንም ፡ ሽምግልናንም ፡ ዕድል አድርጎ ፡ መስጠቱ ፡ ዘመናችን ፡ በሚተላለፍባቸው ፡ በሁለቱም ፡ መንፈሳዊ ፡ ሥራን ሠርተን ፡ እንድንጠቀምባቸው ፡ ስለሆነ ፡ ስንፍናን ፡ በትጋት ፡ ማራቅ ፡ ለሁላችን የተገባን ፡ ነው ።

ፈተናን ፡ ዕፁብ ፡ ዕፁብ ፡ ብሎ ፡ መንፈሳዊ ፡ሥራን ፡ መሥራትን ፡ ማቋረጥ፡ከቶ አይገባም ። ጹሞ ፡ በመዋል ፤ ሰግዶ ፡ ጸልዮ ፡ በማደር ፡ የሚፈጸመውና ፡ የሚታለ ፈው ፡ ለእኛ ፡ የተሰጠንስ ፡ አነስተኛው ፡ ፈተና ፡ ይቄይና ፡ ጻድቃን ፡ ሰማዕታት ለሞት ፡ ለኀልፈት ፡ የሚያበቃውን ፡ ፀዋትወ ፡ መከራ ፡ በተቀበሉ ፡ ጊዜ ፡ ዕፁብ ዕፁብ ፡ በማለት ፡ የተጋድሎ ፡ ሥራቸውን ፡ አላቋረጡም ።

ሐዋርያው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ፈተናን ፡ በመሰቀቅ ፡ መንፈሳዊ ፡ ሥራን፡ማቋ ረጥ ፡ እንዳይገባን ፡ ሲያስረዳን ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ፡ (ወበአንተዝ ፡ ኢንትቄጣዕ፡እስመ ዘእንተ ፡ አፍአነ ፡ ብእሲ ፡ ይበሊ፤ወዘእንተ ፡ ውስጥነሰ ፡ ይትሔደስ ፡ ኵሎ ፡ አሚረ እስመ ፡ ሕማምነ ፡ ዘለሰዓት ፡ ቀሊል ፡ ክብረ ፡ ወስብሐተ ፡ ብዙኀ ፡ አፈድፊዶ ይገብር ፡ ለነ ።

እስመ ፡ ዘኢንሴፎ ፡ ዘያስተርኢ ፡ አላ ፡ ዘኢያስተርኢ ፡ እስመ ፡ ዘያስተርኢ ኃላፊ ፡ ውእቱ ። ወዘሰ ፡ ኢያስተርኢ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡ ውእቱ) ፡ ስለዚህ ፡ አንበ ሳጭ ፡ ቸል ፡ አንበል ፤ በአፍአ ፡ ያለ ፡ ሰውነታችን ፡ የሚጠፋ ፡ ነውና ፡ በውስጥ ያለው ፡ ሰውነታችን ፡ ግን፡ ሁል፡ጊዜ ፡ ይታደሳልና ።



የጥቂት ፡ ሰዓት ፡ መከራችን ፡ ክብርንም ፡ ምስጋናንም ፡ አብዝቶ ፡ ያስደርግል ናልና ፡ የማይተየውን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሚታየውን ፡ ዓለም ፡ ተስፋ ፡ አናደርግምና ፡ የሚታየው ፡ ዓለም ፡ የሚያልፍ ፤ የማይታየው ፡ ዓለም ፡ ግን ፡ ለዘለዓለሙ ፡ የሚ ኖር ፤ ስለሆነ ፡ ሁለተኛ ። ቆሮንቶስ ፡ ም ፡ ፬ ቍ ፡ ፲፮-፲፰ ።

ሊቀ ፡ ሐዋርያቱ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስም ፡ እንዲሁ ፡ ፈተናን ፡ በመሰቀቅ ፡ መን ፈሳዊ ፡ ሥራን ፡ ማቋረጥ ፡ እንዳይገባ ፡ ሲያስረዳ ፡ (አኃዊነ ፡ ኢታንክርዋ ፡ ለእንተ ፡ ትመጽአክሙ ፡ መከራ ፡ ከመ ፡ ዘነኪር ፡ ግብር ፡ ይከውን ፡ ብክሙ ፡ ዳዕሙ ፡ ከመ ትሳተፍዎ ፡ በሕማሙ ፡ ለክርስቶስ ፡ ወተፈሥሑ ፡ ከመ ፡ አመ ፡ ያስተርኢ ፤ በስብ ሐቲሁ ፡ ትትሐሠዩ ፡ ፍሡሐኒክሙ ።

ወእመሰበ ፡ ዘተዐየሩክሙ ፡ በእንተ ፡ ስሙ ፡ ለክርስቶስ ፡ ብፁዓን ፡ አንትሙ፡ እስመ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ወኃይሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወመንፈሱ ፡ የዐርፍ ፡ ላዕሌክሙ ።

ወንድሞቻችን የምትመጣባችሁን ፡ መከራ እንግዳ ፡ ሥራ ፡ እንደሚደረግባ ችሁ ፡ አድርጋችሁ ፡ አታድንቁዋት ፡ የለመዳችኋት ፡ መከራ ፡ ናት ፡ እንጂ ፤ የማት ለምዱትም ፡ መከራ ፡ ይመጣባችኋል ።

በመከራ ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋር፡ አንድ ፡ ትሆኑ ፡ ዘንድ ፡ በጌትነቱ ፡ በተገለጠ ፤ ጊዜም ፡ ክብሩን ፡ አግኝታችሁ ፡ ደስ ፡ ይላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ዛሬ ፡ በመከራው ፡ ደስ፡ ይበላችሁ ።

ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ቢሰድብዋችሁ ፡ የተመሰገናችሁ ፡ ናችሁ ፡ የእግዚአብሔር፡ ክብሩና ፡ ኃይሉ ፡ ሀብቱም ፡ በእናንተ ፡ ያድራልና ፡ ብሏል ፡ ፩ ፡ ጴጥሮስ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፲፪-፲፭ ።

ሊቀ ፡ ሐዋርያቱ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ቃሉ ፡ የነገረን ፤ በመከራ ፡ ከክ ርስቶስ ፡ጋር ፡ አንድ ፡ መሆናችንን ፡ ነው ።

በመከራ ፡ ወይም ፡ በፈተና ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ መሆንን ፡ ለማግኘት ፡ የምንችል ፡ ከሆነ ፤ ጾም ፡ ጸሎት ፡ ሰጊድ ፡ ቁመት ፡ በሚያመጡት ፡ ፈተና ፡ ላይ፡ሰው ነታችንን ፡ መጣልን ፡ ለምን ፡ እንፈራለን ፤ ለምንስ ፡ እንሰቀቃለን ፤ ክርስቶስ ፡ ያዘ ዘልንንና ፡ የፈቀደልንን ፡ ሥራ ፡ ሳንሠራ ፡ የክርስቲያንነትን ፡ ዋጋ ፡ ለማግኘት ፡ አንች ልምና ፡ ሰፊውን ፡ በር ፡ ሰፊውን ፡ መንገድ ፡ ትተን ፡ ወደጸባቡ ፡ ገብተን ፡ መሪያ ችን ፡ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ በእውነተኛው ፡ መንገድ ፡እንከተለው ።

አሁን፡ የማስታውቃችሁ ፡ ጌታችን ፡ ቀድሶ ፡ባርኮ ፡ በሰጠን ፡ በዚህ ፡ በዓቢይ ፡ ጾም ፡ መዝፈንን ፡ መጫዋትን ፡ መሣለቅን ፡ ያለልክ ፡ ጠጥቶ ፡ እግዚአ ብሔርን ፡ አለማሰብን ፡ መጣላትን ፡ መቃናትን ፡ ማሳጣትን ከሰውነታችሁ፤አርቃችሁ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ የመረጣቸውን ፡ ቅዱሳት ምግባራት ፡ መፋቀርን ፤ በመንፈሳዊ ፡ አካሔድ ፡ ደስ ፡ መሰናኘትን ፡ አንድነትን ፡ መታገሥን ፡ መመጽወትን ፡ ቸርነትን ፡ ሃይ ማኖትን ፡ ቅንነትን ፡ ንጹሕነትን ፡ ታገኙ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ከዚህም ፡ ቀጥዬ ፡ ስለ ፡ መላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕይወት ፡ ሰላማዊ ፤ ኑሮና ፡ አንድ
ነት ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የዳዊትን ፡ ሀብተ
መዊዕ ፡ እንዲሰጥልን ፡ በየጸሎታችሁ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ታመለክቱ ፡ ዘንድ ፡ አሳ
ስባችኋለሁ ።

መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በረከተ ፡ ጾሙን ፡ ያሳድርባችሁ ። እሱ
በጾሙ ፡ ዲያብሎስን ፡ ድል ፡ እንደነሣው ፤ በጾማችሁ ፡ ድል ፡ እንድትነሡ ፡ ኃይሉን
ይስጣችሁ ፡ መዋዕለ ፡ ጾሙን ፡ በሰላም ፡ አስፈጽሞና ፡ አሳልፎ ፡ ብርሃነ ፡ ትንሣኤ
ውን ፡ ለማየት ፡ ያብቃን ።

---

የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ስለ ፡ አዲሱ
ዘመን ፡ ዮሐንስ ፡ ጳጕሜን ፡ ፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡
የራዲዮ ፡ ጣቢያ ፡ ለሕዝብ ፡ ያሰሙት ፡ ቃለ ፡ በረከት ።

እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ ተስፋ ፡ ይፈጽም ፡ ለክሙ ፡ ኵሎ ፡ ፍሥሓ ፡ ወሰ
ላመ ፡ በአሚን ፡ ከመ ፡ ያብዝኅክሙ ፡ በተስፋሁ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወበኃይሉ ፡
ሮሜ ፡ ፲፭ ፡ ፲፫ ።

ሕይወትን ፡ ተስፋን ፡ በቸርነቱ ፡ ለመላው ፡ ዓለም ፡ የሚያድል ፡ እግዚአብ
ሔር ፤ በረከተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕለ ፡ ርእሰ ፡ ጻድቃን ፡ ይእቲ ፡ ታብዕል ፡
ወኢታመጽእ ፡ ኃዘነ ፡ ውስተ ፡ ልብ ፡ (ምሳ ፡ ፲ ፡ ፳፪) ።

የእግዚአብሔር ፡ በረከት ፡ በደጋጎች ፡ ሰዎች ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ናት ፡ የእግዚ
አብሔር ፡ በረከትም ፡ ካለች ፡ ዘንድ ፡ ሰላምንና ፡ ብልጥግናን ፡ እንጂ ፡ ኃዘንን ፡
ወደልብ ፡ አታመጣም ፡ ተብሎ ፡ የተነገረውን ፡ ቃለ ፡ ነቢይ ፡ በኛ ፡ በወገኖቹ ፡
ተፈጻሚ ፡ አድርጎ ፡ ሰላምን ፡ እንዲያድለንና ፡ ይህን ፡ የምንቀበለውን ፡ አዲሱን ፡
ዘመን ፡ መዋዕለ ፡ ሣህል ፡ መዋዕለ ፡ ሰላም ፡ እንዲያደርግልን ፡ በሰቂለ ፡ ሕሊና ፡
በነቂሐ ፡ ልቡና ፡ ሆነን ፡ በፍጹም ፡ ሃይማኖት ፡ ልመናችንን ፡ እናቀርባለንና ።

ይልቁንም ፡ ዝናማትን ፡ እያፈሰሰ ፤ ዘመናትን ፡ በየዓመቱ ፡ እያደሰ ፡ ብርሃ
ናትን ፡ እያመላለሰ ፡ ከጊዜ ፡ ወደጊዜ ፡ ስለሚያስተላልፈንና ፡ ባለፉት ፡ ዘመናት ፡
ሰላምና ፡ ሕይወትን ፡ ሰጥቶ ፡ ከዚህ ፡ ከአዲሱ ፡ ዘመን ፡ ስላደረሰን ፡ ወረታ
ውን ፡ በምን ፡ እንደምንመልስ ፡ ማሰብ ፡ ይገባናል ።

ወሮታውንም ፡ መክፈል ፡ የምንችለው ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ በአምላክነቱ ፡
ሁሉ ፡ ፈጥሮ ፡ በቸርነቱ ፡ ለሥጋውያን ፡ ሁሉ ፡ ምግብ ፡ የሚሰጥ ፡ እንደመሆኑ ፡
እኛም ፡ በዝናም ፡ አብቅሎ ፡ በፀሐይ ፡ አብስሎ ፡ ከሰጠን ፡ ሲሳይ ፡ ነዳያንን ፡
በማሰብ ፡ ለቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚገባውንም ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡
በማቅረብ ፡ ከዚህም ፡ ጋር ፡ የትሩፋትን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አብዝቶ ፡ በመሥራት ፡ ነው ፡

ነዳያንን ፡ በምንችለው ፡ መጠን ፡ መርዳትና ፡ ማሰብ ፡ እንዲገባንም ፡ ለማ
ስረዳት ፡ ሊቁ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ብፁዕ ፡ ዘይሴብሑ ፡ ላዕለ ፡ ነዳይ ፡ ወምስ



ኪን ፡ ያለውን ፡ የክቡር ፡ ዳዊትን ፡ ቃል ፡ ሲተረጕም ፤ የነዳያንን ፡ ችግራቸውን ፡
አይተው ፡ ኑሮዋቸውን ፡ ተመልክተው ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ሊሠሩላቸው ፡ ስለሚያስቡ ፡
ሰዎች ፡ ተናገረው ፡ ከማለቱ ፡ ቀጥሎ ፡ የተቸገረን ፡ ሰው ፡ በየህ ፡ ጊዜ ፡ ቸል ፡
አትበል ፡ መቸገሩን ፡ አይተህ ፡ በጎ ፡ ሥራለት ፡ እንጂ ፡ ብሏል ። ተግሣጽ ፡ ፲ ገጽ ፡
፻፷፩—፷፱ ።

ሞተ ፡ ሥጋን ፡ አልፈን ፡ ከሞተ ፡ ነፍስ ፡ ድነን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡
የምንወርስበትን ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ እንዲገባን ፡ ሲያስረዳም ፤ በመንግሥተ ፡
ሰማያት ፡ ሞተ ፡ ሥጋ ፡ ሞተ ፡ ነፍስ ፡ የለም ፡ የሚዘርፍ ፡ የሚገፍ ፡ ጠላት ፡
የለም ። የጻድቃን ፡ አንድነት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ። ይህች ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትም ፡
የማታልፍ ፡ ለዘለዓለም ፡ የምትኖር ፡ ናት ።

እሷም ፡ ከዘመን ፡ በታች ፡ አይደለችም ፡ በኋላፊው ፡ ዘመን ፡ አትመሰል
ምና ፡ ብሏል ፡ ተግሣጽ ፡ ፴ ፡ ገጽ ፡ ፮፻፵፯ ።

ስለዚህ ፡ ከላይ ፡ እንዳልነው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ዘመናትን ፡ እያፈራረቀ ፡ በሕ
ይወት ፡ እየጠበቀ ፡ ከዚህ ፡ ላደረሰን ፡ በወዲያኛውም ፡ ዓለም ፡ ተድላ ፡ መንግ
ሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ላዘጋጀልን ፡ እግዚአብሔር ፡ የልብ ፡ አገልጋዮቹ ፡ መሆንና ፡
ለሚጠብቀን ፡ ክብር ፡ የተገባን ፡ ሆነን ፡ መገኘት ፡ ይገባናል ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወረታ ፡
መክፈል ፡ አለብን ፡ ላልነውም ፡ ሰው ፡ በምን ፡ ዓቅሙ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ወረታ ፡
መክፈል ፡ ይችላል ፡ የሚል ፡ ሕሊናዊ ፡ ምርምር ፡ እንዳይገጥመን ፡ እስራኤልን ፡
"ወልድየ ፡ ዘበኵርየ„ ፡ ይላቸው ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ ብትጠብቁት ፡ እጠብቃችኋለሁ ፡
ብሎ ፡ ከወረታ ፡ ሊቈጥርላቸው ፡ የተዋዋለባቸውን ፡ ቃላትና ፡ ከዚያም ፡ ወዲህ ፡
በሐዲስ ፡ መድኃኒትነት ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ሥጋ ፡ ለብሶ ፡ በቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ የሰጠ
ን ፡ ትእዛዝ ፡ መፈጸም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ወረታ ፡ መክፈል ፡ መሆኑን ፡ ማወቅ ፡
አለብን ።

ከዚህም ፡ ጋር ፡ እግዚአብሔር ፡ ሁልጊዜ ፡ እኛን ፡ መጠበቅ ፡ የባሕርይ ፡
ፈቃዱ ፡ ስለሆነ ፤ በሳቸው ፡ አድሮ ፡ ይጠብቀን ፡ ዘንድ ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ መርጦ ፡
የጠባቂነትና ፡ የመሪነት ፡ ዕድል ፡ ላጐናጸፋቸው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡
ሥላሴ ፡ ቅን ፡ ታዛዥነትን ፡ ገንዘብ ፡ አድርገንና ፡ ደስታቸው ፡ የሁላችን ፡ ደስታ ፡
ክብራቸው ፡ የሁላችን ፡ ክብር ፡ መሆኑን ፡ ተገንዝበን ፡ በታማኝነት ፡ ማገልገል ፡
ይገባናል ።

ይህም ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ እንዳይደለ ፡ ለማስረዳት ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ለእግዚ
አብሔርኒ ፡ ፍርህዎ ፡ ወለንጉሥኒ ፡ አክብርዎ ፡ (እግዚአብሔርን ፡ ፍሩት ፡ ንጉሥ
ንም ፡ አክብሩት ፡) በማለት ፡ ገልጾታል ። ስለዚህ ፡ ጌታ ፡ በወንጌል ፡ የነገረን ፡
ሐዋርያት ፡ በስብከት ፡ ያስረዱንን ፡ ሃይማኖትን ፤ ተስፋን ፡ ፍቅርን ፡ ትሕትናን ፡
ንጽሕናን ፡ ትዕግሥትን ፡ ጾምን ፡ ጸሎትን ፡ ምጽዋትን ፡ መሸጋገሪያ ፡ ድልድይ ፡
አድርገን ፡ አረፍተ ፡ ዘመንን ፡ ለማለፍ ፡ እንድንችል ፡ እግዚአብሔርን ፡ በንጹሕ ፡
ልብ ፡ እንለምነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ ለሀገር ፡ ድጋፍ ፡ ለመንግሥት ፡ ኃይል ፡ ጽንዕ ፡ የሚሆን ፡ ፍቅር ፡ አንድነትን ፡ ሰጥቶ ፡ መለያየትንና ፡ መቃናትን ፡ ከሕሊናችን ፡ አጥፍቶ ፡ የምድርን ፡ ፍሬ ፡ በርከ ፡ ዘመኑን ፡ የተድላ ፡ የደስታ ፡ ዘመን ፡ ያድርግልን ፡ በማለት ፡ ከላይ ፡ አርእስት ፡ ሆኖ ፡ በተጠቀሰው ፡ በሐዋርያው ፡ በቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ቃል ፡ የተስፋ ፡ ባለቤት ፡ እግዚአብሔር ፡ ደስታን ፡ አንድነትን ፡ በሃይማኖት ፡ ይፈጽምላችሁ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በሚገኝ ፡ ተስፋ ፡ በከሃሊነቱ ፡ ያብዛችሁ ፡ እንዲሁም ፡ ዘመንን ፡ በዘመን ፡ የሚያድስ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የጸናውን ፡ ሃይማኖት ፡ የቀናውን ፡ ምግባር ፡ በሥራ ፡ እንድትከታተሉ ፡ ያድርጋችሁ ፡ እያልኩ ፡ ከእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በተሰጠኝ ፡ ሐዋርያዊነት ፡ አማልዳችኋለሁ ።

---

ስለ ፡ ዐቢይ ፡ ጾም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ የካቲት ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በራዲዮ ፡ ያሰሙት ፡

<u>ቃለ ፡ ምዕዳን ።</u>

ወይእዜኒ አኃዊነ ፡ ንነግረክሙ ፡ ወናስተበቍዐክሙ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመ ፡ ተአዘዝክሙ ፡ በኀቤነ ፤ በዘይደሉ ፡ ከመ ፡ ትሑሩ ፡ ወታሥምርዎ ፡ ለእግዚአብሔር ። ወበከመ ፡ ሖርክሙ ፡ ዓዲ ፡ ከመ ፡ ታብዝኁ ፡ ወታፈድፍዱ ፡ በዝንቱ ፡ እስመ ፡ ዝ ውእቱ ፡ ትእዛዙ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወፈቃዱ ፡ ተቀድሶትክሙ ፡ ውእቱ ፡ ፩ ፡ ተሰሎ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፩–፫ ።

ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፤ ሰማዕታትን ፡ ወደደም ፡ ጻድቃንን ፡ ወደገዳም ፡ እንደመራቸውና ፡ የሚጠቀሙበትን ፡ ሥራ ፡ እንደሠራላቸው ፡ እኛንም ፡ በቸርነቱ ፡ ወደጸሎት ፤ ወደጾም ፡ እንዲመራንና ፡ የምንጠቀምበትን ፡ ሥራ ፡ እንዲያሠራን ፡ ፈቃዱ ፡ ይሆንልን ፡ ዘንድ ፡ በሰቂለ ፡ ሕሊና ፡ በነቂሐ ፡ ልቡና ፡ ሆነን ፡ አስቀድመን ፡ ማመልከት ፡ ይገባናል ።

ጌታችንና ፡ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በመዋዕለ ፡ ሥጋዌው ፡ ለእኛ ፡ አብነቶችና ፡ መሠረቶች ፡ እንዲሆኑን ፡ ከሠራቸው ፡ ድንቅ ፡ ድንቅ ፡ ሥራዎች ፡ መጀመሪያው ፡ ጾም ፡ ነው ።

ይኸውም ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ እርሱ ፡ ጌታችን ፡ በማየ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ተጠምቆ ፡ ሳይውል ፡ ሳያድርም ፡ ዕለቱን ፡ ወደገዳም ፡ ሔዶ ፡ ዓርባ ፡ መዓልት ፡ ዓርባ ፡ ሌሊት ፡ ጾሟል ፡ ማቴ ፡ ም ፬ ፡ ቍ ፡ ፪ ።

ተጠምቆም ፡ ሳይውል ፡ ሳያድር ፡ ዕለቱን ፡ ወደገዳም ፤ መሔዱ ፡ ለባሕታውያን ፡ አብነት ፡ ለመሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንዲያው ፡ ለከንቱ ፡ አይደለም ።

ሆኖም ፡ ረቂቅ፡ዘእምረቂቅ ፡ እንደሆነ፡ለማጠየቅ፡ በኀቱም፡ድንግልና ፡ ተፀንሶ ፡ በኀቱም ፡ ድንግልና ፡ እንደተወለደ ፤ ዘኢይትገሠሥ ፡ እምዘኢይትገሠሥ ፡ እንደሆነ ፡ ለማጠየቅ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ እንደሔደ ፤ ብርሃን ፡ ዘእምብርሃን ፡ እንደሆነ ፡ ለማጠየቅ ፡ ብርሃነ ፡ መለኮቱን ፡ በደብረ ፡ ታቦር ፡ እንደገለጠ ፤ ሕይወት ፡ ዘእምሕይወት



እንደሆነ ፡ ለማጠየቅ ፡ ያራት ፡ ቀን ፡ ሬሳ ፡ አልዓዛርን ፡ አስነሥቶ ፡ የአካሉንና ፡ የባሕርዩን ፡ ተዋሕዶ ፡ እንደገለጠልን ፤ ዘኢይርኅብ ፡ እምዘኢይርኅብ ፡ እንደሆነ ፤ ለማጠየቅ ፡ ዓርባ ፡ መዓልት ፡ ዓርባ ፡ ሌሊት ፡ ምንም ፡ ምን ፡ ሳይቀምስ ፡ ጾሞ ፡ የተዋሐዶውን ፡ ምሥጢር ፡ (ሥግው ፡ አምላክ ፡ መሆኑን) ፡ ገልጦልናልና ።

ቅዱስ ፡ ወንጌል ፤ በጾሙ ፡ ጊዜ ፡ የነበረውን ፡ ሁኔታ ፡ ሲነግረን ፤ ዓርባ ፡ መዓልት ፡ አርባ ፡ ሌሊት ፡ ከጾመ ፡ በኋላ ፡ ተራበ ፡ (ወእምዝ ፡ ርኅበ) ፡ ይላል ።

ዓርባ ፡ ቀን ፡ ከመብል ፡ ከመጠጥ ፡ ተከልክሎ ፡ በመጾሙ ፤ ተዋሕዶውንና ፡ የባሕርይ ፡ አምላክነቱን ፡ ከገለጠ ፡ በኋላ ፤ መራቡ ፡ ግን ፡ በፈቃዱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ እኛ ፡ በግድ ፡ አይደለም ።

በፈቃዱ ፡ መራቡም ፡ ለአጽድቆተ ፡ ትስብእትና ፡ ለካሣ ፡ ነው እንጂ ፡ የግድ ፡ ረኃብ ፡ ኖሮበት ፡ አይደለም ። ይኸውም ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ የሚፈታተነው ፡ ዲያብሎስ ፡ አቡሃ ፡ ለሐሰት ፡ ስለሆነ ፤ አብ ፡ በዮርዳኖስ ፡ (ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልድየ) ፡ ይህ ፡ ልጄ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ተዋሕዶውንና ፡ የባሕርይ ፡ አምላክነቱን ፡ ሲመሰክርለት ፤ ሰምቶ ፡ ነበርና ፡ በመራቡ ፡ ጊዜ ፡ ሊፈታተነው ፡ ቀርቦ ፤

(እመሰ ፡ ወልዱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንተ ፡ በል ፡ ከመ ፡ እላ ፡ አዕባን ፡ ኅብስተ ፡ ይኩና) ፡ የእግዚአብሔርስ ፡ ልጅ ፡ ከሆንክ ፡ እኒህ ፡ ደንጊያዎች ፡ ኅብስት ፡ ይሁኑ ፡ ብለህ ፡ እዘዝ ፡ ቢለው ፤ ሰው ፡ የሚኖር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አፍ ፡ በምትወጣ ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ እንጂ ፡ በእንጀራ ፡ ብቻ ፡ እንዳይኖር ፡ ተጽፎዋል ፡ ብሎ ፡ አሳፍሮታል ። በእውነት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ መሆኑንም ፡ ገልጦበታል ።

እንዲሁም ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ምሕዋር ፡ (በጕልላቱ ፡ ላይ) ፡ በቆመ ፡ ጊዜ ፤ በእውነት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ከሆንክ ፤ ከዚህ ፡ ዘለህ ፡ ወደታች ፡ ውረድ ፡ ብሎ ፡ ቢፈታተነው ፡ ፈጣሪህን ፡ እግዚአብሔርን ፡ አትፈታተነው ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ ድል ፡ ነሥቶታል ።

ወደረጅም ፡ ተራራ ፡ በወጣ ፡ ጊዜም ፤ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ክብር ፡ ሁሉ ፡ አሳይቶ ፡ ብትሰግድልኝ ፡ (እጅ ፡ ብትነሣኝ) ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ እሰጥሃለሁ ፡ ብሎ ፡ በድፍረት ፡ ቢፈታተነው ፤ (ጽኑ ፡ ባላጋራዬ) ፡ ሰይጣን ፡ ከኋላዬ ፡ ወግድ ፤ ለፈጣሪህ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ትሰግድ ፡ ዘንድ ፡ እሱንም ፡ ብቻ ፡ ታመልክ ፡ ዘንድ ፡ ተጽፎዋል ፡ ብሎ ፡ ድል ፡ ነሥቶታል ። ከኋላዬ ፡ ወግድ ፡ ባለውም ፡ ጊዜ ፡ እንደጢስ ፡ ተኖ ፡ እንደትቢያ ፡ በኖ ፡ ጠፍቷል ።

ጌታችን ፡ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዓርባ ፡ መዓልት ፡ ዓርባ ፡ ሌሊት ፡ ጾሞ ፡ እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ ዲያብሎስን ፡ ድል ፡ መንሣቱ ፤ እኛን ፡ በጾም ፡ ድል ፡ ንሡት ፡ ብሎ ፡ ሲያዝዘን ፡ ነውና ፡ ተሐድሶተ ፡ ነፍስ ፡ የሚገኝበት ፡ ጾምን ፡ እንደተራ ፡ ነገር ፡ አድርጎ ፡ ማቃለል ፡ አይገባም ።

www.ethiopianorthodox.org

ጾም ፡ ቅዱስ ፡ ተግባር ፡ መሆኑን ፡ እንረዳ ፡ ዘንድ ፣ መምህራችን ፡ እርሱ ፡ ሥራውን ፡ በጾም ፡ ጀምሮ ፡ አሳይቶናልና ፡ የጾምን ፡ ጠቃሚነት ፡ ለማወቅ ፡ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ብዙ ፡ ሐተታ ፡ ለማቅረብ ፡ አያደክምም ።

ስንጾምም ፡ ከቧልት ፣ ከሐሜት ፣ ከዕዕለት ፡ ተከልክለን ፡ የየራሳችንን ፡ ኃጢአት ፡ እያሰብን ፡ በራሳችን ፡ መፍረድና ፡ ራሳችንን ፡ መዝለፍ ፡ ይገባናል ።

ነቢየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዳዊት ፡ ኃጢአትን ፡ እያሰበ ፡ ራስን ፡ ማሳጣት ፡ እንዲገባ ፡ ሲያስረዳ ፣ (ኃጢአትየ ፡ ነገርኩ ፡ ወአበሳየ ፡ ኢኀባእኩ ፣ ወእቤ ፡ አስተዋዲ ፡ ርእስየ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዐእንተ ፡ ኃጢአትየ ፣ ወአንተ ፡ ኀድግ ፡ ጽልሑቶ ፡ ለልብየ) ፡ ኃጢአቴን ፡ ላንተ ፡ ነገርኩ ፣ በደሌንም ፡ አልሸፈንኩም ። (ራሴን ፡ አሳጣለሁ) ፡ መተላለፌን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እነግራለሁ ፡ አልሁ ።

አንተም ፡ የኃጢአቴን ፡ ዐመፃ ፡ ተውክልኝ ፡ መዝሙር ፡ ፴፪ ፡ ቍ ፡ ፭ ።

የቍስጥንጥንያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ሊቁ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈወርቅም ፣ እንዲሁ ፡ ስለ ፡ ሠሩት ፡ ኃጢአት ፡ በራስ ፡ መፍረድ ፡ እንዲገባ ፡ ሲያስረዳ ፣ (ጻድቅ ፡ ያቀድም ፡ ዘለፋ ፡ ርእሱ ፡ ወዳግመሰ ፡ ይከውን ፡ በብዙኅ ፡ ትሕትና) ፡ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ በሠራው ፡ ኃጢአት ፡ አስቀድሞ ፡ በራሱ ፡ ይፈርዳል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፍጹም ፡ ትሕትናን ፡ ይሠራል ፡ ብሏል ። ዮሐንስ ፡ አፈወርቅ ፡ ተግ ፡ ፱ ፡ ገጽ ፡ ፻፹፩ ። ጾምን ፡ አጥብቀን ፡ መፍራት ፡ የሚገባንም ፡ ራሳችንን ፡ እንድንወቅስበትና ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መቅረብን ፡ እንድናገኝበት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሙሉ ፡ መብላትን ፡ ልማድ ፡ ለማድረግ ፡ አይደለም ።

ስለዚህ ፡ በአርእስቱ ፡ የጠቀስነው ፣ የሐዋርያው ፡ ቃል ፡ ጾምንና ፡ እንደጾም ፡ ያሉትን ፡ መንፈሳውያን ፡ ምግባራትን ፣ ጸሎትን ፣ ምጽዋትንና ፡ ሌሎችንም ፡ ሁሉ ፡ ቸል ፡ እንዳንላቸው ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡ ይማልደናል ።

«እሁንም ፡ ወንድሞቻችን ፡ ሆይ ፣ እንነግራችኋለን ፣ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ እንማልዳችኋለን ። ከኛ ፡ ዘንድ ፡ እንደታዘዛችሁ ፡ በሚገባ ፡ ትሔዱ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ደስ ፡ ታሰኙት ፡ ዘንድ ፡ ቀድሞ ፡ ስትሠሩ ፡ እንደኖራችሁ ፣ እንግዲህም ፡ ይህን ፡ አብዝታችሁ ፡ ትሠሩ ፡ ዘንድ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያዘዝናችሁን ፡ ትእዛዝ ፡ ታውቃላችሁ ። የእግዚአብሔር ፡ ትእዛዙ ፡ ይህ ፡ ነውና ፣ ፈቃዱም ፡ በንጽሕና ፡ መኖራችሁ ፡ ነውና» ፡ ሁላችን ፡ በዚህ ፡ ሐዋርያዊ ፡ ትእዛዝ ፡ ጸንተን ፡ ሥጋችንን ፡ በጾም ፡ የክርስቶስ ፡ ተገዥ ፡ ማድረግ ፡ ይገባናል ።

ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ መዋዕለ ፡ ጾሙን ፡ በሰላም ፡ አሳልፎ ፡ ብርሃነ ፡ ትንሣኤውን ፡ ማየትን ፡ ለሁላችሁ ፡ ይክፈላችሁ ። (አ ሜ ን) ።



ስለ ፡ ጌታችንና ፡ ስለ ፡ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በዓለ ፡ ትንሣኤ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ሚያዝያ ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ቀዳሚት ፡ ከምሽቱ ፡ በሁለት ፡ ሰዓት ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ራዲዮ ፡ ጣቢያ ፡ ተገኝተው ፣

## ለሕዝብ ፡ ያሰሙት ፡ ቃለ ፡ ምዕዳን ።

ወንሕነኒ ፡ ንዜንወክሙ ፡ ዘአሰፈዎሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአበዊነ ፣ ወወሀበሙ ፡ ለውሉዶሙ ፡ ወአንሥአ ፡ ለኢየሱስ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ውስተ ፡ መዝሙር ፡ ዘክልኤቱ ፡ ወልድየ ፡ አንተ ፣ ወአነ ፡ ዮም ፡ ወለድኩከ ፣ እስመ ፡ አንሥአ ፡ እሙታን ። ከመ ፡ ኢይገብእኒ ፡ ውስተ ፡ ሙስና ፣ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እሁበክሙ ፡ ጽድቆ ፡ ለዳዊት ፡ ዘእሙን ።

ወውስተ ፣ ካልእኒ ፡ ይብል ፡ ኢትሁብ ፡ ለጻድቅከ ፡ ይርአይ ፡ ሙስና ፣ ወዳዊትኒ ፡ ተልእከ ፡ በመዋዕሊሁ ፡ ለትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኖመ ፡ ወተቀብረ ፡ ኀበ ፡ አበዊሁ ፡ ወርእየ ፡ ሙስና ።

ወዘሰ ፡ አንሥአ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢርእየ ፡ ለሙስና ፡ አእምሩ ፡ እንከ ፡ አኃዊነ ፡ ከመ ፡ በእንቲአሁ ፡ ይትኀደግ ፡ ለክሙ ፡ ኃጢአትክሙ ፡ ዘአሰፈወክሙ ። ግብ ፡ ሐዋ ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ቍ ፡ ፴፪—፴፱ ።

ሕያው ፡ ባሕርይ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፣ ልቡናችንን ፡ አነቃቅቶ ፡ የጌትነቱን ፡ ሥራ ፡ በልባችን ፡ ለማሰብና ፡ በቃላችን ፡ ለመናገር ፡ ስለአበቃን ፣ እንደበታችንንም ፡ መርቶ ፡ ጌትነቱን ፡ ወደ ፡ ማመስገን ፡ ስላደረሰልን ፡ የትንሣኤውን ፡ ምሥራች ፡ እነሆ ፡ እንናገራለን ።

እንዲሁም ፡ በይቅርታውና ፡ በቸርነቱ ፡ ብዛት ፡ እኛን ፡ ልጆቹ ፡ ወዳጆቹ ፡ ሊያሰኘንና ፡ እንደቀድሞው ፡ በደመ ፡ ላሕም ፡ በደመ ፡ ጠሊ ፡ ሳይሆን ፣ በራሱ ፡ ደም ፡ ከፍዳ ፡ ሊያነጻን ፡ ወዶ ፡ የአምላክነቱንም ፡ የሰውነቱንም ፡ ሥራ ፡ በተዋሕዶ ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ፣ የደረሰበትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ፈተና ፡ ሁሉ ፡ ድል ፡ መንሣቱን ፡ ልናስታውሰው ፡ ይገባናል ።

የፈተናውንም ፡ ዓይነት ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በወርኃ ፡ ጾሙ ፡ መግቢያ ፡ ጊዜ ፡ በማየ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ተጠምቆ ፡ ሳይውል ፡ ሳያድር ፡ ዕለቱን ፡ ወደ ፡ ገዳመ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ሔዶ ፡ ዐርባ ፡ መዓልት ፡ ዐርባ ፡ ሌሊት ፡ መጾሙንና ፡ ዲያብሎስ ፣ በሦስቱ ፡ አርእስተ ፡ ኃጣውእ ፡ ያቀረበውን ፡ ጾር ፡ ድል ፡ መንሣቱን ፡ ገልጠነው ፡ ነበርና ፡ አሁን ፡ የምንናገረው ፡ ከዚያው ፡ ከተናገርነው ፡ የሚቀጥለውን ፡ ነው ።

"የሉቃስ ፡ ወንጌል" ፣ ሰይጣን ፡ በሁሉ ፡ ከተፈታተነው ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ጊዜው ፡ ተወው ፡ ብሎ ፡ በአይሁድ ፡ አድሮ ፡ በዕለተ ፡ ዐርብ ፡ እስኪያሰቅለው ፡ ድረስ ፡ ዳግመኛ ፡ ወደርእሱ ፡ አለመድረሱን ፡ እንደነገረን ፣ ተንኰሉን ፡ የሚያፈርስበትን ፡ መለኮታዊ ፡ ጥበቡንና ፡ ተአምራቱን ፡ እያየ ፡ ይፈራ ፡ ይደነግጥ ፡ ነበር ፡ እንጅ ፡ ሊቀርበው ፡ አልቻለም ።

www.ethiopianorthodox.org

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፤ ጽዋዐ ፡ ሞቱን ፡ በፈቃዱ ፡ የሚቀበልበት ፡ ሰዓት ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ በአይሁድ ፡ አድሮ ፡ እየለዋወጠ ፡ ያመጣበትን ፡ ምክንያተ ፡ ፀብእ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ እንናገረዋለን ።

፩ኛ ፡ ዕዉር ፡ ሆኖ ፡ የተወለደውን ፡ ሰው ፡ ዓይን ፡ በተአምራት ፡ ማብራቱን ፡ ሰምቶ ፡ ዕለቱ ፡ ቅዳሜ ፡ ነበርና ፡ (አይሁድ ፡ ዝንቱ ፡ ብእሲ ፡ ዘኢየዐቅብ ፡ ሰንበተ ፡ ኢኮነ ፡ እምእግዚአብሔር) ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ሰንበትን ፡ አያከብርምና ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አይደለም ፡ እንዲሉ ፡ አድርጓል ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፱ ቍ ፲፮ ።

፪ኛ ፡ አልዓዛርን ፡ በሞተ ፡ በአራተኛው ፡ ቀን ፡ እንዳስነሣውና ፡ ወንጌልን ፡ የሚማሩ ፡ ብዙ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ እንደተሰበሰቡ ፡ አይቶ ፤ እነሆ ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ተከተለው ፤ በማናቸውም ፡ እንዳልተረባቹ ፡ ታያላችሁን ? ብለው ፡ ፈሪሳውያን ፡ ለአይሁድ ፡ የሚያበሳጭ ፡ ነገር ፡ እንዲነግሩዋቸው ፡ አድርጓል ፡ ዮሐ ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ቍ ፡ ፲፱ ።

፫ኛ ፡ ተአምራት ፡ ማድረጉንና ፡ የትምህርቱን ፡ መጋነን ፡ አይቶ ፡ "እነሆ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ብዙ ፡ ተአምራት ፡ ያደርጋል ፡ ምን ፡ እናድርግ? እንዲሁም ፡ ብንተወው ፡ ሁሉ ፡ ያምንበታል ፡ የሮሜ ፡ ሰዎችም ፡ መጥተው ፡ አገራችንንም ፡ ወገናችንንም ፤ ይወስዱብናል" ፡ እንዲሉ ፡ አድርጓል ፡ ዮሐ ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ቍ ፡ ፵፯ ።

፬ኛ፡ "በሞት ፡ አርቀው ፡ ስቀለው"፡ እያሉ ፡ አሰምተው ፡ በተናገሩ ፡ ጊዜ ፤ ጲላጦስ ፡ ንጉሣችሁን ፡ ክርስቶስን ፡ ልስቀለውን ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቃቸው ፡ (አልብነ ፡ ንጉሥ ፡ ዘእንበለ ፡ ቄሣር) ፡ ንጉሣችን ፡ ቄሣር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከቄሣር ፡ በቀር ፡ ንጉሥ ፡ የለንም ፡ አሰኝቶ ፡ በሥጋቸውም ፡ በነፍሳቸውም ፡ ሠልጥኖባቸዋል ፡ ዮሐ ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ቍጥር ፡ ፲፭ ።

ጌታ ፡ በፈቃዱ ፡ የሚሞትበት ፡ ጊዜ ፡ እስኪደርስ ፡ በአይሁድ ፡ አድሮ ፡ እንዲህ ፡ እያደረገ ፡ ምክንያተ ፡ ሞቱን ፡ ሲያዘጋጅ ፡ ቢቆይም ፤ በመዋዕለ ፡ ጾሙ ፡ ካቀረበበት ፡ ፈተና ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ስቅለቱ ፡ ድረስ ፡ ባደረገው ፡ መቃወም ፡ ሁሉ ፤ ንጹሐ ፡ ባሕርይ ፡ በሆነ ፡ በጌታችን ፡ በመድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጥቂት ፡ ምክንያተ ፡ ስሕተት ፡ ስንኳ ፡ ሊያገኝበት ፡ አልቻለም ።

ይኸውም ፡ በጌታ ፡ ቃል ፡ አስቀድሞ ፤ የተገለጸና ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ሀ/ የነቢብ ፡ ስሕተት ፡ እንዳልተገኘበት ፡ ሲያስረዳ ፤ በነቢዩ ፡ በኢሳይያስ ፡ አድሮ ፡ ስለወገኖቼ ፡ ኃጢአት ፡ ለሞት ፡ ደረሰ ፤ ክፉዎችን ፡ ሊቀብሩት ፤ ባለጠጎችን ፡ ሊገድሉት ፡ እሰጣለሁ ፡ ኃጢአትን ፡ አልሠራምና ፡ ባፉም ፡ ተንኰል ፡ አልተገኘበትምና ። ብሏል ፡ ኢሳ ፡ ም ፡ ፶፫ ፡ ቍ ፡ ፱ ።

ሊቀ ፡ ሐዋርያቱ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስም ፡ እንደዚሁ ፡ እንደነቢዩ ፡ ቃል ፡ የነቢብ ፡ ስሕተት ፡ እንዳልተገኘለት ፡ ገልጦ ፡ ስለዚህ ፡ ተጠርታችኋል ፡ ክርስቶስ ፡ ስለእናንተ ፡ መከራ ፡ ተቀብሏልና ፡ ፍለጋውን ፡ እንድትከተሉ ፡ ምሳሌውን ፡ ይተ



ውላችሁ ፡ ዘንድ ። እርሱ ፡ ኃጢአት ፡ እንዳልሠራ ፡ በቃሉም ፡ ሐሰት ፡ እንዳልተገኘ ። ሲሰድቡትም ፡ አልተሳደበም ፡ መከራ ፡ ሲያመጡበትም ፡ አልተቀየመም ፡ ፍርድን ፡ በውነት ፡ ለሚፈርድ ፡ (ለአብ) ፡ ሰጠ፡እንጂ ፡ ስለኛ ፡ ኃጢአትም ፡ በሥጋው ፡ በዕንጨት ፡ ተሰቀለ ፡ እኛን ፤ ከኃጢአት ፡ አውጥቶ ፡ ያኖረን ፡ ዘንድ ፡ ፩ ጴጥ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፳፩—፳፬ ።

እኛም ፡ ከሃይማኖት ፡ የሚያናውጽ ፡ ከምግባር ፡ የሚያድጽ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ፈተና ፡ በደረሰብን ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ የመሪያችን ፡ የክርስቶስን ፡ ትዕግሥት ፡ መከተል ፡ ይገባናል ።

ለ/ የገቢር ፡ ስሕተት ፡ እንዳልተገኘበት ፡ ሲያስረዳ ፡ (መኑ ፡ እምኔክሙ ፡ ዘይዛለፈኒ ፡ በእንተ ፡ ኃጢአት ፡ (ከእናንተ ፡ ወገን፡ ስለኃጢአት ፡ የሚወቅሰኝ ፡ ማነው ? ብሏል ፡ ዮሐ ፡ ም ፡ ፰ ፡ ቍ ፡ ፵፮ ።

ሐ/ የሐልዮ ፡ ስሕተት ፡ እንዳልተገኘበት ፡ ሲያስረዳ ፡ (አስቀድሞ ፡ ዐውቆ ፡ የነገረን ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ቢሆን ፡ እንጂ ፡ ነው ፡ ብላችሁ) ፡ ታምኑ ፡ ዘንድ ፡ ሳይደረግ ፡ አስቀድሜ ፡ ዛሬ ፡ ነገርኋችሁ ።

ደግሞ ፡ ለናንተ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ አልነግራችሁም ። የዚህ ፡ ዓለም ፡ አበጋዝ ፡ (ዲያብሎስ) ፡ ይመጣልና ፡ በኔ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ አያገኝብኝም ፡ ብሏል ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፲፬ ፡ ቍ ፡ ፳፱—፴፩ ።

ሥጋ ፡ መልበሱን ፡ ምክንያት፡ አድርጎ ፡ በብዙ ፡ ነገር ፡ ሊፈታተነው ፡ የቀረበ ፡ ዲያብሎስ ፤ ዐርባ ፡ መዓልት ዐርባ ፡ ሌሊት ፡ በጾመ ፡ ጊዜ፡ በትዕቢት ፡ ቢመጣበት ፡ በትሕትና ፤ በስስት ፡ ቢመጣበት ፡ በትዕግሥት ፤ በፍቅረ ፡ ንዋይ ፡ ቢመጣበት ፡ በጸሊአ ፡ ንዋይ ፡ ድል ፡ ከነሣው ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ በአይሁድ ፡ እያደረ ፡ የጠላትነት ፡ ፈተና ፡ ቢያቀርብለት ፡ የነቢብ ፡ የገቢር ፡ ፡ የሐልዮ ፡ ስሕተት ፡ ያልተገኘበት ፡ ንጹሕ ፡ የሆነ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ (ሥግው ፡ አምላክ) ፡ በመሆኑ ፡ የፈተናውን ፡ ጾር ፡ ሁሉ ፡ ሰባብሮ ፡ በታል ።

በፍቃዱም ፡ ቅድስት ፡ ነፍሱን ፡ ከቅዱስ ፡ ሥጋው ፡ በለየ ፡ ጊዜ ፡ የአዳም ፡ ልጆች ፡ ነፍስና ፡ ሥጋ ፡ መቈራኘትን ፡ ልማድ ፡ አድርጎ ፡ ነበረና ፤ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ መስሎት ፡ (ሎቱ ፡ ስብሓት) ፡ ቅድስት ፡ ነፍሱን ፡ ለመቆራኘት ፡ ሲቀርብ ፡ መለኮታዊ ፡ ብርሃኑን ፡ ቦግ ፡ አድርጎ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ መንቀሳቀስ ፡ እንዳይችል ፡ በሥልጣኑ ፡ ወስኖ ፡ (አሥሮ) ፡ አስቀርቶታል ።

ሐዋርያው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፤ እንዲሁ ፡ የዲያብሎስን ፡ ኃይል ፡ በሞቱ ፡ አድክሞ ፡ ለእኛ ፡ ወደተወደደ ፡ አባትነቱ ፡ መቅረብንና ፡ መንፈሳዊ ፡ ኃይልን ፡ እንደሰጠን ፡ ሲነግረን ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ።

«ደግሞ ፡ እነሆ ፡ እኔና ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰጠኝ ፡ ልጆች ፡ አንድ ፡ ነን ፡ አለ ። ዳግመኛም ፡ አምንበታለሁ ፡ አለ ። ልጆች ፡ በሥጋና ፡ በደም ፡ ተገናኝተውታልና ፡ እሱም ፡ በዚህ ፡ ተገናኛቸው ፡ እንደ ባልንጀራም ፡ ሆነላቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

በሞቱ ፡ የሞትን ፡ አለቃ ፡ ይሽረው ፡ ዘንድ ፡ ይኸውም ፡ ሰይጣን ፡ ነው ፡ በሕይወታቸው ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ሞትን ፡ በመፍራት ፡ ለሰይጣን ፡ ባርነት ፡ ተገዝተው ፡ የነበሩትን ፡ ሁሉ ፡ ያሳርፋቸው ፡ ዘንድ ፡ ዕብ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፲፫ ‐፲፭

ስለዚህ ፡ ለአባቶቻችን ፡ ያነገራቸውን ፡ ተስፋ ፡ ለመፈጸም ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ መጥቶ ፡ በባሕርያችን ፡ ላይ ፡ አፍሎ ፡ ያስጨንቅ ፡ የነበረውን ፡ ዲያብሎስን ፡ በሞቱ ፡ ስላስወገደልን ፡ እንደነቅዕ ፡ እንደእስትንፋስ ፡ የማያቋርጥ ፡ ምስጋና ፡ ወደጌትነቱ ፡ እናቀርብ ፡ ዘንድ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ነቢዩ ፡ ዳዊት ፡ ቀዳማዊ ፡ ቃል ፡ ያለመቀላቀል ፤ ያለመለወጥ ፤ ያለመለየት ፡ ግዙፍ ፡ ውሱን ፡ ጸባብ ፡ የሆነውን ፡ የሥጋን ፡ ባሕርይ ፡ ተዋሕዶ ፡ ደኃራዊ ፡ ሥጋ ፡ መሆኑ ፡ ደኃራዊ ፡ ሥጋም ፡ እንዲሁ ፡ የቃልን ፡ ምላት ፤ ስፋት ፡ ርቀት ፡ ተዋሕዶ ፡ ቀዳማዊ ፡ ቃል ፡ መሆኑ ፡ (በተዋሕዶ ፡ ክርስቶስ ፡ መባሉ) ፡ አስቀድሞ ፡ በመንፈሰ ፡ ትንቢት ፡ ተገልጦለት ፡ የተናገረውን ፡ ጠቅሶ ፡ አርእስት ፡ ሁኖ ፡ በተመለከተው ፡ ንባብ ፡ ለዘለዓለሙ ፡ እስከ ልጅ ፡ ልጅ ፡ የማይገታ ፡ የምሥራችን ፡ ሲሰጠን ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ።

እኛ ፡ ለአባቶቻችን ፡ በሆነው ፡ ተስፋ የምሥራችን ፡ እንነግራችኋለን ። እግዚብሔር ፤ ኢየሱስን ፡ ባስነሣው ፡ ጊዜ ፡ ይህንን ፡ ለእኛ ፡ ለልጆቻቸው ፡ ፈጽሞታልና ።

በሁለተኛው ፡ መዝሙር ፡ "አንተ ፡ ልጄነህ ፡ እኔም ፡ ዛሬ ፡ ወለድኩህ ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ እንዳለ ፡ ከሙታን ፡ ለይቶ ፡ አስነሥቶታልና ፡ እንደገናም ፡ ወደ ጥፋት ፡ አይመለስምና ፤ ደግሞ ፡ እንዲሁ ፡ የዳዊትን ፡ የታመነችውን ፡ ጸጋ ፡ እሰጣችኋለሁ ፡ አለ ።

ስለዚህም ፡ በሌላው ፡ መዝሙር ፡ ደግሞ ፡ ወዳጅህን ፡ ጥፋትን ፡ (ሙስና ፡ መቃብርን) ያይ ፡ ዘንድ ፡ አትተወውም ፡ ይላል ።

ዳዊት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፈቃድ ፡ በዘመኑ ፡ ካገለገለ ፡ በኋላ ፡ አንቀላፋ ። ወደአባቶቹም ፡ ሔደ ፤ ጥፋትንም ፡ ሙስና ፡ መቃብርንም ፡ አየ ።

እግዚአብሔር ፡ ያስነሣው ፡ ይህ ግን ፡ ጥፋትን ፡ አላየም ። አሁንም ፡ እላንተ ፡ ወንድማማች ፡ ሰዎች ፤ በዚህ ፡ የኃጢአት ፡ ሥርየት ፡ እንደተነገረላችሁ ፡ በላንት ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ሆኖም ፡ በአካለ ፡ ሥጋ ፤ ወደመቃብር ፡ ወርዶ ፡ ሙስና ፡ መቃብርን ፡ አጥፍቶ ፡ በአካለ ፡ ነፍስም ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ወርዶ ፡ በሲኦልም ፡ ጨለማ ፡ ውስጥ ፡ ተግዘው ፡ የነበሩ ፡ ነፍሳትን ፡ ከእሥራታቸው ፡ ፈትቶ ፤ ለእኛም ፡ የጽድቅንና ፡ የሕይወትን ፡ መንገድ ፡ አቃንቶ ፡ የትንሣኤውን ፡ ብርሃን ፡ በመካከላችን ፡ ለዘረጋልን ፡ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከአብ ፡ ከመንፈስ ፤ ቅዱስ ፡ ጋር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ።

እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ያሰማኋችሁ ፡ ቃል ፡ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ዘር ፡ ሁሉ ፡ የፈጸመውን ፡ ታላቅ ፤ ቸርነት ፡ ስለሚያስረዳ ፡



ምንም ፡ የወረታው ፡ ብድር ፡ ከፋዮች ፡ ለመሆን ፡ ባንችል ፡ ከቀደመው ፡ ኃጢአት በደሙ ፡ ያነጻን ፡ ንጹሐን ፡ ክቡራን ፡ ሆነን ፡ ከኃጢአት ፡ ርቀን ፡ እንድንኖርለት ፡ መሆኑን ፡ እያሰባችሁና ፤ ሕጉን ፡ ትእዛዙን ፡ እየጠበቃችሁ ፡ ከባሕርያችንም ፡ ስሕተት ፡ ሊርቅ ፡ ባይችል ፡ በንስሓ ፡ እየታደሳችሁ ፡ በሞቱ ፡ በትንሣኤው ፡ ለአዘጋጀላችሁ ፡ ክብር ፡ እንድትበቁ ፡ አደራ ፡ እላችኋለሁ ።

የትንሣኤው ፡ በረከት ፡ በላያችሁ ፡ ይደር ።

---

ብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ (አሁን ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘመንግሥተ ፡ ኢትዮጵያ) ፡ በኢትዮጵያ ፡ አውራጃዎች ፡ የሚገኙትን ፡ አብያተ ፤ ክርስቲያናት ፡ በየጊዜው ፡ እየተዘዋወሩ ፡ እንደ መጐብኘታቸው ፡ መጠን ፡ የትግሬን ፡ አውራጃ ፡ ገዳማትና ፡ አድባራትን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትንም ፡ ሁሉ ፡

## በጐበኙ ፡ ጊዜ ፡ የፈጸሙት ፡ ገዳማዊ ፣

ብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ (አሁን ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ) ፡ የኢትዮጵያ ፡ እምነት ፡ መክፈቻ ፡ የሆነች ፡ ታቦተ ፡ ጽዮን ፡ የምትገኝበትን ፡ የአክሱምን ፡ ገዳም ፡ ለመሳለምና ፡ ሌሎችንም ፡ በትግሬ ፡ አውራጃ ፡ የሚገኙትን ፡ ዐበይት ፡ ገዳማት ፡ ለመጐብኘትና ፡ ችግራቸውን ፡ ለማቃለል ፡ ከበረከታቸውም ፡ ለመሳተፍ ፡ ስላሰቡ ፤ በኅዳር ፡ ፮ ቀን ፡ ፲፱፻፷፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ እንዲነሡ ፤ የጕዞው ፡ ጕዳይ ፡ ተቈርጦ ፡ ስለነበረ ፤ በዚሁ ፡ ቀን ፡ ከቀትር ፡ በኋላ ፡ በ፱ ሰዓት ፡ በአውቶሞቢል ፤ ተከታዮቻቸው ፡ በካሚዮን ፡ ተቀምጠው ፡ ጕዘው ፡ ቀጠለ ።

የተከተሏቸውም ፡ አበውና ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ሠራተኞች ።

፩ ሊቀ ፤ ሥልጣናት ፡ መልእክቱ ፡ (አሁን ፡ አቡነ ፡ ቴዎፍሎስ) ።
፪ መምህር ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ብርሃነ ፡ መስቀል ፡ (አሁን ፡ አቡነ ፡ ሉቃስ) ፤
፫ አባ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ መገኖ ፡ (ቀድሞ ፡ አዛዥ) ።
፬ አጋፋሪ ፡ በየነ ፡ አሊ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ዋና ፡ አጋፋሪ ።
፭ ሊቀ ፡ መዘምራን ፡ ተረፈ ፡ ወርቄ ፡ የማኅደረ ፡ ስብሓት ፡ ልደታ ፡ ደብር ፡ አለቃና ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የብፁዕነታቸው ፤ ልዩ ፡ ጸሐፊ ።
፮ ንቡረ ፡ እድ ፡ ገብረ ፡ ሚካኤል ፡ ዘአዲስ ፡ ዓለም ፡ (አሁን ፡ አቡነ ፡ ማቴዎስ) ።

ሌሎችም ፡ ሠራተኞችና ፡ ተላላኪዎች ፡ ነበሩ ።

## የጕዞው ፡ መግለጫ ።

ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ኅዳር ፡ ፮ ቀን ፡ ዐርብ ፤ በ፱ ሰዓት ፡ ተነሥተው ፡ ማታውኑ ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ከተማ ፤ ደርሰው ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ አደሩ ። በማግሥቱም ፡ ኅዳር ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ በማለዳ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገብተው ፡ ጥቂት ፡ ጸሎት ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ፪ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ሲሆን ፡ ወደደሴ ፡ ጕዞው ፡ ቀጠለ ።

www.ethiopianorthodox.org

ደሴ ፡ ከተማ ፡ ለመድረስ ፡ ጥቂት ፡ ሲቀር ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ መርዕድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ እስከ ፡ ክምቦልቻ ፡ አቅራቢያ ፡ በአውቶሞቢል ፡ መጥተው ፡ ብፁዕነታቸውን ፡ ተቀበሉዋቸው ።

ወዲያው ፡ አብረው ፡ ተጉዘው ፡ ፲፩ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ሲሆን ፣ ደሴ ፡ ከተማ ፡ ገቡ ፡ ወደ ፡ ከተማውም ፡ ሲደርሱ ፡ ካህናቱ ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖ ፡ ለብሰው ፡ የመንፈሳዊ ፣ ትምህርት ፡ ተማሪዎችና ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ በደንብ ፡ ተሰልፈው ፡ ይጠባበቁ ፡ ኖሮ ፣ ካህናቱና ፡ ተማሪዎቹ ፡ በዝማሬ ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ በማርሽ ፡ ድምፅ ፡ የደስታ ፡ አቀባበላቸውን ፡ ገለጹ ።

ወዲያው ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ አዳራሽ ፡ ስለብፁዕነታቸው ፡ የእንግድነት ፡ ክብር ፡ ከልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ የሻፓኝ ፡ ግብዣ ፡ ተደርጎ ፡ ከዚያው ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ በተሰናዳው ፡ ማረፊያ ፡ አደሩ ።

በማግሥቱ ፡ ኅዳር ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ እሑድ ፡ ከንጋቱ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ ሔደው ፡ በደሴ ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አስቀድሰው ፡ ከተመለሱ ፡ በኋላ ፣ ብፁዕነታቸው ፡ ከ፭ ፡ ሰዓት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፯ ፡ ሰዓት ፣ ከቀትርም ፡ በኋላ ፡ ከ፲ ሰዓት ፡ እስከ ፡ ምሽቱ ፡ ፪ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ድረስ ፣ በደሴ ፡ የሚገኙትን ፡ አድባራት ፡ ሊቃውንትና ፡ መምህራን ፡ ካህናትና ፡ ተማሪዎች ፡ እየተቀበሉ ፡ ጉዳያቸውን ፡ ሲያነጋግሯቸው ፣ ዋሉ ።

በዚሁም ፡ ቀን ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ችግር ፡ መሙያ ፡ ፩፻ ፣ ብር ፡ ለተቸገሩ ፡ ካህናት ፡ መርጃ ፣ ፫ሺህ ፡ ፪፻፹፯ ፡ ብር ፣ ለመምህራንና ፡ በቅኔ ፡ ትምህርት ፡ ወደፊት ፡ ለገፉት ፡ ተማሪዎች ፡ ጉርሻና ፡ ሽልማት ፡ ፯፻፵፰ ፡ ብር ፣ በትጋት ፡ ላገለገሉ ፣ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ሠራተኞች ፡ ጉርሻ ፡ ፪፻ ፡ ብር ፣ ስጦታ ፡ ተደረገ ።

ኅዳር ፡ ፴ ቀን ፡ ሰኞ ፡ በ፩ ሰዓት ፡ ጉዘው ፣ ወደትግሬ ፡ አመራ ፣ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ብፁዕነታቸውን ፣ ሞፋ ፡ እስከ ፡ ሚባለው ፡ ቀበሌ ፡ ሸኝተው ፡ ወደ ፡ ደሴ ፡ ተመለሱ ። በ፯ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ውጫሌ ፡ ወደ ፡ ሚባለው ፡ መንደር ፡ ደርሰው ፣ ምሳ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ጉዘው ፡ ቀጥሎ ፡ ፲፪ ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ወልድያ ፡ ከተማ ፡ ደረሱ ።

የወረዳው ፡ ገዥ ፡ ደጃዝማች ፡ አያሌው ፡ ብሩም ፡ በመልካም ፡ አቀባበል ፡ ተቀብለው ፡ በዚያው ፡ አዳር ፡ ሆነ ። አገረ ፡ ገዥውም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ አድርገው ፡ አመሹ ። ኅዳር ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ማክሰኞ ፡ ከጧቱ ፣ በ፲፪ ፡ ሰዓት ፡ ተነሥተው ፣ ፭ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ሲሆን ፡ ኮረም ፡ ደረሱ ።

በዋግ ፡ ሥዩም ፡ ወሰን ፡ ቤት ፡ ጥቂት ፡ ዕረፍት ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ኮረም ፡ በንግድና ፡ በእንዱስትሪ ፡ ሚኒስትር ፡ ትጋት ፡ በገር ፡ ልጆች ፡ አስተናባሪነት ፡ ከጥጥና ፡ ከጉጠር ፡ የሚሠሩትን ፡ ድንገትም ፡ ለሚያያቸው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሱፍና ፡ ፈትል ፡ የሚመስሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የልብስ ፡ ጥበባት ፡ የሚሠሩበትን ፡ ሰፊ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጐብኝተው ፡ ጉዘው ፡ ቀጠለ ። ከዚያም ፡ ቆቦ ፡ ሲደርሱ ፡ የማይጨው ፡ ወረዳ ፡ ገዥ ፡ ፊታውራሪ ፡ የማነ ፡ ሐሰን ፡ ብፁዕነታቸውን ፡ ለመቀበል ፡ መጥተው ፡ አብረው ፡ ሲጓዙ ፡ ፺ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ሲሆን ፡ ማይጨው ፡ ከተማ ፡ ደረሱ ።



የከተማው ፡ ካህናትና ፡ ወታደሮችም ፡ ተሰልፈው ፣ ተቀበሏቸው ። በዚሁም ፡ ቀን ፡ ብፁዕነታቸው ፡ የማይጨው ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ገዳምና ፡ የቅድስት ፡ ማርያምን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጐብኝተውና ፡ ተሣልመው ፡ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፣ ገዳም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ፈጽሞ ፡ ያረጀና ፡ ለመፍረስ ፡ የደረሰ ፡ ከመሆኑ ፡ ሌላ ፡ ቦታው ፡ ምቹ ፡ ስላልነበረ ፣ አገረ ፡ ገዥው ፡ ባመለከቱት ፡ መሠረት ፡ በተሻለ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ እንዲሠራ ፡ አዝዘው ፡ ለማሠሪያው ፡ ፲ሺህ ፡ ብር ፡ እንዲሰጥ ፡ አዘዙ ።

(ከታሪኩ ፣ ለማስታወስ) ፡ ይሠራ ፡ የተባለው ፡ ይህ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከዛሬ ፡ ሐምሳ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ጃንሆይ ፡ አፄ ፡ ምኒልክ ፡ ልማደኛውን ፡ የኢጣሊያን ፣ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ለመቋቋም ፡ ወደዐድዋ ፡ ሲጓዙ ፡ ወደ ፡ ዚሁ ፡ ቦታ ፡ ሲደርሱ ፡ በተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ስም ፡ አንዲት ፡ መቃኞ ፡ ተሠርታ ፡ ታቦቱ ፡ በዚያች ፡ ውስጥ ፡ ኑሯል ። ጠበልም ፡ ስለነበረው ፡ አፄ ፡ ምኒልክ ፡ የሚወዱት ፡ ፈረሳቸው ፡ እዚያ ፡ ሲደርሱ ፡ ታሞባቸው ፡ ኖሮ ፡ ከጠበሉ ፡ አጠጥተውት ፡ ማየ ፡ ፈውስ ፡ ሆኖት ፡ ወዲያው ፡ በመዳኑ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ጠላቴን ፡ ድል ፡ አድርጌ ፡ ብመጣ ፣ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠርቼ ፡ ለካህናቱ ፡ ርስት ፡ ጉልት ፡ ሰጥቼ ፡ ገዳም ፡ አደርገዋለሁ ፡ ብለው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብፅዓት ፡ አድርገው ፡ ሳለ ፣ ብፅዓታቸው ፡ ተፈጽሞላቸው ፡ ጠላታቸውን ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ ሲመለሱ ፡ ያሣነጹት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ የገደሙት ፡ ገዳም ፡ ነው ።

ብፁዕ ፡ አባታችንም ፡ ይህን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስጦታ ፡ ማድረግ ፡ ብቻ ፡ ሳይበቃቸው ፡ በወረዳው ፡ ለሚገኙት ፡ ካህናትና ፡ ተማሪዎች ፡ ብዙ ፡ ስጦታ ፡ አደረጉ ። ኅዳር ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ረቡዕ ፡ ከጧቱ ፡ በ፪ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ወደመቀሌ ፡ ጉዘው ፡ ቀጠለና ፡ ክቡር ፡ ራስ ፡ አበበ ፡ አረጋይ ፡ ከ፳ ፡ ሺህ ፡ ክንድ ፡ (፴ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡) የማያንስ ፡ መንገድ ፡ መጥተው ፡ ብፁዕነታቸውን ፡ ተቀበሉ ። ከዚያም ፡ አብረው ፡ ተጉዘው ፡ ፯ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ሲሆን ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ አውራጃ ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ መቀሌ ፡ ደረሱ ። የመቀሌም ፡ ከተማ ፡ እንኳን ፡ ደኅና ፡ መጡ ፡ በሚል ፡ ቅስት ፡ ተቀስታ ፡ በሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ አሸብርቃ ፡ በመታየቷ ፡ ላይ ፡ ካህናቱ ፡ በልብሰ ፡ ተክህኖ ፡ ተሸልመው ፡ ግሥ ፡ እያለዘቡ ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ የማርሽ ፡ ድምፅ ፡ እያሰሙ ፡ የመንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተማሪዎች ፡ መዝሙር ፡ እየዘመሩ ፡ የከተማው ፡ ሕዝብ ፡ በመላው ፡ ይባቤውን ፡ እያቀለጠ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ደረሱ ። ብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ ከተሰናዳላቸው ፡ መንበር ፡ ከተቀመጡና ፡ የወታደሮቹን ፡ የክብር ፡ ሰላምታ ፡ ከተቀበሉ ፡ በኋላ ፡ ክቡር ፡ ራስ ፡ አበበ ፡ አረጋይ ፡ ስለብፁዕነታቸው ፡ መምጣት ፡ የሚከተለውን ፡ ተናገሩ ። «ብፁዕ ፣ አባታችን ፡ ሆይ» ፡ በአውራጃው ፡ ሕዝብ ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ እንኳን ፡ ደኅና ፡ መጡ ፡ እያልኩ ፡ ደስታዬን ፡ እገልጻለሁ ፡ በመንፈስ ፡ ያልተለዩዋቸው ፡ ምእመናኖችዎም ፡ ዛሬ ፡ መጥተው ፣ በመካከላቸው ፡ በመገኘትዎና ፡ ቡራኬዎን ፡ ለመቀበል ፡ በመቻላቸው ፡ የሚሰማቸው ፡ ደስታ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ውዲቱ ፡ አገራችን ፡ በጠላት ፡ በተወረረች ፡ ጊዜ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችንን ፡ ተከትለው ፡ በስደት ፡ ያሳለፉትን ፡ የሥቃይና ፡ የመከራ ፡ ሰዓት ፡ በዛሬው ፡ ቀን ፡ ሳና ስታውሰው ፡ እናልፍም ። እንደዚሁም ፡ የብፁዕነትዎ ፡ ጸሎት ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ ድካም ፡ ጋር ፡ በመተባበሩ ፡ ነፃነት ፡ በሃይማኖት ፡ ሃይማኖት ፡ በነፃነት ፡ መሆኑ ፡ ይታ ወቅ ፡ ዘንድ ፡ የቤተ ፡ መንግሥትና ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ መሪዎች ፡ ያሳያችሁት ፡ ምሳሌ ነፃነትን ፡ እንዳፈራ ፡ የሚዘነጋው ፡ የለም ። ጠላት ፡ ሰላማዊ ፡ ትዳራችንን ፡ እንዳጠ ፋው ፡ መንፈሳዊውን ፡ አስተዳደራችንንም ፡ ለማቃወስ ፡ በተንኰል ፡ ያቀደው ፡ አሳብ ከቶ ፡ ሊከናወንለት ፡ አልቻለም ። ተቋርጦ ፡ የነበረው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ አስ ተዳደር ፡ በብፁዕነትዎ ፡ ትጋት ፡ በአዲሱ ፡ አቅድ ፡ በጽኑ ፡ መሠረት ፡ ሊቋቋም ፡ ቻለ ። የብፁዕነትዎ ፡ አውራጃዎችንና ፡ ቅዱሳት ፡ በታዎችን ፡ መጎብኘት ፡ ለተጀመ ረው ፡ እርምጃ ፡ መልካም ፡ ፍጻሜ ፡ ለመስጠት ፡ የሚረዳ ፡ መሆኑን ፡ እናምናለን ።

እግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ መንግሥታችንና ፡ ቤተ ፡ ክህነታችንን ፡ ይጠብቅልን ፡ ብለው ፡ ንግግራቸውን ፡ ጨረሱ ። ሊቃውንቱም ፡ ቅኔውን ፡ እንደ ፡ ማዕበል ፡ ያወ ርዱት ፡ ነበር ። ወዲያው ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ክፍል ፡ ወደተዘጋጀላ ቸው ፡ ማረፊያ ፡ ገብተው ፡ አዳር ፡ ሆነ ። ኅዳር ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ሐሙስ ፡ ከጧቱ ፡ ፬ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ብፁዕ ፡ ዕጨጌና ፡ ክቡር ፡ ራስ ፡ አበበ ፡ በአንድ ፡ አውቶሞቢል ፡ ሆነው ፡ መቀሌ ፡ የኪዳነ ፡ ምሕረትን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እጅ ፡ ነሥተው ፡ ጸሎት ፡ ከደረጉ ፡ በኋላ ፡ ሁለት ፡ ተማሪዎች ፡ ጠያቂና ፡ መላሽ ፡ ሆነው ፡ ፳ቱን ፡ አዕማደ ፡ ምሥጢር በቀለጠፈ ፡ አማርኛ ፡ በማሰማታቸው ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ተደስተው ፡ በትምህርት ፡ ቅድ ሚያ ፡ ላላቸው ፡ ለመቶ ፡ ተማሪዎች ፡ ሙሉ ፡ ሙሉ ፡ ልብስ ፤ (የትምህርት ፡ ቤት ፡ ልብስ) ፡ ሽልማት ፡ ታዘዘላቸው ።

ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደተመለሱ ፡ ወደንቡረ ፡ እድ ፡ ተስፋ ሚካኤል ፡ ቤት ፡ ገብተው ፡ ፯ ፡ ሰዓት ፡ እስኪሆን ፡ የካህናት ፡ ባለጉዳዮችን ፡ ሲያነጋ ግሩ ፡ ቆይተው ፡ ፯ ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ክቡር ፡ ራስ ፡ አበበ ፡ ስለብፁዕነታቸው ፡ እንግ ድነት ፡ ታላቅ ፡ ግብዣ ፡ አድርገው ፡ ነበርና ፡ ወደዚሁ ፡ ግብዣ ፡ ሔደው ፡ ለሊቃ ውንትና ፡ ለካህናት ፡ ለመኳንንትና ፡ ለጦር ፡ አለቆች ፡ ለመንግሥትም ፡ ሠራተኞች ሙሉ ፡ ግብር ፡ ተደረገ ።

ኅዳር ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ዐርብ ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ የመቀሌ ፡ ማርያምን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ተሳልመው ፤ ለከተማው ፡ ነዳያንና ፡ ችግረኞች ፡ ፳፻ ፡ ብር ፡ ሰጡ ። ከዚያም ፡ ተመ ልሰው ፡ እስከ ፡ ፯ ሰዓት ፡ የካህናት ፡ ባለጉዳዮችን ፡ ሲቀበሉ ፡ ቆይተው ፡ በዚሁ ፡ አካባቢ ፡ በጠላት ፡ ለተቃጠሉና ፡ ለፈረሱ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ማሠሪያና ፡ ማደሻ ለአልባሳትም ፡ የሚሆን ፡ ፲፩ሺ፪፻ ፡ ብር ፤ በየገዳሙና ፡ በየአድባራቱ ፡ ለሚገኙ ካህናትና ፡ ችግረኞች ፡ ፯ሺ ፡ ፱፻፵፪ ፡ ብር ፡ ለተማሪዎች ፡ ጉርሻ ፡ ፶ ፡ ብር ፤ በቅን ነትና ፡ በትጋት ፡ ላገለገሉ ፡ ለቤተ ፡ ክህነት ፡ ሠራተኞች ፡ ጉርሻ ፡ ፳፻፰ ፡ ብር ስጦታ ፡ ተደረገ ።



ከምሳም ፡ በኋላ ፡ ፱ ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ወደአዲግራት ፡ ጕዞው ፡ ቀጠሎ ፡ ጥቂት እንደተጓዙ ፡ ውቅሮ ፡ ወደሚባለው ፡ ስለደረሱ ፤ የአጽቢ ፡ ሥላሴ ፡ ገዳም ፡ የውቅሮ ፡ ቂርቆስ ፡ ካህናትና ፡ ሕዝብ ፡ ወታደሮችም ፡ በሰልፍ ፡ ተቀበሏቸው ። አዲግራት ፡ ለመድረስ ፡ አርባ ፡ ሺህ ፡ ክንድ ፡ (፳ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ) የሚሆን ፡ ሲቀር ፡ የአዲግ ራት ፡ ወረዳ ፡ ገዥ ፡ ደጃዝማች ፡ ኃይሉ ፡ ማርያም ፡ ከተከታዮቻቸው ፡ ጋር ፡ በት ልቅ ፡ አውቶቡስ ፡ ሆነው ፡ ብፁዕነታቸውን ፡ ለመቀበል ፡ መጥተው ፡ አብረው ፡ ጕዞው ፡ ቀጠለና ፡ ከምሽቱ ፡ ፩ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ሲሆን ፡ አዲግራት ፡ ከተማ ፡ ደረሱ ።

ከተማዪቱም ፡ በቅስትና ፡ በሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ተሸልማ ፡ ካህናቱና ፡ ሕዝቡ ፡ የጦር ሠራዊቱም ፡ በአማረ ፡ ሰልፍ ፡ ሆነው ፡ ተቀበሏቸውና ፡ በተዘጋጀው ፡ ማረፊያ ፡ አዳር ፡ ሆነ ። ኅዳር ፡ ፲፬ ፡ ቀን ፡ ቅዳሜ ፡ በአዲግራት ፡ ከተማ ፡ የሚገኙ ፡ የትምህርት ትና ፡ የሥነ ፡ ጥበብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ባዘጋጀው ፡ ትምህርት ፡ ቤትና ፡ በመንፈሳዊ ፡ ትም ህርት ፡ ቤት ፡ የሚማሩት ፡ ወጣቶች ፡ በማረ ፡ ሰልፍ ፡ መጥተው ፡ ጣዕመ ፡ ዝማሬያ ቸውን ፡ ስላሰሙ ፤ ለሁለቱም ፡ ክፍሎች ፤ ከብፁዕነታቸው ፡ ፩፻፲ ፡ ብር ጕርሻ ፡ እን ዲሰጣቸው ፡ ታዘዘ ።

እንዲሁም ፡ ለካህናትና ፡ ለችግረኞች ፡ እርዳታ ፡ ተደረገና ፡ ፫ ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ጕዞው ፡ ወደ ፡ አድዋ ፡ አመራ ። ፭ ፡ ሰዓትም ፡ ሲሆን ፡ ወደደብረ ፡ ዳሞ ፡ አፋዛዥ ፡ (አንጻር) ፡ ሲደርሱ ፡ ወደደብረ ፡ ዳሞ ፡ በመኪና ፡ ለመጓዝ ፡ መንገዱ ፡ ባለመፍቀዱ የደብረ ፡ ዳሞ ፡ ገዳም ፡ አስተዳዳሪ ፡ መምህር ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ በቅሎዎችን ፡ አሰና ድተው ፡ በጎዳናው ፡ አጠገብ ፡ ሲጠባበቁ ፡ ቆይተው ፡ ኖሮ ፡ በግምት ፡ ፴ ፡ ኪሎ ፤ ሜትር ፡ ያህል ፡ በበቅሎ ፡ ተጕዘው ፡ ወ?ተራራው ፡ እግር ፡ ደረሱ ። በዚያም ፡ ከአዲግ ራት ፡ የታዘዙ ፡ ወታደሮች ፡ በሰልፍ ፡ ተቀበሏቸው ። ወደተራራውም ፡ የሚወጣው ጕንጕን ፡ በሆነ ፡ በጠፍር ፡ ገመድ ፡ ተንጠልጥሎ ፡ ስለሆነ ፡ ለዚሁ ፡ አስቸጋሪ ፡ ጕዞ መሰናዳት ፡ ተጀመረ ። በገመዱ ፡ የሚወጣው ፡ የገደሉ ፡ ርዝመት ፡ ፴ ፡ ክንድ ፡ ይሆ ናል ። ገመዱ ፡ ለእጅ ፡ እንደሚሞላ ፡ ሆኖ ፡ በጠፍራሙ ፡ ተጠላልፎ ፡ ተሠርቷል ።

የገመዱ ፡ ስም ፡ እንደ ፡ ሀገሩ ፡ ወግ ፡ ዘንዶ ፡ ይባላል ።ምክንያቱም ፡ «አቡነ ፡ አረጋዊ ፡ ወደዚሁ ፡ ተራራ ሲወጡ ፡ በዘንዶው ፡ ጭራ ፡ ተንጠልጥለው ፡ ወጥተው ፡ ነበርና ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነው» ፡ ይባላል ።ገመዱ ፡ (ዘንዶው) ፡ ሁለት ፡ ክንድ ፡ ያህል በገደሉ ፡ አፋፍ ፡ በሚገኘው ፡ መሬት ፡ ወደውስጥ ፡ በተተከለ ፡ ዕንጨት ፡ ላይ ፡ ተጠ ልፎ ፡ ጫፉ ፡ ወደተራራው ፡ ሥር ፡ ይወርዳል ። አወጣጡን ፡ የለመዱ ፡ የሀገሩ ፡ ሰዎች ሌላ ፡ መረጃ ፡ ሳይደረግላቸው ፡ ወራጁን ፡ ገመድ ፡ ብቻ ፡ በእጃቸው ፡ ይዘው ፡ ለመ ውጣት ፡ ይችላሉ ። አወጣጡን ፡ ላለመደው ፡ ግን ፡ ሌላ ፡ ጠፍር ፡ ደግሞ ፡ በሰው ፡ ኃይል ፡ ወደአፋፍ ፡ የሚሳብ ፡ በወገቡ ፡ ላይ ፡ እንዲታሠር ፡ አስፈላጊ ፡ ይሆናል ።

በዚሁም ፡ ገደል ፡ ላይ ፡ ስላለው ፡ ጕዞ ፡ ታላላቆች ፡ ሰዎች ፡ ሲወጡ ፡ አራት ፡ እርድፍ ፡ በገመድ ፡ የተያዘ ፡ መጋረጃ ይደረግና ፡ እንደመንገደኛው ፡ ጕዞ ፡ መጠን ፡ ከላይ ፡ ያሉት ፡ ሲስቡ ፡ ከታች ፡ ያሉት ፡ እየለቀቁ የአክብሮት ፡ ሥራቸውን ፡ ይፈጽ ማሉና ፡ ብፁዕ ፡ እጨጌ ፡ በሚወጡበት ፡ ጊዜ ፡ እንዲሁ ፡ ተደረገ ።

www.ethiopianorthodox.org

ብፁዕነታቸውና ፡ ተከታዮቻቸው ፡ እንደሌሎቹ ፡ መንገደኞች ፡ ሁሉ ፡ በገደሉ
አወጣጥ ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡ ሳያገኛቸው ፡ በመውጣታቸው ፡ ባላገሮቹ ፡ እንደተገረመ
በት ፡ ገለጡ ። ከነዋሪዎቹም ፡ እንደሰማነውና ፡ በገድላቸውም ፡ እንደሚገኘው ፡ አቡነ
ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በደብረ ፡ ዳሞ ፡ ገዳም ፡ ፲፪ ፡ ዓመት ፡ በእርድና ፡ ኑረው ፡ በዚሁ
ገመድ ፡ ተንጠልጥለው ፡ ሊወርዱ ፡ ሲጀምሩ ፤ ሰይጣን ፡ ለመፈታተን ፡ ገመዱን ፡ ቢበ
ጥስባቸው ፡ በተአምራት ፡ ክንፈ ፡ ጸጋ ፡ አውጥተው ፤ ከተራራው ፡ ሥር ፡ ፪ ፡ ሺህ
ክንድ ፡ ያህል ፡ ርቀው ፡ ዐርፈዋል ፡ ይባላል ።

በዚሁም ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ በጻድቁ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ስም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን
ታንጾበት ፡ ይታያል ። ገደሉንም ፡ ከወጡ ፡ በኋላ ፡ ጥቂት ፡ ዕረፍት ፡ ተደረገና ፡ ወደ
ገዳሙ ፡ ለመድረስ ፡ የእግር ፡ ጕዞው ፡ ቀጠለ ። አቀበቱን ፡ ጨርሰው ፡ ወደ ፡ ደልላዳው
ቦታ ፡ ሲደርሱ ፡ አቡነ ፡ አረጋዊ ፡ መስቀላቸውን ፡ ያሳረፉበት ፡ ነው ፡ የተባለ ፡ ደን
ጊያ ፡ በላዩ ፡ ትእምርተ ፡ መስቀል ፡ እንደተሣለበት ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ።

ወዲያው ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ እድሞ ፡ ጥግ ፡ ሲደርሱ
ካህናቱ ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖ ፡ ለብሰው ፡ ተበቀሏቸው ። ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን
ተሳልመው ፡ የባላገሮቹን ፡ ቤተ ፡ ማኅበር ፡ ከጐበኙ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ተሰናዳላቸው
ማረፊያ ፡ ገብተው ፡ አዳር ፡ ሆነ ።

ኅዳር ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ እሑድ ፡ ከሌሊቱ ፡ ፲ ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ለማስቀደስ ፡ ወደ
ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሔደው ፡ ጸሎተ ፡ ቅዳሴው ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ የመናንያኑን
ቤተ ፡ ማኅበር ፡ ጐበኙ ። የቤተ ፡ ማኅበሩም ፡ አስተዳደርና ፡ ድርጅት ፡ በሚገባ ፡ የተ
ከናወነ ፡ በመሆኑ ፡ ኅብረታዊ ፡ ኑሮዋቸው ፡ እጅግ ፡ የሚያስደስትና ፡ የሚያስቀናም
ነበር ።

ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ በስተ ፡ ምሥራቅ ፡ በኩል ፡ አቡነ ፡ አረጋዊ ፡ የተሠወሩበት
ነው ፡ የተባለ ፡ ምሥዋር ፡ የሚባል ፡ መጠነኛ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አለ ። በመንበሩም
አጠገብ ፡ የተሠወሩበት ፡ ዋሻ ፡ ይታያል ። በዚህ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ በበዓል
ብቻ ፡ ሲቀደስ ፡ ለዘወትሩ ፡ ጸሎተ ፡ ማዕጠንት ፡ ይደረግበታል ። ከነዋሪዎቹ ፡ እንደ
ሚሰማው ፡ ዋሻው ፡ በጣም ፡ ሩቅ ፡ ከሔደ ፡ በኋላ ፡ ወደውጪ ፡ የሚያስወጣ ፡ ሌላ
በር ፡ አለው ፡ ይባላል ። በዚሁ ፡ ቤተ ፡ ክስቲያንም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ሌላ ፡ የታነጸ
ዋሻ ፡ ኖሮ ፡ በዚሁ ፡ አስኬማ ፡ የትቀበሉ ፡ መነኰሳት ፡ እንደሚቀበሩበት ፡ አስረዱ ።
በስተምዕራብ ፡ በኩል ፡ በገደሉ ፡ አፋፍ ፡ እንደቅርጽ ፡ የእጅ ፡ ሕንጻ ፡ በሆኑት ፡ ጥጋ
ጥጎች ፡ የብዙ ፡ ቅዱሳን ፡ ዐፅም ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ አሳዩ ። በስተምሥራቅም ፡ በኩል ፡ አቡነ
ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የጸለዩበትናን ፡ የሰገዱበትን ፡ ከመሬት ፡ ጥቂት ፡ ከፍ ፡ ብሎ
የሚታየውን ፡ የታነጸ ፡ ዋሻ ፡ አሳዩ ።

በውስጡም ፡ ስቍረት ፡ ያላቸው ፡ ሁለት ፡ ደንጊያዎች ፡ እንደመታሰቢያ ፡ ሆነው
ይታያሉ ። በምዕራብም ፡ በኩል ፡ የጽሕፈት ፡ ተግባራቸውን ፡ የሚያከናውኑበት
ነው ፡ የተባለ ፡ በደንጊያ ፡ ላይ ፡ ለቀይና ፡ ለጥቍር ፡ ቀለም ፡ መያዥ ፡ በሁለት
ክፍል ፡ የተፈለፈለ ፡ ሕንጻ ፡ አሳዩ ። በዚሁ ፡ ቀን ፡ በነጋታው ፡ ጾመ ፡ ስብከት ፡ የሚ



ገባበት ፡ ቀን ፡ ስለሆነ ፡ የቀበላውን ፡ በዓል ፡ እንዲያከብሩ ፡ ለመነኰሳቱና ፡ በተራ
ራው ፡ ሥር ፡ ለሚጠባበቁት ፡ ወታደሮች ፡ የሰንጋ ፡ መግዣ ፡ ፩፻፶ ፡ ብር ፤ ለገዳሙ
መርጃ ፡ ፩ ሺህ ፡ ብር ፡ ለካህናቱና ፡ ለገዳሙ ፡ ችግረኞች ፡ ፩፻፺፬ ፡ ብር ፡ ስጦታ ፡
ተደረገ ።

የደብረ ፡ ዳሞ ፡ ተራራ ፡ ከአንድ ፡ ጋሻ ፡ መሬት ፡ አያንስም ፤ አየሩም ፡ መካከ
ለኛ ፡ ነው ። በተራራው ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ኩሬ ፡ ይገኝበታል ። ለነዋሪዎች ፡ የውኃ ፡
ችግር ፡ የለባቸውም ፤ የኩሬው ፡ ውኃ ፡ እንደቀጸላ ፡ በለምለም ፡ ቅጠል ፡ የተሸፈነ ፡
ሆኖ ፡ ልምላሜውን ፡ ሲገልጡት ፡ የውኃው ፡ ጽርየት ፡ (ጥራት) ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ።
የደብረ ፡ ዳሞ ፡ ገዳም ፡ መጠሪያ ፡ ስሙ ፡ ደብረ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ይባላል ። ምክንያቱም
ቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ ራስ ፡ ወጥቶ ፡ "ያድክዋ ፡ ወርኢኩ ፡ ሥነ ፡ ሕንጼሃ ፡
እያለ ፡ በሃሌታ ፡ ዘምሮበት ፡ ስለነበረ" ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አስረድተዋል ።

የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ አክሱም ፡ ጽዮን ፡ ሦስት ፡ መቅደስ ፤ ያለው
ሆኖ ፡ ጣሪያና ፡ ግድግዳው ፡ ምንም ፡ ስንኳ ፡ የዕንጨት ፡ አዕማዶች ፡ ቢኖሩት ፡ በደ
ንጊያ ፡ ሕንጻ ፡ የተሠራ ፡ ነው ። የመጀመሪያው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተሠራው ፡
በዐፄ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ሆኖ ፡ ይህ ፡ አሁን ፡ ያለው ፡ ሕንጻ ፡
በዐፄ ፡ ፋሲል ፡ የተሠራ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ መነኰሳቱ ፡ ገልጸዋል ።

የገዳሙ ፡ ማኅበራዊ ፡ አስተዳደር ፡ ከሁለት ፡ ላይ ፡ የተከፈለ ፡ ነው ። አንደኛው
ክፍል ፡ የመናንያን ፤ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ የአገሩ ፡ ነዋሪዎች ፡ (ባላገሮች) ፡ ሆኖ ፡
ከገዳሙ ፡ የሚገኘውን ፡ ጠቅላላ ፡ አበል ፡ (ሀብት ፡ ) ሁለቱን ፡ እጅ ፡ ድርሻ ፡ ባላገ
ሮቹ ፡ ሲወስወዱ ፤ ሦስተኛውን ፡ ድርሻ ፡ (እጅ) ፡ መናንያኑ ፡ ይወስዳሉ ። ሌሎች ፡ እን
ደሚሉት ፡ ደግሞ ፡ አበሉ ፡ ከሦስት ፡ ተከፍሎ ፡ አንዱን ፡ ድርሻ ፡ መናንያኑ ፡ ሁለ
ተኛውን ፡ ድርሻ ፡ ባላገሮቹ ፡ ሦስተኛውን ፡ ድርሻ ፡ የገዳሙ ፡ መምህር ፡ እንዲወስዱ
ተመድቦ ፡ ሳለ ፤ የገዳሙ ፡ መምህር ፡ ድርሻቸውን ፡ ወደባላገሩ ፡ በመደረባቸው ፡ የባ
ላገሮቹ ፡ ድርሻ ፡ ሁለት ፡ ክፍል ፡ (እጅ) ፡ ሆነ ፡ ብለው ፡ ይተርካሉ ። ይኸውም ፡ ደንብ
ሆኖ ፡ የተሰጣቸው ፡ በዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ነው ፡ ይባላል ። በዚሁ
ቀን ፡ የአስኬማ ፡ ማዕርግ ፡ የሚሰጡትን ፡ ታላቅ ፡ ሽማግሌ ፡ ብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ ወደ ፡
መኖሪያቸው ፡ (በዓታቸው ፡) ፡ ሔደው ፡ አነጋግረዋቸዋል ።

ኅዳር ፡ ፲፮ ፡ ሰኞ ፡ በ፪ ፡ ሰዓት ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ከተከታዮቻቸው ፡ ጋር ፡ ወደ ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሔደው ፡ ከተሳለሙ ፡ በኋላ ፡ መነኰሳቱ ፡ አቡነ ፡ አረጋዊ ፡ ለአጽንዖተ ፡
ገድል ፡ ያደርጉት ፡ የነበረውን ፡ የደንጊያ ፡ ቆብና ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ይለብ
ሱት ፡ የነበረውን ፡ ከቆዳ ፡ የተሠራ ፡ የለፋ ፡ ዐጽፍ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ አምጥተው
አሳዩ ። እንደገዳሙ ፡ ሥርዓትና ፡ ወግ ፡ በመጀመሪያ ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ከዚያም ፡ የተከተ
ሏቸው ፡ አበው ፡ ቆቡን ፡ በራሳቸው ፡ እያደረጉ ፡ ዐጽፉንም ፡ እየለበሱ ፡ አዩት ። እንዲ
ሁም ፡ የአቡነ ፡ አረጋዊ ፡ ነው ፡ የተባለ ፡ ቅርጹ ፡ የቀድሞ ፡ አሠራር ፡ የሆነ ፡ በጫፉ
ትእምርተ ፡ መስቀል ፡ ያለበት ፡ የብረት ፡ ዘንግ ፡ ቀርበ ፡ ታየ ።

www.ethiopianorthodox.org

በዐጽፉም ፡ ላይ ፡ ካንድ ፡ ወገን ፡ በኮፕት ፡ ከሌላው ፡ በኩል ፡ ደግሞ በአረቢኛ ፡ ተጽፎበታል ። ወዲያው ፡ ታላላቆቹን ፡ መጻሕፍት ፡ ፩ኛ ፡ በብራና የተጻፈ ፡ አንድ ፡ የአቡነ ፡ አረጋዊና ፡ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ገድል ባንድ ፡ ጥራዝ ፡ ሆኖ ፡ ባንድ ፡ ገጽ ፡ አራት ፡ ዓምድና ፡ ፳፫ ፡ መሥመር ሲሆን ፤ ብዛቱ ፡ ገድለ ፡ አረጋዊ ፡ ፺፰ ፡ ቅጠል ፤ የገድለ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፹፫ ፡ ቅጠል ፡ የሆነ ፡ በዳሩ ፡ ላይ ፡ የተጻፈበት ፡ ዘመን ፡ በያዕቆብ ፡ ዘመነ መንግሥት ፡ በጴጥሮስ ፡ ጵጵሰና ፡ በ፩ሺ፬፻፺፩ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ መሆኑን ፡ የሚ ገልጽ ፤ ፪ኛ ፡ አንድ ፡ በብራና ፡ የተጻፈ ፡ ሐዊ ፡ መጽሐፍ ፡ ዓምዱ ፡ ፫ ፤ መሥ መሩ ፡ ፴፱ ፤ ብዛቱ ፡ ፫፻፲፱ ፡ ቅጠል ፡ ዘሩ ፡ የቀና ፡ ሆኖ ፡ በ፲ሺ፬፻፳ ፡ ዓመተ ዓለም ፡ ከዓረብ ፡ ወደግዕዝ ፡ ተተረጐመ ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ የሚገኝበት ፫ኛ ፡ አንድ ፡ በብራና ፡ የተጻፈ ፡ ገድለ ፡ ሰማዕታት ፡ ጽሕፈቱ ፡ በጣም ፡ አስ ደናቂ ፡ የሆነ ፡ ወርዱ ፡ ቁመቱ ፡ ፶ ፡ ሣንቲ ፡ ሜትር ፡ መሥመሩ ፡ ፵፩ ፡ ብዛቱ ፬፻፵ ፡ ቅጠል ፡ ሆኖ ፡ በአጼ ፡ ገብረ መስቀል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ከዓረብ ወደግዕዝ ፡ መተርጐሙን ፡ የሚያመለክት ፡ ጽሑፍ ፡ የሚገኝበት ። ፬ኛ ፡ ከዳሩ ላይ ፡ በቀይና ፡ በብጫ ፡ ቀለም ፡ ሐረግ ፡ የተሣለበት ፡ ፬ ፡ ዓምድ ፡ ፳ ፡ መሥ መር ፡ ፭፻፸ ፡ ቅጠል ፡ ብዛት ፡ ያለው ፡ ቁመቱ ፡ ፺ ፡ ወርዱ ፡ ፴ ፡ ሣንቲ ሜትር ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ በብራና ፡ የተጻፈ ፡ ገድለ ፡ ሐዋርያት ፡ አቅርበው አሳይተዋል ። ለጊዜው ፡ ጕዘው ፡ የሚያስቸኵል ፡ ነበርና ፡ ሌሎቹን ፡ ብዙዎቹን መጻሕፍት ፡ ለመመልከት ፡ ሳይቻል ፡ ጕዘው ፡ ቀጠለ ።

ብፁዕነታቸውና ፡ ተከታዮቻቸው ፡ አስቀድሞ ፡ በወጡበት ፡ አኳኋን ፡ ወደ ተራራው ፡ ሥር ፡ በወረዱ ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡ ሲጠባበቁ ፡ የነበሩት ፡ ወታደሮች ፡ በሰ ልፍ ፡ ተቀበሏቸው ። በደብረ ፡ ዳሞ ፡ ገዳም ፡ ሴት ፡ አትወጣምና ፡ እንደአጋጣሚ ዕለቱ ፡ የኪዳነ ፡ ምሕረት ፡ የወር በዓል ፡ ስለሆነ፡ ብፁዕ፡ አባታችን፡ በተራራው፡ ሥር ወደ፡ምትገኘው ፡ ሴት ፡ ደብር፡ ወደምትባለው ፡ የኪዳነ ፡ ምሕረት ፡ ገዳም ፡ ገብተው ጸሎት ፡ ከደረሱ ፡ በኋላ ፤ ለገዳሙና ለመነኰሳይያቱ ፡ መረጃ ፡ ብዙ ፡ የገንዘብ ችሮታ ፡ አደረጉላቸው ።

በተራራውም ፡ ሥር ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ወራጅ ፡ ወንዝ ፡ ስላለ ፤ ባላገሮቹ « ቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ የአቡነ ፡ አረጋዊን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ በዚህ ፡ ወንዝ ፡ ላይ ዓሣ ፡ ሲያድኑ ፡ አግኝቷቸው ፡«ዳኅንኑ ፡ ዝስኩ ፡ አረጋዊ ፡ አቡክሙ» ) ብሎ በዜማ ፡ የዘመረበት ፡ ቦታ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ይተርካሉ ።

ማኅበሮቹም ፡ ብፁዕነታቸውን ፡ እስከ ፡ መኪናው ፡ መንገድ ፤ ድረስ ፡ ሸኝ ተው ፡ ተሰናብተው ፡ ተመለሱ ። ፫ ሰዓት ፡ ሲሆንም ፡ ብፁዕነታቸውና ፡ ተከታዮቻ ቸው ፡ በመኪና ፡ ሆነው ፡ ጕዘው ፡ ቀጠለና ፡ ጥቂት ፡ እንደተጓዙ ፡ እንኪጬው ወደ ፡ ምትባል ፡ ትንሽ ፡ ከተማ ፡ ደረሱ ። ብፁዕነታቸውንም ፡ ለመቀበል ፡ የከተማው ሕዝብ ፡ ተሰልፎ ፡ ከተማዋም ፡ በቅስትና ፡ በሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ አጊጣ ፡ ነበር ፡



ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ስለተደረገላቸው ፡ አቀባበል ፡ ከመኪና ፡ ወርደው ፡ ምስጋና ፡ ከሰጡ ፤ በኋላ ፡ ጕዘው ፡ ቀጠለ ።

የዐድዋ ፡ ወረዳ ፡ ገዥ ፡ ብላቴ ፡ ዳዊት ፡ ዕቁበ ፡ እግዚእ ፡ ዐድዋ ፡ ለመ ድረስ ፡ ፳ ፡ ሺ ፡ ክንድ ፡ (፵ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡) ያህል ፡ ጕዞ ፡ ሲቀር ፡ ብፁዕነታቸውን ለመቀበል ፡ መጥተው ፡ ስለነበረ ፤ አብረው ፡ ጕዘው ፡ ቀጠለና ፡ ፳ ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ዐድዋ ፡ ከተማ ፡ ደረሱ። በዚሁም ፡ ጊዜ ፡ ካህናቱ ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖ ፡ ለብሰው ፡ ሕዝቡ የጦር ፡ ሠራዊቱና ፡ የንግሥተ ፡ ሳባ ፤ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተማሪዎች ፡ በሰልፍ ፡ ሆነው ተቀበሏቸው ። ወዲያው ፡ ካህናቱ ፡ የሚከተለውን ፡ ግሥ ፡ ገሠው ፡ አለዘቡ ። አቅዲሙ ነገረ ፤ ውሂበ ፡ ሥላሴ ፡ (ራስ ፡ አበበን ፡ ማለታቸው ፡ ነው ፡ )ከመ ፡ ይመጽእ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ዘይዜንዋ ፡ ለጽዮን ፡ ቃለ ፡ ትፍሥሕት ። ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ በአፈ ፡ ዳዊት ፡ (የወረዳውን ፡ ገዥ ፡ ብላታ ፡ ዳዊትን፡ሲያዩ፡ ነው) ፤ቡሩክ፡ ዘይመጽእ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ፡ በስመ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ይርዳእ ፡ ዘተኀጕለ ፡ ያስተጋብእ ፡ ዝርዋነ ፡ መጽአ ፡ ኀቤነ ። በዚህም ፡ ካሸበሸቡ ፡ በኋላ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሊቅ ፡ (ዲስኩር ፡) ስብከትና ፡ ቅኔውን ፡ ሲያንጐደጕደው ፡ ዕፁብ ፡ የሚያሰኝ ፡ ስሜት ፡ ከሕሊና ፡ ሲፈልቅ ፡ ይታሰብ ፡ ነበር ።

በዚሁም ፡ ቀን ፡ የዐድዋ ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ ሠራተኞች ፡ ስለብፁዕነታቸው ፡ እንግድነት ፡ መልካም ፡ መሰናዶ ፡ አድርገው ፡ ኖሮ ፡ መጀመሪያ ፡ የምሳ ፡ ቀጥሎ ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ ተደረገ ። ኅዳር ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ማክሰኞ ፡ ከጧቱ ፡ በ፪ ፡ ሰዓት ፡ ብፁዕነታቸው ፡ የዐድዋ ፡ ሥላሴንና ፡ የመድኃኔ ፡ ዓለምን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተሳ ልመው ፡ ጸሎት ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፤ የንግሥተ ፡ ሳባ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱን ፡ ብፁዕነታቸው ፡ እንዲጐበኙለት ፡ ለምኖ ፡ ነበርና ፡ ፫ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ሔደው ፡ የትምህርት ፡ ቤቱን ፡ ክፍሎች ፡ በዝርዝር ፡ ጐበኙ ። ተማሪዎቹም ፡ የእንግሊዘኛ ፡ መዝሙር ፡ በቀለጠፈ ፡ ዜማ ፡ አሰሙ ።

የተማሪዎቹም ፡ ብዛት ፡ ከ፫፻፶ ፡ ይበልጥ ፡ ነበር ። ለነዚሁ ፡ ተማሪዎችና ፡ ለመንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተማሪዎችም ፡ ፱፻፶ ፡ ብር ፡ ጕርሻ ፡ ተሰጠ ። ከዚ ያም ፡ መልስ ፡ ሆኖ ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን፡ ወደማረፊያቸው ፡ እንደደረሱ ፡ እስከ፡ ፯ ሰዓት፡ ድረስ ፡ በአውራጃው ፡ የሚገኙትን ፡ ካህናት ፡ ስለችግራቸው ፡ እያነጋገሩ ፡ ለአብ ያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ችግርና ፡ ጉድለት ፡ ማቃለያ ፡ ፲፪ሺ፮፻፹፭ ፡ ብር ፤ በየገዳ ማቱና ፡ በየአድባራቱ ፡ ላሉ ፡ ካህናትና ፡ ችግረኞች ፡ ፲፯ሺ፻፺ ፡ ብር ፤ በሥራ ፡ ላስደሰቱ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ሠራተኞች ፡ ፩ሺ፩፻፳ ፡ ብር ፡ ስጦታ ፡ ተደረገ ። ከምሳም ፡ በኋላ ፡ ፱፡ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ሲሆን ፡ ወደአክሱም ፡ ጕዘው ፡ ቀጠለና ፡ ዐሥር ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ወደአክሱም ፡ ከተማ ፡ ደረሱ ።

በዚሁም ፡ ጊዜ ፡ ከተማዋ ፡ በባንዲራ ፡ ተሸልማ ፡ ካህናቱ ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖ ፡ ለብሰውና ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ክበብ ፡ ሆነው ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ በሰልፍ ፡ ሆነው ፡ የከተማው ፡ ሕዝብ ፡ እስላሙ ፡ ካማራው ፡ ሳይለይ ፡ ተባብረው ፡ በመ ልካም ፡ አቀባበል ከተቀበሏቸው ፡ በኋላ ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ቅጽር ፡ እንደገቡ ፡ አቅጣጫው ፡ ወደቤተ፡ክርስቲያኑ ፡ የሆነ ፡ ማረፊያ ፡ ተሰናድቶ ፡ ነበርና ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ በተሰናዳላቸው ፡ መንበር ፡ ብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ ሲቀመጡ ፡ ካህናቱ ፡ ግሡን ፡ ቅኔውንና ፡ ስብከቱን ፡ ያጐርፉት ፡ ጀመሩ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ በሁለቱ ፡ የደወል ፡ ቤቶች ፡ መካከል ፡ በሚገኘው ፡ ዓውደ ፡ ጽዮን ፡ በሚባለው ፡ አደባባይ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ቡራኬ ፡ ሰጥተው ፡ ከወርቅ ፡ ብቻ ፡ የተሠራችውን ፡ የምስለ ፡ ፍቁር ፡ ወልዳን ፡ ሥዕልና ፡ መስቀል ፡ ከተሳለሙ ፡ በኋላ ፤ እንደገዳሙ ፡ ሥርዓትና ፡ ወግ ፡ የቀድሞዎቹ ፡ ዕጨጌዎች ፡ በሚቀመጡበት ፡ ከደንጊያ ፡ በታነጸ ፡ መንበር ፡ ላይ ፡ በተቀመጡ ፡ ጊዜ ፡ ነጋሪቱ ፡ ሲጐሰም ፡ እምቢልታና ፡ መለከቶቹ ፡ ሲነፉ ፡ ደወሎቹ ፡ ደግሞ ፡ ድምፃቸውን ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ ያሰሙ ፡ ነበር ።

ወዲያው ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ቀርበው ፡ እጅ ፡ ነሥተው ፡ ከዚያም ፡ ጽላተ ፡ ሙሴ ፡ ወደምትገኝበት ፡ ጽላት ፡ ቤት ፡ ወደሚባለው ፡ ወደመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ ገብተው ፡ ሲሳለሙ ፡ አጣኙ ፡ መምህር ፡ ገብረ ፡ ሚካኤል ፡ ያባትዎ ፡ የዕጨጌ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ የወርቅ ፡ መቋሚያ ፡ አቅርበውላቸው ፡ ጥቂት ፡ ጸሎት ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፤ አጣኙን ፡ መነኰሴ ፡ ስለቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ጥንታዊነት ፡ ሲጠይቋቸው ፡ የአክሱም ፡ ጽዮን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መጀመሪያ ፡ በአብርሀ ፡ ወአጽብሐ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ተሠርቶ ፡ በጉዲት ፡ (ቡዲት ፡) ዘመን ፡ ቢጠፋ ፡ እንደገና ፡ በአንበሳ ፡ ውድም ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ተሠራና ፡ እሱ ፡ ደግሞ ፡ በግራኝ ፡ ቢጠፋ ፡ ይህ ፡ አሁን ፡ ያለው ፡ ሕንጻ ፡ በአፄ ፡ ፋሲል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ተሠራ ፡ ብለው ፡ መለሱላቸው ።

ወዲያው ፡ አባ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ የሚባሉ ፡ በአክሱም ፡ ፴፫ ፡ ዘመን ፡ የተቀመጡ ፡ የሸዋ ፡ መነኰሴ ፡ የማኅበሩን ፡ አስተዳደር ፡ በአጭሩ ፡ አመለከቷቸው ። ከዚያም ፡ እንደተመለሱ ፡ ወደቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ሲደርሱ ፡ የአብርሀ ፡ ወአጽብሐ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተማሪዎች ፡ ባማረ ፡ ጣዕመ ፡ ዝማሬ ፡ ተቀበሏቸውና ፡ በተዘጋጀው ፡ ማረፊያ ፡ አዳር ፡ ሆነ ።

ኅዳር ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ረቡዕ ፡ የእመቤታችን ፡ በዓል ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ የሽሬን ፡ አውራጃ ፡ ገዳማት ፡ ጐብኝቶ ፡ ለመምጣት ፡ የታቀደውን ፡ አቅድ ፡ (ፕሮግራም ፡ ) ለመፈጸም ፡ ለንጋቱ ፩ሰዓት ፡ ሲቀረው ፡ ወደሽሬ ፡ ጉዞው ፡ ቀጠለ። ፪ሰዓት ፡ ሲሆንም ፡ ወደአውራጃው ፡ ከተማ ፡ ወደእንዳ ፡ ሥላሴ ፡ ሲደርሱ ፡ አገረ ፡ ገዥው ፡ ደጃዝማች ፡ መስፍን ፡ ተቀበሏቸውና ፡ ከተማውን ፡ አልፈው ፡ እንዳባጉና ፡ እስከ ፡ ሚባለው ፡ በመኪና ፡ ከተጓዙ ፡ በኋላ ፡ ጥቂት ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ የሚገኘውን ፡ ደብረ ፡ ዐባይ ፡ የተባለውን ፡ የአቡነ ፡ ሳሙኤልን ፡ ገዳም ፡ ለመጐብኘት ፡ መኪና ፡ የማያስኬድ ፡ በመሆኑ ፡ በበቅሎ ፡ ፳ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ወደገዳሙ ፡ ደረሱ ።

ካህናቱም ፡ በክብር ፡ ተቀበሏቸው ። የአቡነ ፡ ሳሙኤል ፡ ገዳም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ በፋሺሽት ፡ ወራሪነት ፡ ስለተቃጠለ ፤ ታቦቱ ፡ የሚገኙት ፡ በአንዲት ፡ መቃኞ ፡ ውስጥ ፡ ነው ። ቤተ ፡ ማኅበሩም ፡ ተቃጥሎ ፡ ስለነበረ ፡ እንደገና ፡ አዲስ ፡ ሊሠሩ ፡ ጀምረው ፡ ገና ፡ ሥራው ፡ አላለቀለትም ፡ ነበርና ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ለቤተ ፡ ማኅበሩ ፡ ማሠሪያ ፡ ፩፻ ፡ ብር ፡ ስጦታ ፡ አድርገዋል ።

በዚሁ ፡ ገዳም ፡ ሴት ፡ የማትገባ ፡ ስለሆነ ፤ ከገዳሙ ፡ ፈቀቅ ፡ ብሎ ፡ ሴት ፡ ደብር ፡ የተባለ ፡ በቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ስም ፡ የተተከለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይገኛል ፡ በዋናው ፡ ገዳም ፡ በቤተ ፡ ልሔም ፡ አጠገብ ፡ ጥሩ ፡ ምንጭ ፡ ይገኝበታል ። በገዳሙ ፡ በስተምሥራቅ ፡ በኩል ፡ የሰውን ፡ ዓይን ፡ ከአየሩ ፡ የሚከላከሉ ፡ በጣም ፡ ታላላቆች ፡ ዛፎች ፡ ይገኛሉ ፡ በዛፍቹም ፡ (በጫካው ፡ ) ውስጥ ፡ ግሩና ፡ ቀኝ ፡ ወራጅነት ፡ ያላቸው ፡ ጅረቶች ፡ አሉ ። የቅዱስ ፡ ሚካኤልም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በወንዙ ፡ አጠገብ ፡ ይገኛልና ፡ ሕፃናቱ ፡ ሀብተ ፡ ልጅነትን ፡ ሲቀበሉ ፡ በዚያው ፡ በጅረቱ ፡ ያጠምቋቸዋል ።

በተቃጠለው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ የአቡነ ፡ ሳሙኤል ፡ መቃብር ፡ ነው ፡ የተባለ ፡ ዋሻ ፡ አለ ። በዚያም ፡ ትንሽ ፡ ጉጆ ፡ ቀልሰው ፡ መነኰሳቱ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ጸሎተ ፡ ማዕጠንት ፡ ያደርጋሉ ። ይህንንም ፡ ሁሉ ፡ ከጐበኙ ፤ በኋላ ፡ ብፁዕ፡አባታችን፡አዲስ ፡ በተጀመረው ፡ ቤተ ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ በተዘጋጀው ፡ ማረፊያ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ ሎሚና ፡ ሙዝ ፡ ሌሎችንም ፡ አትክልቶች ፡ አበረከቱላቸው ።

ጠላም ፡ ወደሚዘጋጅበት ፡ ክፍል ፡ ወስደው ፡ የበሬው ፡ ቆዳ ፡ ሲደርቅ ፡ በገመድ ፡ እየወጠሩ ፡ በጠጕሩ ፡ በኩል ፡ ጠላ ፡ ሲጠምቁበት ፡ በተአምራት ፡ ጠጕሩ ፡ እንደማይላጥና ፡ የጠላውም ፡ ሽታ ፡ እንደማይለወጥ ፡ አሳይተውና ፡ ጠላውም ፡ ተቀምሶ ፡ ቃናው ፡ እጅግ ፡ ጣፋጭ ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል ።

ሌሎችም ፡ በሌላ ፡ ቦታ ፡ የሚሆን ፡ መስሏቸው ፡ እንደዚሁ ፡ ለመጥመቅ ፡ ቢያስቡ ፤ ሽታው፡ ተለውጦ ፡ እንደተበላሸ ፡ መነኰሳቱ አስረዱ ። ከግርማዊ ፡ ጃንሆይና ከግርማዊት ፡ እቴጌ ለገዳሙ ፡ በመምህር ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ (አሁን ፡ አቡነ ፡ ሉቃስ) ፡ እጅ ፡ የተላኩላቸው ፡ ሁለት ፡ ከወርቅ ፡ የተሠሩ ፡ የእጅ ፡ መስቀሎች ፡ ለማኅበሩ ፡ ከተሰጡ ፡ በኋላ ፤ ከብፁዕነታቸው ፡ ለገዳሙ ፡ መርጃና ፡ በገዳሙ ፡ ለሚገኙት ፡ መነኰሳትና ፡ ችግረኞች ፡ መርጃ ፡ ፩፻፴፩ ፡ ብር ፤ ለመንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተማሪዎችና ፡ ለመንግሥትም ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተማሪዎች ፡ ፩፻፵፩ ፡ ብር ፡ ስጦታ ፡ ተደርጎ ፡ በዚያው ፡ አዳር ፡ ሆነ ።

ኅዳር ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ሐሙስ ፡ ከጧቱ፡፲፪ ፡ ሰዓት ፡ ብፁዕ፡አባታችን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ እጅ ፡ ነሥተው ፡ ወደአክሱም ፡ መልስ ፡ ሆነ ። ፬ ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ እንዳ ፡ ሥላሴ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ የሽሬ፡አውራጃ ፡ ከተማ ፡ በሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ተሸልማ ፡ ሕዝቡና ፡ ሠራዊቱ ፡ ተማሪዎቹና ፡ ካህናቱ ፡ በአማረ ፡ አቀባበል ፡ ተቀበሏቸው ። በሽሬም ፡ አውራጃ ፡ ፋሺስት ፡ በአብያተ ፡ ክርስቲያናቱ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ጉዳት ፡ አድርጎ ፡ ነበርና ፡ በጠላት ፡ ለተቃጠሉትና ፡ ለፈረሱት ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ማደሻ ፡ ፩፻ ፱፻ ፶ ፡ ብር ፤ በየገዳሙ ፡ ለሚገኙ ፡ ካህና



www.ethiopianorthodox.org

ትና ፡ ችግረኞች ፡ ፫ሺ፴፩ ፡ ብር ፤ ለመንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተማሪዎችና ፡
ለመንግሥት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተማሪዎች ፡ ፯፻፲ ፡ ብር ፡ ከብፁዕነታቸው ፡
ስጦታ ፡ ተደረገ ።

ከምሳም ፡ በኋላ ፡ በ፱ ፡ ሰዓት ፡ ጕዞው ፡ ቀጥሎ ፡ በ፲፩ ፡ ሰዓት ፡ አክ
ሱም ገብተው ፡ አዳር ፡ ሆነ ። ኅዳር ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ብፁዕ አባታችን ፡ በማረፊያቸው ፡
ሆነው ፡ የገዳማቱን ፡ መምህራንና ፡ መነኰሳት ፡ የያድባራቱን ፡ ሊቃውንትና ፡
ካህናት ፡ በየተራ ፡ እየተቀበሉ ፡ ሲያነጋግሩና ፡ እርዳታ ፡ ሲያደርጉ ፡ እስከ ፡
፯ ፡ ሰዓት ፡ ቆዩ ።

በዚሁ ፡ ቀን ፡ ለአክሱም ፡ ገዳም ፡ መርጃ ፡ ፩ሺ፪፻ ፡ ብር ፤ በገዳሙ ፡ ለሚ
ገኙ ፡ ካህናትና ፡ ችግረኞች ፡ ፩ሺ፪፻፹፩ ፡ ብር ፡ ለአብርሀ ፡ ወአጽብሐ ፡ ትም
ህርት ፡ ቤት ፡ ተማሪዎች ፡ ፩፻ ፡ ብር ፤ ስጦታ ፡ አደረጉ ።

እንዲሁም ፤ በዚሁ ፡ ቀን ፡ የጽዮን ፡ በዓል ፡ ዋዜማ ፡ በመሆኑ ፤ ፩ ፤
ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ሲሆን ፡ የተጋብአው ፡ ደወል ፡ ድምፁን ፡ አሰምቶ ፡ ነበርና ፡
ል ፡ ፯ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ብፁዕነታቸውና ፡ ተከታዮቻቸው ፡ ወደዋዜማው ፡ ሔደው ፡
በመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ በቅኔ ፡ ማኅሌቱ ፡ ከካህናቱ ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ የዋዜ
ማውን ፡ ጸሎት ፡ አደረሱ ።

የዋዜማውም ፡ ጸሎት ፡ በ፳ ፡ ሰዓት ፡ ተፈጽሞ ፡ ፳ ሰዓት ፡ ተሩብ ፡ ሲሆን ፤
ጸሎተ ፡ ቅዳሴው ፡ ተጀምሮ ፡ በ፲ ፡ ሰዓት ፡ ተፈጸመ ። በዚሁ ፡ ቀን ፡ ከዋዜ
ማው ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ብፁዕ ፤ ዕጨጌ ፡ ወደጽላት ፡ ቤት ፡ ሔደው ፡ እጅ ፡
ሥተው ፡ ከአጣኙ ፡ ጋራ ፡ ሰፊ ፡ ንግግር ፡ አድርገው ፡ ቆይተው ፡ ነበር ።
በር ፡ ራስ ፡ አበበም ፡ የጽዮንን ፡ በዓል ፡ ለማክበር ፡ በዚሁ ፡ ቀን ፡ ፱ ፡
ዓት ፡ ሲሆን ፡ መጥተው ፡ ነበርና ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ አብረው ፡ አደሩ ።

ኅዳር ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ከሌሊቱ ፡ ፳ ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
ሔደው ፡ የማኅሌቱን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ለማየት ፡ እንዲመች ፡ በሁለቱ ፡ ቅኔ ፡
ማኅሌት ፡ መገናኛ ፡ በሚገኘው ፡ ረድፍ ፡ ላይ ፡ ቆሙ ። በዚሁም ፡ ጊዜ ፡ የመ
መሪያውና ፡ የሁለተኛው ፡ ቅኔ ፡ ማኅሌት ፡ ካህናት ፡ ቋሙንና ፡ መረግዱን ፡
ቁንና ፡ ወረቡን ፡ እየተቀባበሉ ፡ ሲያሸበሽቡ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ያሰኙ ፡ ነበር ።
ረቡም ፡ ከመረግድ ፡ ወደጽፋት ፡ ሊደርስ ፡ ሲል ፡ ፫ ፡ ጊዜ ፡ ያህል ፡ አሸብ
በው ፡ ወዲያው ፡ ይተዉታል ።

በዚሁም ፡ ጣዕመ ፡ ዜማቸው ፡ "አንሶሱ ፡ ማዕከለ ፡ መርህብኪ ፡ ይቤ ፡
በረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ተንሥኢ ፡ ጽዮን ፡ ልበሲ ፡ ኃይለኪ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡
ሥት" ፡ እያሉ ፡ ይህንና ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ሲዘምሩ ፡ ምሥጢሩና ፡
ዕመ ፡ ዜማው ፡ የሰሚውን ፡ ልቡና ፡ በተመሥጦ ፡ ይማርክ ፡ ነበር ። ማኅሌ
ም ፡ እንደተፈጸመ ፡ ብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ ራሳቸው ፡ ሠራዒ ፡ ካህን ፡ ሆነው ፡



ቀደሱ ። ፬ ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ ለማድረስ ፡ እብነ ፡ ያሬድ ፡
ተብሎ ፡ በሚጠራው ፡ አደባባይ ፡ አጠገብ ፡ ባንድ ፡ ታላቅ ፡ ወርካ ፡ ሥር ፡
ከመሬት ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ በተደለደለው ፡ ሉዓላዊ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ በሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡
የተጌጠ ፡ አጎበር ፡ ተደርጎ ፤ ብፁዕ ፡ ዕጨጌና ፡ ክቡር ፡ ራስ ፡ አበበ ፡ ተቀ
መጡ ። በስተቀኝ ፡ በኩል ፡ ሊቃውንትና ፡ መኳንንት ፤ በስተግራ ፡ የውጭ ፡
አገር ፡ ሰዎች ፡ በየማዕርጋቸው ፡ እንደተቀመጡ ፤ በአክሱም ፡ ሥርዓትና ፡ ሕግ ፡
ታቦት ፡ ተሸክሞ ፡ መውጣት ፡ ወጋቸው ፡ ስላይደለ ፡ ሥዕልና ፡ መስቀል ፡
የወርቅ ፡ ጥላና ፡ ድባብ ፤ የወርቅ ፡ አክሊልና ፡ ዘውድ ፡ ሌሎችንም ፡ እነዚህን ፡
የመሳሰሉ ፡ የከበሩ ፡ ንዋያተ ፡ ቅድሳትን ፡ በየኅብራቸው ፡ ይዘው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡
ወርቀ ፡ ዘቦ ፡ በተንቆጠቆጠ ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖ ፡ ተሸልመው ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሡ ፡
ወደ ፡ ሚፈጸምበት ፡ አደባባይ ፡ ብቅ ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፤ ውበታቸውንና ፡ ድምቀ
ታቸውን ፡ ለመገመት ፡ ለሚተርከው ፡ ሰው ፡ በቂ ፡ መግለጫ ፡ ስለማይገኝ ፡
ዕፁብ ፡ ድንቅ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ መወሰን ፡ ግዴታ ፡ ነበር ።

በዚህም ፡ ላይ ፡ ተመልካቹ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ካህናተ ፡ ኦሪት ፡ (ሌዋውያን) ፡
መጻሕፍተ ፡ ብሉያት ፡ የመጡት ፡ በጽዮን ፡ ምክንያትና ፡ ከጽዮን ፡ ጋራ ፡ ሲሆን ፤
እንዲሁም ፡ የዘመነ ፡ ሐዲስ ፡ ክርስትና ፡ የደረሰ ፡ ወይም ፡ የተራባ ፡ በአክሱም ፡
አካባቢ ፡ በተገኘው ፡ በመጀመሪያው ፡ ጳጳስ ፡ (ፍሬ ፡ ምናጦስ) ፡ በአባ ፡ ሰላማ ፡
ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ ሲሆን ፤ በአክሱም ፡ ሥርዓት ፡ የሌለው ፡ በየክብረ ፡ በዓሉ ፡
ታቦትን ፡ ተሸክሞ ፡ ዑደት ፡ ማድረግ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ሥርዓት ፡ ሆኖ ፡ እን
ደኖረ ፡ ይጠይቅ ፡ ይሆናል ።

ለዚህ ፡ ጥያቄ ፡ ኢያሱ ፡ ዮርዳኖስን ፡ ሲሻገር ፤ ሌዋውያን ፡ (ካህናቱ) ፡
ጽዮንን ፡ ተሸክመው ፡ በባሕሩ ፡ መካከል ፡ በመቆማቸው ፡ ባሕሩ ፡ እንደተከ
ፈለ ፤ ኢያሪኮንም ፡ በከበበ ፡ ጊዜ ፡ ከብዙ ፡ የውካታ ፡ ድምፅ ፡ ጋራ ፡ ፯ ፡ ጊዜ ፡
ያህል ፡ ይዘዋት ፡ በመዞራቸው ፡ ቅጽረ ፡ ኢያሪኮ ፡ እንደፈረሰ ፤ በየዘመቻቸውም ፡
ይዘዋት ፡ ሲወጡ ፡ ጠላታቸውን ፡ ታጠፋላቸው እንደነበረ ፡ መጻሕፍት ፡ የሚ
ተርኩት ፡ በመሆኑ ፤ መልስ ፡ ሳይሆነው ፡ አይቀርም ። ከዚያም ፡ ተያይዞ ፡ የመጣ ፡
ሥርዓት ፡ መሆኑን ፡ ዛሬውኑ ፡ ቅሉ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ከእምነታቸው ፡ ጥን
ካሬ ፡ የተነሣ ፡ አባር ፡ ቸነፈር ፡ ወይም ፡ ጦር ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ታቦት ፡
በማውጣትና ፡ በመማጸን ፡ የሚደረገው ፡ ሃይማኖታዊ ፡ ምግባር ፡ መሠረታዊነ
ቱን ፡ የሚያሳይ ፡ ነው ።

ቢሆንም ፤ በየጊዜው ፡ ስለሚደረገው ፡ ክብረ ፡ በዓል ፡ በአክሱም ፡ ጽዮን ፡
የሚደረገውን ፡ የንግሥ ፡ አከባበር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሌሎችም ፡ አብያተ ፡
ክርስቲያናት ፡ እንዲከተሉት ፡ ቢሆን ፡ የሚያጕዳ ፡ መስሎ ፡ አይታይም ።

ወደ ፡ ጀመርነው ፡ አሳብ ፡ እንመለስ ። ሥርዓተ ፡ ንግሡ ፡ የሚፈጸም
በት ፡ ዕብነ ፡ ያሬድ ፡ የተባለውን ፡ አደባባይ ፤ ቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ በዚሁ ፡ ቦታ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ይ ፡ ሆኖ ፡ «ቀዳሚሃ ፡ ለጽዮን ፡ ሰማየ ፡ ሣረረ ፡ ወበዳግም ፡ አርአዮ ፡ ሙሴ ፡ ዘከመ ፡ ይገብር ፡ ግብረ ፡ ለደብተራ» ፡ እያለ ፡ ዘምሮበት ፡ ነበርና ፡ ዚሁ ፡ መሠረት ፡ መዘምራኑ ፡ ይህንኑ ፡ አለዝበው ፡ አሸብሸቡ ። ወዲያው ፡ አብርሀ ፡ ወአጽብሐ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተማሪዎች ፡ የታቦተ ፡ ጽዮንን ፡ መጣጥ ፡ እንዲሁም ፡ የሐዲሱን ፡ ዘመነ ፡ ክርስትና ፡ አቀባበል ፡ ኀብር ፡ ለው ፡ ምሥጢርና ፡ ዜማ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ዘመሩ ። (ከመዝሙሩ ፡ ንዱን ፡ ቤት ፡ ለማስታወስ) ፡ ቀድሞ ፡ በምኒልክ ፡ ኋላም ፡ በሰላማ ፡ የሃይ ኖት ፡ ዐዋጅ ፡ በደጅሽ ፡ ተሰማ ። ይህንና ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ በማረ ና ፡ ሲያሰሙ ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፤ ብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ አሳርገውና ፡ ቡራኬ ፡ ሰጥ ው ፡ የበዓሉ ፡ ፍጻሜ ፡ ሆነ ።

የአክሱም ፡ ጽዮን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በጥንታዊነቱ ፡ ከዛሬው ፡ ጊዜ ፡ ሕንጻ ፡ ዙ ፡ ይለያያል ። በመመሳሰል ፡ ከመቀሌ ፡ ኪዳነ ፡ ምሕረትና ፡ ከደብረ ፡ ዳሞ ፡ ይቃረ ል ። የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ማዕዘን ፡ በአራት ፡ ገጽ ፡ ሆኖ ፡ በምሥራቅና ፡ በምዕራብ፡ ሚገኘው ፡ የገጹ ፡ ወርድ ፡ መጠነኛ ፡ ሲሆን ፤ በሰሜንና ፡ በደቡብ ፡ የሚገኘው ፡ ገሞ ፡ ወርዱ ፡ በጣም ፡ ሰፊ ፡ ነው ።

በዓይን ፡ ግምት ፡ የወርዱ ፡ ስፋት ፡ ዙሪያ ፡ እስከ ፡ ፺፪ሜትር ፡ (፩፻፹፬ ፡ ክንድ) ፤ ዜገመት ፡ ሲሆን ፡ ቁመቱ ፡ በማናቸውም ፡ ገጽ ፡ ትክክል ፡ ሆኖ ፡ (ከ፲፰ሜትር)፡ ፴ ፡ ድ ፡ አያንስም ። በመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ ቅኔ ፡ ማኅሌቱ ፡ ሲገኝ ፡ ስፋታቸው፡ (ወር ው ፡ (ከ፩ሜትር ፡ ተኩል) ፡ ሦስት ፡ ክንድ ፡ በማይበልጡ ፡ ሦስት ፤ ተራ ፡ ባላቸው፡ ምብ ፡ አዕማዶች ፡ የተከፈሉ ፡ ወደመቅደሱ ፡ የሚያዘልቁት ፡ አምስት ፡ ክፍሎች ፡ ኛሉ ። በሦስቱም ፡ አዕማዶች ፡ መካከል ፡ በሚገኘው ፡ ክፍል ፡ ከቅኔ ፡ ማኅሌቱ ፡ ሮ ፡ በማናቸውም ፡ ክፍል ፡ ሆኖ ፡ ወደመቅደሱ ፡ ለማነጣጠር ፡ (ለመመልከት) ፡ ከልል ፡ ነገር ፡ አይገኝበትም ።

ከቅኔ ፡ ማኅሌቱ ፡ ጀምሮ ፡ ፯ኛው ፡ ክፍል ፡ ሲፈጸም ፤ በ፯ኛው ፡ መቅደሱ ፡ ይገ ። መቅደሱ ፡ ከወደጀ፡ርባው ፡ ዋናውን ፡ ሕንጻ ፡ ተጠግቶ፡የተሠራ ፡ ነው ፡ እንደ ዶሌሎቹ ፡ መቅደሶች ፡ ለምዕዋድ ፡ የሚሆን ፡ ቦታ ፡ አልተሠራለትም ። መቅደሱ ፡ ንባር ፡ በኩል ፡ ሦስት ፤ (አናቅጽ) ፡ በሮች ፡ አሉት ። እነዚሁ ፡ በሮች ፡ በቀኝ ፡ የቀ ፤ ሚካኤል ፤ በግራ ፡ የቅዱስ ፡ ገብርኤል ፤ በመካከሉ ፡ የቅድስት ፡ እመቤታችን ፡ ቶችና ፡ መኖሪያ ፡ ያሉባቸው ፡ የመቅደስ ፡ ክፍሎች ፡ ሲሆኑ ፡ ጸሎተ ፡ ማዕጠንት፡ ያደርጉበት ፡ ጊዜ ፡ ከሦስቱም ፡ ክፍሎች ፡ ከያንዳንዳቸው ፡ ፯ ፡ ልዑካን ፤ በድምሩ፡ ፡ ልዑካን ፡ ተሸልመው ፡ ብቅ ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ መጽሐፋዊ ፡ በሆነ ፡ የሕሊና ፡ አስ ?ት ፡ የምንመለከተውን ፡ ድርገተ ፡ መላእክትን ፡ ወይም ፡ ኻያ ፡ አራቱን ፡ ካህናተ ፡ ይ ፡ በአማናዊ ፡ አስተያየት ፡ ያየናቸው ፡ ያህል ፡ አድርገን ፡ ገምተነዋል ።

በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ አቅራቢያ ፡ የሚገኙ ፡ ሁለት ፡ የደወል ቤቶች ፡ አሉ ። የቤተ፡ ቲያኑ ፡ ቅጽር ፡ (አጥር) ፡ ሁለት ፡ ዙሪያ ፡ ነው ፡ ከውጪ ፡ ሲገቡ ፡ የመጀመሪያ



ውን ፡ ቅጽር ፡ አልፎ ፤ በስተምዕራብ ፡ የነገሥታቱ ፡ መናገሻ ፡ ነው ፡ በተባለው ፤ አደበባይ ፡ ለንጉሡና ፡ ለጳጳሱ ፡ ሁለት ፡ ከደንጊያ ፡ የተቀረጹ ፡ መንበሮች ፡ በአጠገ ባቸውም ፡ የመንበረ ፡ ዳዊት ፡ ሰንደቅ ፡ የመሰሉ ፡ በላያቸው ፡ የዙፋን ፤ ቀጸላ፡የሚጣ ልባቸው ፡ የነበሩ ፡ ናቸው ፡ የተባሉ ፡ የቆሙና ፡ የተኙ ፡ የደንጊያ፡ ዓምዶች፡ይገኛሉ።

ያቀማመጡ ፡ አስተያየት ፤ ወደቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ የሚመለከት፡ስለሆነ ፤ ከንጉሡ፡ መንበር ፡ (ዙፋን) ፡ በስተጀርባ ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ የ፲፪ ፡ መሳፍንት ፡ ከደንጊያ ፡ የታነጹ ፡ መንበሮች ፡ ይታያሉ ። በጥንቱ ፡ ሥርዓት ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥቱ ፡ ሥርዓተ ፡ መንግሥቱን፡ በዚያ ፡ አድርሶ ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይገባል ፡ ይባላል ። ከሁለቱ ፡ ቅጽር ፡ በስተ ውጪ ፡ የኢየሱስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሚገኝበት ፡ ከሰሜን ፡ ወደምሥራቅ ፡ ሲል፡ በግምት ፡ ወርዱ ፤ ባንድ ፡ ወገን ፡ ፫ክንድ ፡ (፩ሜትር ፡ ከ፵ሣንቲ) ፡ ከሌላው ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ሁለት ፡ ክንድ ፡ (፩ሜትር) ፡ ርዝመቱ ፡ (ቁመቱ) ፡ ከ፵ ፤ ክንድ ፡ (፳፫ሜትር፡ የሚበልጥ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቅርጽ ፡ ያለበት ፡ በአጠገቡም ፡ ከሱ ፡ ጥቂት፡አነስ ፡ የሚሉ፡ ሁለት ፡ ከደንጊያ ፡ የታነጹ ፡ ሐውልቶች ፡ ቆመው ፡ ይታያሉ ።

ከነዚህም ፡ ሌላ ፡ በአካባቢያቸው ፡ ጥንት ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ነበር ፡ በሚባ ለው ፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ የሕዝብ ፡ መኖሪያ ፡ መንደር ፡ ከሆነው ፡ ከየመንገዱ ፡ ዳር፡ ቅርጽ፡ የሌላቸው ፡ የቆሙና ፡ የተኙ ፡ ታናናሾች ፡ የደንጊያ ፡ አዕማድ ፡ ይገኛሉ ። ሐው ልቶቹ ፡ ከሚገኙበት ፡ አቅራቢያ ፡ ወደተራራው ፡ ጥግ ፡ ሲል ፡ ለከተማው ፡ ነዋሪ ፡ ሕዝብ ፡ በሲሚንቶ ፡ የተገነባ ፡ ታላቅ ፡ ኩሬ ፡ ስላለ ፡ የከተማው ፡ ሕዝብ ፡ ከውኃ ፡ ችግር ፡ ነጻ ፡ ሆኗል ።

## የበዓሉ ፡ መስተንግዶ ።

በዚሁ ፡ ቀን ፡ ብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ ከየገዳማቱና ፡ ከየአድባራቱ ፡ ለመጡት ፡ ሊቃ ውንትና ፡ መምህራን ፡ ግብዣ ፡ አድርገው ፡ አመሹ ። ኅዳር ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ እሑድ ፡ ክቡር ፡ ራስ ፡ አበበ ፡ ለአክሱም ፡ ካህናትና ፡ ከየገዳማቱ ፤ ለመጡት ፡ ሊቃውንት ፡ ግብዣ ፡ አደረጉ ።

በዚሁም ፡ ቀን ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ብዙ ፡ የገንዘብ ፡ ስጦታ ፡ ሲያደርጉ ፡ ዋሉ ። ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ እግራቸው ፡ በደረሰበት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን፡ለሌሎቹም ፡ ከመንገዳቸው፡ ራቅ ፡ ብለው ፡ ለሚገኙት ፡ ለተምቤን ፡ አውራጃ ፡ ገዳማትና ፡ አድባራት ፡ ካህናትና ፡ ችግረኞች ፡ ፫ሺ፱፻፺ ፡ ብር ፤ በአውሳ ፡ ለራያና ፡ ለአዘቦ ፡ አውራጃ ፡ ለካህናቱ ፡ ፪ሺ ፳፻ ፡ ብር ፤ ለመንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተማሪዎች ፡ ፪ሺ፳፻ ፡ ብር ፡ ስጦታ ፡ አድርገው ፡ ወደአሉበት ፡ ድረስ ፡ እንዲላክላቸው ፡ አድርገዋል ።

የትግሬ ፡ አውራጃ ፡ ገዳማትና ፡ አድባራት ፡ ሊቃውንትና ፡ መምህራን ፡ ተማ ሪዎችና ፡ ችግረኞች ፡ ነዳያኑ ፡ ሳይቀሩ ፤ መንፈሳዊ ፡ አባታቸውን ፡ ብፁዕ ፡ ዕጨጌን፡ በደጃቸው ፡ አግኝተው ፡ ቡራኬ ፡ መቀበላቸው ፡ ታላቅ ፡ ዕድል ፡ ሲሆን ፡ በዚሁ ፡ ላይ ፡ ካህናቱ ፡ እንዳይቸገሩ ፤ ተማሪዎች ፡ ያለችግር ፡ እንዲማሩ ፡ የፈረሱ ፡ አብያተ፡ ክርስቲያናት ፡ እንዲታደሱና ፡ እንዲሠሩ ፡ አስፈላጊያቸውን ፡ ሁሉ ፡ ወደየበዓታቸው ፡

www.ethiopianorthodox.org

መኖሪያቸው) ፡ ሔደው ፡ ስለፈጸሙላቸው ፤ በዚሁ ፡ ዕድል ፡ አካባቢ ፡ የሚገኙት ፡ ሁሉ ፡ መልከሙ ፡ መሪያቸው ፡ ለግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴና ፤ ለቸር ፡ ጠባቂያ ው ፡ ለብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፤ ልባዊ ፡ ምስጋና ፡ ሲያቀርቡ ፡ ደስታ ው ፡ በየገጻቸው ፡ ላይ ፡ እንደጕልህ ፡ ፊደል ፡ በግ ፡ ብሎ ፡ ይነበብ ፡ ነበር ።

## የመልስ ፡ ጕዞ ።

ብፁዕነታቸውና ፡ ተከታዮቻቸው ፡ ኅዳር ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ሰኞ ፡ በ፬ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ አክሱም ፡ ተነሥተው ፡ ፯ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ አዲግራት ፡ ደረሱ ። ጥቂትም ፡ ዕረፍት ፡ ሆነ ፡ በኋላ ፡ በ፲ሰዓት ፡ ተነሥተው ፡ መቀሌ ፡ አዳር ፡ ሆነ ።

ኅዳር ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ማክሰኞ ፡ የቅድስት ፡ ማርያምን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተሳል ው ፡ ፫ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ጕዞው ፡ ቀጠለና ፡ በ፮ሰዓት ፡ ማይጨው ፡ ደረሱ ። በዚያም ፡ ቂት ፡ ዕረፍት ፡ ተደረገና ፡ በ፲ሰዓት ፡ ተነሥተው ፡ ወደኮረም ፡ ተጓዙ ።

ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ከመቀሌ ፡ እስከ ፡ ኮረም ፡ አዋሳኝ ፡ በየመንገዱ ፡ ለሚጠባ ቁዋቸው ፡ ካህናትና ፡ ችግረኞች ፡ ፩ሺ፭፻፺፯ ፡ ብር ፤ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መረጃ ፡ ብር ፡ ስጦታ ፡ አድርገዋል ።

፲፬ ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ኮረም ፡ ስለደረሱ ፡ የዋግ ፡ አውራጃ ፡ ካህናት ፡ በመ ካም ፡ አቀባበል ፡ ተቀብለዋቸው ፡ በዚያው ፡ አዳር ፡ ሆነ ።

ኅዳር ፡ ፳፭ ፡ ቀን ፡ ረቡዕ ፡ ከጧቱ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ እስከ ፡ ፯ ፡ ሰዓት ፡ ረስ ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ በጠላት ፡ ለተጐዱትና ፡ ለተቃጠሉት ፡ ለዋግ ፡ አውራጃ ፡ በያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መርጃ ፡ ፩ሺ፩፻፹ ፡ ብር ፡ ለካህናትና ፡ ለችግረኞች ፡ ፫ሺ ፲፩ ፡ ብር ፡ ለመንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተማሪዎች ፡ ፩፻፶ ፡ ብር ፡ ስጦታ ፡ ድርገው ፡ ፯ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ጕዞው ፡ ቀጠለና ፡ በ፰ ፡ ሰዓት ፡ አላማጣ ፡ ደረሱ ። ቂት ፡ ዕረፍት ፡ ከተደረገ ፡ በኋላም ፡ ፱ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ሲሆን ፡ ቆቦ ፡ ወደሚባለው ፡ ረሱ ።

በዚያም ፡ ካህናቱና ፡ ተማሪዎቹ ፡ በሰልፍ ፡ ተቀበሉዋቸው ። ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ደቅድስት ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዓጸድ ፡ ገብተው ፡ ለካህናቱና ፡ ለተማ ዎቹ ፡ ስጦታ ፡ አደረጉና ፡ ባሕታዊ ፡ አስረስ ፡ የሚባሉት ፡ በሀገሩ ፡ ደኅና ፡ ት ፡ ባለመኖሩ ፡ ለብፁዕነታቸው ፡ መቀበያ ፡ በመቃ ፡ ባሰናዱት ፡ መልካም ፡ ስ ፡ ጥቂት ፡ ዕረፍት ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ጕዞው ፡ ቀጠለና ፡ ከማታው ፡ ፬ሰዓት ፡ ሆን ፡ ወልድያ ፡ ደረሱ ።

አገረ ፡ ገዥው ፡ ደጃዝማች ፡ አያሌው ፡ ብሩም ፡ እንደመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ መልካም ፡ አቀባበል ፡ ተቀበሏቸውና ፡ በዚያው ፡ አዳር ፡ ሆነ ። በዚሁም ፡ ፡ ሁሉ ፡ የየወረዳውና ፡ የየአውራጃው ፡ ገዥዎች ፡ ወይም ፡ እንደራሴዎቻቸው ፡ ንዱ ፡ ሲሸኝ ፡ ሌላው ፡ እንድትቀበሉ ፡ እያለ ፡ ሲያስተላልፍ ፡ ብፁዕነታቸው ፡ እንደብርቅ ፡



ያህል ሆኖላቸው ፡ እንደነበረና ፡ የአቀባበላቸውም ፡ ደስታ ፡ የመንገደኞቹን ፡ ድካም ፡ እንደቀነሰው ፡ እርግጠኛ ፡ ነበር ።

ኅዳር ፡ ፳፮ ፡ ቀን ፡ ሐሙስ ፡ ከጧቱ ፡ በ፱ ሰዓት ፡ ወደደሴ ፡ ጕዞው ፡ ቀጠለና ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መጥተው ፡ ኖሮ ፡ እንደራሴያቸው ፡ ክቡር ፡ ራስ ፡ ገብረ ፡ ሕይወትና ፡ ዲረክተሩ ፡ ፊታውራሪ ፡ ክፍሌ ፡ ዳዲ ፡ ከ፳ሺ ፡ ክንድ ፡ (፴ኪሎ ፡ ሜትር ፡) የሚበልጥ ፡ መንገድ ፡ መጥተው ፡ ተቀበሏቸውና ፡ አንድነት ፡ ጕዞው ፡ ቀጥሎ ፡ ፭ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ሲሆን ፡ ደሴ ፡ ከተማ ፡ ደረሱ ፡ በዚያውም ፡ አዳር ፡ ሆነ ።

ኅዳር ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ዐርብ ፡ ከሌሊቱ ፡ በ፲ ሰዓት ፡ ጕዞው ፡ ቀጥሎ ፡ የወሎና ፡ የአውራጃዋ ፡ ግዛት ፡ ዲሬክተር ፡ ፊታውራሪ ፡ ክፍሌ ፡ ዳዲ ፡ እስከ ፡ ከምቦልቻ ፡ ሸኝተው ፡ ተመለሱ ። ፭ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ሲሆን ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ደርሰው ፡ ሦስት ፡ ሩብ ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ዕረፍት ፡ ተደርጎ ፡ ወደአዲስ ፡ አበባ ፡ ጕዞው ፡ አመራ ። የመንፈሳዊ ፡ ጉባኤ ፡ ምክትል ፡ ሰብሳቢና ፡ የታዕካ ፡ ነገሥት ፡ መታሰቢያ ፡ ቤት ፡ በአታ ፡ ገዳም ፡ መምህር ፡ ሊቀ ፡ ሊቃውንት ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፤ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ መልአከ ፡ ብርሃናት ፡ ገብረ ፡ አጋዕዝትና ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ አለቃ ፡ ልሳነ ፡ ወርቅ ፡ ሰንዳፋ ፡ ድረስ ፡ ለመቀበል ፡ ሒደው ፡ ስለነበረ ፡ አንድነት ፡ ብፁዕነታቸውን ፡ ተከትለው ፡ ፲፩ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ገቡና ፡ የጕዞው ፡ ፍጻሜ ፡ ሆነ ።

---

ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ።

በጐጃም ፡ ያሉትን ፡ ገዳማትና ፡ አድባራት ፡ በመጐብኘት ፡ የፈጸሙት ፡

## ገዳማዊ ፡ ትሩፋት ።

የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ የጐጃምን ፡ ጳጳስ ፡ አቡነ ፡ ማርቆስን ፡ አስከትለው ፡ በጣና ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ገዳማት ፡ ለመጐብኘት ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ኅዳር ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ቅዳሜ ፡ ከጥዋቱ ፡ በሁለት ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ በኢትዮጵያ ፡ የአየር ፡ መንገድ ፡ ወደጐጃም ፡ ጕዞ ፡ አደረጉ ።

ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ከሩብ ፡ ሲሆን ፤ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፤ የጐጃም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ክቡር ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ በለውና ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞችና ፡ የጦር ፡ ሹማምቶች ፡ በአውሮፕላኑ ፡ ጣቢያ ፡ ይጠባበቁ ፡ ስለነበረ ፤ ወዲያውኑ ፡ አውሮፕላኑ ፡ እንደደረሰ ፡ ክቡር ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፤ በለው ፡ ወደአውሮፕላኑ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ተገናኝተው ፡ የብፁዕነታቸውን ፡ በረከት ፡ ተቀብለው ፡ ተሰናብተው ፡ ከተመለሱ ፡ በኋላ ፤ ሁሉም ፡ እንደ ፡ መዓርጋቸው ፡ ወደአውሮፕላኑ ፡ እየገቡና ፡ በረከት ፡ እየተቀበሉ ፡ እንደተመለሱ ፡ አውሮፕላኑ ፡ ተነሣ ።

ወዲያውኑ ፡ የጐጃምን ፡ አውራጃ ፡ አልፎ ፡ ወደ ፡ ዳሞት ፡ አውራጃ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ያገሩን ፡ ለምነትና ፡ ልምላሜ ፡ በመመልከታቸው ፡ የብፁዕነታቸው ፡ ልቡና ፡ በደስታ ፡ ተሸፍኖ ፡ ነበር ።

www.ethiopianorthodox.org

ጥቂት ፡ እልፍ ፡ ብለው ፡ ታላቁ ፡ ወንዝ ፡ ግዮን ፡ የሚፈልቅበትን ፡ ግሽ ፡
ዐባይ ፡ የተባለውን ፡ አውራጃ ፤ በበለጠ ፡ ልምላሜ ፡ ተሸፍኖ ፡ በማየታቸው ፡ ወርኃ
ክረምት ፡ እንጂ ፡ ወርኀ ፡ ሐጋይ ፡ መሆኑን ፡ እያሰገንዝባቸውም ፡ ነበር ፡፡

እንደዚህ ፡ ባለ ፡ ጕዞ ፡ ተጕዘው ፡ አራት ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ባሕር ፡ ጊዮርጊስ ፡
በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ በአውራጃው ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ አማካይነት ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞ
ችና ፡ የከተማው ፡ ሕዝብ ፡ የጦር ፡ ሹማምንቶች ፡ የአፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ትምህ
ርት ፡ ቤት ፡ ተማሪዎች፡ ከነመምህራኖቻቸው ፡ የደብሩ ፡ ካህናቶች ፡ በየቦታቸው ፡
ተሰልፈው ፡ የብፁዕነታቸውን መምጣት ፡ ሲጠባበቁ ፡ አውሮፕላኑ ፡ በባሐሩና ፡
ዓባይ ፡ መውረጃ ፡ ጥቂት ፡ ደቂቃዎች ፡ ተዘዋውሮ ፡ መሬት ፡ ሲይዝ ፡ ሕዝቡ ፡
ሁሉም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ደስታውን ፡ በጭብጨባ ፡ ለብፁዕነታቸው ፡
ለጠ ፡፡ ብፁዕነታቸውም ፡ ለያንዳንዱ ፡ ሕዝብ ፡ ቅዱስ ፡ በረከታቸውን ፡ አድ
ለው ፡ ወደባሕር ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሔደው ፡ ጸሎት ፡ አድርሰው ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ችሮታ ፡ አድርገው ፡ ለማረፊያ ፡ ወደተዘጋጀላቸው ፡ ሥፍራ ፡
ሔዱ ፡፡

ጥቂት ፡ ዕረፍት ፡ አድርገው ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ በዓሥር ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ በመ
ኪና ፡ እየተዘዋወሩ ፡ የባሕሩን ፡ አካባቢዎች ፡ ተመልክተዋል ፡፡

ታኅሣሥ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እሑድ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ጸሎት ፡ ካደረሱ ፡ በኋላ
ዙዎችን ፡ ችግረኞች ፡ አንድ ፡ በአንድ ፡ እየተቀበሉ ፡ አነጋግረው ፡ ችግራቸውን ፡
ላቀለሉላቸው ፤ በተደረገላቸው ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ለብፁዕነታቸውና ፡ ለግርማዊ ፡
ጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዕድሜያቸውን ፡ እንዲያበዛላቸው ፡ ዘመናቸውን ፡ ዘመነ ፡ ሰላም ፡
ንዲያደርግላቸው ፡ ልመናቸውን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቀረቡ ፡፡

ታኅሣሥ ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ሰኞ ፡ በባሕር ፡ ዳር ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ
ን ፡ ጸሎተ ፡ ነግህ ፡ አድርሰው ፡ በአካባቢው ፡ አዲስ ፡ ከተማ ፡ እንዲመሠረትበት ፡
ቀደውን ፡ ቦታ ፡ ዙረው ፡ ጐብኝተው ፡ ተመልሰዋል ፡፡

ታኅሣሥ ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ማክሰኞ ፡ ዞብል ፡ በተባለው ፡ የባሕር ፡ ጀልባ ፡ ቲሳፍ
ው ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ያህል ፡ በባሕሩ ፡ ላይ ፡ እንደተጓዙ ፡ ዳጋ ፡ እስ
ጢፋኖስ ፡ ወደሚባለው ፡ ጥንታዊ ፡ ደሴት ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፤ አለባበሳቸውና ፡ የመል
ቸው ፡ አርአያ ፡ ሰማያውያን ፡ ነገደ ፡ መላእክትን ፡ እንጂ ፡ ምድራውያን ፡ ደቂቀ
ዳምን ፡ የማይመስሉ ፡ መነኰሳት ፡ ብፁዕነታቸውን ፡ ለመቀበል ፡ በየታንኳቸው ፤
ነው ፡ ባሕሩን ፡ መልተውት ፡ ይታዩ ፡ ነበር ፡፡

ወዲያው ፡ መርከቡ ፡ ወደወደቡ ፡ እንደደረሰ ፡ መነኰሳቱ ፡ ወደመርከቡ ፡ እየተ
ጉ ፡ ከብፁዕነታቸው ፡ ቡራኬ ፡ ተቀበሉ ፡፡

ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ከጀልባው ፡ ወርደው ፡ በታንኳው ፡ ፴ ፡ ክንድ ፡ ያህል ፡ ተጕ
ው ፡ የብሱን ፡ በረገጡ ፡ ጊዜ ፡ የመነኰሳቱ ፡ መንፈሳዊ ፡ ደስታቸው ፡ ስሜት ፡
ሰን ፡ አልነበረውም ፡፡



የደሴቱም ፡ ርዝመት ፡ ከባሕሩ ፡ ጀምሮ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ እስከ ፡ ታነጸበት ፡
እስከ ፡ ጫፉ ፡ ድረስ ፡ በግምት ፡ ፲ ፻ ፡ ሜትር ፡ ያህል ፡ ይሆናል ፡፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡
ይህን ፡ ረጅም ፡ ደሴት ፡ በእግራቸው ፤ ተጕዘው ፡ ምዕራፈ ፡ ጻድቃን ፡ በተባለችው
ቦታ ፡ ጥቂት ፡ ዕረፍት ፡ አድርገዋል ፡፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜም ፡ መነኰ
ሳቱ ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖ ፡ ለብሰው ፡ መስቀልና ፡ ማዕጠንታቸውን ፡ ይዘው ፡ በግራና ፡
በቀኝ ፡ ሆነው ፡ ተቀበሏቸው ፡፡

ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደሱ ፡ ገብተው ፤ ጸሎት ፡ ካደረሱ ፡ በኋላ ፤ ለማረ
ፊያ ፡ በተዘጋጀላቸው ፡ ቦታ ፡ ዕረፍት ፡ አደረጉ ፡፡ ከታኅሣሥ ፡ ፫ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ
ታኅሣሥ ፡ ፳ቀን ፡ ድረስ ፡ አበ ፡ መነኰሳት ፡ እንደመሆናቸው ፤ ለልጆቻቸው ፤ መነኰሳት
በጎ ፡ አርአያ ፡ ሆነውላቸዋል ፡፡

ይኸውም ፡ ቦታን ፡ ለይተው ፡ ለብቻ ፡ በመቀመጥ ፤ ውሎ ፡ አንድ ጊዜ
ለመፍቅደ ፡ ሥጋ ፡ ያህል ፡ በመመገብ ፡ ምግብ ፡ ባለማሻሻል ፡ ጊዜያትን ፡ በማድ
ረስ ፡ ማንኛውንም ፡ የችግር ፡ ፈተና ፤ በመታገሥ ፡ ነው ፡፡

ነገር ፡ ግን ፤ እኛ ፡ የማናውቀው ፡ ከልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ የሚተዋ
ወቁበትን ፡ ውሳጣዊ ፡ ትሩፋት ፡ በዚህ ፡ መጣፍ ፡ ልንገልጸው ፡ ባለመቻላችን ፡
ትተነዋል ፡፡

መነኰሳቱም ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ የወጡበትንና ፡ የወረዱበትን ፡ ጎዳና ፡ ርትዕት ፡
ፍኖቱ ፡ ለባስልዮስ ፡ በሚል ፡ ስም ፡ ሰይመውታል ፡፡ ይኸውም ፡ የናፍቆታቸውንና ፡
የፍቅራቸውን ፡ ብዛት ፡ ያስረዳል ፡፡

## የዳጋ ፡ እስጢፋኖስ ፡ አጭር ፡ ታሪክ ፡፡

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የገዳሙን ፡ ታሪክና ፡ ክብር ፡ በጥቂቱ ፡ እንገልጻለን ፡
ከጥርጥር ፡ በራቀ ፡ አስተዋይ ፡ ልቡና ፡ አስተውል ፡፡

ዳጋ ፡ የተባለው ፡ ገዳም ፡ አቀማመጡ ፡ ትእምርተ ፡ መስቀል ፡ ሆኖ ፡ መካከሉ ፡
ርዝመት ፡ ያለው ፡ ነው ፡፡ ገዳሙን ፡ ያቀኑትም ፡ አባ ፡ ኂሩተ ፡ አምላክ ፡ የሚባሉ ፡
ያዔ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ የወንድም ፡ ልጅ ፡ ናቸው ፡፡

እሊህም ፡ ጻድቅ ፡ ከታላቁ ፡ ጻድቅ ፡ ከአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ጋር ፡
በሐይቅ ፡ ከአባ ፡ ኢየሱስ ፡ ሞዐ ፡ በአንድነት ፡ ሥርዓተ ፡ ምንኵስና ፡ ሲማሩ ፡
ኖረዋል ፡፡

አፄ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፤ አባ ፡ ኢየሱስ ፡ ሞዐን ፡ ለመገናኘት ፡ ሔደው ፡
ሳለ ፤ " አባ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፤ ብለህ ፡ ሹመው ፤ አባ ፡ ኂሩተ ፡
አምላክን ፡ ዐቃቤ ፡ ሰዓት ፡ አድርገው › ፡ ብለው ፡ አባ ፡ ኢየሱስ ፡ ሞዐ ፡ ለአፄ ፡
ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ስለነገሯቸው ፡ ወዲያው ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ በመላዋ
ኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ብለው ፡ ሹመዋቸዋል ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

## አባ ፡ ጊዮርጊስ ፡ አምላክንም ፡ ዐቃቤ ፡ ሰዓት ፡ አድርገዋቸዋል ።

እሊህም ፡ አባ ፡ ጊዮርጊስ ፡ አምላክ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በዐቃቤ ፡ ሰዓትነት ፡
ዕርግ ፡ ካገለገሉ ፡ በኋላ ፤ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ንጹሕ ፡ ኅቤሁ ፡ አፍአ ፡ እም
ዕይት ፡ እንዘ ፡ ንጸውር ፡ ትዕይርቶ ፡ እንዳለ ፡ (ዕብ ፡ ፲፫ ፡ ፲፫) ፡ (በዓለም ፡ በከ
ማ) ፡ ተቀምጦ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከማገልገል ፡ ከከተማ ፡ ወጥቶ ፡ ከሰው ፡
ለይቶ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማገልገል ፡ ይበልጣል ፡ ብለው ፡ ከአፄ ፡ ይኩኖ ፡
ምላክ ፡ የተቀበሉትን ፤ መዓርገ ፡ ሢመት ፡ ንቀው ፡ አቃልለው ፡ አልባሴ ፡ መስ
ው ፡ ተርታ ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ ታቦተ ፡ እስጢፋኖስን ፡ ከሐይቅ ፡ ይዘው ፡
ንዱ ፡ ገዳም ፡ ወደ ፡ ገዳም ፡ ሲዘዋወሩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ዳጋ ፡ ወደተ
ው ፡ ደሴት ፡ ደርሰዋል ፡ ከታንኳም ፡ ወርደው ፡ ዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ምዕራፍየ ፡ ለዓ
ም ፡ ብለው ፡ ጥቂት ፡ ሰዓት ፡ ዕረፍት ፡ አድርገዋል ።
ፉበትም ፡ ቦታ ፡ በማዕርግ ፡ ስማቸው ፡ ዐቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ።

በዚህም ፡ ገዳም ፡ በአብርሀና ፡ በአጽብሐ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በቅድስት ፡
ንግል ፡ ማርያም ፡ ስም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ታንጾበት ፡ ስለነበረ ፤ እሊህ ፡
ቅ ፡ ታቦተ ፡ ማርያምን ፡ እያጠኑ ፡ የተባሕትዎ ፡ ሥራ ፡ እየሠሩ ፡ እስከ ፡
፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ቆይተው ፡ በአፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡
ድ ፡ ታቦተ ፡ ማርያምን ፡ በደቅ ፡ ውስጥ ፡ ኩታ ፡ በሚባለው ፡ ቦታ ፡ ተክ
ል ። ታቦተ ፡ እስጢፋኖስንም ፡ በደሴት ፡ ዳጋ ፤ ተክተው ፡ ገዳሙን ፡ አስገድመዋል ።
ያ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ዳጋ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ተብሎ ፡ ሲጠራ ፡ ይኖራል ።

እሊህም ፡ ጻድቅ ፡ ይህን ፡ ገዳም ፡ ከአቋቋሙ ፡ በኋላ ፡ በብዙ ፡ ገድልና ፡
ፉት ፡ ሰውነታቸውን ፡ አድክመው ፡ «ዘጸመወ ፡ በዓለም ፡ የሐዩ ፡ ለዝሉፉ ፡
በሎ ፡ የተነገረውን ፡ ተስፋ ፡ ሲጠባበቁ ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ አረበን ፡
ሆን ፡ ድዉይ ፡ የመፈወስ ፡ ሀብት ፡ ተሰጥቷቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ተአምራት ፡
ርገዋል ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በጐንደር ፡ የነገሡ ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ ይህን ፡ ገዳም ፡
በኙተው ፡ ሦስት ፡ ሱባዔ ፡ አራት ፡ ሱባዔ ፡ ያህል ፡ ከሰው ፡ ተለይተው ፤ ጸሎት ፡ ያደ
ብት ፡ ነበር ። ገዳሙንም ፡ አምሳለ ፡ ገነት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ይገምቱት ፡ ነበር ፡
ላል ። እሑድ ፡ እሑድ ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ የገነት ፡ ነፋስ ፡ ይነፍስበታል ፡ ይባላል።

ተመልካችም ፡ እንደገመተው ፡ የሚነፍሰው ፡ ነፋስና ፡ አየሩ ፡ በምድራዊ ፡ ዓለም ፡
ሚነፍሰው ፡ ነፋስ ፡ የተለየ ፡ ስሜትን ፡ የሚሰጥ ፡ ነው ። በጐንደርም ፡ የነገሡ ፡
ሥታት ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ዐፅማቸው ፡ በገዳመ ፡ ዳጋ ፡ እንዲቀመጥ ፡ ተስፉ ፡
ርጉ ፡ ስለነበረ ፡ የብዙዎቹ ፡ ነገሥታት ፡ ዐፅም ፡ ይገኝበታል ።

የአፄ ፡ ሱስንዮስ ፤ የአፄ ፡ ፋሲል ፤ የአፄ ፡ ዘርዐ ፡ ያዕቆብ ፤ የአፄ ፡ ዳዊት ፡
ማዊ ፤ የአፄ ፡ አይዙር ፡ ስማቸው ፡ ያልተጻፈ ፡ የሌሎችም ፡ ነገሥታት ፡
ም ፡ ይገኝበታል ።



ይልቁንም ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ የነገሡት ፡ አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ይቀበሉበት ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

ዛሬም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የካቲት ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ገዳሙን ፡ ጐብኝተው ፡ ዐፅመ ፡ ነገሥታቱን ፡ አይተው ፡ የነገሥታቱ ፡ ዐፅም ፡ ያለበትን ፡ ሦስት ፡ ሣጥን ፡ በወርቅ ፡ በተሠራ ፡ አረንጓዴና ፡ ቀይ ፡ ሐር ፡ ልብስ ፡ አልብሰው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑም ፡ በአዲስ ፡ ፕላን ፡ እንዲሠራ ፤ ትእዛዝ ፡ ሰጥተዋል ። ለገዳሙም ፡ ብዙ ፡ እርዳታ ፡ አድርገው ፡ መነኰሳቱንም ፡ እያንዳንዳቸውን ፤ አነጋግረው ፡ የዘጉትን ፡ በሕታውያንም ፡ ጐብኝተው ፡ ተመልሰዋል ።

## ከዳጋ ፡ ወደ ፡ ዘጌ ፡ የብፁዕነታቸው ፡ ጕዞ ።

የገዳሙን ፡ ታሪክና ፡ ውበት ፡ በጥቂቱ ፡ ከገለጽን ፤ እንግዴህ ፡ ወደ ፡ ብፁዕነታቸው ፡ መንፈሳዊ ፡ ሥራ ፡ እንመለስ ።

ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፤ ታኅሣሥ ፤ ፳ ፡ ቀን ፡ በገዳመ ፡ ዳጋ ፡ ለሚገኙት ፡ መነኰሳትና ፡ አርድእት ፡ የልብስና ፡ የገንዘብ ፡ ስጦታ ፡ አድርገው ፡ ለመሰነባበት ፡ በቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በተገኙ ፡ ጊዜ ፤ ብዙ ፡ የዘጉ ፡ በሕታውያንና ፡ አበው ፡ መነኰሳት ፡ ተሰብስበው ፡ ጸሎት ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፤ ብፁዕነታቸው ፡ የመንፈሳዊ ፡ ምክር ፡ አድርገው ፡ የመነኰሳትን ፡ ልቡና ፡ አጽናንተዋል ። እንዲሁም ፡ እኔ ፡ በሥጋዬ ፡ ብለያችሁ ፡ በልቡናዬ ፡ አልለያችሁም ፡ ለአገራችሁና ፡ ለመንግሥታችሁ ፡ እዘኑ ፡ ቸል ፡ አትበሉ» ፡ ብለው ፡ ምዕራገ ፡ ጸሎት ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ እንዲደገም ፡ ካዘዙ ፡ በኋላ ፡ የስንብቱ ፡ ሥርዓት ፡ ተፈጸመ ።

ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ከገዳሙ ፡ ወርደው ፡ ወደባሕሩ ፡ ዳር ፡ እንደደረሱ ፡ ዘብል ፡ የተባለው ፡ የባሕር ፡ ጀልባ ፡ ይጠባበቅ ፡ ስለነበረ ፡ የጐጃሙን ፡ ጳጳስ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ማርቆስንና ፡ ሊቀ ፡ ሊቃውንት ፡ መሐሪን ፡ አስከትለው ፡ በመርከብ ፡ ጕዞ ፡ ጀመሩ ።

አንድ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ እንደተጓዙ ፤ ዘጌ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ የማህል ፡ ዘጌ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ገዳም ፡ ካህናት ፡ በባሕሩ ፡ ዳር ፡ ተሰልፈው ፡ ይጠባበቁ ፡ ስለነበረ ፤ ጀልባው ፡ ወደወደቡ ፡ እንደደረሰ ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ከጀልባው ፡ ወጥተው ፡ ከባሕሩ ፡ ዳር ፡ በአባ ፡ በትረ ፡ ማርያም ፡ ስም ፡ የታነጸውን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጐብኝተው ፡ ማህል ፡ ዘጌ ፡ ጊዮርጊስ ፡ በደረሱ ፤ ጊዜ ፡ ካህናቱ ፡ በክብር ፡ እየዘመሩ ፡ ተቀበሏቸው ።

ብፁዕ ፡ አባታችንም ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ገብተው ፡ ጸሎት ፡ አድርገው ፡ ሲወጡ ፡ ለታቦቱ ፡ ምሉ ፡ አልባሳትና ፡ መጽሐፈ ፡ ቅዳሴ ፡ ሌሎችንም ፡ መጻሕፍት ፡ ጨምረው ፡ ሰጥተዋል ። ለካህናቱም ፡ የገንዘብ ፡ ስጦታ ፡ አድርገዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

ቀጥሎም ፡ የማኅበሩን ፡ ቤት ፡ ጎብኝተዋል ። አንድ ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ በዚሁ ፡ ቦታ ፡ ካሳለፉ ፡ በኋላም ፡ ተመልሰው ፡ በጀልባው ፡ ተሳፍረው ፡ ወደ ፡ ዑራ ፡ ኪዳነ ፡ ምሕረት ፡ ጕዞ ፡ አደረጉ ። ፲፪ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ሲሆን ፡ ከጀልባው ፡ በወረዱ ፡ ጊዜ ፡ የዑራ ፡ ኪዳነ ፡ ምሕረት ፡ መነኰሳትና ፡ ካህናት ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖ ፡ ለብሰው ፡ አክሊልና ፡ የብር ፡ የወርቅ ፡ ከለቻ ፡ በየራሳቸው ፡ ደፍተው ፡ ይጠባበቁ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ አንድ ፡ በአንድ ፡ እየቀረቡ ፡ ከተገናኙ ፡ በኋላ ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ለማረፊያ ፡ ወደ ፡ ተዘጋጀላቸው ፡ ቦታ ፡ ሔደው ፡ በዚያው ፡ አዳር ፡ ሆነ ።

ታኅሣሥ ፡ ፳፩ ፡ ቀን ቅዳሜ ፤ ከሌሊቱ ፡ በ፲ ፡ ሰዓት ፡ ወደ ፡ ዑራ ፡ ኪዳነ ፡ ምሕረት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሔደው ፡ ታቦተ ፡ ማርያምን ፡ ባርከው ፡ ሚሮን ፡ ቀብተው ፡ አስቀድሰው ፡ ሲመጡ ፡ ለታቦቷ ፡ ምሉ ፡ አልባሳትና ፡ መጽሐፈ ፡ ቅዳሴ ፤ ሌሎችንም ፡ መጻሕፍት ፡ ጨምረው ፡ ሰጥተዋል ፡ ለካህናቱ ፡ ለድኆችም ፡ የገንዘብ ፡ ስጦታ ፡ አድርገዋል ።

አራት ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ሲሆን ፡ ወደ ፡ ዕቃቤቱ ፡ ገብተው ፡ ለዓይን ፡ ድንቅ ፡ ድንቅ ፡ የሚሆኑ ፡ ዘውዶችና ፡ ዕቃዎቹን ፡ ታላላቅ ፡ መጻሕፍቶችንና ፡ አልባሳቶ ቶን ፡ ጐብኝተዋል ።

ይህንም ፡ አይተው ፡ ዑራ ፡ ኪዳነ ፡ ምሕረት ፡ በዘውድና ፡ በከለቻ ፡ በአክሊ ም ፡ በአልባሳትም ፡ በመጻሕፍትም ፡ ብዛት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ከአሉት ፡ ዳማትና ፡ አድባራት ፡ አንደኛ ፡ መሆኗን ፡ ብፁዕነታቸው ፡ ተገንዝበታል ።

፭ ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ወደ ፡ ኡጋንዳ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ጕዞ ፡ አደረጉ ። ብፁዕነታቸው ፡ ጕዞ ፡ በእግር ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ የቡናው ፡ ቅጠልና ፡ ፍሬ ፡ እንደ ላ ፡ ሆኖላቸው ፡ የፀሐይ ፡ መከለያ ፡ ጥላ ፡ አስፈላጊ ፡ አልሆነም ።

ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ የምድሩን ፡ መባረክና ፡ የቡናውን ፡ ውበት ፤ የዛፉን ፡ ርዝ ት ፡ እያዩ ፡ በማድነቅ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፤ ያህል ፡ በእግር ፡ ሲጓዙ ፡ ድካም ፡ አል ሰማቸውም ፡ ነበር ።

ኡጋንዳ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ መነኰሳቱና ፡ ካህናቱ ፡ እየዘመሩ ፡ ተቀበሏቸው ። ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ገብተው ፡ ጸሎት ፡ አድር ሰው ፡ ሲወጡ ፡ ለታቦቱ ፡ ምሉ ፡ አልባሳትና ፡ አንድ ፡ መጽሐፈ ፡ ቅዳሴ ፡ ሌሎ ችንም ፡ የሃይማኖት ፡ መጻሕፍት ፡ ጨምረው ፡ ሰጥተዋል ። ለመነኰሳቱና ፡ ለካ ህናቱም ፡ የገንዘብ ፡ ስጦታ ፡ አድርገውላቸዋል ።

ቀጥሎም ፡ የማኅበር ፡ ቤቱን ፡ ጐብኝተው ፡ ሲወጡ ፡ ለድኆች ፡ የገንዘብ ፡ ስጦታ ፡ አድርገዋል ።

፲ ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ አዝዋ ፡ ማርያምን ፡ ለመጐብኘት ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ር ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ካህናቱ ፡ በዝማሬ ፡ ሕዝቡ ፡ በእልልታና ፡ በሆታ ፡ ተቀ ቸው ።



ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡ ጸሎት ፡ አድርሰው ፡ ሲወጡ ፡ ለካህናቱና ፡ ለታቦቷ ፡ ስጦታ ፡ አድርገዋል ።

ታኅሣሥ ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ እሑድ ፡ በዓለ ፡ ማርያም ፡ የሚከበርበት ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ ነበረ ፤ በዚያው ፡ ቀን ፡ ፲፩ ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ወደ ፡ ክብራን ፡ ገብርኤል ፡ ለመ ሔድ ፡ በጀልባ ፡ ተሳፍረው ፡ ፲፪ ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ወደገዳሙ ፡ ደረሱ ። ገዳሙም ፡ ከመት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ የሚቀደስበት ፡ የጽሙና ፡ ቦታ ፡ ስለሆነ ፤ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ ገዳማት ፡ በከበሮ ፡ በጸናጽል ፡ እያሸበሸቡ ፡ በእጃቸው ፡ እያጨበጨቡ ፡ የሚቀበሉ ፡ ካህናት ፡ አልተገኙም ።

ነገር ፡ ግን ፤ ሰዎች ፡ ባይገኙም ፡ በውስጡ ፡ የሚገኙ ፡ እንስርት ፡ ሰልፍ ፡ ሠርተው ፡ ክንፍ ፡ ለክንፍ ፡ ሲያንገዋብቡ ፡ ላያቸው ፡ ሰው ፡ በአየር ፡ ኃይል ፡ ትም ህርት ፡ ቤት ፡ በደንብ ፡ ተምረው ፡ በታላቁ ፡ በዓል ፡ በ፳፭ኛው ፡ የግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይል ፡ ሥላሴ ፡ የዘውድ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በተከበረበት ፡ ቀን ፡ ሰልፍ ፡ ሠርተው ፡ ክንፍ ፡ ለክንፍ ፡ ገጥመው ፡ እያንገዋበቡ ፡ ለበዓሉ ፡ ተካፋይ ፡ ሆነው ፡ የዋሉትን ፡ አውሮፕላኖች ፡ ይመስሉ ፡ ነበረ ።

በእውነቱ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በቦታው ፡ ተገኝቶ ፡ ላያቸው ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ሰዎች ፡ ፈንታ ፡ እንስርት ፡ ብፁዕነታቸውን ፡ በሰልፍ ፡ ተቀበሉ ፡ ማለት ፡ የሚ ያሳፍር ፡ መስሎ ፡ አይታየም ።

ትንቢትም ፡ የሚፈጸም ፡ በየጊዜው ፡ ተስማሚ ፡ ነገር ፡ ሲገጥመው ፡ ስለሆነ ፤ ቅዱስ ፡ ዳዊት ፡ (ወኵሎ ፡ አግረርከ ፡ ሎቱ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ፡ አዕዋፈ ፡ ሰማይኒ ፡ ወዓሣተ ፡ ባሕር ፡ ወዘኒ ፤ የሐውር ፡ ውስተ ፡ ፍኖተ ፡ ባሕር) ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ትንቢት ፡ ለብፁዕነታቸው ፡ ተደረገ ፡ ሊባል ፡ ተችሏል ።

ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ከጀልባው ፡ ወርደው ፡ አቀበቱን ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክር ስቲያኑ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ ሥራና ፡ በኖራ ፡ ብቻ ፡ የተሠሩትን ፡ አዕማዶች ፡ ተመልክተው ፡ በአንክሮ ፡ ብዙ ፡ ደቂቃዎች ፡ አሳልፈዋል ።

በገዳሙም ፡ ውስጥ ፡ ሥውራን ፡ ባሕታውያን ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ወጣንያን ፡ መነኰሳት ፡ ስለ ፡ ማይገኙበት ፤ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ርእሰ ፡ ባሕታውያን ፡ እንደ ፡ መሆና ቸው ፡ ዳዋውን ፤ አስጥሰው ፡ በዛፍ ፡ ሥር ፡ ድንኳን ፡ አስተክለው ፤ ጸሎት ፡ ሲያ ደርሱ ፡ ካደሩ ፡ በኋላ ፤ ከሌሊቱ ፡ ፲ ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ገብተው ፡ ታቦቱን ፡ ባርከው ፡ ሲነጋ ፡ ጸሎተ ፡ ቅዳሴው ፡ እንደ ፡ ተፈጸመ ፤ ዑደት ፡ ተደርጎ ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ በበዓሉ ፡ ለተገኙ ፡ መነኰሳትና ፡ ባሕታውያን ፡ ምዕዳን ፡ አድርገው ፡ የበዓሉ ፍጻሜ ፡ ሆነ ።

## የገዳመ ፡ ክብራን ፡ ገብርኤል ፡ አጭር ፡ ታሪክ ።

የገዳመ ፡ ዳጋን ፡ ክብርና ፡ ታሪክ ፡ በአለፈው ፡ ሀምድ ፡ እንዳስረዳን ፤ የገ ዳመ ፡ ክብራን ፡ ገብርኤልንም ፡ ክብርና ፡ ታሪክ ፡ በሚከተሉት ፡ መሥመሮች ፡ ለአ ንባቢዎች ፡ ስንገልጽላቸው ፡ በማስተዋል ፡ እንዲመለከቱት ፡ እናሳስባቸዋለን ።

www.ethiopianorthodox.org

ገዳሙን ፡ የመሠረቱት ፡ አቡነ ፡ ዘዮሐንስ ፡ የሚባሉ፡ ቀኖጥራቸው ፡ ከሀገር፡ከዋክብት፡ ?ሚሆን ፤ አገራቸው ፡ መርሐ ፡ ቤቴ ፡ የሆነ ፡ ጻድቅ ፡ የደቅ ፡ ገዳማትን ፡ ሲጐበኙ ፡ በፈ ቃደ ፡ አምላክ ፡ በደራ ፡ አውራጃ ሮቢት ፡ በእቃ ፡ ወደምትባል ፡ አገር ፡ ደርሰው፡ ?ሚጠጉበት ፡ ቦታ ፡ አጥተው ፡ ሲያዝኑ ፤ ዘገብርኤልና ፡ መስቀል ፡ ክብራን፡ የሚ ባሉ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ተቀብለዋቸዋል ።

እሊህም ፡ ሰዎች ፡ ዓሣ ፡ በመውገር ፡ ብቻ ፡ የሚተዳደሩ፡ ድኆች ፡ ስለነበሩ፤ ብዙ ፡ ወራቶችን ፡ ከእነሱ ፡ ጋር ፡ ሊያሳልፉ ፡ ባለመውደዳቸው ፡ ባልና ፡ ሚስቱ፡ በታ ላኳ ፡ አሳፍረው ፡ ወደ ፡ ደሴቱ ፡ አድርሰዋቸው ፡ ተመልሰዋል ።

ጻድቁም ፡ ቡራኬ ፡ አድርገውላቸው ፡ ከተለዩዋቸው ፡ በኋላ ፡ ዘንዶና ፡ የባሕር ፡ ራዊት ፡ ሁሉ ፡ አንሥተው ፡ ሊውጧቸው ፡ ሲሽቀዳደሙ ፡ ቢያማትቡባቸው ፡ ሉም ፡ እየተሰነጠቁ ፡ አልቀዋል ።

ከጥቂት ፡ ወራት ፡ በኋላም ፡ ዘገብርኤልና ፡ መስቀል ፡ ክብራ ፡ ሙተው ፡ እንደሆነ፡ ንቀብራቸው ፤ በሕይወተ ፡ ሥጋም ፡ እንዳሉ ፡ ሳንጠይቃቸው ፡ ብለው ፡ ቢሔዱ ፤ አንዲት ፡ ዋሻ ፡ ውስጥ ፤ እንደ ፡ ዓምድ ፡ ተተክለው ፡ አግኝተዋቸዋል ።

ጻድቁም ፡ ከበዐታቸው ፡ ወጥተው ፡ ቡራኬ ፡ አድርገውላቸው ፡ ሲሰነባበቱ ፤ ንቢት ፡ ተናግረዋል ። «በዚህ ፡ ደሴት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይታነጻል ፤ ታቦቱ ፡ እን ስምህ ፡ በቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ስም ፡ ይሰየማል ። ቦታው ፤ በሚስትህ ፡ ስም ፡ ክብ ን ፡ ይባላል ፡ ጠቅላላው ፡ ክብራን ፡ ገብርኤል ፡ ይባላል ፡ ከዛሬ ፡ በቀር ፡ የሴት፡እግር፤ ህን ፡ ቦታ ፡ አይረግጠውም» ፡ ብለው ፡ ከነገሯቸው ፡ በኋላ ፡ ተባርከው ፡ ወደቦታ ው ፡ ተመልሰዋል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ በዘመነ ፡ መንግሥታ ው ፡ በጻድቁ ፡ አስተዋሺነት ፡ በዚህ ፡ ደሴት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠርተው ፡ ጨርሱ ፡ እንደ ፡ ጻድቁ ፡ ትንቢት ፡ ታቦተ ፡ ገብርኤልን ፡ አግብተው ፡ የገዳሙን፡ ም ፡ ክብራን ፡ ገብርኤል ፡ ብለው ፡ ሰይመውታል ። እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ በዚህ፡ ም ፡ ይጠራል ።

ኋላም ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ኢያሱ ፡ ዛሬ ፡ የሚገኘውን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡ ልዩ፡ አሠራር ፡ ሠርተውት ፡ ገዳሙን ፡ አጽንተውታል ።

ጻድቁ ፡ አቡነ፡ ዘዮሐንስ ፡ ከዛሬ ፡ በቀር ፡ ይህ ፡ ቦታ ፡ የሴት ፡ እግር፡ አይረግ ውም ፡ ብለው ፡ የተናገሩት ፡ ትንቢት ፡ ስለመፈጸሙ ፤ ጻድቂቱ ፡ ንግሥት፡እቴጌ፡ ንትዋብ ፡ ገዳማቱንና ፡ አድባራቱን ፡ መጐብኘት ፡ ይወዱ ፡ ስለነበረ ፤ ክብራን ፡ ገብርኤልን ፡ ለመጐብኘት ፡ ብዙ ፡ ሠራዊት ፡ አስከትለው ፡ በጀልባ ፡ ተሣፍረው፡ወደ ፡ ደቡ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ከጀልባ ፡ ወርደው ፡ የብሱን ፡ ሲረግጡ ፡ ያለጊዜው ፡ ደም፡ ለመታቸው ፡ ተመልሰው ፡ በጀልባ ፡ ተሣፍረው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥታቸው ፡ ደዋል ።

ይህም ፡ መደረጉ ፡ ጻድቁ ፡ ይህን ፡ ቦታ ፡ ከዛሬ ፡ በቀር ፡ የሴት ፡ እግር ፡ ይረግጠውም ፡ ብለው ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ፡ እንዳይታበል ፡ የጻድቁን ፡ ክብር ፡



ለመግለጽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በዚያች ፡ ጻድቅት ፡ ንግሥት ፡ እግር ፡ ቢረገጥ ፡ ገዳሙ ፡ የሚረክስ ፡ ሆኖ አይደለም ።

ይህማ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ሐዋርያው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ በክርስ ቶስ ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ይታበላልን ? ፡ አይታበልም ።

ጻድቁ ፡ ግን ፡ ሴት ፡ ወደገዳሙ ፡ እንዳትገባ ፡ መከልከላቸው፡በዕድሜ ፡ ሕፃናት ፡ የሆኑ ፡ መነኰሳት ፡ በድንግልና ፡ ፈጣሪያቸውን ፡ አገልግለው፡የድካማቸውን ፡ ዋጋ፡ ለማግኘት ፡ ሲሉ ፡ ወደገዳሙ ፡ ገብተው ፡ ሰውነታቸውን ፡ ለእግዚአብሔር፡የተቀደሰ ፡ መሥዋዕት ፡ አድርገው ፤ ዋጋቸውን ፡ በሚያገኙበት ፡ ጊዜ ፡ ሰይጣን ፡ በዝሙት፡ጾር፡ የሚዋጋቸው ፡ ስለሆነ ፤ «ወለንዑሳትሰ ፡ መበለታት ፡ ተገኅሦን ፡ ሰበ ፡ ፈግዓ ፡ሳዕለ ፡ ክርስቶስ ፡ ወይፈቅድ ፡ ይግብአ ፡ ለአውስቦ ፡ ባለው ፡ መሠረት ፡ (፩ ፡ ጢሞ፡፭-፲፩)።

ሴቶችን ፡ ከማየት ፡ እንዲርቁና ፡ እንዲጠበቁ ፡ እንጂ ፡ ሴቶችን ፡ ከክብር ፡ ለማሳነስ ፡ አይመስልም ።

## የገዳመ ፡ ናርጋ ፡ ታሪክ ።

ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ የገዳመ ፡ ናርጋን ፡ ታሪክ ፡ በጥቂቱ ፡ እንገልጻለንና ፡ በዓ ይነ ፡ ልቡና ፡ አስተውሉ ።

ገዳመ ፡ ናርጋ ፡ በዳጋ ፡ አጠገብ ፡ በሚገኘው ፡ ደቅ ፡ በሚባለው ፡ አገር፡ክፍል፡ ሆኖ ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ በባሕር ፡ የተከበበ ፡ ነው ። የደቅ ፡ ሕዝብ ፡ የሚገባበት፡ በአንድ ፡ ወገን ፡ ባሕሩ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ተከፍሎ ፡ ጠባብ ፡ በር ፡ አለ ። ደቅ ፡ በመ ላው ፡ በባሕር ፡ የተከበበ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ገዳም ፡ መጀመሪያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያነጹ ፡ እቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ ናቸው ። ሥራውንም፡ በማየት ፡ እንጂ ፡ በመስማት ፡ ልቡና ፡ ሊረዳው ፡ አይችልም ። የመቅደሱ ፡ በር ፡ ሦስት ፡ ነው ።

መቅደሱ ፡ በሦስት ፡ አዕማድ ፡ ተለይቷል ፤ መንበሩም ፡ እንደዛሬው ፡ዘመን ፡ ለሥራ ፡ የሚመች ፡ መንበር ፡ ነው ። በመቅደሱ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ሦስትና ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ያላቸው ፡ መጻሕፍት ፡ እንደአሸዋ ፡ ተቆልለው ፡ በብ ዛት ፡ ይገኙበታል ።

በመቅደሱም ፡ ዙሪያ ፤ ያለው ፡ ሥዕል ፡ ከዛሬው ፡ ዘመን ፡ ሥዕል ፤ ብልጫ ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ።

በጠቅላላው ፡ ማንኛውንም ፡ ሥራ ፡ ሲመለከቱት ፡ ኢትዮጵያ ፡ በሥልጣኔ ፤ ቀዳሚነት ፡ እንዳላት ፡ ያስረዳል ።

እሊህም ፡ ደግ ፡ ንግሥት ፡ በዚህ ፡ ቦታ፡ ላይ ፡ ጸሎት ፡ አድርሰው ፡ ዐር ፈው ፡ ሳለ ፡ በስመ ፡ ሥላሴ ፡ በዚህ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዲያንጹ ራእይ ፡ አይተዋል ።

ወዲያው ፡ ልጃቸውን ፡ (ዓለም ፡ ሰገድ) ፡ ብርሃን ፡ ሰገድ ፡ ኢያሱን ፡ ጠርተው፡ ሕንጻ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ በዚህ ፡ ቦታ፡ ላይ ፡ እናድርግ፡ብለው ፡ ቢጠይቋቸው፡

www.ethiopianorthodox.org

ናድርጋ ፡ እናድርጋ ፡ ተባብለው ፡ በዚህ ፡ ናርጋ ፡ ሥላሴ ፡ ተብሏል ። ወዲያው ፡
ት ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሲፈጸም ፡ ገዳሙን ፡ ገድመው ፡ ከገዳመ ፡ ዳጋ ፡ እንዳይለያይ ፡ ናር
ና ፡ ዳጋ ፡ ነፍስና ፡ ሥጋ ፡ የሚል ፡ ማኅተም ፡ ሰጥተው ፡ አጽንተውታል ።

## ልዩ ፡ አስተያየት ።

እነሆ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የባሕሩን ፡ ውበት ፡ የአየሩን ፡
ግብነትና ፡ ተስማሚነት ፡ ጽፈንላችኋል ። ፡ ይህ ፡ ከሆነ ፡ የኢትዮጵያ ፡
ላላቅ ፡ ሰዎች ፡ አየር ፡ ለመቀበል ፡ እያሉ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ እየከፈሉ ፡
ደ ፡ ውጪ ፡ አገር ፡ የሚሔዱ ፡ ስለምን ፡ ይሆን ? እንደእኛ ፡ አስተያየት ፡ የአዳም ፡
ጆች ፡ በመሆናቸው ፡ ብቻ ፡ ይመስለናል ። አዳም ፤ በገነት ፡ ሳለ ፡ የበለጠ ፡ የሚያ
ኝ ፡ መስሎት ፡ የማይገባውን ፡ ሲሻ ፡ እንደተገኘ ፡ እነሱም ፡ የበለጠ ፡ እናገኝ ፡
ስሏቸው ፡ ይሆናል ።

ነገር ፡ ግን ፤ ዛሬ ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ስፌ ፡ አስተያየት ፡ የባሕር ፡
፡ ከተማነት ፡ ስለተቋቋመ ፤ ማንኛውም ፡ አየርን ፡ የሚፈልግ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሁሉ
ግርና ፡ ከወተት ፡ የሚጣፍጥ ፡ የጣናን ፡ ባሕር ፡ እየጠጣ ፤ ዓሣውን ፡ እየተመገበ ፤
ሩውንም ፡ አየር ፡ እየተቀበለ ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜውን ፡ በዚያ ፡ እንዲያሳልፍ ፡ የማይ
ረጠር ፡ ነው ።

በዚያውስ ፡ ላይ ፤ ቅቤውና ፡ ማሩ ፡ ሰንጋውና ፡ ሙክቱ ፡ ቡናውም ፡ በጥቂት ፡ ዋጋ ፡
ሚገኝበትን ፡ አገር ፡ ትቶ ፡ በየቀኑ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ እየከፈለ ፡ አየር ፡ እቀበላለሁ
ሎ ፡ ወደውጪ ፡ አገር ፡ የሚሔድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ይገኝ ፡ ይመስላችኋልን ? አይገ
ም ፡ ይልቁንስ ፡ ወንድሞቻችን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደገለጽንላችሁ ፡ በማናቸውም ፡
ከንያት ፡ ወደዚህ ፡ ቦታ ፡ መሠማራታችሁ ፡ የማይቀር ፡ ነውና ፡ ቦታ ፡ ለመመረት ፡
ድትሽቀዳደሙ ፡ እናሳስባችኋለን ።

## የብፁዕነታቸው ፡ ደብረ ፡ ማርያምን ፡ መጐብኘት ።

እንግዴህ ፡ ቀድሞ ፡ ወደጀመርነው ፡ ወደብፁዕነታቸው ፡ ሥራ ፡ እንመለስ ።
ፁዕ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ በጌምድር ፡ አውራጃ ፡
ትገኘውን ፡ ገዳም ፡ ደብረ ፡ ማርያምን ፡ ለመጐብኘት ፡ በጀልባ ፡ ተሳፍረው ፡ አንድ ፡
ት ፡ ያህል ፡ በጣናና ፡ በዓባይ ፡ መለያያ ፡ አጠገብ ፡ እንደተጓዙ ፡ ስድስት ፡ ሰዓት ፡
ሆን ፡ ከጀልባው ፡ ወርደው ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፤ ገዳሚቱ ፡ ብዙ ፡
ች ፡ የማይገኙባት ፡ ጠፍ ፡ በመሆኗ ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ እየቀረቡ ፡ በረከት ፡ ተቀ
።

ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደሱ ፡ ገብተው ፡ ጸሎት ፡ አድርሰው ፡ ጽላ
፡ ባርከው ፡ ገድለ ፡ ታዴዎስ ፡ ዘጽላልሽን ፡ ሲያስነብቡ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ከቆዩ ፡
ላ ፤ ለካህናቱ ፡ ችሮታ ፡ አድርገውላቸዋል ፤ ለታቦቱም ፡ እንደተለመደው ፡ መርጃ ፤
ተዋል ።



ይህችንም ፡ ገዳም ፡ ያቀኗት ፡ አቡነ ፡ ታዴዎስ ፡ ዘጽላልሽ ፡ ናቸው ። የቀደመ ፡
ስሟ ፡ ደብረ ፡ ደቆን ፡ ነው ። ብዙ ፡ መንፈሳዊ ፡ ሥራ ፡ እንደተሠራባት ፡ ገድሉ ፡ አስረድቶናል ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ስምንት ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ በመጡበት ፡
ጀልባ ፡ ተሳፍረው ፡ በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ወደማረፊያ ፡ ቤት ፡ ደርሰው ፡ ዕረፍት ፡
አድርገዋል ።

በጠቅላላው ፡ እስከ ፡ ጥር ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ መን
ፈሳዊ ፡ ጉዳይ ፡ ሲፈጽሙ ፡ ሰንብተው ፡ ጥር ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ረቡዕ ፡ ከሰዓት ፡
(በኋላ) ፡ በላይ ፡ ከባሕር ፡ ዳር ፡ በኢትዮጵያ ፡ አየር ፡ መንገድ ፡ ተሳፍረው ፡ ብፁዕ ፡
አቡነ ፡ ማርቆስንና ፡ ሊቀ ፡ ሊቃውንት ፡ መሐሪ ፡ ትርፌን ፡ አስከትለው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡
በደረሱ ፡ ጊዜ ፤ ብዙ ፡ ብፁዓን ፡ ጳጳሳትና ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡
በአይሮፕላኑ ፡ ጣቢያ ፡ ተገኝተው ፡ ተቀብለዋቸዋል ።
በዚሁ ፡ ቀን ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንፈሳዊ ፡ አባት ፡ ብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡነ ፡
ባስልዮስን ፡ በቸርነቱ ፡ አቅፎ ፡ ደግፎ ፡ ለመለሰ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የኢትዮጵያ ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ምስጋና ፡ አቅርባለች ።

---

## ከዕጨጌነት ፡ ወደ ፡ ጵጵስና ፡
## እንዲሁም ፡ ሢመተ ፡ ጳጳሳት ፡ ኢትዮጵያውያን ።

የኢትዮጵያና ፡ የእስክንድርያ ፡ (የሁለቱ) ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ጉዳይ ፡ በስም
ምነት ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፤ የሢመተ ፡ ጵጵስና ፡ መዓርግ ፡ ለመቀበል ፡ አምስቱ ፡ ብፁ
ዓን ፡ አባቶቻችን ፡ ብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፤ መምህር ፡ ገሪማና ፡ ሊቀ ፡
ሥልጣናት ፡ መልእክቱ ፤ መምህር ፡ ዘፈረ ፡ ብርሃንና ፡ መምህር ፡ ጌታሁን ፡ ሐምሌ ፡
፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ዐርብ ፡ ከጧቱ ፡ በ፩ ፡ ሰዓት ፡ ከ፲ ፡ ደቂቃ ፡ ከአዲስ ፡
አበባ ፡ ተነሥተው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያየር ፡ መንገድ ፡ ተጕዘው ፡ በ፲፩ ፡ ሰዓት ፡ ካይሮ ፡
ቡ ። ያየሩም ፡ መንገድ ፡ በአሥመራና ፡ በሉክሶር ፡ ላይ ፡ ነበር ።

ብፁዓን ፡ አባቶቻችን ፡ ካይሮ ፡ ፋሩክ ፡ ፊልድ ፡ ላይ ፡ ከአውሮፕላን ፡ ሲወርዱ ፡
በካይሮ ፡ ያሉት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሚኒስትር ፡ ክቡር ፡ ፊታውራሪ ፡ ታፈሰ ፤ ክቡር ፡ ሳባ
ሐበሺ ፡ ፓሻና ፡ ቆሞስ ፡ ኢብራሂም ፡ ሉቃስ ፡ የፓትርያርኩ ፡ መልክተኞችና ፡ ጳጳ
ሳት ፤ ሌሎችም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወዳጆች ፡ ደስ ፡ በሚያሰኝ ፡ አኳ
ኋን ፡ ተቀበሏቸው ። ፋሩክ ፡ ፊልድ ፡ የተባለው ፡ የአኤሮፕላን ፡ ጣቢያ ፡ ከካይሮ ፡
ወደምሥራቅ ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ የሚገኝ ፡ ትልቅ ፡ ጣቢያ ፡ ነው ። ባለፈው ፡ በትልቁ ፡
የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ አሜሪካኖች ፡ ሠርተውት ፡ ለጦርነት ፡ ሲያገለግል ፡ ሳለ ፤
ፒን ፡ ፊልድ ፡ እየተባለ ፡ ይጠራ ፡ ነበር ። ጦርነቱ ፡ እንዳለቀ ፡ የግብጽ ፡ መንግሥት ፡
በብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ስለገዛው ፤ በንጉሡ ፡ ስም ፡ ፋሩክ ፡ ፊልድ ፡ እየተባለ ፡ ይጠራ ፡
ጀመር ። ኢትዮጵያውያኑ ፡ ብፁዓን ፡ አባቶች ፡ በተቀባዮቻቸው ፡ ታጅበው ፡ ካይሮ ፡
ከተማ ፡ እንደገቡ ፤ መጀመሪያ ፡ ወደበትረ ፡ ክናው ፡ ሔደው ፡ ለብፁዕ ፡ ፓትርያርክ
ለአቡነ ፡ ዮሳብ ፡ ሰላምታ ፡ አቀረቡ ። ፓትረያርኩም ፡ በደስታ ፡ ተቀብለው ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡
ከነጋገሩዋቸው ፡ በኋላ ፡ ተሰናብተው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሌጋስዮን ፡ ወደተዘጋጀው ፡ ሥፍራ ፡ ሔዱ ።

www.ethiopianorthodox.org

ብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስና ፡ ብላታ ፡ መርስዔ ፡ ኀዘንም ፡ በዚሁ ፡ ቀን ፡ ወደማታ ፡ በአብዲን ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ በጐብኝዎች ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ስማቸውን ጽፈው ፡ ተመለሱ ።

## የፓትርያርኩ ፡ ሽልማት ።

የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ለሃይማኖት ፡ አባቶቻቸው ፡ ለእስክንድርያ ፡ ፓትርያ ርኮች ፡ ሽልማት ፡ መስጠት ፡ ልማዳቸው ፡ ነው ። በየጊዜው ፡ ለፓትርያርኮቹ ፡ የተላ ኩት ፡ ሽልማቶች ፡ በመስተዋት ፡ ውስጥ ፡ እየሆኑ ፡ ለመታሰቢያነት ፡ በበትረከናው ፡ ተቀምጠው ፡ ይታያሉ ። እንደዚሁ ፡ ሁሉ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ፡ ሥላሴ፡ለብፁዕ ፡ ፓትርያርክ ፡ ለአቡነ ፡ ዮሳብ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ሽል ማት ፡ የወርቅ ፡ ላንቃና ፡ የሥላሴን ፡ ኮርዶን ፡ ኒሻን ፡ ልከውላቸው ፡ ነበረና ፤ ክቡር ፊታውራሪ ፡ ታፈሰ ፡ ይኸንኑ ፡ ሽልማት ፡ ለማስረከብ ፡ ሐምሌ ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ቀዳሜ ፡ በ፱ ፡ ሰዓት ፡ በቀጠሮ ፡ ወደበትረከናው ፡ ሔዱ ። በትረ ፡ ከናው ፡ በግብጽና ፡ በኢት ዮጵያ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ አጊጦ ፡ ነበር ። ፓትርያርኩም ፡ ከጳጳሳትና ፡ ከታላ ላቅ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ ተቀበሏቸው ። ሽልማቱን ፡ አቅርበው ፡ ባስረከቡ ፡ ጊዜ ፡ ዕድሜ ፡ ያደረጉት ፡ አባታችን ፡ ብፁዕ ፡ ፓትርያርክ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ስላላቸው ፡ ወዲያውኑ ፡ ላንቃውን ፡ ለብሰው ፡ ኒሻኑን ፡ አድርገው ፡ ፎቶግራፍ ፡ ተነሡ ። ካሁን ፊትም ፡ በ፲፱፻፳፪ና–፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጥተው ፡ ሳሉ ፤ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በየጊዜው ፡ ተቀብለዋቸው ፡ የነበሩትን ፡ ኒሻኖች ፡ ባለኮርዶን ፡ የኢ ትዮጵያ ፡ ኮከብና ፡ የዳግማዊ ፡ ምኒልክን ፡ ኒሻን ፡ አቅርበው ፡ ለሕዝቡ ፡ እያሳዩ ፡ ደስታ ውን ፡ ገለጹ ። በመጨረሻውም ፡ ቡራኬ ፡ ሰጥተው ፡ እንግዶቹን ፡ አሰናበቱ ።

## አስኬማዊ ፡ ሥርዓት ።

አስኬማ ፡ ማለት ፡ ከመጽሐፈ ፡ ምንኵስና ፡ ከሚገኙት ፡ ከሦስቱ ፡ የምንኵስና ዓርጎች ፡ አንደኛው ፡ ነው ። ፫ቱም ፡ መዓርጋት ፡ ቆብ ፡ ቅናት ፡ አስኬማ ፡ ናቸው ። ይህንም፡መጽሐፉ ፡ቆብዕ ፡ ዘ፫ቱ ፡ ደቂቅ ፤ ቅናት ፡ ዘዮሐንስ ፡ መጥምቅ፡አስኬማ፡ ዘኤ ያስ ፡ ብሎ ፡ ይደለድላቸዋል ። መምህራን ፡ ግን ፡ ቆብዕን ፡ በአክሊለ ፡ ሦክ ፤ ቅናትን ሐብለ ፡ ተቀስፎ ፤ አስኬማን ፡ በንጽሐ ፡ መላእክት ፡ መስለው ፡ ይናገሩዋቸዋል ። አስ ማ ፡ ከልዝብ ፡ ባሕረ ፡ ዓረብ ፡ ተሠርቶ ፡ ትእምርተ ፡ መስቀል ፡ አልፎ ፡ አልፎ ታቶበት ፡ ይገኛል ። በሀገራችንም ፡ የደብረ ፡ ዳሞና ፡ የአክሱም ፡ መነኰሳት ፡ አስኬማ ን ፡ ከክር ፡ ወይም ፡ ከባሕር ፡ ዓረብ ፡ እያማመሩ ፡ ይሠሩታል ። ሐምሌ ፡ ፲፯ ፡ ቀን ዳሜ ፡ ብፁዕ ፡ ፓትርያርኩ ፡ ለጳጳሳት ፤ የሚገባውን ፡ የአስኬማ ፡ ጸሎት ፡ የሚያደርሱ ሆን ፤ በ፱ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ወደበትረከናው ፡ ሔዱ ። ወደዚያም ፡ ሲደርሱ ፡ የደስታ ል ፡ ተደወለ ። ጳጳሳትና ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ በበር ፡ ላይ ፡ ጠብቀው ፡ ተቀበሏቸ ና ፡ ወደማረፊያው ፡ ወሰዱዋቸው ። ከጥቂት ፡ ደቂቃ ፡ በኋላ ፡ በልብሰ ፡ ተክህኖ ጡ ፡ ፲፯ ዲያቆናት ፡ መጥተው ፡ በቀኝና ፡ በግራ ፡ ተሰለፉ ። ብፁዕ ፡ ፓትርያርክ ሳቱን ፡ አስከትለው ፡ ወደዲያቆናቱ ፡ መካከል ፡ ሲደርሱ ፡ የኛም ፡ አባቶች ፡ እጅ ፡ ነሥ



ተው ፡ ተገናኙ ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ዲያቆናቱ ፡ በዜማ ፡ እየዘመሩ ፡ አጅበዋቸው ፡ ወደ ቤተ፡ክርስቲያን፡ገቡ ።ቤተ ፡ክርስቲያኑ፡በኤሌክትሪክ፡ብርሃን ፡አንጸባርቆና፡ ደምቆ ፡ ነበር። የአስኬማን ፡ ሥርዓት ፡ ለማየት ፡ የተሰበሰበውም ፡ ሕዝብ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ነበር ።

ፓትርያርኩ ፡ በመንበራቸው ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ የአስኬማውን ፡ ጸሎት ፡ ሲጀምሩ ፡ የጵጵስና ፡ ማዕርግ ፡ የሚቀበሉት ፡ ጳጳሳት ፡ በወለሉ ፡ ላይ ፡ በወንበር ፡ ተራ ፡ በተራ ፡ ተቀመጡ ። ከገዳመ ፡ ሱርያን ፡ የመጣ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ መነኵሴ ፡ በዚሁ ቀን ፡ ጵጵስና ፡ እንዲቀበል ፡ ተደርጎ ፡ ኖሮ ፡ ከአምስቱ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ጳጳሳት ፡ ጋር ፡ ስድስተኛ ፡ ሆኖ ፡ ተቀመጠ ።

ፓትርያርኩ ፡ የስድስቱን ፡ ጳጳሳት ፡ ስምና ፡ የሀገረ ፡ ስብከታቸውን ፡ ስም ፡ እየ ጠሩ ፡ ረጅም ፡ ጸሎት ፡ አድርገው ፡ ከባረኩዋቸው ፡ በኋላ ፤ አስኬማውን ፡ ለያንዳንዳ ቸው ፡ አጠለቁላቸው ፤ አምስቱ ፡ የኛ ፡ ጳጳሳት ፡ ገና ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ሳሉ ፡ የታሰበ ላቸውና ፡ እነሱ ጭምር ፡ በጸሎት ፡ የመረጡት ፡ ስም ፡ ስለነበረ ፡ ለፓትርያርኩ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ተነገራቸውና ፡ በዚያው ፡ ስም ፡ ሰየሟቸው ፡ ይኸውም ፡ እንደሚከ ተለው ፡ ነው ።



ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ባራቱ ፡ ጳጳሳት ፡ መካከል ፡ ይታያሉ ።

፩ኛ/ ፡ የብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፤ ጊዮርጊስ ፡ ስም ፡ ባስልዮስ ፡
፪ኛ/ ፡ የመምህር ፡ ገሪማ ፡ ስም ፡ ሚካኤል ።
፫ኛ/ ፡ የሊቀ ፡ ሥልጣናት ፡ መልእክቱ ፡ ስም ፡ ቴዎፍሎስ ።
፬ኛ/ ፡ የመምህር ፡ ዘፈረ ፡ ብርሃን ፡ ስም ፡ ያዕቆብ ፡
፭ኛ/ ፡ የመምህር ፡ ጌታሁን ፡ ስም ፡ ጢሞቴዎስ ፡

www.ethiopianorthodox.org

የአስኬማው ፡ ጸሎት ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ ፓትሪያርኩ ፡ እንደፊተኛው ፡ በጳጳ ትና ፡ በዲያቆናት ፡ ታጅበው ፡ ተመለሱ ፡ ኢትዮጵያውያኑም ፡ ጳጳሳት ፡ ተሰ ብተው ፡ ወደማረፊያቸው ፡ ሔዱ ።

## ጵ ጵ ስ ና ።

የጵጵስናው ፡ ሥርዓት ፡ ሐምሌ ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፴ ፡ ዓ፡ ም፡ እሑድ ፡ በበ ረ ፡ ካና ፡ በቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደሚፈጸም ፡ በፕሮግ ሙ ፡ ተነግሮ ፡ ስለነበረ ፡ ሕዝቡ ፡ ከጧቱ ፡ በ፩ ፡ ሰዓት ፡ ጀምሮ ፡ በበትረካ ው ፡ ምድረ ፡ ግቢ ፡ ተጀነጀነ ። በትረካና ፡ ማለት ፡ ፓትሪያርኩ ፡ የሚቀመ በት ፡ ሥፍራ ፡ ወይም ፡ የፓትሪያርክ ፡ ግቢ ፡ ማለት ፡ ነው ።



ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የተላከላቸውን ፡ ሽልማት ፡ የእስክንድርያ ፡ ፓትሪያርክ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ዮሳብ ፡ እንደ ፡ ተቀበሉ ።

በግቢውም ፡ የቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ደብር ፡ ተሠርቶበታል ። ኢትዮጵያውያኑ ፡ ት ፡ በ፩ ፡ ሰዓት ፡ ተሩብ ፡ በበትረካናው ፡ ሲደርሱ ፡ አምስት ፡ ጳጳሳት ፡ ር ፡ ላይ ፡ ጠብቀው ፡ ተቀበሏቸውና ፡ በ፩ ፡ ሥፍራ ፡ አሳረፏዋቸው ።

ከፓትሪያርኩ ፡ ቤት ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ያለው ፡ ል ፡ በምንጣፍ ፡ አጊጦ ፡ ነበር ። ይህም ፡ የትልቅ ፡ በዓል ፡ ወይም ፡ የት ከበሬታ ፡ ምልክት ፡ መሆኑን ፡ አስረዳ ።

ኢትዮጵያውያኑ ፡ ጳጳሳት ፡ በማረፊያው ፡ ሥፍራ ፡ ጥቂት ፡ እንደቆዩ ፡ ፓት ርኩ ፡ በጳጳሳት ፡ ታጅበው ፤ ዲያቆናቱ ፡ በቀኝና ፡ በግራ ፡ ሆነው ፡ በዜማ፡



ይባቤ ፡ እያደረጉላቸው ፡ በትልቅ ፡ ግርማ ፡ ሆነው ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ገብተው ፡ ቅዳሴ ፡ ጀመሩ ። ኢትዮጵያውያኑ ፡ ጳጳሳት ፡ ግን ፡ እስኪጠሩ ፡ ድረስ ፡ በዚያው ፡ ሥፍራ ፡ እንዲቆዩ ፡ አመለከቷቸው ። ቅዳሴው ፡ በ፫ ፡ ደረጃ ፡ የተ መደበ ፡ ነው ። መጀመሪያው ፡ ደረጃ ፡ ቀዳስያኑ ፡ በንዋየ ፡ ቅድሳቱ ፡ ላይ ፡ የሚጸ ለየውንና ፡ ሌላውን ፡ የጸሎት ፡ ጎዝ ፡ የሚፈጽሙበት ፡ ነው ። ሁለተኛው ፡ ደረጃ ፡ የምንባባት ፡ ክፍል ፡ ይባላል ። እርሱም ፡ እስከ ፡ ፍሬ ፡ ቅዳሴ ፡ ያለው ፡ ነው ። ሥርዓተ ፤ ሢመት ፡ የሚያደርጉትም ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። የቅዳሴው ፡ ጸሎት ፡ ወደ ፡ ሁለተኛው ፡ ደረጃ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፤ በጵጵስና ፡ ልብስ ፡ ያጌጡ ፡ አምስት ፡ ጳጳሳት ፡ በአቡነ ፡ ቶማስ ፡ እየተመሩ ፡ መጥተው ፡ ኢትዮጵያውያኑን ፡ ጳጳሳት ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ አጅበው ፡ ወሰዷቸው ። ለባስያኑም ፡ ዲያቆናት ፡ ለፓትሪያርኩ ፡ ባደረጉት ፡ ዓይነት ፡ እያዜሙ ፡ አጅበው ፡ ተከተሉ ። ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑም ፡ ሲገቡ ፡ ሕዝቡ ፡ በደስታ ፡ አወከ ፤ ሴቶቹም ፡ እልል ፡ አሉ ፡ የእልልታው ፡ ቃና ፡ በፍጹም ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነው ።

አዲሶቹን ፡ ጳጳሳት ፡ በመቅደሱ ፡ በር ፡ ላይ ፡ ፊታቸውን ፡ ወደምሥዋዑ ፡ እያደረጉ ፡ በወንበር ፡ አስቀመጧቸውና ፡ ብፁዕ ፡ ፓትሪያርክ ፤ ሌሎችም ፡ ጳጳ ሳት ፡ መጽሐፈ ፡ ሢመቱን ፡ እያነበቡ ፡ በየተራ ፡ ብዙ ፡ ጸሎት ፡ አደረጉ ። በየ ጸሎቱም ፡ ፍጻሜ ፡ ፓትሪያርኩ ፡ የያንዳንዳቸውን ፡ ስምና ፡ ሀገረ ፡ ስብከታቸውን ፡ እየጠሩ ፡ ሲባርኳቸው ፡ መዘምራኑ ፡ በረጅም ፡ ዜማ ፡ አሜን ፡ እያሉ ፡ ይቀበሉ ፡ ነበር ።

በመጀመሪያው ፡ ክፍለ ፡ ጸሎት ፡ አዲሱን ፡ የጵጵስና ፡ ቆብ ፡ ባርከው ፡ ደፉላቸው ። በ፪ኛው ፡ ጊዜ ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ተይዞ ፡ የሔደውን ፡ የወርቁን ፡ ካፓ ፡ ላንቃ ፡ ባርከው ፡ ሲያለብሷቸው ፡ ሕዝቡ ፡ ላንቃውን ፡ ለማየት ፡ ውካታ ፡ ጃጃታ ፡ አደረገ ። የላንቃው ፡ ውበት ፡ እንግዳ ሆኖ ፤ ስለታየ ፡ ለሕዝቡ ፡ ዓይን ፡ ናፍቆትን ፡ አተረፈለት ።

የሹመቱ ፡ ጸሎትና ፡ ሥርዓቱ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ወደመቅደስ ፡ ገቡ ፤ ብፁዕ ፡ ፓትሪያርክ ፡ ገባሬ ፡ ሠናይ ፡ ካህን ሆነው ፡ ቅዳሴ ፡ ባስልዮስን ፡ ቀደሱ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ፯ ፡ የግብጽ ፡ ጳጳሳትና ፡ ፫ቱ ፡ አዲሶች ፡ ጳጳሳት ፡ ቆሞሳትና ፡ ዲያቆናት ፡ ተራዳእያን ፡ ሆነው ፡ አብረው ፡ ቀደሱ ። ስለቀዳስያን ፡ ብዛት ፡ የሀገራችን ፡ ልማድ ፡ በ፯ ፡ ወይም ፡ በ፭ ፡ መቀደስ ፡ ነው ። ወደላይ ፡ ፲፱ ፡ ወይም ፡ ፳፱ ፡ ቢሆን ፡ አያስከለክልም ፡ እንጂ ፡ ከ፭ ፡ ባነሰ ፡ ጊዜ ፡ ቅዳሴው ፡ እንደሚታጐል ፡ የታወቀ ፡ ነው ። በግብጻውያን ፡ ልማድ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ብቻውን ፡ አይቀድስም ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ ቄስና ፡ አንድ ፡ ዲያቆን ፡ ሊቀድሱ ፡ ይችላሉ ። ካህናት ፡ በበረከቱ ፡ ጊዜም ፡ ብዛት ፡ ሳይወሰን ፡ የተቻለው ፡ ሁሉ ፡ ሊቀድስ ፤ ስለሚችል ፤ በዚህ ፡ በሹመቱ ፡ ቀን ፡ ቀዳስያኑ ፡ ፳ ፡ ወይም ፡ ፴ ፡ ያህል ፡ ነበሩ ። ቅዳሴውም ፡ በ፬ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ተፈጸመና ፡ ከቅዱስ ፡ ቍር ባን ፤ በኋላ ፡ ፓትሪያርኩ ፡ መስቀል ፤ ይዘው ፡ በአዲሶቹ ፡ ጳጳሳት ፡ አፍ ፡ ላይ ፡ «ንሥኡ ፡ መንፈሰ ፡ ቅዱሰ» ፡ እያሉ ፡ በንፍሐት ፡ ሀብተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡

www.ethiopianorthodox.org

አሳደሩባቸው ፤ ሠርሆተ ፡ ሕዝብ ፡ ካደረጉም ፡ በኋላ ፡ ከቤተ ፡ መቅደሱ ፡ እወጣለሁ ፡ ሲሉ ፡ አዲሶቹን ፡ ጳጳሳት ፡ ለማየት ፡ በናፍቆት ፡ ያሰፈሰፈው ፡ ሕዝብ ፡ ከብዛቱ ፡ የተነሣ ፡ የማያሳልፍ ፡ ስለሆነ ፡ ወደውስጥ ፡ ተመልሰው ፡ በአንድ ፡ የጓዳ ፡ በር ፡ ይዘዋቸው ፡ ወጡ ።

በደጅ ፡ ሆኖ ፡ ሲጠባበቅ ፡ የነበረው ፡ ከ፫ ፡ ሺህ ፡ የሚበልጥ ፡ ሕዝብ ፡ ጳጳሶቻችንን ፡ ባያቸው ፡ ጊዜ ፡ እጃቸውን ፡ ለመሳለምና ፡ በረከት ፡ ለመቀበል ፡ ሲሽቀዳደምና ፡ ሲጋፋ ፡ የፍቅሩ ፡ ብዛት ፡ በጣም ፡ አስደነቀን ።

በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ የመንግሥት ፡ ሙዚቀኞች ፡ ተሰልፈው ፡ መጥተው ፡ ሙዚቃ ፡ መቱ ። ቀጥሎም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ መዝሙር ፡ በሙዚቃ ፡ አሰሙና ፡ ለጳጳሳቱ ፡ ሰላምታ ፡ አቀረቡ ። ጳጳሳቱ ፡ ወደፓትርያርኩ ፡ ቤት ፡ በገቡ ፡ ጊዜም ፡ ሕዝቡ ፡ እያጨበጨበና ፤ ደስታውን ፡ እየገለጠ ፡ ወደየቤቱ ፡ ሔደ ።

## ግብዣ ።

የሁለቱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ፍቅር ፡ በመልካም ፡ መሠረት ፡ መመሥረቱ ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ስለሰጠ ፤ በትረክናው ፡ በዚሁ ፡ ቀን ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ጳጳሳት ፡ ክብር ፡ በ፮ሰዓት ፡ ተሩብ ፡ ትልቅ ፡ ግብዣ ፡ አደረገ ። በግብዣው ፡ ላይም ፡ ብፁዕ ፡ ፓትርያርክና ፡ ፓሻዎች ፡ ጳጳሳትና ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ (በድምር ፡ ፺ ያህል ፡ ሰዎች) ፡ ነበሩ ።

በፓትርያርኩ ፡ ግራ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ጳጳስ ፡ ዘሸዋ ፡ ወዕጨጌ ፡ ዘደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ተቀመጡና ፡ የቀሩት ፡ ጳጳሳት ፡ ከግብጻውያን ፡ ጳጳሳት ፡ ጋር ፡ እየተሰባጠሩ ፡ በመዓርግ ፡ ሥፍራ ፡ ተቀመጡ ። በስተቀኝም ፡ በኩል ፡ ክቡር ፡ ፊታውራሪ ፡ ታፈሰና ፡ ፓሻዎች ፡ ብላታ ፡ መርሴዔ ፡ ኃዘንና ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ተቀመጡ ። የግብዣው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ውበት ፡ ያለው ፡ ነበር ፤ ምግቡ ፡ በያይነቱ ፡ ቀረበ ፡ በመጠጥ ፡ በኩል ፡ ግን ፡ ከተጣራ ፡ ውኃ ፡ በቀር ፡ አንዳች ፡ የአልኮል ፡ ወገን ፡ ስላልቀረበ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ ደስ ፡ አሰኘ ። የመጠጥ ፡ ፈቃድ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ በቤቱ ፡ ወይም ፡ የመጠጥ ፡ ሥፍራ ፡ በሆነው ፡ ሆቴል ፡ እንደሚያገኘው ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

መንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ በሚሰጥበት ፡ በጳጳሳት ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ሰውን ፡ የሚያሰክር ፡ መጠጥ ፡ ጎኑም ፡ መሆኑ ፡ የተመሰገነ ፡ ልማድ ፡ ነው ። በሀገራችንም ፡ ቢሆን ፡ ይህ ፡ ምሳሌ ፡ በመንፈሳውያን ፡ አባቶች ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ እንዲፈጸም ፡ ተተክሎም ፡ እንዲቀር ፡ የምንመኘው ፡ ነገር ፡ ነው ። ግብዣው ፡ በ፱ሰዓት ፡ ተፈጽሞ ፡ ብፁዓን ፡ ጳጳሳት ፡ ወደማረፊያቸው ፡ ተመለሱ ።

## በኢትዮጵያ ፡ ሌጋሲዮን ።

ሚኒስትሩ ፡ ክቡር ፡ ፊታውራሪ ፡ ታፈሰ ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤል ፡ ሐምሌ ፡ ፲፱ ቀን ፡ ሰኞ ፡ ማታ ፡ ከ፩ሰዓት ፡ ተኩል ፡ እስከ ፡ ፫ሰዓት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሌጋሲዮን ፡



ስለጳጳሳቱ ፡ ክብር ፡ ለፓሻዎችና ፡ ለጳጳሳት ፡ ለአፈንዲዎችም ፡ ግብዣ ፡ አደረጉ ። በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ የሁለቱ ፡ አገሮች ፡ ጥንታዊ ፡ ፍቅርና ፡ ግንኙነት ፡ በጨዋታ ፡ እየተነሣ ፡ ፍሥሓ ፡ ሆኖ ፡ አመሸ ።

## በእስክንድርያ ።

የቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ዐፅመ ፡ ርእሱ ፡ የሚገኝበት ፡ መቃብር ፡ በእስክንድርያ ፡ ስለሆነ ፤ ይህን ፡ ቅዱስ ፡ ሥፍራ ፡ ለመሳለምና ፡ ከቅዱስ ፡ በረከቱ ፡ ለመሳተፍ ፡ አባቶቻችን ፡ ፭ቱ ፡ ጳጳሳት ፡ ለማክሰኞ ፡ አጥቢያ ፤ ሌሊቱን ፡ ወደእስክንድርያ ፡ ወረዱ ።



ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ በቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጉባኤ ፡ መካከል ፡ ይታያሉ ።

ጧት ፡ በ፩ ፡ ሰዓት ፡ በትልቁ ፡ የቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሥዋዕት ፡ አቅርበው ፡ በኢትዮጵያዊ ፡ ሥርዓት ፡ ቅዳሴ ፡ ባስልዮስን ፡ ቀደሱ ።

ከቅዳሴ ፡ በኋላ ፡ ለገዳሙ ፡ እርዳታ ፡ ፴ ፡ ፓውንድ ፡ ሰጥተው ፡ ለነዳያንም ፡ ቸርነት ፡ አድርገው ፡ ወደካይሮ ፡ ተመለሱ ።

---

## ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መመለስ ።

አባቶቻችን ፡ ብፁዓን ፤ ጳጳሳት ፡ ሐምሌ ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ማክሰኞ ፡ ወደበትረክና ፡ ሔደው ፡ ከብፁዕ ፡ ፓትርያርክ ፡ ሲሰናበቱ ፤ ፓትርያርኩ ፡ ጸሎት ፡ አድርሰው ፡ ባረኳቸው ፤ እስከ ፡ በሩም ፡ ድረስ ፡ ዘልቀው ፡ ሸኙዋቸው ።

ሐምሌ ፡ ፳፪ ፡ ረቡዕ ፡ በ፩ሰዓት ፡ ከካይሮ ፡ ተነሥተው ፡ ፓርት ፡ ሱዳን ፡ ዐረፉ ፤ ከዚህም ፡ ተነሥተው ፡ አሥመራ ፡ በ፯ ፡ ሰዓት ፡ ሲደርሱ ፡ አቪያተሩ ፡ ስለአየሩ ፡ አኳኋን ፡ በአሥመራ ፡ ማደርን ፡ ስለመረጠ ፤ ሌሊቱን ፡ በአሥመራ ፡ ማሳ

www.ethiopianorthodox.org

ለፍ ፡ ግድ ፡ ሆነ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ላይዘን ፡ ጸሐፊ ፡ አቶ ፡ ተኮላ ፡
ገብረ ፡ መድኅን ፡ ተቀበላቸውና ፡ መጀመሪያ ፡ ወደቅድስት ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡
ክርስቲያን ፡ ሔደው ፡ ተሳለሙ ። አካሔዳቸውም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በድንገት ፡
ቢሆን ፡ አቡነ ፡ ቄርሎስ ፡ ወዲያው ፡ ደወል ፡ አስደውለው ፡ ወንዱም ፡ ሴቱም ፡
ተሰብስቦ ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ ተቀበላቸው ።

የአቡነ ፡ ማርቆስ ፡ ወኪል ፡ አባ ፡ ቄርሎስና ፡ ሴክሬታሪያቸው ፡ አባ ፡ ገብረ ፡
ሥላሴ ፡ አስቡ ፤ ደጃዝማች ፡ አርአያ ፡ ዋሴ ፡ መልአከ ፡ ሰላም ፡ ድሜጥሮስ ፡ ገብረ ፡
ማርያም ፤ ቀኛዝማች ፡ ፍሥሐዬ ፡ ተስፋ ፡ ሚካኤል ፡ አዝማች ፡ ተስፋዬ ፡ ባራሒ ፡
በፈገግታና ፡ በፍጹም ፡ ደስታ ፡ ተቀብለው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኒቱን ፡ በውስጥም ፡ በው
ጪም ፡ አስጐብኝተው ፡ ለከተማው ፡ እንደጕልላት ፡ ሆኖ ፡ ሞገስ ፡ የሚሰጠውን ፡
ውበት ፡ ብቻ ፡ የሆነውን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከጐበኙ ፡ በኋላ ፤ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስል
ዮስ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያኑና ፡ ለተማሪ ፡ ቤቱ ፤ ተስፋ ፡ ለሌላቸውም ፡ ምእመናን ፡ የገ
ንዘብ ፡ ስጦታ ፡ አደረጉላቸው ። ከዚያ ፡ በኋላም ፡ ወደኢትዮጵያ ፡ ላይዘን ፡ ሔደው ፡
ጐብኝተው ፡ ለማደሪያ ፡ ወደተዘጋጀው ፡ ሆቴል ፡ ገቡ ። ሐምሌ ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ሐሙስ ፡
ጧትም ፡ በ፩ ፡ ሰዓት ፡ ተሩብ ፡ ከአሥመራ ፡ ተነሥተው ፡ በ፬ ፡ ሰዓት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ገቡ ።

---

## ልዩ ፡ ማስታወሻ ።

## የሄልዮፖሊስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

ሄልዮፖሊስ ፡ ከካይሮ ፡ በስተ ፡ ምሥራቅ ፡ የሚገኝ ፡ የካይሮ ፡ ከተማ ፡
ክፍል ፡ ነው ። የግዕዙ ፡ አሪት ፡ ካህነ ፡ ሄልዮቱ ፡ ብሎ ፡ በዘርፍ ፡ የሚያነሣው ፡
ሥፍራ ፡ ይኸው ፡ ሄልዮፖሊስ ፡ ነው ።

በዚህ ፡ ከተማ ፡ ወዳጆችን ፡ ቆሞስ ፡ ኢብራሂም ፡ ሉቃስ ፡ የተከሉትና ፡ በሰ
ቸው ፡ መምህርነት ፡ ውስጥ የሆነ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ የኮፕት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አለ ።

በሐምሌ ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ እሑድ ፡ ማታ ፡ ቆሞስ ፡ ሉቃስ ፡ ልጃቸውን ፡ በተክ
ሊል ፡ የሚድሩበት ፡ ቀን ፡ ኖሮ ፤ ለሙሽሮቹ ፡ በረከታችሁ ፡ እንዲወርድላቸው ፡
ተክሊሉን ፡ ባርኩላቸው ፡ ብለው ፡ ጳጳሶቻችንን ፡ ስለለመኑ ፤ በአንድ ፡ ወገን ፡
የሐሊናቸውን ፡ ትውክልት ፡ ተመልክተው ፡ በ፪ኛውም ፡ ወገን ፡ ወዳጆችን ፡ መሆ
ናቸውን ፡ ተገንዝበው ፡ ልመናቸውን ፡ ተቀብለው ፡ ሔዱላቸው ።

ሕዝቡ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ፀር ፡ ተሰልፎ ፡ ይጠብቅ ፡ ነበርና ፡ አባቶቻችን ፡
ሲደርሱ ፡ አጨበጨበ ፤ ቀጥሎም ፡ ዲያቆናቱ ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖ ፡ ለብሰው ፡ መብ
ራት ፡ ይዘው ፡ መጥተው ፡ እየዘመሩ ፡ ወደመቅደሱ ፡ ይዘዋቸው ፡ ገቡ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሙሽራውና ፡ ሙሽራዪቱ ፡ ቀርበው ፡ የተክሊሉ ፡ ሥርዓት ፡
ፈረሰላቸውና ፡ በጳጳሳቱ ፡ ፊት ፡ እየተንበረከኩ ፡ ከየአንዳንዳቸው ፡ ቡራኬ ፡ ተቀበሉ ።

## ኢትዮጵያዊ ፡ ቅዳሴ ።

ጵጵስና ፡ የተቀበሉት ፡ ጳጳሳት ፡ በሹመታቸው ፡ ማኅታ ፡ ይቀድሱ ፡ ዘንድ ፡
ልማና ፡ ሥርዓቱ ፡ ስለሆነ ፤ ሐምሌ ፡ ፲፱ ፡ ሰኞ ፡ የእኛ ፡ አባቶች ፡ በኢትዮጵያዊ ፡
ሌማ ፡ ቅዳሴ ፡ እግዚእን ፡ ቀደሱ ።



የኢትዮጵያ ፡ ቅዳሴያት ፡ ፲፬ ፡ ሲሆኑ ፤ በግብጻውያን ፡ ቅዳሴያት ፡ ሦስት ፡
ብቻ ፡ ናቸው ። እነሱም ፡ ቅዳሴ ፡ ባስልዮስና ፡ ቅዳሴ ፡ ቄርሎስ ፤ ቅዳሴ ፡ ጎርጎር
ዮስ ፡ ናቸው ።

በቅዳሴውም ፡ ጊዜ ፡ ጳጳሳቱና ፡ ቆሞሳቱ ፡ ቀሳውስቱና ፡ ዲያቆናቱ ፡ የኢት
ዮጵያን ፡ ሥርዓተ ፡ ቅዳሴ ፡ በማድነቅ ፡ እየተመለከቱ ፡ ቆይተው ፡ ከአባቶቻችን ፡
እጅ ፡ ቅዱስ ፡ ቊርባንን ፡ ተቀበሉ ።

ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ገባሬ ፡ ሠናይ ፡ ካህን ፤ አቡነ ፡ ሚካኤል ፡ ንፍቅ ፡
(ተራዳኢ ፡ )የቀሩት ፡ ጳጳሳት ፡ ተራዳእያን ፤ ገባሬ ፡ ሠናይ ፡ ዲያቆን ፡ አባ ፡ ገብረ ፡
ማርያም ፡ ሆነው ፡ ቀደሱ ።

ከቅዳሴም ፡ በኋላ ፡ ፓትርያርኩ ፡ የባረኩት ፡ መታሰቢያ ፡ ነው ፡ ብለው ፡
አንዳንድ ፡ የወርቅ ፡ መስቀል ፡ ሰጡዋቸው ።

## መንፈሳዊ ፡ እርዳታ ።

በትረ ፡ ክናው ፡ ለጳጳሳትና ፡ ለታላላቅ ፡ እንግዶች ፡ ማረፊያ ፡ የሚሆን ፡
አንድ ፡ ትልቅ ፡ ቤት ፡ በዚያው ፡ በምድረ ፡ ግቢው ፡ ነበረው ። ይኸውም ፡ ቤት ፡
በዘመን ፡ ብዛት ፡ ስላረጀ ፡ ፓትርያርኩ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በሰፊና ፡ በመልካም ፡
አኳኋን ፡ ለማሠራት ፡ እንዳስጀመሩት ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ስለሰሙ ፤
ለዚህ ፡ ለበጎ ፡ ሥራ ፡ ርዳታ ፡ ይሁንልን ፡ ብለው ፡ ሐምሌ ፡ ፳ ፡ ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡
በአቡነ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ እጅ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ፓውንድ ፡ ላኩላቸው ።

ፓትርያርኩም ፡ ጸሎት ፡ አድርገው ፡ ባርከው ፡ መንፈሳዊውን ፡ ርዳታ ፡
ተቀብለው ፡ አሰናበቷቸው ።

---

## በአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ ብፁዓን ፡ ጳጳሳትን ፡ ስለመቀበል ፡ የተደረገ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትና ፡ አቀባበል ።

ብዙ ፡ ዘመን ፡ ሲታሰብበትና ፡ ሲደከምበት ፤ ብዙዎቹ ፡ ነገሥታትና ፡ ብዙ
ዎቹም ፡ ትውልዶች ፡ ሲመኙት ፡ የኖሩትን ፡ ታላቅ ፡ ጉዳይ ፡ ለማየት ፡ የቻለ ፡
ዓይን ፡ ዕድለ ፡ መልካም ፡ ነው ።

እንዲሁም ፤ ብዙዎቹ ፡ የደከሙበትን ፡ ወደፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ ዕድሉ ፡
የፈቀደለት ፡ ሰው ፡ ስመ ፡ አጠራሩና ፡ መልካም ፡ ታሪኩ ፡ ለትውልደ ፡ ትው
ልድ ፡ የሚተላለፍ ፡ ነው ።

እንደዚሁም ፡ ሁሉ ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አባቶቻቸው ፡
(ነገሥታቱ ፡ ) ሲጥሩበትና ፡ ሲመኙት ፡ የኖሩበትን ፡ መንፈሳዊ ፡ መብት ፡ በዘመነ ፡
መንግሥታቸው ፡ ለኢትዮጵያዊት ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሲደረግላት ፡
በማየታቸውና ፡ ለማድረግም ፡ በመቻላቸው ፡ እስከ ፡ ዘለዓለሙ ፡ የታሪክ ፡ ዓይን ፡
ትክ ፡ ብሎ ፡ ሲመለከታቸው ፡ ይኖራል ።

ይልቁንም ፡ በዚህ ፡ በሥጋዊው ፡ ነጻነት ፡ ላይ ፡ መንፈሳዊውንም ፡ ነጻነት ፡
ለማቆም ፡ እንዲችሉ ፤ እግዚአብሔር ፡ በአምላካዊ ፡ ልግሥናው ፡ ፈቀደና ፡

www.ethiopianorthodox.org

ካሁን ፡ በፊት ፡ በ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ባስጠረጉት ፡ መንፈሳዊ ፡ ጎዳና ፡ እነሆ ፡ ዛሬ ፡ በቀጥታ ፡ ለመራመድ ፡ ተቻለ ።

መሠረቱ ፡ ያማረ ፡ ነገር ሁሉ ፍጻሜው ፡ (ጠፈሩ) ፡ ያማረ ፡ ይሆናል ፤ መሠረቱ ፡ ግብዝ ፡ የሆነ ፡ ነገር ሁሉ ፡ ግን ፡ መሠረቱም ፡ መዋቅሩም ያለጊዜው ፡ ይወድቃል ፡ እንጂ ፡ የጸና ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

በዚህም ፡ አስተያየት ፡ ከላይ ፡ እንደገለጽነው ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የጠየቁትና ፡ የተደረገላቸው ! መንፈስ ፡ ቅዱሳዊ ፡ መብት ፡ የጠየቁትም ፡ በሚገባ ፡ የተደረገላቸውም ፡ በሚገባ ፡ ባይሆን ፡ ኖሮ ፡ ይህ ፡ የዛሬው ፡ አሳብ ፡ ሁሉ ፡ ዕንቅፋት ፡ ባላጣውም ፡ ነበርና ፡ አሳብ ፡ ሁሉ ፡ ጥልቅ ፡ መሠረት ፡ ያለው ፡ ሊሆን ፡ ያስፈልጋል ።

ስለዚህም ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ስለሚታየው ፡ ታላቅ ፡ ውለታ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡ «እግዚአ ፡ ኰንኔከ ፡ ሀበ ፡ ለንጉሥ ፡ ጽድቀከኒ ፡ ለወልዱ ፡ አምኃ ፡ ሥላሴ ፡ ዘውእቱ ፡ ወራሴ ፡ መንግሥት ፡ አግርር ፡ ፀሮ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ፡ ዕቀብ ፡ ንግሦ ፡ ወሠራዊቶ ፡ ለንጉሥን ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ» ፡ እያለች ፡ እስከ ፡ ዘለዓለሙ ፡ ልባዊ ፡ ጸሎቷን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከማቅረብ ፡ አታቋርጥም ።

እንመለስና ፡ አርእስቱ ፡ ያመለከተንን ፡ እንከተል ።

እግዚአብሔር ፡ በጊዜው ፡ የሚፈጽመው ፡ አምላካዊ ፡ ተስፋ ፡ ደረሰና ፡ ከላይ ፡ ስማቸውና ፡ የሔዱበት ፡ ቀን ፡ የተገለጠው ፡ ፯ቱ ፡ ብፁዓን ፡ አበቶቻችን ፡ በግርማዊነታቸው ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ ሔደው ፡ በሃይማኖት ፡ አባታችን ፡ በቅዱስ፡ ማርቆስ ፡ መንበር ፡ በተቀመጡት ፡ በፓትርያርኩ ፡ በብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ዮሳብ ፡ እጅ ፡ ሐምሌ ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ተሾሙ ።

የቀድሞውም ፡ ያሁኑም ፡ መንፈሳውያን ፡ አበቶቻቸው ፡ ከሆኑት ፡ ከእስክንድርያ ፡ ጳጳሳት ፡ ጋር ፡ የወዳጅነትና ፡ የፍቅር ፡ አንድነታቸውን ፡ ሲገልጡና ፡ ሲጨዋወቱ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ቆይተው ፤ ሐምሌ ፡ ፳፩ ፡ ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በአኤሮፕላን ፡ ተነሥተው ፡ ወደኢትዮጵያዊት ፡ ከተማ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ለመግባት ፡ አሳባቸውን ፡ ከቆረጡ ፡ በኋላ ፤ አኤሮፕላኑ ፡ በአሥመራ ፡ ዐርፎ ፡ በዚያው ፡ አደሩ ።

በዚሁም ፡ ቀን ፡ ይመጣሉ ፡ ተብሎ ፡ ተነግሮ ፡ ስለነበረ ፤ ልክ ፡ በ፱ ፡ ሰዓት ፡ ከመሳፍንትና ፡ ከመኳንንት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ተራ ፡ ሕዝብ ፡ ድረስ ፡ የአኤሮፕላኑን ፡ ማረፊያ ፡ አጥለቅልቆት ፡ ነበር ።

የኢትዮጵያ ፡ መንፈሳዊ ፡ ጉባኤ ፡ ሊቃውንትና ፡ የከተማው ፡ አድባራት ፡ አለቆችም ፡ በሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ በፀባቴ ፡ ጥዑመ ፡ ልሳን ፡ አማካይነት ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ጠቅላይ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ ባቀረበላቸው ፡ አውቶሞቢሎች ፡ እንደየማዕርጋቸው ፡ እየተቀመጡና ፡ ተራ ፡ እየመቱ ፡ እስከ ፡ አኤሮፕላን ፤ ማረፊያ ፡ ድረስ ፡ ከሔዱ ፡ በኋላ ፤ በማግሥቱ ፡ እንጂ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ አለመግባታቸው ፡



ተረጋገጠና ፡ በማግሥቱ ፡ በ፫ ፡ ሰዓት ፡ በታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ከሚገኘው ፡ ከብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ቢሮ ፡ እንዲሰበሰቡ ፡ ተነግሮአቸው ፡ ሁሉም ፡ ወደ ፡ የቤታቸው ፡ ተመለሱ ፤ ይኸንንም ፡ ቍርጠኛ ፡ ቃል ፡ እስኪሰሙ ፡ ድረስ ፡ የከተማው ፡ አድባራት ፡ ቀሳውስትና ፤ ዲያቆናት ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖ ፡ ለብሰው ፡ መስቀል ፡ ይዘው ፡ በታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ በር ፡ ይጠባበቁ ፡ ነበር ።

ይህ ፡ በሆነበት ፡ ቀን ፡ ሌሊቱን ፡ ሁሉም ፡ ከአሳቡ ፡ ጋር ፡ ሲታገል ፡ አድሮ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ተሰምቷል ። በማግሥቱ ፡ ሐምሌ ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ጧት ፡ እንደካፊያ ፡ ያለ ፡ ዝናምና ፡ ጉም ፡ ከተማውን ፡ በሙሉ ፡ ይዞት ፡ ነበር ።

ይሁን ፡ እንጅ ፡ የብፁዓን ፡ አበቶቻችንን ፡ ዓይን ፡ ለማየት ፡ ናፍቆትንና ፡ ችኰላን ፤ ተመልቶ ፡ ሌሊቱ ፡ አልነጋለት ፡ ያለ ፡ ሕዝብ ፡ ስንኳን ፡ የዝናምና ፡ የብርድ ፡ ኃይል ፤ የበረዶም ፡ ኃይል ፡ ቢሆን ፡ ባልተሰማውም ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፤ በዚሁ ፡ ቀን ፡ ከጧቱ ፡ በ፫ ፡ ሰዓት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፤ ልዑላን ፡ መሳፍንትና ፡ ሚኒስቴሮች ፡ ታላላቅ ፡ ሊቃውንትና ፡ መምህራን ፤ መኳንንትና ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፤ የከተማውም ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ አኤሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ ሲጓዝ ፡ የመኪናው ፡ ጕዞና ፡ ሰልፍ ፡ ተመልካቾችን ፡ አስደስቶ ፡ ነበር ።

ልብሰ ፡ ተክህኖ ፡ የለበሱና ፡ መስቀል ፡ የያዙ ፡ ቀሳውስትና ፡ ዲያቆናትም ፡ በአጋፋሪ ፡ በየነ ፡ አሊ ፤ አማካይነት ፡ ተራ ፡ መትተው ፡ በታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ በር ፡ ይጠባበቁ ፡ ነበር ።

በየመንገዱና ፡ በየቤቱ ፡ ላይ ፡ የተሰቀሉት ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማዎች ፡ ለዚሁ ፡ ለዋናው ፡ በዓል ፡ ሞገስ ፡ ሆነው ፡ ከመገኘታቸው ፡ በላይ ፡ ለከተማውም ፡ ውበትና ፡ ድምቀትን ፡ ሰጥተውት ፡ ነበር ።

ልክ ፡ ፬ ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ አኤሮፕላኑ ፡ በአየር ፡ በአንዣበበ ፡ ጊዜ ፡ ብዙዎች ፡ ነገሮችን ፡ በማውጣትና ፡ በማውረድ ፡ ይደክም ፡ የነበረው ፡ የሕዝብ ፡ ሐሊና ፡ አሳቡ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ሆነለትና ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ አኤሮፕላኑ ፡ ዐርፎ ፡ ባየናቸው ፡ ማለትን ፡ ብቻ ፡ ያስብ ፡ ጀመር ።

አኤሮፕላኑም ፡ ዐርፎ ፡ ጥቂት ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ወደ ፡ አኤሮፕላኑ ፡ ገብተው ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትን ፡ መልካም ፡ አሳብ ፡ ገልጸው ፡ ተቀበሏቸው ።

ብላታ ፡ መርስዔ ፡ ኃዘንም ፡ ባለአምበሉን ፡ የኢትዮጵያ ፡ የክብር ፡ ኮከብ ፡ ኒሻን ፡ አድርገው ፡ አስቀድመው ፡ ብቅ ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ የበዓሉን ፡ ክብር ፡ ከመግለጣቸው ፡ በላይ ፡ ተመልካቾችን ፡ ሁሉ ፡ አስደስተዋል ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ብፁዓን ፡ አባቶቻችን ፡ በወርቅ ፡ የተንቆጠቆጠ ፡ ከሞር ፡ ላንቃ ፡ ለብሰው ፤ መስቀል ፡ ይዘው ፡ ብቅ ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ ካህናት ፡ ሰማይን ፡ መስለው ፡ ነበር ።

www.ethiopianorthodox.org

ሰውነታቸውም ፡ በእውነቱ ፡ ማኅደረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሆኖ ፡ ስለነበረ ፡ ከዚህ ፡ ከማገረ ፡ ልብስ ፡ ጋራ ፡ ተመልካችን ፡ ሁሉ ፡ አስደናቂ ፡ ሆኖ ፡ ታይቶ ፡ ነበር ።

በዚያውም ፡ የተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ ደስታውን ፡ በጭብጨባ ፡ በገለጠ ፡ ጊዜ ፡ ጭብጨባው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ድምፅ ፡ ሰጥቶ ፡ ነበረ ።

በዙሪያውም ፡ የተሰለፉት ፡ የጦር ፡ ወታደሮች ፡ ለብፁዓን ፡ አባቶቻችን ፡ የሚገባ ፡ ሰላምታ ፡ ሰጡ ።

የብፁዓን ፡ አባቶቻችን ፡ የተቀብዖ ፡ ስማቸው ፡ ከዚህ ፡ እንደ ፡
ሚ ከ ተ ለ ው ፡ ነ ው ።

፩ኛ/ ብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፤
፪ኛ/ መምህር ፡ ገሪማ ፡ አቡነ ፡ ሚካኤል ፤
፫ኛ| ሊቀ ፡ ሥልጣናት ፡ መልእክቱ ፡ አቡነ ፡ ቴዎፍሎስ ፤
፬ኛ| መምህር ፡ ዘፈረ ፡ አቡነ ፡ ያዕቆብ ፤
፭ኛ| " " " ጌታሁን ፡ አቡነ ፡ ጢሞቴዎስ ፤

እነዚህም ፡ አባቶቻችን ፡ በ፩ቱ ፡ ማዕዘን ፡ አማትበው ፡ ቅድስት ፡ አገራቸውን ፡ ባረኩ ።

ወደ ፡ ሕዝቡም ፡ እየቀረቡ ፡ ቅዱስ ፡ ቡራኬያቸውን ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፤ በተዘጋጁላቸው ፡ አውቶሞቢሎች ፡ ሆነው ፡ በአቶ ፡ ቢስኪሊተኞች ፡ ዘበኞች ፡ ታጅበው ፡ ጉዞው ፡ ወደ ፡ ታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ቀጠለ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የተቀባዮቹ ፡ አውቶሞቢሎች ፡ ጉዞ ፡ ከአኤሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ተያይዘና ፡ ተራ ፡ መትቶ ፡ ነበር ።

በየመንገዱ ፡ ዳር ፡ ይህን ፡ ሥነ ፡ በዓል ፡ ለማየት ፡ የሚጋፋውና ፡ የሚጨናነቀው ፡ ሕዝብ ፡ ቍጥሩ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ነው ።

በቤተ ፡ መንግሥቱም ፡ ግቢ ፡ ስለ ፡ ብፁዓን ፡ ጳጳሳት ፡ ሢመት ፡ በዓል ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማዎች ፡ ቆመዋል ፤ የክብር ፡ ዘበኞች ፡ ተሰልፈዋል ፤ እላይም ፡ እንደተናገር ነው ፡ ካህናት ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖ ፡ ለብሰው ፡ መስቀል ፡ ይዘው ፡ ቆመዋል ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ ግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ ሔደው ፡ በታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ በተዘረጋው ፡ ዙፋን ፡ ሆነው ፡ ጥቂት ፡ እንደቆዩ ፡ ጉዞው ፡ ወደቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ደረሰ ።

በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ብፁዓን ፡ አባቶቻችን ፡ ለማረፊያ ፡ በተዘጋጀላቸው ፡ የክብር ፡ ቦታ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፤ በዋናው ፡ የልፍኝ ፡ አስከልካይ ፡ በኰሎኔል ፡ መኰንን ፡ ደነቀ ፤ ተጠርተው ፡ ገብተው ፡ ወደግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ ወደግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ዙፋን ፡ ፊት ፡ ከቀረቡ ፡ በኋላ ፤ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ያለውን ፡ ታሪካዊና ፡ መሠረታዊ ፡ የሆነውን ፡ ቃል ፡ ተናገሩ ።



## የግርማዊነታቸው ፡ ንግግር ።

ከቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ መንበር ፡ ጋራ ፡ ያላትን ፡ መንፈሳዊ ፡ ግንኙነት ፡ በታላቅ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ጠብቃ ፡ በአፍሪካ ፡ መካከል ፡ የክርስቲያን ፡ ደሴት ፡ እየተባለች ፡ የኖረችው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፤ የተገባትን ፡ ታላቅነትና ፡ ክብር ፡ እንድታገኝ ፡ ስንደክምበት ፡ የቆየነው ፡ ተፈጽሞ ፡ ሁላችንም ፡ በማየታችን ፡ ዛሬ ፡ የመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ደስታ ፡ ነው ።

በቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ መንበርና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መካከል ፡ በተገኘው ፡ መግባባት ፡ ሁለቱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ጎን ፡ ለጎን ፡ ሆነው ፡ የሚፈጽሙት ፡ መንፈሳዊ ፡ አገልግሎት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ፍሬ ፡ የሚሰጥ ፡ መሆኑ ፡ የሚያስተማምን ፡ ነው ።

ይህም ፡ ለግብጽና ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ከፍ ፤ ያለ ፡ ክብር ፡ የሚሰጥ ፡ ሥራ ፡ በዘመናችን ፡ ተጀምሮ ፡ ስለተፈጸመና ፡ ዕድሉም ፡ ለኛና ፡ በቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ መንበር ፡ ለተቀመጡት ፡ ለብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ዮሳብ ፡ ፪ኛ ፡ ስለደረሰ ፤ ይህን ፡ ምክንያት ፡ አድርገን ፡ የታላቅ ፡ አክብሮት ፡ አሳባችንን ፡ ለብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ዮሳብ ፡ ፪ኛ ፡ ስንገልጥ ፡ ደስ ፡ ይለናል ።

የኢትዮጵያ ፡ ታላቅነትና ፡ የሥልጣኔ ፡ እድገት ፡ ከሃይማኖት ፡ ትልቅነቷ ፡ ጋር ፡ የተባበረ ፡ እንዲሆን ፡ ያስፈልጋል ።

ሃይማኖት ፡ በሌለበት ፡ ሥፍራ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ሥልጣኔ ፡ ቢኖር ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ኃይል ፡ ቢገኝ ፡ ሥልጣኔውም ፡ በግፍ ፡ የተሸፈነ ፡ ኃይሉም ፡ በግፍ ፡ የታወረ ፡ ይሆናል ። የሃይማኖትና ፡ የበጎ ፡ ምግባርን ፡ ትምህርት ፡ ለማስፋፋት ፡ ከባድ ፡ አደራ ፡ ያለበትን ፡ ኃላፊነት ፡ ተቀብላችሁ ። የሐዋርያነት ፡ ሥራችሁን ፡ ስትጀምሩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የምትፈጽሙትና ፡ ሰማያዊ ፡ ክብር ፡ የሚያስገኝላችሁ ፡ ሥራችሁ ፡ በመልካም ፡ እንዲከናወንላችሁ ፡ እንመኝላችኋለን ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ጀምረው ፡ ለሁሉም ፡ ለመዓርጋቸውና ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ማዕርግ ፡ መግለጫ ፡ የሚሆን ፡ "አንበሳ ፡ ወጽአ ፡ እምገዳም ፡ ውእቱኬ ፡ ወልደ ፡ አምላክ ፡ ውእቱ" ፡ የሚል ፡ ጽሑፍና ፡ ሁለት ፡ ሥዕለ ፡ አንበሳ ፡ ያለበት ፡ በትረ ፡ ጳጳሳትና ፡ የወርቅ ፡ መስቀል ፡ ሸለሟቸው ።

ይህም ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ በራሳቸውና ፡ በብፁዓን ፡ ጳጳሳት ፡ ስም ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ያለውን ፡ ለትውልደ ፡ ትውልድ ፡ የማይረሳ ፡ ታሪካዊ ፡ ቃል ፡ ተናገሩ ።

## የብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ንግግር ።

## ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ።

ግርማዊነትዎ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ዕድገትና ፡ ልዕልና ፡ በታላቅ ፡ ትጋትና ፡ ድካም ፡ ያዘጋጀው ፡ ታሪክና ፡ መታሰቢያ ፡ በተመሠረተበት ፡ በዛ

www.ethiopianorthodox.org

ሬዩቱ ፡ ቀን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ አብረውኝ ፡ ባሉት ፡ አበው ፡ ጳጳሳት ፡ በኔም ፡ በራሴ ፡ ስም ፡ ለዚህ ፡ ከፍተኛ ፡ ለሆነው ፡ መልካም ፡ ሥራዎና፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ «አፍቀርከ ፡ ጽድቀ ፡ ወዐመፃ ፡ ጸላእከ ፡ በእንተዝ ፡ ቀብዓከ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፡ ቅብዐ ፡ ትፍሥሕት ፡ እምእለ ፡ ከማከ ፡» ብዬ ፡ ንግግሬን ፡ እጀምራለሁ ።

## ጃንሆይ ።

ያለፉትን ፡ አባቶችዎን ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ ስንመለከት ፤ ሀብተ ፡ ሥጋና ፡ ሀብተ ፡ ነፍስን ፡ ሁለቱን ፡ አንድነት ፡ አዋሕዶና ፡ አጣምሮ ፡ ሕዝብን ፡ ወደቀናው ፡ ጎዳና ፡ ለመምራት ፡ ዕድልና ፡ ችሎታ ፡ የተሰጠው ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ።

ስለዚህ ፤ ሕዝብዎ ፡ በሥጋው ፡ የሚበለጽግበትን ፤ በነፍሱ ፡ የሚጠቀምበትን ፡ ሁለቱን ፡ ዓለማት ፡ ለመውረስ ፡ በመሪነትዎ ፡ ጎዳና ፡ ሲጓዝ ፡ ይታያል ።

ይልቁንም ፡ "በትዕግሥትክሙ ፡ ታጠርይዋ ፡ ለነፍስክሙ" ፡ እንደተባለው ፡ እምነትንና ፡ ትዕግሥትን ፡ መሣሪያ ፡ አድርገው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋር ፡ ያላት ፤ ጥንታዊ ፡ ፍቅርና ፡ ወዳጅነት ፡ መንፈሳዊ ፡ ግንኙነትም ፡ ሳይቃወስና ፡ ሳያቋርጥ ፡ የሚገባትን ፡ ነጻ ፡ መብት ፡ እንድታገኝ ፡ የነበረው ፡ ጥረትዋና ፡ ድካምዋ ፡ ሁሉ ፡ ይኸው ፡ ፍሬው ፡ ደርሶ ፡ ለሕዝብዎ ፡ በመሰጠቱ ፡ በሃይማኖት ፡ የጸናች ፡ ተስፋ ፡ የተፈተነች ፡ ድል ፡ አድራጊ ፡ መሣሪያ ፡ ናት ፡ ያሉትን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ ንግግርዎን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ሆኗል ።

## ጃንሆይ ።

አባትዎ ፡ ቅዱስ ፡ ዳዊት ፡ በዘመኑ ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ ለመሥራት ፡ ተመኝቶ ፡ ነበር ።

ይህ ፡ ዕድል ፡ ለልጁ ፡ ለሰሎሞን ፡ እንጂ ፡ ለርሱ ፡ ያልታዘዘ ፡ በመሆኑ ፡ ምኞቱን ፡ በሥራ ፡ ለመግለጽ ፡ አልቻለም ።

ግርማዊነትዎ ፡ ግን ፡ ዕድለኛ ፡ በመሆንዎ ፡ ሺ፭፻ ፡ ዘመን ፡ ባልተደላደለ ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መብት ፡ ዛሬ ፡ በዘመነ ፡ መንግሥትዎ ፡ ወደፍጻሜ ፡ ደርሶ ፡ አርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ ሙሉ ፡ ክብርና ፡ መብት ፡ ባለው ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ ለመቆም ፡ በቃች ።

ስለዚህ ፤ ካህናቷና ፡ ሕዝብዋ ፡ "ወኵሉ ፡ በጥበብ ፡ ገበርከ" ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ እሙን ፡ ተፈጸመ ፡ ፍሥሓሃ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እያሉ ፡ የሚፈልቀው ፡ ደስታ ፡ ወሰን ፡ የለውም ።

## ጃንሆይ ።

ዛሬ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለራሷ ፡ የምትከብርበትንና ። ልጆቿን ፡ ምዕመናንን ፡ የምትመራበት ፡ ታላቅ ፡ የብርሃን ፡ ፋና ፡ አስጨብጠዋታል ፡ እንግዴህ ፡ ይህ ፡ በእጅዋ ፡ የያዘችው ፡ የብርሃን ፡ ፋና ፡ በጥንቃቄ ፡ እንዲጠበቅና ፡ ለምዕመናን ፡ ልጆችዋ ፡ በትክክል ፡ እንዲያበራ ፡ የማድረጉ ፡ ሥራ ፡ የኛ ፡ የካህናቷ ፡ የሕዝቧም ፡ አደራና ፡ ኃላፊነት ፡ ነው ።



## ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፤

የተቀብያውን ፡ ሥርዓት ፡ ለመፈጸም ፡ ካይሮ ፡ በነበርንበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በዚያ ፡ የሚገኙት ፡ የሃይማኖት ፡ ወንድሞቻችን ፡ ያደረጉልንን ፡ መልካም ፡ አቀባበል ፤

በተለይም ፡ ፓትርያርኩ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ዮሳብ ፡ ያደረጉልንን ፡ ያባትነትና ፡ የፍቅር ፡ አስተያየት ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ስንገልጽ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደስታ ፡ ይሰማናል ።

አምላከ ፡ ቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ጸጋውንና ፡ በረከቱን ፡ በግርማዊነትዎና ፡ በግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነን ፡ በተወደዱ ፡ ልዑላን ፡ ልጆችዎ ፡ በሕዝብዎም ፡ ሁሉ ፡ አሳድሮ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ልማትና ፡ ለሕዝቧ ፡ ደኅንነትና ፡ ቸርነትን ፡ ለመንግሥቷ ፡ ጽንዓትን ፡ እንዲሰጥልን ፤ እኛም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነትን ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ትጋት ፡ ለበቃነው ፡ መንፈሳዊ ፡ መዓርግ ፡ የተገባን ፡ እንድንሆን ፤

ደግሞም ፡ ለቤተ ፡ ክህነትና ፡ ለቤተ ፡ መንግሥት ፡ ኅብረታዊ ፡ ምልክት ፡ እንዲሆነን ፤ ከግርማዊነትዎ ፡ የተቀበልነው ፡ በትረ ፡ ክብር ፤ ለምናደርገው ፡ መንፈሳዊ ፡ ተጋድሎ ፡ በትረ ፡ መዊዕ ፡ ሆኖልን ፤ ረዐይኬ ፡ አባግዕየ ፡ የተባለውን ፡ አምላካዊ ፡ ትእዛዝ ፡ ፈጻሚዎች ፡ በመሆን ፤ ሕዝብዎን ፡ በጸሎት ፡ ለመርዳት ፡ አሐቲ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ለማገልገል ፡ እንድንበቃ ፡ ሁሉን ፡ የሚችለውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንለምናለን ።

እንዲህ ፡ ብለው ፡ ንግግራቸውን ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ ለዚህ ፡ ለታላቁ ፡ ክህነታዊ ፡ ክብር ፡ ምልክት ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ፳፩ ፡ ጊዜ ፡ የመድፍ ፡ ድምፅ ፡ ተሰማ ።

ከዚህም ፡ ተያይዞ ፡ የሻምፓኝ ፡ ግብዣ ፡ ተደረገና ፡ የጉዞው ፡ እርምጃ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያዊው ፡ ሰማዕት ፡ ወደ ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሐውልት ፡ ሆነ ።

በአቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሐውልት ፡ አደባባይም ፡ የተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ ቍጥሩ ፡ ብዙ ፡ ስለሆነ ፤ ብፁዓን ፡ አባቶቻችን ፡ በክብር ፡ ታጅበው ፡ ወደዚያ ፡ ሲደርሱ ፡ ለደስታ ፡ መግለጫ ፡ የተደረገው ፡ ጭብጨባ ፡ አደባባዩን ፡ መልቶት ፡ ነበር ።

ወዲያውም ፡ ተዘጋጅቶ ፡ የነበረውን ፡ የአበባ ፡ አክሊል ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ በመጀመሪያ ፡ አንሥተው ፡ በሐውልቱ ፡ አጠገብ ፡ አስቀመጡ ።

ከዚህም ፡ ቀጥሎ ፡ እንደተራቸው ፡ ብፁዓን ፡ ጳጳሳት ፡ ሁሉም ፡ የአበባ ፡ አክሊል ፡ በሐውልቱ ፡ ሥር ፡ ካስቀመጡ ፡ በኋላ ፡ እንደቀድሞው ፡ በአጀብ ፡ ታጅበው ፡ ተመልሰው ፡ ለማረፊያ ፡ ወደተዘጋጀላቸው ፡ ሥፍራ ፡ ሔዱ ።

## የእግዚአብሔር ፡ ሥራ ፡ ዕፁብ ፡ ድንቅ ፡ ነው ።

በግፍ ፡ የፈሰሰው ፡ የታላቁ ፡ ሰማዕት ፡ የአቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ ደም ፡ እንደ ፡ ዘካርያስ ፡ ደም ፡ ጮኸቱ ፡ ወደፈጣሪ ፡ ፊት ፡ ደርሶ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡

www.ethiopianorthodox.org

ነጻነት ፡ ደጋፊ ፡ እንደመሆኑና ፡ በታሪክ ፡ ላይ ፡ ታሪክ ፡ እየቀጠለ ፡ እንደመሔዱ ፡ መጠን ፤ ልክ ፡ ይህ ፡ ደም ፡ በፈሰሰበት ፡ ሐምሌ ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ነጻነቷን ፡ ለመረከብ ፡ ቻለች ፡፡

ከዚህም ፡ በላይ ፡ የሚያስደንቀው ፡ ይህ ፡ በግፍ ፡ የፈሰሰው ፡ የአንድ ፡ ጻድቅ ፡ ደም ፡ ከመንግሥታዊ ፡ ነጻነት ፡ ጋር ፡ ክህነታዊውንም ፡ ነጻነት ፡ አስተባብሮ ፡ አምስት ፡ ጳጳሳት ፡ ለመውለድ ፡ በመቻሉ ፡ ነው ፡፡

ይህ ፡ ሐምሌ ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ሦስት ፡ የተባበሩ ፡ በዓላት ፡ ስላሉበት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ዓቢይ ፡ በዐል ፡ ሆኖ ፡ ሊከበር ፡ ይገባዋል ፡፡

## በዚህ ፡ ቀን ፡ የዋሉት ፡ በዓላት ፡ ዝርዝር ፡፡

፩ኛ/ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ስትመኘውና ፡ ስትደክምበት ፡ የኖረችውን ፡ መንፈሳዊ ፡ ነጻነት ፡ ተረክባለች ፡፡

፪ኛ/ ፡ የታላቁ ፡ ሰማዕት ፡ የአቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ ደም ፡ በግፍ ፡ ፈሶበታል ፡፡

፫ኛ ፡ ከሐምሌ ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ፱ ፡ ሰዓት ፡ ጀምሮ ፡ ስለብፁዓን ፡ ጳጳሳት ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ሕሊና ፡ ያሰበው ፡ አሳብ ፡ ተፈጽሞበታል ፡፡

እግዚአብሔርም ፡ ይህ ፡ ቀን ፡ እንዲከብር ፡ በውነት ፡ የፈቀደ ፡ መሆኑ ፡ የሚታወቀው ፤ በ፳፩ ፡ ቀን ፡ ስንጠብቃቸው ፡ የነበሩት ፡ በፁዓን ፡ (ጳጳሳት) ፡ አባቶቻችን ፡ በዓየር ፡ ምክንያት ፡ ቀርተው ፡ የአቡነ ፡ ጴጥሮስን ፡ ሰማዕትነት ፡ ለማዘከር ፡ ሐምሌ ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ እንድናያቸው ፡ በማድረጉ ፡ ነው ፡፡

በዚህም ፡ በገቡበት ፡ ሐምሌ ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ በ፰ ፡ ሰዓት ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ለወንድሞቻቸው ፡ ለብፁዓን ፡ ጳጳሳትና ፡ ለሊቃውንት ፡ የምሳ ፡ ግብዣ ፡ አድርገዋል ፡፡

---

## ሐምሌ ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በመናገሻ ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ስለብፁዓን ፡ ጳጳሳት ፡ ሢመት ፡ የተደረገ ፡ የበዓል ፡ አከባበር ፡፡

ስለብፁዓ ፡ አባቶቻችን ፡ በገቡበት ፡ ሐምሌ ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ በአንድ ፡ ትልቅ ፡ ዱብር ፡ መንፈሳዊ ፡ ክብረ ፡ በዓል ፡ ለማድረግ ፡ ሰዓቱ ፡ ያጠረ ፡ በመሆኑ ፡ ይኸው ፡ በዓል ፡ ሐምሌ ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ በመናገሻ ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዲደረግ ፡ አስቀድሞ ፡ በራዲዮን ፡ ተነግሮ ፡ ስለነበረ ፤ የቅዱስ ፡ ጊዮርጊስም ፡ በዓል ፡ አጋጥሞት ፡ ነበረና ፡ ከሌሊቱ ፡ ጀምሮ ፡ ማኅሌቱና ፡ አደራረሱ ፡ ሲያምር ፡ አደረ ፡፡

ሌሊቱም ፡ አልፎ ፡ መዓልቱ ፡ ሲተካ ፡ ፖሊሶች ፡ የበዓሉን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በደንብ ፡ ይጠባበቁ ፡ ጀመር ፤ ልክ ፡ ፬ ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ የክብር ፡ ዘበኞች ፡



መጥተው ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ዙሪያ ፡ ተሰልፈው ፡ ደስ ፡ በሚያሰኝ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቆመው ፡ ሲጠባበቁ ፡ ለበዓሉ ፡ ሞገስ ፡ ሆነውት ፡ ነበር ፡፡

፬ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ሲሆን ፡ ብፁዓን ፡ ጳጳሳት ፡ ታጅበው ፡ መጥተው ፡ ወደ ፡ ቅጽረ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሲገቡ ፤ የሕዝቡ ፡ ደስታ ፡ በጭብጨባ ፡ ተገለጠ ፡፡

ያሁኖቹ ፡ ፭ቱ ፡ ብፁዓን ፡ ጳጳሳትና ፡ የቀድሞው ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ይስሐቅ ፡ በወርቅ ፡ የተንቆጠቈጠ ፡ ካፓ ፡ ላንቃ ፡ ለብሰው ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተሸለሙትን « ፡ አንበሳ ፡ ወጽአ ፡ እምገዳም ፡ ውእቱኬ ፡ ወልድ ፡ አምላክ ፡ ውእቱ » ፡ የሚል ፡ ጽሑፍና ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ ሥዕለ ፡ አንበሳ ፡ ያለበትን ፡ በትረ ፡ ጳጳሳት ፡ አንዳንድ ፡ ልዑካን ፡ ይዘውላቸው ፡ ሕዝቡን ፡ በመስቀል ፡ እየባረኩ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገብተው ፡ ሕሊናዊ ፡ ጸሎት ፡ ያደርሱ ፡ ጀመር ፡፡

ልዑላን ፡ መሳፍንትና ፤ ክቡራን ፡ መኳንንት ፤ ሚኒስቴሮችና ፡ ሊቃውንት ፤ ሕዝባውያንም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ በስተውጭ ፡ ሆነው ፡ ይጠባበቁ ፡ ነበር ፡፡

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ሊቀ ፡ መዘምራን ፡ አክሊሉ ፡ ድምፅ ፡ በሚያጕላ ፡ መኪና ፡ ለሕዝቡ ፡ ያሰሙት ፡ ቃለ ፡ ስብከትና ፡ ጊዜያዊ ፡ አስተያየት ፡ ከሕሊና ፡ የሚዋሐድ ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል ፡፡

፭ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ሲሆን ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፤ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽን ፤ አስከትለው ፡ በመኳንንቶቻቸው ፡ ታጅበው ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ በደስታ ፡ ተቀበላቸው ፡፡

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ከታሪክና ፡ በዜና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የተዘጋጀ ፡ የበዓሉ ፡ ፕሮግራም ፡ በአቶ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ተሰማ ፡ እጅ ፡ በዚያ ፡ ለተሰበሰቡት ፡ ሊቃውንትና ፡ መምህራን ፡ ታደለ ፤ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትም ፡ ጸሎተ ፡ ሕሊና ፡ አድርሰው ፡ ወጥተው ፡ በተዘጋጀላቸው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ በተቀመጡ ፡ ጊዜ ፡ የተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ በሙሉ ፡ እጅ ፡ ነሣ ፡፡

ብፁዓን ፡ ጳጳሳት ፤ ልዑላን ፡ መሳፍንት ፡ ክቡራን ፡ መኳንንትና ሚኒስትሮች ፡ ወደ ፡ ዐውደ ፡ ምሕረቱ ፡ ቀርበው ፡ በተዘጋጀላቸው ፡ የክብር ፡ ቦታ ፡ ተቀመጡ ፡፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ካህናቱ ፡ ጸሎተ ፡ ወንጌል ፡ ማድረስ ፡ ጀመሩ ፡፡

## ምስባክ ፡፡

ሀየንተ ፡ አበውኪ ፡ ተወልዱ ፡ ለኪ ፡ ደቂቅ ፡ ወትሠይሚዮሙ ፡ መላእክተ ፡ ለኵሉ ፡ ምድር ፡ ወይዘክሩ ፡ ስመኪ ፡ በኵሉ ፡ ትውልደ ፡ ትውልድ ፡፡

## ከዮሐንስ ፡ ወንጌል ፡፡

ም ፡ ፲ ቁ ፡ ፩ ፡ አማን ፡ አማን ፡ እብለክሙ ፡ የሚለው ፡ ከተነበበ ፡ በኋላ ፤ ምራቱ ፡ ለገነተ ፡ ጽጌ ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ካህናት ፡ ተሰጠና ፡ ቀኝ ፡ ጌታ ፡ ተክለ ፡ ሚካኤል ፡ መሪ ፡ ሲሆኑ ፡ ደብተራ ፡ ኃይለየስ ፡ ለተመሪነት ፡ ቀረቡ ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

## ምልጣን ።

ዓይ ፡ ይእቲ ፡ ዛቲ ፡ መድኃኒት ፡ እንተ ፡ ኃሠሥዋ ፡ ወያድዋ ፡ ነቢያት ፡ ወይቤሉ ፡ ለኖኅ ፡ አመ ፡ አይኅ ፡ ግብር ፡ ታቦተ ፡ በዘትድኅን ፡ እትአመን ፡ ባቲ ፡ እስመ ፡ አርአያ ፡ መስቀል ፡ ይእቲ ፡ አክሊለ ፡ ተቀጺላ ፡ታንሶሱ ።

አንሽነቱም ፡ ለመናገሻ ፡ ቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ደብር ፡አለቃ ፤ ለአለቃ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ተሰጥቶ ፡ ነበረና ፡ በሽምግልናቸው ፡ ወራት ፡ ይኸንን ፡ የመሰለ ፡ የድምፅ ፡ ጣዕምና ፡ ላህይ ፡ በማሰማታቸው ፡ ሰሚዎችን ፡ አስደሰቱ ።

## እስመ ፡ ለዓለም ።

ሢመከሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጳጳሳተ ፡ ቀሳውስተ ፡ ወዲያቆናት ፡ ከመ ፡ ትርዐዩ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ እንተ ፡ አጥረያ ፡ በደሙ ፡ ወዐተበ ፡ በዕፀ ፡ መስቀሉ ።

## ዕ ዝ ል ።

በጽድቅ ፡ ወበተፋቅሮ ፡ እስመ ፡ ረከብኩ ፡ እምውስተ ፡ ደቂቅኪ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ በነቢይ ። የሐነጹ ፡ አሕዛብ ፡ አረፉተኪ ፡ አምኂ ፡ ደቂቀ ፡ እኅትኪ ፡ ኅሪት ፡ መድኃኒት ፡ ወሕይወት ፡ ህየንተ ፡ አበውኪ ፡ ተወልዱ ፡ ለኪ ፡ ደቂቅ ።

## ግ ሥ ።

ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ በነቢይ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በጽድቅ ፡ ወበተፋቅሮ ፡ እስመ ፡ ረከብኩ ፡ እምውስተ ፡ ደቂቅኪ ።

መድኃኒት ፡ ወሕይወት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አምኂ ፡ ደቂቀ ፡ እኅትኪ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ህየንተ ፡ አበውኪ ፡ ተወልዱ ፡ ለኪ ፡ ባስልዮስ ፡ ወይስሐቅ ፤ ሚካኤል ፤ ቴዎፍሎስ ፤ ወያዕቆብ ፤ ወጢሞቴዎስ ፡ ብርሃናተ ፡ ዓለም ።

ይኸንን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈውን ፡ ግሥ ፡ ሊቀ ፡ መዘምራን ፡ አክሊሉ ፤ ገብረ ፡ ኪሮስ ፡ አቶ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ተሰማ ፤ አቶ ፡ ቤተ ፡ ማርያም ፡ ዘወልዴ ፡ ቀርበው ፡ በወረቡት ፡ ጊዜ ፤ የወረቡ ፡ መተካከልና ፡ የድምፃቸው ፡ መተባበር ፡ የላህያቸውም ፡ ውበት ፡ ሰሚውን ፡ ሁሉ ፡ አስደስቶት ፡ ነበር ።

## ፪ኛ ግሥ ።

ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አነ ፡ አጽናዕኩ ፡ አዕማዲሃ ፡ ይቤ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፤ እሉ ፡ እሙንቱ ፡ ጳጳሳት ፡ ባሽልዮስ ፡ ወሚካኤል ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ወያዕቆብ ፡ ወጢሞቴዎስ ።

ይኸንንም ፡ ፪ኛውን ፡ ግሥ ፡ የጊዮርጊስ ፡ ካህናት ፡ ወረቡትና ተሽበሸበበት ። በዚህም ጊዜ ፡ በታሪክና ፡ በዜና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጽሒፈት ፡ የተዘጋጀ ፡ መንፈሳዊ ፡ መዝሙር ፡ በሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ በፀባቱ ፡ ጥዑመ ፡ ልሳን ፡ አማካይነት ፡ ቀርቦ ታደለ ።



ከፈለገ ፡ ሕይወት ፡ ትምህርት ፡ ቤትም የተዘጋጀ ፡ መዝሙር ፡ በዋናው ሹም ፡ በአለቃ ፡ ልሳነ ፡ ወርቅ ፡ አማካይነት ፡ ቀርቦ ፡ ታድሏል ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተማሪዎች ፡ ምሥጢሩ ፡ ከዜማው ፡ የተዋሐደ ፡ መዝሙር ፡ ሲዘምሩ ፡ በጣም ፡ አስደሰቱ ።

ለዚሁ ፡ በዓል ፡ የተዘጋጁትን ፡ ፀዋትወ ፡ ዜማ ፡ ሁሉንም ፡ በጽሑፍ ፡ እንገልጻለን ።

## አ ቡ ን በ ፯ ።

ለሰሚዕ ፡ ዕፁብ ፡ ግብር ፡ ለሰሚዕ ፡ ዕፁብ ፡ ግብር ፡ ጥበቡ ፡ ለእግዚአብሔር ለለዕፁብ ፡ ግብር ። አጽናፈ ፡ ዓለም ፡ እለ ፡ ተዘርዉ ፡ ለስብከተ ፡ ወንጌል ፡ አስተጋብአሙ ፡ በምዕር ፡ ለለዕፁብ ፡ ግብር ። በ ፡ እለ፡ተንሥኡ፡ተጽዒኖሙ ፡ ደመና ፡ብሩህ፡ ለለዕፁብ ፡ ወተፈሥሑ ፡ ሐዋርያት ፡ ሰበ ፡ ተጋብኡ ፡ ኅቡረ ፡ ገብሩ ፡ በከመ ፡ አዘዞሙ ፡ ወከመ ፡ ቀዳሚ ፡ ተመይጡ ፡ ኵሎሙ ።

## አራራይ ፡ እስመ ፡ ለዓለም ።

ወኃይዝተ ፡ ወንጌል ፡ የዐውዳ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እም፬ቱ ፡ አፍላጋት ፡ እንተ ትሰቀይ ፡ ትምህርተ ፡ ለለጽባሒ ፡ እማቴዎስ ፡ ልደቶ ፡ ወእማርቆስ ፡ መንክራቶ ፡ እምሉቃስ ፡ ዜናዊ ፡ ተሰምዮ ፡ ላህም ፡ ወእምዮሐንስ ፡ በግዐ ፡ ወዘንተ ፡ ሰሚዓ ፡ ትገብር ፡ በዓለ ፡ በፍግዓ ።

## ቅንዋት ፡ እስመ ፡ ለዓለም ።

ሥዩማን ጳጳሳት ፡ እለ ፡ ይጸውሩ ፡ አርዑተ ፡ መስቀሉ ፡ ለክርስቶስ ፡ እለ ፡ ሎሙ ሕግ ፡ ወሎሙ ፡ ሥርዓት ፡ እስመ ፡ ሕግ ፡ ይወፅእ ፡ እምአፈ ፡ ካህናት ፡ ምክረ ፡ ራትዓን ፡ አእምሮ ፡ ዲበ ፡ ቅዱሳን ፡ ተኀድር ።

## ሠ ለ ስ ት

ኃይል ፡ ክርስቶስ ፡ ውእቱ ፡ ለሰማዕት ፡ አክሊል ፡ ንጹሕ ፡ ለጳጳሳት ።

## ሰ ላ ም ።

ሰላም ፡ ለክሙ ፡ አማኅበራኒሁ ፡ ለክርስቶስ ፡እለ ፡ ተጋባእክሙ፡ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ደብር ፤ ጳጳሳት ፤ ቀሳውስት ፡ ወዲያቆናት ፤ ሰላም ፡ ለክሙ ፡ አማኅበረ ፡ ደናግል ፡ ወመነኮሳት ፡ እለ ፡ተመሰልክሙ ፡ ከመ ፡ መላእክት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ አቡነ ፡ ይስሐቅ ፡ አሳርገው ፡ በውጪ፡ የተዘጋጀው፡የበዓሉ ፡ ሥነ ሥርዓት ፡ ተፈጸመና ፡ ብፁዓን ፡ ጳጳሳት ፡ ቀዳስያን ፡ ሆነው ፡ በ፮ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ሥርዓተ ፡ ቅዳሴው ፡ ተጀመረ ፤ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትም ፡ በዚያው ፡ ቆመው ፡ አስቀደሱ ።

www.ethiopianorthodox.org

ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ገባሬ ፡ ሠናይ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ተራዳኢ ፡ ሆነው ፡ ሲቀድሱ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አሰኝተው ፡ ነበር ።

በዚሁም ፡ ቀን ፡ ከቀኝ ፡ ጌታ ፡ ተክለ ፡ ሚካኤል ፡ የተደረሰው ፡ ቅኔ ፡ ይቀጥላል ፤

## ክ ብ ር ፡ ይ እ ቲ ።

ኃያል ፡ ሶምሶን ፡ ለእመ ፡ ሞዐ ፡ ሰብአ ፡ ኢሎፍሊ ፡ አዕራረ ፡

ፈቀደ ፡ ይሙት ፡ ምስለ ፡ ኢሎፍሊ ፡ ኅቡረ ፡

በይነ ፡ ሰብአ ፡ ፍዳሰ ፡ ወልድ ፡ ለእመ ፡ ሞተ ፡ ሰብአ ፡ አፍቀረ ፤

አሕየወ ፡ ሰብአ ፡ ወአሰሰለ ፡ ሞተ ፡ ሰብአ ፡ ምድር ፡ መሪረ ።

## ዕ ዝ ል ፡ ዕጣነ ፡ ሙ ገ ር ።

ኢትዮጵያ ፡ አድማስ ፡ ወእስክንድርያ ፡ ጠፈር ፡

ዲበ ፡ ኰኵሐ ፡ ማርቆስ ፡ ጸንዓ ፡ ከመ ፡ አድባር ፡

ምሳሌ ፡ ዘርአ ፡ ጽድቅ ፡ እስከ ፡ ነሥአ ፡ ለሥርወ ፡ ጳጳሳት ፡ ክብር ፡

እስመ ፡ ዐርጋ ፡ በታቦር ።

ወኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ መርሐሙ ፡ ለእሉ ፡ በሕዋረ ፡ ማርቆስ ፡ ኄር ፡

ብርሃነ ፡ አምጣነ ፡ አመሮ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ንስር ፡

ፋሲካ ፡ ሃይማኖት ፡ ትገብር ፡ ለጳጳሳት ፡ ኢትዮጵያዊት ፡ ምድር ፡

እንዘ ፡ ዮም ፡ ትትሐጸብ ፡ ፀደሙ ፡ ለእግዚአ ፡ ባስልዮስ ፡ በኵር ፡

በኃይለ ፡ ሥላሴሰ ፡ እስክንድር ፡

እስክንድርያ ፡ ተሰምየት ፡ ዛቲ ፡ ሀገር ፡

ወበዛቲ ፡ ተገሠጸት ፡ ባሕር ።

---

ስለ ፡ ብፁዓን ፡ ጳጳሳት ፡ ክብረ ፡ ሢመት ፡ በታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡

## የተደረገ ፡ ግብዣ ።

ስለ ፡ ብፁዓን ፡ አባቶቻችን ፡ በዓል ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ ግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ባሉበት ፡ በታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሐምሌ ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ከ፯ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ እስከ ፡ ፱ ፡ ሰዓት ፡ ለብፁዓን ፡ ጳጳሳትና ፡ ለልዑላን ፡ መሳፍንት ፤ ለክቡራን ፡ መኳንንትና ፡ ለሚኒስቴሮች ፡ ለሊቃውንትና ፡ ለመምህራን ፤ ለዲሬክተሮችና ለወይዛዝር ፤ ታላላቅ ፡ ለሆኑም ፡ ለመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፤ ከከተማው ፡ አድባራትና ፡ ከየአውራጃውም ፡ ለመጡ ፡ አለቆችና ፡ ካህናት ፡ ታላቅ ፡ ግብዣ ፡ ተደረገ ።

በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ትጋትና ፡ ዕድል ፡ ኢትዮጵያዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ በትረ ፡ ክብር ፡ ጨበጠች ፡ እየተባለ ፡ ከእያንዳንዱ ፡ ተጋባዥ ፡ ይነገር ፡ ነበር ።

ስድስቱም ፤ ብፁዓን ፡ ጳጳሳት ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተሸለሙትን ሊሻናት ፡ አድርገው ፡ በግርማዊነታቸው ፡ ዙፋን ፡ አጠገብ ፡ ተቀምጠው ፡ ሲታዩ ፡ «ወክ



ሀን ፡ ይነብር ፡ በየማነ ፡ ንጉሥ» ፡ የተባለውን ፡ መጽሐፋዊ ፡ ንግግር ፡ ከማሳሰባቸው ጋር ፡ የካህናት ፡ ክብር ፡ ምጡቅነት ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ለተመልካች ፡ ሁሉ ፡ አስረድተዋል ።

በመጨረሻውም ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ሚካኤል ፡ ተነሥተው ፡ ከቡራኬ ፡ ጋር ፡ አጭር ቃለ ፡ ስብከት ፡ አደረጉ ፤ ቃሉም ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

መልካም ፡ ዕንጨት ፡ መልካም ፡ ፍሬን ፡ እንደሚያፈራ ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችንም ፡ መልካሙ ፡ ሥራቸው ፡ ያስገኘው ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ በዓለም ፡ ላይ የታወቀ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፤ ለዚህ ፡ ለመልካሙ ፡ ሥራቸው ፡ የእኛ ፡ እርዳታ ፡ ይጨመርበት ፡ ዘንድ ፡ ያስፈልጋል ። አሁን ፡ እኛ ፡ በዚህ ፡ በተቀበልነው ፡ ከባድ ፡ ኃላፊነት ፡ ብፁዕና ፡ ቅዱስ ፡ ብትሉን ፡ ምንም ፡ አይደለም ።

ይልቅስ ፡ ሁላችንም ፡ አንድ ፡ ሆነን ፡ ብፁዓን ፡ የምንባልበትን ፡ በጎ ፡ ምግባር መሥራት ፡ ነው ። ለያንዳንዳችን ጥቅም ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ አንዱ ፡ ላንዱ ፡ ሌላው ፡ ደግሞ ፡ ለሌላው ፡ ያስብለት ፤ መልካም ፡ ውለታ ፡ ይዋልለት ፤ «ለራሳችሁ ፡ ሊያደርጉላችሁ ፡ የምትወዱትን ፡ ለሌላውም ፡ አድርጉለት ።

«ለራሳችሁ ፡ ሊያደርጉባችሁ ፡ የማትወዱትን ፡ ግን ፡ ለሌላውም ፡ አታድርጉበት ፡ ተብሎ ፡ ተጽፏልና ፡ ይህን ፡ ስንፈጽም ፡ ብንገኝ ፡ ፈጻምያነ ፡ ሕግ ፡ ለመሆን ፡ እንችላለን ፡ ብለው ፡ መንፈሳዊ ፡ ስብከታቸውን ፡ ሲጨርሱ ፡ አሳርገው ፡ ባርከው ፡ የግብዣው ፡ ፍጻሜ ፡ ሆነ ።

## ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ለብፁዓን ፡ ጳጳሳት ፡ የተሰጠ ፡ ሽልማት ።

ግርማ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ክብር ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ እንዲታይ ፡ በየጊዜው ፡ የሚያደርጉት ፡ ድካም ፡ ብዙ ፡ የታሪክ ፡ ገጽ ፡ የያዘ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ ሐምሌ ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ለመንፈሳውያን ፡ አባቶቻችን ፡ ለብፁዓን ፡ ጳጳሳት ፡ ታላቅ ፡ ክብር ፡ ያለው ፡ ሽልማት ፡ ሸለሟቸው ።

የሽልማቱም ፡ ዓይነት ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለው ፡ ነው ።

ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ ዕጨጌነቱን ፡ ሲሾሙ ፡ እንደ ፡ ተሸለሙት ፡ ያለ ፡ ባለኮርዶን ፡ ሊሻን ፡ ሲያደርጉ ፤

ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ይስሐቅ ፡ ከማንደር ፡ የሥላሴ ፡ ሊሻን ፤

ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ሚካኤል ፡ " " "

ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ " " "

ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ያዕቆብ ፡ " " "

ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ " " "

ተሸለሙ ።

www.ethiopianorthodox.org

የኢትዮጵያ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለዚህ ፡ ከፍ ፡ ላለው ፤ ታላቅ ፡ መዓርግ ፡ ያበቁዋት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታቸው ፡ እንዲጸና ፡ ሕዝባቸውም ፡ እንዲጠበቅ ልባዊ ፡ ጸሎቷን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በማቅረብ ፡ ውለታዋን ፡ ማሰብ ፡ ይኖርባታል ።

## የራት ፡ ግብዣ ።

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጠቅላይ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ብፁዓን ፡ አባቶቻችን ፡ ጳጳሳት ፡ ክብር ፡ ሐምሌ ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ከማታው ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ጀምሮ ፡ ለልዑላን ፡ መሳፍንትና ፡ ለክቡራን ፡ መኳንንት ፡ ለሚኒስቴሮችና ፡ ለሊቃውንት ፡ ታላላቅ ፡ ለሆኑ ፡ ለመንግሥት ፡ ሠራተኞችና ፤ በከተማ ፡ ነዋሪ ፡ ለሆኑ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ለከተማው ፡ አድባራትና ፡ ከየአውራጃውም ፡ ለመጡ ፡ አለቆች ፤ ለመምህራንና ፡ ለቀሳውስት ፤ ለመዘምራንም ፡ በማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ አዳራሽ ፡ ውስጥ ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ አድርጎ ፡ ነበር ።

የግብዣውም ፡ ሥነ ሥርዓት ፡ ከአዲሱ ፡ ሥልጣኔ ፡ አንቀጽ ፡ የተወሰደ ፡ ስለ ሆነ ፤ ማናቸውም ፡ ተጋባዥ ፡ የፈቀደውን ፡ በራሱ ፡ ሥልጣን ፡ ከማግኘቱ ፡ የተነሣ ፡ በምግቡና ፡ በመጠጡ ፡ እንደመፍቅዱ ፡ ሊያዝባቸው ፡ ችሎታ ፡ አግኝቶ ፡ ነበር ።

ይህም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ አስተናባሪዎችንና ፡ አሳላፊዎችን ፡ የሚያሳማ ፡ ሆኖ ፡ ባለመገኘቱ ፡ በጣም ፡ የተወደደና ፡ ሊከተሉት ፡ የሚገባ ፡ ሆኗል ።

ተጋባዦዎችም ፡ ጥሪያቸውን ፡ አክብረው ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ መጥተው ፡ ነበረና ፡ በዚያው ፡ እንዳሉ ፡ ብፁዓን ፡ ጳጳሳት ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ የደስታ ፡ ስሜታቸውን ፡ በጭብጨባ ፡ ገለጡ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ግብዣው ፡ በመጠጥ ፡ ተጀመረና ፡ በታሪክና ፡ በዜና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የተዘጋጁት ፡ ወረቦችና ፡ ቸብቸቦዎች ፡ ቀጠሉ ።

ለዚሁም ፡ መሪውና ፡ አስተናባሪው ፡ አቶ ፡ ደምሴ ፡ ወርቅ ፡ አገኘሁ ፡ ስለነበሩ ፡ ሥነ ፡ በዓሉ ፡ ውበትና ፡ ቅልጥፍናን ፡ ተመልቶ ፡ ነበር ።

፩ኛ ግሥ ፤ እምትካት ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ፤ እስከ ፡ ለዓለም ፡ አንተ ፡ ክመ ፡ ዘእምቅድመ ፡ ዓለም ፤ ዘእምቅድመ ፡ ዓለም ፡ መንግሥቱ ፡ ሰፋኒት ፡ ለእግዚአብሔር ። ንእምን ፡ መንግሥቶ ፡ ለኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ እዘዝ ፡ ለጳጳሳት ፡ ባስልዮስ ፡ ወአኃዊሁ ።

፪ኛ ለጳጳሳቱ ፡ ሥነ ፡ በዓል ፡ በመናገሻ ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተወረበው ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ በነቢይ ፡ የሚለው ፡ ግሥ ፡ ቀጠለ ።

፫ኛ. በደብረ ፡ ነጐድጓድ ፡ (ሐይቅ) ፡ በአቡነ ፡ ኢየሱስ ፡ ሞዐ ፡ ጊዜ ፡ ተጀምሮ ፡ ከጼ ፡ ሰይፈ ፡ አርእድ ፡ መንግሥት ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ የሚነገረው ፡ ቃለ ፡ ይባቤ ፡ በጣዕማዊ ፡ ድምፅ ፡ ካለቃ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ዘሙናገሻ ፡ ማርቆስ ፡ በተነገረ ፡ ጊዜ ፡ ከነተቀባዮቻቸው ፡ ደስ ፡ አሰኝተዋል ።



## በዜማ ፡ የተናገሩት ፡ ቃለ ፡ ይባቤም ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለው ፡ ነው ።

አድባራት ፡ ወገዳማት ፡ ከማሃ ፡ ኢይመስላ ። ደብሩሰ ፡ ለኢየሱስ ፡ ሞዐ ፡ ትመስል ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ ኢየሱስ ፡ ሞዐ ፡ በምሥራቅ ፡ ሃሌ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ። ትቤለከ ፡ ነዓ ፡ ደብረ ፡ ሐይቅ ፡ ሃሌ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ። በደብረ ፡ ነጐድጓድ ፡ ዘመከሩ ፤ ሃሌ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ በሰይፈ ፡ ሚካኤል ፡ ይትመተሩ ፡ ሃሌ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ። ኢየሱስ ፡ አምላኩ ፡ ለአሞፅ ፡ ሃሌ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ሰቀሉከ ፡ እፎ ፡ ዲበ ፡ ዕፅ ። ኢየሱስ ፡ አምላኩ ፡ ለይሁዳ ፡ ሃሌ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ አልበሱኩ ፡ እፎ ፡ ከለሜዳ ፡ ሃሌ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ። አምላክ ፤ ማርያ ፡ ወማርታ ፡ ሃሌ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ቀበሩከ ፡ እፎ ፡ ጎልጎታ ፡ ሃሌ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ።

፬ኛ ለሰሚዕ ፡ ዕፁብ ፡ ግብር ፡ ጥበቡ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አጽናፈ ፡ ዓለም ፡ እለ ፡ ተዘርዉ ፡ ለስብከተ ፡ ወንጌል ፡ አስተጋብአሙ ፡ በምዕር ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በ ፡ እለ ፡ ተንሥኡ ፤ ተዕዪኖሙ ፡ ደመና ፡ ብሩህ ፡ ደመና ፡ ብሩህ ።

፭ኛ በብርሌው ፡ በብርጭቆው ፡ ቀዳበት ፡ ሲል ፡ ከዳር ፡ ዳር ፡ ላይቀር ፡ ብሎ ፡ መቃብር ፡ ጐንደር ፡ ጐንደር ፡ ዓጼ ፡ ኢያሱ ፡ ምንሽ ፡ ነበር ፡ የሚለውን ፡ ከዓጼ ፡ ኢያሱ ፡ ዘመን ፤ በኋላ ፡ ይደረግ ፡ የነበረውን ፡ እንደዘፈንም ፡ እንደወረብም ፡ የሚሆነውን ፡ ታሪኩን ፡ ከመናገር ፡ ጋር ፡ በመልከም ፡ ድምፅ ፡ ከመጋቢ ፡ መክብብ ፡ ደበበ ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ የተጋባዦቹ ፡ ልብና ፡ ዓይን ፡ ከአሰሚው ፡ ጋር ፡ ነበር ።

፮ኛ ቸብቸቦ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ንጉሥኪ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ኢይትመዋዕ ፡ ለፀር ፡ ወኢየኀድጋ ፡ ለሀገር ፡ ወኢየኀድጋ ፡ ለሀገር ፤ ወኢየኀድጋ ፡ ለሀገር ፤ ወኢየኀድጋ ፡ ለሀገር ።

እነዚህን ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሱትን ፡ ወረቦች ፡ አለቃ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ዘመናገሻ ፤ አቶ ፡ ቤተ ፡ ዘወልዴ ፡ ዘበአታ ፤ መጋቢ ፡ መክብብ ፡ ዘበአታ ፤ ሊቀ ፡ መዘምራን ፡ አክሊሉ ፡ ዘበአታ ፤ አቶ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ተሰማ ፡ ዘአዲስ ፡ ዓለም ፡ በመተባበርና ፡ ጣዕም ፡ ባለው ፡ ድምፃቸው ፡ ሲወርቡት ፡ እነሱን ፡ መስማት ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ መንፈሳዊ ፡ ግብዣ ፡ ያህል ፡ ተቈጥሮ ፡ ነበር ።

አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በመካከል የሀገር ፡ ፍቅር ፡ ማኅበር ፡ ተጫዋቾች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዜማ ፡ የሚያሰሙት ፡ መዝሙርና ፤ የሚያሳዩት ፡ እጅ ፡ አነዛዘር ፡ በጣም ፡ አስደንቆ ፡ ነበር ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከክቡር ፡ ቢትወደድ ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፡ የተደረሰው ፡ የደም ፡ ድምፅ ፡ የተባለው ፡ የታላቁን ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሰማዕት ፡ የአቡነ ፡ ጴጥሮስን ፡ የሰማዕትነት ፡ ገድል ፡ የሚያሳየው ፡ ትያትር ፡ ሲደረግ ፡ በዚያ ፡ የተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ የደስታ ፡ ስሜቱን ፡ ወደኃዘንና ፡ ወደ ፡ ለቅሶ ፡ አዘነበለ ።

እውነት ፡ ነው ፤ ትያትሩ ፡ እንደሚያመለክተው ፡ ፍጡር ፡ ሆኖ ፡ ለሞት ፡ ይኸን ፡ ያህል ፡ ጥብዓት ፡ (ጭከኔ) ፡ ማድረግ ፡ እንዲሁም ፡ ፍጡር ፡ ሆኖ ፡ ይኸንን ፡

www.ethiopianorthodox.org

የሚያህል ፡ ስንኳን ፡ ሲያዩትና ፡ ሲሰሙት ፡ እንኳ የሚያንገፈግፍ ፡ ዕፅፍ ፡ ድርብ ፡ የሆነ ፡ ጭከኔ ፡ በፍጡር ፡ ላይ ፡ መፈጸሙ ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ሲያሳዝን ፤ ባንድ ፡ በኩል ፡ ያስገርማል ።

የማይሞትና ፡ መከራ ፡ የማይደርስበት ፡ ይህን ፡ አድርጎት ፡ ቢሆን ፡ እምብዛም ፡ ባልተደነቀ ፡ ነበር ፤ የሚያስገርመው ፡ የሞተውና ፡ የሚሞተውም ፡ ሰው ፡ ይኸንን ፡ ያህል ፡ ግፍና ፡ ጭከኔ ፡ ማሳየቱ ፡ ነው ። ባንድ ፡ በኩልም ፡ የአቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ ቆራጥነት ፡ ነው ።

ይህ ፡ ትያትር ፡ እስኪፈጸም ፤ ትያትሩ ፤ የሰው ፡ ልቡና ፡ ዓይኑ ፡ ሦስቱም ፡ አንድ ነት ፡ ነበሩ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አቶ ፡ አፈወርቅ ፡ አዳፍሬ ፡ ከዚህ ፡ ትያትር ፡ ጋር ፡ የተስማማ ፡ ንግግር ፡ አደረጉ ።

ከዚህም ፡ አያይዘው ፡ መምህር ፡ ሐረገ ፡ ወይን ፡ «የስንዴ ፡ ቅንጣት ፡ ካልተዘራችና ፡ ካልሞተች ፡ ብዙ ፡ ፍሬ ፡ አታፈራም ፤ ብትዘራና ፡ ሞታ ፡ ብትነሣ ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ፍሬ ፡ ታፈራለች ። አቡነ ፡ ጴጥሮስም ፡ ያንን ፡ ከባድ ፡ ግርማ ፡ ያለውን ፡ መሪር ፡ ሞት ፡ በብሩህ ፡ ገጽ ፡ ተቀብለው ፡ ስለሞቱ ፤ እነሆ ፡ በብዙ ፡ የሚቆጠሩ ፡ ብፁዓን ፡ ጳጳሳትን ፡ ለማግኘት ፡ ቻልን» ፡ ብለው ፡ መንፈሳዊ ፡ ስብከታቸውን ፡ ከትያትሩ ፡ ጋር ፡ አስማምተው ፡ አሳረጉ ።

ይህም ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፤ የአቡነ ፡ ጴጥሮስን ፡ ነፍስ ፡ መልአኩ ፡ በክብር ፡ እንዳሳረጋት ፡ ትያትሩ ፡ አመልክቶ ፡ ነበርና ፡ ምሥጢሩን ፡ ከምሥጢር ፡ በማያያዝ ፡ ስማቸው ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ሰዎች ፡ በቸብቸቦ ፡ «አልበሙ ፡ ድምፅ ፡ ወኢይሰማእ ፡ ድምፀ ፡ ክነፊሆሙ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ ሶበሰ ፡ ይወርዱ ፡ መላእክት» ፡ የሚል ፡ ወረብ ፡ ወረቡ ። ከዚህም ፡ ተያይዞ ፡ አስተጋብአተነ ፡ ቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አንተ ፡ ጳጳሳት ፡ ኀበ ፡ ሀለዉ ፡ አግብርተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ህየ ፡ ንሰግድ ፡ ኵልነ ፡ ወበ ህየ ፡ ንትፌሣሕ ፡ ኅቡረ ፡ ተወረበና ፡ የግብዣው ፡ ፍጻሜ ፡ ሆነ ።

---

## የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መነኰሳት ፡ ታሪክ ።

ይህ ፡ ታሪክ ፡ ፩ኛ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ደብረ ፡ አስቦን ፡ (ደብረ ፡ ሊባኖስን ፡) እንዴት ፡ እንደቆረቆሩትና ፡ በእመቤታችን ፡ በቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ስም ፡ የተቀረጸች ፡ ጽላት ፡ ፊት ፡ ጸሎታቸውን ፡ ሲያሳርጉ ፡ እንደነበረ ፤ (፪ኛ) ፡ የእመቤታችን ፡ ጽላት ፡ በዓፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መነኰሳትና ፡ እጨጌው ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ይዘዋት ፡ እንደሔዱ ።

፫ኛ ፡ የእመቤታችን ፡ ጽላት ፡ በአፄ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ከጐንደር ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ተመልሳ ፡ በጥንታዊ ፡ መንበርዋ ፡ እንደኖረች ።

፬ኛ ፡ ብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የአፄ ፡ ምኒልክን ፡ ጅምር ፡ ፈጻሚ ፡ የነው ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ በተባለችዋ ፡ ቦታ ፡ በእመቤታችን ፡ ስም ፡ ቤተ ፡ ክርስ



ቲያን ፡ እንደ ፡ አነጸ ፡ የሚያሳይ ፡ ነው ። አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አስቦ ፡ ዛሬ ፡ ግን ፤ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ወደሚባለው ፡ ትልቅ ፡ ዋሻ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፤ በግራርያ ፡ ውስጥ ፡ ከነበሩ ፡ መሠርያን ፡ ሁሉ ፡ የከፋ ፡ ሐረስ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ መሠርይ ፡ ወደነበረበት ፡ ሲገቡ ፤ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ እየዘመሩ ፤ ከዳዊትም ፡ መዝሙር ፡ «አንተ ፡ ሰበ ፡ ጸዋዕኩዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እድኅን ፡ እምፀርየ ፡ ወይባልሐኒ ፡ እምጸላእትየ ፡ ምንስዋን„ ፡ የሚለውን ፡ እየጸለዩ ፡ ሔደዋል ።

ሐረስም ፡ ይኸንን ፤ ገና ፡ በሩቅ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፤ በፍጹም ፡ ፍርሀትና ፡ ድንጋጤ ፡ ሸሽቷል ። ዳግመኛም ፡ በዚያ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ አልታየም ። አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ወደዚች ፡ በዓት ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፤ እጅግ ፡ ተደስተው ፡ እግዚአብሔር ፡ ‹የምናኔና ፡ የትምህርት ፡ ልጆችህ ፡ (ወዳጆችህ) ፡ ቊጥር ፡ እንደሌላቸው ፡ እንደ ፡ አሸዋዎችና ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡ ከዋክብት ፡ ይበዛሉ› ፡ ብሎ ፡ የነገረኝ ፡ ቃል ፡ በዚች ፡ ቦታ ፡ ይፈጸማል ፡ ብለው ፡ ትንቢት ፡ ተናግረዋል ።

ሐረስ ፡ ይበላባቸውና ፡ ይጠጣባቸው ፡ የነበሩትን ፡ የብረት ፡ ንዋያትንና ፡ ሲሸሽ ፡ የጣላቸውን ፡ ማናቸውንም ፡ ዕቃዎች ፡ ባርከው ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልግሎት ፡ እንዲጠቀሙ ፡ አድርገዋል ።

አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፤ በዚች ፡ ዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ሳሉ ፤ ዝናቸው ፡ ለራቁትም ፡ ለቀረቡትም ፡ ተሰምቷል ።

እሳቸው ፡ ግን ፤ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ይሸሹ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ዝናቸው ፡ ቢሰማባቸው ፡ አይወዱም ፡ ነበር ። ነቢዩም ፡ „እግዚአብሔር ፡ በቅዱሳኑ ፡ የተመሰገነ ፡ ነው„ ፡ እንዳለ ፤ እግዚአብሔር ፡ ስሙ ፡ በእሳቸው ፡ ላይ ፡ ይገለጽ ዘንድ ፡ ስለፈቀደ ፤ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ የታወቁ ፡ የተከበሩ ፡ ለመሆን ፡ አብቅቷቸዋል ።

እግዝእትነ ፡ ማርያምንም ፡ እጅግ ፡ ከመውደዳቸው ፡ የተነሣ ፤ በስሟ ፡ የተቀረጸች ፡ አንዲት ፡ ታቦት ፡ በዚችው ፡ በዓታቸው ፡ በእኩሌታዋ ፡ አኑረዋታል። ለጊዜውም ፡ በብሕትውና ፡ ስለተወሰኑ ፤ በዙሪያዋ ፡ የጋረዱላት ፡ ደጓዕሌ ፡ (ሰሌን ፡) ነበር።

በበዓቱዋ ፡ እኩሌታም ፡ እሳቸው ፡ ካሥራ ፡ አምስት ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቶቻቸው ፡ ጋራ ፡ ተቀምጠው ፡ ጸሎታቸውንና ፡ መሥዋዕታቸውን ፡ ሲያሳርጉባት ፡ ኖረዋል ።

ደራሲውም ፡ „ሰላም ፡ ለመቃብሪከ ፡ እምቅድመ ፡ ትኑም ፡ ውስቴታ ፤ ታቦተ ፡ ማርያም ፡ ድንግል ፡ ዘአንበርከ ፡ በውሳጢታ ። ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ቀናዒ ፡ ኤልያስ ፡ ዘሰራጽታ ። ለበረከትከ ፡ ይከልለኒ ፡ ረድኤታ ፡ ወይዐደኒ ፡ ዘጽድቅከ ፡ ወልታ„ ፡ ብሎ ፡ ጥንተ ፡ ታሪኩን ፡ ገልጾታል ።

www.ethiopianorthodox.org

በዚች ፡ በበዓታቸው ፡ ራስጌ ፡ ላይ ፡ ደብረ ፡ ከርቤና ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ የተባሉ ፡ ሁለት ፡ ተራሮች ፡ ይገኛሉ ። እነዚሁም ፡ ተራሮች ፡ ለደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገዳም ፡ እንደ ፡ በረኛ ፡ (ዘበኛ) ፡ ሆነው ፡ የሚታዩ ፡ ስለሆነ ፤ አቀማመጣቸው ፡ ወግ ፡ አለው ። ደብረ ፡ ከርቤ ፡ በተራራነቱ ፡ እንደሸንተረር ፡ ያለ ፡ ነው ። በላዩም ፡ በቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ስም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ታንጾበታል ።

የደብረ ፡ ጽጌን ፡ ግን ፤ ኋላ ፡ በተራው ፡ እናመጣዋለን ። ስለነዚሁም ፡ ታሪካውያን ፡ ተራሮች ፡ ደራሲው ፡ ሲጽፍ ፤ «ሰላም ፡ ለከናፍሪከ ፡ እለ ፡ ኢነበባ ፡ ከንቶ ፡ እንበለ ፡ ዳዕሙ ፡ አእኰቶ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ፀሐይ ፡ ለጽልመት ፡ ዘተላትቶ ፡ አንተኑ ፡ ደብረ ፡ ከርቤ ፡ ዘመዓዛከ ፡ ይትፈቶ ፡ ወሚመ ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ ዘኢትክል ፡ ተከብቶ ፡ ብሎ ፡ ገልጾታል ።

የቦታውን ፡ ጥንታዊነት ፡ በጥቂቱ ፡ ካስረዳንም ፡ ዘንድ ፤ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፤ በበዓታቸው ፡ አኑረው ፡ ሲጸልዩበት ፡ የነበረችው ፡ የእመቤታችን ፡ ጽላት ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ የፈለሰችበትን ፡ በጐንደር ፡ ከተማ ፡ ካለው ፡ ከደብረ ፡ ብርሃን ፡ ሥላሴ ፡ የታሪክ ፡ መዝገብ ፡ ተገልብጦ ፡ እንደመጣልን ፡ አድርገን ፡ እንገልጣለን ።

፩ኛ ፡ ንጽሕፍ ፡ ዜና ፡ ምጽአታ ፡ ለታቦተ ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ እምደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መካነ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በመዋዕሊሁ ፡ ለንጉሥነ ፡ ሱስንዮስ ፡ እምድኅረ ፡ ነግሠ ፡ በ፫ቱ ፡ ዓመት ። (ንጉሣችን ፡ ሱስንዮስ ፡ በነገሠ ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ አምላክን ፡ የወለደች ፡ የእመቤታችን ፡ ማርያም ፡ ታቦት ፡ (ጽላት ፡ ) የአባታችን ፡ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ቦታ ፡ (በዓት ፡ ) ከሆነች ፡ ከደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ያመጣጧን ፡ ዜና ፡ እንጽፋለን ።

፪ኛ ፡ ወሶበ ፡ አንገሦ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ለይኩኖ ፡ አምላክ ፡ አስተከየዶሙ ፡ ኪዳነ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ከመ ፡ የሀበ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ለአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እምጸባሕተ ፡ መንግሥቱ ፡ ሣልስተ ፡ እድ ፡ እንዲል ።

(አባታችን ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ይኩኖ ፡ አምላክን ፡ በአነገሠው ፡ ጊዜ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ለአባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የመንግሥቱን ፡ ግብር ፡ ፫ኛውን ፡ እጅ ፡ (ሲሶውን) ፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አገባባቸው ፡ (አዋዋላቸው) ።

ወበውእቱ ፡ መዋዕል ፡ ሀሎዉ ፡ በቤተ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሥዩማን ፡ አርባዕቱ ፡ ዘውእቶሙ ፡ ጸባጢ ፡ ወመጋቢ ፤ አሐዱ ፡ ጸባጢ ፡ ይነብር ፡ ምስለ ፡ ንጉሥ ፡ ዘያረትዕ ፡ ኵሎ ፡ ነገረ ፤ ወይትከፈል ፡ ጸባሕተ ፤ ወአሐዱ ፡ ጸባጢ ፡ ይነብር ፡ ምስለ ፡ ዕጨጌ ፡ ዘያረትዕ ፡ ነገረ ፡ ቤተ ፡ ማኅበር ፤ አሐዱ ፡ መጋቢ ፡ የሐውር ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ከመ ፡ ያምጽእ ፡ ጸባሕተ ፡ እምዘተጋብአ ፤ ለቤተ ፡ ማኅበር ፤ ወአሐዱ መጋቢ ፡ ያስተነትን ለቤተ ፡ ማኅበር ።



በዚያን ፡ ዘመን ፡ በተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ቤት ፡ አራት ፡ ሹማምንት ፡ ነበሩ ። እነዚህም ፡ ጸባቲና ፡ መጋቢ ፡ ናቸው ። አንዱ ፡ ጸባቲ ፡ ከንጉሡ ፡ ጋር ፡ ሁሉን ፡ ነገር ፡ እያስማማ ፡ (እያቃና) ፡ ግብሩን ፡ እየተከፈለ ፡ ይኖራል ። አንዱ ፡ ጸባቲ ፡ ግን ፤ የቤተ ፡ ማኅበሩን ፡ ነገር ፡ እያስማማ ፡ ከዕጨጌው ፡ ጋር ፡ ይኖራል ። አንዱ ፡ መጋቢ ፡ ለቤተ ፡ ማኅበሩ ፡ የተሰበሰበውን ፡ ግብሩን ፡ ያመጣ ፡ ዘንድ ፤ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ይሔዳል ። አንዱ ፡ መጋቢ ፡ ግን ፤ ለቤተ ፡ ማኅበሩ ፡ ያከፋፍላል ።

ወበዘከመዝ ፡ ግብር ፡ ሀለዉ ፡ ዕጨጌ ፡ ወሰብአ ፡ ማኅበር ፡ እምአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እስከ ፡ ዕጨጌ ፡ በትረ ፤ ወንጌል ፤ ወእምይኩኖ ፡ አምላክ ፡ እስከ ፡ ንጉሥነ ፡ ሱስንዮስ ። (በዚህም ፡ ሥርዓት ፡ (ሕግ) ፡ የማኅበሩ ፡ ሰዎች ፡ ከዕጨጌው ፡ ጋራ ፡ ከአባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እስከ ፡ ዕጨጌ ፡ በትረ ፡ ወንጌል ፡ ከይኩኖ ፡ አምላክ ፡ እስከ ፡ ንጉሣችን ፡ ሱስንዮስ ፡ ዘመን ፡ ሥራውን ፡ አጽንተው ፡ ኖሩ ።

ወሶበ ፡ ነግሠ ፡ ሱስንዮስ ፡ ተንሥአ ፡ እምድረ ፡ ቆጋ ፡ ወገብረ ፡ ትዕይንተ ፡ በምድረ ፡ ደንቀዝ ፡ (ሱስንዮስም ፡ በነገሠ ፡ ጊዜ ፤ ከምድረ ፡ ቆጋ ፡ ተነሥቶ ፤ ደንቀዝ ፡ ላይ ፡ ከተመ ፡ (ቆረቆረ) ፡ ወኮነ ፡ ኵሉ ፡ ጸባሕት ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ።
(ግብሩም ፡ ሁሉ ፡ ለንጉሥ ፡ ሆነ ። ወእምድኅረዝ ፡ ተርፍ ፡ በሙ ፡ ጸባሕት ፡ ወኮኑ ፡ ርኊባነ ፡ ወዕሩቃነ ፡ ሰብአ ፡ ማኅበር ፡ ዘደብረ ፡ ሊባኖስ ።
(ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ማኅበሮች ፡ ግብሩ ፡ ስለቀረባቸው ፡ የተራቡና ፡ የተራቆቱ ፡ ሆኑ ። ወሶቤሃ ፡ ተጋብኡ ፡ ዕጨጌ ፡ ወሰብአ ፡ ማኅበር ፡ ወአኀው ፡ ይትማከሩ ፡ ምክረ ፡ ሠናየ ። ወይቤሉ ፡ ንዑ ፡ ንሑር ፡ ወንሰአሎ ፡ ለንጉሥ ፡ እመ ፡ ሀለወ ፡ በኪዳነ ፡ አቡሁ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ።

(በዚያን ፡ ጊዜ ፤ የማኅበሩ ፡ ሰዎች ፡ ከዕጨጌው ፡ ጋር ፡ ተሰብስበው ፡ መልካም ፡ ምክርን ፡ ሊመክሩ ፡ ጀመሩና ። ባባቱ ፡ በይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እንዳለ ፡ ንጉሡን ፡ ሔደን ፡ እንለምነው ፡ ተባባሉ ።

ወእምዝ ፡ ተኀርዩ ፡ ፵ወ፯ቱ ፡ መንኰሳት ፡ ማእምራነ ፡ መጻሕፍት ፡ ወጥበበ ፡ ነገር ፤ (ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የመጻሕፍትን ፡ ትርጓሜና ፡ የነገርን ፡ አቅድ ፡ የሚያውቁ ፡ ፵፯መነኰሳት ፡ ተመረጡ ። "ወበጽሑ ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፡ ንጉሥ ፡ (ሔደው ፡ ንጉሡ ፡ ወዳለበት ፡ ደረሱ ። ወይቤሉ ፤ ንግሩ ፡ ለነ ፡ ምጽአተ ፡ ዚአነ ፡ እምደብረ ፡ ሊባኖስ ።

(ከደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መምጣታችንን ፡ ንገሩልን ፡ አሉ ። ወቦኡ ፡ ውስተ ፡ ጽርሐ ፡ መንግሥቱ ፡ ወሰገዱ ፡ ሎቱ ። (ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ አዳራሽ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ እጅ ፡ ነሡት ። «ወይቤሉ ፡ ዕጨጌ ፡ ወሰብአ ፡ ማኅበር ፡ ለእኩነ ፡ ወፈነዉነ ፡ ኀቤከ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ሰላም ፡ ለከ ፡ ወእፎ ፡ ሀሎከ ፡ አንጉሥነ ፡ ሞገስ ፡ ወሰላም ፡ የሀሉ ፡ ምስሌከ» ፡ የማኅበሩ ፡ ሰዎችና ፡ ዕጨጌ ፡ ንጉሣችን ፡ ሆይ ፡ እንደምን ፡ አለህ? ፡ ሰላምና ፡ መወደድ ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ይሁን ፡ ሲሉ ፡ ወዳንተ ፡ ላኩን ፡» አሉ ። ወምጽአትነሰ ፡ መንገሌከ ፡ በእንተ ፡ ዘተነሥተ ፡ ብነ ፡ ኪዳነ ፡ አቡከ ፡ ይኩኖ ፡

www.ethiopianorthodox.org

አምላክ ፡ እመ ፡ ንርኅብ) ፡ ወንጸምዕ ፡ ወንከውን ፡ ዕሩቃነ ፤ እስመ ፡ ነበርነ ፡ ቅድመ ፡ በማልስተ ፡ እዴሃ ፡ ለመንግሥት ፡ አቡከ ፡ ወይእዜኒ ፡ ዘይኄይስ ፡ ወይሜኒ ፡ ግበር ፡ ለነ ።

(ወዳንተ ፡ መምጣታችንም ፡ ከሁን ፡ ቀደም ፡ ከባትህ ፡ መንግሥት ፡ ግብር ፡ ፫ኛውን ፡ እጅ ፡ እየተቀበልን ፡ እንኖራለንና ፡ ይህ ፡ በመቅረቱ ፡ ያባትህ ፡ የይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ስለፈረሰብን ፤ ብንራብና ፡ ብንጠማ ፡ ብናራቆትም ፡ ነው ። ዛሬ ፡ ግን ፤ የተሻለውንና ፡ የቀናውን ፡ ነገር ፡ አድርግልን) ።

ወአውሥአ ፡ ንጉሥ ፡ ወይቤሎሙ ፡ «እነግረክሙ ፡ ተማኪሮየ ፡ ምስለ ፡ መኳንንት ፡ ወመሳፍንት» ፡ ንጉሡም ፡ መልሶ ፡ ከመሳፍንቱና ፡ ከመኳንንቱ ፡ ጋር ፡ ምክር ፡ አድርጌ ፡ የሚሆነውን ፡ እነግራችኋለሁ ፡ አላቸው ። ወእንዘ ፡ ሀለዉ ፡ በዝ ፡ ነገር ፡ ቦአ ፡ ክረምት ፡ ወጸንዐ ፡ በሙ ፡ (በዚህ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ሳሉ ፡ ክረምት ፡ ገባ ፡ በጣምም ፡ ጸናባቸው ።

ወይቤሎሙ ፡ ንጉሥ ፡ እምይእዜሰ ፡ ኢተሐውሩ ፡ እስመ ፡ ቦአ ፡ ክረምት ፡ (ንጉሡም ፡ እንግዴህስ ፡ ክረምት ፡ ገብቷልና ፡ አትሔዱም ፡ አላቸው ። ወይቤልዎ ፡ አይቴ ፡ ንነበር ፡ እነርሱም ፡ እስከዚያ ፡ ወዴት ፡ እንቀመጥ ፡ አሉት ። ወይእተ ፡ ጊዜ ፡ ጸውዖ ፡ ለከንቲባ ፡ ወይቤሎ ፡ ኅረይ ፡ ሊተ ፡ ሀገረ ፡ ዘይከርሙ ፡ ቦቱ ፡ ወዘይትረክብ ፡ ውስቴቱ ፡ ሐሊብ ፡ ወመዓር ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከንቲባውን ፡ ጠርቶ ፡ እነዚህ ፡ መነኮሳት ፡ የሚከርሙበትን ፡ ማርና ፡ ወተት ፡ የሚገኝበትን ፡ ቦታ ፡ ምረጥ ፡ አለው ። ወአውሥአ ፡ ከንቲባ ፡ ወይቤሎ ፡ ሀሎ ፡ ሀገር ፡ ቅሩብ ፡ በአድያሚሃ ፡ ለትዕይንትከ ፡ ከንቲባውም ፡ በከተማህ ፡ አካባቢ ፡ ቅርብ ፡ አገር ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

ወይቤሎ ፡ ንጉሥ ፡ ሠናየ ፡ ነገርከኒ ፤ ቦቱ ፡ ይክርሙ ፡ ንጉሡም ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ነገርኸኝ ፡ ይክረሙበት አለው ። ወይእተ ፡ ጊዜ ፤ መርሐሙ ፡ ከንቲባ ፡ ለእሙንቱ ፡ መነኮሳት ፡ ውስተ ፡ ውእቱ ፡ ሀገር ፡ ወከረሙ ። በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ከንቲባው ፡ በዚህ ፡ ሀገር ፡ ውስጥ ፡ መርቷቸው ፡ ከረሙ ።

ወእምድኅረዝ ፡ መጽኡ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ወተአምኅዎ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፤ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ መጥተው ፡ እጅ ነሡት ፡ ወይቤሎሙ ፡ ንጉሥ ፡ ዳኅነኑ ፡ ሀሎክሙ ፡ ንጉሡም ፡ ደኅና ፡ አላችሁን ፡ አላቸው ።

አውሥኡ ፡ ወይቤሉ ፡ እወ ፡ ዳኅነ ፡ ሀሎነ ፡ እነሱም ፡ አዎን ፡ በሰላምና ፡ በደኅንነት ፡ አለን ፡ ሲሉ ፡ መለሱ ። ወከዕበ ፡ ይቤልዎ ፡ ለንጉሥ ፡ ምንተ ፡ መከርከ ፡ ይትባረክ ፡ መንግሥትከ ፡ ወይሰባሕ ፡ ስምከ ፡ ደግመውም ፡ ንጉሡን ፡ መንግሥትህ ፡ ይባረክ ፡ ስምህ ፡ ይመስገንና ፡ (ከፍ ፡ ከፍ ይበልና) ምን ፡ መከርክ ፡ አሉት ። ወይቤሎሙ ፡ መከርኩ ፡ ዝየ ፡ እግበር ፡ ትዕይንተ ፡ አንትሙኒ ፡ ሑሩ ፡ ወአምጽኡ ፡ ታቦተክሙ ፡ ወይምጽኡ ፡ ዕጨጌ ፡ ወሰብአ ፡ ሀገር ፡ ወለእለ ፡ የዐቅቡ ፡ መቃብሪሁ ፡ ለአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ይኩን ፡ ጸባሕተ ፡ ዚአየ ፡ በምድረ ፡ ሸዋ ፡ በዚህ ፡ ከተማ ፡ ላደርግ ፡ መክሬያለሁና ፡ እናንተም ፡ ሔዳችሁ ፡ ታቦታችሁን ፡ አምጡ ፡ የማኅበሩ ፡ ሰዎችና ፡ ዕጨጌውም ፡ ይምጡ ፡ ያባታችን ፡ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ መቃብር ፡ ለሚጠብቁ ፡ ግን ፤ በሸዋ ፡ የሚገኘው ፡ የኔ ፡ ግብር ፡ ለነሱ ፡ ይሁን ፡ አላቸው ።



ወእምድኅረዝ ፡ ሖሩ ፡ ዕጨጌ ፡ ወሰብአ ፡ ማኅበር ፡ ምስለ ፡ ታቦቶሙ ፡ ወበጽሑ ፡ ምድረ ፡ አምሐራ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የማኅበሩ ፡ ሰዎችና ፡ ዕጨጌው ፡ ከታቦታቸው ፡ ጋር ፡ ሔዱ ፡ ወደአማራም ፡ አገር ፡ ደረሱ ።

ወበህየ ፡ ሐመ ፡ አቡነ ፡ ዕጨጌ ፡ በትረ ፡ ወንጌል ፡ ወአዕረፈ ፡ ወተቀብረ ፤ በመካነ ፡ አትሮኖሰ ፡ ማርያም ። በዚያም ፡ አባታችን ፡ ዕጨጌ ፡ በትረ ፡ ወንጌል ፡ ታሞ ፡ ሞተ ፡ በአትሮኖሰ ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ (በሳይንት) ፡ ተቀበረ ።

ወመጽኡ ፡ ሰብአ ፡ ማኅበር ፡ ነሢአሙ ፡ መንበረ ፡ ወመስቀለ ፡ ወረከብዎ ፡ ለንጉሥ ፡ በምድረ ፡ እንፍራዝ ፡ ወነገርዎ ፡ ሞተ ፡ ዕጨጌ ፡ ወኀዘነ ፡ ዐቢየ ፡ ኀዘነ ።

የማኅበሩም ፡ ሰዎች ፡ መንበርና ፡ መስቀሉን ፡ ይዘው ፡ መጡ ። ንጉሡንም ፡ እንፍራዝ ፡ በተባለው ፡ ቦታ ፡ አግኝተውት ፡ የዕጨጌውን ፡ ሞት ፡ ነገሩት ። ታላቅ ፡ ኀዘንም ፡ አደረገ ። ወይቤሎሙ ፡ ሀቡኒ ፡ አበ ፡ ዘይደሉ ፡ ለዝንቱ ፡ መንበር ። ለዕጨጌነት ፡ የሚበቃውንም ፡ መነኩስ ፡ ምረጡ ፡ አላቸው ።

አውሥኡ ፡ ወይቤልዎ ፡ ለዝሰ ፡ መንበር ፡ ዘይደሉ ፡ ሀሎ ፡ አቡነ ፡ አብርሃም ። ለዚህስ ፡ መንበር ፡ የሚገባ ፡ አባታችን ፡ አብርሃም ፡ አለ ፡ ሲሉ ፡ መለሱለት ፡ ወሰቤሃ ፡ ሤሞ ፡ ለአቡነ ፡ አብርሃም ፡ በአክሊል ፡ ወበቀጸላ ፡ ወበአልባሰ ፡ ኩፋር ። በዚያን ፡ ጊዜም ፡ አቡነ ፡ አብርሃምን ፡ የራስ ፡ ወርቅን ፡ አቅዳጅቶ ፡ በኩፋር ፡ ልብስ ፡ ሸልሞ ፡ ሾመው ።

ወወሀበ ፡ ምድረ ፡ ጕልት ፡ ብዙኀ ፡ ወአንበሮ ፡ በምድረ ፡ ፍርቃ ። ጕልትም ፡ ሰጥቶ ፡ ፍርቃ ፡ በሚባለው ፡ ቦታ ፡ አስቀመጠው ። ወእምዝ ፡ ጸውዖሙ ፡ ለመነኮሳት ፡ ዘመጽኡ ፡ ቀዳሚ ፡ ወወሀቦሙ ፡ ዘከረሙ ፡ ቦቱ ፡ «አስቀድመው ፡ በመልክት ፡ ሔደው ፡ የነበሩትንም ፡ መነኮሳት ፡ ጠርቶ ፡ ከርመውበት ፡ የነበረውን ፡ ቦታ ፡ ሰጣቸው ።

ወአቡነሂ ፡ አብርሃም ፡ አዕረፈ ፡ በምድረ ፡ ፍርቃ ፡ ወተሰይመ ፡ ዕጨጌ ፡ ዘወንጌል ፡ ወበኅዳጥ ፡ መዋዕል ፡ ተሥዕረ ። አባታችን ፡ አብርሃም ፡ በፍርቃ ፡ ዐረፎ ፡ ዕጨጌ ፡ ዘወንጌል ፡ ተሾመ ፡ እርሱም ፡ በጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ተሻረ ። ወከዕበ ፡ ተሠይመ ፡ ዕጨጌ ፡ ዘሚካኤል ።

ቀጥሎም ፡ ዕጨጌ ፡ ዘሚካኤል ፡ ተሾመ ። ወበውእቱ ፡ ዘመን ፡ ወለጠ ፡ ንጉሥ ፡ ሱስንዮስ ፡ ሃይማኖቶ ፡ ወአምነ ፡ በሃይማኖተ ፡ ሮምያ ፡ ወተቈረበ ፡ በእደ ፡ አውፍንሶ ፡ ጳጳስ ፡ ዘሮምያ ። በዚሁም ፡ ዘመን ፡ ንጉሡ ፡ ሱስንዮስ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋ

www.ethiopianorthodox.org

ሕዶ ፡ ሃይማኖቱን ፡ ለውጦ ፡ በሮሜ ፡ የካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ አመነ ። በጳጳሱ ፡ በአውፍንሶም ፡ እጅ ፡ ቆረበ ። ወበዝ ፡ ነገር ፡ ተሰዱ ፡ ዕጨጌ ፡ ዘሚካኤል ፡ ወጸባጢ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ ወመጋቢ ፡ ገድሉ ፡ ወሰብአ ፡ ማኅበር ። በዚህም ፡ ነገር ፡ ዕጨጌ ፡ ዘሚካኤልና ፡ ጸባቲ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ፤ መጋቢ ፡ ገድሉና ፡ የማኅበሩም ፡ ሰዎች ፡ ተሰደዱ ። ወኮነ ፡ ዐቢይ ፡ ሁከት ፤ ውስተ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ? በቤተ ፡ መንግሥቱም ፡ ውስጥ ፡ ትልቅ ፡ ሁከት ፡ ሆነ ።

ወኀልቁ ፡ ብዙኃን ፡ ሰብእ ፡ ዘአልበሙ ፡ ኍልቍ ፡ በሃይማኖት ፡ ወዘተርፉሰ ፡ ዐበዩ ፡ ተቀንዮ ፡ ለንጉሥ ። በሃይማኖትም ፡ ምክንያት ፡ ቍጥር ፡ የሌላቸው ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አለቁ ፡ የቀሩት ፡ ግን ፡ ለንጉሥ ፡ መገዛትን ፡ እንቢ ፡ አሉ ።

ወእምዝ ፡ ተጋብኡ ፡ መኳንንት ፡ ወመሳፍንት ፡ ወይቤልዎ ፡ ለንጉሥ ፡ ኢኮነ ፡ ሠናየ ፡ ዝነገር ፡ ኀልቁ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ወዘተርፉ ፡ ዐበዩ ፡ ተቀንዮ ፡ ለነ ፡ ሚጥ ፡ ሃይማኖተ ፡ እስክንድርያ ፡ ወአንግሥ ፡ ፋሲለደስሃ ፡ ወልደከ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ መኳንንቱና ፡ መሳፍንቱ ፡ ተሰብስበው ፡ ብዙ ፡ ወገኖች ፡ አለቁ ። የተረፉትም ፡ መገዛትን ፡ እንቢ ፡ አሉ ። ይህ ፡ ነገር ፡ መልካም ፡ አልሆነም ። ስለዚህ ፤ ለእኛ ፡ የእስክንድርያን ፡ ሃይማኖት ፡ መልስልን ፡ ልጅህንም ፡ ፋሲለደስን ፡ አንግሥልን ፡ሲሉ ፡ ለንጉሡ ፡ ነገሩት ። ወሰሚዖ ፡ ንጉሥ ፡ አዖደ ፡ ዓዋዲ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ፋሲለደስ ፡ ወልድየ ፡ ይንግሥ ፤ ሃይማኖተ ፡ እስክንድርያ ፡ ትትመየጥ ፡ ወትንበር ፡ ከመ ፡ ቀዳሚ ፡ ሥርዓታ ፡ ወሃይማኖተ ፡ ሮምያ ፡ ትትርፍ ፡ ወትሑር ፡ ብሔራ ። ንጉሡም ፡ ሰምቶ ፡ ልጄ ፡ ፋሲለደስ ፡ ይንገሥ ፤ የእስክንድርያም ፡ ሃይማኖት ፡ ትመለስ ፡ ሥርዓቷም ፡ እንደፊት ፡ ትኑር ፡ የሮሜ ፡ ሃይማኖትም ፡ ትቅርና ፡ ወደ ፡ ሀገሯ ፡ ትሒድ ፡ ሲል ፡ ዓዋጅ ፡ ነገረ ።

ወአመ ፡ ነግሠ ፡ ፋሲለደስ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጸውዖ ፡ ለአውፍንሶ ፡ መምህረ ፡ ሮምያ ፡ ወይቤሎ ፡ ሑር ፡ ብሔረከ ፡ ምስለ ፡ እሊዓከ ፡ ሰብአ ፡ ሮም ፡ በከመ ፡ አዘዘ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሱስንዮስ ፡ አቡየ ።

ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፋሲለደስም ፡ በነገሠ ፡ ጊዜ ፡ የሮሜውን ፡ መምህር ፡ አውፍሶንን ፡ ጠርቶ ፡ አባቴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሱስንዮስ ፡ እንዳዘዘ ፡ ከወገኖችህ ፡ የሮም ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ወዳገርህ ፡ ሒድ ፡ አለው ።

ወአውሥአ ፡ መምህረ ፡ ሮምያ ፡ አውፍንሶ ፡ ወይቤሎ ፡ ኢየሐውር ፡ ዘእንበለ ፡ እትዋሣእ ፡ ነገረ ፡ ሃይማኖት ። የሮሜ ፡ መምህር ፡ አውፍንሶም ፡ የሃይማኖትን ፡ ነገር ፡ ሳልነጋገር ፡ (ሳልከራከር ) አልሔድም ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። ወሰቤሃ ፡ ንጉሥ ፡ አስተጋብአሙ ። ንጉሥ ፡ ፋሲለደስ ፡ ለመምህራነ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ወለካህናተ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዘተርፉ ፡ እሞት ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ፋሲለደስ ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስን ፡ መምህራንና ፡ ከሞት ፡ የተረፉት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ካህናት ፡ ጉባኤ ፡ እንዲያደርጉ ፡ አዘዘ ።

ወይቤሎሙ ፡ ተዋሥኡ ፡ ነገረ ፡ ሃይማኖት ፡ ምስለ ፡ አውፍንሶ ፡ መምህረ ፡ ሮምያ ። ከሮሜው ፡ መምህር ፡ ከአውፍንሶም ፡ ጋር ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ነገር ፡ ተከራከሩ ፡ አላቸው ። አውሥኡ ፡ ወይቤልዎ ፡ እወ ፡ ይኩን ።



እነርሱም ፡ እሺ ፡ ይሁን ፡ ሲሉ ፡ መለሱ ፡ (መከራከሩን ፡ ፈቀዱ ፡ )ወእምዝ ፡ አኀዙ ፡ ይትናገርዎ ፡ መምህራነ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ለአውፍንሶ ፡ መምህረ ፡ ሮምያ ። የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መምህራንም ፤ የሮሜ ፡ መምህር ፡ አውፍንሶን ፡ ሊከራከሩት ፡ ጀመሩ ። ወይቤልዎ ፡ ተዋሥአነ ፡ እንከ ፡ ነገረ ፡ ሃይማኖት ፡ በቃለ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈወርቅ ፡ ወበቄርሎስ ፡ እንግዴህ ፡ የሃይማኖትን ፡ ነገር ፡ በዮሐንስ ፡ አፈወርቅና ፡ በቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ቃል ፡ ተከራከረን ፡ አሉት ፡ ወይቤ ፡ አውፍንሶ ፡ እሉሰ ፡ አብያጽየ ፡ እኑርሉስ ፡ ጓደኞቼ ፡ ናቸው ፡ ሲል ፡ መለሰ ።

አሐዱ ፡ እመምህራነ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ይቤሎ ፡ ትትዋሣእኑ ፡ በቃለ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ከደብረ ፡ ሊባኖሰ ፡ መምህራን ፡ አንዱ ፡ የሆነው ፡ የመጻሕፍት ፡ መምህር ፡ (አባ ፡ በትረ ፡ ጊዮርጊስም) ፡ በሐዋርያው ፡ በጳውሎስ ፡ ቃል ፡ ትከራከራለህን ፡ ሲል ፡ ጠየቀው ። ወይቤ ፡ መምህረ ፡ ሮምያ ፡ በዝንቱሰ ፡ እትዋሣእ ። በሱስ ፡ እከራከራለሁ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ። ወይቤሎ ፡ እምከመሰ ፡ ትትዋሣእ ፡ ከመዝ ፡ ይብል ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ።

«ወሶበ ፡ እንዘ ፡ ፀሩ ፡ ንሕነ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተሣህለነ ፡ በሞተ ፡ ወልዱ ። የምትከራከርስ ፡ ከሆነ ፡ እኛ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጠላቶቹ ፡ ሆነን ፡ ሳለ ፡ በልጁ ፡ ሞት ፡ ይቅር ፡ አለን ፡ ይልብሃል ፡ አለው ፡ (ተዋሕዶውን ፡ ለማስረዳት ፡ ነው ።)

ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡ ሃይማኖት ፡ ተፈጽመ ፡ አፉሁ ፡ ወተመውዐ ። ይህንንም ፡ የሃይማኖት ፡ ክርክር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ አፉ ፡ ተዘጋ ፡ ተሸነፈ ፤ (ምላሽ ፡ በማጣት ) ።

ወይእተ ፡ ጊዜ ፡ ተፈሥሑ ፡ ካህናተ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ወወደስዎ ፡ ለአቡነ ፡ በትረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ «ረከብናሁ ፡ ለበትር ፡ እንተ ፡ ያደክማ ፡ ለሮሜ ፤ ጽሩብ ፡ በንባብ ፡ ወቅሩጸ ፡ በትርጓሜ» ፡ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ካህናት ፡ ደስ ፡ ተሰኙ ። አባ ፡ በትረ ፡ ጊዮርጊስንም ፡ በንባብ ፡ የተጠረበ ፤ በትርጓሜ ፡ የተቀረጸ ፡ ሮሜን ፡ የሚያደክማት ፡ በትር ፡ አገኘን ፡ ሲሉ ፡ አመሰገኑት ።

ወእምድኅረዝ ፡ ሰደዶሙ ፡ ንጉሥ ፡ ፋሲለደስ ፡ ለሰብአ ፡ ሮም ፡ ምስለ ፡ መምህሮሙ ፡ አውፍንሶ ፡ ኀበ ፡ ብሔሮሙ ። ከዚህ ፡ በኋላም ፡ ንጉሡ ፡ ፋሲለደስ ፡ የሮምን ፡ የሃይማኖት ፡ ሰዎች ፡ ከነመምህራቸው ፡ ወደ ፡ ሀገራቸው ፡ እንዲሔዱ ፡ አደረገ ።

ወሠረወ ፡ ምድረ ፡ ጕልቶሙ ፡ ዘተወነፉ ፡ ቀዲሙ ፡ ወወሀበ ፡ ለደብረ ፡ ሊባኖስ ። አስቀድሞ ፡ የተሰጣቸውንም ፡ ጕልት ፡ ነቅሎ ፡ ለደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ሰጠ ።

ወአዖደ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ምድረ ፡ ርስት ፡ ዘእምየ ፡ ወምድረ ፡ ጕልት ፡ ዘአቡየ ፡ ይኩን ፡ ሞፃሃ ፡ ለደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ እምከርከር ፡ እስከ ፡ ፈንጠር ፡ ወእማውራ ፡ እስከ ፡ ብራሕላ ። የናቴ ፡ ርስትና ፡ ያባቴ ፡ ጕልት ፡ ከከርከር ፡ እስከ ፡ ፈንጠር ፡ ከማውራ ፡ እስከ ፡ ብራሕላ ፡ ለደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ካሣ ፡ ይሁን ፡ ሲል ፡

www.ethiopianorthodox.org

ዓዋጅ ፡ አናገረ ። ወእምዝ ፡ አብእዋ ፡ ካህናት ፡ ደብረ ሊባኖስ ፡ ለታቦተ ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ዘሐነጹ ፡ ሎቱ ፡ ሰብአ ፡ ሮም ፡ ለታቦተ ፡ ኢየሱስ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፣ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ካህናት ፡ የእመቤታችን ፡ የቅድስት ፡ ማርያምን ጽላት ፡ የሮም ፡ ሰዎች ፡ በኢየሱስ ፡ ስም ፡ ወደ ፡ ሠሩት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ አግብተው ፡ አኖርዋት ። ‘ወቀደሳ ፡ ዕጨጌ ፡ በትረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ለይእቲ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ። «ይህችንም ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ዕጨጌ ፡ በትረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ባረካት ።

ወእምድኅረ ፡ ብዙኅ ፡ መዋዕል ተማከሩ ፡ ንጉሥ ፡ ፋሲለደስ ፣ ወዕጨጌ ፡ በትረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ምስለ ፡ ካህናተ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ወይቤሉ ፡ ኢትንበር ፡ ታቦተ ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ በመቅደሰ፡ ሰብአ ፡ ሮም ፡ ዳዕሙ ፡ ንሕንጽ ፡ ላቲ ፡ ካልአ ፡ መቅደሰ ፡ ዘትነብር ፡ ውስቴቱ ። ከብዙ ፡ ጊዜም ፡ በኋላ ፣ ንጉሡ ፡ ፋሲለደስና ፡ ዕጨጌ ፡ በትረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የእመቤታችን ፡ የቅድስት ፡ ማርያም ፡ ጽላት ፡ በሮም ፡ ሰዎች ፡ መቅደስ ፡ ከምትቀመጥ ፡ ሌላ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ብንሠራላት ፡ ይሻላል ፡ ሲሉ ፡ ከደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ካህናት ፡ ጋራ ፡ ምክር ፡ አደረጉ ። ወሐነጹ ፡ ላቲ ወአብእዋ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ መቅደስ ። ሠርተው ፡ ባዲሱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ አኖርጥት ።

ናሁ ፡ ተፈጸመ ፡ ዜና ፡ ምጽአታ ፡ ለታቦተ ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ እምደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መካነ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ወዜና ፡ ንብረታ ፡ ውስተ ፡ ብሔረ ፡ አዘዞ ።

የእመቤታችን ፡ ጽላት ፡ የተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መንበር ፡ ከሆነው ፡ ከደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ እንደምን ፡ እንደመጣችና ፡ አዘዞ ፡ በሚባለው ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ እንደኖረች ፡ የሚናገረው ፡ ዜና ፡ ተፈጸመ ።

በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ዕጨጌ ፡ በትረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ አውፍንሶን ፡ ስለመርታቱ ፡ የተደረሰው ፡ መወድስ ፡ ቅኔ ፡ የሚከተለው ፡ ነው ።

ከንቶ ፡ ነገረ ፡ እመ ፡ ተናገሩ ፣
ሰብአ ፡ ሮምያ ፡ አዕራር ፡ ኢይከውን ፡ ለቅያሜ ።
በባህለ ፡ ነገሮሙ ፡ ሮም ፡ እንተ ፡ አልቦቱ ፡ ፍጻሜ ።
እስመ ፡ አብደ ፡ ሕሊና ፡ ልቦሙ ፡ ወከነ ፡ ሐማሜ ።
ወየብሰ ፡ እምልምላሜ ፣ ጽጌ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ምጽልው ፡ ዘተዘርወ ፡ ከመ ፡ ጊሜ።

(ለዓለም ።)

ኢትባልሂ ፡ ወላዲሁ ፡ በተቀብዖ ፡ ንባብ ፡ አበሜ ።
ዮሴፍ ፡ ለቃለ ፡ አብ ፡ እንተ ፡ ዐቀበ ፡ ምስለ ፣ ሰሎሜ።



ረከብናሁ ፡ ለበትር ፡ (ዕጨጌ ፡ በትረ ፡ ጊዮርጊስን ፡ ማለቱ ፡ ነው) ፡ እንተ ፡
ያደክማ ፡ ለሮሚ ።
ርኢናሁ ፡ ለበትር ፡ ዘይጌሥጻ ፡ ለሮሚ ፡ ጽሩበ ፡ በንባብ ፡ ወቅሩጸ ፡ በትርጓሜ ።

አንዱ ፡ ድርሰት ፡ ከሌላው ፡ ድርሰት ፡ በጥቂቱ ፡ ቀርቶ ፡ በብዙውም ፡ የሚለያይበት ፡ አሳብ ፡ ስለሚገጥመው ፣ ሊቁ ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ ዋዜማ ፡ በተባለው ፡ መጽሐፋቸው ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስን ፡ ዕጨጌዎች ፡ ዝርዝርና ፡ ታሪክ ፡ ሲጽፉ ፡ (ዘትረ ፡ ወንጌል ፡) በትረ ፡ ወንጌል ፡ በአፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ዘመን ፡ እንደነበረና ፡ በአፄ ፡ ሱስንዮስም ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ የነበሩት ፡ ዕጨጌዎች ፡ አብርሃምና ፡ ዘወንጌል ፡ እንደነበሩ ፡ ጽፈውታል ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያተትነውንም ፡ ታሪክ ፡ ፈጽሞ ፡ ሳያነሡ ፡ አፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ የነገሠው ፡ በዕጨጌ ፡ አብርሃም ፡ ዘመን ፡ እንደነበረና ፡ የሁለቱን ፡ ፍቅር ፣ እንዲሁም ፡ አፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስን ፡ ገዳም ፡ ማኅበር ፡ እንደረዳና ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትንም ፡ ከመውደዱ ፡ የተነሣ ፡ በመንግሥቱ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ላይ ፡ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ሥዕል ፡ ያደርግ ፡ እንደነበር ፡ ገልጸዋል ።

ነገር ፡ ግን ፡ ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፣ የዕጨጌዎቹን ፡ ወይም ፡ የነገሥታቱን ፡ ተራ ፡ ባለማፋለሱ ፡ የተቀራረበ ፡ ከመሆኑ ፡ በቀር ፡ ልዩነት ፡ አለው ፡ ለማለት ፡ የሚያስደፍር ፡ ነገር ፡ የለበትም ። ለዚህም ፡ ማስረጃ ፡ ስንኳንስ ፡ በጥያቄና ፡ በምርመራ ፡ የሚደረገው ፡ ይቅርና ፡ አንዱን ፡ ጽሑፍ ፡ ወደሌላ ፡ ለመገልበጥ ፡ ሲታሰብ ፡ በገልባጩ ፡ ግድፈት ፡ ጸሐፊ ፡ ስለማይታጠበት ፣ ከዋናው ፡ ጽሑፍ ፡ ገልባጩ ፡ ባዘር ፡ (በፊደል ፡) ወይም ፡ ከዚህ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ነገር ፡ ጥቂት ፡ ልዩነት ፡ እንደማያጣው ፡ ማስተዋል ፡ ብቻ ፡ ሳይበቃ ፡ አይቀርም ።

ባለታሪኩም ፡ በመቅድሙ ፡ አጠገብ ፡ የጸሐፊዎቹ ፡ ቃልና ፡ አሳብ ፡ ይልቁንም ፡ የዘመኑ ፡ ቍጥር ፡ ልዩነት ፡ ያለበት ፡ በመሆኑ ፡ ከንዱ ፡ መጽሐፍ ፡ ሁለቱ ፡ መጻሕፍት ፡ የተስማሙበትንና ፡ ለልባቸው ፡ የመሰላቸውን ፡ እንደጻፉት፣ ስለዘመኑም ፡ ቍጥር ፡ አጥብቆ ፡ ለመከራከር ፡ ድፍረት ፡ እንደሌላቸው ፡ በማስታወቂያ ፡ ገልጠውታልና ፡ የሚያከራክር ፡ ነገር ፡ የለበትም ።

## በእመቤታችን ፡ በቅድስት ፡ ማርያም ፡ ስም ፡ የተሰየመችው ፣ ያችው ፡ ጥንታዊዋ ፡ ጽላት ፡ ከጐንደር ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ስለ ፡ መመለሷ ።

በ፲፰፻፶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ደርቡሽ ፡ ጐንደርን ፡ ለማጥፋት ፡ ወጥቶ ፡ ሳለ ፣ ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ድርቡሽን ፡ እንዲወጉ ፡ በአፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ታዘው ፡ ነበርና ፡ ሣር ፡ ውኃ ፡ በሚባለው ፡ ቦታ ፡ ተዋግተው ፡ ለጊዜው ፡ ድል ፡ ስለሆኑ ፣ የሸዋው ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ወደ ፡ ደርቡሽ ፡ እንዲዘምቱ ፡ አስፈለገ ።

ስለዚሁም ፡ ሁኔታ ፡ የሚናገረው ፡ በግዕዝ ፡ የተጻፈው ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ። ንጉሥ ፡ ምኒልክም ፡ ደርቡሾች ፡ ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይ

www.ethiopianorthodox.org

ማኖትን ፡ ድል ፡ እንዳደረጉና ፡ ደንቢያንና ፡ ጐንደርን ፡ እንዳጠፉ ፤ አብያተ ፡ ክርስቲያናቱንም ፡ እንደአቃጠሉ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፤ ሠራዊታቸውን ፡ አስከትተው ፡ ፈጥነው ፡ ተነሡና ፡ በታላቅ ፡ ግርማና ፡ ሰልፍ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ሔዱ ። ደርቡሾቹም ፡ የንጉሥ ፡ ምኒልክን ፡ መምጣት ፡ ቢሰሙ ፡ ደንግጠው ፡ በግሥጋሤ ፡ ወደ ፡ ሀገራቸው ፡ ወደ ፡ መተማ ፡ ገቡ ።

ንጉሥ ፡ ምኒልክም ፤ በሠፈሩበት ፡ ቦታ ፡ ለሠራዊቱ ፡ የሚበቃ ፡ ውኃና ፡ ለከብት ፡ ምግብ ፡ ሣር ፡ ስላላገኙ ፤ በጣና ፡ ባሕር ፡ አጠገብ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ ፎገራ ፡ ወረዱ ።

ስለ ፡ ሠራዊቱም ፡ ብዛት ፤ ከተማው ፡ ከፎገራ ፡ እስከ ፡ ደምቢያና ፡ እስከ ፡ አምባጫራ ፡ ደረሰ ። በዓለ ፡ ፋሲካንም ፡ በዚያው ፡ በአምባጫራ ፡ ላይ ፡ አክብረው ፡ ዋሉ ።

በግንቦት ፡ ወርም ፤ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ሲመለሱ ፤ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ቀድሞ ፡ በንጉሡ ፡ በይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ዘመን ፡ በበዓታቸው ፡ በደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ሲጸልዩባትና ፡ ሲቀድሱባት ፡ የነበረችውን ፡ ታቦተ ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያምን ፡ አሲዘው ፡ መጡ ።

ይህችውም ፡ ታቦት ፤ ከዚያ ፡ በፊት ፡ በጐንደር ፡ አጠገብ ፡ አዘዞ ፡ ባለው ፡ በአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ገዳም ፡ ትኖር ፡ ነበርና ፡ ደርቡሾች ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፤ የአዘዞ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ አቡነ ፡ ሠምረ ፡ አብ ፡ ደብር ፡ ወደማርያም ፡ ውኃ ፡ አሸሽተዋት ፡ ነበር ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ይህችኑ ፡ ታቦት ፡ ወደ ፡ በለሳ ፡ አምጥተው ፡ ለንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ሰጥተዋቸዋል ።

ንጉሥ ፡ ምኒልክም ፤ አንድ ፡ የበቃ ፡ መነኰሴ ፡ ይህች ፡ ታቦት ፡ በእጃቸው ፡ ስትገባ ፡ የመላዋ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ እንዲሆኑ ፡ ነግረዋቸው ፡ ነበርና ፡ ገና ፡ ሲሰጡዋቸው ፡ ስለኔ ፡ የተነገረው ፡ ትንቢት ፡ ደረሰ ፡ ብለው ፡ በደስታ ፡ ተቀበሏቸው ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፤ ደስታቸውን ፡ በሠራዊታቸው ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ ገልጸው ፡ በፈረሳቸው ፡ ላይ ፡ ተቀመጡና ፡ በታላቅ ፡ ግርማ ፡ ጕዞዋቸውን ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ቀጠሉ ። ወደእንጦጦ ፡ ከተቸማውም ፡ ገብተው ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ዕረፍት ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፤ የደብረ ፡ ሊባኖስን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሠራዊቱን ፡ አዝዘው ፡ አሠርተው ፡ ነበርና ፡ የሕንጻውን ፡ መፈጸም ፡ ቢሰሙ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ሳሉ ፤ ይቀድሱባት ፡ የነበረችውን ፡ ይህችኑ ፡ ታቦተ ፡ ማርያምን ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ አድርሰው ፡ እንድትገባ ፡ ስላሰቡ ፡ ከእንጦጦ ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ተጓዙ ።

ከጕዞውም ፡ በፊት ፡ የንጉሡና ፡ የእቴጌዪቱ ፡ አዛዦች ፡ ቀድመው ፡ ሔደው ፡ ሲደግሱ ፡ ሰንብተው ፡ ነበርና ፤ ስለ ፡ በዓሉ ፡ አስደናቂ ፡ የሆነ ፡ ግብዣ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ነበር ። ንጉሡና ፡ እቴጌዪቱ ፡ በሠራዊታቸው ፡ ታጅበው ፡ ወደደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፤ ሥነ ፡ በዓሉና ፡ ሥርዓተ ፡ በዓሉ ፡ የሚደረግበት ፡ ቀን ፡ በመቃረቡ ፡ ሕዝቡ ፡ ከጨጨሆና ፡ ከግቢ ፡ ሳይቀር ፡ ተሰብስቦ ፡ በመታየቱ ፡ ብዛት ፡ ዓይንን ፡ የሚበዘብዝ ፡ ሆኗል ። ለድግሱም ፡ ቁመቱ ፡ መቶ ፡ ሐያ ፡ ክንድ ፤ ወርዱ ፡ ዘጠና ፡



ክንድ ፡ የሆነ ፡ ዳስ ፡ ተሠርቶ ፡ ነበር ። ወዲያው ፡ በግንቦት ፤ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ጳጳሱ ፡ አቡነ ፡ ማቴዎስ ፤ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴና ፡ ካህናቱ ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስበው ፤ ወደቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ገብተው ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሡን ፡ ሲያደርሱ ፡ አደሩ ።

ሲነጋም ፡ ንጉሡ ፡ አጼ ፡ ምኒልክ ፡ በቤት ፡ አሽከሮችና ፡ በዘበኞች ፡ ታጅበው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፤ ክርስቲያኑ ፡ በክብር ፡ ሔዱ ።

መላው ፡ ሠራዊቱ ፡ ግን ፤ ሸንኰርት ፡ ከሚባለው ፡ ከራስ ፡ ዳርጌ ፡ ከተማ ፡ አንሥቶ ፡ ቦሎ ፡ እስከነበረው ፡ እስከ ፡ ደጃዝማች ፡ ናደው ፡ ቤት ፡ ድረስ ፤ ተራራውንና ፡ ሜዳውን ፡ መልቶ ፤ ፀአፋፍ ፡ አፋፉም ፡ ተደርድሮ ፡ ሦስት ፡ ክብ ፡ ሆኖ ፡ ተሰለፈ ። መድፈኞችም ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ መድፍ ፡ አጥምደው ፡ ከግቢ ፡ በስተጀርባ ፡ ተሰለፉ ። አጼ ፡ ምኒልክም ፡ ታቦቲቱን ፡ አንግሠው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሲመለሱ ፤ ወደ ፡ ሰልፉ ፡ መጥተው ፡ መድፉ ፡ ወደተጠመደበት ፡ ላይ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፤ መድፉ ፡ ሳያቋርጥ ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ተተኰሰ ።

ቀጥሎም ፡ ከራስ ፡ ዳርጌ ፡ ከተማ ፡ ከሸንኰርት ፡ አንሥቶ ፡ የደጃዝማች ፡ ናደው ፡ ቤት ፡ እስካለበት ፡ እስከቦሎ ፡ ድረስ ፡ የተሰለፈው ፡ ሠራዊት ፡ ነፍጥ ፡ ቢተኵስ ፤ ዓለም ፡ ያለፈ ፡ ያህል ፡ መሰለ ። ንጉሡም ፡ ግባቱ ፡ ከተተኰሰ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ድንኳኑ ፡ ገቡ ። ፊትም ፡ እንደተናገርነው ፡ በዚያ ፡ በተሠራው ፡ ዳስ ፡ ውስጥ ፡ ንጉሡ ፡ በዙፋናቸው ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ ለካህናት ፤ ለመኳንንት ፤ ለመላው ፡ ሠራዊትም ፡ ብዙ ፡ ግብዣ ፡ ተደረገ ።

ለዚሁም ፡ ሰዓተ ፡ መዓልቱ ፡ የማይበቃቸው ፡ ቢሆን ፤ ለንጋቱ ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ሲቀረው ፡ የሥራው ፡ ድርጅት ፡ ተጀመረና ፡ ከመዓልቱ ፡ በአሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ሲከናወን ፡ ውሎ ፤ ስለ ፡ ድርጅቱ ፡ ብዛት ፡ ከምሽቱ ፡ በኋላ ፡ አምስት ፡ ሰዓትን ፡ ቀጠለ ።

በሰፊው ፡ ዳስም ፡ ውስጥ ፤ ብዙ ፡ ፋና ፡ ይበራ ፡ ነበርና ፡ ዘጠኝ ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ ሠራዊቱን ፡ ለማስተናገድ ፡ ተቻለ ።

ከዚሁም ፤ ራስ ፡ ዳርጌ ፡ ያንዱን ፡ ቀን ፡ ግብር ፡ ችለዋል ። የራስ ፡ ዳርጌም ፡ አሽከር ፡ ደጃዝማች ፡ ለየህ ፡ ያንዱን ፡ ቀን ፡ እኩሌታ ፡ ግብር ፡ አብልተዋል ።

ለጊዜውም ፡ የግብሩ ፡ ነገር ፡ መጠኑ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ምሳሌውም ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ አልተቻለም ፡ ነበር ። እንዲህም ፡ እየተደረገ ፡ ንጉሡ ፡ በሠራዊታቸው ፡ መከከል ፡ ዘጠኝ ፡ ቀን ፡ ያህል ፡ ተቀምጠው ፡ ግብር ፡ ካበሉ ፤ በኋላ ፤ ራስ ፡ ሚካኤልንና ፤ ራስ ፡ ወሌን ፡ ከጨጨሆ ፡ እስከ ፡ ግቢም ፡ የተሰበሰበውን ፡ ሠራዊት ፡ ሁሉ ፡ አሰናበቱ ። በግንቦት ፡ ፳፫ ፡ ቀንም ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ገብተው ፡ የቤተ ፡ መንግሥታቸውን ፡ ሕንጻ ፡ አስጀመሩ ።

---

<u>፲፰፻፹፱</u> ፡ ዓ ፡ ም ፡ ብፁዕ ፤ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ ላይ ፡ በእመቤታችን ፡ በቅድስት ፡ ማርያም ፡ ስም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ <u>ስለማነጻቸው ።</u>

ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፤ ከደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ወደጐንደር ፡ ሔዳ ፡ የነበረችውን ፡ ታቦተ ፡ ማርያምን ፡ አምጥተው ፡ ወደጥንታዊ ፡ በዓቷ ፡ ወደደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ በክብር ፡ እንድትገባ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ከደረገ፡በኋላ፤አጼ ፡ ዮሐንስ፡ከድርቡሽ ፡ ጋራ ፡ ተዋግተው፡መተማ ፡ ላይ ፡ በሰማዕትነት፡
ስላረፉና ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥትነትን ፡ መዐርግ ፡ ደርበው ፡ የመላዋ፡
ኢትዮጵያ ፡ ገዥ ፡ ስለሆኑ ፤ ከላይ ፡ እንደተመለከተው ፡ ያ ፡ መነኰሴ ፡ በታቦቷ፡ምክ
ንያት ፡ የሚያገኙትን ፡ ዕድል ፡ የነገራቸው ፡ ትዝ ፡ ብሏቸው ፡ ኖሮ ፡ ከደብረ ፡ ሊባ
ኖስ ፡ አውጥተው ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ በተባለችው ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ
ያን ፡ ለማሠራትና ፡ ታቦተ ፡ ማርያምን ፡ ወደዚያ ፡ ለማስገባት ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መዘ
ምራንም ፡ ወደዚሁ ፡ መጥተው ፡ እንዲያገለግሉና ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ በሰዓታትና ፡ በቅ
ዳሴ ፡ ብቻ ፡ እንዲገለገል ፡ በሰፌው ፡ አቅደው ፡ በደብረ ፡ ጽጌና ፡ በአካባቢዋ ፡ ለሚ
ገኙት ፡ ባላባቶች ፡ ሁሉ ፡ የቦታቸውን ፡ ግምትና ፡ ለውጥ ፡ ከሰጡ ፡ በኋላ፡ያሰቡትን፡
ሳይፈጽሙ ፡ ስለታመሙ ፡ አሳባቸው ፤ ተቋርጦ ፡ ቆየ ።

ኢጣልያኖች ፡ በወራሪነት ፡ ገብተው ፡ የደብረ ፤ ሊባኖስን ፡ ገዳምና ፡ ሌሎችንም፡
ገዳማት ፡ አፍርሰው ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናቱንም ፡ ሁሉ ፡ ሲዘርፉና ፡ ሲያቃጥሉ ፡ ቆይ
ተው ፡ የበረገገውን ፡ ሕዝብ ፡ ለማረጋጋት ፡ ሲሉ ፡ ባንዳንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ (ሰብሮ ፡
መጠገን ፡ እንደሚባለው ፡ ሁሉ) ፡ ሲያፈርሱ ፡ የየራሳቸውን ፡ ሲሠሩ ፡ ነበርና፡
በዚችም ፡ በደብረ ፡ ጽጌ ፡ ላይ ፡ ጥንተ ፡ ታሪኳን ፡ በመጠየቅ ፡ ሕንጻ ፡ ጀምረው ፡
ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ለመሰለው ፡ በጎ ፡ ተግባር ፡ ያልታደሉ ፡ በመሆናቸው ፡
ጅምራቸውን ፡ ሁሉ ፡ ድል ፡ ስላቋረጠው ፡ ሥራቸው ፡ ከመ ፡ ሕንጻ ፡ ደቂቀ ፡ ሆኖ ፡
ቀረ ። ማህሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በጊዜሁ ፡ እንደተባለ ፡ ብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡነ ፡
ባስልዮስ ፡ የአጼ ፡ ምኒልክን ፡ ውጥን ፡ ለመፈጸም ፡ ዕድላቸው ፡ ሆኖ ፡ ኖሮ ፡ በዚ
ችው ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ በምትባል ፡ ተራራ ፤ በእመቤታችን ፡ ስም ፡ ቤተ ፡
ክርስቲያን ፡ ለመሥራት ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ አስፈቅደው ፡ በ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡
ሥራውን ፡ አስጀመሩ ። ግርማዊነታቸውም ፡ ኻያ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ እርዳታ ፡ ሰጥተው፡
ወደፊትም ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ አገልጋዮች ፡ ርስት ፡ እንደሚሰጣቸው ፡ ተስፋ ፡
የተመላበትን ፡ ንጉሣዊ ፡ ቃል ፡ ሰጥተዋቸዋል ። እንዲሁም ፡ ግርማዊት ፡ እቴጌ ፡
ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽና ፡ ልዑል ፡ መኰንን ፡ ቃለ ፡ ተስፋቸውን ፡ አበርክተ
ዋል ። ሥራውም ፡ እንደተፈጸመ ፡ በ፲፱፻፴፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጥር ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡
ቅዳሴ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ ለማክበር ፡ አስበው ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ አድባራት ፡
ሊቃውንትና ፡ ካህናት ፡ ሔደው ፡ እንዲያከብሩላቸው ፤ ጥሪ ፡ አድርገውላቸው ፡ ነበርና፡
ጥር ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ (በዋዜማው) ፡ ሊቃውንቱ ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ በካሚዎንና ፡ በየ ፡ አው
ቶሞቢሉ ፡ ወደደብረ ፡ ጽጌ ፡ ሲጓዙ ፡ ከብዛታቸውና ፡ ከድምቀታቸው ፡ የተነሣ፡ተመ
ልካቹ ፡ ሁሉ ፡ ሊገረምበት ፡ ችሏል ። የቤተ ፡ ክርስቲያኑም ፡ ቡራኬ ፡ በዋዜማው ፡
ተፈጽሞ ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ቀድሰዋል ። የአዲስ ፡ አበባም ፡ ሊቃውንት ፡ ወደዚያ ፡
እንደደረሱ ፡ ለብፁዕነታቸው ፡ ማረፊያ ፡ በተሰናዳው ፡ ግቢ ፡ ክበብ ፡ በተተከለው፡
ከ፫ሺህ ፡ የማያንስ ፡ ሰው ፡ ወደሚይዘው ፡ ድንኳን ፡ ገብተው ፤ እንዲሁም ፡ ዋዜማ
ውን ፡ የቆሙት ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስና ፡ የአካባቢው ፡ ካህናት ፡ በሌላው ፡ ክፍል ፡
ሆነው ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ ሆኖ ፡ አመሸ ።



ጥቂትም ፡ ዕረፍት ፡ ተደርጎ ፡ ፮ ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፤ ደወሉ ፡ የተጋብኦ ፡ ድምፁን ፡
በሰማ ፡ ጊዜ ፤ ከላይ ፡ የተመለከቱት ፡ ሊቃውንትና ፡ ካህናት ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያኑ፡
ሲጐዳኙ ፡ ከብዛታቸው ፡ የተነሣ ፡ ሥርዓተ ፡ ማኅሌቱን ፡ ለማከናወን ፡ በቂ ፡ ቦታ፡
ይገኛል ፡ ብሎ ፡ ለመገመት ፡ ችግር ፡ መስሎ ፡ ይታይ ፡ ነበር ። በዚሁም ፡ ጊዜ ፡
መዘምራኑ ፡ "እንሥኢ ፡ አዕይንተኪ ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ ወነጽሪ ፡ ዐውደኪ ፡ አስመ ፡
አዕበየ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ማህሎ ፡ ላዕሌኪ ፡ ይትጋፈሩ ፡ ጸላእትኪ ፡ እለ ፡ ኢይ
ቀርቡ ፡ ኀቤኪ ፡ ወኢይሁብ ፡ ለባዕድ ፡ ክብረኪ ፡ ደብረ፡ሊባኖስ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ፡
ንጉሠ ፡ ነገሥት» ፡ እያሉ ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ሁሉ ፡ ምሥጢራዊ ፡ ጣዕመ ፡
ዝማሬ ፡ ሲያሰሙ ፡ የሰሚዎችን ፡ ሕሊና ፡ ይማርክ ፡ ነበር ። ፲ሰዓትም ፡ ሲሆን ፡
ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ ለማድረስ ፡ ታቦታቱ ፡ በዐውዱ ፡ ላይ ፡ ብቅ ፡ ባሉ ፡
ጊዜ ፡ በዓሉን ፡ ለማክበር ፡ የተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ ሴቱ ፡ በእልልታ ፡ ወንዱ ፡
በሆታ ፡ ካህናቱ ፡ በሃሌታ ፡ የደስታ ፡ ድምፁን ፡ አጕልቶ ፡ ሲያሰማ ፡ የታየው ፡
ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ለአንክሮው ፡ በቂ ፡ መግለጫ፡አልተገኘለትም ። ክቡር ፡ ጸሐፌ፡
ትእዛዝ ፡ ኃይሌ ፡ ወልደ ፡ ሩፌ ፡ በዓሉን ፡ ለማክበር ፡ ከአዲስ ፡ አበባ፡ሔደው፡
ነበር ። በንግሡም ፡ አደባባይ ፡ በሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ በመልአከ ፡ ብርሃናት ፡ ገብረ ፡
እግዚእት ፡ ተቀዳሚነት ፡ የቤተ ፡ ክህነቱ ፡ ዋና ፡ አጋፋሪና ፡ ከሰላሌ ፡ አውራጃ ፡
የመጡት ፡ ፖሊሶች፡የማስተናበሩን ፡ ሥራ ፡ በቅልጥፍና ፡ ያከናውኑት ፡ ነበር ።

የዑደቱም ፡ ሥርዓት ፡ ተፈጽሞ ፡ መዘምራኑ ፡ ዝማሬ ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡
የአዲስ ፡ አበባ ፡ መንበረ ፡ ጸባኦት ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ገዳም ፡ መምህር ፡ ሊቀ ፡
ሥልጣናት ፡ መልአክቱ ፡ (አሁን ፡ አቡነ ፡ ቴዎፍሎስ) ፡ የእመቤታችን ፡ የቅድስት፡
ድንግል ፡ ማርያምን ፡ ዕረፍት ፡ በሚገባ ፡ አስረድተው ፡ ንግግራቸውን ፡ በመቀ
ጠል ፡ ለእመቤታችን ፡ በዕረፍቷ ፡ ጊዜ ፡ ልጅዋ ፡ ፈጣሪዋ ፡ በስምሽ ፡ በጎ ፡ መታ
ሰቢያ ፡ ያደረገውን ፡ ሁሉ ፡ እምርልሻለሁ ፡ ብሎ ፡ የሰጣትን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ መሠ
ረት ፡ በማድረግ ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ይህን ፡ ያማረ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በብዙ ፡
ድካም ፡ መሥራታቸው ፡ ለምእመናን ፡ ሁሉ ፡ ፍጹም ፡ ደስታን ፡ የሚያድል ፡ ነው ።
በብፁዕነታቸውም ፡ ስም ፡ ሆኗ ፡ ይህ ፡ ቦታ ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ በመባሉ ፡ ላይ ፡ «ደብር፡
ቅዱስ» ፡ ተብሎ ፡ እንዲጠራ ፡ መሰየሙን ፡ ስገልጽ ፡ „ደብር ፡ ቅዱስ„ ፡ የተባለበት ፡
ምክንያት ፡ አዳምና ፡ ሔዋን ፡ ፈጣሪያቸውን ፡ በድለው ፡ ከገነት ፡ እንዲወጡ ፡
ከተፈረደባቸው ፡ በኋላ ፤ ደብር ፡ ቅዱስ ፡ የተባለውን ፡ ቦታ ፡ መከነ ፡ ንስሓ ፡ ተቀብ
ለው ፡ ገነትን ፡ እያሻገሩና ፡ እያዩ ፡ ወደፈጣሪያቸው ፡ ሲያዝኑና ፡ ሲያለቅሱ ፡ ኖረው፤
ጊዜው ፡ ሲደርስ ፡ ወደቀደሞው ፡ ቦታቸው ፡ ገነት ፡ ለመግባት ፡ እንደቻሉ ፡ እን
ዲሁም ፡ ፈጣሪያቸውን ፡ በኃጢአት ፡ ያሳዘኑ ፡ ሰዎች ፡ ስለኃጢአታቸው ፤ ሥርየት ፡
መለመኛ ፡ መከነ ፡ ንስሓ ፡ እንዲሆናቸው ፡ በመታሰቡ ፡ ነው ።

በዚሁም ፡ ቦታ ፡ ደንበኛ ፡ የሆነ ፡ መንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ቤትን ፡ ከፍ
ተው ፡ እናትና ፡ አባት ፡ የሌላቸውን ፡ ልጆች ፡ በምግብና ፡ በልብስ ፡ እየረዱ ፡
በአዳሪነት ፤ ሌሎችም ፡ በአካባቢው ፡ የሚገኙት ፡ በተመላላሽነት ፡ እንዲማሩ ፡

www.ethiopianorthodox.org

የብፁዕነታቸው ፡ አሳብ ፡ ስለሆነ ፤ በዚሁ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ብዙ ፡ ወጣቶች ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ለሀገራቸው ፡ የአገልግሎት ፡ ፍሬያቸውን ፡ እንዲያሳዩ ፤ ባከባቢውም ፡ የሚገኙት ፡ ምእመናን ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኑና ፡ በትምህርት ፡ ቤቱ ፡ አማካይነት ፡ በእውነተኛው ፡ አምልኮ ፡ እንዲጸኑ ፡ የአሳቡ ፡ ግምት ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅም ፡ የሚሰጥ ፡ ይሆናል ፡ ሲሉ ፡ ሌላውንም ፡ ጠቃሚ ፡ ምክር ፡ በመስጠት ፡ መልካም ፡ ስብከት ፡ አደረጉ ።

ከዚህም ፡ ቀጥሎ ፤ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ አሁን ፡ እንደተነገረው ፡ ይህን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሥራቴ ፡ ሥጋዊ ፡ ክብርና ፡ ጥቅም ፡ ልፈልግበት ፡ ሳይሆን ፤ ከታላቁ ፡ ሐዋርያ ፡ ከአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በረከት ፡ ለመሳተፍ ፡ የሚፈልጉ ፡ ምእመናን ፡ ሁሉ ፤ እንዲያርፉበትና ፡ ለታላቁ ፡ ገዳም ፡ መቃረቢያ ፡ እንዲሆናቸው ፡ ነው ።

ስለቤተ ፡ ክርስቲያኑም ፡ ሥራ ፤ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በበጎ ፡ ፈቃዳቸው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እርዳታ ፡ ስላደረጉልኝ ፤ ሥራው ፡ ፍጻሜ ፡ ሊያገኝ ፡ ቻለ ። እኔም ፡ ባለኝ ፡ አቅም ፡ ሁሉ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑንና ፡ ትምህርት ፡ ቤቱን ፡ በሚገባ ፡ ለማቋቋም ፡ የምጥርበትና ፡ የምደክምበት ፡ ተግባሬ ፡ ይሆናል ።

በዚሁም ፤ በዓሉን ፡ ለማክበር ፡ የተሰበሰባችሁ ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ጸሎታችሁ ፡ የሠመረና ፡ የተወተደደ ፡ ሆኖ ፡ ዋጋችሁን ፡ እግዚአብሔር ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ይክፈላችሁ ። ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴን ፡ ረጅም ፡ ዕድሜና ፡ ጤና ፡ ሰጥቶ ፡ በዙፋናቸው ፡ ያቆይልን ። መንግሥቱን ፡ ጽኑ ፡ ሰላም ፡ ያድርግልን ። ለሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ ሣህልና ፡ ምሕረትን ፡ ይዘዝልን ፡ ሲሉ ፡ ሰፊ ፡ ቡራኬያቸውን ፡ ሰጥተውና ፡ ጸሎቱን ፡ አሳርገው ፡ የሥርዓተ ፡ ንግሡ ፡ ፍጻሜ ፡ ሆነ ።

በዚሁ ፡ ቀን ፡ ብፁዕነታቸው ፡ ከሌሎች ፡ ተራዳእያን ፡ መነኰሳት ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ ስለቀደሱ ፤ ጸሎተ ፡ ቅዳሴው ፡ እጅግ ፡ በማረ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሊፈጸም ፡ ቻለ ። ፱ ፡ ሰዓት ፡ ተኩልም ፡ ሲሆን ፡ ለግብሩ ፡ ከተሰናዳው ፡ ድንኳን ፡ ሊቃውንቱና ፡ ካህናቱ ፤ መኳንንቱና ፡ ሠራዊቱ ፤ ሕዝበ ፡ ክርስቲያኑም ፡ ሁሉ ፡ በየማዕርጉ ፡ ገብቶ ፡ ሙሉ ፡ ግብር ፡ ተደርጎ ፡ አመሸ ።

በማግሥቱ ፡ ጥር ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ሐሙስ ፡ ከቀኑ ፡ ፯ ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ካለፉት ፡ ቀኖች ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ታላቅ ፡ ግብር ፡ ተደርጎ ፡ እስከ ፡ ፲ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ቆየ ። በዚሁም ፡ ቀን ፡ ከደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ካህናት ፡ በዓሉን ፡ ለማክበር ፡ በተግባር ፡ ምክንያት ፡ ሳይመጡ ፡ የቀሩት ፡ ሁሉ ፡ በመላው ፡ እንዲመጡ ፡ ታዞ ፡ ነበርና ፡ በግብሩ ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ ሕዝብ ፡ ብዛት ፡ ልክ ፡ አልነበረውም ።

በግብዣውም ፡ ላይ ፤ ሊቃውንቱ ፡ ምርቃቱንና ፡ ቅኔውን ፡ እንደማዕበል ፡ ሲያወርዱት ፤ የቅኔው ፡ ምርትና ፡ ድምፃቸው ፡ የድንኳኑን ፡ አካባቢ ፡ መልቶት ፡ ነበር ።



ግብር ፡ መልስ ፡ ሆኖም ፡ ጥቂት ፡ እንደቆየ ፤ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ የመጡት ፡ ሊቃውንት ፡ በነጋታው ፡ ወደአዲስ ፡ አበባ ፡ የሚመለሱበት ፡ ቀን ፡ ስለሆነ ፤ ከምሽቱ ፡ ፩ ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ ተደርጎላቸው ፡ እስከ ፡ ፫ ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ አመሹ ። ብፁዕ ፡ አባታችንም ፡ በዚሁ ፡ ግብር ፡ ራሳቸው ፡ ተቀምጠው ፡ ያን ፡ ሁሉ ፡ ሕዝብ ፡ ያለመሰልቸት ፡ በብርሃናዊ ፡ ገጻቸው ፡ እያስደሰቱ ፡ በመጋበዛቸው ፡ ላነጋገሩ ፡ ኅብር ፡ የሆነው ፡ ግብረ ፡ ሰፊነታቸው ፡ በየአንዳንዱ ፡ ሊቅ ፡ አንደበት ፡ ሲነገር ፡ ይሰማ ፡ ነበር ።

ሊቃውንቱም ፡ በየተራ ፡ እየተነሡ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥቅስ ፡ እየጠቀሱ ፡ የበታውን ፡ ዝክረ ፡ ነገርና ፤ የብፁዕነታቸውንም ፡ የተቀደሰ ፡ አሳብ ፡ እያስታወሱ ፡ የሚያቀርቡት ፡ ምርቃትና ፡ የሚለምኑላቸውም ፡ ዕድሜ ፡ ልባዊ ፡ እንጂ ፡ አፍአዊ ፡ አልነበረም ። ይህ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ሊቃውንቱ ፡ በያመቱ ፡ በዚህ ፡ ቦታ ፡ እየተሰበሰቡ ፡ በዓሉን ፡ ለማክበር ፡ እንደብፅዓት ፡ ያለ ፡ ቃላቸውን ፡ ሲሰጡ ፤ ብፁዕ ፡ አባታችንም ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ድረስ ፡ ደክመው ፡ በዓሉን ፡ ስላከበሩላቸው ፡ ለሊቃውንቱ ፡ ልባዊ ፡ ደስታቸውን ፡ ይገልጡ ፡ ነበር ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሊቃውንቱ ፡ ከብፁዕነታቸው ፡ እየተሰናበቱ ፡ ለማረፊያ ፡ በተዘጋጀላቸው ፡ ድንኳን ፡ አድረው ፡ በማግሥቱ ፡ ወደአዲስ ፡ አበባ ፡ ተመለሱ ። ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ግን ፡ ጥር ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ በዓል ፡ አክብረው ፡ ለመመለስ ፡ በዚያው ፡ ቆዩ ።

ጥር ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ዐርብ ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ አዳራቸውን ፡ ወደደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ሔደው ፡ ጥር ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ በዓል ፡ አከበሩ ። ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ሔደው ፡ ከነበሩትም ፡ ሊቃውንት ፡ በዓሉን ፡ አክብረው ፡ ለመመለስ ፡ የቆዩ ፡ ነበሩና ፡ በዓሉ ፡ ድምቀት ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ ነበር ።

በዚሁም ፡ በጥር ፡ ፳፬ ፡ ቀንና ፡ በጥር ፡ ፳፭ ፡ ቀን ፡ ለካህናትና ፡ ለባላባት ፡ በአካባቢውም ፡ ለሚገኙት ፡ ባላገሮች ፡ ሁሉ ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ በተሠራችው ፡ በአዲሲቱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መቃረቢያ ፡ ታላቅ ፡ ግብር ፡ ተደርጎ ፡ ዋለ ። እንዲህም ፡ በለ ፡ አከባበር ፡ ያከባበሩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ተፈጽሞ ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ በጥር ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ወደአዲስ ፡ አበባ ፡ ተመለሱ ።

---

ብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እሑድ ፡ በ፫ ሰዓት ፡ የአቴና ፡ ርእሰ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ እስፒሪዶን ፡ ለስድስቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጳጳሳት ፡ ስለላኩት ፡ ሽልማት ፡ የተናገሩት ።

## በመንፈሳዊ ፡ ፍቅር ፡ የተመላ ፡ ቃል ።

የክርስትና ፡ ብርሃን ፡ በመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ ከወጣባቸው ፡ ከታላላቁ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ አንዲቱ ፡ ጽርአዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ናት ።

www.ethiopianorthodox.org

የብርሃኑዋም ፡ ጮራ ፡ በብዙ ፡ አገሮች ፡ ላይ ፡ እንዳንጸባረቀ ፡ የታወቀ ፡
ነው ። በዚያ ፡ በመጀመሪያው ፡ የክርስትና ፡ ዘመን ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሕገ ፡ ኦሪት ፡
አምልኮቱዋን ፡ ይዛ ፡ በምዕራብ ፡ ኦሪት ፡ ትገኝ ፡ ነበር ። በአራተኛው ፡ መቶ ፡
ክፍለ ፡ ዘመን ፡ በመጀመሪያው ፡ ሩብ ፡ የክርስቶስ ፡ ብርሃን ፡ ስለ ፡ ተገለጸላት ፡
ከምዕራብ ፡ ኦሪት ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተዛወረች ። ለዚህ ፡ ብርሃን ፡
ምክንያት ፡ ሆኖላት ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ ነገዱ ፡ ጽርአዊ ፡ ወይም ፡ ጢሮሳዊ ፡
መዐርገ ፡ ጵጵስናውን ፡ ከእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ከቅዱስ ፡ አትናቴዎስ ፡
የተቀበለው ፡ ቅዱስ ፡ ፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ነው ።

በአፍሪቃ ፡ ምሥራቅ ፡ የምትገኘውን ፡ የሐዋርያውንና ፡ የወንጌላዊውን ፡
የቅዱስ ፡ ማርቆስን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዚያ ፡ በመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ የመሠረ
ተው ፡ ይህ ፡ ቅዱስ ፡ ፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ሥርዓተ ፡ ረበናትን ፡ አስወግዶ ፡ የወንጌ
ልን ሰላም ፡ አቋቋመ ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ ሰላማ ፡ ብላ ፡ ሰየመችው ።

የግሪኮችና ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ወድማማችነትና ፡ መንፈሳዊ ፡ ፍቅር ፡ ይህን ፡
በመሰለ ፡ በጠንካራ ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ ተመሥርቶ ፡ የቆየ ፡ መሆኑ ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

ባለፈው ፡ ዓመት ፡ በእርስዎ ፡ በብፁዕ ፡ አባ ፡ ኒቆላኦስ ፡ እጅ ፡ ስድስቱ ፡
ወጣቶቻችን ፡ ለሊቅነት ፡ ትምህርት ፡ ወደግሪክ ፡ አገር ፡ ለመሔድ ፡ መብቃታ
ቸውም ፡ ከዚሁ ፡ ፍቅር ፡ በተገኘው ፡ ፍሬ ፡ መሆኑ ፡ አይጠረጠርም ።

የአቴና ፡ ርእሰ ፡ ጳጳሳት ፡ ብፁዕ ፡ አባ ፡ እስፒሪዶን ፤ ለኔና ፡ ላጅቱ ፡ የኢት
ዮጵያ ፡ ጳጳሳት ፡ የላኩዋቸው ፡ እንደ ፡ መስቀል ፡ በደረት ፡ ላይ ፡ የሚውሉ ፡ የሥዕል ፡
ሽልማቶች ፡ በሁለቱ ፡ ሀገሮች ፡ መከከል ፡ ያለውን ፡ ጥንታዊ ፡ ፍቅር ፡ የሚያስታውሱ ፡ ናቸው ።
እነዚህንም ፡ ሽልማቶች ፡ (አይኮኖች ፡ ) በደስታ ፡ መቀበላችንና ፡ በዚህም ፡ ምክንያት ፡
ያቀረብነውን ፡ ምስጋናችንን ፡ ለብፁዕ ፡ ርእሰ ፡ ጳጳስ ፡ አባ ፡ እስፒሪዶን ፡ እንዲያ
ቀርቡልን ፡ በራሴና ፡ በወንድሞቼ ፡ በጅቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጳጳሳት ፡ ስም ፡ እለምን
ዎታለሁ ። የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፤ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ፍቅር ፤ የመንፈስ ፡
ቅዱስ ፡ አንድነት ፡ በሁላችን ፡ ላይ ፡ ይደር ።

ታኅሣሥ ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ በመንበረ ፡ ፀባዖት ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ቤተ ፡
ክርስቲያን ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስና ፡ አቡነ ፡ ቴዎፍሎስ ፤ በሉበት ፤ መሪ ፡
አባ ፡ እስፒሪዶን ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ ጳጳሳት ፡ ያበረከቷቸውን ፡ ኤንኰልፒያት ፡
ሲያቀርቡ ፡ ከብፁዕ ፡ ሜትሮፖሊት ፤

## ከአባ ፡ ኒኮላኦስ ፡ የተነገረ ፡ ቃል ።

ኤንኰልፒዮን ፡ እንደ ፡ መስቀል ፡ በደረት ፡ ላይ ፡ የሚውል ፡ የቅዱሳን ፡
በተለይም ፡ የእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ሥዕል ፡ ያለበት ፡ ጳጳሳት ፡ የሚለብሱት ፡
ሽልማት ፡ ነው ።



ከስድስት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ያህል ፤ ከነዚያ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጠላት ፡ በመ
ከላከል ፡ ጀግኖች ፡ የነበሩትና ፡ ስለነጻነት ፡ ያለፉት ፡ አርበኞች ፡ አዕፅምት ፡ በተቀ
መጠበት ፡ በዚህ ፡ በቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሕንጻ ፡ ውስጥ ፡ ተገኝቻ
ለሁ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፤ የሐዋርያውና ፡ የወንጌላዊው ፡ ማርቆስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
ለኢትዮጵያና ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥትዋ ፡ በታማኝነት ፡ ለተገኘ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡
ክህነት ፡ ፍቅሯንና ፡ አክብሮቷን ፡ ለመግለጥ ፡ ፈለገች ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፤ ከዚህ ፡ ሥፍራ ፡ ከብፁዕ ፡ የእስክንድርያ ፡ ፓትሪያርክ ፡
በዚያን) ፡ ጊዜ ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ለነበሩት ፡ (ዛሬ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡
ባስልዮስ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ የተገቡ ፡ መሪና ፡ የተከበሩ ፡ ለኢትዮ
ጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተጠሪ ፡ በመሆናቸው ፡ የተላከውን ፡ የደረት ፡ መስቀል ፡
አስረክቤአለሁ ።

የቅዱስ ፡ ፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በእስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክር
ስቲያን ፡ ልብ ፡ ሥፍራዋን ፡ እንደያዘች ፡ ናት ። እናት ፤ ልጅዋን ፡ በመውደድ ፡
አለች ፡ ልጅቷም ፡ ለፍቅር ፡ የተገባች ፡ መሆንዋን ፡ አላቋረጠችም ።

ስለዚህ ፤ ስለ ፡ ኢትዮጵያና ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሌ
ላም ፡ የግሪክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እነሆ ፡ የፍቅር ፡ ምልክት ፡ ደረሰ ።

ግሪኮች ፡ ኢትዮጵያን ፡ ወደዱ ፡ ይወዳሉም ። ይህም ፡ ፍቅራቸው ፡ ለመቼውም ፡
ቢሆን ፡ አያቋርጥም ።

የሐዋርያው ፡ የቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፤ በመሪዋ ፡ በብፁዕ ፡ አባ
እስፕሪዶን ፡ ሰውነት ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መንገድ ፡ ይህችን ፡ ፍቅር ፡ ትገልጻለች ።
አምና ፡ በኔ ፡ እጅ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተላኩትን ፡ ስድስት ፡ ወጣ
ቶች ፡ ተቀብለዋል ።

እነርሱም ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በሚያፈቅራት ፡ በቆሮንቶስ ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡
ክህነት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ገቡ ። ዘንድሮ ፡ የግሪክ ፡ መልክተኛ ፡ ሙሴ ፡ ሚሊያሬ
ሲስ ፡ ከአቴና ፡ ሲመለሱ ፤ ስድስት ፡ ኤንኰልፒያት ፡ ይዘውልኝ ፡ መጡ ። ብፁዕ ፡
የአቴና ፡ ርእሰ ፡ ጳጳስ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ለቤተ ፡ ክህነት ፡ መሪዎች ፡
የላኩት ፡ መታሰቢያ ፡ ነው ።

እነዚህ ፡ ኤንኰልፒያት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ታሪክ ፡ አንድ ፡ ምዕ
ራፍ ፡ በሆነው ፡ በታላቁ ፡ ፍጻሜ ፡ ምክንያት ፡ የግሪክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተሰ
ማትን ፡ ደስታ ፡ የሚገልጡ ፡ ናቸው ።

በዚህች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ታሪክ ፤ ከኢትዮጵያ ፤ ሕዝብ ፡ ሰውነት ፡ ለቤተ
ክህነትዋ ፡ መሪ ፡ ከማግኘት ፡ የበለጠ ፤ ፍጻሜ ፡ ይኖር ፤ ይሆን ?፡ ለስድስቱ ፡ ኢት
ዮጵያውያን ፡ ጳጳሳት ፡ የጽርእ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስድስት ፡ ኤንኰልፒያት ፡ ትል
ካለች ።

www.ethiopianorthodox.org

ከነዚህ ፡ ኤንጎልፒያት ፡ ጋራ ፡ ብፁዕ ፡ የግሪክ ፡ አገር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሪ ፡ የላኩትን ፡ መልክት ፡ እንዳለ ፡ ለማንበብ ፡ ዛሬ ፡ የተገባ ፡ ጊዜ ፡ ነው

«ብፁዕና ፡ በክርስቶስም ፡ ዘንድ ፡ ወንድም ፡ የተከበሩ ፡ ሙሴ ፡ ሚሊያሬሲስ ፡ የግሪክ ፡ ጉዳይ ፡ ፈጻሚ ፤ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ መናገሻ ፡ ከተማ ፡ መመለስን ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ወደ ፡ ፍቅርዎ ፡ የወንድምነት ፡ በረከት ፡ ስድስት ፡ የጳጳሳት ፡ ኤንጎልፒያት ፡ በርሳቸው ፡ በኩል ፡ ለመላክ ፡ ምክንያቱን ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ እንጠቀምበታለን ።

ለእናት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፤ የወንድምነት ፡ የፍቅርና ፡ የአክብሮት ፡ ምልክት ፡ የሚሆኑ ፡ እነዚህን ፡ ኤንጎልፒያት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ርእሰ ፡ ጳጳስ ፡ ለብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስና ፡ ለቀሩትም ፡ ብፁዓን ፡ ጳጳሳት ፡ እንዲሰጡልን ፡ እንለምንዎታለን ።

ግሪኮችን ፡ አፍቃሪ ፡ በሆኑ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በትረ ፡ መንግሥት ፡ ሥር ፡ ክቡር ፡ በሚሆነው ፡ የሥራ ፡ ትግል ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚጠብቃት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለሚኖሩት ፡ ኦርቶዶክሳውያን ፡ ግሪኮች ፡ የሚደረግላቸውን ፡ የፍቅር ፡ አስተያየት ፡ አንዘነጋውም ።

ለብፁዕነትዎ ፡ የጋለ ፡ ምስጋና ፡ እያቀረብን ፤ ወዳጅ ፡ ብፁዕነትዎን ፡ በክርስቶስ ፡ ፍቅር ፡ እንሳለማለን ።

በክርስቶስ ፡ ዘንድ ፡ የተወደደ ፡ ወንድም ፡ የአቴና ፡ ርእሰ ፡

ጳጳስ ፡ እስፒሪዶን ።

ለብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ መስቀሉን ፡ ስሰጥና ፡ ደረቴም ፡ በደስታ ፡ ሲሰፋ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሪዎች ፡ ሌላም ፡ የፍቅርና ፡ የአክብሮት ፡ ምልክት ፡ ለማቅረብ ፡ የበለጠ ፡ ደስታ ፡ እንዲሰጠኝ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለምኜው ፡ ነበር ። እግዚአብሔር ፡ ምኞቴን ፡ ሰማኝ ፡ (ፈጸመልኝ) ።

ነገር ፡ ግን ፤ የኢትዮጵያ ፡ ጳጳሳት ፡ መሾም ፡ የኔ ፡ ብቻ ፡ ምኞት ፡ አልነበረም ፡ የኢትዮጵያውያንም ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የሌሎችም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወዳጆች ፡ የሚሆኑ ፡ በብዙ ፡ ሚሊዮን ፡ የሚቈጠሩ ፡ ምኞት ፡ ነበር ።

ይኸውም ፡ ምኞት ፡ አሁን ፡ በሕይወት ፡ ያሉት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ በልባቸው ፡ ጥልቀት ፡ ይህን ፡ መልከም ፡ ምኞት ፡ እንደያዙ ፡ ዓይኖቻቸውን ፡ የዘጉ ፡ ያለፉት ፡ ትውልዶችም ፡ ምኞት ፡ ነበር ፡ እንጂ ። እግዚአብሔር ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ክርስቲያን ፡ ስድስት ፡ መላእክት ፡ ሰጠ ። የጽርእ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በእነዚህ ፡ በስድስት ፡ ኤንጎልፒያት ፡ ስለዚህ ፡ ፍጻሜ ፡ ደስታዋን ፡ ትገልጣለች ። ከወንድሞች ፡ ለወንድሞች ፡ የሚገለጥ ፡ ደስታ ፡ ነው ።

ግሪኮች ፤ ኢትዮጵያውያንን ፡ እንደ ፡ ወንድሞች ፡ ዘወትር ፡ ይመለከቷቸዋል ። የሃይማኖት ፡ ወንድምነት ፡ ነው ። የዚህን ፡ የወንድምነት ፡ የመሠረቱን ፡ ደንጊያ ፡ የተቀደሱት ፡ የቅዱስ ፡ ፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ እጆች ፡ ባረኩ ።



የዚህ ፡ ወንድምነት ፡ ዛፍ ፡ ፍሬያማ ፡ በሆነው ፡ በኢትዮጵያ ፡ መሬት ፡ አደገ ። ቆይቶ ፡ ግን ፤ ነፋሶች ፡ ነፈሱ ፤ እጅግም ፡ ብርቱዎች ፡ ነበሩና ፡ የዛፉ ፡ ግንድ ፡ ተሰበረ ። ዛፉም ፡ ወደቀ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከሥሩ ፡ አልተነቀለም ። የተቀደሱ ፡ እጆች ፡ ተከሉት ። የኢትዮጵያ ፡ መሬት ፡ የተባረከ ፡ ነው ። ስል ፡ መጥረቢያ ፡ በባሕር ፡ ዛፎቻችሁ ፡ ቢወድቅባቸውና ፡ ቢሰባብራቸው ፡ እንኳ ፡ እነሱ ፡ አይደርቁም ። እንደገና ፡ አዳዲስ ፡ ቍጥቋጦች ፡ ከማውጣትና ፡ ከመለምለም ፡ አይዘገዩም ። እኛ ፡ ያዲሱ ፡ ትውልድ ፡ የነዚህ ፡ ቍጥቋጦች ፡ ተጠሪዎች ፡ ነን ። ወጣቶችም ፡ ብንሆን ፤ ያለፈውን ፡ አንዘነጋውም ።

ግሪኮችና ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አንድ ፡ የሆኑ ፡ መተሳሠሪያዎችና ፡ ምልክቶች ፡ አሉን ። የኢትዮጵያና ፡ የጽርእ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አንድ ፡ በሆነ ፡ ብህል ፡ ተዋሕደዋል ።

ሁለቱም ፡ ነጻነትን ፡ ይወዳሉ ። የነጻነት ፡ ፍቅር ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለልጆቿዋ ፡ የምታጠባው ፡ ወተት ፡ ነው ። ቤተ ፡ ክህነቷ ፡ ስለ ፡ ነጻነት ፡ ይሠዋል ።

የግሪክ ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ ስለ ፡ ነጻነት ፡ የመሥዋዕት ፡ አብነት ፡ የሚሆኑ ፡ ፓትሪያርክ ፡ ግሪጎሪዮስ ፡ ቢኖሩትም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክህነትም ፡ የራሱ ፡ አብነት ፡ አለው ። ሰማዕቱ ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ ናቸው ።

ኢትዮጵያውያኖች ፡ እጆች ፡ በኰረብታዎች ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ በኵራት ፡ የያዙትና ፡ የሚይዙትን ፡ የሃይማኖትና ፡ የነጻነት ፡ ፋና ፡ ግሪኮች ፡ በአፓርሊስ ፡ (የእምነት ፡ ምሽግ) ፡ ሆነው ፡ ይመለከታሉ ።

ብፁዓን ፡ ወንድሞቼ ፡ ጳጳሳት ።

ዛሬ ፡ በተለይ ፡ ኵራት ፡ ይሰማኛል ። የግሪክ ፡ አገር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሪ ፡ እነዚህን ፡ ኤንጎልፒያት ፡ እንዳቀርብላችሁ ፡ ጠየቁኝ ። ይህ ፡ መልእክት ፡ ልዩ ፡ ክብር ፡ ይሰጠኛል ። የፍቅር ፡ ምልክት ፤ የማክበር ፡ ምሳሌ ፤ የወንድምነት ፡ ዐረቦን ፡ የሚሆኑትን ፡ ኤንጎልፒያት ፡ አቀርባለሁ ።

ኤንጎልፒዮን ፡ ለምሥራቃዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መዓርግ ፡ ጵጵስና ፡ መለያ ፡ ምልክት ፡ ነው ። ይህን ፡ በደረታችሁ ፡ ባደረጋችሁ ፡ ጊዜ ፤ ሁሉ ፡ የክሪግ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በጎናችሁ ፡ ቆማ ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ አብራ ፡ ለመሥራት ፡ እጆቿን ፡ እንደምትዘረጋ ፡ ታስታውሳላችሁ ።

የአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ተባብሮ ፡ መሥራት ፡ በተለይ ፡ ዛሬ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ሕዝቦች ፡ ከአብያተ ፡ ክርስቲያናቶቻቸው ፡ መሪዎች ፡ ብዙ ፡ ይጠብቃሉ ።

ዛሬ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በክርስቶስ ፡ መንፈስ ፡ ተባብረው ፡ ለመሥራት ፡ ይጥራሉ ። መንፈሳውያት ፡ ኃይላት ፤ በሚያሰጋ ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ናቸው ። ግዙፍ ፡ መንፈስ ፡ እውነተኛ ፡ የሕይወትን ፡ ጤዛ ፡ ለማድረቅ ፡ በአሥጊነት ፡ ላይ ፡ ነው ።

ዓለም ፡ ሰላምን ፡ ተጠምቷል ። እውነተኛ ፡ ዳኝነትን ፡ ይናፍቃል ። ሕይወትን ። ይሻል ። በክርስቶስ ፡ መንፈስና ፡ ፍቅር ፡ ካልሆነ ፤ ሰው ፡ ዕረፍቱን ፡ አያገኛትም ።

www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ መንግሥት ፡ እንሥራ ፤ እንድከም ። እነዚህን ፡ ኤንጎያ ልፒያት ፡ ሳቀርብ ፡ ሠሬ ፡ በምትሆን ፡ በታላቁ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ትንፋሽ ፡ ሥር ፡ የኖላዊነት ፡ ተግባራችሁ ፡ እንዲባረክና ፡ ሃይማኖት ፡ እንደ ፡ ጋለች ፡ ነጻነት ፡ እንደ ለመለመች ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያናችሁና ፡ በኢትዮጵያችሁ ፡ እንዲኖሩ ፤ ወደ ፡ እግዚአብ ሔር እመኛለሁ ።

ፍቅራችን ፤ አክብሮታችን ፤ ልባችን ፡ በሙሉ ፡ ኢትዮጵያንና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያ ንዋን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱዋንም ፡ ይመለከታሉ ።

ከጵጵስና ፡ ወደ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳትነት ፡ ከብፁዓን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ጳጳሳትም ።

## የሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ መመረጥ ።

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚገባትን ፡ መብት ፡ ለማግኘት ፡ ወደ ፡ ከፕት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፤ ደብዳቤዎቿንና ፡ መልክተኞቿን ፡ እየላ ከች ፡ በመጠየቋ ፡ የተደረገው ፡ ክርክር ፡ በሰላም ፡ መንገድ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፤ በ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሚያዝያ ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መምህራን ፡ ምርጫ ፡ ሲደረግ ፡ በተጻፈው ፡ ፕሮግራም ፡ በ፫ኛው ፡ ክፍል ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ለጊዜው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተጠባባቂ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መምህራን ፡ በእስ ክንድርያ ፡ ፓትርያርክ ፡ ቅብዓ ፡ ጵጵስና ፡ ይቀበላል ።

ደግሞ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳትም ፡ በበታቹ ፡ ጳጳሳትና ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶ ሳት ፡ ለመሾም ፡ መብት ፡ እንዲኖረው ፡ ተብሎ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ የቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ እስኪፈጸም ፡ ንግግሩ ፡ እንዲቀጥል ፡ ሆኖ ፡ መቈየቱ ፡ ሳይዘነጋ ፤ አሁን ፡ ለጊዜው ፡ የተመረጡት ፡ ጳጳሳት ፡ ከፓትርያርኩ ፡ ይቀበሉ ፡ በተባለው ፡ ስምምነት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ሹመት ፡ ጊዜ ውን ፡ ሲጠብቅ ፡ ቈየ ። አሁን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ቄር ሎስ ፡ ጥቅምት ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በማረፋቸው ፡ ኢትዮጵያዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በኀዘን ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ከቈየች ፡ በኋላ ፤ በስምምነቱ ፡ መሠ ረት ፡ በአቡነ ፡ ቄርሎስ ፡ ቦታ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ለመተካት ፡ ከ፭ቱ ፡ ጳጳሳት ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ እንዲሾም ፡ ምርጫ ፡ ይደረግ ፡ ዘንድ ፡ ተወሰነ ።

ይህንንም ፡ ታላቅ ፡ የሆነ ፡ የሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ መሾም ፡ ምርጫ ፡ የዘውድ ፡ አማካ ሮች ፤ ክቡራን ፡ ሚኒስትሮችና ፡ ምክትል ፡ ሚኒስትሮች ፡ የሕግ ፡ መምሪያ ፤ የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንቶችና ፡ አማካሪዎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ የሚገኙ ፡ አድባራትና ፡ ገዳማት ፡ አለቆች ፤ መምህራንና ፡ በከተማ ፡ ያሉት ፡ ሊቃውንት ፡ ተሰብስበው ፡ ታኅሣሥ ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ በሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ አዳራሽ ፡ ፈጸሙ ።

የአመራረጡም ፡ ሥራ ፡ በኮሚቴው ፡ ተዘጋጅቶ ፡ የተመራጮቹ ፡ ስም ፡ የተ ጻፈበትንና ፡ የሚመረጡትን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ የሚያመለክት ፡ ሠሌዳ ፡ ለመራጮቹ ፡ እየተሰጠ ፡ በተመራጩም ፡ ስም ፡ አኳያ ፡ መራጮቹ ፡ ምልክት ፡ እያደረጉ ፡ በተ ዘጋው ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ አገቡ ።



የምርጫ ፡ ተቀባዮቹ ፡ ከሚቴዎች ፡ ሁሉንም ፡ ተቀብለው ፡ ካጠቃለሉ ፡ በኋላ ፤ መራጮቹ ፡ ወደ ፡ የጉዳያቸው ፡ ሔዱ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፤ የምርጫው ፡ ምል ክት ፡ የተደረገባቸውን ፡ ጽሑፎች ፡ የምርጫው ፡ ከሚቴ ፡ ከተዘጋው ፡ ሣጥን ፡ አው ጥቶ ፡ በመረመረው ፡ ጊዜ ፤ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ዕጨጌ ፡ ወጳጳስ ፡ ዘኢትዮ ጵያ ፡ ከመቶ ፡ አምስት ፡ በዘጠና ፡ ስድስት ፡ ድምፅ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ እንዲሆኑ ፡ መመረጣቸው ፡ ተገለጠ ።

በዚህ ፡ ቀንም ፡ ከቀኑ ፡ በ፲ሰዓት ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ብፁዓን ፡ ጳጳሳትን ፡ አስከትለው ፡ ወደ ፡ ላይኛው ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሔዱና ፡ በግርማዊነ ታቸው ፡ ዙፋን ፡ ፊት ፡ ቁመው ፡ ልዑላን ፡ መሳፍንትና ፡ ክቡራን ፡ መኳንንት ፡ ባሉበት ፡ ስለ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስናው ፡ ሹመት ፡ የሚደረገውን ፡ ሥርዓት ፡ መሐላ ፡ ፈጸሙ ።

## የብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ቃለ ፡ ኪዳን ።

## ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሆይ ።

እኔ ፡ አባ ፡ ባስልዮስ ፡ ዛሬ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ተመርጬ ፡ ጃን ሆይ ፡ ሹመቱን ፡ ፈቅደውልኝ ፤ አሁን ፡ ወደግርማዊነትዎ ፡ ፊት ፡ ቀርቤ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ አገልጋይ ፡ መሆኔን ፡ ስገልጽ ፡ በፊትም ፡ የታ መንኩ ፡ አገልጋይ ፡ ነኝ ። ሃይማኖትና ፡ እውነትም ፡ ይመሰክሩልኛል ።

ከአባቶቻችን ፡ ከሐዋርያትና ፡ ከሠለስቱ ፡ ምዕት ፡ ሲያያዝ ፡ የመጣውን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሕግና ፡ ሥርዓት ፡ አክብሬ ፡ እጠብቃለሁ ።

መሠረቷ ፡ ከእስክንድርያ ፡ ከቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ መንበር ፡ በሆነ ፡ በኦርቶዶክሳ ዊት ፡ ተዋሕዶ ፡ ሃይማኖት ፡ ጸንቼ ፡ እኖራለሁ ። ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ለቀ ዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴና ፡ በሕግ ፡ ለታወቁ ፡ ለወራስያነ ፡ መንግሥትዎ ፡ ፍጹም ፡ ታዛዥ ሆኜ ፡ አገለግላለሁ ።

በኔም ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ ጳጳሳት ፤ ቀሳውስትና ፡ ዲያቆናት ፡ እንደ ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕግና ፡ ሥርዓት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ እን ዲጠብቁ ፤ ለግርማዊነትዎና ፡ በሕግ ፡ ለታወቁ ፡ ወራስያነ ፡ መንግሥትዎ ፡ ታማኞች ፡ ሆነው ፡ እንዲያገለግሉ ፡ አደርጋለሁ ። ታኅሣሥ ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ።

## አባ ፡ ባስልዮስ ፡ ዕጨጌ ፡ ወጳጳስ ።

እኛ ፡ ባለንበት ፡ በዚህ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገብተው ፡ ሲፈርሙ ፡ ተመልክተናል ፡ ያሉ ፡ ጳጳሳት ፦

| | |
|---|---|
| አባ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ | ጳጳስ ፡ ዘሐረር ፡ |
| አባ ፡ ያዕቆብ ፡ | ጳጳስ ፡ ዘለቀምት ፡ |
| አባ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ | ጳጳስ ፡ ዘይርጋ ፡ ዓለም ፡ ዓለም ፡ |
| አባ ፡ ይስሐቅ ፡ | ጳጳስ ፡ ዘሰሜን ፡ ኢትዮጵያ ። |

www.ethiopianorthodox.org

## የግርማዊነታቸው ፡ ቃል ።

በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የተደረገውን ፡ የሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ምርጫ፡ ተመልክተን ፤ ለቤተ ፡ ክርስቲያናችንና ፡ ለቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ፍጹም ፡ ታማኝ ፡ መሆንዎን ፡ እየገለጹ ፡ ያቀረቡትን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ተቀብለን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ እንዲሆኑ ፡ ፈቅደናል ።

ኦርቶዶክሳዊት ፡ የተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የምትስፋፋበትን ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ ሰብአ ምእመናን ፡ የሚበዙበትን ፡ መንፈሳዊ ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲረዳዎት ፡ ከልባችን ፡ እንመኝልዎታለን ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፤ ሥርዓተ ፡ ሢመቱን ፡ ለመፈጸም ፡ በማግሥቱ ፡ ጥር ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ካይሮ ፡ ለመሔድ ፡ የሚዘጋጁ ፡ ናቸውና ፡ ከግርማዊነታቸውና ፡ ከግርማዊት ፡ ስንብት ፡ በሚያደርጉበት ፡ ጊዜ ፤ የአሥር ፡ ሰዓት ፡ የቁርስ ፡ ግብዣ ፡ ለልዑላን ፡ መሳፍንትና ፡ ለብፁዓን ፡ ጳጳሳት ፤ ለክቡራን ፡ መኳንንት ፡ ተደረገና ፡ ስንብቱም ፡ ተፈጽሞ ፡ ወጡ ።

እንዲሁ ፡ ከላይ ፡ እንደተባለው ፤ ጥር ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ በ፤ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ የሊቀ ፡ ጵጵስናውን ፡ ሥርዓተ ፡ ሢመት ፡ ለመፈጸም፡ በአኤሮፕላን ፡ ወደ ፡ ካይሮ ፡ ሔዱ ።

### ብፁዕነታቸውን ፡ ተከትለው ፡ ካይሮ ፡ የሔዱ ።

ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ቴዎፍሎስ ።
ክቡር ፡ ብላታ ፡ መርሥዔ ፡ ኀዘን ፡ ወልደ ፡ ቂርቆስ ፡
አባ ፡ ገብረ ፡ ማርያምና ፡ አባ ፡ ወልደ ፡ ሐዋርያት ፡ ናቸው ።

### ብፁዕነታቸውን ፡ ለመሸኘት ፡ እስከ ፡ አኤሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ ድረስ ፡ የሔዱ ።

ልዑል ፡ መኰንን ፡ መስፍነ ፡ ሐረር ፡
ብፁዓን ፡ ጳጳሳት ፡ በሙሉ ፡
ክቡር ፡ ራስ ፡ አበበ ፡ አረጋዊ ፡
ክቡር ፡ ቢትወደድ ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፡ (አሁን ፡ እራስ)፡
ክቡር ፡ ራስ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡
ክቡር ፡ ብሬጋዲየር ፡ ጀኔራል ፡ ዐቢይ ፡ አበበ ፡
" ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ (አሁን ፡ ደጃዝማች) ፡
" አቶ ፡ መኰንን ፡ ሀብተ ፡ ወልድ ፡
" ቢትወደድ ፡ ነጋሽ ፡
" ልጅ ፡ አርአያ ፡ አበበ ፡
" ደጃዝማች ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡
" አቶ ፡ ዘውዴ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡
" ኰሎኔል ፡ ክፍሌ ፡ ዕርገቱ ፡



ክቡር ፡ ሌተና ፡ ኰሎኔል ፡ ተአምራት ፡
" ኰሎኔል ፡ ወሰን ፡ ኃይሉ ፡
ሌሎችም ፡ የመንግሥት ፡ ታላላቅ ፡ ሠራተኞች ፡ ናቸው ።

ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ማርቆስም ፡ ለሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ምርጫ ፡ ከኤርትራ ፡ ስለመጡ ፡ ብፁዕነታቸውን ፡ እስከ ፡ አኤሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ ሸኝተው ፡ ተመልሰዋል ።

ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ምርጫ ፡ ከየጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ የመጡ ፡ ካህናት ፡ ስም ፡ ከነሀገራቸው ፡ ከዚህ ፡ ይቀጥላል ።

አንደኛ ፡

### ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ።

፩ መልአከ ፡ ፀሐይ ፡ ዘለቀ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፤
፪ መምህር ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ብርሃነ ፡ መስቀል ፤
፫ መልአከ ፡ ገነት ፡ ሀብተ ፡ ወልድ ፤

ሁለተኛ ፡

### ከሸዋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፤

፩ ንቡረ ፡ እድ ፡ ገብረ ፡ ሚካኤል ፤
፪ አለቃ ፡ ልሳነ ፡ ወርቅ ፡ ወልደ ፡ ዳዊት ፤
፫ አለቃ ፡ መኩሪያ ፡ አብዬ ፡ ሆይ ፡ (አሁን ፡ ንቡረ ፡ እድ ፡)
፬ አፈ ፡ ንቡረ ፡ እድ ፡ ተክለ ፡ ማርያም ፤

ሦስተኛ ፡

### ከሐረር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፤

፩ መምህር ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተክሌ ፤
፪ ቄሰ ፡ ገበዝ ፡ ዓለሙ ፡ ጓንጉል ፤
፫ መምህር ፡ ወልደ ፡ ትንሣኤ ፡ ግዛው ፤

አራተኛ ፡

### ከአሩሲ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፤

፩ መምህር ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡
፪ አለቃ ፡ ተክለ ፡ ዮሐንስ ፤

አምስተኛ ፡

### ከሲዳሞ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፤

፩ አባ ፡ ኪዳነ ፡ ማርያም ፡ ፈረደ ፤
፪ አባ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የምሩ ፤

ስድስተኛ ፡

### ከከፋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፤

፩ አባ ፡ አረጋዊ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፤
፪ አለቃ ፡ መንግሥቱ ፡ ባይለየኝ ፤
፫ መምሬ ፡ መኰንን ፡ ወልደ ፡ አረጋዊ ፤

ሰባተኛ ፡

### ከኢሉባቦር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፤

፩ መምህር ፡ መንግሥቱ ፡ ጥሩነህ ፤
፪ አባ ፡ በላይ ፡ ድረሴ ፤
፫ መሪጌታ ፡ ደምሴ ፡ ጌታሁን ፤

www.ethiopianorthodox.org

ስምንተኛ ፡ **ከወለጋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፤**

፩ አባ ፡ ወልደ ፡ ሐና ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፤
፪ አባ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ ሐዲሱ ፤
፫ መምሬ ፡ ውሂብ ፡ ገብሩ ፤

ዘጠነኛ ፡ **ከጐጃም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፤**

፩ ሊቀ ፡ ጠበብት ፡ መንግሥቱ ፡ ወርቅነህ ፤
፪ መምህር ፡ ኃይለ ፡ ኢየሱስ ፡ ተሰማ ፤
፫ አለቃ ፡ ዓለማየሁ ፡ ጣመ ፤

ዐሥረኛ ፡ **ከወሎ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፤**

፩ መምህር ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሐጐስ ፤
፪ አለቃ ፡ ገብረ ፡ ዮሐንስ ፡ ገብረ ፡ ኪዳን ፤
፫ መምህር ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ ኃይለ ፡ ኢየሱስ ፤

ዐሥራ ፡ አንደኛ ፡ **ከበጌምድር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፤**

፩ መምህር ፡ ምሕረቱ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፤
፪ » » ዜና ፡ ገብርኤል ፤
፫ » » ማህሌ ፤

ዐሥራ ፡ ሁለተኛ ፡ **ከትግሬ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፤**

፩ ንቡረ ፡ እድ ፡ ተስፋ ፡ ሚካኤል ፤
፪ መምህር ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፤
፫ መሪጌታ ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስ ፤

ዐሥራ ፡ ሦስተኛ ፡ **ኤ ር ት ራ ፤**

፩ አባ ፡ ተወልደ ፡ ብርሃን ፤
፪ መምህር ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ ዘደብረ ፡ ድማህ ፤
፫ » » ተስፋ ፡ ማርያም ፡ ዘደብረ ፡ ቢዘን ፤
፬ መልአከ ፡ ሰላም ፡ ድሜጥሮስ ፤

---

**ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ስለ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ምርጫ ፡ ለብፁዕ ፓትርያርክ ፡ አቡነ ፡ ዮሳብ ፡ የጻፉት ፡ ቃል ።**

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሥዩመ ፡
እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።
ለብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ዮሳብ ፡ ፪ኛ ፤

ቅዱስ ፡ ቡራኬዎ ፡ ይድረሰን ፡ ዘንድ ፡ እየለመንን ፡ ሰላምታችንን ፡ እናቀርባለን ። የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ሥርዓተ ፡ ቅብዓት ፡ ጥር ፡ ፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፩ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ካይሮ ፡ ላይ ፡ እንዲፈጸም ፡ የብፁዕነትዎ ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ መሆኑን ፡ የካይሮ ፡ ሚኒስትራችን ፡ ስላስታወቀን ፤ በቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ብፁዕ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ሆነው ፡ የተመረጡበትን ፡ ተመልክተን ፡ እኛም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ እንዲሆኑ ፡ ሹመታቸውን ፡ ፈቅደናል ። ስለዚህም ፡ ሥርዓተ ፡ ቅብዓቱ ፡ እንዲፈጸምላቸው ፡ ልከናቸዋል ።

ሁለቱን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ በፍቅር ፡ አስተሣሥሮ ፡ ለማኖር ፡ ሁላችንም ፡ የደከምንበት ፡ ጉዳይ ፡ በዘመነ ፡ መንግሥታችንና ፡ ብፁዕነትዎ ፡ በመንበረ ፡ ማርቆስ ፡ በተቀመጡበት ፡ ዘመን ፡ ፍጻሜ ፡ በማግኘቱ ፡ ይህን ፡ ዕድል ፡ ለፈቀደልን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ እያቀረብን ፡ የተሰማንን ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ለብፁዕነትዎ ፡ እንገልጻለን ።

ለብፁዕነትዎ ፡ ረጅም ፡ ዕድሜ ፡ መልካም ፡ ጤና ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲሰጥ ፡ ከልባችን ፡ እንመኛለን ።

ታኅሣሥ ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ሺ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ሦስት ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ። በነገሥን ፡ በሐያኛው ፡ ዓመት ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ተጻፈ ።

ቀ. ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ን ፡ ነ ፡ ዘኢ ፤

**የብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ወደ ፡ ካይሮ ፡ መሔድ ።**

ጥር ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ በ፺ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ የሊቀ ፡ ጵጵስናውን ፡ ሥርዓተ ፡ ሢመት ፡ ለመፈጸም ፡ በአኤሮፕላን ፡ ወደ ፡ ካይሮ ፡ ሔዱ ። ብፁዕነታቸውን ፡ ተከትለው ፡ የሔዱ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ቴዎፍሎስና ፡ ክቡር ፡ ብላታ ፡ መርስዔ ኀዘን ፡ ወልደ ፡ ቂርቆስ ፡ ናቸው ።

ለኢትዮጵያዊ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ የተደረገ ፤

**የመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ ሥርዓተ ፡ ቅብዕ ።**

የክርስትናን ፡ ሥርዓት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ከገለጠው ፡ ከቅዱስ ፡ ፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ (ከአባ ፡ ሰላማ) ፡ አንሥቶ ፡ በዘመናችን ፡ እስከ ፡ ነበሩት ፡ አቡነ ፡ ቄርሎስ ፡ ድረስ ፡ በየጊዜው ፡ የተሾሙት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ በቍጥር ፡ ፻፲ ፡ ናቸው ።

የታሪክ ፡ መፍለቂያ ፡ የሆነው ፡ የግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ለኢትዮጵያዊ ፡ ስላደረገው ፤ ፻፲፩ኛው ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ ለብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ሆነ ። መጀመሪያው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ መንፈሳዊውን ፡ ቅብዓት ፡ ለማድረስ ፡ ከተከታዮቻቸው ፡ ከአቡነ ፡ ቴዎፍሎስና ፡ ከብላታ ፡ መርስዔ ፡ ኀዘን ፡ ወልደ ፡ ቂርቆስ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ካይሮ ፡ መሔዳቸው ፡ ባለፈው ፡ ጊዜ ፡ በጋዜጦች ፡ ተነግረዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

አሁንም ፡ ስለ ፡ ቅብዓቱ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የደረሰንን ፡ ወሬ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ገልጠነዋል ። በካይሮ ፡ ላይ ፡ የነበረ ፡ የአክብሮት ፡ አቀባበልና ፡ የብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ከእስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባለ ፡ ሥልጣኖች ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ ማድረግ ።

ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስና ፡ ተከታዮቻቸው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የአየር ፡ መንገድ ፡ ተጕዘው ፡ ጥር ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ረቡዕ ፡ ካይሮ ፡ ሲደርሱ ፡ ክቡር ፡ ፊታውራሪ ፡ ታፈሰ ፡ የፓትሪያርኩ ፡ መልክተኞችና ፡ ሌሎች ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በአይሮፕላን ፡ ማረፊያው ፡ ላይ ፡ ተቀበሏቸው ።

ወደበትረ ፡ ካናውም ፡ ሲደርሱ ፡ ደወሎች ፡ በረጅም ፡ ድምፅ ፡ ያክብሮት ፡ ሰላምታቸውን ፡ ሰጡ ። ፳፬ ፡ ዲያቆናት ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖ ፡ ለብሰው ፡ በቀኝና ፡ በግራ ፡ ተሰልፈው ፡ ይጠባበቁ ፡ ነበርና ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ በዲያቆናቱ ፡ ታጅበው ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገብተው ፡ እጅ ፡ ነሡ ።

ቀጥሎም ፡ ፓትሪያርኩ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ዮሳብ ፡ ወዳሉበት ፡ ገብተው ፡ ሰላምታ ፡ አቀረቡ ። ከዚያም ፡ በኋላ ፤ የሀገሩን ፡ ፕሮቶኮል ፡ ለመጠበቅ ፡ በአብዲን ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ በእንግዶች ፡ መፈረሚያ ፡ መዝገብ ፡ ስማቸውን ፡ ከጻፉ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ በትረካናው ፡ ተመልሰው ፡ ፓትሪያርኩ ፡ ባዘጋጁላቸው ፡ ማረፊያ ፡ ተቀመጡ ።

## ሢመተ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስናው ።

ጥር ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የሢመተ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስናው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በማርቆስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደሚፈጸም ፡ በጋዜጦች ፡ ከመነገሩ ፡ በላይ ፡ ብፁዕ ፡ ፓትሪያርክ ፡ በተለይ ፡ ለብዙዎች ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ጥሪ ፡ አድርገው ፡ ነበር ።

ከጧቱ ፡ በ፪ ፡ ሰዓት ፡ በትረካናው ፡ በሕዝብ ፡ ተመላ ። ክቡራን ፡ ሚንስትሮችና ፡ ፓሻዎች ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ጳጳሳትና ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ የበዓሉ ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ መጥተው ፡ ነበር ።

እንዲሁም ፡ የኢትዮጵያና ፡ የኤርትሪያ ፡ እንግድነት ፡ ማኅበር ፡ ዋና ፡ ጸሐፊ ፡ አቶ ፡ ተድላ ፡ ባይሩ ፡ ኬሌክ ፡ ሴክሴስ ፡ ሲመለሱ ፡ ዕለቱ ፡ አጋጥሟቸው ፡ በዓሉን ፡ ለማክበር ፡ በመካከላችን ፡ ነበሩና ፡ ይህ ፡ ዓመት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ያስገኛቸውን ፡ ዕድሎች ፡ በመጫወት ፡ ጊዜውን ፡ በደስታ ፡ አሳለፍነው ።

በ፬ ፡ ሰዓት ፡ ተሩብ ፡ ብፁዕ ፡ ፓትሪያርክ ፡ ገባሬ ፡ ሠናይ ፡ ቀዳሽ ፡ ሆነው ፡ ከ፮ ፡ ሜጥሮጶሊሶችና ፡ ከ፴ ፡ ጳጳሳት ፡ ጋር ፡ ሥርዓተ ፡ ቅዳሴ ፡ ጀመሩ ፡ ከጸሎተ ፡ ወንጌል ፡ ላይ ፡ ሲደርሱ ፡ መጽሐፈ ፡ ሢመቱን ፡ እያነበቡ ፡ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ ሥርዓተ ፡ ሢመቱን ፡ ሲፈጽሙ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ በመንበሩ ፡ ፊት ፡ በወንበር ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ፡ ፓትሪያሪኩ ፡ በረጅም ፡ ድምፅ ፡



‹ባስልዮስ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ነው ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በረከት ፡ ይደርበት» ፡ እያሉና ፡ በመስቀል ፡ እየባረኩ ፡ ፫ ፡ ጊዜ ፡ በዜማዊ ፡ አነጋገር ፡ ለሕዝቡ ፡ አሰሙ ።



ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ዮሳብ ፡ ዳግማይ ፡ የእስክንድርያ ፡ ፓትሪያርክ ።

በቅብዓቱ ፡ ጊዜም ፡ የጸሎቱ ፡ ተካፋይ ፡ የነበሩት ፡ ሜጥሮጶሊሶችና ፡ ጳጳሳት ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ። አቡነ ፡ አትናቴዎስ ፡ የቤኒሱዊፍ ፡ ሜጥሮጶሊስ ፡ አቡነ ፡ ቶማስ ፡ የገርቢያ ፡ ሜጥሮጶሊስ ፡ አቡነ ፡ ሚካኤል ፡ የአስዩጥ ፡ ሜጥሮጶሊስ ፡ አቡነ ፡ ባኩሚዮስ ፡ የአምዱርሀማን ፡ ሜጥሮጶሊስ ፡ አቡነ ፡ ዮሐንስ ፡ የጊዛ ፡ ሜጥሮጶሊስ ፡ አቡነ ፡ ዮሐንስ ፡ የካርቱም ፡ ሜጥሮጶሊስ ፡ አቡነ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ የሐረር ፡ ጳጳስ ፡ አቡነ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ የዴር ፡ ሱርያን ፡ ጳጳስ ፡ አቡነ ፡ አርሳንዮስ ፡ የዴር ፡ በሎስ ፡ ጳጳስ ፡ አቡነ ፡ ባኩሚዮስ ፡ የዴር ፡ መሐረክ ፡ (ቍስቋም) ፡ ጳጳስ ።

በ፬ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ሥርዓተ ፡ ቅዳሴው ፤ ተፈጽሞ ፡ ሠርሖተ ፡ ሕዝብ ፡ ሆነ ። በዚሁም ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ ብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ የቅዱስ ፡ ማርቆስን ፡ መካነ ፡ መቃብር ፡ ለመሳለም ፡ ከተከታዮቻቸው ፡ ጋር ፡ በባቡር ፡ ተሳፍረው ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ ወረዱ ።

www.ethiopianorthodox.org

## በእስክንድርያ ፤ የተደረገ ፤ አቀባበል ።

ከካይሮ ፡ እስከ ፡ እስክንድርያ ፡ ርኅቀቱ ፡ ፪፻፳ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ነው ። ይህንኑም ፡ ጕዞ ፡ በ፫ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ውስጥ ፡ ፈጽመው ፡ እስክንድርያ ፡ ሲደርሱ ፤ ከሁለት ፡ ሺህ ፡ የማያንሱ ፡ የኮፕት ፡ ኦርቶዶክሳውያኖች ፡ ።ባቡሩ ፡ ጣቢያ ፡ ይጠባበቁዋቸው ፡ ኖሮ ፡ ጣቢያውን ፡ በጭብጨባ ፡ አደመቁት ። ከባቡሩም ፡ ሲወርዱ ፡ የብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስን ፡ መስቀል ፡ ለመሳለምና ፡ የልብሳቸውን ፡ ዘርፍ ፡ በመዳሰስ ፡ በረከት ፡ ለማግኘት ፡ ሕዝቡ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ሲጋፋ ፡ የደስታ ፡ ሁካታ ፡



ብፁዕ ፡ ፓትርያርኩ ፡ብብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ላይ ፡ የቅብዓቱን ፡ ሥርዓት ፡ ፈጽመው ፡ ቃለ ፡ ቡራኬ ፡ ሲያደርሱ።

ጣቢያውን ፡ ሞላው ። ከዚያም ፡ አልፈው ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሲደርሱ ፡ የገዳሙ ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ አቡነ ፡ መንሱር ፡ ዲያቆናቱን ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖ ፡ አልብሰው ፡ «አግዮስ ፡ ኬርዮስ» ፡ እያሰኙ ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ ተቀብለዋቸው ፡ በዚያው ፡ አደሩ ።

ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ በእስክንድርያ ፡ በቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ መቅደስ ፡ ኢትዮጵያዊውን ፡ ቅዳሴ ፡ ሊመቀደስ ፡ አስበው ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ በዘመናዊ ፡ አሠራር ፡ እንዲሠራ ፡ ታስቦ ፡ ጣሪያውም ፡ ግድግዳውም ፡ ፈርሶ ፡ እንደገና ፡ በመታነጽ ፡ ላይ ፡ ነበርና ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ስላልተቻለ ፤ በዚያው ፡ አጠገብ ፡ በምትገኝ ፡ በመሐረም ፡ ቤይ ፡ ቅድስት ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጥር ፡ ፺ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ፡ ም፡ ሰኞ ፡ ጧት ፡ ቅዳሴ ፡ አደረጉ ።



ቅዳሴውን ፡ ለመስማትና ፡ ቡራኬያቸውን ፡ ለመቀበል ፡ የተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ ነበር ። እንደ ፡ አጋጣሚ ፡ ሰባት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ መነኰሳት ፡ ከየገዳማቱ ፡ ተሰብስበው ፡ በዚያ ፡ ስለተገኙ ፡ ቅዳሰው ፡ በሚገባ ፡ ደምቆ ፡ ተሰምቷል ።



በቅዳሴ ፡ ጊዜ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ከጳጳሳት ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ ይታያሉ ።

ከቅዳሴ ፡ በኋላ ፡ አቡነ ፡ መንሱር ፡ ዑደት ፡ አድርጉልን ፡ ብለው ፡ ስለለመኑ ፤ ፫ ፡ ጊዜ ፡ ዑደት ፡ ተደረገ ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ፎቶግራፍ ፡ አንሺዎች ፡ ሰፎቶግራፍ ፡ ይሽቀዳደሙ ፡ ነበር ። ሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ለቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕንጻ ፡ ስለ ፡ እርዳታ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ፓውንድ ፡ ሰጥተው ፡ በ፺ ፡ ሰዓት ፡ ከተከታዮቻቸው ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ካይሮ ፡ ተመለሱ ።

## ስለ ፡ በዓሉ ፡ ክብር ፡ የተደረጉ ፡ ግብዣዎች ።

ስለ ፡ መጀመሪያው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ክብር ፡ እየተባለ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥፍራ ፡ ግብዣ ፡ ተደረገ ።

www.ethiopianorthodox.org

(ሀ) ጥር ፡ ፺ ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓመተ ፡ ም፡ሰኞ ፡ በ፲ ፡ ሰዓት ፡ ብፁዕ ፡ ፓትረያርክ ፡ ከ፱፻ ፡ የሚበልጡ ፡ መኳንንት ፡ ጠርተው ፡ በበትረካናው ፡ የሻይ ፡ ግብዣ ፡ አደረጉ ።

በዚህ ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ጳጳሳትና ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ነበሩ ።



ፓትረያርኩ ፡ ጸሎተ ፡ ንስሓ ፡ ሲጸልዩ ፡ ጳጳሳቱ ፡ አስተብርከዋል ።

(ለ) ከኢትዮጵያ ፡ ወዳጆች ፡ አንዱ ፡ ክቡር ፡ አዚዝ ፡ ቤይ ፡ ሚሸሬቂ ፡ ደስታቸውን ፡ ለመግለጽ ፡ በዚሁ ፡ ዕለት ፡ ማታ ፡ ፻ ፡ ያህል ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎችን ፡ ጠርተው ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ አደረጉ ።

ክቡራን ፡ ሚኒስትሮችና ፡ ፓሻዎች ፡ ጳጳሳት ፡ ሜጥሮጶሊሶች ፡ በግብዣው ፡ ላይ ፡ ነበሩ ። የጊዛ ፡ ሜጥሮጶሊስ ፡ አቡነ ፡ ዮሐንስ ፡ ኢትዮጵያዊውን ፡ ቅዳሴ ፡ በጥር ፡ ፺ ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ በግራማፎን ፡ አንሥተውት ፡ ኖሮ ፡ በግብዣው ፡ ሰዓት ፡ ዜማውን ፡ እያሰሙ ፡ መኳንንቱን ፡ ደስ ፡ አሰኙዋቸው ።

(ሐ) ጥር ፡ ፳ ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ማክሰኞ ፡ የአንግሊካን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቢሾፕ ፡ አሌን ፡ ለብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስና ፡ ለተከታዮቻቸው ፡ ለሌሎችም ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ የምሳ ፡ ግብዣ ፡ አደረጉ ።

(መ) በዚሁ ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ ክቡር ፡ ፊታውራሪ ፡ ታፈሰ ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤል ፡ ለ፩፻ ፡ ሰዎች ፡ ጥሪ ፡ አድርገው ፡ በኢትዮጵያ ፡ አምባሳድ ፡ ታላቅ ፡ ግብዣ ፡ አደረጉ ።



በዚህ ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ መሳፍንትና ፡ ሚኒስትሮች ፡ የውጪ ፡ አገር ፡ መንግሥታት ፡ አምባሳደሮችና ፡ ሚኒስትሮች ፡ እንዲሁም ፡ ሜጥሮጶሊሶችና ፡ ጳጳሳት ፡ ነበሩ ።



በኢትዮጵያ አምባሳድ የፓኪስታን አምባሳደርና ሌሎችም ታላላቅ መኳንንቶች ከብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ጋራ ይነጋገራሉ ።

አምባሳደሮች ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ በየተራ ፡ እየቀረቡ ፡ መልካም ፡ ምኞታቸውን ፡ በመግለጽ ፡ አነጋገሩዋቸው ። ይልቁንም ፡ የፓኪስታን ፡ አምባሳደር ፡ ሐጂ ፡ አብዱልሰተር ፡ ሳይት ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የኮር ፡ ዲፕሎማቲክ ፡ ተቀዳሚ ፡ ስለሆኑ ፤ ደስ ፡ በሚያሰኝ ፡ አኳኋን ፡ ከነጋገሩዋቸው ፡ በኋላ ፡ ፓኪስታንን ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ እንዲጎበኙ ፡ እመኛለሁ ፡ ሲሉ ፡ አሳባቸውን ፡ ገለጡ ።

የሊግ ፡ ዐረብ ፡ ጀኔራል ፡ ሴክሬታሪ ፡ አዛም ፡ ፓሻ ፡ ደግሞ ፡ እንደዚሁ ፡ ልባዊ ፡ ንግግር ፡ አደረጉላቸው ።


(ሠ) የጤና ፡ ጥበቃ ፡ ሚኒስትር ፡ የነበሩት ፡ ክቡር ፡ ነጊብ ፡ እስካንዳር ፡ ፓሻ ፡ ስለ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ክብር ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ጠርተው ፡ በዚያው ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ አደረጉ ።

እንዲሁም ፡ ግብዣ ፡ ለማድረግ ፡ እየፈቀዱ ፡ ክቡር ፡ ፊታውራሪ ፡ ታፈሰን ፡ የጠየቁ ፡ ብዙ ፡ ወዳጆች ፡ ነበሩ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ተከታዮቹ ፡ ቀኖች ፡ ጾመ ፡ ረቡዕና ፡ ጾመ ፡ ገሃድ ፡ ዘጥምቀት ፡ መሆናቸውን ፡ እየገለጡ ፡ ስለነገሩዋቸውና ፡ አለመቻሉን ፡ ስላስረዷቸው ፤ ዕድል ፡ ሳያገኙ ፡ በመቅረታቸው ፡ እያዘኑ ፡ ተመለሱ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ኢኖ ፡ ሊትማን ።

ኢኖ ፡ ሊትማን ፡ የግእዝና ፡ የአማርኛ ፡ የትግርኛ ፡ ሊቅ ፡ በመባል ፡ የታወቁት ፡ ጀርመናዊ ፡ ፕሮፌሶር ፡ ናቸው ። በዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጥተው ፡ የአክሱምን ፡ አንቲካ ፡ ስለመረመሩና ፡ ይህንኑ ፡ ስያሜ ፡ የያዘ ፡ የታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ስለጻፉ ፤ ከዚህም ፡ በቀር ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያና ፡ ስለ ፡ ምሥራቃውያን ፡ ሥነ ፡ ትምህርት ፡ ብዙ ፡ ምርመራ ፡ ያደረጉና ፡ የጻፉ ፡ በመሆናቸው ፡ የተመሰገኑ ፡ ናቸው ። ባለፈው ፡ ወር ፡ ወደ ፡ ካይሮ ፡ መጥተው ፡ ሰንብተው ፡ ኖሮ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያዊው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ የተደረገውን ፡ ሥነ ፡ በዓል ፡ ለማየት ፡ ጊዜው ፡ አጋጠማቸው ።



በኢትዮጵያ ፡ አምባሳደር ፡ ከተሰበሰቡት ፡ መኳንንት ፡ አንዳንዶቹ ፡ በዚህ ፡ ሥዕል ፡ ይታያሉ ።


እንዲሁም ፡ በኢትዮጵያ ፡ አምባሳድ ፡ ለግብዣ ፡ ከተጠሩት ፡ ታላላቆች ፡ አንደኛው ፡ እሳቸው ፡ ስለሆኑ ፤ በዚያ ፡ በግብዣ ፡ ሰዓት ፡ ከአቡነ ፡ ቴዎፍሎስና ፡ ከብላታ ፡ መርስዔ ፡ ኀዘን ፡ ጋራ ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ ሲጨዋወቱ ፡ አመሹ ።

ሽማግሌው ፡ ፕሮፌሰር ፡ ዛሬ ፡ የ፸፫ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ናቸው ። የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ ለመመርመር ፡ የጀመሩት ፡ ግን ፡ የ፲፯ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ሳሉ ፡ ጀምሮ ፡ መሆኑን ፡ ለብላታ ፡ መርስዔ ፡ ኀዘን ፡ ያጫውቷቸው ፡ ነበር ። አሁንም ፡ ዕድል ፡ ቢያጋጥማቸው ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለማየት ፡ ከመመኘት ፡ አላቋረጡም ።



## የኒሻን ፡ ሽልማት ።

የኢትዮጵያና ፡ የግብጽ ፡ ወዳጅነት ፡ እየሰፋ ፡ ከመሔዱ ፡ የተነሣ ፡ ከሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ የወዳጅነት ፡ መግለጫ ፡ የሚሆን ፡ የኒሻን ፡ መቀባበል ፡ ከተጀመረ ፡ ቆይቷል ።



ፕሮፌሶር ፡ ሊትማንና ፡ ብላታ ፡ መርስዔ ፡ ኀዘን ፡ በግዕዝ ፡ ሲጨዋወቱ ።

አሁንም ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በአምባሳደራቸው ፡ በኩል ፡ ኒሻን ፡ ልከው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ወዳጆች ፡ ስለሸለሙ ፤ ዝርዝራቸውን ፡ እንገልጻለን ። ሌላውንም ፡ ከመጻፍ ፡ አስቀድሞ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ፋሩክ ፡ ታላቁን ፡ ማኅተመ ፡ ሰሎሞን ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ እንደተሸለሙ ፡ ለአንባቢዎች ፡ መግለጽ ፡ የተገባ ፡ ነው ። ቀጥሎም ፡ አልጋ ፡ ወራሹ ፡ ልዑል ፡ መሐመድ ፡ አሊ ፡ ጥር ፡ ፯ ፤ ፲፱፻፵፫ ፡ የሰሎሞንን ፡ ኮርዶን ፡ ስለተሸለሙ ፤ የሁለቱ ፡ አገሮች ፡ ወዳጅነት ፡ የተስፋፋ ፡ መሆኑን ፤ የግብጽ ፡ ጋዜጦች ፡ በሰፊው ፡ ጽፈውታል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፤ ብፁዕ ፤ አቡነ ፡ ዮሳብ ፡ ፪ኛ ፤ ጥር ፡ ፳ ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ም ፡ የሰሎሞንን ፡ ኮርዶን ፡ ተሸለሙ ። ዳግመኛ ፡ በጥር ፡ ፳፭ና ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ለተጻፉት ፡ ለቤተ ፡ ክህነትና ፡ ለቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሰዎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ አምባሳደር ፡ በዓል ፡ ተደርጎ ፡ የኒሻን ፡ ሽልማት ፡ ተሰጠ ።

አቡነ ፡ አትናቴዎስ ፡ የቤኒሱዌፍ ፡ ሜጥሮጶሊስ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ኮርዶን ፡ አቡነ ፡ ቄርሎስ ፡ የኪና ፡ ሜጥሮጶሊስ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ኮርዶን ፤ አቡነ ፡ ዮሐንስ ፡ የጊዛ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሜጥሮጶሊስ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ኮማንደር ፡ ከነፕላኩ ፤ አቡነ ፡ ባኩሚዮስ ፡ የዴር ፡ መሐረክ ፡ ጳጳስ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ኮማንደር ፤ አቡነ ፡ ቴዎፋሎስ ፡ የዴር ፡ ሐርያን ፡ ጳጳስ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ኮማንደር ፤ አቡነ ፡ መንሱር ፡ የእስክንድርያ ፡ ዴር ፡ ማርቆስ ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ኮከብ ፡ አምበል ፡ የሌለው ፤ ዶክቶር ፡ ካሚል ፡ ረዝል ፡ የፓትሪያርኩ ፡ ሐኪም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ኮከብ ፤ አምበል ፡ የሌለው ።



በኢትዮጵያ ፡ አምባሳደር ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ከታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ይታያሉ ።

ክቡር ፡ አብደል ፡ ሐዲ ፡ ፓሻ ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስቴር ፡ የነበሩት ፡ የምኒልክን ፡ ኰርዶን ፤ ክቡር ፡ ከሽባ ፡ ፓሻ ፡ የውጪ ፡ ጕዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ የነበሩ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ኮርዶን ፤ ክቡር ፡ ነጊብ ፡ እስካንዳር ፡ ፓሻ ፡ የጤና ፡ ጥበቃ ፡ ሚኒስቴር ፡ የነበሩ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ኮርዶን ፤ ክቡር ፡ ሳባ ፡ ሐበሺ ፡ ፓሻ ፡ የንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ የነበሩ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ኮርዶን ፤ ክቡር ፡ ሐሱና ፡ ፓሻ ፡ የውጪ ፡ ጕዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ የነበሩ ፡ የምኒልክን ፡ ኮማንደር ፡ ከነፕላኩ ፤ ክቡር ፡ ከረም ፡ ሳቤት ፡ ፓሻ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ኮማንዶር ፡ ከነፕላኩ ፤ ክቡር ፡ ፉዓድ ፡ ጊርጊስ ፡ ፓሻ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ኮማንደር ፡ ከነፕላኩ ፤ ክቡር ፡ አዚዝ ፡ ቤ ፡ ምሽሪቂ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ኮማንደር ፤ ክቡር ፡ ራግብ ፡ ቤይ ፡ እስካንዳር ፡ የኢትዮጵያን ፡ ኮማንደር ፡ ክቡር ፡ እስካንዳር ፡ አሳብጊ ፡ ፓሻ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ኮማንደር ፤ ዶክተር ፡ ሙራድ ፡ ካሚል ፡ የኢትዮጵያን ፡ ኮማንደር ፡ ተሸልመዋል ።

## ሄልዮፓሊስ ።

ሄልዮፓሊስ ፤ በስተምሥራቅ ፡ በኩል ፡ የሚገኘው ፡ ዘመናዊው ፡ የካይሮ ፡ ከተማ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ሥፍራ ፡ የሻቹ ፡ የቆሞስ ፡ ኢብራሂም ፡ ሉቃስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይገኛል ። «የሚቹ ፡ ልጆች ፡ "ላባታችን ፡ ጸሎተ ፡ ፍትሐትና ፡ ጸሎተ ፡ ቅዳሴ ፡ ያድርጉልን ፡ ብለው ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስን ፡ ስለለመኑዋቸው ፤ ጥር ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ም ፡ ሐሙስ ፡ በዚያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጸሎተ ፡ ቅዳሴ ፡ አደረጉ ።



## እርዳታ ።

ፓትሪያርኩ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ዮሳብ ፤ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ፕሮግሬስ ፡ የሚወዱ ፡ ናቸው ። ስለዚህም ፡ ለቤተ ፡ መጻሕፍትና ፡ ለጳጳሳት ፡ ማረፊያ ፡ የሚሆን ፡ ባለአራት ፡ ደርብ ፡ የሆነ ፡ ትልቅ ፡ ቤት ፡ አሁን ፡ በቅርቡ ፡ ጊዜ ፡ በበትረ ፡ ካናው ፡ አሠርተዋል ።

ይህንንም ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፤ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ስለሰሙ ፤ ስለ ፡ እርዳታ ፡ ፪፻ ፡ ወቄት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወርቅ ፡ ልከውላቸው ፡ ነበርና ፡ ጥር ፡ ፱ ቀን ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ም ፡ በጸሎትና ፡ በቡራኬ ፡ ተቀብለውታል ።

እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ ገዳማትና ፡ ለችግረኞች ፡ ስለ እርዳታ ፡ ከሰጡት ፡ ፪፻፶ ፡ ፓውንድ ፡ በላይ ፡ ለበትረካናው ፡ ፪፻ ፡ ፓውንድ ፤ ለቤተ ፡ ክህነት ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ (መሐመሽ) ፡ ፲ ፡ ፓውንድ ፤ ለበትረካናው ፡ ገዳም ፡ ለዲያቆናቱና ፡ ለመዘምራኑ ፤ ለአርድእቱም ፡ ፶፯ ፡ ፓውንድ ፤ ለሄሊዮፓሊስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ፲ ፡ ፓውንድ ፡ ስለሰጡ ፡ ተመልካቹን ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ አሰኙት ።

## ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መመለስ ።

ጥር ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ዐርብ ፡ ከጧቱ ፡ በ፬ ፡ ሰዓት ፡ ኮንቤር ፡ በሚባለው ፡ ባዲሱ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዓየር ፡ ባቡር ፡ ተሣፍረዋል ፤ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ክቡር ፡ ፊታውራሪ ፡ ታፈሰ ፤ ጳጳሳትና ፡ ሌሎችም ፡ ወዳጆች ፡ እስከ ፡ አይሮፕላን ፡ ሜዳ ፡ ወጥተው ፡ ሸኝተዋቸዋል ።

በካይሮ ፡ ሥፍረ ፡ ሰዓት ፡ ፳፤ ሰዓት ፡ ሲሆን ፤ አሥመራ ፡ ደርሰዋል ። በአይሮፕላን ፡ ጣቢያ ፡ ክቡር ፡ ኰሎኔል ፡ ነጋ ፤ አቡነ ፡ ቄርሎስና ፡ ብዙ ፡ መኳንንት ፤ እንዲሁም ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ወንዱ ፡ ሴቱ ፡ ተሰብስቦ ፡ ይጠባበቁ ፡ ኖሮ ፡ ብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ከአይሮፕላን ፡ ሲወርዱ ፡ ጭብጨባና ፡ እልልታ ፡ ሆነ ።

የተባለው ፡ ግሥም ፡ "ወብዙኃን ፡ ኖሎት ፡ መጽኡ ፡ ወስዕኑ ፡ ከሚቶታ ፡ ለመንበረ ፡ ማርቆስ ፡ እስከ ፡ ይመጽእ ፡ ዐቢይ ፡ ኖላዊ ፡ ባስልዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ከሠተ ፡ ወአጥመቀ ፡ ብዙኃነ ፡ በውስቴታ» ፡ የሚል ፡ ነው ። የተሰናዳውን ፡ ድርሰት ፡ ለመፈጸም ፡ በቂ ፡ ጊዜ ፡ ባለመገኘቱ ፡ ቀረ ፡ እንጂ ፡ ካህናቱ ፡ ምስባክና ፡ ወንጌል ፡ እስመ ፡ ለዓለም ፡ አዘጋጅተው ፡ ነበር ።

የቅድስት ፡ ማርያም ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ወጣቶች ፡ ወንዶቹም ፡ ሴቶቹም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ይዘው ፡ ተሰልፈው ፡ መዝሙር ፡ እየዘመሩ ፡ ተቀበሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

«አብያተ ፡ ትምህርት ፡ ዘአግዐዝያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ መምህራን»፡የሚል ፡ ቃል ፡ የተጻፈበትን ፡ የተማሪ ፡ ቤቱን ፡ አርማ ፡ ይዘው ፡ ነበር ።

በተማሪዎቹ ፡ መካከል ፡ ፀሐይ ፡ አብርሃም ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡ ወጣት ፡ ወደብፁዕነታቸው ፡ ፊት ፡ ቀርቦ ፡ ስለብፁዕነታቸው ፡ ክብር ፡ በተማሪ ፡ ቤቱ ፡ የተሰናዳውን ፡ ዲስኩር ፡ አቀላጥፎ ፡ ሲናገር ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አሰኘ ።

እንዲሁም ፡ በሴቶች ፡ ተማሪዎች ፡ መካከል ፡ ርብቃ ፡ ኢያሱ ፤ ሰንበቱ ፡ ገብረ ፡ ኪዳን ፤ ገነት ፡ ግደይ ፡ የተባሉ ፡ ፫ት ፡ ቈንጃጅት ፡ ወጣቶች ፡ በዓውደ ፡ ብርት ፡ የተዘጋጀ ፡ አበባ ፡ ይዘው ፡ ቀርበው ፡ ለብፁዕነታቸው ፡ አበረከቱ ።

ሕዝቡ ፡ የደስታውን ፡ ስሜት ፡ ለመግለጽና ፡ ገና ፡ በመቀዳደም ፡ ሳለ ፤ የተወሰነው ፡ የዕረፍቱ ፡ ጊዜ ፡ አጭር ፡ ስለሆነ ፤ የምኞቱን ፡ ያህል ፡ ለመፈጸም ፡ ጊዜው ፡ ሳይፈቅድ ፡ ቀረ ። እኩል ፡ ሰዓት ፡ ከቈዩ ፡ በኋላም ፤ ብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ሕዝቡን ፡ በመስቀል ፡ ባርከው ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ሰጥተው ፡ አሳረጉ ። ከዚያም ፡ በኋላ ፤ ከአሥመራ ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ጕዞአቸውን ፡ ቀጠሉ ። በዐድዋና ፡ በአክሱም ፡ መካከል ፡ አልፈውም ፡ የደጀንን ፡ ተራራ ፡ በስተቀኝ ፡ እያዩ ፡ ተጕዘው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በ፲፩ ፡ ሰዓት ፡ ከ፵፭ ፡ ደቂቃ ፡ ገቡ ።

## የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ለመቀበል ፤ የተነገረ ፡ የበዓሉ ፡ ፕሮግራም ።

፩ኛ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ጥር ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ከእኩለ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ በ፲ ፡ ሰዓት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያየር ፡ መንገድ ፡ ኤሮፕላን ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ገብተዋል ።

፪ኛ ፤ ልዑል ፡ መኰንን ፡ መስፍነ ፡ ሐረር ፡ በግርማዊነታቸው ፡ ስም ፡ አኤሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ ድረስ ፡ ሔደው ፡ ተቀብለዋቸዋል ። እንዲሁም ፡ ብፁዓን ፡ ጳጳሳት ፡ ክቡራን ፡ ሚኒስትሮች ፤ የመንግሥት ፡ የሲቪልና ፡ የወታደር ፡ ክፍል ፡ ታላላቅ ፡ ሹማምንት ፤ አኤሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ ድረስ ፡ ሔደው ፡ ተቀብለዋቸዋል ።

፫ኛ ፤ አይሮፕላኑ ፡ እንደገባ ፡ ልዑል ፡ መኰንን ፡ መስፍነ ፡ ሐረር ፡ ወደኤሮፕላኑ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ የግርማዊነታቸውን ፡ የመልካም ፡ ምኞት ፡ መልእክት ፡ ለብፁዕነታቸው ፡ አቅርበዋል ።

፬ኛ ፤ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ሔዶ ፡ ተሰልፎ ፡ የተጠባበቀው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ የክብር ፡ ሰልፈኛ ፡ ብፁዕነታቸው ፡ ከአኤሮፕላን ፡ ሲወርዱ ፡ የክብር ፡ ሰላምታ ፡ ሰጥቷቸዋል ።

፭ኛ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፤ ብፁዕነታቸው ፡ በልዩ ፡ አቶሞቢል ፡ ተቀምጠው ፡ በኦቶቢ ፡ ሲክሴት ፡ ታጅበው ፡ በፊልድ ፡ ማርሻል ፡ ስሙትና ፡ በቸርችል ፡ መንገድ ፤ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጎዳና ፡ ወደ ፡ ታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሔዱ ።



## በቤተ ፡ መንግሥት ።

፩ኛ/ አንድ ፡ የክብር ፡ ዘበኛ ፡ ጓድ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ቅጽር ፡ ግቢ ፡ ተሰልፎ ፡ ይጠባበቅ ፡ ነበርና ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ የክብር ፡ ሰላምታ ፡ ሰጥቷል ።

፪ኛ/ የያድባራቱ ፡ አለቆች ፡ የክብር ፡ ልብሳቸውን ፤ ካህናቱም ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖዋቸውን ፡ ለብሰው ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ በተለይ ፡ በተዘጋጀላቸው ፡ ሥፍራ ፡ ሆነው ፡ ተጠባበቁ ።

፫ኛ| በ፲ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ ግርማዊት ፡ እቴጌ ፤ ልዑላን ፡ መሳፍንት ፤ ክቡራን ፡ ሚኒስትሮችና ፡ መኳንንት ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ አለቆችና ፡ ካህናት ፡ ባሉበት ፡ ብፁዕነታቸውን ፡ ለመቀበል ፡ በታላቁ ። ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ተገኝተዋል ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የኮርዲፕሎማቲኮች ፡ በዓሉን ፡ ለማክበር ፡ በዚያው ፡ ተገኝተዋል ።

፬ኛ| ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ወደቤተ ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ የቡራኬ ፡ ሰላምታ ፡ ሰጥተዋል ።

በዚሁም ፡ ጊዜ ፤ ፳፩ ፡ ጊዜ ፡ መድፍ ፡ ተተኵሷል ። የከተማው ፡ አድባራትም ፡ የመድፉን ፡ ድምፅ ፡ ተከትለው ፡ ስለ ፡ ደስታው ፡ የደወል ፡ ድምፅ ፡ አሰምተዋል ።

፭| ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ንግግር ፡ አድርገዋል ። ቀጥሎም ፡ ክቡር ፡ ራስ ፡ ቢትወደድ ፡ መኰንን ፡ ንግግር ፡ አድርገዋል ።

፮ኛ| ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ስለ ፡ በዓሉ ፡ ክብር ፡ ንግግር ፡ አደርገው ፡ እንደጨረሱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ መዝሙር ፡ ተዘምሮዋል ።

፯ኛ| ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሻምፓኝ ፡ ግብዣ ፡ ተደርጓል ።

፰ኛ| ጥር ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ በዓሉ ፡ ክብር ፡ በ፯ ፡ ሰዓት ፡ በታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ለልዑላን ፡ መሳፍንት ፤ ለክቡራን ፡ ሚኒስትሮችና ፡ መኳንንት ፤ ለቤተ ፡ ክህነት ፡ አለቆችም ፡ የምሳ ፡ ግብዣ ፡ ተደረገና ፡ የበዓሉ ፡ ፍጻሜ ፡ ሆነ ።

www.ethiopianorthodox.org

ጥር ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፹፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የሚመተ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስናው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፤ ተፈጽሞ ፤ ጥር ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፹፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በክብር ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፤

## ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ያደረጉት ፡ ንግግር ።

### ጃንሆይ ።

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዕድል ፡ በሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ መዓርግ ፡ ዕድገት ፡ አግኝቶ ፤ ለዚሁም ፡ ዕድል ፡ ቀዳሚ ፡ ሆኜ ፡ በመገኘቴ ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰግነዋለሁ ።

### ግርማዊ ፡ ሆይ ።

በክርስቶስ ፡ ክርስቲያን ፡ የመባልን ፡ ዕድል ፡ ቀደም ፡ ብላ ፡ የወሰደችው ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሃይማኖትና ፡ የምግባር ፡ ባለቤት ፡ በመሆኑዋ ፤ መንፈሳዊና ፡ ሥጋዊ ፡ ሀብትን ፡ አጣምራ ፡ ይዛ ፡ ስትሠራበት ፡ እስከዚህ ፡ ዘመን ፡ ደርሳለች ። የመንፈስ ፡ ብርታት ፡ ለሥጋ ፡ ደካማነት ፡ ኃይልን ፡ ስለሚሰጠው ፤ መንፈሳዊ ፡ ሀብትና ፡ ሥጋዊ ፡ ሀብት ፡ ተደጋጋፊዎች ፡ ሆነው ፡ ይኖራሉ ።

ኢትዮጵያ ፡ በፊት ፡ በኦሪት ፡ በኋላም ፡ በወንጌል ፡ የእግዚአብሔርን ፡ አምልኮ ፡ ተቀብላ ፡ ስታምን ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱና ፡ ቤተ ፡ ክህነቱ ፡ ባንድ ፡ ልቡና ፡ ባንድ ፡ ፈቃድ ፡ ተቀብለውታል ።

ኢትዮጵያ ፡ በደጋጎቹ ፡ በአብርሀና ፡ በአጽብሐ ፡ ዘመን ፡ የክርስቶስ ፡ ብርሃን ፡ ስለበራላት ፡ የመጀመሪያውን ፡ መሪዋን ፡ ሰላማን ፡ ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ አሰኝታዋለች ።

እሱዋ ፡ በክርስቶስ ፡ ልብሰ ፡ ብርሃን ፡ የተጐናጸፈች ፡ ክርስቲያናዊት ፡ ሁና ፡ ዳግም ፡ በሱዋ ፡ ሐዋርያዋ ፡ ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ በመባሉ ፡ ማኅቶተ ፡ ብርሃን ፡ ተቀባይ ፡ የሆነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በወንጌል ፡ ስብከት ፡ ዘይትና ፡ ፈትል ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝለት ፡ ነው ።

እንዲሁም ፡ አብርሀና ፡ አጽብሐ ፡ የወንጌልን ፡ ብርሃን ፡ መጀመሪያ ፡ ተቀባይ ፡ በመሆናቸው ፡ ይህን ፡ ከብርሃን ፡ የተወረሰ ፡ ስም ፡ አትርፈዋል ።

ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ሕጽዋ ፡ ለህንደኬ ፡ የተባለው ፡ የኢየሩሳሌም ፡ መንገደኛ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ የተነገረውን ፡ (የኢሳይያስን ፡) ተፈጻሚ ፡ ትንቢት ፡ በሐዋርያው ፡ በፊልጶስ ፡ ቃል ፡ ሰምቶ ፡ ሳይጠራጠር ፡ ማመኑ ፡ ኢትዮጵያ ፡ «ሳያዩኝ ፡ ያመኑብኝ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው» ፡ የተባለውን ፡ ብፅዕና ፡ ተቀባይ ፡ መሆኗን ፡ ያስረዳል ።

ወንጌል ፡ በኦሪት ፡ ተተክታ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ከተስፋፋች ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ



ያን ፡ በሊቀ ፡ ጳጳስና ፡ በጳጳስ ፡ በኩል ፡ መብት ፡ እንዲኖራት ፡ ብዙ ፡ ጥያቄዎች ፡ ሳይደረጉ ፡ አልቀሩም ።

ነገር ፡ ግን ፤ ጊዜው ፡ ሳይደርስ ፡ በመቅረቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ብዙውን ፡ ዘመን ፡ በዚያው ፡ በቄየው ፡ ልማድ ፡ ስትተዳደር ፡ ኖረች ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ችግር ፡ ምክንያት ፡ በፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በተሾመላት ፡ በኢትዮጵያዊ ፡ ጳጳስ ፡ ሥራዋን ፡ መቀጠሏ ፡ አልቀረም ።

በፈቃደ ፡ እግዚአብሔርም ፤ ከኢትዮጵያ ፡ ቅዱሳን ፡ ጳጳስ ፡ ለመሆን ፡ የበቁት ፡ ታላቁ ፡ ሐዋርያ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መሆናቸውን ፡ ስናገር ፡ መንፈሳዊው ፡ ብርሃን ፡ በሁላችን ፡ ላይ ፡ ይደር ፡ እያልኩ ፡ ነው ።

የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ታሪክ ፡ በአጭሩ ፡ ሳስታውስ ፤ አባትዎ ፡ አፄ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የዋሉላት ፡ ውለታ ፡ አብሮ ፡ ይታሰበኛል ። ከዚህ ፡ በቀር ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ በጠቅላላው ፡ ለሕዝባቸው ፡ አስተዳደር ፡ የብርሃን ፡ መሪዎች ፡ ከመሆናቸው ፡ በላይ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ በኩል ፡ የመንፈሳዊ ፡ መሪዎች ፡ ሆነው ፡ የሠሩትን ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አትዘነጋውም ።

### ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ከመጀመሪያው ፡ አባትዎ ፡ ከዳዊት ፤ ቀጥሎም ፡ ከሰሎሞን ፡ ሥራ ፡ ጋር ፡ የመካከለኛውንና ፡ ያሁኑን ፡ ኑሩታዊ ፡ ምግባር ፡ ስናመዛዝነው ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የዋለላትና ፡ የፈጸመላት ፡ መንፈሳዊ ፡ አገልግሎት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መሆኑን ፡ ሥራዎ ፡ ይገልጸዋል ።

ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ሲያያዝ ፡ የመጣው ፡ መገናኛ ፡ ሳይለወጥ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚገባትን ፡ ለማግኘት ፡ የቻለችው ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ታጋሽነት ፡ ነው ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በመታገሥና ፡ በሃይማኖት ፡ ወደተጠበቀልን ፡ ተስፋ ፡ እንገሥግሥ ፡ (ዕብ ፡ ፲፪ ፡ ፩ ፡) ብሎ ፡ የተናገረውን ፡ በመከተል ፡ ግርማዊነትዎ ፡ የፈጸመው ፡ ተግባር ፡ ይህን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መንፈሳዊ ፡ ዕድገት ፡ ለማስገኘት ፡ ቻለ ።

እግዚአብሔር ፡ ለአብርሃም ፡ «እኔ ፡ ላንተ ፡ ጋሻ ፡ ነኝ ፤ ዋጋህም ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ነው» ። (ዘፀ ፡ ፲፭ ፡) ያለውን ፡ የፈጸሙልዎ ፡ ይህን ፡ መልካም ፡ ፈቃድዎን ፡ ተመልክቶ ፡ ነው ።

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውለታዎን ፡ የማትዘነጋ ፡ በመሆኑዋ ፡ በምትጸልየው ፡ ጸሎትና ፡ በምታቀርበው ፡ መሥዋዕት ፡ ስለንጉሠ ፡ ነገሥትዋ ፡ ሕይወትና ፡ ስለሕዝብዎ ፡ ደኅንነት ፡ ተከላካይ ፡ በመሆንዋ ፡ እግዚአብሔር ፤ በዘረጋችው ፡ እጅዋ ፡ የድል ፡ አክሊል ፡ ሳያገባላት ፡ ቀርቶ ፡ አያውቅም ።

www.ethiopianorthodox.org

ባለፈው ፡ በመከራችን ፡ ሰዓት ፡ ሞቱን ፡ ሕይወት ፤ መራራውን ፡ ጣፋጭ ፡ ከባዱን ፡ ቀላል ፡ አድርገው ፡ የተቀበሉትን ፡ መንፈሳውያን ፡ አርበኞች ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስንና ፡ አቡነ ፡ ሚካኤልን ፡ በዚህ ፡ ገጽ ፡ እናስታውሳቸዋለን ። ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የዋሉላትን ፡ ውለታ ፡ በመገንዘብና ፡ ስለ ፡ እውነት ፡ መሥዋዕት ፡ መሆን ፡ የሚገባ ፡ መሆኑን ፡ በማሰብ ፡ የሚገባቸውን ፡ ፈጸሙ ።

«እነግረክሙ ፡ አኃዊነ ፡ ጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘተውህበ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡» ብሎ ፡ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ የተናገረውን ፡ ስናስብ ፡ በዛሬው ፡ ጊዜ ፡ የተፈጸመው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ክብር ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ያለው ፡ ለመሆኑ ፡ ምስክር ፡ ነው ።

በ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሐምሌ ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጳጳሳት ፡ ሥርዓት ፡ ሢመት ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፤ በዚሁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ተሰብስበን ፡ እግዚአብሔር ፡ ያደረገልንን ፡ ደስታ ፡ አብረን ፡ ስንካፈል ፡ በግርማዊ ፡ ቃልዎ ፡ «የኢትዮጵያ ፡ ታላቅነትና ፡ የሥልጣኔ ፡ ዕድገት ፡ ከሃይማኖት ፡ ትልቅነቷ ፡ ጋር ፡ የተባበረ ፡ እንዲሆን ፡ ያስፈልጋል» ፡ ብለው ፡ በተናገሩት ፡ መሠረት ፡ የሃይማኖቷ ፡ ዕድገት ፡ ይህን ፡ ታላቅ ፡ የሆነ ፡ መንፈሳዊ ፡ መብት ፡ አስገኘ ።

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ የግብጽ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከቀድሞ ፡ ጀምሮ ፡ የቈየውን ፡ መንፈሳዊ ፡ መገናኛ ፡ በመጠበቃቸው ፡ የተደረገው ፡ ስምምነት ፡ ይህን ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ አስገኘ ። ይህንም ፡ የጋራ ፡ ደስታ ፡ አብሮ ፡ በመካፈል ፡ በምድረ ፡ ግብጽ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ዳግማዊ ፡ ዮሳብ ፡ ያደረጉልንን ፡ ደግነትና ፡ አቀባበል ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ፊት ፡ አስበዋለሁ ።

ግርማዊነትዎ ፡ የሚገባውን ፡ ሁሉ ፡ ፈጽሞ ፤ የኢትዮጵያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጉዳይ ፡ እስከመጨረሻው ፡ አድርሰዋል ። ይህ ፡ ሲሆን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መዓርጉዋ ፡ በማደጉ ፡ መጠን ፤ አላፊነቷም ፡ እንዲሁ ፡ እያደገ ፡ መሔዱን ፡ ተረድተነዋል ።

ለተደከመበት ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍሬ ፡ እንዲሰጥ ። የግርማዊነትዎን ፡ ዘር ፡ ይባርክ ። ዙፋንዎ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ሲተላለፍ ፡ ለዘላለም ፡ ይኑር ።
ከኢትዮጵያ ፡ ከሀገራችን ፡ የእግዚአብሔር ፡ በረከትና ፡ ረድኤት ፡ አይለይ ።
አሜን ።



## የክቡር ፡ ራስ ፡ ቢትወደድ ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፡ ንግግር ።

### ግርማዊ ፡ ሆይ ።

በዚህ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ታሪካዊ ፡ ሥራ ፡ በተፈጸመበት ፡ ቀን ፡ እንድናገር ፡ ፈቃድ ፡ በማግኘቴ ፤ የተሰማኝን ፡ ደስታ ፡ ለመግለጽ ፡ እንዲፈቀድልኝ ፡ በታላቅ ፡ ትሕትና ፡ እለምናለሁ ።

ዛሬ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የብዙ ፡ ዘመን ፡ ምኞትዋ ፡ ተፈጸመላት ። ለጥንታዊነቷም ፡ የተገባውን ፡ ክብርና ፡ ደስታ ፡ አገኘች ። የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገና ፡ ከሕፃንነቷ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እየጠበቁ ፡ ያሳደጓትን ፡ የነገሥታት ፡ አባቶቿን ፡ አርአያ ፡ በመከተል ፡ የማይናወጥ ፡ የክብር ፡ መንበር ፡ ስለ ፡ መሠረቱላት ፤ ለጃንሆይ ፡ የደረሰው ፡ ዕድል ፡ ለአብርሀና ፡ ለአጽብሐ ፡ ከተሰጣቸው ፡ ዕድል ፡ ጋር ፡ የተካከለ ፡ ነው ።

ለነጻዪቱ ፡ አገሬ ፡ ነጻ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያስፈልጋታል ፡ በማለት ፡ አስቦና ፡ አርቆ ፡ ተመልክቶ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ከዛሬ ፡ ኻያ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የጣለው ፡ መሠረት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ለታወቀው ፡ ክብርዋና ፡ ስምዋ ፡ የተገባውን ፡ የተቀደሰ ፡ የነጻነት ፡ መብት ፡ አስገኘላት ።
ማንኛቸውንም ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ሲታሰብ ፤ ሁለት ፡ ችግሮች ፡ መኖራቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ። እነርሱም ፡ መጀመርያና ፡ መጨረሻ ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ሀብቶች ፡ ዕድልዎ ፡ ሆነው ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ስለተሰጡ ፡ በዘመንዎ ፡ ተጀምሮ ፡ መልካም ፡ ፍጻሜውን ፡ ያላገኘ ፡ አንድም ፡ ትልቅ ፡ ሥራ ፡ የለም ።

### ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ጥንታዊ ፡ ወጉንና ፡ ሥርዓቱን ፡ ጠብቆ ፡ የኖረውን ፡ ሕዝብዎን ፡ የአዲሱ ፡ ዘመን ፡ ሥልጣኔ ፡ ያስገኘውን ፡ ጥቅም ፡ ተካፋይ ፡ ለማድረግ ፤ ኑሮውን ፡ በሀብት ፡ ለማደርጀትና ፡ በጥበብ ፡ ለማደላደል ፡ ከሁሉ ፡ የተሻለው ፡ ዘዴ ፡ ትምህርትን ፡ ማስፋፋት ፡ መሆኑን ፡ በማሰብ ፤ የግርማዊነትዎ ፡ ትጋት ፡ ያደራጃቸው ፡ የተማሩ ፡ ልጆች ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቀዋሚ ፡ ዕድል ፡ ለመስጠት ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በሰፊው ፡ ለሚደከምበት ፡ ሥራ ፡ ዋና ፡ ረዳቶች ፡ ለመሆን ፡ ችለዋል ።

ማንኛውንም ፡ የተገኘውን ፡ ጥበብና ፡ ዕውቀት ፡ ጠቃሚ ፡ የሚያደርገው ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ መሆኑ ፡ በሕፃናቱ ፡ አእምሮ ፡ እንዲቀረጽ ፡ ለማድረግ ፡ በየጊዜው ፡ ግርማዊነትዎ ፡ የሚሰጠው ፡ ምክር ፡ የሕሊና ፡ ምስክርና ፡ ጠቃሽ ፡ ሆኖ ፡ ሁሉንም ፡ ወደ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ስለሚመራቸው ፡ እርምጃቸው ፡ የቀናውን ፡ መንገድ ፡ ተከትሎዋል ።

«ሰው ፡ ፈጣሪውን ፡ ካመነ ፡ ሥልጣኔው ፡ የደኅንነት ፡ ሥልጣኔ ፡ ሊሆንለት ፡ ይችላል» ፡ ሲል ፡ ግርማዊነትዎ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ሃይማኖትና ፡ ምግባር ፡ የሌለበት ፡ ሥልጣኔ ፡ አጥፊ ፡ መሆኑን ፡ አስረድቷል ።

www.ethiopianorthodox.org

ይህም ፡ እየተደጋገመ ፤ በሥራ ፡ የተመሠከረለት ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ታሪክ ፡ ነው ። የሰው ፡ ልጅ ፡ በዕውቀቱና ፡ በጥበቡ ፡ በዙሪያው ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለማወቅና ፡ ለመመርመር ፡ ችሎዋል ። ራሱን ፡ ግን ፡ ለመመርመርና ፡ ለማወቅ ፡ የሚችለው ፡ በሃይማኖትና ፡ በምግባር ፡ ብቻ ፡ ነው ።

የሰው ፡ ልጅ ፡ ከበጎ ፡ ምግባር ፡ ከራቀ ፡ በኋላ ፡ ጥበቡም ፡ ዕውቀቱም ፡ ሀብቱም ፡ ከጭንቅ ፡ ሊያድነው ፡ እንደማይችል ፡ የዛሬው ፡ ዓለም ፡ ሁኔታ ፡ ያስረዳል ።

የአገርን ፡ ነጻነትና ፡ ክብርን ፡ ሕይወትንም ፡ ከሁሉ ፡ አብልጦ ፡ የሚያስበው ፡ ግርማዊነትዎ ፡ የሕዝብዎ ፡ የሥልጣኔ ፡ እድገት ፡ ዘላቂ ፡ ጥቅም ፡ ሊሰጥ ፡ የሚችለው ፡ ከመንፈሱ ፡ እድገት ፡ ጋር ፡ ትይዩ ፡ ሆኖ ፡ ሲሔድ ፡ መሆኑን ፡ በማስተዋል ፤ በዚህ ፡ ታላቅ ፡ በሆነው ፡ ታሪካዊ ፡ ዘመን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያስገኙላት ፡ መብት ፡ የዕድልን ፡ በር ፡ ከፋች ፡ ነው ።

እንዲሁም ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ትዕግሥትና ፡ ዕውቀት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከእስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋር ፡ ያላትን ፡ ጥንታዊ ፡ መገናኛ ፡ ሳታቋርጥ ፡ የጠየቀችውን ፡ መብት ፡ በስምምነት ፡ እንድታገኝ ፡ መደረጉ ፤ በሁለቱ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መካከል ፡ የጠበቀ ፡ ዝምድናን ፡ የሚያስከትል ፡ ነው ።

## ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ታሪክዎን ፡ ዘወትር ፡ ከፍ ፡ ያደረገው ፡ ሥራዎን ፡ ሁልጊዜ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ረድኤት ፡ በታች ፡ በመጣልና ፡ «የኔ ፡ ድካም ፡ ምንም ፡ አያደርግም ፡ ሁሉንም ፡ የሚፈጽም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ብቻ ፡ ነው» ፡ በማለትዎ ፡ ነው ። በሥራና ፡ በድካም ፡ የተገኘ ፡ ዕውነተኛ ፡ ደስታ ፡ ዘላቂ ፡ ስለሆነ ፤ የግርማዊነትዎ ፡ ዕድል ፡ አያቋርጥም ። ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ የጀመረ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ይጨርሳል ፡ ተብሎአል ።

እግዚአብሔር ፡ የኢትዮጵያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እርምጃ ፡ ያቃና ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፤
» » ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡
» » ለልዑላን ፡ ንጉሣውያን ፡ ቤተ ፡ ሰብ ።



## የግርማዊነታቸው ፡ ንግግር ።

በዘመናችን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዲፈጸሙ ፡ ካሰብናቸውና ፡ ከሠራናቸው ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ አድርገን ፡ የምንቈጥረው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የመሾሙ ፡ ጕዳይ ፡ ስለ ፡ ተፈጸመ ፡ ድካማችንን ፡ ለባረከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ እናቀርባለን ።

ይህም ፤ ዛሬ ፡ ተፈጽሞ ፡ የምናየው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ራሷን ፡ የሚያስችል ፡ ሥራ ፡ ከተጀመረበት ፡ ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ አንሥቶ ፡ ጕዳዩ ፡ እያደገ ፡ እንዲሔድና ፡ እዚህ ፡ እንዲደርስ ፡ ለማድረግ ፡ የነበረውን ፡ ድካም ፡ ያለፈበትን ፡ መንገድ ፡ ስናስብ ፤ የክብድነቱ ፡ ታላቅነት ፡ የሚዘነጋ ፡ አይደለም ። አሁን ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚሠራውን ፡ ሥራ ፡ በፈቀደ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚፈጽም ፤ ኢትዮጵያ ፡ አገራችን ፤ ነጻ ፡ ሕዝባችንና ፡ መንግሥታችን ፡ ራሷን ፡ የቻለች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዲኖራቸውና ፡ በዓለምም ፡ እንዲታወቅ ፡ አደረገ ። ይህም ፡ በዘመናችን ፡ ስለ ፡ ተፈጸመልን ፡ እኛም ፡ ሕዝባችንም ፡ እኩል ፡ የምንኰራበት ፡ ነው ።

ያለፉት ፡ አባቶቻችን ፡ ነገሥታቶች ፡ ይህን ፡ ተመኙ ፤ በተስፋም ፡ ተመለከቱት ። በሃይማኖት ፡ የጸናችም ፡ ተስፋ ፡ በዘመናችን ፡ ስትፈጸም ፡ ለማየት ፡ አብቃን ።

ብፁዕ ፡ አባታችንም ፡ ለዚህ ፡ ከፍ ፡ ላለና ፡ ለተቀደሰ ፡ ሥራ ፡ በዘመናችን ፡ ጀማሪ ፡ ለመሆን ፡ መልካሙ ፡ ዕድል ፡ ስለደረሰዎ ፡ ደስታችንን ፡ እንገልጥልዎታለን ። በዚህም ፡ በዛሬው ፡ ቀን ፡ የግብጽና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ በበለጠ ፡ የሚከባበሩበትና ፡ የሚተማመኑበት ፡ አዲስ ፡ ዘመን ፡ ተከፈተ ። ይህም ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በተገለጠላቸው ፡ ብሩህ ፡ በሆነ ፡ የመገባበት ፡ መንፈስ ፡ በበኩላቸው ፡ ለረዱ ፡ በቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ መንበር ፡ ለተቀመጡ ፡ ለብፁዕ ፡ ዳግማዊ ፡ ዮሳብ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስጋናችንን ፡ እንገልጣለን ።

በዘመናችንና ፡ በዘመናቸውም ፡ የተፈጸመው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አስተዳደር ፡ መሻሻልና ፤ ዕድላቸው ፡ ከዕድላችን ፡ ጋራ ፡ መግጠሙን ፡ ስናስብም ፡ ደስ ፡ ይለናል ። መንፈሳዊ ፡ ኃይል ፡ ከፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ ለሆነው ፡ ለሰው ፡ ለዓለማዊውና ፡ ለሰማያዊ ፡ ሕይወቱ ፡ ለሁለቱም ፡ ዓለም ፡ ኀዳና ፡ መሪው ፡ ነው ። በመንፈሳዊ ፡ ኃይልም ፡ መሪነት ፡ ሰው ፡ የተቀደሰ ፡ ፍጥረቱ ፡ ሊደርስበት ፡ ወደሚገባው ፡ ለመድረስ ፡ ይችላል ። ብፁዕ ፡ አባታችንም ፡ ለዓለም ፡ ቍስል ፡ የመንፈሳዊ ፡ ኃይል ፡ መጽናኛና ፡ መዳኛ ፡ እንዲሆነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ ባለበት ፡ መጠን ፡ ከሚደርስብዎ ፡ ታላቅ ፡ ሸክም ፡ በቀር ፡ በተለየ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በመንፈሳዊ ፡ ኃይል ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ተግባሩን ፡ ለማደርጀት ፡ ሰማያዊ ፡ መንገዱንም ፡ ለማቅናት ፡ ከባድ ፡ የሆነው ፡ አላፊነት ፡ በብፁዕነትዎ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ወደቀ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋና ፡ ኃይል ፡ እንዲረዳዎ ፡ ከልባችን ፡ እንመኝልዎታለን ።

www.ethiopianorthodox.org

## ስምን ፡ መልአክ ፡ ያወጣዋል ።

የደጋጎችን ፡ ስም ፡ ከልደታቸው ፡ አስቀድሞ ፡ መልአክ ፡ እንደሚያወጣው ፡ በብዙ ፡ አንቀጸ ፡ መጻሕፍት ፡ ተጽፏል ።

ይኸውም ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ ዮሐንስ ፡ መጥምቅ ፡ ከመፀነሱ ፡ አስቀድሞ ፡ መልአኩ ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ለአባቱ ፡ ለዘካርያስ "ሚስትህ ፡ ኤልሳቤጥ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ትወልድልኻለች ፤ ስሙንም ፡ ዮሐንስ ፡ ብለህ ፡ ትጠራዋለህ ። ላንተ ፡ ፍጹም ፡ ደስታ ፡ ይሆንኻል ። በመወለዱም ፡ ብዙዎች ፡ ይደሰታሉ ። በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ ይሆናልና" ብሎ ፡ በተናገረው ፡ መሠረት ፡ ስሙን ፡ ዮሐንስ ፡ ብሎ ፡ ሰይሞታል ።

እንዲሁም ፤ ለአምላክ ፡ እናት ፡ ለድንግል ፡ ማርያም ፡ የአምላክን ፡ መወለድ ፡ ሲያበስር ‹እነሆ ፡ ፀንሰሽ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ትወልጃለሽ ፡ ስሙንም ፡ ኢየሱስ ፡ ብለሽ ፡ ትጠሪዋለሽ» ብሎ ፡ ከመፅነሷ ፡ አስቀድሞ ፡ የልጅዋን ፡ ስም ፡ ነግሯታል ።

በየጊዜውም ፤ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ የመረጣቸው ፡ ሕፃናት ፡ ከመፀነሳቸውና ፡ ከመወለዳቸው ፡ አስቀድሞ ፡ ስማቸው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድና ፡ በመልአክ ፡ ቃል ፡ ተሰይሞ ፡ የወደፊት ፡ ዕድላቸውንና ፡ ክብራቸውን ፡ አስረጂ ፡ ሆኖ ፡ ስለሚገኝ ፡ በአባቶች ፡ ቃል ፡ ስምን ፡ መልአክ ፡ ያወጣዋል ፡ ይባላል ።

ስለዚህ ፤ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘኢትዮጵያ ፤ ''ባስልዮስ» ፡ የተባለውን ፡ ስመ ፡ ተቀብዖ ፡ ሐምሌ ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተቀብለው ፡ ይኸው ፡ ክቡር ፡ ስመ ፡ ጵጵስና ፡ በፈቃደ ፡ ግዚአብሔር ፡ እንደተመረጠና ፡ መልአክ ፡ እንዳወጣው ፡ ሆኖ ፤ ብፁዕነታቸው ፡ በፍጹም ፡ የባስልዮስ ፡ ዘቂሣርያን ፡ ሥራና ፡ ሀብት ፡ ተከታይ ፡ በመሆኑ ፡ ያልተገረመ ፡ የለም ።

ይልቁንም ፡ ጥር ፡ ፯ ቀን ፡ ፲፱፻፵፫ ዓ ም ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ መምህራን ፡ የክብር ፡ መጀመሪያ ፡ ሆነው ፡ ቅብዐ ፡ ሢመት ፡ ጵጵስና ፡ የተቀበሉበት ፡ ዕለት ፡ የባስልዮስ ፡ ዘቂሣርያ ፡ ዝክረ ፡ ታሪክ ፡ የሚነገርበትና ፡ በየአብያተ ፡ ክርስቲያናቱ ፡ ቅዳሴ ፡ ባስልዮስ ፡ የሚቀደስበት ፡ ስለ ፡ ነበረች ፤ ጥንቱን ፡ የብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ መሠረጥ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ መሆኑን ፡ ተመልክተው ፡ ብዙ ፡ ሊቃውንት ፡ አንክሮ ፡ አድርገው ፡ ውለዋል ።

በብፁዕነታቸው ፡ ላይ ፡ ያረፈውን ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ፈቃድ ፡ በብዙ ፡ ወገን ፡ ለመረዳት ፤ ከባስልዮስ ፡ ዘቂሣርያ ፡ ጋር ፡ የተመሳሰሉበትን ፡ ሥራና ፡ ሀብተ ፡ ጸጋ ፡ ወደ ፡ አድናቆት ፡ ለማቅረብ ፡ ይመቸን ፡ ዘንድ ፡ የባስልዮስ ፡ ዘቂሣርያን ፡ ታሪክ ፡ ከዚህ ፡ እናስከትላለን ።

## ዜና ፡ ባስልዮስ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ዘቂሣርያ ።

የቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ አባት ፡ ኤስድሮስ ፡ ይባል ፡ ነበር ። የተወለደበት ፡ አገሩም ፡ አንፆኪያ ፡ ይባላል ። በመንፈሳዊ ፡ ሥርዓትም ፡ መዓርገ ፡ ቅስና ፡ የተሰጠው ፡ ቅዱስ ፡ ነው ።



አምስት ፡ ልጆችም ፡ ወልዷል ። ስማቸውም ፡ የሚከተለው ፡ ነው ፤ የበኵር ፡ ልጁ ፡ ባስልዮስ ፤ ሁለተኛው ፡ ጎርጎርዮስ ፣ ሦስተኛው ፡ ኮርዮር ፤ ዐራተኛው ፡ ጴጥሮስ ፤ አምስተኛው ፡ መከሪና ፡ ናቸው ።

እነዚህም ፡ አምስቱ ፡ ሁሉ ፡ ቅዱሳን ፡ ሆኑ ።

በባስልዮስም ፡ መንፈስ ቅዱስ ፡ ስለመላበት ፡ መጽሐፈ ፡ ቅዳሴን ደረሰ ፤ በጁም ፡ እግዚአብሔር ፡ ብዙ ፡ ተአምራት ፡ አደረገለት ። ያደረገለትም ፡ ተአምራት ፡ በገድሉ ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ።

«፩ኛው ፡ ተአምር» ፡ ወንድሙ ፡ ጴጥሮስ ፡ ምሽት ፡ አግብቶ ፡ ሰብያጥ ፡ በምትባል ፡ አገር ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስነትን ፡ ተሹሞ ፡ ነበርና ፡ ምሽት ፡ አግብቶ ፡ እንዴት ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስነት ፡ ይሾማል ? ፡ ብለው ፡ ሕዝቡ ፡ አምተውት ፡ ነበር ። ለቅዱሳን ፡ ሐሜት ፡ የሚከተለው ፡ ንጽሕና ፡ ልማዳቸው ፡ ነው ።

ድሜጥሮስ ፡ ምሽት ፡ አግብቶ ፡ በእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስነት ፡ ቢሾም ፤ ሕዝቡ ፡ „አንተ ፡ በቅተኻል ፤ አንተ አልበቃህም ፡ እያለ ፡ የኛን ፡ ኃጢአት ፡ በአፍኣ ፡ ይገልጣል ። እሱ ፡ ግን ፤ ሚስቱን ፡ አግብቶ በማርቆስ ፡ መንበር ፡ ተቀምጧል" ፡ ብለው ፡ ቢያሙት ፤ ምሽቱን ፡ ካገባት ፡ ጀምሮ ፡ እንዳልደረሰባትና ፤ እሱም ፤ እሷም ፡ በንጽሕና ፡ መቀመጣቸውን ፡ ዐውቆ ፤ እሳት ፡ አስነድዶ ፡ በእሳቱ ፡ መካከል ፤ ቆሞ ፡ የሚስቱን ፡ ልብስ ፡ ዘርጊ ፡ ብሎ ፡ አዘርግቶ ፡ ፍሙን ፡ በእጁ ፡ እያነሣ ፡ በእሳቱ ፡ መካከል ፡ እንደቆመች ፡ በልብሷ ፡ ላይ ፡ ቢያደርግላት ፡ እንደ ፡ ፫ቱ ፡ ደቂቅ ፡ የሁለቱንም ፡ ልብሳቸውንና ፡ ሰውነታቸውን ፡ እሳቱ ፡ ሳይነካው ፡ በመቅረቱ ፡ ንጽሕናውን ፡ ገለጠላቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አባታችን ፡ ይቅር ፡ በለን ፡ ብለው ፡ በእግሩ ፡ ቢወድቁበት ፡ «ይፍታሕ ፡ ይኅድግ» ፡ ብሎ ፡ ናዘ ፡ ኃጢአታቸውን ፡ አስተሠረየላቸው ። ኑዛዜንም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ጀመረ ።

ከላይ ፡ የባስልዮስን ፡ ወንድም ፡ የጴጥሮስን ፡ የንጽሕናውን ፡ ታሪክ ፡ ከድሜጥሮስ ፡ ታሪክ ፡ ጋራ ፡ ለማያያዝ ፡ ለቅዱሳን ፡ ሐሜት ፡ የሚከተለው ፡ ንጽሕና ፡ ልማዳቸው ፡ ነው ፡ ያልነው ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ ወደ ፡ ጀመርነው ፡ ወደ ፡ ባስልዮስና ፡ ወደ ፡ ወንድሙ ፡ ወደ ፡ ጴጥሮስ ፡ ታሪክ ፡ እንመለስ ። የባስልዮስን ፡ ወንድም ፡ ጴጥሮስን ፡ ምሽት ፡ በማግባቱ ፡ ሲያሙት ፤ ወንድሙ ፡ ባስልዮስ ፡ ደርሶ ፡ ነገሩን ፡ በተመለከተ ፡ ጊዜ ፤ የወንድሙን ፡ የጴጥሮስንና ፡ የምሽቱን ፡ ገድልና ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ እየጠበቃቸው ፤ እሱም ፡ እስዋም ፡ በንጽሕና ፡ በድንግልና ፡ መቀመጣቸውን ፡ ለሕዝቡ ፡ በገለጠላቸው ፡ ጊዜ ሕዝቡም ፡ ነገሩን ፡ አድንቀው ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገኑት ። በብፁዕ ፡ ጴጥሮስ ፡ እግርም ፡ ወድቀው ፡ አባታችን ፡ ይቅር ፡ በለን ፡ ቢሉት ፡ በሐሜት ፡ የሠሩትን ፡ ኃጢአት ፡ እንደ ፡ ድሜጥሮስ ፡ "ይፍታሕ ፡ ይኅድግ" ፡ ብሎ ፡ አስተሠረየላቸው ። ቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ መጀመሪያ ፡ ያደረገው ፡ ተአምራት ፡ ይህ ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፫ኛው ፡ ተአምር“ ፡ በክርስቶስ ያላመኑ ፡ አሕዛብ ፡ አንዲቱን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከበው ፡ መዝጊያውን ፡ ከፍተን ፡ እንግባ ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፤ መዝጊያው ፡ በኃይለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተዘግቶ ፡ አልከፈትም ፡ ቢል ፤ አሕዛብ ፡ ምንም ፡ ሳያ ደርጉ ፡ ጥለው ፡ ስለሔዱ ፤ ምእመናን ፡ ተሰብስበው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኒቱ ፡ እንድትከፈትላቸው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አመለከቱ ። የተአምራት ፡ ክፍልም ፡ ለቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ ተሰጥቷልና ፡ በቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ ጸሎት ፡ የቤተ ፡ ክር ስቲያኒቱ ፡ መዝጊያ ፡ ተከፍቶላቸው ፡ ገብተው ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግነዋል ።

፳፬ኛው ፡ ተአምር„ ፡ ቅዱስ ፡ ኤፍሬም ፡ አይቶ ፡ የጻፈው ፡ ነው ። ኤፍሬም ፡ ሶርያዊ ፡ ከምድር ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ የሚደርስ ፡ ዐምደ ፡ ብርሃን ፡ ተተክሎ ፡ በራእይ ፡ ስለታየው ፤ ይህ ፡ የምታየው ፡ ዐምደ ፡ ብርሃን ፡ ባስልዮስ ፡ ዘቂሣርያ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ሰማ ።

ቅደስ ፡ ኤፍሬምም ፤ ርቆ ፡ ያዩትን ፡ ቀርቦ ፡ ሊረዱት ፡ ይገባል ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ቂሣርያ ፡ ሔዶ ፡ የቅዱስ ፡ ባስልዮስን ፡ ትሩፋቱንና ፡ ክብሩን ፡ ከየ ፡ በኋላ ፤ ባስ ልዮስ ፡ ኤፍሬምን ፡ ዲቁና ፡ ሾመው ። ቀጥሎም ፡ በዮናኒ ፡ ቋንቋ ፡ ተነጋግ ረዋል ።

፳፭ኛው ፡ ተአምር ፤ መጪውንና ፡ ኃላፊውን ፡ ዐውቃለሁ ፡ የሚል ፡ አንድ ፡ አይሁዳዊ ፡ ነበር ። ቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ ጸልዮ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ድካም ፡ የሚ ያልፍበት ፡ ጊዜ ፡ ሞቱ ፡ ስለተገለጸለት ፤ ያንን ፡ ዐውቃለሁ ፡ የሚል ፡ አይሁ ዳዊ ፡ አስጠርቶ ፡ አንተ ፡ ሁሉን ፡ ዐውቃለሁ ፡ ትላለህና ፡ እኔ ፡ መቼ ፡ ነው ፡ የምሞት ? ብሎ ፡ ጠየቀው ።

ቅዱሳን ፡ የሰይጣን ፡ ዕውቀት ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ የሚሆነውን ፡ ነገር ፡ የሚጠይቁ ፡ ሆነው ፡ አይደለም ። ያንን ፡ አይሁዳዊ ፡ ከአምልኮተ ፡ ሰይጣን ፡ በተአምራት ፡ ወደ ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልሶ ፡ አጥምቆ ፡ የክርስ ቶስ ፡ ወገን ፡ ሊያደርገው ፡ ስለወደደ ፡ ነው ።

ያም ፡ አይሁዳዊ ፡ ቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ የሚሞትበትን ፡ ቀን ፡ ስለጠየቀው ፤ ከልቡ ፡ የጠየቀው ፡ መስሎት ፡ ዛሬ ፡ በምሽት ፡ ነፍስህ ፡ ከሥጋህ ፡ ትለያለች ፡ አለው ። ቅዱስ ፡ ባስልዮስም ፡ ዛሬ ፡ ሳልሞት ፡ አድሬ ፡ እስከ ፡ ነገ ጧት ፡ የቈየሁ ፡ እንደሆን ፤ ተጠምቀህ ፡ ክርስቲያን ፡ ትሆን ፡ አለህን ፡ ? አለው ።

አይሁዳዊውም ፡ አዎን ፡ ክርስቲያን ፡ እሆናለሁ ፡ አለው ። ቅዱስ ፡ ባስል ዮስም ፤ ያንን ፡ አይሁዳዊ ፡ ለማጥመቅ ፡ ቀን ፡ እንዲጨመርለት ፡ እግዚአብሔ ርን ፡ ቢለምን ፡ ጌታም ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ጨመረለት ።

አይሁዳዊውም ፤ በክርስቶስ ፡ አምኖ ፡ ከነቤተ ፡ ሰቦቹ ፡ በቅዱስ ፡ ባስል ዮስ ፡ እጅ ፡ ተጠመቀ ። ቅዱስ ፡ ባስልዮስም ፡ ጥር ፡ ፮ ፡ ቀን ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ድካም ፡ ዐረፈ ።



፳፮ኛው ፡ ተአምር ። ተጠምቆ ፡ ክርስትናውን ፡ የካደ ፡ ያንድ ፡ ባርያ ፡ ታሪክ ፡ ነው ። ያም ፡ “ያመንሁብትን ፡ ክርስቶስንና ፡ ጥምቀትን ፡ ክጃለሁ„ ፡ ብሎ ፡ በወረቀት ፡ ጽፎ ፡ ለሰይጣን ፡ የሰጠው ፡ ነው ። ቅዱስ ፡ ባስልዮስም ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ተገ ልጾለት ፡ ያንን ባርያ ፡ ባንድ ፡ ቦታ ፡ በሥልጣኑ ፡ ኃይል ፡ ዐሥረው ። ቀጥሎ ፡ ያ ፡ ሰይጣን ፡ ተቀብሎ ፡ የወሰደውን ፡ ወረቀት ፡ እስቲመልስ ፡ ድረስ ፡ ቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ ለዚያ ፡ ባርያ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቢጸልይለት ፡ ያ ፡ ሰይጣን ፡ የወሰደውን ፡ ወረቀት ፡ መልሶ ፡ አምጥቶ ፡ ለባርያው ፡ ስለሰጠው ፤ ያንን ፡ ባርያ ፡ ከስሕተትና ፡ ከክሕደት ፡ አድኖታል ።

፳፯ኛ ፡ ተአምር ፤ አንድ ፡ ቄስ ፡ ክፉ ፡ ኵስል ፡ ወድቆበት ፡ በአልጋ ፡ ላይ ፡ ተኝቶ ፡ ሲኖር ፡ ከዕለታት ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ለቅዱስ ፡ ባስልዮስ የቄሱ ፡ መታመም ፡ ተገልጾለት ፡ ለዚያ ፡ ቄስ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸልዮለት ፡ ቄሱ ፡ ከደዌው ፡ ተፈውሷል ።

፳፰ኛ ፡ ተአምር ፡ የዚያች ፡ የከበረች ፡ ሴት ፡ ታሪክ ፡ ነው ። አንዲት ፡ የከበረች ሴት ፡ በቅዱሳን ፡ ጸሎት ፡ ኃጢአት ፡ እንዲደመሰስ ፡ ስላወቀች ፤ ከልጅነት ፡ እስከ ፡ ዕውቀት ፡ የሠራችውን ፡ ኃጢአቷን ፡ ሁሉ ፡ በወረቀት ፤ ጽፋ ፡ (አትማ) ፡ ለቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ “በዚህ ፡ በወረቀት ፡ የተጻፈው ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአቴ ፡ እስቲደመሰስ ፡ ወደ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ጸልይልኝ„ ፡ ብላ ፡ ሰጠችው ። ቅዱስ ፡ ባስልዮስም ፤ ወረቀቱ ፡ ያለበት ፡ ክርታስ ፡ እንደታተመ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ እየጠራ ፡ ቢጸልይበት ፡ ካንዲት ፡ ትልቅ ፡ ኃጢአት ፡ በቀር ፡ የቀረው ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአቷ ፡ ተደምስሶላታል ።

ስለዚያች ፡ ስለአንዲቱ ፡ ኃጢአቷም ፤ “ወደ ፡ ኤፍሬም ፡ ሶርያዊ ፡ ሒጂ ፡ ያችን ፡ የቀረችውን ፡ ኃጢአትሽን ፡ እሱ ፡ ያስተሠርይልሻል„ ፡ ብሎ ፡ ሰደዳት ። እሷም ፡ ወደ ፡ ኤፍሬም ፡ ሔዳ ፡ “ይቺን ፡ ኃጢአቴን ፡ በጸሎትህ ፡ አስተሥርይልኝ„ ፡ ብትለው ፤ እሱም ፡ በመጣሽበት ፡ መንገድ ፡ ተመልሰሽ ፡ በተሎ ፡ ሳይሞት ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ ሒጂ ፡ እሱ ፡ ያስተሠርይልሻል ፡ “ብሎ ፡ መልሶ ፡ ሰደዳት ። ያች ፡ ሴትም ፡ ተመልሳ ፡ ብት ሔድ ፡ ቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ ዐርፎ ፡ ሊቀብሩት ፡ በአልጋ ፡ ላይ ፡ ተሸክመው ፡ ይዘ ውት ፡ ሲሔዱ ፤ ባየች ፡ ጊዜ ፡ መራራ ፡ ልቅሶ ፡ አልቅሳ ፡ የቀረችውን ፡ ኃጢአቷን ፡ የጻፈችበትን ፡ ወረቀተ ፡ ሳትጠራጠር ፡ በአስከሬኑ ፡ ላይ ፡ ብታኖረው ፡ ኃጢአቷ ፡ ተደመሰሰችላትና ፡ በአስከሬኑ ፡ ዙሪያ ፡ የነበሩት ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሁሉ ፡ የቅዱስ ፡ ባስ ልዮስን ፡ ብቃት ፡ አይተውና ፡ አድንቀው ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገኑ ።

ቅዱስ ፡ ባስልዮስም ፤ ከጊዜ ፡ ሞቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ከዚህ ፡ ከጻፍናቸው ፡ ፳ ፡ ተአ ምራቶች ፡ ሌላ ፡ በቍጥር ፡ የማይገመት ፡ ብዙ ፡ ተአምራት ፡ አድርጓል ።

መነኰሳትም ፡ ተጠብቀው ፡ የሚኖሩበት ፡ ብዙ ፡ ድርሰት ፡ ደርሶ ፡ ብዙ ፡ ተግሣጽ ፡ ተናግሯል ፤ ጽፎዋልም ። ከብሉያትና ፡ ከሐዲሳት ፡ አወጣጥቶ ፡ ተርጕሞ ፡ ብዙ ፡ መጻ ሕፍት ፡ አውጥቶዋል ። ብዙ ፡ ቀኖናም ፡ ሠርቷል ። ይኸውም ፡ በሀገሩ ፡ ቂሣርያ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በምዕመናን ፡ እጅ ፡ ይገኛል ። የዚያችን ፡ ሴት ፡ ኃጢአት ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ እንደደመሰሰላት ፤ የኛንም ፡ ኃጢአታችንን ፡ ይደምስስልን ። አሜን ።

www.ethiopianorthodox.org

ይህችንም ፡ ጥር ፡ ፮ ፡ ቀን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከድንግል፡ማርያም ፡ ስለኛ ፡ በኛ ፡ ሥጋ ፡ ተወልዶ ፡ ሕገ ፡ኦሪትን ፡ ለመፈጸም ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ግዝረት ፡ ገብቶ ፡ የሚገዝረው ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ሳይዘውና ፡ የምላጩ ፡ ኃይል ፡ ሳያርፍበት ፡ በግብር ፡ መለኮታዊ፡ግዝረቱን ፡ አሳይቶ ፡ አምላክነቱን ፡ ገልጦ፡ ያከበራት፡ናት።

ሰውም ፡ ሳይሆን ፤ ኖኅን ፡ ያሳረፈበት ፡ ኤልያስን ፡ ያሳረገባት ፡ ቀን ፡ ናት ። ይህች ፡ ጥር ፡ ፮ ፡ ቀን ፡ ጌታችን ፡ ግዝረቱን ፤ የገለጠባት ፡ ኖኅ ፡ ያረፈበት ፤ ኤልያስ ፡ ያረገባት ፡ የተቀደሰች ፡ ዕለት ፡ ናት ፡ ብለን ፤ የተረክንበት ፡ ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ስምን ፡ ከስም ፡ ግብርን ፡ ከግብር ፡ አያይዘን ፡ ለመጻፍ ፡ ነው ።

በተቀደሰችው ፡ በጥር ፡ ፮፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ፡ ም ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ፡ የኢትዮጵያ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስነት ፡ የተሾሙባት ፡ ቀን ፡ ስለሆነች ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሥራውን ፡ እናደንቃለን ።

ባስልዮስ ፡ ዘቂሣርያ ፡ የሠራው ፡ ትሩፋቱና ፡ ገድሉ ፡ የበዛ ፡ እንደሆነ ፡ ብፁዕ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ፡ የክርስቶስን፡ አክሊለ ፡ ሦክ፡ ከተቀበሉ ፡ ጀምረው ፡ የሠሩት፡ ትሩፋትና ፡ ገድል ፡ የበዛ ፡ ነውና ፡ ባስልዮስ ፡ ዘቂሣርያ ፡ ለቂሣርያ ፡ ዐምደ ፡ ብርሃን ፡ እንደሆነ ፤ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ዘኢትዮጵያም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ዐምደ ፡ ብርሃን ፡ ናቸው ። በስም ፤ በትዕግሥት ፤ በየዋሃት ፤ በኂሩት ፤ በኀድአት ፡ ሁለቱም፡ የተመሳሰሉ፡ በመሆናቸው ፡ ባስልዮስ ፡ ዘቂሣርያ ፡ ባረፈበት ፡ ቀን ፤ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳትነት ፡ በመሾማቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ በስም ፡ ላይ ፡ ስምን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሥራን ፡ መግለጡን ፡ እንመልከት ።

ከጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ በፊት ፡ የሮም ፤ የእስክንድርያ ፤ የአንጾኪያ ፤ የኤፌሶን፡ ፬ቱ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ በኦርቶዶክሳዊት ፡ ሃይማኖት ፡ ጸንተው ፤ ተባብረው ፡ እየተላላኩ ፡ ሃይማኖተ ፡ አበውን ፡ ጽፈዋል ።

የዚህም ፡ ማስረጃ ፡ አቡሊዲስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሮሜ ፡ ናጣሊስ ፡ (ብሩህ ፡ ማኅቶት) ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሮሜ ፤ ሰለባስትርዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሮሜ ፡ እነዚህ ፡ ሦስቱ ፡ ሮማውያን ፡ (ኦርቶዶክሳውያን) ፡ ተላልከው ፡ የጻፉት ፡ የተዋሕዶ ፡ ሃይማኖት ፡ በሃይማኖተ ፡ አበው ፡ ውስጥ ፡ አለ ።

በዚህ ፡ ልማድ ፡ ከእለ ፡ እስክንድሮስ ፡ ቀጥሎ ፡ በእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስነት ፡ የተሾመው ፡ አትናትዮስ ፡ የጳውሎስንና ፡ የጴጥሮስን ፡ መቃብር ፡ እጅ ፡ ለመንሣት ፡ ሮም ፡ ሔዶ ፡ «ሰላም ፡ ለክሙ ፡ ብፁዓን ፡ ሐዋርያት» ፡ ብሎ ፡ መቃብራቸውን ፡ እጅ ፡ ቢነሣ ፤ « ለከሂ ፡ ይብሉከ ፡ ሐዋርያ» ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ከመቃብራቸው፡ ተሰማ ። ስለዚህ ፡ በሃይማኖተ ፡ አበው ፡ ካሉት ፡ ሊቃውንት ፡ ሁሉ ፡ ተለይቶ፡አትናትዮስ ፡ ሐዋርያዊ ፡ ተባለ ። ታሪክና ፡ ታሪክ ፡ ሲገጥም ፡ አይታለፍምና ፡ በአብርሀ ፡ ወአጽብሐ ፡ መሥራችነት ፡ የኢትዮጵያውያንን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስነት ፡ መሾም ፡ የጀመረ ፡ አትናትዮስ ፡ ሐዋርያዊ ፡ ስለሆነ ፡ ዛሬም ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ፈጻሚነት ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ እስክንድርያ ፡ ሔደው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳትነት ፡ ከተሾሙ ፤ በአትናትዮስ ፡ የግብር ፡ ስም ፤ ባስልዮስ ፡ ሐዋርያዊ፡መባል፡ይገባቸዋል።



ቅዱስ ፡ ጳውሎስን ፡ ጌታ ፡ በፍና ፡ ደማስቆ ፡ መርጦ ፡ "ሖር ፡ ከመ ፡ ትጹር ፡ ስምየ) ፡ ሒድ ፡ በስሜ ፡ አስተምር ፡ ቢለው ፡ እምጳውሎስ ፡ ገብሩ ፡ ወሐዋርያሁ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ብሎ ፡ እየጻፈ ፡ አስተምሯል ።

ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ በንጽሕና ፤ በድንግልና ፤ በሃይማኖት ፤ በምግባር ፡ ፍጹም ፡ ሆነው፡ተገኝተው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስነት ፡ ጌታ ፡ እንደ ፡ ጳውሎስ ፡ ከመረጣቸው ፤ ሐዋርያሁ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ብላ ፡ እናታቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የምስጋና ፡ ደስታዋን ፡ ገልጣለች ።

ነቢየ ፡ ያነሥእ ፡ ለክሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡ እምአኃዊክሙ ፡
<u>ዘከማየ ፡ ወሎቱ ፡ ስምዕዎ ፡ ኵሎ ፡ ዘየቢለክሙ ።</u>

"ከተወላጆቻችሁ ፡ ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደኔ ፡ ያለ ፡ ነቢይ ፡ ያስነሣላችኋል " ብሎ ፡ ሙሴ ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፤ ከሱ ፡ ቀጥሎ ፡ ለሚነሣው ፡ ለኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፡ ትንቢት ፡ ተናግሮለት ፡ ነበር ። ኦሪ ፡ ዘዳ ፡ ም ፲፰ ፡ ቊ ፡ ፲፭ ፤ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ም ፫ ፡ ቊ ፡ ፳፪ ።

ይኸውም ፡ ትንቢት ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ሙሴ ፡ ካረፈ ፡ በኋላ ፤ ምስፍናው ፡ ለኢያሱ ፡ ተሰጠና ፡ በኢያሱ ፡ መሪነት ፡ እስራኤል ፤ እግዚአብሔር ፡ ለአባታቸው ፡ ለአብርሃም ፡ የሰጠውን ፡ ርስታቸው ፡ ከነዓንን ፡ ወርሰው ፡ ኖረዋል ።

የፊተኛው ፡ ምሳሌ ፡ ለኋለኛው ፡ ምሳሌ ፡ መጽሔት ፡ (መስታዋት) ፡ በመሆኑ ፤ ሙሴ ፡ የተናገረው ፡ ተስፋ ፡ በእስራኤል ፡ ተወላጅ ፤ በኢያሱ ፡ እንደተፈጸመ ፤ በአብርሀና ፡ አጽብሐ ፡ የተመሠረተው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተወላጅ ፡ ሢመተ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ "ሲገጥም ፡ ዕድልና ፡ ዕድል ፤ ይገኛል ፡ ድል" ፡ እንደተባለው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴና ፡ የሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ የብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ዕድል፡ ስለገጠመ ፤ ሰላማዊው፡ ክርክር ፡ በተመሠረተ ፡ በሺ፮፻፲፫ ፡ ዘመን ፡ ተፈጽሞልና ፡ የፊተኛው፡ ምሳሌ ፡ ለኋለኛው፡ ምሳሌ፡ መጽሔት፡ መሆኑ ፤ በጕልህ፡ ተገለጠ ።

እንዳልነውም ፡ በእስራኤል ፡ ተወላጅ ፡ በኢያሱ ፡ የተፈጸመው ፡ ተስፋ ፡ በጊዜው ፡ ሲገለጥ ፡ የደመቀ ፡ እንደነበረ ፤ በኢትዮጵያ ፡ ተወላጅ ፡ በብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ላይ ፡ የተፈጸመው ፡ የሢመተ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፤ ተስፋም ፡ ጥር ፡ ፮ ቀን ፡ ሲፈጸም ፡ ጕልህነቱ ፡ ከመላው ፡ ዓለም ፡ የማይሠወር ፡ ሆነ ፤ ስለዚህ ፡ በብር ፡ ሥራ ላይ ፡ የተቀባ ፡ የወርቅ ፡ ሥራ ፡ ሲያንጸባርቅ ፡ እንዲኖር ፤ ይህ ፡ የኢትዮጵያዊ፡ ሢመተ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ታሪክም ፤ ዓለም ፡ እስኪያልፍ ፡ የዕውቀት ፡ ብርሃንን ፡ ሲሰጥ ፡ ይኖራል ።

ከዚህ ፡ አያይዘን ፡ ለብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ የተደረገውን ፡
<u>ያቀባበሉን ፡ ሥርዓት ፡ እናስከትላለን ።</u>

ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ በሕዝብ ፡ ተመርጠው ፡ ከሔዱበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ሕዝቡ ፡ የሚመጡበትን ፡ ሰዓት ፡ በናፍቆት ፡ ይጠብቅ ፡ ጀመር ።

www.ethiopianorthodox.org

እንዲያውም ፡ አብዛኛው ፡ ሕዝብ ፡ ለጥምቀት ፡ በዓል ፡ ይገቡና ፡ በበዓሉ ፡ ይገኛሉ ፤ እያለ ፡ ይጓጓ ፡ ነበር ። ዜና ፡ ሚመታቸው ፤ በራዲዮ ፡ እንደመሰማቱ ፤ ያመጣጣቸው ፡ ዜና ፡ ጥር ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ በ፲ ፡ ሰዓት ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ተነግሮ ፡ ነበርና ፡ በዚሁ ፡ ቀንና ፡ ሰዓት ፡ የከተማው ፡ ሕዝብ ፡ በብዛት ፡ በአይሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ ተሰብስቦ ፡ ይጠባበቅ ፡ ጀመር ።

አይሮፕላኑ ፡ ከተባለው ፡ ሰዓት ፡ እልፍ ፡ ስላለ ፡ ሕዝቡ ፡ ስለመንገዳቸው ፡ በብርቱ ፡ አሳብ ፡ ሲያወጣ ፡ ሲያወርድ ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ ፲፩ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ሲሆን ፡ አይሮፕላኑ ፡ ብቅ ፡ ሲል ፡ ሕዝቡ ፡ ከደስታው ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ወደ ፡ አየሩ ፡ ወጥቶ ፡ የሚቀበላቸው ፡ መሰለ ።

ለመቀበልም ፡ ወደአይሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ የወረዱት ፡ ልዑል ፡ መኰንን ፡ መስፍነ ፡ ሐረር ፤ ብፁዓን ፡ ጳጳሳት ፡ በሙሉ ፤ ሊቃውንትና ፡ መምህራን ፤ አንድ ፡ ሳይለይ ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋራ ፡ የአይሮፕላኑን ፡ ሜዳ ፡ መልተውት ፡ ነበርና ፡ አይሮፕላኑ ፡ ገና ፡ ምድር ፡ ሲነካ ፡ መስቀላቸውን ፡ ለመሳለም ፡ ሕዝቡ ፡ ይዘጋጁ ፡ ጀመር ።

አኤሮፕላኑ ፡ ዐርፎ ፡ መዝጊያው ፡ ሲከፈት ፡ ልዑል ፡ መኰንን ፡ መስፍነ ፡ ሐረር ፡ ወደአይሮፕላኑ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ የግርማዊነታቸውን ፡ የመልካም ፡ ምኞት ፡ መልእክት ፡ ለብፁዕነታቸው ፡ አቀረቡ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፤ ስለብፁዕነታቸው ፡ ክብር ፡ ከዚያ ፡ የተሰለፉት ፡ አንድ ፡ ጓድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ በሚገባ ፡ ሰላምታ ፡ ሰጡ ።

አቡነ ፡ ባስልዮስም ፤ እየዞሩ ፡ ሕዝቡን ፡ ባረኩ ። እንዲሁም ፡ ሕዝቡን ፡ እየባረኩ ፡ አልፈው ፡ በተዘጋጀላቸው ፡ ቦታ ፡ ሲቆሙ ፡ ሁሉም ፡ እየቀረበ ፡ መስቀል ፡ ተሳለመ ። ከዚህም ፡ ወዲያ ፡ በልዩ ፡ አውቶሞቢል ፡ ሆነው ፡ ወደታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ጕዘው ፡ በቀጠለ ፡ ጊዜ ፤ የተከታዮቹ ፡ አውቶሞቢል ፡ አበዛዝና ፡ የጕዘው ፡ ተራ ፡ የሚያስገርም ፡ ሆኖ ፡ ይታይ ፡ ነበር ።

ወደታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥትም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፤ የተሰበሰቡት ፡ ሊቃውንትና ፡ መምህራን ፤ ቀሳውስትና ፡ ዲያቆናት ፡ በደስታ ፡ ተቀበሏቸው ። እንዲሁም ፡ በዚሁ ፡ የተሰለፉ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ የክብር ፡ ዘበኞች ፡ የክብር ፡ ሰላምታ ፡ ሰጡ ።

ወደ ፤ ቤተ ፡ መንግሥቱም ፡ ገብተው ፡ ልዑላን ፡ መሳፍንትና ፡ ክቡራን ፡ ሚኒስትሮች ፡ ታላላቅ ፡ መኳንንትና ፡ የውጪ ፡ አገር ፡ መንግሥታት ፡ እንደራሴዎች ፡ ባሉበት ፡ ወደግርማዊነታቸውና ፡ ወደግርማዊት ፡ ዙፋን ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ የቡራኬ ፡ ሰላምታ ፡ ሰጡ ።

---

ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሊቀ ፡ ጵጵስናን ፡ መብት ፡ ከተረከቡበት ፡ ጊዜ ፡ ከ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ም ፡ ጀምሮ ፡ በመሳፍንትና ፡ በመኳንንት ፤ በመምህራንና ፡ በሊቃውንት ፤ በካህናትና ፡ በሕዝብ ፡ ድምፅ ፡ ተመርጠው ፡ በብፁዕነታቸው ፡ ቡራኬ ፡ የተሾሙ ፡ ጳጳሳት ።



## በአንደኛው ፡ ምርጫ ።

| | |
|---|---|
| ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ገብርኤል ፡ | ጳጳስ ፡ ዘወሎ ። |
| ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ታዴዎስ ፡ | " ዘኢሉባቦር ። |
| ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ | " ዘከፋ ። |
| ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ማርቆስ ፡ | " ዘኤርትራ ። |
| ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ፊልጶስ ፡ | " ዘኢየሩሳሌም ። |

## በሁለተኛው ፡ ምርጫ ።

| | |
|---|---|
| ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ማርቆስ ፡ | ጳጳስ ፡ ዘጐጃም ። |
| ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ሉቃስ ፡ | " ዘአሩሲ ። |
| ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ሳዊሮስ | " ዘገሙ ፡ ጐፋ ። |

## በሦስተኛው ፡ ምርጫ ።

| | |
|---|---|
| ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ዮሐንስ ፡ | ጳጳስ ፡ ዘትግሬ ። |

ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተመለከተው ፡ በኢትዮጵያዊው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ቀባዒነት ፤ የጵጵስና ፡ መዐርግ ፡ ተቀብለዋል ።

---

## ብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ የደብር ፡ ቅዱስ ፡ (ደብረ ፡ ጽጌን ፡) መሠረት ፡ ጣሉ ።

ብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በዕጨጌነታቸው ፡ ዘመን ፡ በደብር ፡ ቅዱስ ፡ (ደብረ ፡ ጽጌ) ፡ መጠነኛ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ማሳነጻቸውን ፡ ተናግረን ፡ ነበርና ፡ አሁን ፡ የምንቀጥለው ፡ የአዲሱን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መመሥረት ፡ ነው ።

ሆኖም ፤ የደብር ፡ ቅዱስን ፡ (የደብረ ፡ ጽጌን ፡) መሠረት ፡ በጸሎት ፡ ቡራኬ ፡ ለመወጠን ፡ ስላሰቡ ፤ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ፡ ም፡ መስከረም ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ ከነግሁ ፡ በሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ የትግሬ ፡ ሀገረ ፡ ስብከት ፡ ጳጳስ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ዮሐንስንና ፡ የዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ መታሰቢያ ፡ ቤት ፡ አስተዳዳሪ ፡ ክቡር ፡ ሊቀ ፡ ሊቃውንት ፡ መሐሪ ፡ ትርፌን ፤ ሌሎችን ፡ የቤተ ፡ ክህነትን ፡ ሠራተኞችም ፡ አስከትለው ፡ ከሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ግቢ ፡ ተነሡና ፡ በሁለት ፡ ሰዓት ፡ ከሩብ ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ ደረሱ ።

ከመኪናው ፡ ላይ ፡ ሲወርዱም ፡ ልዩ ፡ ጸሐፊያቸው ፡ አቶ ፡ ብሥራት ፤ ማስረሻና ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገዳም ፡ ሹም ፡ ፀባቴ ፡ ብርሃነ ፡ መስቀል ፡ እንዲሁም ፡ አዛዥ ፡ ባየህ ፡ ካህናቱንና ፡ ምእመናኑን ፡ መምህራኑንና ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ አሰልፈው ፡ አሥራ ፡ አራት ፡ ልዑካንም ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖ ፡ አስለብሰው ፡ ተቀበሏቸው ።

ብፁዕ ፡ አባታችንም ፡ የሕሊና ፡ ጸሎት ፡ ካደረሱ ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈው ፡ ድርጅት ፡ በተራው ፡ ተከናወነ ።

www.ethiopianorthodox.org

በሦስት ፡ ሰዓት ፡ በሕንጻው. መከከል ፡ የጸሎቱ ፡ ሥርዓት ፡ በብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ጀማሪነት ፡ ቀጠለና ፡ ወንጌለ ፡ ዮሐንስ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፤ መዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ተዘለቀ ። ወዲያውም ፡ ውዳሴ ፡ ማርያም ፡ ተደገመና ፡ ነአኰቶ ፡ በመነኰሳቱ ፡ ተደረሰ ።

ብፁዕ ፡ ሊ.ቀ ፡ ጳጳሳትም ፡ ፍትሐት ፡ ዘወልድን ፡ ደገሙ ። ልብሰ ፡ ተክህኖ ፡ የለበሰው ፡ ዲያቆንም ፡ ከቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ «አስተበቍዐክሙ ፡ አኃዊነ ፡ ሙቁሐ ፡ ለክርስቶስ» ፡ የሚለውን ፡ አነበበ ፡ ኤፌሶን ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፩–፳፫።

## ም ስ ባ ክ።

ደብረ ፡ ጽዮን ፡ ዘአፍቀረ ። ሐነጸ ፡ መቅደሶ ፡ በአርያም። ወሣረረ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ዘለዓለም ።

## ወ ን ጌ ል።

ብፁዕ ፡ ሊ.ቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ከማቴዎስ ፡ ወንጌል ፡ «ወበጺሖ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ቂሣርያ» ፡ የሚለውን ፡ አነበቡ ።

«ወአንሰ ፡ እብለከ ፡ ከመ ፡ አንተ ፡ ኰኵሕ ፡ ወዲበ ፡ ዛቲ ፡ ኰኵሕ ፡ አሐንጻ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያንየ ፡ ወአናቅጸ ፡ ሲኦል ፡ ኢይኄይልዋ» ፡ የሚለውን ፡ ኃይለ ፡ ቃል ባነበቡ ፡ ጊዜም ፡ የወንጌሉ ፡ ምሥጢር ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሕንጻ ፡ አመሠራረት ፡ የተገባ ፡ በመሆኑ ፡ እጅግ ፡ ተደነቀ ። ማቴ ፡ ም ፡ ፲፮ ፡ ቍጥር ፤ ፲፫–፳፪ ።

ከዚህ ፡ በኋላም ፡ ወካዕበ ፡ ናስተበቍዓ ፡ ለንግሥተ ፡ ኵልነ ፡ ማርያም ፡ እምነ ፡ ወእሙ ፡ ለእግዚእነ ፡ ተባለና ፡ አራት ፡ መቶ ፡ እግዚኦታ ፡ ደረሰ ።

ቀጥሎም ፡ ኪዳን ፡ በአራራይ ዜማ ፡ ተጀመረና ፡ ተደገመ ። ወዲያው ፡ ብፁዕ ፡ ሊ.ቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ጸሎተ ፡ ቡራኬ ፡ ሰጥተው ፡ አሳረጉ ።

ከዚ.ህም ፡ ቀጥለው ፡ መዘምራኑ «ሐነጽዋ ፡ ወሣረርዋ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ አርአያ ፡ ዘበሰማያት ፡ ወከመ ፡ ትኩን ፡ ምስትሥራየ ፡ ኃጢ.አት ፡ ዳዊትኒ ፡ ይቤ ፡ ዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ምዕራፍየ ፡ ለዓለም» ፡ እያሉ ፡ ዘምረዋል ።

## በብፁዕነታቸው ፡ ቅዱሳት ፡ እጆች ፡ የመታሰቢያዎቹ ፡ አቀማመጥ ።

ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ በተመሠረተበት ፡ መስከረም ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ም ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ሊ.ቀ ጳጳሳት ፡ ዘኢ.ትዮጵያ ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ በመሠረቱ ፡ ላይ ፡ የሚደርሰው ፡ ሥርዓተ ፡ ጸሎት ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፤ ለአራት ፡ ሰዓት ፡ ሩብ ፡ ጉዳይ ፡ ሲሆን ፡ ከዚ.ህ ፡ ቀጥለው ፡ የተዘረዘሩትን ፡ የክብር ፡ መታሰቢያዎች ፡ በመሠረቱ ፡ ውስጥ ፡ አኑረዋል ።

፩ኛ ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ በደወል ፡ ቤቱ ፡ መግቢያ ፡ በር ፡ ሥር ፡ በወደ ቀኝ ፡ ወገን ፡ በመሠረቱ ፡ ውስጥ ፡ በጥርብ ፡ ድንጋይ ፡ ሣጥን ፡ ስፋቱ ፡ ፸ ፡ በ፵ ፡



ሳንቲ ፡ ሜትር ፡ በሆነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ መስቀል ፤ ወርቅ ፡ ቅብ ፤ አንድ ፡ የብር ፡ ጽና ፤ አንድ ፡ የብር ፡ መቋሚያ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ጸናጽል ፤ አንድ ፡ ቢልቃጥ ፤ የዮርዳኖስ ፡ አፈር„ ፡ አንድ ቢልቃጥ ፡ የዮርዳኖስ ፡ ጠበል ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ የመጣ ፤ አንድ ፡ ቢልቃጥ ፡ ሜሮን ፤ በንዋያተ ፡ ቅድሳቱ ፡ ላይም ፤ «አባ ፡ ባስልዮስ ፡ ሊ.ቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘኢ.ትዮጵያ„ ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መስከረም ፡ ፲፯ ፡ ቀን የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ አለባቸው ።

፪ኛ ፡ በምዕራቡ ፡ በኩል ፡ በዋናው ፡ መቅደስ ፡ መግቢያ ፡ በር ፡ ሥር ፡ ከመሠረቱ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ፷ ፡ × በ፴ ፡ ሣንቲ ፡ ሜትር ፡ ስፋት ፡ ባለው ፡ በጥርብ ፡ ድንጋይ ፡ ሣጥን ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ጽዋ ፤ የግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ አፄ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢ.ትዮጵያና ፡ የግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነን ፡ መልክ ፡ የተቀረጸበት ፡ አራት ፡ ካራት ፡ ወርቅ ፤ የዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ መልክ ፡ ያለበት ፡ አንድ ፡ ሩብ ፡ ወርቅ) ፡ አራት ፡ ጥንታውያን ፡ የአክሱም ፡ አንቲካዎች) ፡ ከአንድ ፡ እስከ ፡ አሥር ፡ የኢ.ትዮጵያ ፡ ብሮችና ፤ ከመዳብና ፡ ከብር ፡ የተሠሩ ፡ በያይነቱ ፡ ሣንቲሞች( ፡ አንድ ፡ ቢልቃጥ ፡ ሜሮን ፤ ያለበት ።

፫ኛ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ በክቡ ፡ መቅደስ ፡ ላይ ፡ በመስኮቶቹ ፡ አቅጣጫ ፡ በመሠረቱ ፡ ውስጥ ፡ ፵ ፡ × በ፳፰ ፡ ሣንቲ ፡ ሜትር ፡ ስፋት ፡ ባለው ፡ በድንጋይ ፡ ሣጥን ፡ ስለቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ አመሠራረት ፡ የተጻፈ ፡ አራት ፡ ጥቅል ፡ ወረቀትና ፡ አራት ፡ ካራት ፡ ወርቅ ፤ የተገዛበት ፡ ፋክቱር ፡ ያለበት ። ከዚ.ህ ፡ በላይ ፡ የተጻፉትን ፡ ንዋያተ ፡ ቅድሳትና ፡ አንቲካዎች ፡ የያዙ ፡ ሦስት ፡ የመሠረት ፡ ድንጋዮች ፡ አኑረዋል ።

የአመሠራረቱ ፡ ድርጅት ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ብፁዕ ፡ ሊ.ቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ለመቅድስነት ፡ ከተመረጡት ፡ ሥፍራዎች ፡ በማዕከላዊው ፡ መቅደሳዊ ፡ ሕንጻ ፡ ላይ ፡ ቅዱስ ፡ መስቀልን ፡ ይዘው ፡ ቆመው ፡ አራቱን ፡ መዓዝናት ፡ ባረኩና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ንግግሮች ፡ ተደረጉ ።

## ኀይሉ ፡ ተክሉ ፡ የተባለው ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ያደረገው ፡ ንግግር ።

በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አሐዱ ፡ አምላክ ፡ አሜን ።

ብፁዕ ፡ ሊ.ቀ ፡ ጳጳሳትና ፡ ብፁዓን ፡ አባቶች ፡ ሆይ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ዕድል ፡ በዛሬዪቱ ፡ ቀን ፤ የገጠማችሁ ፡ በሀገሩ ፡ የምትገኙ ፡ ምዕመናንና ፡ ተማሪዎች ፡ ሆይ ።

«ደብር ፡ ቅዱስ ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ ማርያም» ፡ ተብላ ፡ በተሰየመችው ፡ በታ ፡ ላይ ፡ ይህ ፡ መሠረት ፡ በሚጣልበት ፡ ቀን ፡ ንግግር ፡ እንዳደርግ ፡ ላበቃኝ ፡ አምላክ ፡ የንግግሬን ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ከመቀጠሌ ፡ በፊት ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ምሥጋናዬን ፡ ሳቀርብለት ፡ የሚሰማኝ ፡ ደስታ ፡ ወሰን ፡ የለውም ።

www.ethiopianorthodox.org

## ብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ሆይ ።

ከብዙ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ በዚች ፡ በተቀደሰችው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ትን ቢት ፡ እንደ ፡ ተነገረና ፡ ብዙ ፡ ታላላቅ ፡ ሥራዎች ፡ እንደተሠሩ ፡ ታሪክ ፡ በሰፊው ፡ በመ ነገሩ ፡ ብዙ ፡ ሐተታ ፡ ስለ ፡ ማያስፈልግ ፡ ከተሠሩት ፡ ታላላቅ ፡ ታሪኮች ፡ ውስጥ ፡ ለምስክር ፡ ያህል ፡ በትንሹ ፡ እንድገልጽ ፡ መንፈሴ ፡ ያስገድደኛል ።

አንደኛ/ ትልቁ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሐዋርያ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማ ኖት ፡ ብዙ ፡ ተአምራት ፡ እንደሠሩበት ፡ ስለሳቸው ፡ በተጻፈው ፡ መልክ ፡ ውስጥ ፡ ተአምራቱ ፡ ከነሀገሪቱ ፡ ስም ፡ ተጽፎ ፡ እንደሚገኝ ፡ ለማንም ፤ የተሰወረ ፡ መስሎ ፡ አይታይም ።

ሁለተኛ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ እንደብፁዕነትዎ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሠርተው ፡ ላሁኑ ፡ ትውልድ ፡ በዚች ቦታ ፡ ባያበረክቱም ፤ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሥራ ፡ እስኪደርስ ፡ በድንኳን ፡ እንዳስቀደሱ ፡ በዚሁ ፡ ቦታ ፡ የተገኘው ፤ ንዋየ ፡ ቅድሳትና ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲ ያኑ ፡ ሕንጻ የሚሆን ፡ ድንጋይ ፡ መሰብሰባቸውን ፡ በዚችው ፡ ቦታ ፡ በገዳሟ ፡ አቅራቢያ ፡ (በምንጭ ፡ አጠገብ ፡ ተከምሮ ፡ የሚታየው ፡ ድንጋይ ፡ በቂ ምስክር ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

## ብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ሆይ ።

ስለዚች ፡ ቦታ ፡ የሚነገረው ፡ ትንቢትና ፡ ሊደረጉ ፡ ተሞክረው ፡ ሳይደረጉ ፡ የቀሩት ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃዱ ፡ ሆኖ ፡ በብፁዕነትዎ ፡ ጊዜ ፡ ትንቢቱ ፡ ተፈጽሞ ፡ በወዳጅዎ ፡ በቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ስም ፡ ይህንን ፡ የመሠረት ፡ ድንጋይ ፡ ሲያኖሩበት ፡ የጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መወለድ ፡ በነቢያት ፡ ሲነገር ፡ የነበረው ፡ ትንቢት ፡ ባዚን ፡ የሚባለው ፡ ንጉሥ ፡ በነገሠበት ፡ ዘመን ፡ የነቢያት ፡ ትንቢት ፡ በሱ ፡ ዘመን ፡ እንደተፈጸመ ፡ እንዲ ሁም ፡ ይህን ፡ የመሰለው ፡ የተመልካቾች ፡ አእምሮ ፡ የሚያድር ፡ ሥራ ፡ በመ ሠራቱ ፡ የብፁዕነትዎን ፡ ታሪክ ፡ ከባዚን ፡ ማነጻጸር ፡ ግዴታ ፡ ይሆንብኛል ።

## ብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ሆይ ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ የብፁዕነትዎ ፡ አሳብ ፡ ሁልጊዜ ፡ ይህንን ፡ የመሰለው ፡ ለመጪው ፡ ትውልድ ፡ ቋሚ ፡ ሆኖ ፡ እንዲገኝ ፡ የሚገባውን ፡ ሥራ ፡ ለመሥ ራት ፡ ቢሆንም ፡ በዚች ፡ በዛሬዪቱ ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ብፁዕነትዎ ፡ በፈጣሪዎ ፡ ቃል ፡ ከመጥፎ ፡ ምግባር ፡ እየመለሰ ፡ እንዲያሳድጋቸው ፡ ለተቀበሏቸው ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ ወደፈጣሪዎ ፡ የሚያገናኛቸውን ፡ አዲስ ፡ በር ፡ ለኦርቶዶክሳውያን ፡ ልጆችዋ ፡ ከፈቱላቸው ፡ ብል ፡ ስሕተት ፡ መስሎ ፡ አይታይም ።

ይህንንም ፡ ለማለት ፡ የደፈርኹበት ፡ ሰሎሞን ፡ በዘመኑ ፡ ለሚገኙት ፡ ምዕመናን ፡ በመጀመሪያ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሠርቶ ፡ ብዙ ፡ ምዕመናን ፡ እንደ



ተጠቀሙበት ፡ ስለሰሎሞን ፡ ታሪክ ፡ በተጻፈው ፡ መጽሐፍ ፡ ስለሚገኝ ፡ ሐተታ ፡ አላበዛም ።

## ብ ፁ ዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳ ጳ ሳ ት ሆ ይ ።

እግዚአብሔር ፡ ይህንን ፡ ዓለም ሲፈጥር ፡ እኛ ፡ ፍጥረቶቹ ፡ በማንኛውም ፡ ረገድ ፡ እንዳንቸገር ፡ ለማድረግ ፡ ምድርን ፡ መፍጠሩ ፡ ከችግር ለመዳኛ ፡ ነው ። ይህንኑም ፡ ከእኛ ፡ በፊት ፡ እነሱን ፡ በመፍጠሩ ፡ ለመገንዘብ ፡ እንችላለን ። እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ብፁዕነትዎ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ ከመሥራቱ ፡ በፊት ፡ በዚህ ፡ ለሚገኙት ፡ ምዕ መናንና ፡ ተማሪዎች ፡ ለችግራቸው ፡ ማቃለያ ፡ ያሠሩት ፡ ገዳምና ፡ የሰጡት ፡ ሀብት ፡ በዚሁ ፡ ቦታ ፡ አስተዳደር ፡ ውስጥ ፡ በሰፊው ፡ ተጽፎ ፡ ስለሚገኝ ፤ አንድ ፡ በአ ንድ ፡ በመዘርዘር ፡ የብፁዕነትዎን ፡ ወርቅ ፡ የሆነ ፡ ጊዜ ፡ ለማጥፋት ፡ አልፈቅድም ።

## ብ ፁ ዕ ፡ ሊ ቀ ፡ ጳ ጳ ሳ ት ፡ ሆይ ።

ይህ ፡ በብፁዕነትዎ ፡ ትጋትና ፡ ሰፊ ፡ ችሮታ ፡ ተጀምሮ ፡ የምናየው ፡ ሕንጻ ፡ በአማረ ፡ አኳኋን ፡ አልቆ ፡ ብፁዕነትዎ ፡ ወደ ፡ አሰበው ፡ ግብ ፡ እንዲደርስ ፡ የየአ ንዳንዳችን ፡ ምኞት ፡ መሆኑን ፡ እንድንገልጽልዎ ፡ እወዳለሁ ።

ሁሉን ፡ ለማድረግ ፡ የሚችል ፡ ጥበበኛ ፤ የነገሥታት ፡ ንጉሥ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእናቱ ፡ ስም ፡ የመሠረቱትን ፡ ሕንጻ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለመፈጸምና ፡ ዋጋዎን ፡ ለማግኘት ፡ እንዲያበቃዎ ፡ ጸሎታችን ፡ አያቋርጥም ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፤ ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፤ ዕድሜ ፡ ለብ ፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ። የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በኦር ቶዶክስ ፡ ሃይማኖቷ ፡ ኰርታ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ። አሜን ።

## ፀ ባ ቴ ፡ ኃ ይ ለ ፡ መ ስ ቀ ል ፡ የ ተ ና ገ ሩ ት ።

## በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ዱ ፡ አምላክ ፡ አሜን ።

«ወበከመ ፡ ጸጋሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘወሀበኒ ፡ አስተናደፍከ ፡ መሠረተ ፡ ከመ ፡ ጠቢብ ፡ ሊቀ ፡ ጸረብት ። ወባሕቱ ፡ አልቦ ፡ ካልዕ ፡ ዘይሔድሳ ፡ ለሕንጸት ፡ ወኵሉ ፡ ለይትዐቀብ ፡ ዘከመ ፡ የሐንጽ ፡ ወካልእሰ ፡ መሠረተ ፡ አልቦ ፡ ዘይክል ፡ ሣርሮ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘተሣረረ ። ወመሠረቱኒ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ውእቱ ። እመቦ ፡ ዘየሐ ንጽ ፡ ዲበ ፡ ዝንቱ ፡ መሠረት ፡ ወርቀ ፡ ወብሩረ ፡ ወዕብነ ፡ ክቡረ ፡ ወዕፀ ፡ ለለ፩ዱ ፡ ይትከሠት ፡ ምግባሩ ።

## ብ ፁ ዕ ፡ ሆ ይ ።

የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ እንደተሰጠዎ ፡ መጠን ፡ እንደብልህ ፡ ገበዝ ፡ አምባ ፡ ያማረ ፡ መሠረትን ፡ መሠረቱ ፤ እያንዳንዱ ፡ ግን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ እንዲያንጽ ፡ ይጠንቀቅ ። ከተመሠረተው ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ ሌላ ፡ መሠረት ፡ ሊመሠርት ፡ አይችልም ።

www.ethiopianorthodox.org

ይኸንንም ፡ መሠረት ፡ በብፁዕነትዎ ፡ አድሮ ፡ የመሠረተው ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ የሆነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው” ፤ ማንም ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ በወርቅም ፡ ቢሆን ፡ በብርም ፡ በከበረ ፡ ድንጋይም ፡ በዕንጨትም ፡ ቢያንጽ ፡ ለያንዳንዱ ፡ በጎ ፡ የሆነ ፡ ሥራው ፡ ይገለጻል» ፡ ብሎ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ለቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ በመጀመሪያ ፡ መልእክቱ ፡ ፫ ምዕራፍ ፡ ፲ ቍጥር ፡ እስከ ፡ ፲፫ ፡ የጻፈውን ፡ ለንግግሬ ፡ መነሻ ፡ አደርጋለሁ ።

## ብ ፁ ዕ ሆ ይ ።

እግዚአብሔር ፡ በሰጠዎ ፡ ሐዋርያነት ፡ ቸር ፡ ጠባቂ ፤ ሊቀ ፡ መምህራን ፡ እንደመሆንዎ ፡ በዚች ፡ ቦታ ፡ በደንግል ፡ ማርያም ፡ ስም ፡ የሕንጻ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን መሠረት ፡ በዛሬው ፡ ቀን ፡ አስቀመጡ ።

ነገር ፡ ግን ፤ ይህን ፡ የጀመሩትን ፡ ሥራ ፡ ወደፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ የተስፋ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይረዳዎ ፡ ዘንድ ፡ የሁላችን ፡ ምኞት ፡ ስለሆነ ፤ ከዚህ ፡ ቀጥዬ የደብር ፡ ቅዱስ ፡ ደብረ ፡ ጽጌን ፡ ታሪክ ፡ ባጭሩ ፡ አስታውሳለሁ ። ደብር ፡ ቅዱስ ፡ የተባለ ፡ ቦታ ፡ ለገነት ፡ መቃረቢያ ፡ ሆኖ ፡ በኵረ ፡ ፍጥረት ፡ አዳም ፡ እንደነበረበት ።

ይህችም ፡ ደብር ፡ ቅዱስ ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ ማርያም ፡ ለታላቁ ፡ ሐዋርያ ፡ ለአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መከነ ፡ ዐጽም ፡ ለሆነችው ፡ ለቅድስት ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መቃረቢያ ፡ ከመሆኗም ፡ በላይ ፡ በጻድቁ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ የተመሠረተችና ፡ በኪደተ ፡ እግራቸው ፡ የተቀደሰች ፡ ስለሆነች„ ፤ “ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተሠርቶባት ፡ ምዕራፈ ፡ ጻድቃን ፡ ትሆናለች” ፡ እየተባለ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ትንቢት ፡ ሲነገርላት ፡ ይኖር ፡ ነበር ።

ይህንኑ ፡ ትንቢት ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ ከተነሡት ፡ ነገሥታትና ፡ ጳጳሳት ፡ በዚችው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ መታሰቢያ ፡ ለማቆም ፡ የተመኙ ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ዕድል ፡ በተለይ ፡ ለብፁዕነትዎ ፡ ብቻ ፡ የቆየ ፡ በመሆኑ ፡ ያሰቡት ፡ አሳብ ፡ ሳይፈጸም ፡ አረፍተ ፡ ዘመን ፡ ገቷቸው ፡ በሞት ፡ አልፈዋል ።

ብፁዕነትዎን ፡ ግን ፡ ዕድልና ፡ ጊዜ ፡ አጋጥሞት ፡ የተነገረው ፡ ትንቢት ፡ ዛሬ ፡ ተፈጽሞ ፡ አየነው ። አሁንም ፡ ይህንኑ ፡ የመንፈሳዊ ፡ አባትዎን ፡ ታሪክና ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ በመገንዘብ ፡ በእመቤታችን ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ስም ፡ የመሠረቱትን ፡ ሕንጻ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰላም ፡ አስፈጽሞ ፡ የመጨረሻውን ፡ ቅዳሴ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ ባርከው ፡ ለመቀደስና ፡ የደስታውን ፡ ሥነ ፡ በዓል ፡ ለሃይማኖት ፡ ልጆችዎ ፡ ለማካፈል ፡ እንዲአበቃዎ ፡ የሕሊና ፡ ምኞት ፡ እያቀረብኩ ፡ ቤተ፡ክርስቲያኒም ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ማደሪያ ፡ ሆና ፡ ባካባቢዋ ፡ የሚገኙትን ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ በሃይማኖተ ፡ ወንጌል ፡ ጠብቃ ፡ እንድትኖር ፡ ያድርግልን ፡ በውስጧም ፡ የሚጸለየው ፡ ጸሎትና ፡ የሚሠዋው ፡



መሥዋዕት ፡ ብፁዕነትዎን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ የሚጠብቅ ፤ በማያልፈው ፡ ዓለም ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ የሚያወርስ ፡ ያድርግልን ፡ አሜን ።

ዕድሜ ፡ ለብፁዕ ፡ አባታችን ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘኢትዮጵያ ።
» ለግርማዊ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡
» ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነን ።
ኢትዮጵያ ፡ ሀገራችን ፤ አርቶዶክስ ፡ ሃይማኖታችን ፡ በሰላም ፡ ተጠብቀው ፡ ይኑሩ ።

የአፈ ፡ ሊቀ ፡ ሊቃውንት ፡ አክሊሉ ፡ ገብረ ፡ ኪሮስ ፡

## ንግግርና ፡ „መወድስ ፡ ቅኔ„ ።

ብልሁ ፡ ሰሎሞን ፡ በጊዜ ፡ ለነሚት ፤ ወበ ፡ ጊዜ ፡ ለሐኒጽ ፡ (ለማፍረስ ፡ ጊዜ ፡ አለው ፤ ለማነጽም ፡ ጊዜ ፡ አለው ) ብሎ ፡ ተናግሮ ፡ ነበር ።

ቸር ፡ እግዚአብሔር ፡ የማፍረስን ፡ ጊዜ ፡ ለአረማውያንና ፡ ለዐላውያን ፡ ጠላቶቻችን ፡ ሰጥቶ ፤ የማነጽን ፡ ጊዜ ፡ አባቶቻችን ፡ ወገኖቻችን ፡ ክርስቲያን ፡ ለሆኑና ፤ በክርስትና ፡ ጸንተን ፡ ለምንገኝ ፡ ለእኛ ፡ አደለን ።

ይህም ፡ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መንበር ፡ (እጨጌነት ፡ ) ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ለአርቶዶክስ ፡ ሃይማኖት ፡ ቀናተኛ ፡ ለሆኑ ፡ ወላዲተ ፡ አምላክን ፡ በጥልቅ ፡ ፍቅር ፡ ለወደዱና ፡ የኢትዮጵያን ፡ መንፈሳዊ ፡ ባህል ፡ ላከበሩ ፡ መንፈሳውያን ፡ አበው ፡ ሲሰጥ ፡ የኖረ ፡ ነው ።

አሁንም ፡ እነዚህ ፡ ሦስቱ ፡ ሀብታት ፡ በብፁዕነታቸው ፡ ላይ ፡ አድረው ። በማየታችን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቸርነት ፤ የወላዲተ ፡ አምላክን ፡ ረድኤት ፡ እናደንቃለን ፡

ስለዚህ ፤ ሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ የኢትዮጵያ ፡ ምዕመናን ፡ የሚሳሱለትን ፡ የብፁዕነታቸውን ፡ ሕይወት ፡ በረቂቅ ፡ ክንዱ ፡ ደግፎ ፡ የዚህን ፡ ሕንጻ ፡ ፍጻሜ ፡ እንዲያሳይልን ፡ በኅብረት ፡ እንለምነው ።

## ቅኔ ።

ሠናያነ ፡ ዜና ፡ ባስልዮስ ፡ ወኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ላዕለ ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ አስምዑ ፡ ተዋሕዶቶሙ ፡ በሐተታ ።
እስመ ፡ እመቃብር ፡ ተንሥአት ፡ ሕንጻ ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ ጣቢታ ፡
በኃይለ ፡ ኂሩቶሙ ፡ ለክልኤቱ ።
ወኢይክሉ ፡ አዕይንተ ፡ ንስር ፡ ዕፀ ፡ ሐቅል ፡ ርእዮታ ፡
ለኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ወባስልዮስ ፡ እንዘ ፡ ሀብቶሙ ፡ ርእይ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሠናይታ ፡
አመ ፡ በጽሐ ፡ ለደብረ ፡ ጽጌ ፡ ጊዜ ፡ ተሐንጾታ ፡
መንክራተ ፡ ባስልዮስ ፡ መላእክት ፡ እለ ፡ ፍንዋን ፡ ለተልእኮታ ፡
የዐርጉ ፡ ላዕለ ፡ ወይወርዱ ፡ ውስቴታ ፡
እስመ ፡ ሠምሩ ፡ ዕበኒሃ ፤ ወዘአክበርዋ ፡ ለመሬታ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ባርከው ፡ አሳርገው ፡ ሠርሆተ ፡ ሕዝብ ፡ ሆነ ። ወዲያው ፡ ላገለገሉት ፡ ካህናት ፡ በቤተ ፡ ማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ግብሮ ፡ እንዲደረግ ፡ ለብፁዕነታቸው ፡ ልዩ ፡ ጸሐፊ ፡ ለአቶ ፡ ብሥራት ፡ ማስረሻ ፡ ትእዛዝ ፡ ተሰጠና ፡ ብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ከተከታዮቻቸው ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ተመለሱ ።

---

ብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከማታው ፤ በአንድ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ስለ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ልደት ፡

## ያ ስ ሙ ት ፡ ስ ብ ከ ት ።

«ወአመ ፡ ካዕበ ፡ ፈነዎ ፡ ለበኵር ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ይቤ ፡ ይስግዱ ፡ ሎቱ ፡ ኵሎሙ ፡ መላእክተ ፡ እግዚአብሔር ።

ወበእንተ ፡ መላእክቲሁ ፡ ይቤ ፡ ዘይሬስዮሙ ፤ ለመላእክቲሁ ፡ መንፈሰ ፡ ወለእለ ፡ ይትለአክዎ ፡ ነደ ፡ እሳት ።

ወበእንተ ፡ ወልዱሰ ፡ ይቤ ፤ መንበርከ ፡ እግዚኦ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ በትረ ፡ ጽድቅ ፡ ወበትረ ፡ መንግሥትከ ፡ ዕብ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፮–፱ ።

መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ በሃይማኖት ፡ የተከተላችሁ ፤ በስሙ ፡ የከበራችሁ ፤ የባሕርይ ፡ አምላክነቱንና ፡ ገዥነቱን ፡ አምናችሁ ፡ ልቡናችሁን ፡ በመንፈሳዊ ፡ ዕውቀት ፡ ያጸናችሁ ፡ ምእመናን ፡ ሆይ ።

ከሌላው ፡ ንግግሬ ፤ አስቀድሜ ፤ ሊቀ ፡ ሐዋርያቱ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፤ አምላካችንና ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ በማወቅ ፡ ሞገስና ፡ ሰላም ፡ ይብዛላችሁ ።

ወደ ፡ ሕይወትና ፡ ወደ ፡ ጽድቅ ፡ የሚያደርሰውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ለእኛ ፡ በሰጠን ፡ በመለኮቱ ፡ ኃይል ፡ ወደ ፡ ጌትነቱና ፡ ወደ ፡ ቸርነቱ ፡ የጠራን ፡ እሱ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ያሰማንን ፡ ብስራት ፡ እነሆ ፡ አሁን ፡ በዕለተ ፡ ልደቱ ፡ እናሰማችኋለን ፡ ፪ ፡ ጴጥ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፪–፬ ።

መድኃኒታችን ፡ እኛን ፡ ወደ ፡ ጌትነቱና ፡ ወደ ፡ ቸርነቱ ፡ ከመጥራቱ ፡ አስቀድሞ ፤ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ የምንናገረው ፡ የሚያሳዝን ፡ ውርደት ፡ በሰው ፡ ዘር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ምንም ፡ የታወቀ ፡ ቢሆን ፤ የፈጣሪያችን ፡ የመሐሪነቱንና ፡ የታዳጊነቱን ፡ ታላቅነት ፡ ለማስታወስ ፡ ያህል ፡ በጥቂቱ ፡ እንናገረዋለን ።

አዳምና ፡ ሔዋን ፤ ብርሃን ፡ ለብሰው ፡ ብርሃን ፡ ተጐናጽፈው ፡ ገነትን ፡ ወርሰው ፤ አዳም ፡ በጌትነት ፡ ሔዋን ፡ በእመቤትነት ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ከኖሩ ፡ በኋላ ፤ ዲያብሎስ ፡ በታዬን ፡ ወረሱብኝ ፤ ክብሬን ፡ ወሰዱብኝ ፡ በሚለት ፡ የሚቀናባቸው ፡ ሆኗል ።

ወዲያው ፡ ጸጋቸው ፡ የሚገፈፍበትን ፤ ክብራቸው ፡ የሚዋረድበትን ፡ ምክንያት ፡ ፈልጎ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ የተከለከሉትን ፡ ነገር ፡ በማስወደድ ፤ በኃጢአት ፡ እንዲወድቁ ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ረድኤት ፡ እንዲርቁ ፡ አድርጓል ።



የንጉሥ ፡ ባለሟል ፡ ሆኖ ፡ በንጉሥ ፡ ላይ ፡ የዐመፅ ፡ ሥራ ፡ ከሠሩ ፤ ያዋቂ ፡ አጥፌ ፡ ተብሎ ፡ ድርብ ፡ ፍርድ ፡ መቀበል ፡ እንደማይቀር ፡ የቀድሞው ፡ ባለሟልነትም ፡ የኋላውን ፡ ቅጣት ፡ እንዳያስቀረው ፤ አዳምና ፡ ሔዋን ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ከምድር ፡ በላይ ፡ ያለውን ፡ ፍጥረት ፡ ግዙ ፡ ንዱ ፡ ብሎ ፡ ታላቅ ፡ መብት ፡ የሰጣቸውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ በበደሉ ፡ ጊዜ ፤ የአምላካቸው ፡ የሱ ፡ ባሕርይ ፡ ርኅሩኅ ፡ ሲሆን ፤ በሞተ ፡ ሥጋ ፡ ላይ ፡ ሞተ ፡ ነፍስን ፤ በርደተ ፡ መቃብር ፡ ላይ ፡ ርደተ ፡ ገሃነምን ፡ አደራርቦ ፡ ፈረደባቸው ፡ እንጂ ፡ የቀድሞው ፡ ባለሟልነታቸውን ፡ አስቦ ፡ ርኅራኄ ፡ አላደረገላቸውም ።

ይህንን ፡ ከባድ ፡ ፍርድ ፡ ተቀብለው ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ ፋይድ ፡(አሁን ፡ እኛ ፡ ወደ ፡ አለንበት ፡ ዓለም)፡ ወርደው ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ያህል ፡ ኃጢአታቸውን ፡ እያሰቡ ፤ የቀድሞ ፡ ክብራቸውን ፤ የኋላ ፤ ኃሣራቸውን ፡ እያስታወሱ ፡ በመኖራቸው ፡ ርኅሩኅ ፡ ባሕርይ ፡ ፈጣሪያቸው ፡ ከቅድስት ፡ ድንግል ፡ ተወልጄ ፡ አድናችኋለሁ ፡ የሚል ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ አሰምቷቸዋል ።

በየጊዜው ፡ ያናገራቸውንም ፡ ተስፋ ፡ የሚፈጽምበት ፡ ዘመን ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፤ (አምስት ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ሲሞላ)፡ የአምላክ ፡ ቀጠሮ ፡ ጽኑ ፡ ነውና ፡ ካመታቱ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ከወራቱ ፡ አንድ ፡ ወር ፤ ከዕለታቱ ፡ አንድ ፡ ዕለት ፡ ከሰዓታቱ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ሳያሳልፍ ፡ መጋቢት ፡ ኻያ ፡ ዘጠኝ ፡ ቀን ፡ (እሑድ)፡ በሦስተኛው ፡ ሰዓተ ፡ መዓልት ፡ በእመቤታችን ፡ በቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ማሕጸን ፡ አድሮ ፡ ከሥጋዋ ፡ ሥጋን ፡ ከነፍሷ ፡ ነፍስን ፡ ነሥቶ ፡ ተዋሕዷል ።

እኛ ፡ ኦርቶዶክሳውያን ፤ ተዋሕዶ ፡ የምንለው ፡ ዋናው ፡ የሃይማኖታችን ፡ መሠረት ፡ ያለው ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ነው ። ቀዳማዊና ፡ አካላዊ ፡ የሆነ ፡ ቃል ፡ ሰውን ፡ ስለ ፡ መውደዱ ፡ ልዑል ፡ ባሕርዩን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ በእመቤታችን ፡ በድንግል ፡ ማርያም ፡ ማሕጸን ፡ በተጸነሰ ፡ ጊዜ ፤ ሰማይና ፡ ምድር ፡ የማይወስኑት ፡ ምሉዕ ፡ ስፉሕ ፡ ረቂቅ ፡ አምላክ ፡ ሲሆን ፤ ሥጋን ፡ በመዋሐዱ ፡ ግዙፍና ፡ ውሱን ፡ ሆነ ።

ሥጋ ፡ ግዙፍና ፡ ውሱን ፡ ሲሆን ፡ ቃልን ፡ በመዋሐዱ ፡ ምሉዕ ፡ ስፉሕና ፡ ረቂቅ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ሆነ ።

በጠቅላላውም ፡ ሊቁ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ (እንቲአሁ ፡ ለቃል ፡ ኮነ ፡ ለሥጋ ፡ ወእንቲአሁ ፡ ለሥጋ ፡ ኮነ ፡ ለቃል) ፡ ብሎ ፡ እንደተናገረ ፤ የቃል ፡ ክብር ፡ ለሥጋ ፡ ተላልፎ ፡ ሥጋ ፡ በዘባነ ፡ ኪሩብ ፡ ተቀምጦ ፡ መላእክት ፡ የሚሰግዱለት ፡ የሚገዙለት ፤ የሥጋም ፡ ግዙፍነት ፡ ውሱንነት ፡ ለቃል ፡ ተላልፎ ፡ አካላዊ ፡ ቃል ፡ በአጭር ፡ ቁመት ፡ በጸባብ ፡ ደረት ፡ ተወስኖ ፡ የሚታይ ፤ የሚዳሰስ ፡ ሆነ ።

የቃል ፡ ገንዘብ ፡ ምልዓት ፡ ስፋት ፤ ርቀት ፡ ሕያውነት ፡ አምላክነት ፡ (መለኮት) ፡ ሲሆን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ በተዋሕዶ ፡ ለሥጋ ፡ ተላለፈና ፡ ሥጋ ፡ ምልአት ፡ ስፋት ፡ ርቀት ፡ ሕያውነት ፡ አምላክነት ፡ ያለው ፡ ሆነ ።

የሥጋ ፡ ገንዘብ ፡ ግዙፍነት ፡ ውሳኔ ፡ ጽበት ፡ ሲሆን ፤ ይህ ፡ ሁሉ ፡ በተዋሕዶ ፡ ለቃል ፡ ተላለፈ ። ስለዚህ ፡ በተዋሕዶ ፡ ስሙ ፡ ክርስቶስ ፡ ተብሎ ፡ በመጠራት ፡

www.ethiopianorthodox.org

አንድ ፡ አካል ፣ አንድ ፡ ባሕርይ ፣ አንድ ፡ ፈቃድ ፣ አንድ ፡ ግብር ፡ ያለው ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ብላ ፡ ቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አመነችበት ፣ ሌሎችንም ፡ አሳመነችበት ።

አንዳንድ ፡ መናፍቃን ፡ ሥጋ ፡ መልበሱን ፡ ምክንያት ፡ እያደረጉ ፣ ብዙ ፡ ስሕተት ፡ የተመላበትን ፡ ነገር ፡ ተናግረዋል ። በስሕተታቸውም ፡ መለኮታዊ ፡ አካሉንና ፡ ባሕርዩን ፡ ራሳቸው ፡ ደፍረው ፡ ሌሎችን ፡ ለማስደፈር ፡ በብዙ ፡ ሞክረዋል ።

ቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ግን ፣ ራሱ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ "ወብፁዕ ፡ ውእቱ ፡ ዘኢተዐቅፈ ፡ ብየ" ፡ (በእኔ ፡ የማይሰናከል ፡ ምስጉን ፡ ነው) ያለውንና ፡ ሐዋርያው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ወአልቦ ፡ ዘይክል ፡ ብሂለ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላዕሌሁ ፡ (መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ካደረበት ፡ ሰው ፡ በቀር ፡ ኢየሱስ ፡ ጌታ ፡ ነው) ፡ )የባሕርይ ፡ ገዥ) ፡ ነው ፡ ማለት ፡ የሚችል ፡ የለም ፡ ብሎ ፡ የሰጣትን ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ሳትዘነጋ ፡ ክርስቶስ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ በመሆኑ ፡ ፍጡርነት ፡ ተገዥነት ፡ ዐላዋቂነት ፡ የሌለበት ፡ በተዋሕዶ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ የባሕርይ ፡ ገዥ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ያስተማሩ ፡ የእነቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈወርቅ ፡ የእነቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ የእነቅዱስ ፡ ዲዮስቆሮስን ፡ የእነዚህን ፡ ሊቃውንትና ፡ የመሳሰሉትን ፡ ትምህርት ፡ ተቀብላ ፡ አክብራ ፡ ይዛ ፡ ኖራለች ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ክቡር ፡ ዳዊት ፡ በትንቢት ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ እየጠቀሰ ፡ የክርስቶስን ፡ ተዋሕዶውንና ፡ የባሕርይ ፡ አምላክነቱን ፡ በብዙ ፡ ክፍል ፡ አስረድቷል ።

ከዚህም ፡ ጥቂቱን ፡ እንናገረዋለን ፣ ዕብራውያን ፡ የስብከቱ ፡ ብርሃን ፡ ደርሷቸው ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ (ካመኑ ፡ ከተጠመቁ ፡ በኋላ ፡ ክርስቶስን ፡ መልአክ ፡ እንበለው? ፡ ወይስ ፡ ነቢይ ፡ እንበለው? ፡ እያሉ ፡ በምርምር ፡ ስለተቸገሩ ፣ ኢላይ ፡ አርእስት ፡ አድርገን ፡ የጠቀስነውን ፡ ቃል ፡ ጽፎ ፡ ከመላእክት ፡ መብለጡንና ፡ እኛን ፡ ከኃጢአት ፡ ማንጻቱን ፡ አስረድቷቸዋል ። ትርጓሜውም ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዳግመኛ ፡ ልጁ ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፣ የእግዚአብሔር ፡ መላእክት ፡ (መልክተኞች) ፡ ሁሉ ፡ ይሰግዱለታል ፡ አለ ።

ስለ ፡ መላእክትም ፡ መላእክቱን ፡ ነፋሳት ፡ አገልጋዮቹንም ፡ የእሳት ፡ ነበልባሎች ፡ ያደረጋቸው ፡ የፈጠራቸው ፡ እሱ ፡ ነው ፡ አለ ።

ስለ ፡ ልጁ ፡ ግን ፡ አቤቱ ፡ ዙፋንህ ፡ የዘለዓለም ፡ ነው ፡ የመንግሥትህ ፡ በትርም ፡ የቅንነት ፡ በትር ፡ ነው ።

ታላቁ ፡ ሊቅ ቅዱስ ፡ ቄርሎስም ፡ የክርስቶስን ፡ ተዋሕዶ ፡ በምሳሌ ፡ ሲያስረዳ ፣ እሳት ፡ ብረትን ፡ በተዋሐደ ፡ ጊዜ ፣ ጽሉምነትን ፣ ቈሪርነትንና ፡ ዝገትን ፡ ከብረት ፡ አካል ፡ እንዲያስወግድ ፣ ቃል ፣ ሥጋን ፡ በተዋሐደ ፡ ጊዜ ፡



ሥጋ ፣ ፍጡርነት ፡ አላዋቂነትና ፡ ተገዥነት ፡ የሌለበት ፡ ፍጹም ፡ መለኮታዊ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ያስተማረው ፡ ትምህርት ፡ ከዚህ ፡ ከቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ቃል ፡ የመነጨ ፡ ነው ።

ዕድሜውን ፡ በተባሕትዎ ፡ የፈጸመ ፡ በጣም ፡ የበቃው ፡ ሊቅ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈወርቅም ፡ የቅዱስ ፡ ጳውሎስን ፡ ቃል ፡ እየጠቀሰና ፡ የአርዮስን ፡ ክህደት እየተቃወመ ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፣ መላእክት ፡ ለክርስቶስ ፡ ይሰግዱለታል ፡ በማለቱ ፣ ጌታ ፡ ከአሽከሮቹ ፡ እንዲበልጥ ፣ ክርስቶስ ፡ ከመላእክት ፡ ይልቅ ፡ እንዲከብርና ፡ እንዲበልጥ ፣ እነሆ ፡ አስረዳ ።

መላእክትን ፡ የፈጠራቸው ፡ እሱ ፡ ነው ፡ በማለቱ ፡ የመላእክትን ፡ ፍጡራንነት ፣ ስለልጁ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ግን ፡ አቤቱ ፡ ዙፋንህ ፡ የዘለዓለም ፡ ነው ፡ በማለቱ ፡ የሱን ፡ ፈጣሪነት ፡ አስረዳ ።

በፈጣሪና ፡ በፍጡር ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ መለያየትና ፡ መብለጥ ፡ እነሆ ፡ ሐዋርያው ፡ ተናገረ ።

ከፍጡራንስ ፡ ሊለየው ፡ ካልወደደ ፡ ሠራዊተ ፡ መላእክትን ፡ ብቻ ፡ ሰገዱ ፡ ባላለም ፡ ነበር ። እሱም ፡ ፍጡር ፡ ነውና ፡ ይሰግዳል ፡ ባለነበር ፡ እንጂ ።

ፈጣሪን ፡ እሱን ፡ ከፍጡራን ፡ መላእክት ፡ ለይቶ ፣ ጌታን ፡ እሱን ፡ ከላእካን ፡ መላእክት ፡ ለይቶ ፣ የአብ ፡ የባሕርይ ፡ ልጁን ፡ እሱን ፡ ከአግብርት ፡ መላእክት ፡ ለይቶ ፣ በብዙ ፡ ማስረጃ ፡ እንደ ፡ አስረዳ ፣ ዐወቅህን ፡ ተረዳህን? ።

ናሁኬ ፡ ዘለፎሙ ፡ በዝየ ፡ ለንፋቃን ፡ አይሁድ ፡ ወለሕዝበ ፡ ጳውሎስ ፡ ሳሚሳጢ ፣ ለአርዮሳውያን ፣ ወለመርክላን ፣ ለሰባልዮስ ፡ ወለመንክዮን ፣ (በዚህ ፡ ተጠራጣሮችን ፡ አይሁድን ፡ የጳውሎስ ፡ ሳሚሳጢን ፡ ወገኖች ፣ አርዮሳውያንን ፡ መርክላንን ፣ ሰባልዮስንና ፡ እለመንክዮንን ፡ ረታቸው ።

አምላክ ፡ ወሰብእ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ተናግሮ ፡ አይሁድን ፡ ረታቸው ። ክርስቶስ ፡ ከተዋሕዶ ፡ በፊት ፣ ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፣ ቀዳማዊ ፡ የአብ ፡ የባሕርይ ፡ ልጁ ፡ መሆኑን ፡ አስረድቶ ፡ እነጳውሎስ ፡ ሳሚሳጢን ፡ ተከራከራቸው ።

አቤቱ ፡ ዙፋንህ ፡ የዘለዓለም ፡ ነው ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ በመጥቀስ ፡ በባሕርዩ ፡ ፍጡር ፡ እንደ ፡ አይደለ ፡ አስረድቶ ፡ አርዮሳውያንን ፡ አሳፈራቸው ። የሐ ፡ አ ፡ ወ ፡ ድር ፡ ፫ ።

የእኛ ፡ አባቶች ፡ ይህን ፡ የሊቁን ፡ የዮሐንስ ፡ አፈወርቅን ፡ ቃልና ፡ ሀብተ ፡ ምሥጢራት ፡ የተሰጠው ፡ ሐዋርያው ፡ ዮሐንስ ፡ ፍቁረ ፡ እግዚእ ፣ ወልድን ፡ የሚክድ ፡ ሁሉ ፡ አብን ፡ በማመን ፡ የለም ፣ በወልድ ፡ የሚያምን ፡ አብንም ፡ በማመን ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ ያስተማረውን ፡ ትምህርት ፡ የመንፈስ ፡ መከላከያ ፡ በማድረግ ፣ ኢትዮጵያን ፡ የመናፍቃን ፡ ክህደት ፡ ከሚያመጣው ፡ አደጋ ፡ ጠብቀው ፡ አቆይተውናል ። ፩ ፡ ዮሐ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፳፫ ።

www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ ፣ የኢትዮጵያውያን ፡ አባቶቻችንን ፡ መንፈስ ፡ የተባረከና ፡ የተቀደሰ ፡ የሃይማኖት ፡ ዓምድ ፡ አድርጎ ፡ እውነተኛውን ፡ የተዋሕዶውን ፡ ምሥጢር ፡ ላስተላለፈልንና ፡ ይህንኑ ፣ በዚህ ፡ በልደቱ ፡ ዕለት ፡ ለመስማትም ፡ ለማሰማትም ፡ ላበቃን ፡ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ።

## ጸሎት ፡

አምላካችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፣

ንጹሐንና ፡ ቅዱሳን ፡ የሆኑ ፡ ደቀ፡መዛሙርትህን ፡ (ሐዋርያትን) ፡ እንዲህ ፡ ያልኻቸው ፣ ብዙ ፡ ነቢያትና ፡ ጻድቃን ፡ እናንተ ፡ ዛሬ ፡ የምታዩትን ፡ ያዩ ፡ ዘንድ ፡ ወደዱ ፣ አላዩም ።

እናንተ ፡ ዛሬ ፡ የምትሰሙትንም ፡ ይሰሙ ፡ ዘንድ ፡ ወደዱ ፣ አልሰሙም ። ዛሬ ፡ ይህን ፡ ያዩ ፡ የእናንተ ፡ ዐይኖችና ፡ ይህን ፡ የሰሙ ፡ የእናንተ ፡ ጆሮዎች ፡ ግን ፡ የተመሰገኑ ፡ ናቸው ።

የከበረ ፡ የወንጌልህን ፡ ቃል ፡ ሰምተን ፡ እንሠራ ፡ ዘንድ ፡ እኛንም ፡ በቅዱሳን ፡ ጸሎት ፡ እንደ ፡ እነሱ ፡ የበቃን ፡ አድርገን ።

ሰውን ፡ የምትወድ ፡ አምላካችንና ፡ መድኃኒታችን ፡ ሆይ ፣ የመንግሥትህን ፡ ወንጌል ፡ ይሰብኩና ፡ ያስተምሩ ፡ ዘንድ ፡ በሕዝብህ ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ ጨለማውን ፡ (ክህደቱን) ፡ ደዌውንና ፡ በሽታውን ፡ ሁሉ ፡ ያስወግዱ ፡ ዘንድ ፣ ከዓለም ፡ አስቀድሞ ፡ የነበረውንም ፡ የተሠወረውን ፡ ምሥጢርህን ፡ ገልጠው ፡ ያስተምሩ ፡ ዘንድ ፡ ብፁዓን ፡ ሐዋርያትን ፡ ወደዓለም ፡ ሁሉ ፡ የላክኻቸው ፡ አንተነህና ፡ ምስጋና ፡ ይግባህ ።

---

ኅዳር ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለ ፡ ስብከተ ፡ ወንጌል ፡ መስፋፋት ፡ በተደረገው ፡ ታላቅ ፡ ስብሰባ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ የተናገሩት ፡ መንፈሳዊ ዜና ።

«ወብነ ፡ አሐዱ ፡ መንፈስ ፡ ዘሃይማኖት ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ መጽሐፍ ፡ አመንኩ ፡ በዘነበብኩ ። ወንሕነኒ ፡ አመነ ፡ በዘነበብነ ፡ ወነአምር ፡ ከመ ፡ ዘአንሥአ ፡ ለኢየሱስ፡ እግዚእነ ፡ ያነሥአነ ፡ ኪያነሂ ፡ ምስሌሁ ፡ ለኢየሱስ ። ወያቀውመነ ፡ ምስሌክሙ» ። (ሃይማኖትን ፡ የምንናገርበት ፡ አንድ ቃል ፡ አለን ። መጽሐፍ ፡ በተናገርኩበት ፡ አመንኩ እንዳለ ፣ እኛም ፡ በተናገርነው ፡ ቃል ፡ እናምናለን ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ከሙታን ፡ ለይቶ ፡ ያስነሣው ፣ እኛንም ፡ እንደርሱ ፡ እንዲያስነሣን ፣ ከናንተም ፡ ጋራ ፡ በፊቱ ፡ እንዲያቆመን ፡ እናውቃለን፡ ፪ ፡ ቆሮ፡ ምዕ ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፲፫ ።

በአንድ ፡ ሃይማኖት ፣ በፍቅር ፡ አንድነት ፣ ለመሰብሰብ ፡ ላበቃን ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ማቅረብን ፡ እናስቀድማለን ።



ስንኳን ፡ በሃይማናት ፡ በማናቸውም ፡ ጕዳይ ፡ ተሰብስቦ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ሰላማዊ ፡ ጥቅምን ፡ ማስገኘቱ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

የጉባኤ ፡ ወንጌል ፡ መሪ ፡ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለአባቶቻችን ለሐዋርያትና ፡ ለተከተሉት ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፣ መጀመሪያ ፡ ያስተማራቸው ፡ ተባብሮና ፡ ተሰብስቦ ፡ ያንድነት ፡ ሥራ ፡ መሥራትን ፡ ነው ።

ይህንኑም ፡ ከዚህ ፡ በሚከተሉ ፡ ማስረጃዎች ፡ እንገልጻለን ።

፩ኛ| "ከእናንተ ፡ ሁለቱ ፡ በምድር ፡ ተባብረው ፡ ቢለምኑ ፣ የለመኑት ፡ ሁሉ ፡ ከሰማይ ፡ አባቴ ፡ ዘንድ ፡ ይደረግላቸዋል ። ሁለት ፣ ወይም ፡ ሦስት ፡ ሆነው ፡ በስሜ፡ ከሚሰበሰቡበት ፡ ከዚያ ፡ በመካከላቸው ፡ እገኛለሁ" ፡ ብሎ፡ የመተባበርንና ፡ የመሰብሰብን ፡ ጠቃሚነት ፡ ለሐዋርያት ፡ አስረድቷቸዋል ። ማቴ ፡ ምዕ ፡ ፲፰ ፡ ቍ ፡ ፲፱ ።

፪ኛ| ባረገ ፡ ጊዜ ፣ "እነሆ ፡ የአባቴን ፡ ተስፋ ፡ እልክላችኋለሁ ፡ እናንተ ፡ ግን ፣ ከላይ ፡ ኀይልን ፡ እስክትለብሱ ፡ ድረስ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተቀመጡ" ፡ ብሎ ፡ ካዘዛቸው ፡ በኋላ ፣ ከቢታንያ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተመልሰው ፡ ሁልጊዜ ፣ እግዚአብሔርን ፡ በኅብረት ፡ እያመሰገኑ ፡ ሰንብተዋል ፡ ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፶፪ ።

፫ኛ| ይህንኑ ፡ የፈጣሪያቸውን ፡ ትእዛዝ ፡ እየጠበቁ ፣ ባንድ ፡ ሥፍራ ፡ ተሰብስበው ፡ ሳሉ ፣ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስለ ፡ መላባቸው ፣ ሰማያዊ ፡ ኀይልን ፡ ለብሰው ፣ ወንጌልን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋ ፡ የሚሰብኩ ፡ ሆነዋል ። ግብ ፡ ሐዋ ፡ ምዕ ፡ ፪ ፡ ፩-፳።

መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በእሳት ፡ ላንቃ ፡ አምሳል ፡ ወርዶ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለቱን ፡ ሐዋርያት ፣ ሰባ ፡ ሁለቱን ፡ አርድእት ፣ ሠላሳ፡ስድስቱን፡ቅዱሳት፡አንስት፡ (በመላው፡መቶኻያውን ፡ ቤተ ፡ ሰብ፡) ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋ ፡ ባናገራቸው ፡ ጊዜ ፣ ሊቀ ፡ ሐዋርያቱ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ በጉባኤው ፡ መካከል ፡ ድምፁን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ፡ ተናግሮዋል ።

"ይህ ፡ በነቢዩ ፡ በኢዩኤል ፡ የተባለው ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ ይላል ፡ በኋለኛዩቱ ፡ ቀን ፡ ይሆናል ፡ ሥጋ ፡ በለበሰ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ከመንፈሴ ፡ አፈሳለሁ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችሁም ፡ ትንቢት ፡ ይናገራሉ ፡ ጎበዛዝቶቻችሁም ፡ ራእይ ፡ ያያሉ ፣ ሽማግሎቻችሁም ፡ ሕልምን ፡ ያልማሉ ። ደግሞም ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ በወንዶችና ፡ በሴቶች ፡ አገልጋዮቼ ፡ ላይ ፡ ከመንፈሴ ፡ አፈሳለሁ ፡ ትንቢትም ፡ ይናገራሉ" ፡ ኢዩኤል ፡ ምዕ ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፳፰ ። ግብ ፡ ሐዋ ፡ ምዕ ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፲፯ ።

ሊቀ ፡ ሐዋርያቱ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፣ የነቢዩ ፡ ትንቢት ፡ መፈጸሙን ፡ በተናገረ፡ ጊዜ ፣ ሦስት ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ በስብከቱ ፡ ደስ ፡ ስላላቸው ፣ አምነው ፡ ተጠምቀው፡ ከምእመናኑ ፡ ጋራ ፡ ተቈጥረዋል። ግብ ፡ ሐዋ ፡ ምዕ ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፵፩ ።

ዳግመኛ ፣ ከነቢያት ፡ ትንቢት ፡ አያይዞ ፡ እግዚአብሔር ፡ አስቀድሞ ፡ ለእናንተ ፣ ልጁን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ አስነሣላችሁ ፣ ከክፋታችሁም ፡ ብትመለሱ ፣

እያንዳንዳችሁን ፡ ይባርካችሁ ፡ ዘንድ ፡ ላከው„ ብሎ ፡ በሰበከላቸው ፡ ጊዜ ፤ አምስት ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ አምነዋል ። ግብ ፡ ሐዋ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ፬ ።

ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፤ ስብከተ ፡ ወንጌልን ፡ የተቀበሉ ፡ ምእመናን ፤ ሁሉ ፡ በሃይማኖት ፡ ስለ ፡ ተባበሩ ፤ ያንድነት ፡ ሥራ ፡ ይሠሩ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፤ አንዳች ፡ መለያየት ፡ አልነበረባቸውም ። ሐዋርያትም ፤ ከምእመናኑ ፡ በተገኘ ፡ ገንዘብ ፡ የያንዳንዱን ፡ ምእመን ፡ ችግር በልዩ ፡ ልዩ ተራድኦ ፡ እያቃለሉ ፤ ማኅበራዊውን ፡ ምግባርና ፡ ትሩፋት ፡ በመፈጸማቸው ፤ ሃይማኖታቸው ፡ የሚስፋፋና ፡ በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ መከበርንና ፡ መወደድን ፡ የሚያስገኝላቸው ፡ ሆኗል ። ግብ ፡ ሐዋ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፴፪-፴፯ ።

ዳግመኛ ፡ በየጊዜው ፡ ጸሎት ፡ በማድረስና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ (ወንጌልን ፡) በማስተማር ፤ በሥልጣናቸውም ፡ ተአምራት ፡ በማድረግ ፤ ሕዝቡ ፡ (ወንዶቹም ፡ ሴቶቹም) ፡ በምግብና ፡ በልብስም ፡ የመረዳዳትን ፡ ተግባር ፡ በማከናወን ኅብረታቸውን ፡ ስለ ፡ አሳዩ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እየሰፋ ፤ ክህደት ፤ ድንቍርናም ፡ እየጠፋ ፤ የምእመናንም ፡ ቍጥራቸው ፡ እየበዛ ፡ ሔዷል ።

ልማደ ፡ ኦሪትን ፡ አንለቅም ፤ ወንጌልን ፡ አንቀበልም ፡ እያሉ ፡ የሐዋርያትን ፡ ትምህርት ፡ ይቃወሙ ፡ ከነበሩት ፡ ከአይሁድ ፡ ሊቃውንት ፡ ወገን ፡ እንኳ ፤ ብዙዎቹ ፡ ትንቢቱ ፡ እንደ ፡ ተፈጸመ ፤ ተስፋው ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሥጋ ፡ እንደ ፡ ለበሰ ፡ አምነው ፡ ወደ ፡ ወንጌል ፡ ተመልሰዋል። ግብ ፡ ሐዋ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፯ ።

ምእመናን ፡ ሁሉ ፡ ያላንዳች ፡ መጠራጠርና ፡ መነጣጠል ፤ ማኅበራዊውን ፡ ኑሮ ፡ መሥርተው ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ሲራመዱ ፤ "ሁለትም ፡ ሦስትም ፡ ሆናችሁ ፡ በስሜ ከተሰበሰባችሁ ፡ በመካከላችሁ ፡ አገኛለሁ „ ብሎ ፡ ተስፋ ፡ የሰጣቸው ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መንፈሳዊ ፡ እርምጃቸውን ፡ እየባረከላቸው ፤ ሃይማኖታቸውን ፡ ወደ ፡ አልደረሰበት ፡ ለማዳረስ ፡ ችለዋል ።

ኢትዮጵያ ፤ ይህ ፡ ታላቅ ፡ መንፈሳዊ ፡ ዕድል ፡ በዚያው ፡ በሐዋርያት ፡ ዘመን ፡ ደርሷት ፡ ስትሠራበትና ፡ ስትጠቀምበት ፡ ኖራለች ፡ እንጂ ፡ ከጥንታዊው ፡ ስብከት ፡ ተለይታ ፡ ወደኋላ ፡ የቀረችበት ፡ ጊዜ ፡ አይገኝም ።

ይህንኑ ፡ ባጭሩ ፡ የሚያስረዳን ፡ የተለመደ ፡ ታሪክ ፡ አለ ። ሕጽዋ ፡ ለህንደኬ ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ኦሪቱ ፡ ሥርዓት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሊሰግድ ፡ ወደበዓሉ ፡ ሔዶ ፡ ነበር ። ሥርዓተ ፡ ኦሪቱን ፡ ፈጽሞ ፤ ለፈጣሪው ፡ ሰግዶ ፡ ሲመለስ ፡ በሠረገላ ፡ ላይ ፡ እንደተቀመጠ ፡ የነቢዩን ፡ የኢሳይያስን ፡ መጽሐፍ ፡ ያነብ ፡ ነበር ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፤ የሃይማኖትን ፡ ብርሃን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለመዘርጋት ፡ ያሰበ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ ፊልጶስን ፡ "ወደ ፡ ሠረገላው ፡ ቅረብና ፡ ያን ፡ ሰው ፡ ተገናኘው„ አለው ።



ፊልጶስም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንዳዘዘው ያን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰው ፡ ከተገናኘው ፡ በኋላ ፤ ያነብበው ፡ በነበረ ፡ በኢሳይያስ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ሥጋ ፡ መልበስ ፡ የተጻፈውን ፡ አስረድቶታል ። ይህም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰው ፡ መጻሕፍተ ፡ ብሉያትን ፡ የተማረ ፡ በመሆኑ ፡ ስለ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ መሆን ፡ የተነገረውን ፡ ትንቢትና ፤ የተቈጠረውን ፡ ሱባዔ ፡ ያውቅ ፡ ነበርና ፡ የቀድሞ ፡ ትምህርቱ ፡ ወደ ፡ ሐዋርያት ፡ ሃይማኖት ፡ ስለ ገፋፋው ፤ ክርስቶስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ልጁ ፡ መሆኑን ፡ አምኛለሁና ፡ አጥምቀኝ ፡ ብሎ ፡ ለምኖታል ። ፊልጶስም ፡ ወዲያው ፡ አጥምቆታል ።

እንደምታውቂት ፤ ያ የኢትዮጵያ ፡ ሰው ፡ በፊልጶስ ፡ እጅ ፡ ተጠምቆ ፡ ሃይማኖተ ፡ ወንጌልን ፡ ይዞ ፡ ስለመጣ ፤ ኢትዮጵያ ፡ የመንፈሳዊ ፡ ነጻነትን ፡ ቅድሚያ ፡ ገና ፡ በዘመነ ፡ ሐዋርያት ፡ አግኝታ ፡ ሃይማኖቷን ፡ በማኅበራዊ ፡ ተግባር ፡ ስታስፋፋ ፡ ኖራለች ።

ቅዱስ ፡ ሉቃስ ፡ ከኢትዮጵያዊው ፡ ሰው ፡ እምነትና ፡ ጥምቀት ፡ በኋላ ፡ ቀጥሎ ፡ በዘመነ ፡ ሐዋርያት ፡ ያሙኑ ፡ የመጀመሪያዎቹን ፡ ምዕመናን ፡ ታሪክ ፡ ሲተርክ ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ።

፩/ "ወነበራ ፡ በሰላም ፡ ኵሎን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ዘይሁዳ ፡ ወሰማርያ ፡ ወገሊላ ፡ ወተሐንጸ ፤ ወሖራ ፡ በፍርሃተ ፡ እግዚአብሔር ። ወበዝኃ ፡ ሕዝብ ፡ በትምህርተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ። (በይሁዳ ፤ በገሊላና ፡ በሰማርያ ፡ የነበሩት ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሁሉ ፤ በሰላም ፡ ኖሩ ። እግዚአብሔርን ፡ በመፍራትና ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ረዳትነት ፡ እየታነጹና ፤ እየጸኑ ፡ ሔዱ ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ም ፱ ፡ ቍ ፡ ፴፩ ።

፪/ ወተሰምዩ ፡ አርድእት ፡ ክርስቲያነ ፡ ቀዲሙ ፡ በአንጾኪያ ፤ (ምዕመናን ፡ መጀመሪያ ፡ በአንጾኪያ ፡ ክርስቲያን ፡ ተባሉ) ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ም ፲፩ ፡ ቍ ፡ ፳፮ ።

ኢትዮጵያ ፡ ለመጀመሪያዎቹ ፡ ምእመናን ፡ ማመናቸው ፡ ከመጻፉና ፡ በተለይ ፡ ክርስቲያን ፡ ተብለው ፡ ከመጠራታቸው ፡ በፊት ፡ የእምነታቸው ፡ ተካፋይ ፡ ስለሆነች ፤ ዕድሏም ፡ ታሪኳም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ።

ይኸውም ፡ እንደሌሎቹ ፡ ምእመናን ፡ በባዕድ ፡ ሐዋርያ ፡ መምህርነት ፡ ሳይሆን ፤ በወገኗ ፡ ሃይማኖተ ፡ ወንጌልን ፡ ተቀብላ ፡ በሥርዓተ ፡ ወንጌል ፡ ጸንታ ፡ ስለ ተገኘች ፡ ነው ።

ሌሎች ፡ ምእመናን ፡ የሐዋርያቸውን ፡ ደም ፡ ሲያፈሱ ፤ ኢትዮጵያ ፡ በዚሁ ፡ የግፍ ፡ ሥራ ፡ ተካፋይ ፡ ስላልሆነች ፡ ነው ።

ሌሎች ፡ ምእመናን ፡ ሐዋርያ ፡ ሲላክላቸው ፤ ኢትዮጵያ ፡ ሐዋርያ ፡ ሳይላክላት ፡ በራስዋ ፡ ሐዋርያ ፡ ስለ ፡ አመነች ፡ ነው ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ምሕረት ፡ የባሕርዩ ፡ የሚሆን ፡ ቸር ፡ እግዚአብሔር ፡ ብርሃነ ፡ ረድኤቱ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ሲያበራ ፡ እንዲኖር ፤ ነ መጀመሪያዎቹ ፡ ምእመናን ፡

www.ethiopianorthodox.org

አይሁድ ፡ ቤተ ፡ አይሁድ ፡ ወገናቸው ፡ ቅዱስ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ስለ ክርስቶስ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክነት ፡ ከአብርሃም ፡ እስከ ፡ ሰሎሞን ፤ ከሰሎሞን ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ የተነገረውን ፤ ትንቢት ፡ ቢነግራቸው ፡ አናምንም ፡ ብለው ፡ በደንጊያ ፡ ወግረው ፡ ሲገድሉት ፤ ኢትዮጵያ ፡ ስለ ክርስቶስ ፡ የተነገረውን ፡ ትንቢት ፡ በእምነት ፡ መከተሏ ፡ ለዘላለም ፡ ታሪክ ፡ ሆኖ ፡ ሲነገር ፡ በመኖሩ ፡ ነው ።

እላይ ፡ እንደተናገርነው ፤ ኢትዮጵያ ፡ በጥንት ፡ ስብከት ፡ ጀምራ ፡ ሃይማኖተ ፡ ወንጌልን ፡ ተቀብላ ፡ ከቆየች ፡ በኋላ ፤ ሥርዓተ ፡ ወንጌልን ፡ በመልእክተኛዋ ፡ በፍሬ ምናጦስ ፡ አስመጥታለች ።

መልእክተኛዋ ፡ ፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ከእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ከቅዱስ ፡ አትናቴዎስ ፡ የሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ መዓርግ ፡ ተቀብሎ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፤ ኢትዮጵያ ፡ እንደአላመኑት ፡ አይሁድ ፤ ስለጌታችን ፡ የተነገረውን ፡ ንባቡን ፤ ምሳሌውንና ፡ ትንቢቱን ፡ በመስማት ፡ ብቻ ፡ ሳትወስን ፡ ትርጓሜውን ፤ ምሥጢሩን ፡ ሃይማኖቱን ፡ ዐውቃ ፡ ለማሳወቅ ፡ በመፋጠኗ ፡ የቍስጥንጥንያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ሊቁ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ተፈጽሞባታል ።

፩/ ምሥራብ ፡ አነመት ፡ ፀምረ ፡ ወቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተፀጽፈቶ) ። ምሥራብ ፡ ፀምር ፡ ሠራች ። ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለበሰችው ።

አይሁድ ፡ ንባቡን ፤ ምሳሌውንና ፡ ትንቢቱን ፤ ሰሙ ። ትርጓሜውን ፤ ምሥጢሩንና ፡ ሃይማኖቱን ፡ ግን ፤ ምእመናን ፡ ገንዘብ ፡ አደረጉ ።

፪ኛ | ፡ አሕዛብ ፡ አስተጋብኡ ፡ ጽጌ ፡ ረዳ ፡ በኂሩቱ ፡ ወሦኩስ ፡ ተርፈ ኀበ ፡ አይሁድ ። ዘውእቱ ፡ ሕፀተ ፡ ሃይማኖት ። "አሕዛብ ፡ በቸርነቱ ፡ አበባ አበባውን ፡ ሰበሰቡ ። እሾሁ ፡ ግን ፡ በአይሁድ ፡ ዘንድ ፡ ቀረ ። ትርጓሜውን ፤ ምሥጢሩንና ፡ ሃይማኖቱን ፡ ምእመናን ፡ ገንዘብ ፡ አደረጉ ። ክህደትና ፡ ኑፋቄ ግን ፤ በአይሁድ ፡ ዘንድ ፡ ቀረ ። (ሃይ ፡ አበው ፡ ፷ ፡ ድርሳን) ።

የኢትዮጵያ ፡ ትውልዷ ፤ ነገዷ ፤ ወልድየ ፡ ዘበኵርየ ፡ ከተባሉ ፡ ከእስራኤል ፡ (ከአይሁድ) ፡ ወገን ፡ ሲሆን ፤ እንደ ፡ እስራኤል ፡ ንባቡን ፡ ምሳሌውንና ፡ ትንቢቱን ፡ ሰምታ ፤ እንደ ፡ ምእመናነ ፡ አሕዛብ ፤ ትርጓሜውን ፤ ምሥጢሩንና ፡ ሃይማኖቱን ፡ ተረድታ ፤ በሃይማኖቷ ፡ በኵል ፡ ያሳየችው ፡ ፈቃደኛነቷ ፡ በማንም ፡ ዘንድ ፡ የማይዘነጋ ፡ ነው ።

እንደዚሁ ፡ ጸሎት ፡ የሚደርስበትን ፤ መሥዋዕት ፡ የሚሠዋበትን ፤ ሃይማኖት ፡ የሚሰበክበትን ፡ በታ ፡ ለዩልን ፡ (ሕንጻ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዲመሠረት ፡ ፍቀዱልን ፡ ብለው ፡ ለሐዋርያት ፡ ጥያቄ ፡ አቅርበው ፤ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕንጻ ፡ በፊልጵስዩስ ተጀምሯል ።

ኢትዮጵያ ፡ ግን ፤ እንደ ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ በአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ጸንታ ፤ በኦሪቱ ፡ ሥርዓት ፡ ላም ፤ በግና ፡ ፍየል ፤ ዋኖስንና ፡ ርግብን ፡ በምሥራብ ፡ ኦሪት ፡ እየሠዋች ፤ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ አራት ፡ ዓመታትን ፡ አሳልፋ ፡ ስለነበረች ፤ የብሉይን ፡ ንባብ ፡ በወንጌል ፡ ትርጓሜ ፤ የብሉይን ፡ ምሳሌ ፡ በወንጌል ፡ አማናዊ ፡ ምሥጢር ፤ የብሉይን ፡ ትንቢት ፡ በወንጌል ፡ ሃይማኖት ፡ እንደ ፡ መቀበሏ ፡ መጠን ፤ በምሥራብ ፡ ኦሪት ፡ ፈንታ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፤ መሥዋዕተ ፡ ኦሪትን ፤ በመሠዋት ፡ ፈንታ ፡ መሥዋዕተ ፡ ወንጌልን ፡ ተክታ ፤ በሃይማኖቷ ፡ ጸንታ ፡ የኖረች ፡ ናት ።



ለዚህ ፡ ሁሉ ፡ ለተቀደሰ ፡ ታሪኳ ፤ ዋና ፡ መሠረት ፡ የሆናት ፡ የቀዳማዊ ፡ ምኒልክና ፡ የሁለቱ ፡ መንፈሳውያን ፡ ነገሥታት ፡ የአብርሀና ፤ የአጽብሐ ፡ መሪነት ፡ እንደሆነ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ከዚያ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፤ በየጊዜው ፡ የተነሡት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ መሳፍንትና ፡ መኳንንት ፤ ወይዛዝር ፡ ባላባቶችና ፡ መላው ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፤ በቤተ ፡ ክህነትም ፡ በኩል ፤ ሊቃውንትና ፡ መምህራን ፤ አለቆችና ፡ ካህናት ፡ በታሪክ ፡ ተያይዞ ፡ ከመጣው ፡ ከባቶቻቸው ፡ መንፈሳዊ ፡ እርምጃ ፡ ሳይወጡ ፤ ኦርቶዶክስ ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ በሚገባ ፡ አገልግለዋል ።

በሚገባም ፡ መሥዋዕት ፡ ሆነውለታል ፡ ነገሥታቱና ፡ መሳፍንቱ ፤ ከሊቃውንቱ ፤ መኳንንቱና ፡ ወይዛዝሩ ፤ ባላባቶቹና ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ከመምህራኑና ፡ ከካህናቱ ፡ (ከቀሳውስቱ) ፡ ጋራ ፡ በሃይማኖታቸው ፡ እየተባበሩ ፤ ዳርዋን ፡ እሳት ፤ መሐሏን ፡ ገነት ፡ አድርገው ፡ በጥንቃቄ ፡ የጠበቁዋትን ፡ አገራችን ፡ ኢትዮጵያን ፡ እነሆ ፡ ለእኛ ፡ ለልጆቻቸው ፡ አቆይተውናል ።

ይሁን ፡ እንጂ ፤ ዛሬ ፡ የዚህ ፡ ሁሉ ፡ አላፊነት ፡ በእነማን ፡ ላይ ፡ አረፈ? ብለን ፡ ስንጠይቅ ፡ በሁላችን ፡ ላይ ፡ ነዋ ፡ የሚል ፡ መልስ ፡ ከየልባችን ፡ ይመጣል ።

አላፊነቱ ፡ የሚመለከተው ፡ ሁላችንን ፡ ከሆነ ፤ አባቶቻችን ፡ በዘመነ ፡ ብሉይ ፡ ከአምልኮተ ፡ ጣዖት ፤ በዘመነ ፡ ሐዲስ ፡ ከአይሁድ ፡ ክህነት ፡ ጠብቀው ፡ ላቆዩዋት ፡ ለእናታችን ፡ ኢትዮጵያ ፤ ምን ፡ ዓይነት ፡ የኀብረት ፡ ሥራ ፡ ልንሠራላት ፡ ይገባን ፡ ይሆን? ።

ኦርቶዶክስ ፡ ሃይማኖታችን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕይወት ፡ ለሁላችን ፡ ያስገኘልን ፡ ነው ፡ ወደፊትም ፡ ያስገኝልናል ።

ለህብታችንም ፡ ምንጭ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕይወት ፡ ነውና ፤ የኢትዮጵያን ፡ ሕይወት ፡ ለመታደግ ፡ ለቻለ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ሃይማኖታችን ፡ አንድ ፡ የኀብረት ፡ መታሰቢያ ፡ አቋቁመን ፡ ለመጪው ፡ ትውልድ ፡ ማቆየት ፡ እንጂ ፤ ያለፈውን ፡ ያባቶቻችንን ፡ ድካም ፡ ማውራታችን ፡ ብቻ ፡ በቂ ፡ አገልግሎት ፡ ሊሆነን ፡ አይችልም ።

ዛሬ ፡ የዓለም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ ያስፋፉት ፡ በማኅበራዊ ፡ ተግባር ፡ መሆኑን ፡ ተረድተናል ።

www.ethiopianorthodox.org

የኛም ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ሃይማኖት ፤ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፤ መሳፍንትና ፡ መኳንንት ፤ ሊቃውንትና ፡ መምህራን ፤ ካህናትና ፡ ምእመናን ፡ በማኅበራዊ ፡ ሥርዓት ፡ ደግፈው ፡ ያቆዩት ፡ መሆኑን ፤ እነሆ ፡ በታሪክ ፡ ተመልክተናል ። እንግዲህ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ንግሥት ፡ ከህንደኬ ፡ ሹም ፡ (በጅሮንድ) ፡ እምነት ፡ ጀምሮ ፡ አንድ ፡ ሺ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ዘመናት ፡ ለኖረ ፤ በታሪክ ፡ ለታወቀና ፡ ለከበረ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ሃይማኖታችን ፡ እንደምን ፡ ያለ ፡ ማኅበራዊ ፡ ተግባር ፡ ልናቋቁምለት ፡ ይገባን ፡ ይሆን ? ።

ስለዚህ ፤ የሐዋርያትን ፡ አንድነት ፡ የባረከ ፡ እግዚአብሔር ፤ የኛንም ፡ አንድነታችንን ፡ ባርኮ ፤ ጉባኤያችንን ፡ አስፍቶ ፤ ምእመናን ፡ የሚታነጹበት ፤ አገር ፡ የሚጠበቅበት ፤ ሃይማኖት ፡ የሚስፋፋበትን ፡ ይህን ፡ የስብከት ፡ ሥራ ፡ እንድናቋቁም ፡ ይረዳን ፡ ዘንድ ፡ (ወይኩን ፡ ፈቃድከ) ፈቃድህ ፡ ይሁን ፡ እያልን እንጸልያለን ።

እኔም ፡ ለስብከተ ፤ ወንጌል ፡ በተዘጋጀው ፡ በዚህ ፡ አዳራሽ ፡ ጥሪያችሁን ፡ አክብራችሁ ፡ እየተሰበሰባችሁ ፡ ሥራችሁን ፡ እንድታከናውኑ ፤በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ አደራ ፡ እላችኋለሁ ።

---

## ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ የፈጸሙት ፡ ገዳማዊ ፡ አገልግሎት ።

ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ገና ፡ በዐሥራ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ዕድሜያቸው ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገብተው ፡ የፈጸሙት ፡ ገዳማዊ ፡ አገልግሎት ፡ በሌላ ፡ ክፍል ፡ ተገልጧል ።

እንዲሁም ፡ ወደ ፡ ዋሻ ፡ ሚካኤል ፤ ወደ ፡ መናገሻ ፡ ገዳምና ፤ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ገዳማት ፡ ገብተው ፡ በቅን ፡ መሪነታቸውና ፡ ርኅራኄን ፡ በተመላ ፡ አስተዳዳሪነታቸው ፡ ያሳዩት ፡ የገዳማዊነት ፡ አርአያ ፡ በጥቂቱ ፡ ተነግሮዋል ።

እየተዘዋወሩ ፡ በትሩፋታቸው ፤ በደግነታቸው ፡ የጐበኙዋቸው ፡ ገዳማትና ፡ አድባራትም ፡ መታሰቢያቸው ፡ በሆን ፤ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ያንዳንዱ ፡ ማስታወሻ ፡ መዘግብት ፡ ሆነዋል ።

ይሁን ፡ እንጂ ፤ ብፁዕነታቸው ፤ ዛሬ ፡ ላለነው ፡ ትውልድ ፡ የገዳማዊነትን ፡ አርአያ ፡ በበለጠ ፡ ሲያመለክትን ፡ ይታያል ።

ብፁዕነታቸው ፡ ለሥጋውያንም ፤ ለመንፈሳውያንም ፡ ምቹ ፡ ሆኖ ፡ መንፈሳቸውን ፡ ወደ ፡ ክርስቲያናዊት ፡ ፍቅርና ፡ ወደ ፡ ሃይማኖታዊት ፡ ዝንባሌ ፡ መሳብ ፡ የተለየ ፡ ስጦታው ፡ በመሆኑ ፤ የዝግታ ፡ መሪ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ችኵል ፡ አይደሉም ።

በዚሁም ፡ ምክንያት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አባትነታቸውን ፡ በምሳሌነት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በአማናዊነት ፡ ጭምር ፡ ይመለከተዋል ።

ብፁነታቸው ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ መከተል ፡ የዘወትር ፡ ተግባሩ ፡ ስለ ፡ ሆነም ፤ መናንያን ፡ ባሕታውያንና ፡ መነኰሳት ፡ ወደ ፡ ብፁዕነታቸው ፡ ቀርበው ፡ የሃይማኖታቸውን ፡ ነጻነት ፡ ሁልጊዜ ፡ ከመግለጣቸው ፡ በላይ ፤ ብፁዕነታቸው ፡ የእግዚአብሔር ፡ እንደራሴ ፡ መሆኑን ፡ በልማድ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በትክክል ፡ ያምናሉ ።



ብፁዕ ፡ አባታችንም ፡ ጕዳያቸውን ፡ በትሕትና ፡ ተቀብለው ፡ ከመፈጸማቸው ፡ በላይ ፡ ለነእዚሁ ፡ ለመንፈሳውያኑ ፡ መረጃ ፡ የሚሆን ፡ ገንዘብ ፡ ከግል ፡ ገቢያቸው ፡ እየተመደበ ፡ ይቀመጣል ።

መንፈሳውያኑ ፤ ከየገዳማቸው ፤ የመጡት ፡ ለመፍቅደ ፡ ገዳም ፡ ሲሆን ፤ ጕዳያቸው ፡ በብፁዕነታቸው ፤ ወይም ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ዘንድ ፡ ከተፈጸመላቸው ፡ በኋላ ፤ ለዐፅፍ ፡ ለመጽሐፍ ፡ መግዣና ፡ ለስንቅ ፡ የሚሆን ፡ በቂ ፡ ገንዘብ ፡ ሰጥተው ፡ በደስታ ፡ ወደ ፡ ገዳማቸው ፡ ወደ ፡ በአታቸው ፡ እንዲመለሱ ፡ ያደርጋሉ ። ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ የመንፈሳዊ ፡ መሪነታቸው ፡ ተግባር ፡ ምንም ፡ እጅግ ፡ የበዛ ፡ ቢሆን ፤ ቅዱስ ፡ ሰውነታቸው ፡ በሱባዔና ፤ በቀኖና ፡ ሁልጊዜ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተጸመደ ፡ ነው ።

ይህንንም ፡ ስንናገር ፡ ያንድ ፡ ሊቅ ፡ ቅኔ ፡ ይታሰበናል ። ቅኔው ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ "ከመሰ ፡ ኢይኩን ፡ እግረ ፡ ልብከ ፡ ሐታቲ ፤ በፍቅረ ፡ ዋልድባ ፡ ወአብረንታንቲ ። እመሰ ፡ ተአምር ፡ ባቲ ፡ ገረገራ ፡ ዋልድባ ፡ ይእቲ ።

ይህ ፡ የሊቁ ፡ ቅኔ ፡ የሚያሳስበው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ የመናኝነትና ፡ የገዳማዊነት ፡ ፈቃድ ፡ ካለው ፡ በዓለማውያን ፡ ዘንድ ፡ እያለ ፡ የመናኝነትና ፡ የገዳማዊነት ፡ ሥራ ፡ ሊሠራ ፡ መቻሉን ፡ ነው ።

እንዲሁ ፤ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ዓለማውያንንና ፡ ሥጋውያንን ፡ ወደ ፡ መንፈሳዊ ፡ አካሔድ ፡ ለመምራት ፡ ከሚያደርጉት ፡ ሰፊ ፡ ተጋድሎ ፡ ጋራ ፤ ከልጅነታቸው ፡ ጀምሮ ፡ የለመዱትን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ የሚያገናኛቸውን ፡ ቀኖና ፡ ማዘውተራቸው ፡ እጅግ ፡ አስደናቂ ፡ ነገር ፡ ነው ። ይህም ፡ ፍጹም ፡ መናኝነታቸውን ፡ ያስረዳል ። ለሕዝበ ፡ ክርስቲያንም ፡ በጎ ፡ አርአያ ፡ ይሆናል ።

በዚህም ፤ ቅዱስ ፡ ጳውሎስን ፡ መስለውታል ። ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ከከተማ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ እየተዘዋወረ ፡ ሲያስተምር ፡ የያንዳንዱን ፡ ሰው ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋና ፤ ኃጢአትን ፡ ለማድከም ፡ እንዲመቸው ፡ እንዲህ ፡ ይል ፡ ነበር ።

፩ኛ ፡ ለሮሜ ፡ ሰዎች ፡ በጻፈው ፡ መልእክቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ እንደተነሣ ፡ታውቃላችሁ ። እንግዴህ ፡ ወዲህ ፡ ዳግመኛ ፡ አይሞትም ። እንግዲህ ፡ ሞት ፡ አያገኘውም ። የሞተ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሞተ ። በሞቱም ፡ ኃጢአትን ፡ ሻራት ፤ የተነሣም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተነሣ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ወከማሁ ፡ አንትሙሂ ፡ ረስዩ ፡ ርእሰክሙ ፡ ምውታነ ፡ ለኃጢአት ፡ ወሕያዋነ ፡ ኩኑ ፡ ለፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደዚሁ ፡ እናንተም ፡ ራሳችሁን ፡ ለኃጢአት ፡ የሞተ ፡ አድርጉ ፤ ለኃጢአት ፡ ሬሳ ፡ መስላችሁ ፡ ታዩ ። ስለ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፈቃድ ፡ ለመፈጸም ፡ ሕያዋን ፡ ሁኑ ፡ ሮሜ ፡ ም ፡ ፮ ቍ ፡ ፲፩ ፡

www.ethiopianorthodox.org

፪ኛ ፡ ለገላትያ ፡ ሰዎች ፡ በጻፈው ፡ መልእክቱ ፡ «አንሰ ፡ ሐሰ ፡ ሊተ ፡ ኢይዜ ሀር ፡ ዘእንበለ ፡ በመስቀሉ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእነ ። ወበኀቤየሰ ፡ ምዉት ፡ ዓለም ፡ ወአነሂ ፡ ምዉት ፡ በኀበ ፡ ዓለም» ፡ «እኔ ፡ ግን ፡ ያለ ፡ ጌታ ችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መከራ ፡ ልመካ ፡ አይገባኝም ። በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ዓለሙ ፡ የሞተ ፡ ነው ። እኔም ፡ በዓለሙ ፡ ዘንድ ፡ የሞትኹ ፡ ነኝ» ፡ ገላትያ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፲፬ ።

ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ይህን ፡ የቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ምክርና ፡ አርአያ ፡ ተከ ትለው ፡ በዓለማውያን ፡ ዘንድ ፡ ሳሉ ፣ የገዳማዊነታቸውን ፡ ተግባር ፡ ከማዘው ተራቸው ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ አባቶቻችን ፡ እንደ ፡ ሐዋርያት ፡ ለምእመናን ፡ ወን ጌል ፡ በጎ ፡ አርአያን ፡ ያመለከቱ ፡ ናቸው ።

በዚሁም ፡ ላይ ፡ ብፁዕነታቸው ፡ ንጽሕናና ፡ ቅድስና ፡ የተከተሉት ፡ ትዕግ ሥትን ፡ ልባዊነትና ፡ አስተዋይነት ፡ የተከተሉት ፡ አርምሞን ፣ ፍቅረ ፡ ቢጽና ፡ ፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተከተሉት ፡ ትሕትናን ፡ ተጐናጽፎ ፡ የሚታይ ፡ ነው ።

---

## የብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፣ ጠቅላላ ፡ ሕይወታዊ ፡ ታሪክ ።

ከዚህ ፡ አስቀድመን በመቅድሙ ፡ እንደገለጥነው ፣ የደጋጎች ፡ አበውን ፡ ታሪክ ፡ ጽፎ ፡ ለሚመጣው ፡ ትውልድ ፡ ማቆየት ፡ የተገባ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፣ በየጊዜው ፡ ኢት ዮጵያን ፡ በዕውቀታቸውና ፡ በመንፈሳዊነታቸው ፡ ያገለገሉ ፡ ሊቃውንት ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ የታሪክ ፡ ሥራ ፡ ለማደራጀት ፡ ሙሉ ፡ ሕይወታቸውን ፡ አሳል ፈው ፡ እንደ ፡ ሰጡ ፡ ይተረካል ።

ይልቁንም ፡ በሊቁ ፡ በዮሐንስ ፡ ከማ ፡ (በሰባተኛው ፡ ዕጨጌ ፡ ) ተዘጋጅቶ ፡ ለዓለም ፡ የተዳረሰው ፡ የደገኛው ፡ ሐዋርያችን ፡ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ታሪክ ፡ ከበሥረ ፡ ፍጥረት ፡ አዳም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ትውልድን ፡ ከትውልድ ፡ ሥነ ፡ ጽድቅን ፡ ከሥነ ፡ ጽድቅ ፡ አያይዞ ፡ የወረደ ፡ በመሆኑ ፡ የትውልድ ፡ መሥመሩን ፡ ሳይለቅ ፡ ቅዱስ ፡ ቡራኬ ፡ ባልተለየው ፡ ዘር ፡ ተያይዞ ፡ የመጣውን ፡ የአበውን ፡ በረከት ፡ ያሳስባል ። የተቀደሰውንም ፡ አብርሃማዊ ፡ ሃይማኖት ፡ ያስታውሳል ። የክርስትናን ፡ ብርሃንም ፡ ከሁለቱ ፡ ቅዱ ሳን ፡ ነገሥታት ፡ ከአብርሀና ፡ ከአጽብሐ ፡ ቅድሳናዊ ፡ ታሪክ ፡ ጋራ ፡ አዋሕዶ ፡ ፀጣም ፡ ወደ ፡ ተስፋፋበት ፡ ዘመን ፡ ይመራል ።

ስለዚህ ፣ ታሪክ ፡ ዓይነ ፡ ልቡናችን ፡ ወደ ፡ ኋላም ፡ ወደፊትም ፡ እንዲ መለከት ፡ የሚያበረታታ ፡ በመሆኑ ፣ ነቢዩ ፡ ዳዊት ፡ «ትውልደ ፡ ጻድቃን ፡ ይት ባረኩ» ፡ (የቅኖች ፡ ትውልድ ፡ ትባረካለች ፡ ) ብሎ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ መነሻ ፡ በማድረግ ፡ በጊዜያችን ፡ የመንፈሳዊ ፡ መሪያቸውን ፡ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ መንበረ ፡ ክብር ፡ (ዕጨጌነትን ፡ ) ወርሰው ፡ ከኖሩ ፡ በኋላ ፣ ከኢትዮጵያ ፡ መም ህራን ፡ መካከል ፡ ተመርጠው ፡ ለኢትዮጵያዊው ፡ ሢመተ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ መጀመሪያ ፡ በመሆን ፡ የተሰጡትን ፡ የብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡነ ፡ ባስል ዮስን ፡ ታሪክ ፡ ከትውልዳቸውና ፡ ከነገዳቸው ፡ ጥንተ ፡ ዜና ፡ ጋር ፡ አያይዘን ፡ ለመጻፍ ፡ እነሆ ፡ ጀመርን ።



### የብፁዕነታቸው ፡ ዜና ፡ ልደትና ፡ ትውልዳቸው ፣ ነገዳቸውም ፡ ያለበት ፡ ሀገር ።

ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ፲፰፻፹፬ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ መጋ ቢት ፡ ፲፬ ፡ ቀን ፡ ከደብተራ ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡ ሰሎሞንና ፡ ከወይዘሮ ፡ ወለተ ፡ ማርያም ፡ (በኋላ ፡ እማሆይ ፡ ) በሸዋ ፡ አውራጃ ፡ በሚገኘው ፣ ሜዳ ፡ ሚካኤል ፡ በሚባለው ፡ ሀገር ፡ ላይ ፡ ተወለዱ ።

አባታቸው ፡ ደብተራ ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡ ሰሎሞን ፡ የተወለዱበትና ፡ የት ውልድ ፡ ሀገራቸው ፡ በይፋት ፡ አውራጃ ፡ (በቀወት ፡ ) ልዩ ፡ ስሙ ፡ ጌሥ ፡ ማር ያም ፡ የተባለው ፡ ሀገር ፡ ነው ።

የጌሥ ፡ ማርያምን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያቀና ፡ የሸዋ ፡ ዋና ፡ ባላባትና ፡ ገዥ ፡ (መስፍን ፡ ) የነበረው ፡ ነጋሢ ፡ ክርስቶስ ፡ ነውና ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የብፁዕ ነታቸው ፡ ሐረገ ፡ ትውልድ ፡ በዚያ ፡ ከነበሩት ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ የወረደ ፡ ነው ።

### የእናታቸው ፡ የእማሆይ ፡ ወለተ ፡ ማርያም ፡ የትውልድ ፡ ሀገራቸው ።

መንዝ ፡ (አፍቀራ ፡ ) ጌራ ፡ ምድር ፡
ገዶምበ ፡
አሎ ፡ ርሴ ፡
አሎ ፡ ሲጠር ፡ (ገብርኤል ፡
ጉመር ፡
ፍጨት ፡
አመድ ፡ ጓያ ፡
ጠዶ ፡ በር ።

እንዲሁም ፡ የእናታቸው ፡ ሐረገ ፡ ትውልድ ፡ የወረደባቸው ፡ ታላላቅ ፡

### ነገዶቻቸውና ፡ ሀገራቸው ።

ቀዳሜ ፡ ክርስቶስ ፡ (መንዝ) ሀገሩ ፡ አጋንቻ ፡ ኪዳነ ፡ ምሕረት ፡ ይኸ ውም ፡ ከዋናዎቹ ፡ የመንዝ ፡ ባላባቶች ፡ ከነጋሢ ፡ ክርስቶስና ፡ ከጌራ ፡ ክር ስቶስ ፡ የተወለደ ፡ ነው ።

| | |
|---|---|
| አፄ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ | ሀገሩ ፡ መንዝ ፡ |
| አፄ ፡ በድል ፡ ነጠር ፡ | ” ” |
| ራስ ፡ ድልይ ፡ | ” ” |
| ተክለ ፡ ነቢያት ፡ | ” ” |

ይኸውም ፡ ከአባቱ ፡ ከራስ ፡ ድልይ ፡ ተክለ ፡ ነቢያት ፡ ወደ ፡ መን ግሥት ፣ ሄም ፡ ወደ ፡ ርስት ፡ የሚል ፡ ቃለ ፡ በረከት ፡ የተሰጠው ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

| | | |
|---|---|---|
| አዛዥ ፡ ጠጉ ፡ | ሀገሩ ፡ (መንዝ) ፡ | አሉ ፡ ሊባኖስ ፡ |
| ጢኖ ፡ | ። | ላሎ ፡ ምድር ፡ |
| ቅብዐቶ ፡ | ። | አሉ ፡ ማርያም ፡ |
| ርእሴ ፡ | ። | ሲጠር ፡ ሚካኤል ፡ |
| የመንዝ ፡ ዕርገቱ ፡ | ። | ሐና ፡ ማርያም ፡ |
| አምሳሉ ፡ | ። | መሰለ ፡ ማርያም ፡ |
| ናዝራዊ ፡ | ። | መንዝ ፡ |
| ብፅዕት ፡ | ። | ምስአለ ፡ ማርያም |
| እይርክናን ፡ | ። | ። ። |
| ዮሐንስ ፡ | ። | ። ። |
| ዳዊት ፡ | ። | ፍጨት ፡ |
| መንፈሳዊት ፡ | ። | የትኖራ ፡ (ቍስቋም) |
| አዛዥ ፡ መሔዴ ፡ | ። | ። ። |
| ሊቀ ፡ ሠርጤ ፡ | ። | መርሐ ፡ ቤቴ ፡ |
| ሜም ፡ | ። | ላሎ ፡ ምድር ፡ (ጣማ ፡ ወንዝ) |

እንደ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ትውልድ ፡ አቈጣጠር ፡ የትውልዳቸውን ፡ ዝርዝር ፡ ከላይ ፡ ጀምረን ፡ በተራ ፡ ለማውረድ ፡ ምንም ፡ ባንሞክር ፤ በደግነታቸው ፣ በሃይማኖታውያንነታቸውና ፡ በዘረ ፡ መልካምነታቸው ፡ በጣም ፡ የታወቁትንና ፡ የከበሩትን ፡ አባቶቻቸውንና ፡ እናቶቻቸውን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ዝርዝር ፡ እነሆ ፡ ገልጠናቸዋል ።

ብፁዕ ፡ አባታችን ፤ በሕጻንነታቸው ፡ ወራት ፡ መንፈሳዊ ፡ ትምህርትን ፡ እየተማሩ ፡ የከሶ ፡ ማርያምን ፡ (የአመልሳ) ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እያገለገሉ ፡ በመንፈሳዊ ፡ አስተዳደግ ፡ አድገዋል ።

ዕድሜያቸው ፡ ዐሥራ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ሲሆንም ፤ በምናኔና ፡ በትምህርት ፡ ጣዕም ፡ ተመሥጠው ፡ ከአባታቸውና ፡ ከእናታቸው ፡ ቤት ፡ ወጥተው ፡ አምላካዊ ፡ ጥበብ ፡ እየመራቸው ፡ ወደ ፡ ትልቁ ፡ ገዳም ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገብተዋል ።

በዚሁም ፡ ምክንያት ፡ የመጀመሪያው ፡ መንፈሳዊ ፡ ዕድላቸው ፡ ሆኖ ፤ «አባቱንና ፡ እናቱን ፡ ከኔ ይልቅ ፡ የወደደ ፡ ለእኔ ፡ ሊሆን ፡ አይገባውም» ፡ እንዲሁም ፡ ቤቱን ፡ የተወ ፡ ሁሉ ፤ ወንድሞችንም ፡ እቶችንም ፡ አባትንም ፡ እናትንም ፡ ሚስትንም ፡ ልጆችንም ፡ እርሻንም ፡ ስለ ፡ ስሜ ፡ የተወ ፡ መቶ ፡ ዕጽፍ ፡ ይወስዳል» ። ብሎ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወደ ፡ ከፈተው ፡ ፍኖተ ፡ ምናኔ ፡ አድርሷቸዋል ። ማቴ ፡ ም ፡ ፲ ፡ ቍ ፡ ፴፯ ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ቍ ፡ ፳፱ ።

ኢያሱን ፡ ከሙሴ ፤ ኤልሣዕን ፡ ከኤልያስ ፤ ጢሞቴዎስንና ፡ ቲቶን ፡ ከቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ጋራ ፡ ያገናኘ ፤ አምላካዊ ፡ ፈቃድም ፡ ድንግልና ፡ ንጹሕ ፡ ከሆኑ ፡ በጾም ፡



በጸሎትና ፡ በስግደት ፡ ከተወሰኑት ፡ ከታላቁ ፡ መናኝ ፡ ሊ.ቅ ፡ ከመምህር ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስ ፡ ጋራ ፡ አገናኝቷቸዋል ።

መምህር ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስ ፡ ከምናኔያቸው ፡ ጽናትና ፡ ከባሕታዊነታቸው ፡ ፍጹምነት ፡ የተነሣ ፤ ከቀዳሚትና ፡ ከእሑድ ፡ በቀር ፡ ከሰኞ ፡ እስከ ፡ ዐርብ ፡ ያሉትን ፡ ዕለታት ፡ በጽኑ ፡ ትኅርምት ፡ የሚያሳልፉ ፤ በየሳምንቱም ፡ በዕለተ ፡ ዐርብ ፡ ጌታችን ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰውን ለማዳን ፡ የተቀበለውን ፡ መከራ ፡ እያሰቡ ፡ ለነዳያንና ፡ ለምስኪናን ፡ ምጽዋት ፡ የሚያደርጉና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ትሩፋት ፡ የሚሠሩ ፤ ስለ ፡ ንጽሕናቸውና ፡ ስለትሩፋታቸው ፡ ብዛትም ፡ ሕሙማን ፡ በጸሎታቸው ፡ የሚፈውሱላቸው ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፤ ይህን ፡ ቅዱስ ፡ አርአያ ፡ ለመውሰድና ፡ አብነትነታቸውን ፡ ለመከተል ፡ ብፁዕ ፡ አባታችንን ፡ የተባረከ ፡ ግንኙነት ፡ ገጥሞዋቸዋል ።

ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ የቅኔን ፡ ትምህርትና ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መጻሕፍትን ፡ ትርጓሜ ፡ ከመምህር ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስ ፡ ተምረዋል ፤ ከአባ ፡ ገብረ ፡ ሕይወትም ፡ ቅዳሴ ፡ አጥንተዋል ።

መንፈሳዊ ፡ ትምህርትን ፡ ጠንቅቀው ፡ ካወቁ ፡ በኋላ ፤ ሀብተ ፡ ሙሴ ፡ በኢያሱ ፤ ሀብተ ፡ ኤልያስ ፡ በኤልሣዕ ፡ እንደ ፡ አደረ ፤ በመምህር ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስ ፡ ያደረ ፡ መንፈሳዊ ፡ ሀብት ፡ ስለ ፡ አደረባቸው ፤ ለመንፈሳዊ ፡ ትምህርትና ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልግሎት ፡ ጽሙድ ፡ እንደ ፡ መሆናቸው ፡ መጠን ፤ የአቡነ ፡ ተክለ ሃይማኖትን ፡ በረከት ፡ ለመሳተፍና ፡ የመናንያን ፡ አበውን ፡ አርአያ ፡ ለመከተል ፡ ወደ ፡ ገዳሙ ፡ ቤተ ፡ ማኅበር ፡ ገብተው ፡ ከጽሙዳን ፡ አርድእት ፡ ጋራ ፡ በእርድና ፡ አገልግለዋል ።

በዚህ ፡ ጊዜም ፡ ከትሕትናቸው ፡ ፍጹምነት ፡ የተነሣ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወገቡን ፡ ታጥቆ ፡ የደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ እግር ፡ በአጠበ ፡ ጊዜ ፤ እኔ ፡ ጌታ ፡ መምህር ፡ ስሆን ፤ እግራችሁን ፡ ካጸብሁ ፡ እላንተም ፡ ደግሞ ፡ የባልንጀሮቻችሁን ፡ እግር ፡ ታጽቡ ፡ ዘንድ ፡ ይገባችኋል ። ምሳሌ ፡ ሰጥቻችኋለሁና ፡ «እኔ ፡ በእላንተ ፡ እንዳደረግሁ ፡ እላንተም ፡ ደግሞ ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ» ፡ ብሎ ፡ የሰጠንን ፡ ትእዛዝ ፡ ፈጽመዋል ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ቍ ፡ ፲፬ ― ፲፯ ።

ለመፍቀደ ፡ ገዳም ፡ የሚሆነውን ፡ የመንፈሳዊ ፡ ተአዝዞ ፡ ሥራን ፡ ሁሉ ፡ በመሥራት ፡ ያሳዩትን ፡ በጎ ፡ አርአያ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ከተመለከቱት ፡ ካህናት ፡ ዛሬም ፡ አንዳንዶቹ ፡ ስላሉ ፡ በዓይን ፡ ምስክርነታቸው ፡ ሊያስረዱ ፡ ይችላሉ ።

ሦስት ፡ ዓመት ፡ ያህልም ፡ በእርድና ፡ የገዳሙን ፡ ማኅበር ፡ ካገለገሉ ፡ በኋላ ፤ ፲፱፻፳ ፡ ዓ ም ፡ ሐምሌ ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ሥርዓተ ፡ ምንኵስናን ፡ ፈጽመው ፡ ከሊ.ቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ከአቡነ ፡ ማቴዎስ ፡ የቅስና ፡ ሥልጣን ፡ ተቀብለዋል ።

በሥልጣናቸውም ፡ ከካህናትና ፡ ከዲያቆናት ፡ ጋራ ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ በሚያገለግሉበት ፡ ጊዜ ፡ በየካህናቱና ፡ በየምዕመናኑ ፡ ዘንድ ፡ እጅግ ፡ መከበርና ፡ መወደድ ነበራቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

በደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገድልና ፡ ትሩፋት ፡ እየሠሩ ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፤ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ግብረ ፡ ገቢነታቸው ፡ ከሚያቀርብላቸው ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ለመሸሽ ፡ ፲፱፻፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ሔዱና ፡ ከሰው ፡ ተለ ይተው ፡ በጎሐ ፡ ጽዮን ፡ በታች ፤ ወደሚገኘው ፡ በዐባይ ፡ ዳር ፡ ወደ ፡ አለው ፡ ወደ ፡ ዋሻ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ገዳም ፡ ደረሱ ።

በዚያም ፡ ወደ ፡ አንዲት ፡ ዋሻ ፡ ገቡና ፡ የመንፈሳዊ ፡ ተጋድሎ ፡ ሥራቸውን ቀጠሉ ። ሦስት ፡ ወር ፡ ያህልም ፡ በተባሕትዎ ፡ ሥራ ፡ ተወስነው ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ የመናገሻ ፡ (የአምባ) ፡ ማርያም ፡ ገዳም ፡ ብዙ ፡ ግሑሣን ፡ ባሕታውያን ፡ ያሉበት ፡ በመሆኑ ፡ ወደዚያ ፡ ተዛውረው ፡ የገድል ፡ ሥራቸውን ፡ ይቀጥሉ ፡ ዘንድ ፡ ከወደ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ምልክት ፡ ስለ ፡ አገኙ ፤ ወደ ፡ መናገሻ ፡ ገዳም ፡ ገብተው ፡ ከባሕታው ያን ፡ ጋራ ፡ በተባሕትዎ ፡ ተወስነው ፡ ተቀመጡ ።

ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱና ፡ ከፍላጎቱ ፡ ሸሽተው ፡ በዚያው ፡ ገዳም ፡ ተቀ ምጠው ፡ ሳሉ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሥራውን ፡ ሁሉ ፡ በምክንያት ፡ ስለሚሠራው ፤ የኢትዮ ጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ልጅ ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ የትሩፋታቸውን ፡ ብዛትና ፡ ግብረ ፡ ገብነታቸውን ፡ ስለሰሙ ፤ መልክተኞቻቸውን ፡ ልከው ፡ ወደዋናው ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ አስጠሩዋቸው ።

ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ምኒልክ ፡ እንደ ፡ ደጊቱ ፡ እንደ ፡ ዕሌኒ ፡ ንግ ሥት ፡ ሃይማኖታቸው ፡ የጸና ፤ ምግባራቸው ፡ የቀና ፡ ከመሆናቸው ፡ የተነሣ ፡ ካህ ናተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያከብሩ ፤ የመነኰሳትንና ፡ የባሕታውያንን ፡ መንፈሳዊ ፡ አር አያ ፡ በጣም ፡ የሚያፈቅሩ ፡ ነበሩና ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ወደ ፡ ንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ ዝናቸው ፡ የተሰማ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ መጠን ፡ እንደ ፡ አባ ቶቻቸው ፡ እንደ ፡ ሐዋርያት ፡ እጅግ ፡ መወደድና ፡ መከበርን ፡ አገኙ ።

ንግሥቲቱም ፤ ‹በመናገሻ ፡ ግርጌ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠራለሁ ፡ በእመቤታ ችን ፡ በወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ስም ፡ አስገድሜም ፡ የመነኰሳትና ፡ የባሕታውያን ፡ መኖ ሪያ ፡ አደርገዋለሁና ፡ እባክዎ ፡ አባቴ ፡ ለገዳሙ ፡ አስተዳደር ፡ እርስዎ ፡ ረዳት ፡ ይሁኑ ልኝ ፡ መነኰሳቱንም ፡ ይጠብቁልኝ» ፡ ብለው ለምነዋቸዋል ።

ብፁዕ ፡ አባታችንም ፡ ንግሥቲቱን ፡ ያነጣጣቸው ፡ ፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መሆ ኑን ፡ ተመልክተው ፤ መንፈሳዊ ፡ አሳባቸውን ፡ በቅንነት ፡ ተቀብለው ፡ ወደ ፡ መናገሻ ተመልሰዋል ።

እንደ ፡ ገናም ፡ ገዳማዊ ፡ አገልግሎታቸውን ፡ ቀጥለው ፡ ሌሊት ፡ በቤተ ፡ ክር ስቲያኑ ፡ ውስጥ ፡ ጸሎተ ፡ ዕጣን ፡ ደግመው ፡ ሲያጥኑና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጸሎት ፡ ሲያደርሱ ፡ አድረው ፡ ቀን ፡ ቅዳሴ ፡ በማስተማር ፡ ይውሉ ፡ ነበር ።

በዚህ ፡ አገልግሎት ፡ ተወስነው ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፤ የገ ዳሙ ፡ መነኰሳት ፡ መርጠዋቸው ፡ በንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ምኒልክ ፡ ፈቃድ ፡ የገዳሙ ፡ መምህር ፡ (አበ ፡ ምኔት) ፡ ሆነው ፡ ተሾመዋል ።



በሹመታቸውም ፡ እንደ ፡ ኄር ፡ ላእክ ፡ ሆነው ፡ በገዳሙ ፡ ውስጥ ፡ ለሚያገለ ግሉት ፡ መነኰሳት ፡ የፍቅርና ፡ የትሕትናን ፡ አርኣያ ፡ እያሳዩ ፡ አባት ፡ እናት ፡ ለሌ ሏቸውም ፡ የርኅራኄ ፡ እርዳታ ፡ እያደረጉ ፡ ትሩፋትን ፡ አብዝተው ፡ ሠርተዋል ። የማኅበሩንም ፡ ጉዳይ ፡ ለመንግሥት ፡ እያመለከቱ ፡ ለገዳሙ ፡ ብዙ ፡ መተዳደሪያ ፡ አሰጥተዋል ።

ግርማዊት ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ፲፱፻፳፪ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ መጋ ቢት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ዐርፈው ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ ከተለዩ ፡ በኋላ ፤ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥታዊው ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ተተኩ ፤ የብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ግብረ ፡ ገብነት ፡ ከቀድሞ ፡ ጀምሮ ፡ በግርማዊ ነታቸው ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ በመሆኑ ፤ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ አስጠርተው ፡ ፲፱፻፳፬ ዓ ፡ ም ፡ የካቲት ፡ ፳፮ ፡ ቀን ፡ በመናገሻ ፡ ገዳም ፡ ሹመታቸው ፡ ላይ ፡ የመንበረ መንግሥትን ፡ (የቅዱስ ፡ ገብርኤልን ፡ ደብር ፡ ) መምህርነት ፡ ሰጧቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የመናገሻ ፡ ገዳም ፡ ማኅበር ፡ “ደጉ ፡ ርኅሩኁ ፡ ቸሩ ፡ አባታችን እንግዲህ ፡ ሊርቁን ፡ ነው ፤» ብለው ፡ አዝነዋል ።

የመንበረ ፡ መንግሥት ፡ ካህናት ፡ ግን ፡ ቸር ፡ ግብረ ፡ ገብ ፡ ዐዋቂ ፡ መም ህር ፡ ተሾሙልን ፡ ብለው ፡ በጣም ፡ ተደስተዋል ።

የመንበረ ፡ መንግሥትን ፤ ካህናት ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ትሩፋት ፡ እያስደሰቱ ፡ ዐሥር ፡ ወር ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፤ ያንኑ ፡ የለመዱትን ፡ ገዳማዊ ፡ አገልግሎት ፡ ስለ ፡ መረጡ ፤ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትን ፡ አስፈቅደው ፡ ወደ ፡ መናገሻ ፡ ገዳም ፡ ተመልሰዋል ።

ከዚህ ፡ በኋላም ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አስጠርተው ፡ ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መጋቢት ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ያሉትን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ገዳማት ፡ መምህርነት ፡ ሰጥተው ፡ ሹመዋቸዋል ። በዚህ ፡ ጊዜም ፡ የመናገሻ ፡ ገዳም ፡ መነኰሳት ፡ “እኛን ፡ ለማን ፡ ትተውን ፡ ይሔዳሉ„ ፡ እያሉ ፡ ተላቅሰዋል ።

ይኸውም ፡ የእስራኤል ፤ ቸር ፡ ጠባቂያቸው ፡ ኤልያስ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ባረገ ፡ ጊዜ ፤ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ኤልሣዕ ፡ „አባቴ ፡ ሆይ ፡ የእስራኤል ፡ ኃይላቸው ፡ ብርታታቸው ፡ ስትሆን ፤ ለማን ፡ ትተኸን ፡ ትሔዳለህ„ ፡ እያለ ፡ እንደ ፡ አለቀሰው ፡ ልቅሶ ፡ ነው ።

ፍቅረ ፡ እግዚአብሔርና ፡ ፍቅረ ፡ቢጽ ፡ ብፁዕ ፡ አባታችንን ፡ ሁልጊዜ ፡ ስለ ፡ ማይለዩዋቸው ፤ ወደ ፡ ተሾሙባቸው ፡ ወደ ፤ ኢየሩሳሌም ፡ ገዳማት ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ የሀገሩ ፡ ሰዎችና ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ መነኰሳት ፡ በትሩፋታቸው ፡ ይጠቅሙናል ፡ ብለው ፡ በደስታ ፡ ተቀበሏቸው ።

የኢየሩሳሌምን ፡ መነኰሳት ፡ በሰላምና ፡ በፍቅር ፡ በደግነታቸውም ፡ እያጽናኑ ፡ ገዳማቱንም ፡ ጧትና ፡ ማታ ፡ እየጐበኙ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡

www.ethiopianorthodox.org

በሆነበት ፡ ዘመን ፡ (በመዋዕለ ፡ ሥጋዌው) ፡ ድንቅ ፡ ድንቅ ፡ ተአምራት ፡ ያደረገ ባቸውን ፡ ቅዱሳት ፡ መካናት ፡ እየጐበኙ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ቆይተዋል ።



ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ገዳማት ፡ መምህርነት ፡ በተሾሙ ፡ ጊዜ ።

ከሁለት ፡ ዓመት ፡ በኋላም ፤ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንዲመለሱ ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ቃለ ፡ መልእክት ፡ በደረሳቸው ፡ ጊዜ ፤ የገዳማቱ ፡ መነኰሳት ፡ ትተውን ፡ ሊሔዱብን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ በጣም ፡ አዝነዋል ።

በተነሡ ፡ ጊዜም ፡ እኅሌቶቹ ፡ እስከ ፡ ልዳ ፡ ድረስ ፤ እኅሌቶቹ ፡ እስከ ፡ ባቡሩ ፡ ጣቢያ ፡ ድረስ ፡ በጥልቅ ፡ አፍቅሮት ፡ ሸኝተዋቸዋል ።

፲፱፻፳፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የካቲት ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ መናገሻ ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፤ ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ገብተው ፡ በአ



ምኃ ፡ መንፈሳዊት ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ከቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጋራ ፡ ተገናኝተዋል ።

ወዲያው ፡ ባራተኛው ፡ ቀን ፡ መጋቢት ፡ ፳፬ ፡ (በአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ወርኀዊ ፡ በዓል) ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በጎ ፡ ፈቃድ ፡ ዕጨጌ ፡ ተብለው ፡ ተሾመው ፡ በአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መንበር ፡ ላይ ፡ ተቀምጠዋል ።

የበቁት ፡ መናኒ ፡ አስተማሪያቸው ፡ መምህር ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስ ፡ "በደቀ ፡ መዛሙርቶቼ ፡ መካከል ፡ ለዕጨጌነት ፡ ሹመት ፡ የሚበቃ ፡ የተመረጠ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ አለ" ፡ እያሉ ፡ ትንቢት ፡ ይናገሩ ፡ ነበርና ፡ ትንቢታቸው ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ተፈጽሟል ።

የዕጨጌነቱንም ፡ መዓርግ ፡ በተቀበሉ ፡ ጊዜ ፤ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ለዕጨጌዎች ፡ የተሠራውን ፡ ሥርዓተ ፡ ክብር ፡ አድርሰውላቸዋል ። ይኸውም ፤ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡ መሳፍንት ፡ መኳንንትና ፡ ሠራዊት ፡ ሊቃውንትና ፡ ካህናት ፡ በተሰበሰቡበት ፡ የክብር ፡ ልብስ ፡ አልብሰው ፡ ጌራ ፡ ወርቅ ፡ አቀዳጅተው ፡ በእጃቸው ፡ ቀጸላ ፡ ሥን ፡ የወርቅ ፡ መስቀል ፡ የወርቅ ፡ ዘንግ ፡ ሰጥተው ፡ የሚቀመጡበትንም ፡ የወርቅ ፡ ወንበርም ፡ ሰጥተው ፡ በክብር ፡ አስቀምጠዋቸዋል ።

ከዚህ ፡ በኋላም ፡ በወርቅ ፡ በብር ፡ ጌጥ ፡ በተንቈጠቈጠ ፡ በቅሏቸው ፡ ላይ ፡ አስቀምጠው ፡ የወርቅ ፡ ጥላ ፡ (ተድባበ ፡ ወርቅ) ፡ ሰጥተው ፡ እንደ ፡ ሥርዓቱ ፡ እስከ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ በር ፡ ድረስ ፡ በእግራቸው ፡ ሸኝተዋቸዋል ።

መሳፍንቱና ፡ መኳንንቱ ፡ ሊቃውንቱና ፡ ካህናቱም ፡ ብፁዕ ፡ አባታችንን ፡ አጅበው ፡ (በፊት ፡ በኋላ ፡ ተሰልፈው ፡ እስከ ፡ ማረፊያቸው ፡ ሔደዋል ። ወደ ፡ ማረፊያ ፡ ቤታቸው ፡ በገቡ ፡ ጊዜም ፡ ለተከተሏቸው ፡ ሁሉ ፡ ሰፊ ፡ ግብዣ ፡ ተደርጓል ።

## በዕጨጌነታቸው ፡ የፈጸሙት ፤
## ሐዋርያዊ ፡ ተጋድሎ ፡

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በግፍ ፡ ለመውረር ፡ የመጡትን ፡ ፋሽሽቶች ፡ ለመከላከል ፤ ሠራዊቶቻቸውን ፡ አስከትተው ፡ በዘመቱ ፡ ጊዜ ፤ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የገለጥነውን ፡ የጅግኖችን ፡ መንፈስ ፤ የሚያበረታታ ፡ ብርቱ ፡ ብርቱ ፡ ቃለ ፡ ስብከት ፡ ለመላው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ አስተላልፈዋል ።

አርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ሃይማኖትን ፡ የሚያናውጥ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ የሚያቃጥል ፡ ምእመናንን ፡ የሚያሠቃይና ፡ የሚፈጅ ፡ አረማዊ ፡ ከመጣ ፡ የመከራው ፡ ቀዳሚ ፡ መሆን ፡ ይገባኛል ፡ ብለው ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጋር ፡ ዘምተዋል ።

በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ የተቀመጡበት ፡ በቅሎ ፡ በአረር ፡ ተመትቶ ፡ እስኪወድቅና ፡ የለበሱት ፡ ካፓ ፡ አምስት ፡ ላይ ፡ በጥይት ፡ እስኪበሳሳ ፡ ድረስ ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሳይለዩ ፡ ብዙ ፡ የቈራጥነት ፡ ሥራ ፡ ሠርተዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

ሠራዊቱንም ፡ እያጽናኑ ፡ ቆይተዋል ። አፍሮ ፡ አይገባ ፡ የተባለውንም የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ የእጅ ፡ መስቀል ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ራስ ፡ ላይ ሲዘረጉና ፡ ቡራኬ ፡ ሲያደርጉ ፣ በላያቸው ፡ ያንዣበበው ፡ የፋሽሽቶች ፡ እሳታዊ አደጋ ፡ ምንም ፡ ሳይነካቸው ፡ ይመለስ ፡ ነበር ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፣ በጦርነቱ ፡ ውስጥ ፡ እንዳንድ ፡ ወታደር ፡ ሆነው ፡ ሕይወታቸውን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ለማሳለፍ ፡ ቍርጥ ፡ አሳብ ፡ ባደረጉ ፡ ጊዜ ፣ ብፁዕ ፡ አባታችን ፣ ከመሳፍንት ፣ ከመኳንንትና ፡ ከጦር ፡ አለቆች ፡ ጋራ ፡ ተመካክረው ፡ ከብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ ጋራ ፡ በመንፈሳዊ ፡ ሥልጣናቸው ፡ እስከ ፡ መያዝና ፡ እስከ መወሰን ፡ ደርሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ረድኤት ፡ በብፁዕነታቸው ፡ ጸሎት ፡ አንደኛውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ምክንያተ ፡ ድኅነት ፡ ለማትረፍ ፡ ችለዋል ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከጦርነቱ ፡ ግንባር ፡ ተመልሰው ፡ ወደ ፡ ኤሮፕ ፡ ሲሔዱ ፣ እስከ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ አብረዋቸው ፡ ሔደዋል ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ሳሉም ፣ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደገለጥነው ፡ የቀረቧቸውን ፡ በስብከት ፣ የራቋቸውን ፡ በመልእክት ፡ እያጽናኑ ፡ ስለ ፡ ነፃነታቸው ፡ በተሟቀዩ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ የማይረሳ ፡ የአባትነትና ፡ የሐዋርያነትን ፡ ውለታ ፡ ፈጽመዋል ።

በኢየሩሳሌም ፡ ሳሉ ፣ በያመቱ ፡ ወደ ፡ ቆሮንቶስና ፡ ወደ ፡ ዮርዳኖስ ፡ በረሃ ፡ እየገቡ ፣ ጾመ ፡ አርብዓን ፡ በጽኑ ፡ ተጋድሎና ፡ በጽኑ ፡ ቀኖና ፡ ይጾሙ ፡ ነበር ። ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነጻነት ፣ ስለ ፡ ሃይማኖታዊ ፡ ጉዳይና ፡ ስለ ፡ መንፈሳዊ ፡ አገልግሎት ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጋራ ፡ ይላላኩ ፡ ነበር ።

በዚሁ ፡ ጊዜም ፣ የግርማዊነታቸውን ፡ መንፈሳዊ ፡ ፈቃድ ፡ ተመልክተው ፡ የመድኀኔ ፡ ዓለምን ፡ ጽላት ፡ (ዛሬ ፡ ምስካየ ፡ ኅዙናን ፡ የተባለውን) ፡ አምስት ፡ መነኰሳትን ፡ ለግብረ ፡ ተልእኮ ፡ የሚፈለጉትን ፡ ንዋያተ ፡ ቅድሳትንና ፡ ቅዱሳት ፡ መጽሐፍትን ፡ ወደ ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ልከዋል ።

---

## የኢትዮጵያ ፡ ትንሣኤና ፡ የብፁዕነታዊ ።
## ሐዋርያዊ ፡ ረድኤት ።

እግዚአብሔር ፡ ኢትዮጵያን ፡ በተአምራቱ ፡ የሚጐበኝበት ፡ ዘመን ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፣ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጦርነቱን ፡ ለመቀጠል ፡ ከእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ካርቱም ፡ ስለ ፡ መጡ ፣ ብፁዕ ፡ አባታችንን ፣ ከብፁዕነታቸው ፡ ጋራ ፡ የነበሩትንም ፡ መሳፍንትና ፡ መኳንንት ፣ በኢየሩሳሌም ፡ የነበሩትን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አስጠሯቸውና ፡ ፲፱፻፴፪ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ በካርቱም ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ ተገናኙ ።

ከዚያም ፡ ተጕዘው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጠረፍ ፡ ወደ ፡ አሜድላ ፡ ደረሱ ። በአሚድላ ፡ ላይ ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ በመጀመሪያ ፡ በጸሎተ ፡ አኰቴት ፡



ጸለዩ ። ቀጥሎም ፡ የዳዊትን ፡ መዝሙር ፡ ይጸልዩ ፡ አሏቸውና ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ኻያኛውን ፡ መዝሙር ፡ እግዚኦ ፡ በኀይልከ ፡ ይትፌሣሕ ፡ ንጉሥ ፡ ወብዙኀ ፡ ይትሐሠይ ፡ በአድኅኖትከ ፡ ብለው ፡ እስከ ፡ ፍጻሜው ፡ ጸለዩ ።

ብፁዕ ፡ አባታችንም ፡ ዐሥራ ፡ ዘጠኘኛውን ፡ መዝሙር ፣ ይስማዕከ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዕለተ ፡ ምንዳቤከ ። ወይቁም ፡ ለከ ፡ ስሙ ፡ ለአምላከ ፡ ያዕቆብ ፡ ወይፈኑ ፡ ለከ ፡ ረድኤተ ፡ እመቅደሱ ፡ ብለው ፡ እስከ ፡ ፍጻሜው ፡ ጸለዩ ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎም ፡ ከማቴዎስ ፡ ወንጌል ፡ ሰባተኛ ፡ ምዕራፍን ፡ ሰባተኛ ፡ ቍጥርን ፡ አውጥተው ፡ „ሰአሉ ፡ ወይትወሀበክሙ ፡ ኅሡ ፡ ወትረክቡ ። ጐድጕዱ ፡ ወይትረኀወክሙ ። እስመ ፡ ኵሉ ፡ ዘሰአለ ፡ ይነሥእ ፣ ወዘሂ ፡ ኀሠሠ ፡ ይረክብ ። ወለዘሂ ፡ ጐድጐደ ፡ ይትረኀዋ ፡ ብለው ፡ እስመ ፡ ከማሁ ፡ አሪትኒ ፡ ወነቢያትኒ ፡ እስከሚለው ፡ ድረስ ፡ አነበቡ ።

ነቢዩ ፡ ዳዊት ፣ "የእግዚአብሔርን ፡ ድንቅ ፡ ሥራውን ፡ ተናገሩ ፡ ባለው ፡ መሠረት ፣ እዚህ ፡ ላይ ፡ ለአንባቢዎችና ፡ ለተመልካቾች ፡ የምንገልጠው ፡ እግዚአብሔር ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ያደረገው ፡ አንድ ፡ ድንቅ ፡ ተአምራት ፡ አለ ። ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መስከረም ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ በካርቱም ፡ የመስቀል ፡ ደመራ ፡ ተደምሮ ፡ ሳለ ፣ ወወሀብኮሙ ፡ ትእምርተ ፡ ለእለ ፡ ይፈርሁከ ፡ ተብሎ ፡ ከተሰበከ ፡ በኋላ ፣ ከዮሐንስ ፡ ወንጌል ፡ ም፡ ፫ ቍ፡ ፩–፳፫ ፡ ሲያነቡ ፡ ቀስተ ፡ ደመና ፡ ድንገት ፡ በወንጌሉና ፡ በብፁዕነታቸው ፡ ላይ ፡ ተተክሎ ፡ ታይቷል ።

ይህንንም ፣ ያን ፡ ጊዜ ፣ የነበሩ ፡ መኳንንት ፡ እነ ፡ ራስ ፡ ብሩ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤልና ፡ አንድ ፡ የውጪ ፡ ሀገር ፡ ሰው ፡ አይተናል ፡ ብለው ፡ ተናግረዋል ።

ያ ፡ የውጪው ፡ ሀገር ፡ ሰውም ፡ (እንግሊዛዊው) ፡ አሁን ፡ እርስዎ ፡ ወንጌሉን ፡ ሲያነቡ ፡ መጥቶ ፡ በላይዎ ፡ የታየው ፡ ቀስተ ፡ ደመና ፡ የምን ፡ ምልክት ፡ ይመስልዎታል ? ብሎ ፡ ቢጠይቃቸው ፡ ለኖኅ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ የዕርቅ ፡ ምልክት ፡ ያሳየው ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ አሳይቶ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በምሕረቱ ፡ የሚጐበኛት ፡ ቢሆን ፡ ነው ። ሰንደቅ ፡ ዓላማችንም ፡ ይህንኑ ፡ ቀስተ ፡ ደመናውን ፡ የሚመስል ፡ ነው ፡ ብለው ፡ መልሰውለታል ። አሪ ፡ ዘፍ ፡ ም፡ ፱ ቍ፡ ፲፫ ።

ከዚህም ፡ አያይዘው ፣ ከሉቃስ ፡ ወንጌል ፡ ዐሥራ ፡ ሁለተኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ሠላሳ ፡ አምስተኛ ፡ ቍጥር ፡ አወጡና ፡ "ወይኩን ፡ ቅናተ ፡ ሐቌክሙ ፡ ወኀትወ ፡ መኃትዊክሙ ፣ አንትሙኒ ፡ ኩኑ ፡ ከመ ፡ ዕደው ፡ እለ ፡ ይጸንሑ ፡ እግዚኦሙ ፡ እስከ ፡ የአቱ ፡ እም ፡ ከብካብ ። ከመ ፡ መጺአ ፣ ወጐድጕዶ ፡ ያርኅውዎ ፡ ሶቤሃ ። ብፁዓን ፡ እሙንቱ ፡ አግብርት ፡ ሰበ ፡ ይመጽእ ፡ እግዚኦሙ ፡ እለ ፡ ይረክቦሙ ፡ እንዘ ፡ ከመዝ ፡ ይገብሩ ፡ ወይተግሁ ፡ የሚለውን ፡ ወአንትሙኒ ፡ ድልዋኒክሙ ፡ ሀልው ፡ እስከ ፡ ሚለው ፡ ድረስ አነበቡ ።

www.ethiopianorthodox.org

ከዚህ ፡ በኋላም ፡ «ወክዕበ ፡ ናስተበቍዖ ፡ ለአምላክ ፡ ምሕረት ፡ ዘረዳእኮ ፡ ለአብርሃም ፡ አመ ፡ ይቀትሎሙ ፡ ነገሥት» ፡ የሚለውን ፡ ጸሎት ፡ አደረሱና ፡ አራቱን ፡ መዓዝናተ ፡ ምድር ፡ (መዓዝናተ ፡ ኢትዮጵያ) ፡ ባረኩ ። ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትንም ፡ ባረኳቸው ። ወዲያውም ፡ «ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ እስራኤል ፡ ዘተሣሀለነ ፡ ወገብረ ፡ መድኀኒተ ፡ ለሕዝበ ፡ ዚአሁ ፡ አንሥአ ፡ ለነ ፡ ቀርነ ፡ መድኀኒትነ ፡ እም ፡ ቤተ ፡ ዳዊት ፡ ገብሩ ። ብለው ፡ በሣህሉ ፡ ወበምሕረቱ ፡ ለአምላክነ ፡ ለዘሐወጸነ ፡ እም ፡ አርያም ፡ ወሠረቀ ፡ ከመ ፡ ያርእዮሙ ፡ ብርሃኖ ፡ ለእለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡ ወጽላሎተ ፡ ሞት ፡ ከመ ፡ ያርትዕ ፡ እገሪነ ፡ ውስተ ፡ ፍኖተ ፡ ሰላም ፡ እስከ ፡ ሚለው ፡ ድረስ ፡ ጸለዩ ።

## ከማሳረጋቸው ፡ በፊት ፡ የተናገሩት ፡ ቃለ ፡ በረከት ።

« እግዚአብሔር ፡ ቀድሞ ፡ በኢያሱ ፡ አድሮ ፡ ኢያሱም ፡ ታቦተ ፡ ጽዮንን ፡ አሲዞ ፡ ከተጓዘ ፡ በኋላ ፤ ለአምሳ ፡ ለስሳ ፡ የማይከፈት ፡ የብረት ፡ ሣንቃ ፡ ሰባብሮ ፡ ከፍቶ ፡ ቅጽሩንም ፡ አፍርሶ ፡ አሕዛብን ፡ አጥፍቶ ፡ አባቶቻችንን ፡ እስራኤልን ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ ርስት ፡ እንደ ፡ አገባቸው ፡ ግርማዊም ፡ ስደተኞች ፡ ሕዝብዎንና በዱር ፡ በገደል ፡ ያሉ ፡ አርበኞች ፡ ሠራዊትዎን ፡ ሰብስበው ፡ ወደ ፡ ተወደደች ፡ ወደ ፡ ለምለሚቱ ፡ ሀገርዎ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለመግባት ፡ ያብቃዎ ። አምላከ ፡ አበው ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የአባቶችዎን ፡ ሀብተ ፡ መዊዕ ፡ ያሳድርብዎ ። ብለው ፡ መርቀዋል ።

ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ቃለ ፡ በረከቱን ፡ ከተናገሩና ፡ ካሳረጉ ፡ በኋላ ፤ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጥር ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ በኡሜድላ ፡ ላይ ፡ አቁመዋል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፤ ጥር ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጋራ ፡ ከኡሜድላ ፡ ተነሥተው ፡ ድንድር ፡ ወደ ፡ ተባለው ፡ ወንዝ ፡ ደርሰዋል ። በዚያም ፡ አንድ ፡ ሳምንት ፡ ከተቀመጡ ፡ በኋላ ፡ ወደምድረ ፡ ጐጃም ፡ ክፍል ፡ ወደ ፡ በለያ ፡ ገብተዋል ። በዚያም ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ያህል ፡ ቆይተው ፡ ወደ ፡ ቡሬ ፡ መጥተዋል ።

ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ላይ ፡ ኀይሉን ፡ ስለ ፡ አሳደረ ፤ በግርማዊነታቸው ፡ ድል ፡ አድራጊነት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጠላቶች ፡ እየተባረሩላቸውና ፡ ሥፍራውን ፡ ሁሉ ፡ እየለቀቁላቸው ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ገቡ ።

በደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በአምስቱ ፡ ዘመናተ ፡ መከራ ፡ ለተጐዱት ፡ ሕዝቦቻቸውና ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ብዙ ፡ ችሮታ ፡ ሲያደርጉ ፤ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ የቀዳም ፡ ሥዑር ፡ በዓል ። በዋለበት ፡ ቀን ፡ የጐጃም ፡ ገዳማ



ትና ፡ አድባራትን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትንም ፡ በተለመደው ፡ ትሩፋታቸው ፡ ጐብኝተዋል ።

በዓለ ፡ ትንሣኤውንም ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጋራ ፡ በዚያው ፡ በደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ካከበሩ ፡ በኋላ ፤ ከዚያ ፡ ተነሥተው ፡ ጕዞዋቸውን ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ቀጥለዋል ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጠላቶች ፡ (ሠራዊተ ፡ ሮም) ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከብዙ ፡ ኃይል ፡ ጋራ ፡ መምጣታቸውን ፡ እየሰሙ ፡ ምንም ፡ በቍጥር ፡ እጅግ ፡ የበለጡ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ቢኖሩዋቸውም ፤ በታላቅ ፡ ድንጋጤ ፡ የጦርነት ፡ ድርጅታቸውን ፡ እያፈረሱ ፡ በመብረራቸውና ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ እጅ ፡ ላይ ፡ በመውደቃቸው ፤ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ኃይሉን ፡ ለሰጠ ፡ እግዚአብሔር ፡ የማይቋረጥ ፡ ምስጋና ፡ ያቀርቡ ፡ ነበር ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ዐባይ ፡ የተባለውን ፡ ትልቅ ፡ ወንዝ ፡ (ፈለገ ፡ ግዮንን) ፡ ከተሻገሩ ፡ በኋላ ፤ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ለአምላከ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ምስጋና ፡ ማቅረብን ፡ ስለፈቀዱ ፤ ብዙ ፡ ሠራዊት ፡ ተከትሏቸው ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ደረሱ ።

ከጠላቶች ፡ አደጋ ፡ (ከሞት) ፡ የተረፉ ፡ በጥላ ፡ ያረፉ ፡ ካህናትና ፡ ምእመናን ፡ በብዙ ፡ ምስጋና ፡ በብዙ ፡ ይባቤ ፡ ተቀበሏቸው ። ካህናቱም ፡ የዘመሩት ፡ መዝሙር ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ነው ። «ንግሩ ፡ አድኅኖቶ ፡ ለኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ወዜንዉ ፡ ሠናይቶ ፡ ለወልደ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ (ልዑል ፡ ራስ ፡ ካሣ) ፡ ስብኩ ፡ ይሰማእ ፡ እስከ ፡ አጽናፈ ፡ ምድር ።

ወደቂቀ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ይትሐሠዩ ፡ በንጉሦሙ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ። እስመ ፡ ተሞዐ ፡ ሞት ፤ ወተሰደ ፡ ኃይለ ፡ ጽልመት ፡ በገብረ ፡ ጊዮርጊስ» ። ብፁዕ ፡ አባታችንና ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ። የካህናቱና ፡ የምእመናኑ ፡ ቍጥር ፡ እጅግ ፡ ማነሱን ፡ ተመልክተው ፡ በጣም ፡ አዝነዋል ።

ወዲያውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጠላቶች ፡ በግፍ ፡ የፈጀዋቸው ፡ የካህናቱና ፡ የምእመናኑ ፡ አዕጽምት ፡ ከየተበተኑበትና ፡ ከየወደቁበት ፡ እንዲሰበሰቡ ፡ ጽኑ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጥተዋል ። በትእዛዛቸውም ፡ መሠረት ፡ ፍልሰተ ፡ አዕጽምቱ ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ግንቦት ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ተፈጽሟል ። በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ የነበሩት ፡ ካህናቱና ፡ ምእመናኑም ፡ በዚሁ ፡ በአዕጽምቱ ፡ መሰብሰብ ፡ ምክንያት ፡ ግፍን ፡ ያስወገዱላቸውን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱንና ፡ የብፁዕነታቸውንም ፡ ፅድለኛነት ፡ አድንቀዋል ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡ ወደ ፡ ዋና ፡ ሙናገሻ ፡ ከተማቸው ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ የሚገቡበት ፡ ቀን ፡ በተቃረበ ፡ ጊዜ ፤ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ ጋር ፡ ከደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ተነሥተው ፡ በልዑል ፡ ራስ ፡ ካሣ ፡ ከተማ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ አድረዋል ።

ከሁለት ፡ ቀን ፡ በኋላም ፡ ከዚያ ፡ ተነሥተው ፡ ጕዞዋቸውን ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ቀጥለው ፡ ሳሉ ፤ አምስት ፡ ዓመት ፡ በዱር ፡ በገደል ፡ ተበትነው ፡ የአርበኝ

www.ethiopianorthodox.org

ነት ፡ ተጋድሎ ፡ ያደርጉ ፡ የነበሩ ፡ ጀግኖች ፡ የጦር ፡ መሪያቸውን ፡ ራስ ፡ አበበ ፡ አረጋይን ፡ ተከትለው ፡ በደብረ ፡ ጽጌ ፡ አቅራቢያ ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከብፁዕ ፡ አባታችንና ፡ ከልዑል ፡ ራስ ፡ ካሣ ፡ ጋራ ፡ ተገናኝተዋል ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በጦር ፡ ሠራዊቶቻቸውና ፡ በየመንገዱ ፡ በሚቀበሏቸው ፡ አርበኞቻቸው ፡ ታጅበው ፡ ወደአዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ም ፡ ሚያዝያ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ገብተዋል ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ ሐዋርያዊ ፡ ቃል ፡ ተናግረዋል ። "ከወዳጁ ፡ ከዳዊት ፡ ወገን ፡ ለድኅነታችን ፡ ምክንያት ፤ ለልቡናችን ፡ መመኪያ ፤ ጠላትን ፡ ማጥቂያ ፡ የሆንንን ፡ ከመገዛት ፡ ነጻ ፡ ያደረገን ፡ ግርማዊነትዎን፡ ያስነሣልን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ።

እግዚአብሔር ፡ ቀድሞ ፡ በኢያሱ ፡ አድሮ ፡ ኢያሱም ፡ ታቦት ፡ ጽዮንን ፡ አሲዞ፡ ከተጓዘ ፡ በኋላ ፤ ለአምሳ ፡ ለስሳ ፡ የማይከፈት ፡ የብረት ፡ ሣንቃ ፡ ሰበብሮ ፡ ከፍቶ፡ ቅጽሩንም ፡ አፍርሶ ፡ አሕዛብን ፡ አጥፍቶ ፡ አባቶቻችን ፡ እስራኤልን ፤ ወደምድረ ፡ ርስት ፡ እንደ ፡ አገባቸው ፤ ግርማዊነትዎ ፡ ምስክየ ፡ ኅዙናን ፡ ታቦተ ፡ መድኃኔ ፡ ዓለምን ፡ ይዞ ፤ ግፈኛውን ፡ ጠላታችንንም ፡ አጥፍቶ ፡ ከመገዛትም ፡ ነጻ ፡ አውጥቶ፡ ወደ ፡ ለምለሚቱ ፡ ሀገራችን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስለአገባን ፤ ለእግዚአብሔር ፡ የማቀርበው ፡ ምስጋና ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ ለግርማዊነትዎ ፤ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነንም ፡ ከልዑላን ፡ ልጆችዎ ፡ ጋራ ፡ የዕድሜ ፡ መርዘምን ፡ የጠላት ፡ መድከምን ፡ ይስጥልን ።

ምድራዊ ፡ መንግሥትን ፡ አምልቶ ፡ አስፍቶ ፡ እንደ ፡ ሰጠዎት ፤ ኋላም ፡ የማታልፍ ፡ ሰማያዊት ፡ ርስትዎን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ይስጥዎት ፡ ኢትዮጵያ ፡ በነጻነት ፡ ትኑር„ ፡ ብለው ፡ ካሳረጉ ፡ በኋላ ፤ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በታላቁ ፡ ቤተ መንግሥታቸው ፡ ላይ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ አቆሙ ።

በዚህ ፡ ዕለት ፡ በዚህ ፡ ሰዓት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ሽማግሌዎችና ፡ ሕፃናት ፡ የዘንባባ ፡ ቅጠል ፡ ይዘው ፡ ስለ ነጻነታቸው ፣ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አደራረግ ፡ የገለጡትን፡ ደስታ፡ በረጅሙ፡ ለመጻፍ ፡ ከተነሡ ፡ ጸሐፍት ፡ ታሪክ፡ በቀር ፤ በዚህ ፡ በአጭሩ ፡ አገላለጥ ፡ ልንወስነው ፡ አልቻልንም ።

---

## የብፁዕ ፡ አባታችን ፡ መንፈሳዊ ፡ መሪነት ።

ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ም ፡ ሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ እንደቀድሞው ፡ በዕጨጌነታቸው፡ የመሪነታቸውንና ፡ የኃላፊነታቸውን ፡ ሥራ ፡ ማከናወን ፡ ጀምረዋል ። በተለመደው ፡ ትሩፋታቸውም ፡ የግል ፡ ገንዘባቸውን ፡ ሳይቈጥቡ ፤ በመከራው ፡ ለተጐዱ፡ ለብዙ፡ ካህናትና ፡ ምእመናን ፡ በየጊዜው ፡ እርዳታ፡ አድርገዋል ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ አድርገን ፡ በዚሁ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደገለጥነው ፡ በትዕግሥታቸውና ፡ በርኅራኄያቸው፤ በልግሥናቸውና ፡ በደግነታቸው ፡ «የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅን ፡ መሪ» ፡ ተብለው ፡ እጅግ ፡ ተመስግነዋል ።



ይኸውም ፡ ቅን ፡ መሪነታቸውና ፡ መንፈሳዊ ፡ ገድላቸው ፡ ወደ ፡ አላሰቡትና ፡ ወደ ፡ አልተመኙት ፡ ታላቅ ፡ ሀብት ፡ እየሳቧቸው ፤ በብዙ ፡ ካህናትና ፡ በብዙ ፡ ምእመናን ፡ ድምፅ ፡ ተመርጠው ፡ ፲፱፻፵ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሐምሌ ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ (እሑድ) ፡ ሢመተ ፡ ጵጵስናን ፤ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ም ፤ ጥር ፡ ፮ ፡ ቀን ፡ (እሑድ) ፡ ሢመተ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስናን ፡ ተቀብለዋል ።

እስከዚህ ፡ የዘረዘርነውን ፡ የብፁዕነታቸውን ፡ ታሪክ ፡ ለዝክረ ፡ ዜና ፡ ያህል ፡ በጥቂቱ ፡ ገለጥነው ፡ እንጂ ፤ መንፈሳዊ ፡ ሥራቸውን ፡ በሙሉ ፡ ጽፈነዋል ፡ ለማለት ፡ አንደፍርም ።

የዚህን፡ የታሪካቸውን ፡ እውነተኛነትና ፡ የመንፈሳዊነታቸውን፡ ሙሉነት ፡ ለመረዳት ፡ የሚፈልጉ ፡ አንባቢዎችና ፡ ተመልካቾች ፣ ግን ፤ ቅዱስ ፡ ብፁዕነታቸውን ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ መላልሰው ፡ ቢመለከቱት ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ሊያገኙበት ፡ ይችላሉ ።

ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ፡ በየጊዜው፡ የተቀበሏቸው፡ ሽልማቶች ።

፩ኛ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላሉ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ገዳማት ፡ ራይስ ፤ ሲባሉ ፡ የአንገት ፡ ሥላሴ ፡ ኒሻን ፡ ከነፕላኩ ።
፪ኛ ፡ ዕጨጌ ፡ ሲባሉ ፡ ባለ ፡ ኮርዶን ፡ ሥላሴ ፡ ኒሻን ፡ ከነፕላኩ ።
፫ኛ ፡ ከጠላት ፡ ወረራ ፡ ወዲህ ፡ የአንገት ፡ ሥላሴ ፡ ኒሻን ፡ ከነፕላኩ ።
፬ኛ ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የጦር ፡ ሜዳይ ፡ ባለ ፡ አንድ ፡ ዘንባባ ።
፭ኛ ፡ የስደት ፡ ባለ ፡ አምስት ፡ ዘንባባ፡ ሜዳይ ።
፮ኛ ፡ ዕጨጌ ፤ ወጳጳስ ፡ በተባሉ፡ ጊዜ ፡ ባለ ፡ ኮርዶን፡ ሥላሴ ፡ ኒሻን ፡ ከነፕላኩ ።
፯ኛ ፡ በ፳፭ተኛው ፡ የብር ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በዓል ፡ ባለኮርዶን ፡ የንግሥተ ፡ ሳባ ፡ ኒሻን ፡ ከነፕላኩ ።
፰ኛ ፡ ገነተ ፡ ልዑል ፡ የሚል ፡ ፕላቲን ፡ ወርቅ ፡ ሜዳይ ።

---

ሊቃውንትና ፡ መምህራን ፡ በየጊዜው ፡ ፍቅራቸውን ፡ በመግለጥ ፡ ለብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ያበረከቷቸው ፡ ቅኔዎች ።

፲፱፻፳፬ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ የካቲት ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ መምህር ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ተብለው ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ መንበረ ፡ መንግሥት ፡ የቅዱስ ፡ ገብርኤልን ፡ ደብር ፡ መምህርነት ፡ በተሾሙ ፡ ጊዜ ፡ አለቃ ፡ አምኃ ፡ ወልደ ፡ አረጋዊ ፡ ያበረከቷቸው ፤ መወድስ ፡ ቅኔ ።

ተፈሥሐ ፡ ጽዮን ፡ መንበረ ፡ መንግሥት ፤
አምጣነ ፡ ሠረቀ ፡ ለኪ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ብርሃን ።
ሕፀተ ፡ ሃይማኖት ፡ ፍቅር ፡ ከመ ፡ ኢይኩን ።
ወልብከ ፡ ኄር ፡ መምህረ ፡ ጽድቅ ፡ ባርክ ፡ እግዚአ ፡ ለዛቲ ፡ መክን ።

www.ethiopianorthodox.org

ውስቴታ ፡ እስመ ፡ ተተክለ ፡ ስብከተ ፡ አብርሃም ፡ አብ ፡ ጕንደ ፡ ሃይማ
ኖት ፡ ሐረገ ፡ ወይን ።

ናሰምክዪ ፡ ውስተ ፡ ዐረፍቱ ፡ ለኒሩትከ ፡ ፀወን ።
ከመ ፡ ንድኅን ፤ እም ፡ ተገፍዖ ፡ ደቂቅከ ፡ ብዙኃን ፡
ወይትፌሣሕ ፡ ካዕበ ፡ ልቡና ፡ ብእሲ ፡ ኅዙን ።
እስመ ፡ ዕለተ ፡ በርህ ፡ ሢመትከ ፡ ሠረቀ ፡ ለጻድቃን ።

፲፱፻፴፰ ፡ ዓ፡ ም፡ ኢትዮጵያ ፡ ከተወላጆቿ ፡ ጳጳስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ መሾም ፡ ይገባታል? ፡ ወይስ ፡ አይገባትም? ፡ በመባባል ፡ የተነሣውን ፡ ክርክር ፡ ለመወሰን ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ታላቅ ፡ የሊቃውንት ፡ ጉባኤ ፡ ተደርጎ ፡ ነበረ ። በዚያ ፡ ዘመን ፡ የጉባኤው ፡ ሰብሳቢ ፡ ብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ጥር ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ የእ መቤታችንን ፡ በዓል ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ፰ ፡ ቀን ፡ ሳይቋረጥ ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ መጠን ፡ የሌለው ፡ ግብር ፡ አበሉ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የብፁዕ መልአከ ፡ ብርሃን ፡ አድማሱ ፤ ዠምበሬ ፡ የሚከተሉትን ፡ ቅኔዎች ፡ አበረከቱ ።

፭ኛ እስራኤል ፡ እምግብጽ ፡ አመ ፡ ይወፅኡ ፤

ምስለ ፡ መና ፡ ሰማይ ፡ ሥጋ ፡ ለእመ ፡ ይዘንም ፡ ሎሙ ።
እንዘ ፡ ዓዲሁ ፡ መብልዕ ፡ ውስተ ፡ አፉሆሙ ።
ተመይጦተ ፡ ግብጽ ፡ ኀበ ፡ ሐለዩ ፡ ዘበልዕዎ ፡ ሥጋ ፡ ሕማመ ፡ ከኖሙ ።
አመሰ ፡ አውጻእከነ ፤ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ አቡነ ፡ እምቅንየተ ፡ ግብጽ ፡ ከማሆሙ ።
ሥጋ ፡ ዘታዘንም ፡ ለለጌሠሙ ፡ ወአሙ ።
ጽንዕ ፡ ለድኩማን ፤ ወሕይወት ፡ ለእለ ፡ ሐሙ ።
ኀበ ፡ አእመሩ ፡ ሕዝብ ፡ አበሳ ፡ እስራኤል ፡ ኵሎሙ ።
ሐልዮ ፡ ሚጠት ፡ መንገለ ፡ ግብጽ ፡ አምጣነ ፡ አልቦ ፡ በኅቤሆሙ ።

፮ኛ ፡ ስለ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ሹመት ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ በግብጽ ፡ ቤተ ፡ ክር ስቲያንና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መካከል ፡ ብዙ ፡ ክርክር ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ግብጻውያን ፡ ይህን ፡ መብት ፡ አንፈቅድም ፡ ስላሉ ፤ በኢትዮጵያ ፡ ሊቃው ንት ፡ ጉባኤ ፡ ከግብጽ ፡ አንድነት ፡ ለመለየት ፡ ቊርጥ ፡ አሳብ ፡ ተደርጎ ፡ ነበረ ።

ነገር ፡ ግን ፡ በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ብርታትና ፡ አስተዋይ ነት ፡ የእስክንድርያው ፡ ፓትረያርክ ፡ አቡነ ፡ ዮሳብ ፡ ፈቅደው ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አድርገው ፡ ስለሾሙ ፤ መልአከ ፡ ብርሃን ፡ አድማሱ ፡ የሚከተለውን ፡ መወድስ ፡ ቅኔ ፡ አበረከቱ ።

ለእመ ፡ ከመዝ ፡ ኢኮነ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ምንት ፡ እንከ ፡ ረባሑ ፡ ለተይህዶ ።
ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ባስልዮስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘንእዶ ።
እንዘ ፡ ኢይትዔገሥ ፡ ለፍጻሚ ፤ እስከነ ፡ አክበሮ ፡ ወሢሞ ፡ ፈቂዶ ።
ዮሳብ ፡ ዘወለዶ ፡ አምጣነ ፡ አኮ ፡ ዘኮነ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ሐይዶ ።



ፍና ፡ ክብርሂ ፡ አመ ፡ ሐለፍነ ፡ በዘከመዝ ፡ ተዘምዶ ።
መንገለ ፡ ፀጋም ፡ ኅደግናሃ ፡ ለቆጵሮስ ፡ ተዋርዶ ።
ባሕቱ ፡ ጸላዒ ፡ ኢያንሥእ ፡ ሐሜተ ፡ ልሳን ፡ ማዕፀዶ ።
በብሂለ ፡ ምንት ፡ ሥላጤሃ ፡ ለግዝረት ፡ ተዋሕዶ ።
እምክርዳደ ፡ ልማድ ፡ ናንጽሕ ፡ ለሲኖዶስነ ፡ ዐውዶ ።
በብሂለ ፡ ምንት ፤ ሥላጤሃ ፡ ለግዝረት ፡ ተዋሕዶ ።

፯ተኛ ፡ በ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ፡ ም፡ ጥር ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ ላይ ፡ ብፁዓን ፡ ጳጳሳት ፡ ባሉበት ፡ የአቡነ ፡ እንጦንዮስ ፡ በዓል ፡ በተከበረበት ፡ ቀን ፡ ከመልአከ ፡ ብርሃን ፡ አድማሱ ፡ ዠምበሬ ፡ የተሰጠ ፡ ቅኔ ።

አአበው ፡ ንቡራነ ፡ እድ ፡ (አአበው ፡ እለ ፡ ባስልዮስ ፤)
ዘእምእጦንዮስ ፡ ሴሬቀ ፡ ዐጸደ ፡ ወይንክሙ ፡ ብሕትውና ።
ዘአዕጹቂሃ ፡ ትሕርምት ፡ ወዘአንበለ ፡ ዓቅም ፡ ቀኖና ።
ወዘሥረዊሃ ፡ ውሣጣይ ፡ ጽሙና ። ተረክበ ፡ ምንኵስና ፤
ወይነ ፡ እንጦኒ ፡ ወለጠ ፡ ምረረ ፡ ዕጕስታር ፡ ሰብእና ።
አኮኑ ፡ ታስተጥዕም ፡ ምረረ ፡ መርገም ፡ መና ።
ኅምዘ ፡ ሞት ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ልህኵተ ፡ ነቢይ ፡ ድንግልና ።
ዘሐጸበታ ፡ ድንግል ፡ በማየ ፡ ባሕርያ ፡ ንጽሕና ።
ውስቴታ ፡ ከመ ፡ ትምልዑ ፡ ጵጵስናክሙ ፡ ማየ ፡ ቃና ።

፰ተኛ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ በበዓለ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ደብረ ፡ ሊባ ኖስ ፡ ወርደው ፡ ግብር ፡ ሲያበሉ ፤ ከመልአከ ፡ ብርሃን ፡ አድማሱ ፡ ዠምበሬ ፡ የተሰጠ ፡ መወድስ ፡ ቅኔ ። ይኸውም ፡ ቅኔ ፡ በጠላት ፡ ወረራ ፡ ጊዜ ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ቢታጡ ፤ እንዲሁም ፡ መንፈሳዊ ፡ አባት ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስ ልዮስ ፡ ቢታጡ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይልቁንም ፡ ቅድስት ፡ ሀገር ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መጥፋቷን ፡ የሚያስታውስ ፡ ነው ።

ቀዳሚ ፡ ሕይወቱ ፡ ለሰብእ ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ባስልዮስ ፡ እክል ፤
ወማየ ፡ ሕይወት ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ።
ኢይጥፍዑ ፡ ብነ ፡ እምቅድመ ፡ ትጥፋዕ ፡ ብናሴ ።
እሉ ፡ እመ ፡ ተኀጥኡ ፤ እስመ ፡ ኮነ ፡ ጥንተ ፡ ጸላዒነ ፡ ለኵሉ ፡ ወራሴ ።
እምኵሉሰ ፡ ዘየዐቢ ፡ ተኀትመት ፡ ጽዮን ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ጽላተ ፡ ሙሴ ።
ርኢነሂ ፡ ከመ ፡ በልያ ፡ ከመ ፡ አርዌ ፡ ምድር ፡ ብእሲ ።
ምናሴ ፡ ለዘኤፍሬም ፡ ወኤፍሬም ፡ ለምናሴ ።
ወንሕነ ፡ ኮነ ፡ በዘአሚሃ ፡ ድምሳሴ ።
በኢትዮጵያ ፡ ሀገሪትነ ፡ ነግደ ፡ ወፈላሴ ።

ብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ እየተባሉ ፡ በዕጨጌነ ታቸው ፡ ሳሉ ፤ ቀጥራቸው ፡ ካንድ ፡ ሺህ ፡ በላይ ፡ ስሆነ ፡ ሊቃውንትና ፡ መኳን

www.ethiopianorthodox.org

ንት ፡ ለካህናትና ፡ ለምእመናን ፡ ግብዣ ፡ ባደረጉ ፡ ጊዜ ፤ አለቃ ፡ መርዓዊ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ በፊት ፡ የተንታ ፡ ሚካኤል ፡ ደብር ፡ ቀኝ ፡ ጌታ ፡ የነበሩ ፡ ሊቀ ፡ ለብፁዕነታቸው ፡ ያበረከቱት ፡

መወድስ ፡ ቅኔ ።

አኒሩት፡ ዘእንበለ ፡ አቅም፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ፡ ሥጋከ፡ ለነፍስ፡ ኵልነ፡ ዘትሴሲ።
ሰብዐተ ፡ ሀብታተ ፡ እንዘ ፡ አሐደ ፡ ትሬሲ ።
በጸጋ ፡ ፍጹም ፡ እስመ ፡ ነሣእከ ።
ወእንበለ ፡ ጸጋ ፡ ጸጋከ ፡ ተዐሲ። ለነግድ ፡ ወለፈላሲ ።
እስመ ፡ ኢትዘግብ ፡ ወርቀ ፡ ወኢታስተጋብእ ፡ ለወራሲ ።
አንተሰ ፡ ትልወኒ ፡ እመ ፡ ይብለከ ፡ ነጋሢ ።
አፍራሰ ፡ እሳት ፡ ዘጳውሎስ ፡ ወዘጴጥሮስ ፡ ታስተሬሲ ።
ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ መልአክ ፡ ወመሬታዊ ፡ ብእሲ ።
አምጣነ ፡ ትዔዐን ፡ ላዕለ ፡ ተኵላ ፡ ወትከይድ ፡ ላዕለ ፡ ከይሲ ።

የእንጦጦ ፡ ኪዳነ ፡ ምሕረት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አለቃ ፡ የነበሩ ፡ አለቃ ፡ ባሻህ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡ የሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ሹመት ፡ በብፁዕነታቸው ፡ ላይ ፡ በረፈ ፡ ጊዜ ፤ ለብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፤ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ያበረከቷቸው ፡ ቅኔዎች ።

፩ኛ ፡ ሥላሴ ፡ ቅኔ ።

አስተጋብእ ፡ ጽጌ ፡ ረዳ ፡ ሕይወተ ፡ ዕዝራ ፡ ወኤልያስ ፡ ዐርከ ፡ መርዓዊ ፡ባስልዮስ ፡ መልአከ ፡ ጽባሕ ፡ ወሠርክ ።
እስመ ፡ ተርፈ ፡ በኀበ ፡ ይሁዳ ፡ ደዌ ፡ ሔዋን ፡ ሦክ ።
ወእመ ፡ ተሰመይከ ፡ አንተ ፡ ዐርከ ፡ መርዓዊ ፡ ቡሩክ ።
እንዘ ፡ ንብል ፡ ንስአል ፡ ኀበ ፡ አምላክ ።
ጊዜ ፡ ፍና ፡ አቤል ፡ ሞት ፡ ዘምስለ ፡ ኄኖክ ።
ለይቅድምከ ፡ ሚካኤል ፡ መልአክ ።

፪ኛ ፡ መወድስ ፡ ቅኔ ።

አሣዕነ ፡ ፍርሃት ፡ ፈትሐ ፡ እምእግረ ፡ ልቡና ፡ ሙሴ ፡ ባስልዮስ ፡ መምሀራነ ፡ ሮሜ ፡ ዘይትቃወም ።
ምስለ ፡ አንበሳ ፡ ግብጽ ፡ ማርቆስ ፡ ከባቴ ፡ አበሳ ፡ ግሩም ።
ወአንበረ ፡ በላዕለ ፡ አሐዱ ፡ መንበሩ ፡ ተቀዋም ።
አዕጹቀ ፡ ብርሃን ፡ ጳጳሳተ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ተሀሉ ፡ ዘእንበለ ፡ ኀዘን ፡ ወሕማም ፡
እሳትሂ ፡ ጣዕመ ፡ ነገሩ ፡ ዘኢያገምሮ ፡ ዓለም ።
ለሐድሶተ ፡ ንስር ፡ ተፋቅሮ ፡ ውስተ ፡ ብሔረ ፡ ግብጽ ፡ ይዘንም ።
አኮኑ ፡ ባስልዮስ ፡ በነሢአ ፡ አክሊል ፡ ወስም ።
እምነ ፡ ባሕረ ፡ ግብጽ ፡ ተቃውሞ ፡ ወጽአ ፡ በሰላም ።

---

በፊት ፡ የሐረርጌ ፡ ከምቦልሻ ፡ ማርያም ፡ ደብር ፡ አለቃ ፡ የነበሩ ፡ አሁን ፡ በደጅ ፡ ጥናት የሚገኙ ፡ አለቃ ፡ አርአያ፡ ተክለ፡ ሥላሴ ፡ ለብፁዕነታቸው ፡ ያበረከቷቸው ፡ ቅኔዎች ።



፩ኛ ፡ ጉባኤ ፡ ቃና ።

ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ባስልዮስ ፡ ምንዳቤ ፡ ሕዝቡ ፡ መቅለሊ ።
እስመ ፡ ለግፉዓን ፡ ይትቤቀል ፡ ወለርኁባን ፡ ይሔሊ ።

፪ኛ ፡ ዘአምላኪየ ።

ባስልዮስ ፡ ገብረ ፡ ሥርዓተ ፡ እግዚኡ ፡ ጥዩቀ ። ለዓለም ፡ እስመ ፡ አስተርአየ ፡ ምሥጢረ ፡ ረቂቀ። ወመርሐ ፡ ፍኖቱ ፡ ረሰየ ፡ አብርሃምሃ ፡ ጻድቀ ።

፫ኛ ፡ ዋዜማ ።

ማዕደ ፡ ሥልጣንከ ፡ ዘተሠርዐ ፡ አሚነነ ፡ ንብላዕ ፡ እንበለ ፡ ኅዳጥ ፡ ኃሠሣ ።
በንጽሕ ፡ አምጣነ ፡ ተሠርዐ ፡ ሥልጣንከ ፡ ዓሣ ።
ወአኮ ፡ ሕኑቀ ፡ በደመ ፡ ልዮን ፡ እንስሳ ።
ሶበ ፡ ለሀገርነ ፡ ጽዮን ፡ ትቄድሳ ፡
እስመ ፡ አንተ ፡ ለጥበብ ፡ ርእሳ ።

፬ኛ ፡ ሥላሴ ።

ሣኔር ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ ቅርብተ ፡ ኤርሞን ፡ ተሐድሶ ፡ እምነ ፡ መካሕ ፡ ዮሴፍ ፡ ጸራቢ ፡ እንዘ ፡ ትትሐመይ ፡ ገሀደ ፡ አዕደለ ፡ ገጻ ፡ ምስብዒተ ፡ እደ ፡ ባስልዮስ ፡ ወልድ ፡ ዘበኵራ ፡ እስመ ፡ እምኒሃ ፡ ተወልደ ።
ወእምነ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘተግህደ ።
ኅዲጎ ተስዓ ፡ ወተሰዓተ ፡ ነገደ ፡
ካህናተ ፡ ረሰየ ፡ አዝማደ ።

፭ኛ ፡ ዘይእዜ ።

ማኅበረነ ፡ ባርክ ፡ ወተዘከር ፡ ከመ ፡ እምላዕሌነ ፡ ይኅልፍ ፡ ኃላፌ ፡ ፍኖት ፡ ዐፀባ ።
ወልታ ፡ ጽድቅ ፡ ባስልዮስ ፡ ዘላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ለገነት ፡ ሀገረ ፡ ዚአነ ፡
እምኵሉ ፡ ትዕቀባ ፡
እምዝኒ ፡ ዳግመ ፡ ሞት ፡ ኢይረክባ ፡
ወዘቀዳሚ ፡ ጽልመት ፡ ኢይቀርባ ፡
አምጣነ ፡ ብዙኃት ፡ አህጉር ፡ ለስብሓቲከ ፡ ነበባ ፡
ወዘቀዳሚ ፡ ጽልመት ፡ ኢይቀርባ ።

---

ስለ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ትሩፋት ፡ ከአቶ ፡ ሣህለ ፡ ሚካኤል ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ የተደረሰ ።

መወድስ ፡ ቅኔ ።

በነዊኅ ፡ ጸሎት ፡ ሐፀ ፡ ልሳንከ ፤ ወበልቡጠ ፡ ወርቅ ፡ ምጽዋት ፤ ወልታ ፡ እደዊከ ፡ ይትዐቀባ
ሃይማኖት ፡ ወፍቅር ፡ አባግዐ ፡ ቤቱ ፡ ለላባ ፡
ለያዕቆብ ፡ ሕሊና ፡ ልብከ ፡ አኮኑ ፡ ተውህበ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወበትረ ፡ ሀብትከ ፡ ሐመልሚል ፡ ያስተባዝኖን ፡ ዘልፈ ፡ ለአባግዒከ ፡ ከመ ፡ ዘግባ ።

ተዐቍረኒ ፡ ጠለ ፡ ክብርከ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኀንባባ ፡
እስመ ፡ ገድላቲከ ፡ ደመናት ፡ መልዕልተ ፡ ገዳማት ፡ (አድባራት ፡) ይረብባ ፡
ዘበኀበ ፡ ነሀብት ፡ ኮንከ ፡ ፍቱነ ፡ እሳት ፡ አባ ፡
ጽሩየ ፡ ባሕርይ ፡ ወመልክዐ ፡ ባስልዮስ ፡ ወርቀ ፡ ሳባ።

---

የደብረ ፡ አሚን ፡ ሊቀ ፡ ጠበብት ፡ አያሌው ፡ እምሩ ፡ ለብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ያበረከቱት ።

## መ ወ ድ ስ ፡ ቅ ኔ ።

ገፋዔ ፡ ከንቱ ፡ መንፈስ ፡ በጽድቀ ፡ አሚን ።
ወሰዳዲሁ ፡ ለፀር ፡ በኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ኬንያ ፡
ሐዋርያ ፡ ስብሓት ፡ ባስልዮስ ፡ ተሰዶተከ ፡ እስያ ፡
አንከረት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ማእምንት ፡ ርእያ ።
እንዘ ፡ ይተልዋ ፡ እገሪከ ፡
ውስተ ፡ ኑኀ ፡ ገጻ ፡ ለሳሌም ፡ ኃያላት ፡ እስመ ፡ ተርዕያ ፡
ዝኒ ፡ ሥነ ፡ ገድልከ ፡ ምሀርከ ፡ ሰርያ ፡
ሕፄሃ ፡ ለመርዓትከ ፡ ሐዳስ ፡ ኢትዮጵያ ።
ወበእንተዝ ፡ ይብላከ ፡ አዋልደ ፡ ጽዮን ፡ ልያ ፡
ባስልዮስ ፡ ባስልዮስ ፤ ባስልዮስ ፡ ሐዋርያ ።

---

በደብረ ፡ ብርሃን ፡ (ዘሸዋ) ፡ የብሉያትን ፡ ትርጓሜና ፡ ቅኔ ፡ ያስተምሩ ፡ የነበሩ ፡ አለቃ ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስ ፡ ወልደ ፡ አማኑኤል ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ፲፱፻፴፯ ፡ ዓመተ ፡ ም ፡ በየካቲት ፡ ወር ፡ (በዕጨጌነት ፡ ሳሉ ፡) ደብረ ፡ ብርሃንና ፡ የአንኮበርን ፡ አድባራት ፡ በሰፈ ፡ ችሮታ ፡ በጐበኙ ፡ ጊዜ ፡ ለብፁዕነታቸው ፡ ያበረከቷቸው ።

## ቅኔ ።

አፍላጋተ ፡ ወንጌል ፡ ኤፌሶን ፡ አመ ፡ ሰቀይዋ ፤ ለደብረ ፡ ብርሃን ፡ ገነት ፡ እንተ ፡ ትፈሪ ፡ አዕላፈ ።
ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ አዳም ፡ ታሕተ ፡ ጽላሎታ ፡ አዕረፈ ።

ለሙሴ ፡ ርቱዕ ፡ ሃይማኖትነ ፤ አሮን ፡ መንፈስ ፡ ዚአሁ ፡ ይኩነነ ፡ አፈ ።
ወአመ ፡ መላእክተ ፡ ተሳተፈ ። በርቀተ ፡ ምክሩ ፡ አጥፍአ ፡ ኢያእምሮ ፡ ግዘፈ ።

በጸሎትሂ ፡ ሠረገላሁ ፡ ውስተ ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ኀለፈ ። ልበ ፡ መዘምራን ፡ ኢዮስያስ ፡ በሐፀ ፡ ፍቅሩ ፡ እስመ ፡ ተነድፈ ። ገብረ ፡ አጋእዝት ፡ ይኩነነ ፡ እንተ ፡ ክራድዮን ፡ ዖፈ ። ለዘሐመ ፡ ንብረትነ ፡ ሕማሞ ፡ እስመ ፡ ተወክፈ ።

---

ሊቁ ፡ አለቃ ፡ አበበ ፡ ኀይሉ ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ባንድ ፡ ሳምንት ፡ መላል ሰው ፡ ሰፈ ፡ ግብር ፡ (ግብዣ) ፡ በማድረጋቸው ፡ የሰጡት ፡ ፩ኛ ፡ ቅኔ ፡



ዳግመ ፡ አስተዳሉ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ማዕዳቲከ ። እስመ ፡ ለማዕድ ፡ ሕፃን ፡ ብሑተ ፡ ሥጋ ፡ ልደት ።

ወሰድዎ ፡ ከመ ፡ ይግዝርዎ ፡ በሰሙን ፡ ዕለት ። አሰሰለሂ ፡ ዳግመ ፡ ሀብተ ፡ ዚአከ ፡ ዳዊት ፡ ጽዕለተ ፡ እስራኤል ፡ ካህናት ። አኮኑ ፡ ማዕደ ፡ ዘመነከሰት ፡ ይጸንሐ ፡ መኳንንት ፡ ዐበይት ።

## ፪ኛመወድስ ።

ዳዊት ፡ ኢኮነ ፡ አክሊል ፡ ምክሕነ ፤ ወኢኮነነ ፡ ኢያሱ ፡ መድኀኒተ ፡ ሥጋነ ፡ ቀዳማይ ፡ ዘያነሥአ ፡ እምድር ፡ ለአክሊልነ ፡ ነዳይ ። አኮኑ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ።
ወኢኮነ ፡ ትምክሕተ ፡ ንጽሕና ፡ ኤልያስ ፡ ነቢይ ። ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ምክሐ ፡ ንጽሕነ ፡ እስመ ፡ በጸሎቱ ፡ ለጐመ ፡ አፈ ፡ ኆኅተ ፡ ሮም ፡ ሰማይ ።

ኢትበልሂ ፡ እም ፡ ሕዝብከ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ኀሩይ ። አንተ ፡ ቀዳማይ ፡ ወአንተ ፡ ደኃራይ ። ባሕቱ ፡ ተዘከር ፡ ቃለ ፡ አዶናይ ። በቅጽበት ፡ እስመ ፡ ኀረዮ ፡ ለዘአምነ ፡ ፈያታይ ። እስከነ ፡ ለአዳም ፡ ቀደሞ ፡ በዊአ ፡ ገነት ፡ ዐባይ ። በቅጽበት ፡ እስመ ፡ ኀረዮ ፡ ለዘአምነ ፡ ፈያታይ ።

---

የወሎ ፤ ተንታ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ደብር ፡ ቀኛ ፡ ጌታ ፡ (ኋላ ፡ አለቃ) ፡ መርዓዊ፤ ለብፁዕነታቸው ፡ ያበረከቷቸው ።

## መ ወ ድ ስ ።

እሮ ፡ ታነክር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ርእያ ፡ መንክረ ፡ ንጽሐ ፡ ልብከ ፡ ቢረሌ ፡ እንተ ፡ በውስቴታ ፡ ተቀድሐ ፡ ወይነ ፡ ኤልያስ ፡ ክላሌ ። እስመ ፡ ለስምከ ፡ መላእክት ፡ ያብእዎ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ሃሌ ። ወረዱ ፡ እም ፡ ሉዓሌ ፡ ገብረ ጊዮርጊስ ፡ ዘኮንከ ፡ ምዕራገ ፡ ጸሎት ፡ ወትንባሌ ። ተፈነዉሂ ፡ መንገሌከ ፡ ከመ ፡ ይስምኡ ፡ ምሳሌ ። ለዮሐንስ ፡ አርዳኢሁ ፤ ንጽሕ ፡ ወድንጋሌ ።
አኮኑ ፡ ተጽሕፈ ፡ በሠሌዳ ፡ ልብከ ፡ ጽሌ ፡ ምሳሌ ። መኃልይ ፡ ዘሎሰምን ፤ ወጥበበ ፡ ሲራክ ፡ ዘኩፋሌ ።

---

## የዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ መታሰቢያ ፡ ቤት ።

አፈ ፡ ሊቀ ፡ ሊቃውንት ፡ አክሊሉ ፡ ገብረ ፡ ኪሮስ ፡ ስለ ፡ ደብር ፡ ቅዱስ ፡ ሕንጻ ፡ መፈጸም ፡ ያበረከቱት ።

## መወድስ ።

ደብር ፤ ቅዱስ ፡ ሰማዕተ ፡ ወንጌል ። መንገለ ፡ ምሥራቅ ፡ ሜጠ ፡ ገጸ ፡ ለለዕለቱ ።

በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ (በስመ ፡ ወላዲ ፡ ወወልድ) ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሠለስቱ ። እንዘ ፡ ያመዐትብ ፡ ኵለንታሁ ።

ወሰበከ ፡ ለሕዝበ ፡ ወንጌል ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ በዝንቱ ። ነስሑ ፡ እስመ ፡ ቀርበት ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ዐባይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መንግሥቱ ።

www.ethiopianorthodox.org

አልበስዎሂ ፡ ልብሰ ፡ ብርሃን ፡ እስከነ ፡ ሳዕሉ ፡ እም ፡ ታሕቱ ። ለአበ ፡ ኵልነ ፡ ባስልዮስ ፡ ጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ። እንዘ ፡ በትዕግሥት ፡ የኀልፍ ፡ እመዐርጋት ፡ ሰመንቱ ፡ ለከዊነ ፡ ብርሃን ፡ አምጣነ በጽሐ ፡ በጽንዐ ፡ ገድሉ ፡ ወሃይማኖቱ ።

---

የዲማ ፡ ቂሰ ፡ ገበዝ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ሣህሉ ፡ ኢርትራ ፡ ነጻነቷን ፡ ባገኘች ፡ ጊዜ ፡ የሰጡት ።

ቅ ኔ ፡ (መ ወ ድ ስ) ።

ሐፀ ማይ ፡ መንግሥተ ፤ ሳኦል ፡ መርገመ ፡ ሳሙኤል ፡ ርግብ ፡ አመ ፡
ኀቢሁ ፡ ተፈነወት ።
እስመ ፡ ሳኦል ፡ ወፅአ ፡ እምክረ ፡ ሳሙኤል ፡ ቤተ ፡
ወዖዝያን ፡ ተመሰሎ ፡ አምጣነ ፡ ፍኖቱ ፡ ዘሳኦል ፡ ፍኖት ።
ባሕቱ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ።
ለእመ ፡ የኀብር ፡ ምክረ ፡ ምስለ ፡ ብፁዓን ፡ ጳጳሳት ፤
ቀጥቀጠ ፡ ወሰበረ ፡ ኆኅተ ፡ ብርት ፡
ወበኃይለ ፡ ኤልያስ ፡ መዊዖቱ ፡ ሞዐ ፡ ኃይለ ፡ ሞት ።
ወተርኅወት ፡ ለነ ፡ በዘባስልዮስ ፡ ጸሎት ፡
ኆኅተ ፡ ገነት ፡ ምድረ ፡ ኤርትራ ፡ ቀዳሚ ፡ ዘተዐፅወት ።

---

የመካነ ፡ ኢየሱስ ፡ አለቃ ፡ ደስታ ፡ ወልዱ ፡ ለብፁዕነታቸው ፡ ያበረከቱት

መ ወ ድ ስ ።

ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ዮሴፍ ፡ ኀዳጌ ፡ በቀል ።
እሮፍ ፡ አልዓልከ ፡ ክፍለ ፡ ብንያም ፡ አሐዱ
እምነ ፡ አኃው ፡ ጠበብት ፡ እለ ፡ ኀቤከ ፡ ነገዱ ።
እንዘ ፡ በአእምሮ ፡ ወበለብዎ ፡
ዮሐንስ ፡ ልቡና ፡ ዚአከ ፡ ለአምላክ ፡ ዘመዱ ።
አእጋረ ፡ መድሎት ፡ መዓርግየ ፡ እስመ ፡ የዐርጉ ፡ ላዕለ ፡ ወታሕተ ፡ ይወርዱ ።

ለ ዓ ለ ም ።

አመ ፡ ቀርበሂ ፡ ፍትሐ ፡ ቃልከ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ማዕዱ ።
ተጸውዑ ፡ ሊቃውንት ።
ወኢያኀጥዖሙ ፡ ዘፈቀዱ ።
ወአመ ፡ ተረሣዕኩ ፡ አነ ፡ እንዘ ፡ ኣንቀዐዱ ።
ኅሥሦ ፡ ለገብርከ ፡ አለቃ ፡ ደስታ ፡ ወልዱ ፡
ለየዋህ ፡ ልብከ ፡ አምጣነ ፡ ኒሩት ፡ ልማዱ ።

---

ደራሲው ፡ ያልታወቀ ፡

መወድስ ፡ ቅኔ ።

እሡራተ ፡ ከና ፡ በሐብለ ፡ ፍቅርከ ።
እስክንድርያ ፡ ክብርት ፡ ወኢትዮጵያ ፡ እምነ ፡
አባስልዮስ ፡ እንተ ፡ ከሠትከ ፡ ብርሃነ ፡



ታሰስል ፡ ጽልመተ ፡ ኑፋቄ ፡ እምወሰን ፡ ወሰነ ።
ወመጻእኩ ፡ ለክብርከ ።
አምጣነ ፡ ባስልዮስ ፡ አንተ ፡ እንዘ ፡ ከመ ፡ ኤፍሬም ፡ አነ ።
ንሕነሂ ፡ ከመ ፡ ንሑር ፡ ፍኖተ ፡ ቅዱሳን ፡ የማነ ፡
ውስተ ፡ አሐቲ ፡ በረከትከ ምግባረ ፡ ሠናይ ፡ ደምረነ ።
በረከተ ፡ ቅድስት ፡ እዴከ ፡ እንዘ ፡ ንሴፎ ፡ ኵልነ ፡
አምጣነ ፡ ቡሩክ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ኪያሃ ፡ ዘወሀበነ ።

---

አለቃ ፡ ወልደ ፡ ማርቆስ ፡ ብርሃኑ ፡ ዘዲማ ፡ የተቀኙት ፡ መወድስ ፡ ቅኔ ።

በክብረ ፡ ትንሣኤ ፡ ዐረዩ ፡ ለእመ ፡ ዐረዩ ፤ በሕማም ፡ ወሞት ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ወባስልዮስ ።

ወእምዝ ፡ ዳግመ ፡ ኢይመውቱ ፡ በነፍስ ።
እንዘ ፡ ሥርግዋን ፡ በቀጠንት ፡ አልባስ ።
እስከ ፡ እግር ፡ እምነ ፡ ርእስ ፤ ሰሎሞን ፡ ጥቀ ፡ ወጥቀ ፡ ሕዝቅያስ ።

ለ ዓ ለ ም

ከመ ፡ አሐዱ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ወከመ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ንጉሥ ።
ኢለብሱ ፡ ልብሰ ፡ ጽጌ ፡ ዘአናሚሁ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ።
ወአልቦ ፡ ዘገብረ ፡ በዓለ ፡ ፋሲካ ፡ ሐዲስ ።
ከማሁ ፡ ለንጉሥነ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ኢዮስያስ ።
ወከመ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ዘገብረ ፡ በዓለ ፡ መርዓዊ ፡ ክርስቶስ ።
ከማሁ ፡ ለንጉሥነ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ኢዮስያስ ።

---

የአዲስ ፡ አበባ ፡ ገነተ ፡ ጽጌ ፡ ሊቀ ፡ አለቃ ፡ ነጋሽ ፡ ኃይሉ ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጥር ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ለብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ያበረከቱት ፡ መወድስ ፡

እለ ፡ እስክንድሮስ ፡ ሊቅ ፡ ወቈስጠንጢኖስ ፤ ሰበ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ ዘርዑ ፡ ለተዋሕዶ ፡ ሥርናያ ።

ገራህተ ፡ ሥጋዌ ፡ ኤፌሶን ፡ ወገራህተ ፡ ተሥልስት ፡ ኒቅያ ።
እምክርዳድ ፡ እንዘ ፡ ይነጽሓ ፡ አዕላፈ ፡ ፈረያ ።
ወለጽምእተ ፡ ቃል ፡ ቊስጥንጥንያ ፤ ፶ ፡ ወይተ ፡ እደ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አርወያ ።

ለ ዓ ለ ም

አውዐዩሂ ፡ ሐሠረ ፡ ሮሜ ፡ እንተ ፡ ሮማዊ ፡ ሐሰያ ።
በዓለ ፡ ማዕረር ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ወባስልዮስ ፡ ሐዋርያ ።
እስመ ፡ ዐዋዲሆሙ ፡ ይብል ፡ ማዕከሌክሙ ፡ ነያ ።
አርቶዶክሳውያን ፡ ዘትበውኡ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ኢትዮጵያ ።

አፈ ፡ ሊቀ ፡ ሊቃውንት ፡ ያበረከቱት ፡ መወድስ ።

ቅዳሴ ፡ መላእክት ፡ ይምላእ ፡ በኢትዮጵያ ፤ ድልዋነ ፡ ክብር ፡ ኮኑ ፡ ጳጳሳቲነ ፡ ኀምስቱ ።

www.ethiopianorthodox.org

እስመ ፡ እምጅቱ ፡ ባስልዮስ ፡ ገባሬ ፡ ሠናይ ፡ ውእቱ ።
ወካህን ፡ እንተ ፡ ይትራድአ ፡ ሚካኤል ፡ ዝንቱ ።
ዲበ ፡ መትክፈ ፡ ይስሐቅ ፡ ይትረአይ ፤ ዘበተአምር ፡ ኮነ ፡ ትንሣኤ ፡ አበዊነ ፡ እለ ፡ ሞቱ ።

ለ ዓ ለ ም

ቴዎፍሎስሂ ፡ ወያዕቆብ ፡ ወጢሞቴዎስ ፡ ፫ቱ ።
ተዚያነዉ ፡ ሚጠተ ፡ ፄዋ ፡ ለተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሀብተ ፡ ክህነቱ ።
እምከመ ፡ ሀብተዝ ፡ ተውህበ ፡ ለኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ባሕቲቱ ።
አኃው ፡ ጳጳሳት ፡ ሶበ ፡ ይሄልዉ ፡ በመንግሥቱ ።
አምጣነ ፡ ናሁ ፡ ሠናይ ፡ ለኀብረቶሙ ፡ ርእየቱ ።
አኃው ፡ ጳጳሳት ፡ ሶበ ፡ ይሄልዉ ፡ በመንግሥቱ ።

የመናገሻ ፡ ቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ደብር ፡ አለቃ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ሀብቴ ፡
በሢመተ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በዓል ፡ ያበረከቱት ፡ መወድስ ።

አባስልዮስ ፡ ገባሬ ፡ ሠናይ ፡ ሥርዓተ ፡ ቅዳሴ ፡ ዘግብጽ ፡ ይእዜ ፡ እመ ፡ ደገምከ፡
ዘበደኃሪ ፡ ለይኩን ፡ ፍሬ ፡ ቅዳሴ ፡ ዕድሜከ ።
ለዘአልባቲ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ቅድመ ፡ ዮም ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ዘተዘግበት ፡ ለከ ።
ይእዜ ፡ እስመ ፡ ወሀብከ ።

ፍጹመ ፡ ትኩን ፡ አሐተ ፡ ዘተረፈተከ ።
ተመጠወሂ ፡ ጽላተ ፡ ሕግ ፡ እንተ ፡ ማርቆስ ፡ አቡከ ።
አርዌ ፡ ብርት ፡ ዘአቀመ ፡ ሙሴ ፡ ሀብተ ፡ ዚአከ ።
ዘይሜኒሰ ፡ ለሕዝብ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ወይነከ ።
እምአስትዮቱ ፡ እስከ ፡ ይእዜ ፡ ለምንት ፡ አስተደኀርከ ።

የቦሩ ፡ ሜዳ ፡ ሥላሴ ፡ ደብር ፡ አለቃ ፡ ገብረ ፡ ዮሐንስ ፡ ያበረከቱት ፡ መወድስ ።

እፎ ፡ ታነክር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደመና ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ክብር ፡ ለባስልዮስ ፡ አመ ፡ ሠወሮ ።

እምሊቀ ፡ ምርፋቅ ፡ ዘዮም ፡ አምጣነ ፡ ነሥአት ፡ አንክሮ ።
እንዘ ፡ ኢየሐጽጽ ፡ አንክሮታ ፡ ለኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ መንግሥቶ ፡ ወክብሮ ።
በኵረ ፡ ትንሣኤሰ ፡ ባስልዮስ ፡ በብዝኀ ፡ ብርሃኑ ፡ ረቂቅ ፡ ለጽልመተ ፡ ሮሜ፡ አያር ።

ይትነበብሂ ፡ በበዕለቱ ፡ ለእለ ፡ በሙ አእምሮ ።
መዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘአፈ ፡ ባስልዮስ ፡ ይፌክሮ ።
ወእለ ፡ ሰምዑ ፡ ይቤሉ ፡ ነጐድጓደ ፡ ማርቆስ ፡ ሠምሮ ።
ወበ ፡ እለ ፡ ይቤሉ ፡ መልአክ ፡ ተናገሮ ።

አለቃ ፡ አምኃ ፡ ወልደ ፡ አረጋይ ፡ በ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሐር ፡ አምባ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ደብር፡ የተቀኙት ።



አሠረ ፡ ንጉሥ ።

ቡሩክ ፡ ባስልዮስ ፡ ዘይመጽእ ፡ ኀበ ፡ ቀዳማዊ ፡ ክህነት ።
በስመ ፡ አቡሁ ፡ ማርቆስ ፡ ዘልብሰ ፡ ዕፃሁ ፡ ስብከት ።
ባሕቲቱ ፡ ተሰምየ ፡ ሊቀ ፡ ኖሎት ።
እምነጳጳሳት ፡ ዘቀድሑ ፡ ባሕረ ፡ ሃይማኖት ።
እስመ ፡ አኮ ፡ እንተ ፡ በ ፡ ሕፀት ።

የደብር ፡ ቅዱስ ፤ (ደብረ ፡ ጽጌ) ፡ ታቦተ ፡ ማርያም ፡ በ፲፱፻፴፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በብፁዕ ፡ ዕጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ጸሎተ ፡ ቡራኬ ፡ መቃረቢያው ፡ ቤተ ፡ ክርቲያን ፡ ተባርካ ፡ በገባች ፡ ጊዜ ፡ አለቃ ፡ ምሕረት ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስ ፡

የተቀኙት ፡ ፩ኛ ፡ቅኔ ፡ ዋዜማ ።

ለኢየሩሳሌም ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ ኰሉ ፡ ፍጥረት ፡ ይትሜነይዋ ፡ ገሀደ ።
መቅደስ ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ እስመ ፡ ዮም ፡ ተወልደ ።
እምዘርአ ፡ ዳዊት ፡ ጥበብ ፡ እንተ ፡ ስብሓቲሁ ፡ ፈድፈደ ።
ወቀናዔ ፡ ልብ ፡ ኄሮድስ ፡ በቅንአት ፡ ነደ ።
ወዜናሁ ፡ ምድረ ፡ ግብጽ ፡ ወረደ ።

፪ኛ ፡ቅኔ ፡ መ ወ ድ ስ ።

ሐድሶ ፡ ሕንጻታ ፡ ለሳሌም ፡ ክብረ ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ በሕዋረ ፡ ሰሎሞን ፡ ይም ጻእ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ተሰአለ ።
እንዘ ፡ መንክረ ፡ ወልድ ፡ ይገብር ፡ ወይትመረጐዝ ፡ መስቀለ ።
ከመ ፡ ይርአይ ፡ ፍጻሜሃ ፡ ዳዊት ፡ ልቡና ፡ ዚአሁ ፡ ዘበጽድቅ ፡ መሐለ ።
ወዐብየ ፡ ወተልዕለ ።
እስመ ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ ጳውሎስ ፡ አክሊለ ፡ ብርሃን ፡ ተቀጸለ ።
አመ ፡ ርእዩሂ ፡ ሥነ ፡ ሕንጼሃ ፡ እለ ፡ ሰበኩ ፡ ወንጌለ ።
ለተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መገብተ ፡ ቤቱ ፡ ዘበቃለ ፡ ልሳን ፡ ኢተሐበለ ።
ደምሂ ፡ ወማይ ፡ እምክሣደ ፡ ሰማዕት ፡ ፈልፈለ ።
ሞት ፡ ወተዋርዶ ፡ በዘመነ ፡ ሮም ፡ አመ ፡ ኀየለ ።

በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መስከረም ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ አዲሱ ፡ የደብር ፡ ቅዱስ ፡ ደብረ ፡ጽጌ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከተመሠረተ ፡ በኋላ ፡ አለቃ ፡ ምሕረት ፡
ገብረ ፡ኢየሱስ ፡ በበዓለ ፡ አስተርእዮ ፡ የተቀኙት ፡ ፩ኛ ፡ ቅኔ ፡ ዋዜማ ።

በታቦር ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ መሠረተ ፡ መቅደስ ፡ አምላክ ፡ ለእመ ፡ ይሠርዕ ፡ ሕገ ።
ኤልያስ ፡ ሕንጻ ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ ሰማያተ ፡ ዐርገ ።
ወባስልዮስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ዘባሕረ ፡ ኒሩቱ ፡ ለኢነትገ ።
ይቤሎ ፡ ለወልድ ፡ ንንበር ፡ ዲርገ ፡ ወግበር ፡ ሠለስተ ፡ ኀዳገ ።
የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሕንጻ ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፤

www.ethiopianorthodox.org

## በበዓለ ፡ አስተርእዮ ፡ የተቀኙት ፡ ፪ኛ፡ዋዜማ ።

ሰገደ ፡ በብረኪሁ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ባስልዮስ ፡ ወእንተ ፡ እዴሁ ፡ አልዐለ ።
ጰራቅሊጦስ ፡ በላዕለ ፡ መቅደሱ ፡ እስመ ፡ ዮም ፡ ጸለለ ።
እምድኅረ ፡ ሕያው ፡ ፈጸመ ፡ ሐኒጸ ፡ ቤቱ ፡ ኀያለ ።
ወበደብረ ፡ ጽጌ ፡ ወረደ ፡ ዘምሕረት ፡ ቃለ ።
በጸሎታ ፡ ለድንግል ፡ ድንግለ ።

---

ብላታ ፡ መኰሪያ ፡ ጎዳና ፡ ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መስከረም ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ በዓለ ፡ ሢመተ ፡ ጵጵስናን ፡ ከብፁዓን ፡ ጳጳሳት ፡ ጋራ ፡ በደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ባስከበሩ ፡ ጊዜ ፡ ያበረከቷቸው ፡ ቅኔዎች ።

፩ኛ ፡ መወድስ ፡ (ቅኔ) ፡ ዝናመ ፡ ጳጳሳት ፡ ሢመት ፡ ዘኢያስተርአየ ፡ አስተርአየ ፡ ለነ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ደመና ። አምጣነ ፡ ኢትዮጲ ፡ ነበረት ፡ በዘፈጣሪ ፡ ሕሊና ። እም ፡ ቅድመ ፡ ሥርዋፁ ፡ ለአብርሃም ።

ዘከነ ፡ አዕቃጼ ፡ ሢመቱ ፡ ለጴጥሮስ ፡ ሰኰና ፤ ወእም ፡ ከርሠ ፡ እሙ ፡ እስክንድርያ ፡ ኅሩየ ፡ ኅሩያን ፡ ባስልዮስ ፡ ለመንበረ ፡ ማርቆስ ፡ ዕንቄ ፡ ብርሃና ።
አንፈርዐፁሂ ፡ ወተፈሥሑ ፡ አድባረ ፡ ሊባኖስ ፡ ወሲና ፤ አመ ፡ ቦአ ፡ ደብረ ፡ ዐስበ ፡ ባስልዮስ ፡ ሆሣዕና ። አኮኑ ፡ ይቤሎሙ ፡ አብ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጸወና ፡ እም ፡ ግብጽ ፡ ጸዋዕክዎ ፡ ለወልድየ ፡ ጵጵስና ።

### ፪ኛ ፡ መወድስ ።

መድኃኒተ ሥጋ ፡ ወነፍስ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፤ አሕዛብ ፡ ወሕዝብ ፡ ለኪ ፡ ይሰግዱ ። ደቂቀ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ማያት ፡ ዘእምኔኪ ፡ ተወልዱ ፡ ህየንተ ፡ አበውኪ ፡ ሕሙማን ፡

ለምሕረት ፡ አምጣነ ፡ ተሠይሙ ፡ ወሕማመ ፡ ኬዱ ። ወእንዘ ፡ ስመኪ ፡ ይዘክሩ ፡ አጋእዝተ ፡ ዓለም ፡ ክብረኪ ፡ ወአፍቅሮተኪ ፡ አፈድፈዱ ።
ባስልዮስሂ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ወተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አሐዱ ። ሥነ ፤ ሃይማኖትኪ ፡ ተዋሕዶ ፤ ወሰላመ ፡ ዚአኪ ፡ ይፈቅዱ ። እስመ ፡ ተዋሕዶ ፡ ወፍቅር ፡ አጻብዐ ፡ ወንጌል ፡ እዱ ፡ አውታረ ፡ ሃይማኖት ፡ ሊቃውንተኪ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ ያስተዋድዱ ።

---

መልአከ ፡ ብርሃን ፡ አድማሱ ፡ ዝምበሬ ለብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ፲፱፻፵፪ ፡ ዓ ም መስከረም ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ (በርእሰ ፡ ዐውደ ፡ ዓመት ፡) ያበረከቱት ።

### (ዕ ን ቍ ጣ ጣ ሽ) ፡ ቅኔ ።

ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ አበዊነ ።
ስቡሕኒ ፡ ውእቱ ፡ ወልዑልኒ ፡ ውእቱ ፡ ለዓለም ።
ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ።



ስቡሕኒ ፡ ውእቱ ፡ ወልዑልኒ ፡ ውእቱ ፡ ለዓለም ።
ይትባረክ ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ ባስልዮስ ።
ስቡሕኒ ፡ ውእቱ ፡ ወልዑልኒ ፡ ውእቱ ፡ ለዓለም ።

### ባ ስ ል ዮ ስ ፡ ዘ ቂ ሣር ያ ።

ሕገ ፡ ሞተ ፡ ዐከን ፡ ተዘኪሮ ፡ ዘእንበለ ፡ ድልወት ፡ ፈትሐ ፡ ፍትሐ ፡ ቃለ፡
ሙሴ ፡ ንጉሥ ።
ለትሠረው ፡ በመልዕልተ ፡ ልብሱ ፡ ዘትትሐወስ ፡ ነፍስ ።
እስመ ፡ ሕገ ፡ ሙሴ ፡ ፈተወ ፡ እንዘ ፡ ዘመኑ ፡ ሐዲስ ።
ዘኢትዮጵያሰ ፡ ባስልዮስ ።
ሕሙማነ ፡ ልብስ ፡ አሕየወ ፡ በዘፈረ ፡ ልብስ ።
እስመ ፡ ሕጉ ፡ ሕገ ፡ ወልድ ፡ ክርስቶስ ።

### ብ ፁ ዕ ፡ ሆ ይ ።

ስንኳን ከዘመነ ፡ ማቴዎስ ፡ ወደ ፡ ዘመነ ፡ ማርቆስ ፡ አሸጋገረዎ ። ይህን፡ ሐዲሱንም ፡ ዘመን ፤ ሐዲስ ፡ ሆኖ ፡ በሰፊው ፡ ለታቀደ ፡ መንፈሳዊ ፡ ሥራዎ ፡ ማከናወኛ ፡ ያደርግልዎ ፡ ዘንድ ፡ እየተመኘሁ ፡ እንቍጣጣሽ ፡ እላለሁ ።
በቅን ፡ ታዛዥዎ ፡ መልአከ ፡ ብርሃን ፡ አድማሱ ።

---

፲፱፻፵፩ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ አለቃ ፡ አምኃ ፡ ወልደ ፡ አረጋይ ፡ የሰላይ፡ ድንጋይ ፡ ቅዱስ ፡ ማርቆስን ፡ ደብር ፤ ልቅና ፡ ተሹመው ፡ ሳሉ ፤ ለብፁዕ ፡ ሊቀ ጳጳሳት ፡ ያበረከቱት ፡ ፩ኛ ፡ መወድስ ፡ ቅኔ ፡ ተዋሕዶ ፡ በሕርይ ፡ ኤፌሶን ፡ ፈለገ ፡ ሐሊብ ፤ ወፈለገ ፡ መዓር ፡ ጤግሮስ ፡ በብሂል ፡ ይተረጐም ። ወይቤ ፡ ልብነ፡ ሙሐዘ ፡ ስባሔ ፡ ጥዑም ። ተፈሥሒ ፡ ጽዮን ፡ ኢትዮጵያ ።

እስመ ፡ በጽሐ ፡ ክብረ ፡ ጵጵስና ፡ ሰላምኪ ፡ ዮም ። እንዘ ፡ ቃለ ፡ ባስልዮስ ፡ መተርጕም ። ምጽአተ ፡ ብርሃን ፡ ይሰብክ ፡ ለነቂሀ ፡ እም ፡ ንዋም ።
ለስምከሂ ፡ ትሴብሖ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በጥበብከ ፡ ዘተነግረ፡ ለዓለም ፡ እስመ ፡ ብርሃነ ፡ ክብር ፡ ለብሱ ፡ በተዋሕዶ ፤ ፍጹም ፡ ኢትዮጵያ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ወእስክንድርያ ፡ አርሞንዔም ።
አለቃ ፡ አምኃ ፡ ወልደ ፡ አረጋይ ፡ ፲፱፻፵፪ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በወርኀ ፡ ጥር ፡ በሰላ ፡ ድንጋይ ፡ ቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ደብር ፡ የተቀኙት ፡ ፪ኛ ፡ መወድስ፡ በኤጲፋንያ ፡ ተነግረ ፡ ዝክረ ፡ ቅድሳቱ ፡ ለሥግው ፡ ቃል ዘተዐውቀ ፡ በኒቅያ ፡ እንዘ ፡ ቅድመ ፡ ንጉሥ ፡ ይትከፈል ፡ ምህርካ ፡ ሃይማኖት ፡ ሰርያ ። እስመ ቦ ፡ ባስልዮስ ፡ ሐዋርያነ ።

ዘይነሥእ ፡ ኀይለ ፡ ደማስቆ ፡ እንዘ ፡ ጽድቅ ፡ ነያ ። ሃይማኖት ፡ እንተ ፡ ኀረያ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሰሎሞን ፡ ለሐኒጸ ፡ መቅደስ ፡ ኢትዮጵያ ።

www.ethiopianorthodox.org

ማርቆስሂ ፡ ይቤለነ ፡ በቃለ ፡ ትርጓሜ ፡ ኬንያ ። ገደፈቶ ፡ ለንጉሣ ፡ ሕገ፡ ልዮን ፡ ሰማርያ ። እስመ ፡ በስብከቱ ፡ ሐዳስ ፡ ለደብረ ፡ ኅሩያን ፡ አዕበያ ። ወበዕንቄ ፡ ሰንፔር ፡ ተዋሕዶ ፡ እም ፡ አርእስተ ፡ አድባር ፡ አሠነያ ።

ቀኝ ፡ ጌታ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ ፀሐዩ ፡ ዘብሔረ የጁ ፡
ያበረከቱት ፡ ቅኔ ።

ሐመረ ፡ መድኃኒት ፡ ባስልዮስ ፡ ማዕዶተ ፡ ግብጽ ፤ አድያመ ፡ ዮርዳኖስ ፡
ዖደ ፡ ከመ፡ ይዜኑ ፡ ትዕግሥቶ ።
ለኃይለ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሥ ፡ ወእምዘርአ ፡ ዳዊት ፡ ምጽአቶ ።
እስመ ፡ ሀለወነ ፡ ፍቁራን ፤ ከመ፡ ንርአይ ፡ በዓይነ፡ ሥጋዊ ፡ ዳግመ፡ ልደቶ ።
ባሕቱ ፡ ሕዝበ ፡ ሮምያ ፡ ሙሴ ፡ ዘርዕደ ፡ ስእነ ፡ ጠይቆቶ ።
ባሕርሂ ፡ ግርምት ፡ ሙሴ ፡ ለእመ ፡ ርእዮቶ ።
ሰገደት ፡ በብረኪሃ ፡ ወበቃለ ፡ ሰላም ፡ አእኰተቶ ።
ከመ ፡ ተወፈየት ፡ እም ፡ ኢትዮጵያ ፡ መንግሥቶ ።
እሞ ፡ እስመ ፡ ረሰያ ፡ ወከነት ፡ ወላዲቶ ።

፫ ኛ ፡

ሕዝበ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ቅድስት ፡ በዘይትሐነጽ ፤ ምንት ፡ ውእቱ ፡ ለስነ ፡ ጥበብ፡ ትርጓሜሁ ።
እስመ ፡ ሰመዮ ፡ ጳውሎስ ፡ ነገረ ፡ በሐውርት ፡ ዘበዝኀ ።
ወእሉ ፡ ይሰምይዎ ፤ በስነ ፡ ጥበብ ፡ ይትለወል ፡ ለሊሁ ።
ለነሰ ፡ ይደልወነ ፡ ንስቲተ ፡ ናእምር ፡ ለንባብ ፡ ፍካሬሁ ።

ለ ዓ ለ ም ።

ወኣከ ፡ ለእመ ፡ ንቤ ፡ ዘኢንኀድግ ፡ ኪያሁ ።
ለዝ ፡ ተስናነ ፡ ሜድ ፡ አምጣነ ፡ ጳውሎስ ፡ ሠራዒሁ ።
ባሕቱ ፡ ይሰመይ ፡ ፍካሬ ፡ ወንጌል ፡ ላዕሌሁ ።
ኪያሁ ፡ ለዘይጼሊ ፡ ይትሐነጽ ፡ ልቡናሁ ።

---

አለቃ ፡ ምሕረት ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስ ፡ የተቀኙት ።
፩ኛ ፡ አሠረ ፡ ንጉሥ ።

ጉባኤ ፡ ሃይማኖት ፡ ባስልዮስ ፡ አስተጋብአ ፡ እለ ፡ ተዘርዉ ፡ ወጽንፍ። ድኅረ ፡ ኖላዊሆሙ ፡ ከነ ፡ ለሕዝበ ፡ እስራኤል ፡ አዕላፍ ።
ወይቤ ፡ ወንጌል ፡ ልሳነ ፡ ሰይፍ ። ሰማይ ፡ ወምድር ፡ እንዘ ፡ የኀልፍ ። ደብረ፡ ጽጌ ፡ ትነብር ፡ ለዘልፍ ።

፪ኛ ፡ አሠረ ፡ ንጉሥ ።

ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከርካዕ ፡ ሐመልማለ ፡ እንዘ ፡ ይለብስ ፡ ሀለወ ። ውኂዘ ፡ መንግሥት ፡ ኤፌሶን ፡ እስመ ፡ በላዕሌሁ ፡ ተክዕወ ።
ወፍሬ ፡ ሃይማኖት ፡ አስተዳለወ ። በደብረ ፡ ጽጌ ፡ ባስልዮስ ፡ ድኅረ ፡ አንሶ ሰወ ፡ በመስቀሉ ፡ ጸላኤ ፡ ዘረወ ።



የደብረ ፡ ብርሃን ፡ ቀኝ ፡ ጌታ ፡ መዘምር ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ለብፁዕ ፡ አባታችን ፡
ያበረከቱት ፡ መወድስ ።

ባስልዮስ ፡ ከል ፡ ጼና ፡ ተዋሕዶ ፤ በምሥያጠ ፡ ሕግ ፡ ዘአሮን ፡ ወዘውገ ፡ መልከ፡ ጼዴቅ ፡ ይረፍቁ ። እስመ ፡ ዘፈቀደ ፡ ይንሣእ ፡ ለህልዋነ ፡ ሕግ ፡ ደቂቁ ። ኖህ ፡ መድሎቱ ፡ ወአብርሃም ፡ ወርቁ ። ወይስሐቅ ፡ ተከሊሁ ፡ ወሰቃይሁ ፡ ያዕቆብ ፡ ማየ ፡ ቃለ ፡ ጽድቁ ። ኤልሳዕሂ ፡ ወኤልያስ ፡ እንዘ ፡ ይትላጸቁ ፡ ዓቀብተ፡ ቃላት ፡ አቅማሒሁ ፡ በመስፈርተ ፡ ሙሴ ፡ እስከ ፡ ተዐውቁ ።
በዘሥርወ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሥርዉ ፡ ወበዘአጽቀ ፡ ሳውል ፡ አጽቁ ፡ አዕዋፈ ፡ ልዮን፡ ኢይብልኡ ፡ ወሰረቅተ ፡ ንስጥሮስ ፡ ኢይሰርቁ ።

፪ኛ ፡ መወድስ ።

መዝገበ ፡ ረድኤት ፡ ባስልዮስ ፡ ምሉኅ ፡ ርኅራኄ ፤ ፀቃውዓ ፡ ዮሴፍ ፡ ንህብ ፡ ዮሐንስ ፡ ዘአተበ ። ወአስተጋብአ ፡ ያዕቆብ ፡ አስተራታኢ ፡ መዝገበ ።
እምከመ ፡ ደመና ፡ ደመና ፡ ተዓቅበ ።
አድብረ ፡ ባስልዮስ ፡ ሕዋሳተ ፡ ዘበ ፤ ሳሙኤል ፡ ወኃይለ ፡ ቃለ ፡ ሳአል ፡ አልበ ።
(ለዓለም) ፡ ወለደቶሂ ፡ እንበለ ፡ ዘርእ ፡ ዖፈ ፡ መዋዕል ፡ ተውህበ ።
ለእንቄ ፡ ባሕርይ ፡ ጽጽስና ፡ ዘብርሃን ፡ ይገለብበ ።
አከኑ ፡ ዘሀብት ፡ እንቄ ፡ ጽጽስና ፡ ተረክበ ።
ተዋሕዶ ፡ መብረቅ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ወባስልዮስ ፡ ማየ ፡ ዐሎበ ።

ሣልስተኛ ፡ መወድስ ፤

ይበወእ ፡ ምዕረ ፡ ለለመዋዕል ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ሀብት ፡ ቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡
ሥጋከ ። እስመ ፡ እምርጉቅ ፡ ይጼኑ ፡ ሙዳየ ፡ ዕፍረት ፡ ስምከ ።
ወበተፋቅሮ ፡ ሥነ፡ ፍጥረት ፡ አመተአዘዙ ፡ ወተፈጥሩ ፡ ሰርከ ፤
ፍጥረተ ፡ ቀደምት ፡ አዝማኒነ ፡ በነግህ ፡ ተፈጥረ ፡ አዳም ፡ ጽጽስናከ ።
(ለዓለም) ፡ ትሴብሐከሂ ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ ወታሌዕለከ ።
ሥርወ ፡ ሃይማኖት ፡ እስመ ፡ ከነ ፡ አብርሃም ፡ ክህነትከ ።
ወመምህረ ፡ ሕግ ፡ ጴጥሮስ ፡ አመ ፡ ቃለ ፡ ወንጌል ፡ ሰበከ ።
ያስተጋብእ ፡ መጻሕፍተ ፡ ቀሌምንጦስ ፡ ልቡናከ ።
ባስልዮስ ፡ አበ ፡ ለዕጓለ ፡ ማውታ ፡ ዘኮንከ ።

ቀኝ ፡ ጌታ ፡ መዘምር ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡
ደብረ ፡ ብርሃን ።

---

በደብረ ፡ ብርሃን ፡ ሥላሴ ፡ ተቀምጠው ፡ ብሉይና ፡ ቅኔ ፡ ያስተምሩ ፡ የነበሩት ፡ አለቃ ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስ ፡ ለብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በዕጨጌነታቸው ፡ ጊዜ ፡ ያበረከቷቸው ።

መወድስ ፡ ቅኔ ፤

ካዕበተ ፡ መንፈስ ፡ ወሀብት ፡ ለእሙ ፡ ተውህበ ፡
ለገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፤ ኤልሳዕ ፡ ላዕከ ፡ ኤልያስ ፡ አእምሮ ፡
ምክረ ፡ ደማስቆ ፡ አእመረ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ነቢሮ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ለአዴር ፡ ፀረ ፡ መንግሥትነ ፡ ከመ ፡ ይሥዓር ፡ ምክሮ ፡
እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘፈጠሮ ፡
በዓምደ ፡ ደመና ፡ ብሩህ ፡ መንበረ ፡ ማርቆስ ፡ ተድኅሮ ።
በጸሎቱሂ ፡ ቅጽረ ፡ እሳት ፡ ለኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሐፀሮ ፡
በውስተ ፡ ሕጽኑ ፡ አመ ፡ ረፈቀ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ዘያፈቅሮ ፡
አምጣነ ፡ ሎቱ ፡ ተውህበ ፡ ምስለ ፡ ቅድስና ፡ ተድኅሮ ፡
ሞቶ ፡ አቤል ፡ ጸላኢሁ ፡ ከመ ፡ ይግባዕ ፡ ተኃፊሮ ፡

---

የጐጃም ፡ ጥድ ፡ ማርያም ፡ ካህን ፡
አለቃ ፡ ገብረ ሥላሴ ፡

<u>መወድስ ፡ ቅኔ ።</u>

፲፱፻፶፱ ዓመተ ፡ ምሕረተ ፡ ሚያዝያ ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ለቀዳም ፡ ሥዑር ፡ በዓል ፡ ያበረከቷቸው ፡

ፀሐይ ፡ ባስልዮስ ፡ ሰዳዴ ፡ ጽልመት ፡
ጊዜ ፡ ፀአትከ ፡ ኮኑ ፡ ጽልሙታነ ፡ ግብር ፡ ብርሃናተ ።
ከመ ፡ ይኩን ፡ ለነ ፡ መግቦትከ ፡ መዓልተ ።
እስመ ፡ ሠምረ ፡ ወፈቀደ ፡ አምላከ ፡ በጸልዮትከ ፡ ዘሠዓረ ፡ ሞተ ።
ወአውረደ ፡ ዝናማተ ።
ነቢየ ፡ ተአውቆ ፡ ሀብትከ ፡ ዘነሥአ ፡ በረከተ ።
ስብከትከሂ ፡ ዘበወንጌል ፡ ድኅረ ፡ ፈጠረ ፡ አዕይንተ ።
አሠርገወ ፡ ልቡናነ ፡ ምሥጢራተ ፡ ጳውሎስ ፡ ትርሚታተ ።
ወበበዕለት ፡ ሜመ ፡ ዘያሴስሉ ፡ ሴሊተ ።
ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በጠፈራ ፡ ዕልፈ ፡ ከዋክብተ ።

---

የመቀሌ ፡ መልአከ ፡ ፀሐይ ፡ አብርሀ ፡ ጽጌ ፡ ለብፁዕ ፡ አባታችን ፡
<u>በየጊዜው ፡ ያበረከቷቸው ፡ ቅኔዎች ፡</u>

<u>፩ኛ ፡ መወድስ ፡</u>

በደመና ፡ ምሥጢር ፡ ዐረጉ ፡ ሰማየ ፡ ትርጓሜ ፤ ወነጸርክዎ ፡ ለአብ ፡
ባስልዮስ ፡ ምስለ ፡ ጻድቃን ።
አኮኑ ፡ ባረከ ፡ ዓመተ ፡ ጻድቃን ፡ ኄራን ።
ለባስልዮስ ፡ አበ ፡ እንቲአነ ፡ መስቀሉ ፡ ብርሃን ፡
ንሕነ ፡ መላእክት ፤ አመ ፡ ተናግሮ ፡ ወጠነ ፡ ምስለ ፡ ሰብአ ፡ ሐዲስ ፡ ልሳን ፡
ትኩላንሂ ፡ ማዕከላ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መካን ።
አፅማደ ፡ ምሥጢር ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ወባስልዮስ ፡ ጽኑዓን
ወአልዐልዎ ፡ እምድር ፡ ለወልታሆሙ ፡ ሥልጣን ።
እስመ ፡ ፀንዓ ፡ መሠረት ፡ መንግሥት ፡ ዳዊት ፡ ወሰሎሞን ።



<u>፪ኛ ፡ መወድስ ፡</u>

እግዚአብሔር ፡ ገብረ ፡ በከመ ፡ ነበበ ፤ አምጣነ ፡ ጸውዓ ፡ ለምድር ፡ መዓ
ርገ ፡ ጴጥሮስ ፡ እምሮምያ ።
ወአኮ ፡ ዘተርፈ ፡ በእስክንድርያ ፡
ዘንቡር ፡ ላዕሌሃ ፡ ማርቆስ ፡ ኬንያ ፡
እምአድባረ ፡ ሕግ ፡ አንፃኪያ ፡
ወቁስጥንጥንያ ፡ ዘኮነት ፡ እንተ ፡ ኤፌሶን ፡ አርአያ ፡
ቅድስት ፡ ወብፅዕት ፤ ኢትዮጵያ ፡
ድኅረ ፡ በስመ ፡ አብ ፡ ጸውአቶ ፡ ለባስልዮስ ፡ ሐዋርያ ፡
ወጽጽስናሁ ፡ ስንበት ፡ በዓለ ፡ አምላክ ፡ ነያ ።
ለጽዮን ፡ ሰብእናሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ ኃረያ ።

<u>፫ኛ ፡ መወድስ ፡</u>

ማርያም ፤ ግብዕ ፡ እምዕፍረተ ፡ ርእሳ ፡ ጽጽስናሃ ፡ ዕፍረተ ፡ ቀብዓቶ ፡
ለእግዚእነ ።
ይሁዳሰ ፡ ፀር ፡ በምግባራቲሃ ፡ ኃዘነ ።
እንዘ ፡ ይብል ፡ ዛቲ ፡ አኅጕልት ፡ መከነ ።
ባሕቱ ፡ ኢያእመረ ፤ ከመ ፡ በምግባሩ ፡ ሠናይ ፡ ድኅነተ ፡ ዓለም ፡ ኮነ ።
እስመ ፡ ብዙኃን ፡ ነቢያት ፡ ወጻድቃነ ፡ ከዊን ፡ ጻድቃነ ።
ቀደሙነ ፡ ተጋድሎ ፤ ወነሚአ ፡ አክሊል ፡ ኢቀደሙነ ።
ወአመ ፡ አርኃወ ኃይል ፡ ገነተ ፡ ኅሩያን ፡ ለነ ።
ፍሬ ፡ ምግባሮሙ ፡ ለጻድቃን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ወሀበነ ።

<u>፬ኛ ፡ መወድስ ።</u>

ሕንፃ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ አርአየ ፡ ዘኢትዮጵያ ፤

ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሰሎሞን ፡ ወቆመ ፡ ብእሲ ፡ ውስቴቱ ።
ለቤተ ፡ መቅደስ ፡ ዘገብረ ፡ እስመ ፡ ትኩላን ፡ እሙንቱ ።
አዕማደ ፡ ሕግ ፡ ጳጳሳት ፡ ፭ቱ ።
ለስምዕ ፡ ይትከሠቱ ፤ ወጸሐፍተ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፡ እምዕሉ ፡ እስከ ፡ ታሕቱ ።
ባስልዮስሂ ፡ አንሶሰወ ፡ በሕዋረ ፡ ሰሎሞን ዝንቱ ።
ሐምሰ ፡ መካልዕየ ፡ እስመ ፡ ገብረ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ።
ወበእርፈ ፡ መስቀል ፡ ቅዱስ ፡ እንዘ ፡ ሐራሲ ፡ ውእቱ ።
ለርኅባነ ፡ ምክር ፡ አጽገቦሙ ፡ ኅብስተ ፡ አእምሮ ፡ በበረከቱ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፰ኛ ፡ መወድስ ።

ትጉሐ ፡ ባሕርይ ፡ ልብ ፡ ዘኢየዓርፍ ፤ በእግረ ፡ ሕሊና ፡ ተንሥአ ፡ ወዐ
ርገ ፡ ውስተ ፡ ፅማይ ።
አኮኑ ፡ ፈቃደ ፡ ከመ ፡ ይርአይ ።
ሠርጐ ፡ ጽጽስና ፡ ዘስሙ ፡ ፀሐይ ።
ወመብረቀ ፡ ስብሐት ፡ ይሰመይ ።
ቅድመ ፡ ገጸ ፡ መልአከ ፡ ወሰብእ ፡ ዘርእየቶሙ ፡ ሠናይ ።
ድኅረ ፡ አንገሥዎ ፡ በትፍሥሕት ፡ ለወልደ ፡ አእምሮ ፡ ዕሜይ ።
እለ ፡ ተጋብዑ ፡ እስራኤል ፡ ጥበባተ ፡ ሐዲስ ፡ ወብሉይ ።
ወይቤ ፡ እንተ ፡ መጽአ ፡ ቃል ፤ እምደመና ፡ ግብዕ ፡ ዓባይ ።
ሰማይ ፡ ይትፌሣሕ ፡ ወምድር ፡ ትትሐሠይ ።

መልአከ ፡ ፀሐይ ፡ አብርሃ ፡ ጽጌ ፡ (መቀሌ) ።

---

አለቃ ፡ ሥርግው ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡ ለብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ያበረከቱት ፡

## መወድስ ፡ ቅኔ ።

ምኵራበ ፡ ምኒልክ ፡ ዐነመት ፡ ፀምረ ፡ ተዋሕዶ ፤
ወቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተዐጽፈት ፡ በኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘመነ ፡ ማህል ።
እስመ ፡ አናሚሁ ፡ ባስልዮስ ፡ ፀዋሬ ፡ መስቀል ።
ወውእቱ ፡ መስቄሁ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ቃል ።
ወእምአፍላጋት ፡ ፬ቱ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ትሰቀይ ፡ ፈለገ ፡ ትምህርቱ ፡ ለሚካኤል ።
ጳውሎስሂ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ እንተ ፡ አልበቱ ፡ አምሳል ።
ተነግረ ፡ በመልእክቱ ፡ ወእስከ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ይትሌዐል ።
ያዕቆብሂ ፡ ዘሥሩግ ፡ በውስተ ፡ ድርሳኑ ፡ ዘይብል ።
ለዘጳጳሳት ፡ ፋሲካሆሙ ፡ ቀዳሚት ፡ ሕገ ፡ ወንጌል ።

---

አለቃ ፡ ነጋሽ ፡ ኃይሉ ፡ ለብፁዕ ፡ አባታችን ፡ በዓለ ፡ ሢመተ ፡ ሊቀ ፡

## ጽጽስና ፡ ጊዜ ፡ ያበረከቱት ፡ ቅኔ

ያፍ ፡ እስክንድርያ ፡ ወእጐልት ፡ ያፍ ፡ ኢትዮጵያ ፤ በባሕረ ፡ ሥጋዌ
ዕሙቅ ፡ ለእመ ፡ ፀንሳ ፡ ፀሐየ ፤
ረከባ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘርእ ፡ አሐደ ፡ ባሕርየ ።
ዝኒ ፡ ባሕርይ ፡ አሐዱ ፡ እንዘ ፡ የዐርግ ፡ ሰማየ ።
አመ ፡ ውስተ ፡ ምድርነ ፡ አስተርአየ ።
ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ናርዶስ ፡ አሜሃ ፡ ጸገየ ።
ወሮማን ፡ ባስልዮስ ፡ ፈረየ ።

---



አለቃ ፡ ይትባረክ ፡ መርሻ ፡ ለብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡

## ያበረከቷቸው ፡ ቅኔዎች ፡ ፩ኛ ፡ መወድስ ።

አ አበው ፤ እለ ፡ ትቀንቱ ፤ ሐቌ ፡ ድንጋሌ ፡ በሊሐ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ
ሰይፈ ፡ ወንጌል ።
መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ሳውዕ ፡ ዘደብረ ፡ ቤቴል
ተበውሐ ፡ ይምራሕክሙ ፡ በኀበ ፡ ተተክለ ፡ ባስልዮስ ፡ ፀዳል ።
ሐዋርያተ ፡ ግፍዕ ፡ እስራኤል ።
ዘበብርሃኑ ፡ ተመርሑ ፡ መንገለ ፡ ፍናሁ ፡ ፍና ፡ መስቀል ።
ዕዝንክሙሰ ፡ ብዝኃ ፡ አእምሮ ፡ ሙሐዘ ፡ ርደቱ ፡ ለቃል ።
ለብልጣሶር ፡ ይጸመሞ ፡ ወኢይጸመሞ ፡ ለዳንኤል ።
እስመ ፡ ኀበ ፡ አኮ ፡ ርቱዕ ፡ ነገረ ፡ ቃየል ።
በቃየል ፡ ተሠወረ ፡ ወተከሥተ ፡ በአቤል ።

## ፪ኛ ፡ መወድስ ።

ባስልዮስ ፡ ኅሀ ፡ ዐሠረ ፡ ብርሃን ፤ ዕረፍት ፡ ይስሐቅ ፡ ትርጓሜ ፡ ስሙ ፡ ለኖህ ።
ቴዎፍሎስ ፡ ቤዝ ፡ ኮከበ ፡ ጽባሕ ።
ሠረገላ ፡ ትዕግሥት ፡ ጢሞቴዎስ ፤
ያዕቆብ ፡ ዘመነ ፡ ዕሪና ፡ ምልዓቱ ፡ ለወርኅ ።
በትረ ፡ ቀኖና ፡ ጎርጎርዮስ ፤
ሐመረ ፡ ጸሎት ፡ ፊልጶስ ፡ ብሔረ ፡ ሕያዋን ፡ ዘታበጽሕ ።
ማርቆስ ፡ ምድረ ፡ ሲና ፡ መሠረተ ፡ ሕጉ ፡ ለፍትሕ ።
መንበረ ፡ ገብርኤል ፡ ብሥራታዊ ፡ ገብርኤል ፡ ዓውደ ፡ ንጽሕ ።
ነቢየ ፡ ድንጋሌ ፡ ታዴዎስ ፡ ዘትንቢትከ ፡ ረባሕ ።
ሕጡተ ፡ ብዕልክሙ ፡ ጽጽስና ፡ በኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ለይትባዛሕ ።

## ፫ኛ ፡ መወድስ ።

እምኍልቈ ፡ እስራኤል ፡ ወጽአ ፡ በትእዛዘ ፡ ሙሴ ፤
መገሥፀ ፡ መዓት ፡ ኤልዳድ ፡ ወእመ ፡ ኤልዳድ ፡ ተሞዐ ።
ሙሴ ፡ መክሕ ፡ በዊአ ፡ ምድረ ርስት ፡ ተከልአ ።
ነገረ ፡ ዝንቱሰ ፡ ይትኀደግ ፤
ባስልዮስ ፡ ምስለ ፡ ሠራዊቱ ፡ ምድረ ፡ ርስት ፡ ቦአ ።
እንዘ ፡ ያስተጋብእ ፡ ሠራዊቶ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወግብፀ ፡ እለ ፡ ይትዓፀፉ ፡ ርትዐ ።
ዐርገሂ ፡ ንጉሠ ፡ ፋርስ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ይጽብአ ።
ወሕዝቅያስ ፤ እምግርማሁ ፡ ደንገፀ ፡ ወተኀብአ ።
እምቃለ ፡ ዓዋዲሰ ፡ ወልድ ፡ ብሥራተ ፡ መስቀል ፡ ዘሰምዐ ።
ንጉሥነ ፡ ለኢዮጴ ፡ ዐሥራተ ፡ ምሕረት ፡ አስተዋጽአ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ከአቡነ፡ተክለ፡ሃይማኖት፡ጀምሮ፡በደብረ፡ሊባኖስ፤ የተሾሙት፡ዕጨጌዎች፡ዝርዝር ።

| ተራ፡ ቍ፡ | ስማቸው፡ | አገራቸው፡ | በዘመናቸው፡የነበሩ፡ ነገሥታት፡ |
|---|---|---|---|
| ፩ | ተክለ፡ሃይማኖት፡ | እቲሳ፡ | ይኩኖ፡አምላክ፡ |
| ፪ | ኤልሳዕ፡ | ወላሞ፡ | » » |
| ፫ | ፊልጶስ፡ | ሀሮ፡ | በዓምደ፡ጽዮን፤በሰይፈ፡አርዕድ፡ |
| ፬ | ሕዝቅያስ፡ | | በአጼ፡ሰይፈ፡አርዕድ፡ |
| ፭ | ቴዎድሮስ፡ | | |
| ፮ | ዮሐንስ፡ | | |
| ፯ | ዮሐንስ፡ከማ፡ | | በአጼ፡ይስሐቅ፡ |
| ፰ | እንድርያስ፡ | | » » ዘርዐ፡ያዕቆብ፡ |
| ፱ | መርሐ፡ክርስቶስ፡ | | » » እስክንድር፡ |
| ፲ | ጴጥሮስ፡ | | » » ናዖድ፡ |
| ፲፩ | ዕንባቆም፡ | | » » ልብነ፡ድንግል፡ |
| ፲፪ | ያዕቆብ፡ | | |
| ፲፫ | ማትያስ፡ | | በሚናስ፡ |
| ፲፬ | ዮሐንስ፡ | | በአጼ፡ሠርፀ፡ድንግል፡ |
| ፲፭ | ዮሐንስ፡ | | » " » |
| ፲፮ | ዘትረ፡ወንጌል፡(በትረ፡ወንጌል) | | » » » |
| ፲፯ | አብርሃም፡ | | በያዕቆብ፤በዘድንግል፤በሱስንዮስ፡ |
| ፲፰ | ዘወንጌል፡ | | በአጼ፡ሱስንዮስ፡ |
| ፲፱ | ዘሚካኤል፡ | | በአጼ፡ፋሲል፡ |
| ፳ | በትረ፡ጊዮርጊስ፡ | ሸዋ፡ | » » |
| ፳፩ | ዘክርስቶስ፡ | ሻሚ፡ | » " |
| ፳፪ | የማነ፡አብ፡ | አንዳቤት፡ | » » |
| ፳፫ | ዘክርስቶስ፡ | ደንከላ፡ | በአጼ፡ዮሐንስ፡ |
| ፳፬ | ሕርያቆስ፡ | ማኅደረ፡ማርያም፡ | » » " |
| ፳፭ | ቃለ፡ዓዋዲ፡ | ቤተ፡ልሔም፡ | ባጼ፡ኢያሱ፤አድያም፡ሰገድ፡ |
| ፳፮ | ጸጋ፡ክርስቶስ፡ | ቤተ፡ልሔም፡ | በአጼ፡ኢያሱ፡ |
| ፳፯ | ዮሐንስ፡ | አንጋር፡ | " " " |
| ፳፰ | ሰፋኔ፡ክርስቶስ፡ | | |
| ፳፱ | ዘሚካኤል፡ | (ትግሬ፡ተምቤን፡) | |
| ፴ | አግናጥዮስ፡(አግናጤዎስ) | ትግሬ፡ተምቤን፡ | |
| ፴፩ | ወልደ፡ሐዋርያት፡ | | |
| ፴፪ | ተወልደ፡መድኅን፡ | | |
| ፴፫ | መተከ፡ | | |
| ፴፬ | ዘሚካኤል፡ | | |
| ፴፭ | ዘወልደ፡ማርያም፡ | መጉና፡ | በአጼ፡ዮስጦስና፤በአጼ፡ዳዊት ። |
| ፴፮ | ተክለ፡ሃይማኖት፡ | ትግሬ፡ | በአጼ፡ዳዊት፡ |
| ፴፯ | አቡሊዲስ፡ | ማኅደረ፡ማርያም፡ | በአጼ፡ዳዊት፡ |
| ፴፰ | ኤዎስጣቴዎስ፡ | ሸደሆ፡ | |
| ፴፱ | ሄኖክ፡ | ቤተ፡ልሔም፡ | |
| ፵ | ኢሳይያስ፡ | አዘዞ፡ | |
| ፵፩ | ተስፋ፡ጊዮርጊስ፡ | ውዶ፡ | በአጼ፡ይስሐቅ፡ |
| ፵፪ | ወልደ፡ኢየሱስ፡ | ጎንደር፡ልደታ፡ | » » |
| ፵፫ | ወልደ፡ዮና፡ | ዋልድባ፡ | በአጼ፡ኢዮአስና፡በራስ፡ጉግሣ፡ |
| ፵፬ | ዮሐንስ፡(ዓርከ፡ዮሐንስ) | ሳጋ፡ | በአጼ፡ጊጋር፡ |
| ፵፭ | ፊልጶስ፡ | አትሮንስ፡ማርያም፡ | በራስ፡ጉግሣ፡ |
| ፵፮ | ዘወልደ፡ማርያም፡ | ወቅሮ፡ | በራስ፡አሊ፡ |
| ፵፯ | ገብረ፡ሥላሴ፡ | ሰረፍ፡ | |
| ፵፰ | ገብረ፡ሥላሴ፡ | ዳጋ፡ | |
| ፵፱ | ገብረ፡ማርያም፡ | ሸዋ፡ | |
| ፶ | ማኅጸንተ፡ሚካኤል፡ | ነኝ፡ | |
| ፶፩ | ገብረ፡ማርያም ። | ትግሬ፡ጉድጉንዲ፡ | |
| ፶፪ | ወልደ፡ማርያም፡ | ዋልድባ፡ | |
| ፶፫ | ወልደ፡ትንሣኤ፡ | ጋሸላ፡ | በአጼ፡ቴዎድሮስ፡ |
| ፶፬ | ገብረ፡ኢየሱስ፡ | ናበጋ፡ | በአጼ፡ተክለ፡ጊዮርጊስ፡ |
| ፶፭ | ቴዎፍሎስ፡ | ስሜን፡ወገራ፡ | በአጼ፡ዮሐንስ፡፬ኛ፡ |
| ፶፮ | ገብረ፡ሥላሴ፡ | ትግሬ፡ | በአጼ፡ምኒልክ፡ |
| ፶፯ | ወልደ፡ጊዮርጊስ፡ | ፎገራ፡ | በአጼ፡ምኒልክ፡ |
| ፶፰ | ገብረ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ | ደራ፡አቡነ፡ሐራ፡ | በንግሥት፡ዘውዲቱ፡ |
| ፶፱ | ገብረ፡ጊዮርጊስ፡ | | በቀዳማዊ፡ኃይለ፡ሥላሴ፡ |

www.ethiopianorthodox.org

## ከውጪ ፡ አገር ፡ በየጊዜው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመጡ ፡ የተሰዓቱ ፡ ቅዱሳን ፡ ዝርዝር ።

| ተራ ፡ ቍ ፡ | ስማቸው ፡ | ሀገራቸው ፡ | በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የነበሩበት ፡ ገዳም ፡ |
|---|---|---|---|
| ፩ | አባ ፡ ሊቃኖስ ፡ | ቍስጥንጥንያ ፡ | ደብረ ፡ ቄናጽል ፡ |
| ፪ | አባ ፡ ይምዓታ ፡ | ቆስያ ፡ | ገልዓታ ፡ በሚባል ፡ ገዳም ፡ |
| ፫ | አባ ፡ ጽሕማ ፡ | አንጾኪያ ፡ | ዲድያ ፡ » » |
| ፬ | አባ ፡ ጉባ ፡ | ቂልቅያ ፡ | አባ ፡ ሊቃኖስ ፡ በኖሩበት ፡ አቅራቢያ ፡ በሚገኝ ፡ ገዳም ፡ |
| ፭ | አባ ፡ አፍጼ ፡ | እስያ ፡ | ያሐ ፡ |
| ፮ | አባ ፡ ጰንጠሌዎን ፡ | ሮምያ ፡ | አባ ፡ ሊቃኖስ ፡ ባሉበት ፡ አቅራቢያ ፡ በሚገኝ ፡ ገዳም ፡ |
| ፯ | አባ ፡ አሌፍ ፡ | ቂሣርያ ፡ | ብሕዛና ፡ አሕፀዓ ፡ |
| ፰ | አቡነ ፡ አረጋዊ ፡ | ሮም ፡ | እገላ ፡ በምትባል ፡ ገዳም ፡ |
| ፱ | አባ ፡ ገሪማ ፡ | » » | አባ ፡ ሊቃኖስ ፡ ባሉበት ፡ አቅራቢያ ፡ በሚገኝ ፡ ገዳም ። |



## የኢትዮጵያ ፡ ተወላጆች ፡ ቅዱሳን ፡ የስማቸውና ፡ የገዳማቸው ፡ ዝርዝር ።

| ተራ ፡ ቍ ፡ | ስማቸው ፡ | ገዳማቸውና ፡ ዐፅማቸው ፡ ያለበት ፡ ሥፍራ ፡ | |
|---|---|---|---|
| ፩ | አቡነ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ | አላጌን ፡ | |
| ፪ | አቡነ ፡ ዮሐንስ ፡ | ማይ ፡ ተክሊ ፡ | |
| ፫ | አቡነ ፡ ገብር ፡ ኄር ፡ | ታሕታይ ፡ ደብር ፡ | |
| ፬ | አቡነ ፡ ሲኖዳ ፡ | አስገዴ ፡ | |
| ፭ | አቡነ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ | ሽጉሬ ፡ | |
| ፮ | አቡነ ፡ ሳሙኤል ፡ | ቈየጻ ፡ | |
| ፯ | አቡነ ፡ መርዓዌ ፡ ክርስቶስ ፡ | ቀላቅል ፡ | |
| ፰ | አቡነ ፡ አብራንዮስ ፡ | ማይ ፡ በራዝዮ ፡ | |
| ፱ | አቡነ ፡ አሮን ፡ | ክትሮ ፡ | |
| ፲ | አቡነ ፡ ዐቢየ ፡ እግዚእ ፡ | መረታ ፡ | |

www.ethiopianorthodox.org

## ከውጪ ፡ አገር ፡ በየጊዜው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመጡ ፡ የቅዱሳን ፡ ዝርዝር ።

| ተራ፡ ቍ፡ | ስማቸው ፡ | ገዳማቸውና ፡ ዐፅ ማቸው ፡ ያለበት ፡ | |
|---|---|---|---|
| ፩ | አቡነ ፡ ገብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ | ምድረ ፡ ከብድ ፡ | |
| ፪ | አቡነ ፡ ሠምረ ፡ ልዑል ፡ | ዛና ፡ | |
| ፫ | አቡነ ፡ አብሳዲ ፡ | ድቅድቆ ፡ (ሳዕሳይ ፡) ደብር ፡ ) | |
| ፬ | አቡነ ፡ መርዓዌ ፡ ክርስቶስ ፡ | በናቌ ፡ | |
| ፭ | አቡነ ፡ ቴዎድሮስ ፡ | አድያቦ ፡ | |
| ፮ | አቡነ ፡ ሠረቀ ፡ ብርሃን ፡ | ደባጕና ፡ | |
| ፯ | አቡነ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ | ሊጋሶ ፡ | |
| ፰ | አቡነ ፡ አሮን ፡ | ገሊላ ፡ | |



## ብላታ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስ ፡ ለብፁዕነታቸው ፡ ያበረከቱት ።

### ፩ኛ ፡ መወድስ ።

መሠረታቲሃ ፡ ለደብር ፡ አዕባነ ፡ ሎዛ ፤ እለ ፡ ርሑሳን ፡ በዘይት ፡ ያዕቆብ ፡ ዘዘከሮ ፤
እስመ ፡ ተክለ ፡ አሚን ፡ በዝየ ፡ አስተዳለወ ፡ መንበሮ ፤
ወንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፤ ዘአድኅኖ ፡ ሕዝቦ ፡ ወአግረሮ ፡ ፀሮ ፤
በኪነ ፡ ጥበብ ፡ አሠንያ ፡ ለደብረ ፡ ጽጌ ፤ ዘኮነት ፡ ምዕራገ ፡ ጸሎት ፡ ወዘምሮ ፤
ባስልዮስሂ ፡ አመ ፡ ቀደሰ ፡ ለአምላክነ ፡ ማሕደሮ ፤
ዕበያ ፡ ለደብረ ፡ ጽጌ ፤ ኢይትከሀል ፡ ለተነግሮ ፤
በዘሰማያዊት ፡ አምሳል ፡ እስመ ፡ ለመቅደስ ፡ ገብሮ ፤
መፍቀሬ ፡ አምላክ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አምላክ ፡ ዘአፍቀሮ ።

### ፪ኛ ፡ መወድስ ።

ኵሉ ፡ ይትሐረይ ፡ በድምፀ ፡ ብእሲ ፤ ወኵሉ ፡ ይረውጽ ፡ ለኃሢሠ ፡ ሢመት ፡ ፍሬ ፡ ሰግላ ፤
እመሰ ፡ ይትሐተት ፡ ምሥጢረ ፡ ሕርየት ፡ ኵላ ፤
ለባስልዮስ ፡ ዘሐረዮ ፡ ድምፀ ፡ ሰብእ ፡ አኮ ፡ ድምፀ ፡ ወልድ ፡ አላ ፤
እስመ ፡ በ ፡ እለ ፡ ተሐርዩ ፡ በከርሰ ፡ እሞሙ ፡ ቅድመ ፡ ወበ ፡ ድምፀ ፡ ሰብእ ፡ ከዋላ ፤
ወበሒሩቱ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፤ በይነ ፡ ዘአልዓላ ፤
ለደብረ ፡ ጽጌ ፡ አምሳለ ፡ መኑ ፡ ወምስለ ፡ መኑ ፡ ናስተማስላ ፤
እስመ ፡ ከመ ፡ ናዝሬት ፡ ትትዐወቅ ፡ ወከመ ፡ ካልዕታ ፡ ገሊላ ፤
በስነ ፡ ማርያም ፡ አዋከየት ፡ አክሊለ ፡ ስብሐት ፡ ተቀጺላ ።

### ሦስተኛ ፡ መወድስ ።

### ስለ ፡ እመቤታችን ፡ ድንጋሌ ።

እምጕንደ ፡ ዕፀው ፡ ይትወለድ ፡ ነደ ፡ ነበልባል ፤ ወተመይጦ ፡ ይከውን ፡ ዕፀ ፡ ዘይውኢ ፤
እምውስተ ፡ ሐቌሁ ፡ ለግብር ፤ እስመ ፡ ይትወለድ ፡ ጸላኢ ፤
ዘሲኖስ ፡ ዕፀ ፡ ፈውስ ፤ አመ ፡ ወለደቶ ፡ ለእሳት ፡ በላኢ ፤
በነበልባሉ ፡ አሕመልመለት ፡ ዘያውኢ ፡ ነድ ፡ እስመ ፡ ከነ ፡ ዘያጥኢ ፤
መንክረሂ ፡ ዲበ ፡ መንክር ፡ መንክረ ፡ ልደት ፡ ያርኢ ፡
አመ ፡ ውስተ ፡ ከርሥ ፡ ተጋብአ ፡ እንዘ ፡ ለሊሁ ፡ አስተጋባኤ ፤
እንግዳ ፡ መሰለ ፡ ለእዝነ ፡ ሰማኢ ፤
እምውስተ ፡ ገራሕት ፡ ጸአተ ፡ ፍሬ ፤ ዘእንበለ ፡ ዘርዕ ፡ ወዘራኢ ።

ብላታ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወ/ ዮሐንስ ።

www.ethiopianorthodox.org



ለመ፡ዐሠርቱ፡ወተሰዓቱ፡ምዕት፡ወሰማንያ፡ዓመተ፡ምሕረት፡
ወአመ፡ዕሥራ፡ወአሚሩ፡ለወርኃ፡ሰኔ።
አነ፡ባስልዮስ፡ -

ከመ፡ዝ፡ሰበኩ፡ወከመ፡ዝ፡መሀርኩ፡ለሕዝብ፡ኢትዮጵያ —
በእንተ፡ምሥጢረ፡አሐቲ፡ቅድስት፡ሥላሴ ——
ወበእንተ፡ምሥጢረ፡ትስ. ብእሲ፡ወተሰብኦቱ፡ --
ለእግዚእነ፡ወአምላክነ፡ወመድኃኒነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡.
በእንተ፡አሰተቀዮተ፡ለእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡
በክልኤ፡ማርያም፡ወለዲተ፡አምላክ —
ወበእንተ፡ትንብልናሆሙ፡ለቅዱሳን፡መላእክት ።
እለ፡ይቀውሙ፡ወትረ፡ቅድመ፡መንበሩ፡ለፀባኢት ።
ወበእንተ፡ስእለቶሙ፡ለቅዱሳን፡ነቢያት፡ወሐዋርያት፡
ጻድቃን፡ወሰማዕታት፡ደናግል፡ወመነኮሳት —
ወኵሉሙ፡ሊቃውንት፡ቤተ፡ክርስቲያን፡እለ፡ተጋደሉ፡
ወእለ፡ፈጸሙ፡ስምዖሙ፡በእንተ፡ስሙ፡ለክርስቶስ —
ሰላም —
ባስልዮስ፡ሊቀ፡ጳ፡ዘኢት —

ለ ........................................

የእግዚአብሔር ፡ ፈቃዱ ፡ ሆኖ ፡ የደብር ቅዱስ ፡ ደብረ ጽጌ ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕንጻ ፡ አልቆ ፡ የምረቃው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በሰኔ ፡ ፳፩ ቀን ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. ስለሚፈጸም ፤ በዚሁ ፡ ቀን ፡ በቦታው ፡ ላይ ፡ ተገኝተው ፡ በፕሮግራሙ ፡ መሠረት ፡ የበዓሉ ፡ ተካፋይ እንዲሆኑ ፡ እናሳስብዎታለን ።

ስለደብር ፡ ቅዱስ ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ ማርያም ፡ ገዳም ፡ በዓል ፡ አከባበር ፤
ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ (ፕሮግራም) ።

ብፁዕ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ።

የደብር ፡ ቅዱስ ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ ማርያምን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባማረ ፡ ሕንጻ ፡ አሠርተው ፡ ሥራው ፡ ተፈጽሞ ፡ ታቦቷ ፡ ወደ አዲሱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የምትገባበት ፡ ሰኔ ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ፡ ም፡ በመሆኑ ፡ በዚሁ ፡ ቀን ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ የግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ወደ ፡ ደብር ፡ ቅዱስ ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ የመሔዳቸውና ፡ የበዓሉ ፡ አከባበር ።

## ፕ ሮ ግ ራ ም ።

፩ኛ| ከሰኔ ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፱ ዓ፡ ም፡ ጀምሮ ፡ በጸሎተ ፡ ምህላና ፡ በጸሎተ ፡ ዕጣን ፡ ይደርስ ፡ የነበረው ፡ የጸሎተ ፡ ቡራኬ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በሰኔ ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ይፈጸማል ።

፪ኛ| ሰኔ ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ዐርብ ፡ ከጧቱ ፡ በ፲፪ ፡ ሰዓት ፡ በአዲሱ ፡ ቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ የመኅትው ፡ ጸሎት ፡ ይደርሳል ።

፫ኛ| በዚሁ ፡ ቀን ፡ ከ፩ ፡ ሰዓት ፡ ጀምሮ ፡ የዋዜማው ፡ ጸሎት ፡ ይደርስና ፡ በቅዳሴ ፡ ይፈጸማል ።

፬ኛ| ቅዳሴው ፡ እንደተፈጸመ ፤ ብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ብፁዓን ፡ ጳጳሳት ፡ ባሉበት ፡ ስለዋዜማው ፡ በዓል ፡ ከየአድባራቱ ፡ ለተጠሩት ፡ ሊቃውንት ፤ መምህራንና ፡ ካህናት ፡ ሙሉ ፡ ግብር ፡ ይደረጋል ።

፭ኛ ፡ በዚሁ ፡ ቀን ፡ ከሌሊቱ ፡ ከ፯ ፡ ሰዓት ፡ ጀምሮ ፡ በአዲሱ ፡ ቤተ ፡ ክር ስቲያን ፡ የሰዓታትና ፡ የማኅሌት ፡ ጸሎት ፡ ይደርሳል ።

www.ethiopianorthodox.org

፮ኛ| ፡ ሰኔ ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ቅዳሜ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ ግርማዊት ፡ እቴጌ ፤ ልዑላን ፡ መሳፍንትንና ፡ ልዑላትን ፤ ክቡራን ፡ ሚኒስትሮችንና ፡ መኳንንትን ፡ አስከትለው ፡ ከጧቱ ፡ በ፲፱ ፡ ሰዓት ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ይነሣሉ ።

፯ኛ| ፡ ከጧቱ ፡ በ፪ ፡ ሰዓት ፡ ደብር ፡ ቅዱስ ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሲደርሱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ከብፁዓን ፡ ጳጳሳት ፤ ከሊቃውንትና ፡ ከመምህራን ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ ይቀበሏቸዋል ።

፰ኛ| ፡ ጸሎተ ፡ ቅዳሴው ፡ ልክ ፡ ለ፪ ፡ ሰዓት ፡ ሩብ ፡ ጉዳይ ፡ ሲሆን ፡ ተጀ ምሮ ፡ በ፫ ፡ ሰዓት ፡ ከሩብ ፡ ይፈጸማል ።

፱ኛ| ፡ ሥርዓተ ፡ ዑደቱ ፡ በ፫ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ይጀመርና ፡ በ፬ ፡ ሰዓት ፡ ከሩብ ፡ ይፈጸማል ። በዚሁም ፡ ጊዜ ፡ ብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ስለ ፡ በዓሉ ፡ አጭር ፡ መንፈሳዊ ፡ ንግግር ፡ አድርገው ፡ ጸሎተ ፡ ቡራኬ ፡ ይሰጣሉ ።

፲ኛ| ፡ ስለ ፡ በዓሉ ፡ ክብር ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በተሰናዳው ፡ ሰፊ ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ድንኳን ፡ (አዳራሽ ፡) ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ ግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ በተገኙበት ፡ ለልዑላን ፡ መሳፍንት ፡ ለልዑላትና ፡ ለክቡራት ፡ ወይዛዝር ፡ ለክቡራን ፡ ሚኒስትሮችና ፡ መኳንንት ፡ የምሳ ፡ ግብዣ ፡ ይደረጋል ።

፲፩ኛ| ግብዣው ፡ እንደተፈጸመ ፤ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ ግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ በሔዱበት ፡ አኳኋን ፡ በክብር ፡ ተከታዮቻቸው ፡ ታጅበው ፡ ወደአዲስ ፡ አበባ ፡ ይመለሳሉ ።

፲፪ኛ| በዚሁ ፡ ቀን ፡ በዓሉን ፡ ለማክበር ፡ ለተጠሩት ፡ ሊቃውንትና ፡ መም ህራን ፤ እንዲሁም ፡ ከየአድባራቱ ፡ ለተጠሩት ፡ ካህናት ፡ በተለይ ፡ በተሰናዳው ፡ አዳራሽ ፡ ብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳትና ፡ ብፁዓን ፡ ጳጳሳት በተቀመጡበት ፡ሙሉ ፡ ግብር ፡ ተደርጎ ፡ የበዓሉ ፡ ፍጻሜ ፡ ይሆናል ።



### መዝሙር ዘክብረ በዓል (በዜማ)
### በደብር ቅዱስ ደብረ ጽጌ ።

አንቺ ደብረ ጽጌ ፤ ጽጌ ደንጎላት
መዓዛሽ ባስልዮስ ፍሬሽ ሃይማኖት ።
ቤትሽን ለማሠራት ፤ ሁሉ ከደከመ (በኋላ)
በኃይለ ሥላሴ መሠረትሽ ቆመ ።

ክብርሽን ለማየት ከዚህ እንዳለን
ዳግም ይሰብስበን በደብረ ጽዮን ።

ለቀደምት አልሆነም ድንግል ፈቃድሽ
ዛሬ በባስልዮስ ተሠራ ቤትሽ ።



ግርማዊት እቴጌ መነን ።

የመንገድህን ሰላም የሰጠህ ለሙሴ
ዛሬም ስጥልነ ለኃይለ ሥላሴ

ክብርሽን ለማየት ከዚህ እንዳለን
ዳግም ይሰብስበን በደብረ ጽዮን ።

አንተ ጸሎት ሰሚ ቸር አምላክ ነህና
መንገዱን ጠብቀህ መልሰው በደኅና ።
ለግርማዊትና ለአስፋ ወሰን
ደግሞም ለልዑላን ሁናቸው ብርሃን ።

ክብርሽን ለማየት ከዚህ እንዳለን
ዳግም ይሰብስበን በደብረ ጽዮን ።

ብፁዓን ጳጳሳት መኳንንቱ ሁሉ
ስለቸርነቱ ሃሌ ሉያ በሉ ።

ሰላምን ለሰጠ ለኢትዮጵያ
በሉ ሃሌ ሃሌ ፤ ሃሌ ሃሌ ሉያ ።

ሃሌ ፤ ዓለም ሳይፈጠር የነበረ
ሉያ ፤ ዓለምን አሳልፎ የሚኖር አምላክ
ሃሌ ሉያ ፤ በሰማይ ላለ ለእግዚአብሔር
ምስጋና ይገባል ።



መጣ ዘምሩለት ለይሁዳ አንበሳ
የቆመው ይራመድ የተኛው ይነሣ ።

## ጥ ቅ ስ

«ማለዳ ቸርነትህን በሌትም እውነትህን ለማውራት ።
ልዑል ሆይ አንተን ማመስገንና ለስምህ መዘመር መልካም ነው ።»
መዝ ፺፩ ፩—፪ ።

www.ethiopianorthodox.org

## አባታችን ሆይ ። !

አባታችን ሆይ የምትኖር በሰማይ
መንግሥትህ ትምጣልን ክብርህን እንድናይ።
ፈቃድህ በሰማይ ሕይወት እንደሆነ
እንዲሁም በምድር ሰላምን ስጠነ ።
ስጠነ ለዛሬ የዕለት ምግባችንን

ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምሴተ ሐሙስ ምሥጢራዊውን ራት ከደቀመዛሙርቱ ጋር ሲመገብ ።



በደላችንንም ይቅር እንድትለን ።
ጌታ ሆይ አታግባን ከክፉ ፈተና
አንተ ካልረዳኸን ኃይል የለንምና ።
ኃይልና ምስጋና ፤ መንግሥትም ያንተ ናት
አሜን ለዘለዓለም ይሁንልን ዕረፍት ።

በግርማዊት እቴጌ መነን ትምህርት ቤት ከመንፈሳዊ አስተማሪ

ከኢሳይያስ ዓለሜ ተዘጋጀ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ቅዳሴ ፡ ቤት ፡ ክርስቲያና ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ በደብር ፡ ቅዱስ ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ።

በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ዱ ፡ አምላክ አሜን ።

ኢትዮጵያዊው ፡ ሐዋርያ ፡ የሁላችን ፡ አባት ፡ ብፁዕ ፡ ወቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፣ በኢትዮጵያ ፡ አውራጃዎች ፡ እየተዘዋወሩ ፡ የወንጌልን ፡ ቃል ፡ በለሰለሰው ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ልቡና ፡ ላይ ፡ እንደዘሩ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

አምልኮተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መላልሰው ፡ በሰፊው ፡ ከመስበካቸው ፡ በላይ ፣ እግዚአብሔር ፡ የቀደሳትንና ፡ ያከበራትን ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያምን ፡ ማክበርን ፡ የሐዋርያነታቸው ፡ ሥራ ፡ መጀመሪያ ፡ አድርገዋል።

ይኸውም ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ የተባሕትዎ ፡ ሥራቸውን ፡ ከዓለማውያን ፡ ተለይተው ፡ ለመሥራት ፡ ገና ፡ ወደደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ በገቡ ጊዜ ፣ ጉማላጅነቷን ፡ ከመማጸናቸው ፡ የተነሣ ፡ በስሟ ፡ የተቀረጸች ፡ ጽላት ፡ ወደበዓታቸው ፡ ይዘው ፡ ገብተው ፡ ከአሥራ ፡ አምስት ፡ ደቀ ፡ መዛርቶቻቸው ፡ ጋራ ፡ ይጸልዩ ፡ ነበር ። ይህንኑም ፡ ደራሲው ፡ ዕጨጌ ፡ ዮሐንስ ፡ ከማ ፡ «ሰላም ፡ ለመቃብሬከ ፡ እምቅድመ ፡ ትኑም ፡ ውስቴታ ፣ ታቦተ ፡ ማርያም ፡ ድንግል ፡ ዘአንበርከ ፡ በውሳጢታ» ብለው ፡ ገልጠውታል ። በዚችው ፡ ጽላት ፡ ፊት ፡ ጸሎታቸውንና ፡ መሥዋዕታቸውን ፡ በሚያሳርጉበት ፡ ጊዜ ፣ ኑሮዋቸው ፡ በብሕትውና ፡ የተወሰነ ፡ በመሆኑ ፡ በዙሪያዋ ፡ የጋረዱት ፡ ደጓዕሌ ፡ (ሰሌን ፡) ነበር ።

የወላዲተ ፡ አምላክን ፡ መታሰቢያ ፡ እንዲህ ፡ አድርገው ፡ በማክበራቸው ፡ ለሁላችን በጎ ፡ አርአያ ፡ ሆነውናል ።

ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፣ ወደደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ከመግባታቸው ፡ በፊት ፡ የነበረውን ፡ ሐረስ ፡ የተባለ ፡ ሙዋርተኛ ፡ (መሠርይ ፡) ከነወገኖቹ ፡ ሲያባርሩት ፡ "እንተ ፡ ሶበ ፡ ጸዋዕክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አድኅነ ፡ እምፀርየ ፡ ያለውንና ፡ ወይባልሐኒ ፡ እምጸላእትየ ፡ ምንስዋን ,, የሚለውን ፡ የዳዊትን ፡ መዝሙር ፡ ይጸልዩ ፡ ነበር ። በአጋንንት ፡ ኃይል ፡ የሚተማመን ፣ የግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ በሚረዳው ፡ ሰው ፡ ፊት ማፈሩና ፡ መደንገጡ ፡ አይቀርምና ፡ ሐረስ ፡ በአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ጸሎትና ፡ በመንፈሳዊ ፡ ግርማቸው ፡ ደንግጠ ፡ ይበላባቸውና ፡ ይጠጣባቸው ፡ ሙዋርትም ፡ ያደርግባቸው ፡ የነበሩትን ፡ የብረት ፡ ንዋያት ፡ ጥሎ ፡ ከአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ፊት ፡ ሸሸቷል ። አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ሐረስ ፡ ሲሸሽ ፡ የጣላቸውን ፡ ንዋያት ፡ ባርከው ፡ ለቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልግሎት ፡ እንዲጠቅሙ ፡ አድርገዋል ።



እንዲሁም ፤ እግዚአብሔር ፡ ቀድሞ ፡ በአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ላይ ፡ ኃይሉን ፡ እንደገለጠ ፡ በእርሳቸው ፡ ተመሥርቶ ፡ እስካሁን ፡ በደረሰው ፡ በዕጨጌነት ፡ መንበር ፡ ላይ ፡ ድንቅ ፡ ሥራውን ፡ ከመግለጥ ፡ አላቋረጠም ።

እንዲህም ፡ ብለን ፡ የምንናገርበት ፡ ዋናው ፡ ምክንያት ፡ ከአቡነ ፡ ተክለ ሃይማኖት ፡ ዘመን ፡ ስብከት ፡ እስከ ፡ ግራኝ ፡ ወረራ ፡ ድረስ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልግሎት ፡ ይፈጸምባት ፡ የነበረችው ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፤ እንደገና ፡ ስለታደሰች ፡ ነው ።


በደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ራስጌ ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፣ ደብረ ፡ ከርቤ ፡ የተባሉ ፡ ሁለት ፡ ተራራዎት ፡ ይገኛሉ ። በደብረ ፡ ከርቤ ፡ አሁን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ቀድሞ ፡ እስከ ፡ ግራኝ ፡ ወረራ ፡ ድረስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ነበረበት ። አሁንም ፡ በቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ስም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተሠርቶበታል ። በደብረ ፡ ጽጌ ፡ ላይም ፡ በእመቤታችን ፡ ስም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተሠርቶባት ፡ እስከ ፡ ግራኝ ፡ ወረራ ፡ ድረስ ፡ ኖርዋል ።

የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ታሪክ ፡ (መንፈሳዊ ፡ ዜና ፡ ገድል) ፡ ያሰናዱ ፡ ዕጨጌ ፡ ዮሐንስ ፡ ከማ ፡ "አንተኑ ፡ ደብረ ፡ ከርቤ ፡ ዘመዓዛከ ፡ ይትፌቶ ፡ ወሚመ ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ ዘኢትክል ፡ ተከብቶ» ፡ ብለው ፡ በድርሰታቸው ፡ ውስጥ ፡ ሁለቱ ፡ ተራራዎች ፣ ቅዱሳት ፡ መካናት ፡ መሆናቸውን ፡ ገልጠዋል ።

በእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ መንበር ፡ የወረሱ ፡ ብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስም ፣ የቀድሞውን ፡ ታሪክ ፡ በማስታወስ ፡ «ደብር ፡ ቅዱስ» ፡ ተብሎ ፡ ተደራቢ ፡ ስም ፡ የተሰጠው ፡ ይኸው ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ ለመንፈሳዊ ፡ ትምህርትና ፡ ለገዳማዊ ፡ አገልግሎት ፡ መሠረት ፡ ሆኖ ፡ እንዲኖር ፡ በግል ፡ ገንዘባቸው ፡ ትልቅ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለሠሩበት ፣ የምረቃውና ፡ የቡራኬው ፡ ሥርዓት ፡ ሰኔ ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እንዲፈጸም ፡ ተደረገ ።

ይኸውም ፤ በዚሁ ፡ ቀን ፡ እንዲመረቅ ፡ የተደረገበት ፡ ምክንያት ፤ አባቶቻችን ፡ ሐዋርያት ፡ በጥንተ ፡ ስብከት ፡ በፊልጵስዩስ ፡ የመጀመሪያዪቱን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ትእዛዝ ፡ ሠርተው ፡ ሲፈጽሙ ፣ የቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ራሷ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የእናቱ ፡ መታሰቢያ ፡ አድርጎ ፡ በዛሬው ፡ ዕለት ፡ በእናቱ ፡ ስም ፡ ስለአከበራትና ፡ ስለቀደሳት ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org



ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የደብረ ፡ ጽጌ ፡ ማርያምን ፡ ቤተ፡ክርስቲያን ፡ መርቀው ፡ እንዳከበሩ ።



ግርማዊት እቴጌ መነን።

www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ አቡን ባስልዮስ ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ።



ብፁዕ አቡን ባስልዮስ ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በግል ገንዘባቸው ያሳንጽዋት የደብር ቅዱስ ደብረ ጽጌ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ቤትዋ በተከበረበት ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፶ ዓ ም የ፫ን በዓሉ ጠቅላላ ድርጅት ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በሥርዓት ፡ ዑደቱ ፡ ጊዜ ፡ የተናገሩት ፡ ሐዋርያዊ ፡ ስብከት ።

በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አሐዱ ፡ አምላክ ፡ አሜን ።

ይእቲኬ ፡ መድኃኒት ፡ እንተ ፡ ኀሠሥዋ ፡ ወየድዋ ፡ ነቢያት ፡ እለ ፡ ተነበዩ ፡ በእንተ ፡ ክብርክሙ ፡ እንዘ ፡ የኀሥሡ ፡ ለአይ ወለማዕዜ ፡ መዋዕል ፡ ዘነገረ ፡ በላዕሌሆሙ ፡ መንፈሱ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፲-፲፮ ።

እግዚአብሔር ፡ ሥራውን ፡ ያለምክንያት ፡ አይሠራውምና ፡ አስቀድሞ ፡ በነቢያት ፤ ኋላም ፡ በአበው ፡ ቀደምት ፡ እያደረ ፡ ስለበጎ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ትንቢት ፡ ማናገሩ ፡ አልቀረም ።

ይኸውም ፤ ንጉሠ ፡ እስራኤል ፤ ዳዊት ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሊሠራ ፡ አስቦ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቢያመለክት ፤ ለሱ ፡ የበለጠ ፡ የሥጋዌ ፡ ነገር ፡ ሲገለጽለት ፤ ለነቢዩ ፡ ለናታን ፡ የቤተ ፡ መቅደስ ፡ ነገር ፡ ተገልጾለት ፡ «እግዚአብሔር ፡ ለስሜ ፡ ቤት ፡ የምትሠራልኝ ፡ አንተ ፡ አይደለህም ። ካንተ ፡ በኋላ ፡ ካንተ ፡ የሚወለደው ፡ ልጅ ፡ ለስሜ ፡ ቤት ፡ ይሠራልኛል ፡ ብሎሃል» ፡ ብሎ ፡ ለዳዊት ፡ ነገረው ። ፪ ፡ ሳሙ ፡ ም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፲፪-፲፫ ።

የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ሰሎሞንም ፤ ነቢዩ ፡ ናታን ፡ በመንፈሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተገልጾለት ፡ እንደተናገረው ፡ በነገሠ ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ እስራኤል ፡ ከምስር ፡ ምድር ፡ በወጡ ፡ በአራት ፡ መቶ ፡ ሰማኒያ ፡ ዓመት ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መሥራት ፡ ጀመረ ። ፩ ነገ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ፩-፪ ።

ሰሎሞን ፡ ያሠራው ፡ የነበረው ፡ የቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሥራ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ፤ አባቱ ፡ ዳዊት ፡ አክብሮ ፡ ለቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰጠውን ዕቃ ፡ ብሩንና ፡ ወርቁን ፤ አምጥቶ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማጥን ፡ አገባ ።

በዚያም ፡ ጊዜ ፤ የእስራኤልን ፡ ሽማግሎችና ፡ የነገዱን ፡ ሁሉ ፡ አለቆች ፤ መሳፍንቱንና ፡ መኳንንቱን ፡ ሰብስቦ ፤ ታቦተ ፡ ጽዮንን ፡ ከአባቱ ፡ ከዳዊት ፡ ከተማ ፡ አስመጥቶ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አስገባ ። ፩ ፡ ነገ ፡ ም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፶፩ ፡ ም ፰ ፡ ቍ ፡ ፳፪ ።

እንደዚሁም ፡ እስራኤል ፡ በባቢሎን ፡ ሳሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቸርነቱ ፡ መከራቸውን ፡ ተመልክቶ ፤ ልመናቸውን ፡ ሰምቶ ፤ ነጻ ፡ እንዲያወጣቸው ፡ ብፅዓት ፡ ሲያደርጉ ፡ አስቀድመው ፡ እንሠራለን ፤ ብለው ፡ የተመኙት ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ ነው ።

እግዚአብሔርም ፡ ልመናቸውን ፡ ሰምቶ ፤ ብፅዓታቸውን ፡ ተቀብሎ ፡ ካወጣቸው ፡ በኋላ ፤ ምንም ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ለራሳቸውና ፡ ለእንግዳ ፡ ማረፊያ ፡ የሚሆን ፡ ቤት ፡ በመሥራት ፡ ቢቆዩ ፤ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ ከሌላው ፡ ሥጋዊ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አስቀድመው ፡ በንጉሡ ፡ በዘሩባቤል ፤ በሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ በዮሴዕ ፡ ወልደ ፡ ዮሴዴቅ ፡ አማካይነት ፡



ቤተ ፡ መቅደስን ፡ ሠርተዋል ። የዚህም ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ በዐርበ ፡ ስድስት ፡ ዘመን ፡ የተፈጸመ ፡ መሆኑን ፡ ቃለ ፡ ወንጌል ፡ ይናገራል ። ዮሐ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቍ ፡ ፳ ።

የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሕንጻ ፡ በሰፊው ፡ ማቋቋም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዕድል ፡ ሆኖ ፡ በተሰጣቸው ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ግን ፤ ማናቸውም ፡ ሥራ ፡ ቢሆን ፡ ተጀምሮ ፡ የብዙ ፡ ጊዜ ፡ ድካምን ፡ ሳይጠይቅ ፡ በቶሎ ፡ የሚፈጸም ፡ ስለሆነ ፤ ይህ ፡ ሥራው ፡ ተፈጽሞ ፡ አልቆ ፡ የምታዩት ፡ አዲስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መስከረም ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ተጀምሮ ፡ በዛሬዩቱ ፡ ሰኔ ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተፈጽሟል ።

እግዚአብሔር ፡ የስሙ ፡ ማደሪያ ፡ ሲያዘጋጅ ፡ ዛሬ ፡ መጀመሪያ ፡ ጊዜው ፡ አይደለም ፤ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ማደሪያውና ፡ የስሙ ፡ መጠሪያ ፡ ሰው ፡ ሲሆን ፡ ደግሞ ፡ ሰው ፡ ፈጣሪውን ፡ የሚያውቅበት ፤ በጸሎት ፡ ስሙን ፡ የሚጠራበት ፡ የተለየ ፡ የስሙ ፡ መታሰቢያ ፡ እንዲያዘጋጅ ፡ በመፍቀዱ ፡ ለስሙ ፡ ማደሪያ ፡ ፩ኛ ፡ ደብተራ ፡ ኦሪትን ፤ ፪ኛ ፡ በሰሎሞን ፡ ጊዜ ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ ሰጥቷል ።

ይህም ፡ ቦታ ፡ በተለይ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ። ምክንያቱም ፡ ‹እግዚአብሔርና ፡ ሰው ፤ በጸሎት ፡ የሚገናኙበት ፡ ስሙ ፡ የሚጠራበት ፡ ስለሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ "ሰማይ ፡ ዙፋኔ ፡ ነው ፤ ምድርም ፡ መመላለሻዬ ፡ ናት ፤ ለኔ ፡ ምን ፡ ቤት ፡ ትሠሩልኛላችሁ ? ያለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባንድ ፡ ቦታ ፡ ተወስኖ ፡ የሚኖር ፡ ሆኖ ፡ አይደለም ።

የእውነተኛ ፡ ነገር ፡ ምሳሌዎች ፡ የሆኑት ፡ ደብተራ ፡ ኦሪትና ፡ ቤተ ፡ መቅደስም ፡ ካለፉ ፡ በኋላ ፡ ጌታችን ፡ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሥጋ ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ የመጣበትን ፡ ሥራ ፡ ፈጽሞ ፡ ባረገ ፡ በስምንት ፡ ዓመት ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ጣዖት ፡ በመገሥገሥ ፡ ፈንታ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዲሔድ ፤ በልዩ ፡ በልዩ ፡ ዓይነት ፡ ለተቀረጸ ፡ ጣዖት ፡ በመስገድ ፡ ፈንታ ፡ በቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ለቅዱስ ፡ ስሙ ፡ እንዲሰግድ ፡ በመፍቀዱ ፡ በደመ ፡ ላህም ፡ በደመ ፡ በግዕ ፡ ከብረው ፡ ከነበሩት ፡ ከደብተራ ፡ ኦሪትና ፡ ከቤተ ፡ መቅደስ ፡ የበለጠችውን ፤ በክቡር ፡ ደሙ ፡ የዋጃትን ፡ ቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ በዛሬው ፡ ሰኔ ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ሐዋርያትን ፡ አቁሞ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ መሥርቶ ፡ ሠርቶ ፡ ፈጽሞ ፡ በስሙ ፡ ባርኮ ፡ ቀድሶ ፡ ሰጥቶናል ።

ይህችንም ፡ በስሙ ፡ የቀደሳትን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በእናቱ ፡ በቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ስም ፡ ባራቱ ፡ መዓዝነ ፡ ዓለም ፡ ለሚሠሩ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ መታሰቢያ ፡ አድርጓታል ።

ስለዚህም ፡ በቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚሰገደው ፡ ለቅዱስ ፡ ስሙ ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ መታሰቢያነቱ ፡ ዕንሱን ፡ ልደቱን ፡ ለመሰሉት ፡ ሥራዎቹና ፡ ለእናቱ ፡ ለቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፤ ለወዳጆቹ ፡ ለጻድቃን ፤ ለሰማዕታት ፤ ለመላእክትም ፡ ስም ፡

www.ethiopianorthodox.org

እንዲሆን ፡ ፈቃዱ ፡ ስለሆነ ፤ ከሐዋርያት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ እኛ ፡ የደረሰው ፡ ሥራ ፡ ምስክር ፡ ነው ።

አባቶቻችን ፡ ሐዋርያት ፤ በጥንት ፡ ስብከት ፡ ወንጌልን ፡ ወደ ፡ ሁሉ ፡ ለማዳረስ ፡ በተፋጠኑበት ፡ ጊዜ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በየደረሱበት ፡ እንደጌታቸው ፡ እየቀደሱ ፡ ያቈርቡ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ እንዲህ ፡ እንደዛሬው ፡ ሕንጻ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ታቦትን ፤ ንዋየ ፡ ቅድሳትን ፤ አልባሳትን ፤ ልዑካንን ፡ አልፈለጉም ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ጌታ ፡ ባረገ ፡ በ፳ ፡ ዓመት ፡ አምኖ ፡ ወደ ፡ ወንጌል ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፤ እርሱና ፡ በርናባስ ፡ ወደፊልጵስዩስ ፡ ገብተው ፡ ወንጌልን ፡ ባስተማሩ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ አመኑ ፡ ተጠመቁ ።

«ካመናችሁ ፡ ከተጠመቃችሁ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዴህ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ጣዖት ፡ አትሒዱ» ፡ አሏቸው።

ሕዝቡም ፡ የለመድነውንማ ፡ ከነጣችሁን ፡ መከነ ፡ ጸሎት ፡ ለዩልን ፡ አሉዋቸው ።

እነሱም ፡ ነገሩ ፡ ደግ ፡ እንደሆነ ፡ ዐውቀው ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ (ወዘእንበሌየሰ ፡ ኢልበ ፡ ዘትክሉ ፡ ገቢር ፡ ወኢምንትኒ) ፡ ያለእኔ ፡ አንዳች ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ ፡ አትችሉም ፡ ብሎ ፡ የነገራቸውን ፡ በማሰብ ፡ ሱባዔ ፡ ይዘዋል ።

ሱባዔያቸውን ፡ በፈጸሙ ፡ ጊዜ ፤ ጌታችን ፡ ተገልጠ ፡ “ለእናቴ ፡ ስም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ከጽንፍ ፡ እስከ ፡ ጽንፍ ፡ ሊታነጹ ፡ ፈቃዴ ፡ ነውና ፡ ሕንጻ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ላስተምራችሁ ፤ ሰብስቤያችኋለሁ„ ፡ ብሎ ፡ አስከትሏቸው ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ወጥቷል ።

በተአምራትም ፡ ሦስት ፡ ደንጎችን ፡ ተራርቀው ፡ ሳሉ ፡ አቃርቦ ፡ ጥቃቅን ፡ ሁነው ፡ ሳሉ ፡ ታላላቅ ፡ አድርጎ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ መሠረት ፡ ባርኮ ፡ ስለ ፡ ሰጣቸው ፡ ቀድሞ ፡ ለሙሴ ፡ የደብተራ ፡ ብርሃንን ፡ አርአያ ፡ እንዳሳየው ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሥሩ ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ አሳያቸው ፡ ሥራ ፡ ጀምረዋል ።

የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መጽሐፈ ፡ ታሪክ ፡ (ወአዕባን ፡ ከና ፡ ይለመልማ ፡ ውስተ ፡ እደዊሆሙ ፡ ለሐዋርያት) ፡ ብሎ ፡ እንደተናገረ ፤ ሰም ፡ እሳት ፡ ሲያሳዩት ፡ እንዲለመልም ፡ በእጃቸው ፡ እየተሳበ ፡ ሠርተው ፡ ፈጽመውታል ።

ይህም ፡ የሆነ ፡ እመቤታችን ፡ ባረገች ፡ ባራተኛው ፡ ዓመት ፡ በሰኔ ፡ ኻያ ፡ ቀን ፡ ነው። ቅዳሴ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ በዛሬዩቱ ፡ በሰኔ ፡ ኻያ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ተፈጽሟል ። የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕንጻ ፡ መታነጽ ፡ የተጀመረ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ነው።

መተርጉማን ፡ የሆኑ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሊቃውንት ፡ ሦስት ፡ ደንጊያዎች ፡ የሥላሴ ፡ አምሳል ፡ ናቸው ።

ከታች ፡ አቀማመጣቸው ፡ (መሠረትነታቸው ፡) ሦስት ፡ ሲሆን ፤ እላይ ፡ ሕንጻቸው ፡ አንድ ፡ መሆኑ ፡ የሥላሴ ፡ ያንድነታቸው ፡ የሦስትነታቸው ፡ አምሳል ፡ ነው ፡ ብለዋል ።



ይህንኑም ፡ ስለእመቤታችን ፡ ክብር ፡ ማኅሌት ፡ ጽጌ ፡ የደረሱ ፡ ሊቁ ፡ አባ ፡ ጽጌ ፡ ብርሃን ፤ (በሠላስ ፡ አዕባን ፡ ገጸ ፡ ሥላሴሁ ፡ ለአምሮ ፡ ሕንጻ ፡ ቤትኪ ፡ ድንግል ፡ ድኅረ ፡ ፈጸመ ፡ ማርሮ ፡ ብለው ፡ በድርሰታቸው ፡ ገልጠውታል ።

ዛሬም ፡ በአምላክነቱ ፡ ፊት ፤ ናሁ ፡ እሰይም ፡ ውስተ ፡ ጽዮን ፡ ዕብነ ፡ ማዕዘንት ፡ ኅሪት ፡ ወክብርት ፡ ወዘአምነ ፡ ባቲ ፡ ኢይትኀፈር ፡ ለዓለም» ፡ በማለት ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሁሉ ፡ ከፈጣሪያቸው ፡ ጋር ፡ ሊገናኙበት ፤ ሊተዋወቁበት ፡ ጸሎታቸውን ፤ ሁሉ ፡ ሊያቀርቡበት ፤ በጥምቀት ፡ ልጅነትን ፡ ሊያገኙበት ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ሊቀበሉበት ፡ በእናቱ ፡ በቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ስም ፡ መታሰቢያ ፡ አድርጌ ፡ ለቅዱስ ፡ ስሙ ፡ ለክህሊነቱ ፡ በረከተ ፡ ገጽ ፡ አቅርቤአለሁ ።

በቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚገኘውን ፡ ተስፋ ፡ አምኖ ፡ የሚማጸን ፡ ሁሉ ፡ ለዘላለም ፡ እንዳያፍር ፤ የለመነውንም ፡ እንዳያጣ ፡ ለስሙ ፡ መጠሪያ ፤ ለእናቱ ፡ ለድንግል ፡ ማርያም ፤ መታሰቢያ ፡ አድርጌ ፡ ባዘጋጀኋት ፡ በዚች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ልመናዬን ፤ ልመናችሁን ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ ‹ወይኩን ፡ ፈቃድከ› ፡ እያልኩ ፡ እለምነዋለሁ ።

ይህችንም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለመሥራት ፡ አስቤ ፡ የተነሣሁበት ፡ የቀደሙት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ነገሥታት ፤ መኳንንት ፤ ጳጳሳት ፤ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፤ የጀመሩትን ፡ ዓላማ ፡ በመከተል ፡ ስለሆነ ፤ ምእመናን ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ እንዲያጸኑ ፤ መናፍቃን ፡ በጉባኤ ፡ እንዳይሠለጥኑ ፡ ክህደት ፡ እየጠፋ ፡ ሃይማኖት ፡ እየሰፋ ፡ እንዲሔድ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ደንብ ፡ አቋቋም ፤ በገዳም ፡ ደንብ ፡ ሆኖ ፡ እናታችን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ወርሳ ፡ የሰጠችን ፡ የትምህርት ፡ ዓይነቶች ፡ ተዘጋጅተው ፡ ይገኙበታል ።

እነዚህም ።

(ሀ) ፡ ግዕዝና ፡ አማርኛ ፤ ጽሕፈትና ፡ ድጕሰት ፤
(ለ) ፡ ቅኔና ፡ ሰዋስው ፤
(ሐ) ፡ ፀዋትወ ፡ ዜማ ፤
(መ) ፡ የብሉያት ፡ መጻሕፍት ፡ ትርጓሜ ፤
(ሠ) ፡ የሐዲሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ትርጓሜ ፤
(ረ) ፡ የሊቃውንት ፡ » »
(ሰ) ፡ መጻሕፍተ ፡ መነኮሳት ፡ ትርጓሜ ፡ ናቸው ።

ነገር ፡ ግን ፡ የቦታው ፡ አስተዳደር ፡ ምንም ፡ በገዳምነት ፡ ቢሆን ፤ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ የሚሰጠው ፡ ፍሬ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ፈጽሞ ፡ የሚችል ፡ ቢኖር ፡ ይታገሥ ፡ ባለው ፡ መሠረት ፤ በፈቃዳቸው ፡ ለመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ራሳቸውን ፡ ጃንደረባ ፡ ለማድረግ ፡ የፈቀዱ ፡ ቢኖሩ ፡ በየመዓርጋቸው ፡ የተዘጋጁላቸውን ፡ ትምህርቶች ፤ ይልቁንም ፡ መጻሕፍተ ፡ መነኮሳትን ፡ አጥንተው ፡ በመዓርገ ፡ ምንኵስና ፡ እንዲያገለግሉ ፤ የቀሩትም ፡ ምንኵስናን ፡ ባይችሉ ፡ ትምህርታቸውን ፡ ሲፈጽሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ በፈቀደላቸው ፤ በየሥራቸው ፡ ደረጃ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፤ አገራቸውንና ፡ መንግሥታቸውን ፤ እንዲያገለግሉ ፡ ፈቅደናል ።

www.ethiopianorthodox.org

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በቆሮንቶስ ፡ ላሉ ፡ ምእመናን ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ ሰይጣን ፡ መልአከ ፡ ብርሃን ፡ ይመስላልና ፡ ሐዋርያትን ፡ መስለው ፡ የሚመጡ ፡ አሰ ተኞች ፡ መምህራን ፡ ስለማይታጡ ፤ እኛ ፡ ያልሰበክንላችሁ ፡ ሌላ ፡ ኢየሱስ ፤ እኛ ፡ ያልሰጠናችሁ ፡ ሌላ ፡ መንፈስ ፤ እኛ ፡ ያላስተማርናችሁ ፡ ሌላ ፡ ወንጌል ፡ የለምና ፡ በሐሰተኛ ፡ ትምህርታቸው ፡ እንዳትሰነካከሉ ፡ ሲል ፡ ፪ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ምዕራፍ ፡ ፲፩ ፡ ቍጥር ፡ ፩-፲፬ ። ጽፎላቸዋል ።

እኛም ፡ የሐዋርያውን ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፤ በሐሰተኛ ፡ ትምህርት ፤ እንዳይሸነፉ ፤ ያጠኑትንም ፡ እንዳይገድፉ ፤ ከኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ሃይማኖታቸው ፡ እንዳይናወጡና ፡ ሥርዓተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ እንዳይለውጡ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ አደራ ፡ እንላቸዋለን ።

በደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ራስጌ ፡ በሚታዩት ፡ ደብረ ፡ ከርቤ ፤ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ በሚባሉት ፡ በነዚህ ፡ በሁለቱ ፡ ተራሮች ፡ ከአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ስብከት ፡ ጀምሮ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ተተክለውባቸው ፡ እስከ ፡ ግራኝ ፡ ወረራ ፡ ድረስ ፡ ቆይተዋል ።

በዚህ ፡ በደብረ ፡ ጽጌ ፡ ላይ ፡ የተተከለው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በእመቤታችን ፡ ስም ፡ ነበር ።

የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ታሪክ ፡ የጻፉ ፡ ሰባተኛው ፡ ዕጨጌ ፤ ዮሐንስ ፤ ከማ «አንተኑ ፡ ደብረ ፡ ከርቤ ፡ ዘመዓዛከ ፡ ይትፌቶ ። ወሚመ ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ ዘኢትክል ፡ ተከብቶ» ፡ ብለው ፡ በድርሰታቸው ፡ ውስጥ ፡ በሁለቱ ፡ ተራሮች ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ መንፈሳዊ ፡ ታሪክ ፡ ገልጠውታል ።

በደብረ ፡ ከርቤ ፡ ላይ ፡ አሁንም ፡ በቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ስም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተሠርቶበታል ።

ስለዚህ ፤ በግራኝ ፡ ወረራ ፡ ምክንያት ፡ ተቋርጦ ፡ የነበረው ፡ ስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲነገርበት ፤ መሥዋዕት ፡ እንዲሠዋበት ፡ መለኮታዊ ፡ ፈቃዱ ፡ ሆኖ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ተጀምሮ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ተፈጽሞ ፡ በማየቴ ፤ ለፈጣሪዬ ፡ የሕሊና ፡ ምስጋና ፡ አቀርባለሁ ።

ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ተስፋ ፡ ያደረግሁበት ፤ የዚህ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕንጻ ፡ በመፈጸሙ ፤ ነቢዩ ፡ ዳዊት ፤ ለከ ፡ እሠውዕ ፡ መሥዋዕተ ፡ ስብሐት ፤ ወእሁብ ፡ ብፅዓትየ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በቅድመ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ በዐጸደ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ። (ላንተ ፡ የምስጋና ፡ መሥዋዕት ፡ እሠዋለሁ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ እጠራለሁ ። ስለቴን ፡ በሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ አደባባዮች ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እፈጽማለሁ) ፤ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ረድኤት ፡ በወላዲተ ፡ አምላክ ፡ በረከት ፡ ስለተፈጸመልኝ ፡ ይህችን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እግዚአብሔር ፡ መሠረታት ፡ እግዚአብሔር ፡ አነጻት ፤ እግዚአብሔር ፡ አከናወናት ፡ ፈጸማት ፡ ብዬ ፡ ፈጣሪዬን ፡ ያለማቋረጥ ፡ አመሰግነዋለሁ ።



አርእስት ፡ ሆኖ ፡ የተጠቀሰው ፤ የሐዋርያው ፡ ቃልም ፡ እንደ ፡ አመለከተን ፤

በዚህ ፡ በደብረ ፡ ጽጌ ፡ ላይም ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተሠርቶ ፤ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰፍቶ ፡ ይነገርበታል ፤ የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ይመሰገንበታል ፡ እየተባለ ፡ በደጋጉ ፡ አበው ፡ ሲነገር ፡ የነበረው ፡ በጎ ፡ ትንቢት ፡ እነሆ ፡ በዛሬዪቱ ፡ ቀን ፡ ተፈጸመ ።

ስለዚህ ፤ ቸር ፡ እግዚአብሔር ፡ በእድለኛው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፤ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ይህን ጥንታዊውን ፡ ቅዱስ ፡ ሥፍራ ፡ ለማደስ ፡ ስላበቃኝና ፡ በደጋጎቹ ፡ አባቶቹ ፡ ያናገረውን ፡ ትንቢት ፡ ለእኔ ፡ ስለአደረገው ፤ እንደ ፡ ነቢዩ ፡ ዳዊት ፡ «ምንተኑ ፡ አዐሥዮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡ ዘገብረ ፡ ሊተ» ፡ እያልኩ ፡ ንግግሬን ፡ እፈጽማለሁ ።

የእግዚአብሔር ፡ ምሕረት ፡ ቸርነት ፤ የእመቤታችን ፡ የድንግል ፡ ማርያም ፡ በረከት ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፤ በግርማዊት ፡ እቴጌ ።

በልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽና ፡ በንጉሣውያን ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡

በመላውም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ይደር ።

አ ሜ ን ።

---

www.ethiopianorthodox.org

የበዓሉም ፡ አከባበር ፡ እንደተፈጸመ ፤ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በተለይ ፡ በተሰናዳው ፡ በግብር ፡ አዳራሽ ፡ ውስጥ ፤ ለብፁዓን ፡ ለጳጳሳት ፤ ለክቡራን ፡ መኳንንትና ፤ በበዓሉም ፡ ላይ ፡ ለተገኙት ፡ ለደብር ፡ አለቆችና ፡ መምህራን ፡ ሰፊ ፡ ግብር ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ዋና ፡ መናገሻ ፡ ከተማቸው ፡ ከተመለሱ ፡ በኋላ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ከ፯ ፡ ሰዓት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፲፪ ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ ለሊቃውንትና ፡ ለካህናት ፤ ለህገሩ ፡ ሕዝብም ፡ ሙሉ ፡ ግብር ፡ አድርገዋል ።

በግብገሩው ፡ ላይ ፡ የነበረውንም ፡ ሕዝብ ፡ ብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በደስታና ፡ በፈገግታ ፡ መልክ ፡ ሲጋበዙ ፤ ከሊቃውንት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቅኔዎች ፡ ይነገሩ ፡ ስለነበር ፤ ጥቂቶቹን ፡ ቀጥለን ፡ አትመናቸዋል ።

የመናገሻ ፡ ቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ደብር ፡ አለቃ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ሀብቴ ፡ ብፁዕ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ግብር ፡ በሚያበሉበት ፡ ጊዜ ፡ ያቀረቡት ፡ ቅኔና ፡ መዝሙር ።

ሕንጻ ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ ትንቢት ፡ አመ ፡ ተፈጸመ ፤ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አጽነነ ፡ ወወረደ ፡ እመንበሩ ።

እስከ ፡ ተመይጠ ፡ ወገብአ ፡ ኀበ ፡ ስብሓቲሁ ፡ ወክብሩ ።
ወኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ለባስልዮስ ፡ ውእቱ ፡ የማኑ ፡ ወውእቱ ፡ ምክሩ ፤
በደብረ ፡ ጽጌስ ፡ ማኅደሩ ፤

ለሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ባስልዮስ ፡ ደመና ፡ መንኰራኵሩ ።
ኪሩቤልሂ ፡ ጳጳሳቲሁ ፡ መናብርተ ፡ ክህነት ፡ ዘጾሩ ፤
በኀበ ፡ አንጸረ ፡ ቀዳማዊ ፡ ሥልጣነ ፡ ባስልዮስ ፡ የሐውሩ ።
ይትባደሩሂ ፡ ጸሐፍት ፡ ለመልእክተ ፡ ጽዋዕ ፡ ምሥጢሩ ፤
ነገደ ፡ መላእክት ፡ ማዕዳቲሁ ፡ ዘእንበለ ፡ ሥጋ ፡ እስመ ፡ ተፈጥሩ ።

## አ ማ ር ኛ ፡ መ ዝ ሙ ር ።

እኔ ፡ ጋራው ፡ መስሎኝ ፡ ጎርፎ ፡ የተባለው ፤
ይኸም ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ ጎርፎ ፡ ነው ፡ ጎርፎ ፡ ነው ፤
የስሉልታው ፡ ዝናም ፡ ላይ ፡ ላዩን ፡ አለፈ ፤
ደብረ ፡ ጽጌ ፡ ብቻ ፡ ሳይዘንም ፡ አጎረፈ ፤
በንጀራ ፡ ገድበው ፡ እንደተለመደ ፤
ባስልዮስ ፡ በደጅህ ፡ የሰው ፡ ጎርፍ ፡ ወረደ ፤
ጠጅህን ፡ ባስልዮስ ፡ ስፈልገው ፡ ኖሬ ፤
ደብረ ፡ ጽጌ ፡ ወድቆ ፡ አገኘሁት ፡ ዛሬ ፤
ከከተማ ፡ ወጥቶ ፡ ጠጅህ ፡ ገሠገሠ ፤
ሲወድቅ ፡ ሲነሣ ፡ በሰኔ ፡ ደረሰ ።



ዐርብ ፡ ደኅና ፡ ውዬ ፡ ታመምሁኝ ፡ ቅዳሜ ፡
ታናሽ ፡ እቴ ፡ የለች ፡ ወይ ፡ ታላቅ ፡ ወንድሜ ፤
በሽታዬ ፡ ጸና ፡ ባሣሉኝ ፡ እመሜ ፤
ቶሎ ፡ ድረስልኝ ፡ ባስልዮስ ፡ ሐኪሜ ፤
አሁን ፡ እድናለሁ ፡ ባንተ ፡ እጅ ፡ ታግሜ ።
(ዓሣ ፡ በግብሩ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ነበረ) ።

የአዲስ ፡ ዓለም ፡ ደብረ ፡ ጽዮን ፡ ቅኔ ፡ መምህር ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ መንገሻ ፡ ያበረከቷቸው ፡ ቅኔዎች ።

## መወድስ ፡ ቅኔ ።

ሕንጻ ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ ሰምሰን ፡ እመከነ ፡ ዕድሜ ፤
ተምኔተ ፡ ልቡና ፡ ይፀንስ ፡ ወይትወለድ ፡ በብሥራት ።
ፈቃደ ፡ አቡሁ ፡ ለኄር ፡ ላዕከ ፡ ውሳጣዊ ፡ ተምኔት ።
ተፈነወ ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፡ ባስልዮስ ፡ አቡሃ ፡ ለሐዳስ ፡ ሥርዓት ።
ደብረ ፡ መቅደሱ ፡ ለባስልዮስ ፤

ሰማኢተ ፡ ብሥራት ፡ ኢትብላእ ፤ ዘኢኮነ ፡ ለመሥዋዕት ።
ሰምሰንሂ ፡ ወልደ ፡ ማኑኄ ፡ ዘንጉሥነ ፡ ሚጠት ።
ማዕከለ ፡ ጉቡዓን ፡ አመ ፡ ቆመ ፡ አኀዘ ፡ ይትነሠት ።
ቤተ ፡ አምልኮት ፡ ለባዕድ ፡ ፍጻሜ ፡ ዘጽልእ ፡ አረፍት ።
እስመ ፡ ኮነ ፡ አምሳሊሁ ፡ ለእንተ ፡ ይመጽእ ፡ በስብሓት ።

## ፪ተኛ ፡ መወድስ ።

ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ባስልዮስ ፡ ሕንጻ ፡ መቅደስከ ፤
ዘበብሥራትከ ፡ ኮነ ፡ ዕንስታ ፡ ወተወልዶታ ።
አዕላፈ ፡ ትኩን ፡ ወከመ ፡ ከመ ፡ ትለድ ፡ መንታ ።
ጰራቅሊጦስ ፡ ፌማ ፡ ለይኅድር ፡ ውስቴታ ።
ወኢይርኅቅ ፡ እምኔሃ ።

በረከተ ፡ ሚም ፡ ወያፌት ፡ ለደብረ ፡ ገሪዛን ፡ በረከታ ።
ኢይኅልቅሂ ፡ መዋዕሊሃ ፡ ወይትመክዐብ ፡ ዓመታ ።
እንዘ ፡ ጠፈራ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ወአንተ ፡ መሠረታ ።
አምጣነ ፡ ይቤ ፡ ሕግከ ፡ ሥርወ ፡ ጳጳሳት ፡ ዖታ ።
ዝየ ፡ አኀድር ፡ እስመ ፡ ኀረይክዋ ፡ ለባሕቲታ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፫ተኛ ፡ መወድስ ።

ተክለ ፡ ፍጻሜሃ ፡ ለሕግ ፡ ሕንጻ ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡
ዘሥረዊሃ ፡ በምድር ፡ ወዘበሰማይ ፡ አዕጹቂሃ ።
በብሥራተ ፡ ባስልዮስ ፡ ጠል ፡ ድኅረ ፡ አርአየት ፡ ጽጌሃ ።
አመ ፡ ወርኀ ፡ ጽጌ ፡ ብሥራተ ፡ ቃሉ ፤
ዘያጸግብ ፡ ኵሎ ፡ አርአየት ፡ ፍሬሃ ።
ከመ ፡ ትኩን ፡ ምዕራፎሙ ፤

ለዘእምርጉቅ ፡ መጽኡ ፡ አዕዋፈ ፡ ገነት ፡ ክህናቲሃ ።
ሚካኤልሂ ፡ ወገብርኤል ፡ ዐቀብተ ፡ ሥርዓት ፡ ኪያሃ ።
ምስሌሁ ፡ ለዮሐንስ ፡ ወሳዊሮስ ፡ ላዕካኒሃ ።
ኀበሩ ፡ ቃለ ፡ ወተጋብኡ ፡ ኀቤሃ ።
በኀጹረ ፡ ማርቆስ ፡ ሃይማኖት ፡ ይትኀጸር ፡ አድያሚሃ ።

## ማ ረ ሚ ያ ።

በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ በገጽ ፡ ፻፸፰ ፡ ጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ አሁን ፡ ደጃዝማች ፡ የሚለው ፡ አሁን ፡ የአሩሲ ፡ ጠቅላይ ፡ ገዥ ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

www.ethiopianorthodox.org